

# የቀናት ዘር

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

ከሲሳይ ንጉሡ

# የቅናት ዛር

ከሲሳይ ንጉሡ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ክፍል አንድ

«ላገባሽ ወይንም ልገድልሽ ወስኛለሁ፤ ከሁለቱ አንዱን ምረጭ!»

ሰማይነህ ሽብሩ ኮስተር ብሎ እንዲህ አይንቱን ምርጫ ሲያቀርብላት፤ ህይወት ስዩም ግራ ገብቷት በዝምታ ዓይኑን ትመለከተው ጀመር። አኳኋኑ አስፈርቷት ነው እንጂ መሳቅ ፈልጋ ነበር። ተፈጥሮዋ ፍልቅልቅ ነው። በሆነው ባልሆነው መሳቅ ትወዳለች፤ ከንትሹም ከትልቁም ትሳሳቃለች፤ ሁልጊዜም ደስተኛ ለመሆን ወይም ለመምሰል በሳቅ አለም ውስጥ መኖርን የመረጠች ትመስላለች። በማያስቀው ስትስቅ ታስቃለች። «ምነው?» ብለው ሲጠይቋት «ሳቅ የደስታ ምንጭ» ትላለች። ሳቋን አፍና ስሜቷን እየታገለች በመቆየቷ ሰማይነህ ጥያቄውን ደገመው።

«መልስ ስጭኝ እንጂ! ከማግባትና ከመሞት አንዱን መምረጥ ይኖርብሻል»

«ምን አይነት ምርጫ ነው - ጋሼ ሰማይነህ?» አለችው ላለመሳቅ እየታገለች» መኖርና መደሰት ሲቻል የሞትን ምርጫ ምን አመጣው?»

«ደግሞ ይህንን ጋሼ  የምትይውን ቅጥያ ሁለተኛ መስማት አልፈልግም። ባልሽ እንጂ አጎትሽ ወይም ታላቅ ወንድምሽ ለመሆን አልመጣሁም» አላት እንደተኮሳተረ።

«እሺ» አለች በደፈናው የሰማይነህ ሁኔታ እያስፈራት።

«ልታገቢኝ ፈቃደኛ ከሆንሽ ማንኛውንም ነገር ማፋጠን አለብን፤ ጊዜ መስጠት አያስፈልግም፤ ትርፉ ለጠላት መመቸት ነው።..... በዚህ ወር ውስጥ ጋብቻችንን ፈፅመን ጠላቶቻችንን ከው ማድረግ አለብን። አንቺን ፍለጋ የሚያንዣብቡትና እዚህ ቤት እየመጡ የሚያፈጡትንም እርማቸውን ያወጣሉ።

ሰማይነህ ይህን ሲናገር ከፍቅር ይልቅ ዕልህ የሚንጠው ይመስል ከአዕምሮው ጓዳ አንዳች ድምፅ እየደወለ ያስፈራራዋል።

‹ይህች ልጅ ገድህ ናት.... የብዙ ሰዎች አይን ያርፍባታል ብዙ ነው። እሷን ካጣህ ሀብትህ ይረግፋል፤ ህይወትህም መቅኖ ያጣል።.....›

ይህወት አሁንም ዝምታን መረጠች። ሁኔታውም ሆነ ጥያቄው የጤንነት ይሁን የዕብደት መለየት አልቻለችም። ሰማይነህ ለጋብቻ የሚፈልጋት መሆኑን ከገለፀላት ሰንበትበት ብሏል። ሆኖም ግን ውሳኔ ላይ አልተደረሰም። በእሷ በኩል ጉዳዩን ሀገር ሰምቶት፤ ፀሐይሞቆት፤ ተመክሮበት ሊደረግ ይችላል የሚል ዕምነት ነበራት። በትዳር አብሮ ለመኖር ከባድ ጥያቄ እንዲህ ድንገተኛ ዱብ ዕዳ ይሆናል ብላ አልገመተችም። ቶሎም አልተዋጠላትም። ለወትሮው ማታ ማታ ብቻ ብቅ የሚለው ሰማይነህ ዛሬ በጠራራ ፀሐየ ከስራው ላይ ተነስቶ መጥቶ ይህንን ውሳኔውን እንደመርዶ መተንፈሱ ጤነኛነቱን አጠራጠራት።

«ምንድነው ዝምታው?..... በሀሳቤ መስማማትሽን በቃላት ግለጪልኝና ሁለታችንም ዝግጅታችንን እንጀምር።

«ትንሽ ጊዜ ስጥተሽኝ ከእናቴ ጋር ብንመክርበት ደስ ይለኛል» አለችው በማግባባት ቅላፄና አስተያየት።

«እናትሽ የምታመጣው ለውጥ የለም። የማገባሽ እኔ ሰማይነህ ሽብሩ ነኝ። ለማንኛውም አማክሪያትና መልሳችሁን አዘጋጅታችሁ ጠብቁኝ። ማታ ተመልሼ እመጣለሁ» ብሎአት በር ላይ ወደቆመችው መኪናው አመራ።

የዘመናዊ መኪናውን ቁልፍ በፍጥነት አስነስቶ እያበረረ ሲሄድ፤ ህይወት ከግቢያቸው ዋና በር ላይ እንደ ቆመች በአይኗ ተከተለችው። ከአጠገቧ ከራቀላት በኋላ ሁኔታው አስገርሟት ለብቻዋ ሳቀች። በሳቅዋ ውስጥ ግን ምስቅልቅል ያለ ስሜት እየተሰማት ነበር። በቀጥታ ወደ ጓዳ ተመልሳ ከአክስትዋ ጋር መወያየቱን መረጠች። «እናቴ» የምትላት አክስቷን ወ/ሮ ስራሽ ብዙ ይመርን ነው። ሁሉም የሚጠራትና የሚያውቃት ስሟን አሳጥሮ «ወ/ሮ ስራሽ» በሚል ነው።

«ጋሽ ሰማይነህ እኮ ነው ያስጠራኝ። ደሞ ጋሼ አትበይኝ ብሎ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶኛል» አለቻት።

ሰማይነህ ውጭ በር ላይ መኪናውን አቁሞ ህይወትን በዘበኛ ያስጠራት ከአክስትዋ ጋር ጓዳ ውስጥ ቡና በመጠጣት ላይ እንዳለች ነበር። የመጣው ሰው ማን መሆኑን ዘበኛውን አስቀድማ ጠይቃ ያወቀች ቢሆንም፤ አክስትየዋ ለነገሩ እንግዳ ለመምሰል ሞከረች።

«..... ደግሞ ዛሬ በጠራራ ፀሐይ ምን አመጣው?.... ለነገሩስ ወደ ቤት ገብቶ እኔን ሰላም ሳይለኝ ተመልሶ ሄደ እንዴ?»

«አዎ፤ የተቻኮለ ይመስላል። እኔንም በቅጡ አላናገረኝም። አጭር ምርጫ ወርውሮልኝ ነው የሄደው»

«የምን ምርጫ ነው እሱ?» አለች አክስትየዋ የነገሩ አቅጣጫ እየገባት።

ህይወት እንደማፈር ብላ ዓይኖቿን ከአክስቷ እያሸሸችና እየተቅለሰለሰች «ሊያገባኝ ወይንም ሊገድለኝ ወስኖ መምጣቱን ነው የነገረኝ» ብላ ሳቀች።

አክስትየዋም ከት ከት ብላ ረዥም ሳቅ ሳቀችና «አይ ሰማይነህ! ዕድሜው ነው እንጂ ትልቅ ነገረ ስራው ሁሉ ገና የልጅ አይነት ነው። የሚፈልጋትን ሴት በስነ ሥርዓቱ ለጋብቻ መጠየቅ ሲችል የግድያን ምርጫ አሁን ምን አመጣው?!.... ይገርማል እኮ እባካችሁ» አለች።

«እኔንም የገረመኝ ይኸው ነው» አለች ህይወትም የአክስቷን ድጋፍ በማግኘቷ ተደስታ።

«.....ብቻ አትፍረጅበት። ያፈቀረና ያበደ አንድ ነው። አንቺ ልጅ ሆነሽ ነገሩን ባታውቂው ነው። ለመሆኑ ምን መልስ ሰጠሽው?.....»

«መጀመሪያ ነገሩን ከአንቺ ጋር እንደምወያይበት ነግሬው ለመልሱ ማታ ተመልሶ እንደሚመጣ አስጠንቅቆኛል። የእሱ ፍላጎት ጋብቻን በዚህ በያዝነው ወር ውስጥ እንዲፈፀም ነው።»

አክስቷ ይህን ስትሰማ ደስ አላት። ህይወት አባትም፤ እናትም የላትም። ወላጆቿና ታላቅ ወንድሟ በአንድ መኪና ወደ ሽርሽር ሲሄዱ ተገልብጠው የሞቱት ህይወት ገና የሦስት አመት ህፃን እያለች ነበር። ያን ጊዜ አክስቷ ቤት ጥለዋት እንደሄዱ አልተመለሱም። እሷም እዚሁ አክስቷ ቤት እንደ ተጣለች ማደግ ዕጣ ክፍሏ ሆኖ ለአቅመ - ሄዋን ደረሰች። እንደ እናት «እማዬ» የምትላት ከህፃንነት ጀምሮ ያሳደገቻት አክስቷ ወይዘሮ ስራሽብዙን ነው። እሷም ብትሆን መሀን በመሆኗ ህይወትን ማሳደጉ በፀጋ ተቀብላው፤ ደስታ ሰጥቷት ኖራለች። አሁን ለአቅመ - ሄዋን ስትደርስላትና ለጋብቻ ስትፈለግ መስማቱም ደስ አሰኝቷታል። ይሁን እንጂ ጠምቃ፣ ጠጅ ጥላ፣ ለቱጃር ወዳጆቿና መሸተኞቿ በየጠረጴዛው ውስኪ ደርድራ፣ የብፌ ዝግጅቷን አሰማምራ ልትድራት ነበር ፍላጎቷ። የሰማይነህ የጥድፊያ ጥያቄ ግን ለዚህ ሁሉ አመቺ አልሆነም።

የወ/ሮ ስራሽ ብዙ ይመር መተዳደሪያ የቡና ቤት ንግድ በመሆኑ ከብዙ ሰዎች ጋር ለመተዋወቅ ዕድሉን ከፍቶላታል። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ካዛንቺስ በሚገኘው ግቢዋ ውስጥ ከመኖሪያ ቤትዋ ለይታ አነስተኛ የውስኪ ቤት በመክፈቷ በከተማው ውስጥ ሀብት አላቸው የሚባሉ ውስኪ ቀማኖች በየምሽቱ ይጎበኟታል። ሰማይነህን ጎትታ ያማጣችውም ይህችው ውስኪ ቤት ናት። መኖሪያ ቤቱ አሮጌው አይሮፐላን ማረፊያ ሲሆን የወርቅ ቤትና ሌሎች የንግድ እንቅስቃሴዎቹን የሚያካሂደው

መርካቶ ነው። ማታ - ማታ ማምሻው ደግሞ ካዛንቺስ ወ/ሮ ስራሽ ውስኪ ቤት ሆኗል። ህይወት ከጓዳ ወጥታ ከአክስቷ ጎን ውስኪ ቤቷ መቆም ከጀመረች ወዲህ የወ/ሮ ስራሽብዙ ገበያ ደርቷል። አብዛኛው ህይወትን ተመልካችና ፈላጊ መሆኑም ገብቷታል። የአሁኑ የሰማይነህ ጥድፊያ ሌሎች ተወዳዳሪዎቹን ለመቅደም መሆኑን ገመተች። መጣደፋን የፈለገችው ቢሆንም እንዲህ «ሱሪ በአንገት» ይሆንብኛል ብላ አላሰበችም።

«.....ይሄማ ዕብደት ይሆናል» አለች የመጣደፉን ነገር በሀሳብዋ ስታወጣና ስታወርድ ቆይታ።

«እኔም እኮ ያልኩት እሱን ነው።»

«ተይው በቃ..... እሱን እኛ እናስተካክለዋለን። ለድግሱ የሚያስፈልጉንን ነገሮች እስክናዘጋጅ ቢያንስ የስድስት ወር ዕድሜ ያስፈልገናል።..... ዋንው ነገር ለጋብቻ መስማማቱ ነው።»

«ለጋብቻውም ቢሆን እኮ.....» ብለ ህይወት በማመንታት አይነት አቋረጠች።

«ምን?!...» አለቻት አክስትየዋ የማመንታት አዝማሚያዋን በመቃወም ዓይነት ግንባሯን ከስክሳ «የሰማይነህ ፍላጎት አንቺን ልጄን ለጊዜው ለማማገጥና በሴትነትሽ ለመቀለድ ቢሆን ኖሮ እኔም እናትሽ አልፈቅድለትም ነበር። በአሁኑ በተበላሸ ዘመን እንዲህ በቁም ነገር ለጋብቻ የሚጠይቅን ወንድ ማስቀየም አይገባም።..... በዚያ ላይ ደግሞ ሰማይነህ የተትረፈረፈ ሀብት ያለው ሰው መሆኑን የምታውቂ ይመስለኛል። ሰተት ብለሽ እግዚአብሔር የሰጠሽ አዱኛ ውስጥ መግባት ነው»

የአክስቷ አቋም ከዚህ እንደማይቀር ህይወት ቀድሞውንም ታውቃለች። ማንኛውንም ሰው የምትመዝነው በሀብቱ ነው። የደንበኞቿን ክብደትና ቅለት የምትመዝነው ውስኪ ቤቷ ውስጥ በሚያጠፉት ገንዘብ መጠን ነው። የሰማይነህን ፍላጎት ከተረዳችበት ጊዜ ጀምሮ ይህወትን በተለያየ መግነድ ስትቀሰቅሳት ቆይታለች። እንድትቀርበው፤ እንድትሽኮረመምለት፣ ውስኪውን እሷ እንድትቀዳለትና በፍቅር እንድታዋልለው የግል ልምዷን በመንተራስ ደጋግማ መክራታለች። ከሰማይነህ ጋር ከውስኪ ቤት ደንበኝነት አልፎ በጋብቻ መተሳሰሩ ሀብቱን በርቀት መጋራት መሆኑን ስታሰላው ቆይታለች። መተዳደሪያቸው የውስኪ ቤቷ ገቢ እንደመሆኗ መጠን ህይወትም አክስቷና የረዳች እየመሰላት ከሁሉም ጋር እየተሳሳቀች ሳልፋለች። አሁን ግን እንዲህ አይነት ወሳኝ ጉዳይ ከተነሳ ቅሬታዋን መግለፅ ሊኖርባት ነው።

«.....ጋሽ ሰማይነህ እኩያዬ አይደለም። ጋሼ እያልኩት እንዴት ባሌ እንደሚሆን አይገባኝም» ብላ ሳቀች።

«ይሄ ምንም ችግር የለውም። አንሶላ መጋፈፍ ስትጀምሩ ‹ጋሼ› ማለትሽ ይቀርና እንዲያውም በቁልምጫ ‹ሰሚ› ትይዋለሽ የዕድሜውም ነገር የሆነ እንደሆን ለትዳር ጥሩ የሚሆነው ወንዱ ተለቅ ሴቷ አነስ ስትል ነው.... ሰልሎ ያልጠገበ ጎረምሳ ለትዳር ሊሆን አይችልም፤ የስሜት ወረቱን ሲጨርስ ‹አይንሽን ላፈር› ብሎ ከነዲቃላሽ ነው ሜዳ ላይ የሚጥልሽ። ምራቁን የዋጠ ሰው ለትዳር ጥሩ ነው.....»

«.....በዚያ ላይ ደግሞ ቅናቱ በጣም ያስጠላኛል...» በማለት አቋረጠቻት» ከእሱ ጋር ካልሆነ በቀር ከማንም ጋር እንዳወራና እንድጫወት አይፈልግም። እዚህ ቤት በመጣ ቁጥር እንኳ እኔ እስረኛ የሆንኩ ነው የሚመስለኝ። ገና በውጭው እንዲህ የሚቀና ከሆነ ቤቱ ውስጥ ካስገባኝ በኋላ ምን እንደሚያደርገኝ አላውቅም።»

«ይሄንን አትጥይው፤ ጥሩ ምልክት ነው። ወንድ መውደዱ የሚታወቅበት እንዲህ በቅናት ሲጦፍ ነው። ‹ቅናት የፍቅር ጥላ ናት› ሲባል አልሰማሽም?!..... አግብቶሽ የራሱ ማድረጉን ካረጋገጠ በኋላ፥

ደግሞ ይሄ ፀባዩ ይለቀዋል። አሁን እኮ የሚቀናው ሌሎች ፈላጊዎችሽ እንዳይቀድሙት በመፍራት ነው።»

የአክስቷ መከላከያ ነጥቦች ለህየት አልተዋጡላትም። የዕድሜያቸው ልዩነት ትንሽ አይደለም። ሰማይነህ የአርባ ሰባት አመት ጎልማሳ ሲሆን፣ ህይወት የሃያ ሁለት አመት ወጣት ናት። ቢወልድ ያደርሳታል። ቁመቱና ሰውነቱ መካከለኛ ሲሆን ገብስማ ፀጉሩ ገባ - ገባ ብሏል። ግንባሩ ሁሌም እንደተኮሳተረ ነው። የቅናቱም ጉዳይ ገደብ ያጣ ነው። በሚረባውም፣ በማይረባውም በቅናት ሲብከነከርን ህይወት ደጋግማ ታዝባዋለች። ይህም ሆኖ ግን ከአክስቷ ግን ቆማ ውስኪ ቤት ውስጥ እንደመኖሯ መጠን የሰማይነህ ሀብትና ንብረት ህይወትንም አጓጉቷታል። እንደሸሚዝ እየለዋወጠ የሚይዛቸውን ዘመናዊ መኪናዎች የራሷ አድራ መንዳት፣ እንደጉድ የሚነገርለት የተንጣለለ ቪላ ቤት ውስጥ ገብታ ማዘዝና የሀብቱ ምንች የሆኑትን የወርቅ ቤትና የሸቀጣ ሸቀጥ ማከፋፈያ ድርጅቶች ባለቤት መሆን ልቧ ከጅሏል።

ውበቷን አይተው የሚነሆልሉ ብዙ ብዙ ናቸው። ወይዘሮ ስራሽ ብዙ ውስኪ ቤት የሚጠጡት መደበኛ ደንበኞቿ ሁሉ አይናቸውን ጥለውባታል። ለባብሳ ወደ ውጭ ስትወጣ እየጠበቁ «እንሸኝሽ» የሚሏት እግረኞችና ባለመኪናዎች፣ በርቀት የሚሳለሚት የአይን ፍቅረኞች፣ ቀርበው የሚለክፏት አለሌዎች የትየለሌ ናቸው። ለማንም ቢሆን ምንጊዜም ፈገግታ ከፊቷ ላይ አይጠፋም። የተሟላ ውበት ከተመጣጠነ ቁመት ጋር ታድላለች። በተለይ ጠይም ፊቷ ላይ ጎላ ጎላ ብለው የሚታዩት አይኖቿና ረዥም አፍንጫዋ ቁንጅናዋን አድምቀውታል። ወጣትነቷ ራሱ ደግሞ ሌላ ውበት ነው። ይህችን የፈካች አበባ ለመቅጠፍ ብዙ እጆች ቢዘረጉም ዕድሉ የአንድ ሰው ብቻ ነው። ያ ሰው ከጀርባው በሀብት ተደግፎ በድፍረት ቀርቧል።

«እማዬ.... እኔ እንጃ......ፍርሀት ፍርሀት አለኝ» አለች ህይወት ሀሳቧን ስታወጣና ስታወርድ ቆይታ።

«እንግዲህ ሁልጊዜ ልጅ እንደሆኑ አይኖርም። ውበትም ረጋፊ ነው፤ ዕድሜም ሀላፊ ነው። ሁሉንም ነገር በጊዜው መጠቀም ያስፈልጋል። በወጣትነት ዕድሜ በትዳር የመታሰርን ነገር ሲያስቡት ማስፈራቱ አይቀርም። ሁላችንም ያለፍንበት ስለሆነ እናውቃለን። እኔም በወጣትነት ዘመኔ ስንቱ ወንድ ‹ላግባሽ› እያለ አማላጅ ሲልክ፣ ስንቱ ቀብራራ ዝቅ ብሎ እግሬን ሲስም፣ ስንቱ ቱጃር ወርቅ ሲያነጥፍልኝ ‹አሻፈረኝ› ብዬ በውበቴ ኮርቼ ይኸው መጨረሻዬ በቡና ቤት ንግድ መተዳደር ሆኖ ቀርቷል። በወጣትነት ዘመን ዓይንን ጨፍነው ቆይተው በኋላ ሲገልጡት ይቆጭል። እንደነበር የሚቆይ ነገር የለም.... እኔ እናትሽ ዕድልሽ እንዳበላሽ የመጠበቅ ኃላፊነት አለብኝ። ስትዘናጊ ዝም ብዬ አላይሽም።»

በተዘዋዋሪ ዕቅጩን ነገረቻት። ህይወትም ትንፋሿን አምቃ ስታዳምጥት ከቆየች በኋላ በረዥሙ ተነፈሰች። አስቸጋሪ ምርጫ ውስጥ የመግባት አተነፋፈስ ነበር።

«....ደግሞም ሞኝ አትሁኒ» በማለት ቀጠለች አክስትየዋ «ባዶ ፍቅር ዋጋ የለውም። ትርፉ ጭቅጭቅ ነው። ፍቅር የሚታፍጠው ከገንዘብ ጋር ሲሆን ነው፤ የገንዘብን ኃይል ለማወቅ ዕድሜሽ ገና ነው። ለጅላጅል ባዶ ፍቅር የምትጠቂበት አደገኛ ዕድሜ ላይ ነው ያለሽው። ከአስር አመት በኋላ ግን እንደአሁኑ አታስቢም። ዓይኖችሽን ትገልጫለሽ። ያኔ ወደ ኋላ ዘወር ብለሽ ታመሰግኚኛለሽ። »

ህይወት ምርጫዋ አክስቷ ቤት በሚመላለሱ መሸተኞች ዙሪያ ብቻ መሆኑ አመለካከቷና አጥብቦታል። ሌሎች የመዝናኛም ሆኑ የመገናኛ ቦታዎች እንደ ልቧ መሄድ ስለማይፈቀድላት ሌላ ሙከራ ለማድረግ ዕድሉን አላገኘችውም። ሆኖም ግን የትምህርት ቤት ጓደኛዋ የነበረ አንድ ወጣት ምንጊዜም አዕምሮዋ ውስጥ አለ። ሄኖክ አንበሴ ይባላል። ለአጭር ጊዜም ቢሆን በወጣትነት አፍላ ፍቅር ብን ብለው ነበር። የአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከጨረሱ በኋላ ኮሌጅ የመግባት ዕድል ስላላገኙና ሥራ የማግኘት ዕድሉም እጅግ የጠበበ ስለሆነ ሄኖክ አሜሪካን ሀገር ወደ ሚገኙ ዘመዶቹ ዘንድ ሲሄድ፤ ህይወትም የአክስቷ ውስኪ ቤት አድማቂ ሆና ቀረች። ከሄኖክ ጋር በተከታታይ የፍቅር ደብዳቤዎች ይላላኩ ነበር። ድምፁ ከጠፋባት አንድ አመት ያክል ሆኖታል። አሁን በዚች ወሳኝ የጋብቻ ጥያቄ ሰዓት ላይ ሄኖክ አዕምሮዋ ውስጥ መጥቶ ድቅን አለ።

«እማዬ..... አንድ ያልነገርኩሽ ነገር አለ» አለች ስትፈራ ስትቸር ቆይታ።

«ምንድነው እሱ?» አክስትየዋም አፍራሽ ሀሰብ ላለመቀበል ግንባሯን አኮሳተረች።

«ሄኖክ የሚባል የትምህርት ቤት ጓደኛዬ..... ፍቅረኛዬ.... ነበር።

«እና.....ታዲያ ምን ይሆናል?!»

«አሜሪካን ሀገር ሄዶ አሁን የሚኖረው ዘመዶቹን ተጠግቶ ነው። አስተማማኝ ሥር ሲይስዝና በግሉ መኖር ሲጀምር እኔንም እንደሚወሰደኝ በደብዳቤ ቃል ገብቶልኛል።»

«አንቺ ልጅ ጤነኛ አልመሰልሽኝም» አለቻት አክስትዋ በማመናጨቅ አይነት። አጠገብሽ የቀረበልሽን አዱኛ ጥለሽ ገና ሩቅ ሀገር ሄደሽ በህልም ትዋኛለሽ?! ማነው አንቺ ብቻ ነሽ ቆንጆ ያለሽ?! ይሄ የምትይው ወጣት እኮ አሜሪካን አገር ሲገባ ዓይኑን ይገልጣል፤ ስንቱን ቆነጃጅት ያያል። የአንቺን መፈጠር እስከናካቴውም ይረሳዋል።... በዚያ ላይ ለትዳር የሚሆነው ምራቁን ዋጥ ያደረገ ሰው መሆኑን ቅድም ነግሬሻለሁ። ይልቅ ልብሽ ሲወላውል በእጅሽ የገባውን ዕድል እንዳታስመልጪ። እኔ ርግጡን ልነግርሽ እፈልጋለሁ። አንደኛ ነገር ሰማይነህን አግብቶ ሀብቱ ውስጥ ለመዋኘት የማይጓጓ ሴት የለም። ስንቶቹ ቆነጃጅቶች በውበታቸው ሊያጠምዱት ሞክረው አልተሳካላቸውም። ጭራሹን ጥብርር ነው የሚልባቸው። የዕጣ ክፍል ነገር ሆነና አንቺ ላይ ልቡ ወድቆ እሱ ራሱ ጠያቂ ሆነ። ይህኢንን እግዚአብሔር ያመጣልሽን ፀጋ ንቀሽ ብትተይው ግፉ በኋላ አጓጉል ቦታ ይጥልሻል። ሁለተኛ ነገር ደግሞ ሰማይነህ የኔ ቤት ምሰሶ መሆኑን ማሰብ አለብሽ፤ ገብያዬ የደራው በእሱ ሳቢያ እሱን ተከትለው በሚመጡና በሚገባበዙ ሰዎች ነው። እሱም ራሱ እኔ ቤት የሚያፈሰውን ገንዘብ ታውቂያለሽ። ተሰለው ጡት የሚጣቡት ሰው ነው። እግዜር ስተት አድርጎ ቤታችን ድረስ ሲያመጣው ደግሞ እንኳን ደህና መጣህ ብሎ እጅ ነስቶ ማስገባት ብቻ ነው!..... ይልቅ መወላወሉንና በወጥትነት ህልም ውስጥ መዋዠቁን ትተሽ መንፈስሽን ለሞቀ ትዳርና ለሚተርፍ ቤት አዘጋጅው፤ ደሞም አትጨነቂ። አንዴ ተፈራርማችሁ ቤቱ ከገባሽ በኋላ የማይሆንሽ እንኳ ሆኖ ከተገኘ ፍርድ ቤት ገትረሽው ሀብቱን እኩል ተካፍለሽ ነው የምትለያዩት። ነገሩን ማለቴ ነው እንጂ ይህንን እንኳ የሠይጣን ጆሮ አይስማ።»

ማታ፤ ገና ጨለማው ለዓይን ያዝ ሲያደርግ፣ ወ/ሮ ስራሽ ብዙ ዕጣን አጫጭሳና ውኃ አርከፍክፋ የውስኪ ቤቷን ከመክፈቷ ሰማይነህ ከተፍ አለ። ማንም ሳይቀድመው መጀመሪያ የመጣው አስቦበት ነው።

‹ይህ ሰው በፍቅር አብዷል ማለት ነው› አለች ወ/ሮ ስራሽ በልቧ።

«.....የታለች?!» አለ ገና ከመግባቱ፣ የረባ ሰላምታ እንኳ ሳይሰጣት፣ ህይወትን በዓይኑ እየፈለአ።

«ትመጣለች። ወዲያኛው ቤት ልብሷን እየለበሰች ነው» አለችው የፈለገውን በማወቅ።

«ምን ታደርግ ትመጣለች?! እዚያው ጓዳ ትቀመጥ እንጂ! ከንግዲህ እዚህ ቦታ ወጥታ መታየት የለባትም። አንቺም ውስኪ ቀጅሽን አዘጋጅ» አላት ተኮሳትሮ።

«ገና ምኑ ተያዘና?!..... ሳትፈራረሙ..... ቃል ሳይቋጠር..... ቀለበት ሳይታሰር...... እንዲያው ከመሬት ተነስቶ ማዘዝ ይቻላል እንዴ?»

የወ/ሮ ስራሽ አቀራረብ በቀልድ መልክ ቢሆንም ሰማይነህ ግን አምርሯል።

«ይሄ ሁሉ ጣጣ በአንድ ቀን የሚያልቅ ነገር ነው። ጊዜ መስጠት አያስፈልግም። ይልቅ አሁን አንቺን በግል ማነጋገር ስለምፈልግ ወዲያኛው ቤት እንሂድ»

«ውስኪዬንስ ማን ይሸጥልኝ?»

«ካስፈለገ በሩን ዝጊው፤ የዛሬ ማታውን ኪሳራ እኔ እከፍላለሁ።›

«እንደሱ እንኳ አይሆንም። በሰላም ሀገር በሬን መዝጋት የዘወትር ደንበኞቼን ማባረር ነው።»

«እንዲያው እዚህ ሠራተኞችሽን አቁሚና አስቀጂ፤ እንጂ የፈለግኩሽ ለከባድ ቁም ነገር ነው።
»

«ወ/ሮ ስራሽ በልቧ «እንዲህ ያጣደፈው ነገር ምንድነው?» እያለች የቤት ሰራተኛዋን ከዋናው ቤት ጠርታ ባንኮኒው ውስጥ አቆመቻትና ማስጠንቀቂያ ሰጠቻት።

«.....ሰዎች ሲመጡ እኔ የሌለሁ መስሏቸው እንዳይመለሱ። ‹ልብሳቸውን እየለበሱ ነው፤ ይመጣሉ› በያቸው።..... ስትቀጂ እንዳትከለብሺው ተጠንቀቅሽ። እኔም አልቆይም መጣሁ።»

ወ/ሮ ስራሽና ሰማይነህ በጓዳ በኩል ወጥተው ወደ ዋናው ቤት ሲሄዱና ህይወት ወደ ውስኪው ቤት ስትመታ ተገጣጠሙ።

«ወዴት ልትሄጅጂ ነው?!» በማለት ሰማይነህ እንደባል ተቆጣት። ህይወትም ሳታስበ እንደ ሚስት ደንገጠች።

«ከጓዳ እንዳትወጪ ተፈርዶብሻል። ተመለሺና መኝታ ክፍልሽ ሁኚ» አለቻት አክስቷም በማከታለብ።

ህይወት በማዘን ፊንታ እየሳቀች ግራ በተጋባ ስሜት ወደ መኝታ ክፍሏ ተመልሳ ቴፐሪኮርደሯን ከፈተች። የተጠመደው ክር የሚዘፍነው ሌላ ነው። በህይወት ጆሮ ውስጥ የሚደውለው ግን «ያዋከቡት ነገር ምዕራፍ አያገኝም» የሚለው የጥላሁን ገሠሠ ዘፈን ነበር።

«የማነጋግርሽ ጉዳይ ሳታውቂው የቀረሽ አይመስለኝም» አለ ሰማይነህ ሳሎን ገብተው ከመቀመጣቸው።

«ስለ ህይወት ይመስለኛል» አለችው ወ/ሮ ስራሽም ከሞቀ ፈገግታ ጋር።

«ትክክል ነሽ.... ህይወትን ላገባት ወስኛለሁ። ሠርጋችንም በዚህ ወር ውስጥ መከናወን አለበት።»

«ከሷም ጋር ይህንኑ ስንነጋገር ነበር የቆየነው። ዋናው የናንተ መፈላልግ ነው። እኔም ልጄ እንዳንተ ያለ ቁም ነገረኛና ትልቅ ሰው እጅ ላይ መውደቋ ደስ ይለኛል።......ሆኖም ለጋብቻ የወሰንከው ጊዜ በጣም አጠረ። መጀመሪያ በባህላችን መሠረት ሽማግሌ መላክ አለበት። ለሽማግሌዎቹ የአዎንታ መልስ ከተሠጠ በኋላ ደግሞ የሠርጉን ጊዜ በጋራ መወሰን አለብን። ለዝግጅቱ ብቻ ቢያንስ ስድስት ወር ያስፈልገናል።»

«እኛ ቤተሰብ ነን። ሁሉንም አሳጥረን መጨረስ ስንችል በዙሪያ ጥምጥም መሄድ የለብንም።
»

«ቢሆንም.....ባህላችንን መጠበቅ ያስፈልገናል። ክብሩስ ቢሆን.....ወግ ማዕረጉስ ቢሆን.....»

«የለም፤ እኔ ደግሞ ከዚህ ወር ማለፍ አልችልም» ብሎ ግንባሩን ከስክሶ በማምረር ተናአገረ።

ሰውዬው ሀሳቡን እንዳይቀይር ወ/ሮ ስራሽ ልቧ ፈራ። ጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ መሆናቸውን በሃሳቧ አሰላችው። ብዙ መከራከር አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፤ ገበያ መግፋት ነው። ለማንኛውም አንድ ሙከራ አደረገች።

«እንዴ!..... አንተ ከዚህ ወር ምን አለህ?»

ወደ ጆሮዋ እንደመጠጋት ብሎ በሹክሹክታ ድምፅ «ጠንቋይ ነግሮኛል» አላት።

«እውነትህን ነው?» አለችው የምታውቀውን ጉዳይ እንዳላወቀች ሆና።

«ስራሽ ሙች፤ ዕውነቴን ነው። ይህንን ወር ካለፍን በመካከላችን ምቀኛ እንደሚገባና የጋብቻው ሀሳብ እንደሚከሽፍ እኔ የምሄድበት ባለውቃቢ ዛሬ ጥዋት ነግሮኛል። ይህን ስለሰማሁ ነው ቅድም መጥቼ ለህይወት በአስቸኳይ መሆን እንዳለበት የነገርኳት። ህይወትን ፈላጊ ምቀኞች ዙሪያዬን ስለከቡብኝ ሳልቀደም መቅደም አለብኝ፤ ማታ - ማታ አንቺ ቤት እያመሹ ከህይወት ጋር የሚቃለዱትንና የሚቁለጨለጩትን ጓደኞቼንም ቢሆን አላምናቸውም። ምቀኛ የሚነሳ ከአጠገብሽ ነው። ስለዚህ ለማንኛውም ነገር ጊዜ መስጠት አያስፈልግም።»

ወ/ሮ ስራሽ ራሷም በጠንቋይ ታምናለች። ገበያዋ ቀዝቀዝ ሲል ወይንም አንድ ያለመችው ነገር ሲኖር በየጊዜው የምትሄድበት ባለውቃቢ አላት። ከእሱ ቃል አትወጣም። አሁንም የስማይነህ ችግር ልቧ ስለሚያውቀው ቶሎ ተሸንፈች።

«እንደዚያ ከሆነሳ መፋጠን አለበት። ትንሽም ቅር የሚያሰኘው የሠርጉ ጉዳይ ነው እንጂ»

«ሠርጉ ምንም ችግር የለውም። ሒልተን ወይንም ግዮን ሆቴል ልናደርገው እንችላለን። ማንኛውም ነገር በአስቸኳይ እንዲደርስ ይደረጋል። ለዚህ አታስቢ። ገንዘብ ሁሉንም ያፋጥነዋል። ሀገር ምድሩ ‹ጉድ!› የሚልለት ሠርግ እንደሚሆን አልጠራጠርም።»

ወ/ሮ ስራሽ «ልጄን ጠጅ ጥላ፣ ጠላ ጠምቃ፣ ድል ያለ ድግስ ደግሳ ዳረች» ለመባል የነበራት ከፍተኛ ጉጉት ቢሰናከልም፣ በሒልተን ወይንም በግዮን ሆቴል መሠረጉ ታላቅ ዝናን እንደሚያጎናፅፋት በማሰብ ተፅናናች።

«በል እንዳሻህ አድርገው እንግዲህ። ሁሉንም ላንተ ትቻለሁ። አደራ የምልህ እንደ ባልም፣ እንደ አባትም ሆእንህ ልጄን በደንብ እንድትይዝልኝ ነው። ጋብቻችሁ የተባረከ እንዲሆን መርቄ ሰጥቼሃለሁ።»

«ሁለቱም ተነስተው ትከሻ ለትከሻ ከተሳሳሙ በኋላ «አንድ ጥያቄ ግን ልጠይቅሽ እፈልጋለሁ» አላት ሰማይነህ።

«ምንድነው እሱ?»

«ህይወት.....እስከዛሬ ከማንም ወንድ ጋር እንዳልሄደች እርግጠኛ ነኝ....»

«እንዴዬ!.... ምን ማለትህ ነው ሰማይነህ?!.....እንዲያው ተፈጥሮዋ ሆኖ ከሁሉም ጋር ስትስቅ ስትጫወት ሂያጅ ትመስል ይሆናል እንጂ የኔ ልጅ በዚህ ረገድ ቁጥብ ናት። እኔ እናቷም በፍፁም አላስደፍራት።»

«እኮ...... ክብረ ንፅህናዋ እንደ ተጠበቀ ነው?»

«በአስር ጥቶቼ እፈርምልሀለሁ።»

«ይህንን ሳቋንም ቆጠብ ማድረግ ወይንም ማቆም አለባት። መጥፎ ነው። ለወንዶች መግቢያ ቀዳዳ ይሆናል።»

«ልክ ነህ እንመከራታለን። በተፈጥሮዋ ተጫዋች ሳቂታ ሆና ነው እንጂ ሌላ ብልግና እንኳ የላትም። ሆኖም ትዳር ሲይዙ ጥርስን ከደን ማድረግ እንደሚያስፈልግ እናስተምራታለን።»

ፅዋቸውን በማንሳት ውሳኔያቸውን ለማፅደቅ ተስማምተው ወደ ውስኪዋ በኢት ተመለሱ። ባለጀሮው ጠርሙስ ውስኪ ወርዶ ወ/ሮ ስራሽና ሰማይነህ በክዳኑ ቀመሱለት። እሷ ቤት ጎራ ሳይሉ ወደ ቤታቸው የማይገቡ አራት ያክል ደንበኞቿ ገብተው መለኪያቸውን ጨብጠው ነበር።

«ለእኛም አካፍሉን እንጂ..... ፍንጥሩ ምንድን ነው?» አለ ባህሩ ፂሞ ባንኮኒው ጥግ ብርጭቆውን ይዞ እንደ ቆመ።

«ና ጠጋ በል እንጂ ፂሞ። ልብ አላልኩህም እኮ» በማለት ሰማይነህ ጋበዘው።

ባህሩ ብርጭቆውን ይዞ ተጠግቶ አብሮአቸው ፅዋውን እያነሳ «ምክንያቱ ይገለፅልና» አላቸው።

«ሚስጥር ነው፤ ወደ ፊት ይገለፅልሀል። አሁን አርፈህ ጠጣ» አለችው ወ/ሮ ስራሽ።

«እኔ የጠየቅሁት ጋባዡን ነው። የአንቺን እጅ እንደሆነ አይተነው አናውቅም» አለና የተንዠረገገ ፂሙን እየላገ ቀላለደ።

ፊቱን የዋጠው ፂሙ ለረዥም አመታት ምላጭም ሆነ መቀስ ነክቶት አያውቅም። የቁመቱ መርዘምና የፂሙ መንዠርገግ ልዩ ምልክቶቹ ናቸው። «ፂሞ» የሚለው ቅፅል የወጣለትም በዚሁ ምክንያት ነው። ብዙ ያነበበ ምሁሩ ነው ይባላል። በህግና በምጣኔ ሀብታዊ ጉዳዮች ላይ የአማካሪነት ቢሮ ከፍቶ የሚተዳደር ሲሆን ጥሩ ገቢ ያገኛል። ሆኖም ገንዘቡ ከአረቄ ቤት አያልፍም። አረቄ ውስጥ ተደብቆ በብቸኝነት የሚኖር ይመስላል። ጓደኞችም እኚሁ አረቄ ቤት በየምሽቱ የሚያገኛቸው ሰዎች ብቻ ናቸው። ሴቶችን አይወድም። ለሴቶች ጥሩ ነገር ሲያወራ ተሰምቶ አይታወቅም። ሰማይነህ እዚህ ቤት ከሚመጡ ሰዎች ሁሉ ባህሩ ፂሞን የሚቀርበውና የሚወደው ህይወትን ስለማይፈልግበት ነው። ብዙዎቹ ህይወትን ለማሽኮርመምና በህይወት ፊት ለመታየት የሚያደርጓቸውን ሲያሳጣቸው ባህሩ ግን ከነመኖሯም ትዝ አትለውም። ከሚያነባቸው መፃህፍት ውስጥ አንድ - አንድ ጥቅስ እየለቀመ የሴቶችን ደካማ ጎን ማጉላት ይወዳል። ለማይህነህ ይህንንም ተግባሩን ይወድለታንል።

«ስለ ሴቶች..... አንድ በለን እንጂ» አለው በጨዋታው ለመዝናናት ፈልጎ።

«ባልዛክ የተባለ ደራሲ ምን አለ መሰለህ፤ ሴትን ማስተዳደር የቻለ ወንድ ሀገር ማስተዳደር ይቻላል።»

«ትክክል ነው» ብሎ ሰማይነህ መሳቅ ጀመረ። ወ/ሮ ስራሽ ደግሞ በቅሬታና በነቀፋ ባህሩ ፂሞን ገላመጠችው።

ይህ የተለመደ የዘወትር ሁኔታቸው ነው። ፂሞ ስለ ሴቶች ሲናእር ሰማይነህ ይደስታል፤ ወ/ሮ ስራሽ ትናደዳለች። ፂሞ ግን የእሷን ንዴት ከቁብ አይቆጥረው።

«ቮልቴር ደግሞ ምን ብሏል መሰለህ?.....» አለ ብርጭቆውን ጨልጦ እያስቀመጠ «ሴት ልጅ አንድ ሚስጥር ብቻ መጠበቅ ትችላለች። ያም የዕድሜዋ ሚስጥር ነው»

ይሄ በቀጥታ ወ/ሮ ስራሽን ለመንካት ይመስላል። በሀምሳዎቹ አጋማሽ ዕድሜ ውስጥ የምትገኝ መሆኑ ቢታወቅም እሷ ግን «ገና ልጅ ነኝ» ከማለት ወደ ኋላ አትልም። ደግሞም በኑሮ ምቾት፣ በፀጉር አተኳኰስና በልብስ አመራረጥ ዕድሜዋን ደብቃዋለች። እሷ ቤት የሚመጡ መሸተኞችም ሆኑ ሌሎች የቅርቧ ሰዎች «አንቺ» እንዲሏት አድርጋለች። በየጊዜው የሚለዋወጡ የማድቤት ሰራተኞቿ ብቻ ናቸው «አንቱ» የሚሏት።

«ሴቶችን የሚያስጠላ በሽታ.... ከኮሶ ጋር ደባልቀው አጠጥተውሀል መሰለኝ» አለች ፂሞን የጎድን እያየች።

ሰማይነህ ሳቁን አላቋረጠም ነበር።

«አንተ ደሞ የማያስቀው ያስቅሀል፤ ይልቅ ውስኪውን ጠጣ» ብላ ለሁለቱም ቀዳችላቸው።

ባህሩ ፂሞ ቀልዱን ሊቀጥል እያሰበ ጥቅሶች በማሰብ አዕምሮውን ሲፈታትሽ የሁለት ሰዎች መምጣት አጨነገፈበት።

ኩራታቸው ገፅታቸው ላይ የሚነበብ፣ በአለባበሳቸው የደመቁ፣ እጃቸውና አንገታቸው ላይ ቦግ ብሎ የሚታይ የወርቅ አምባርና ሀብል ያጠለቁ ጐት ወፋፍራሞች እየተጐማለሉ ወደ ውስኪዋ

ቤት ገቡ። ይትባረክ አበራና አቡበከር ደሜ ናቸው። በከተማው ውስጥ የታወቁ ባለ ሀብቶችና ነጋዴዎች መሆናቸው ይነገርላቸዋል። ከሰማይነህም ጋር ጓደኞች ናቸው። አብረው ይበላሉ ይጠጣሉ፣ ይዝናናሉ፤ ከልባቸው ግን አይተማመኑም። በንግዱ ዓለም አንዳቸው ሌላቸውን ለመጣል የሚያሴሩ ምቀኞች ተደራርገው ስለሚወሳሰዱ እንዲያውም በውስጣቸው የጠላትነት ስሜት አለ። በሚገናኙበትም ሆነ አብረው በሚሄዱባቸው ቦታዎች የሚያሳዩት ፉክክር ጤናማ አይመስልም።

ሰላምታ ተሰጣጥተወ ባንኮኒውንና ወ/ሮ ስራሽን ከብበው ከቆሙ በኋላ «እንዴት ነው?..... ዛሬውስ በደንበኛን ተያያዝሽው እንዴ?» በማለት አቡበከር በቀልድ መልክ ሰማይነህን ወጋ አደረገው።

«የደስ ደስ ነው። አናንተም እንድትጠጡ ተጋብዛችኋል» አላቸው። ወ/ሮ ስራሽ ፈጠን ብላ የመቀዳዳት ስራዋን አከናወነች።

«ምክንያቱም ይነገረን እንጂ..... ምን አገኘህ?» አሉት ሁለቱም በአንድ ድምፅ።

«እሱን ወደ ፊት ታውቁታላችሁ፤ አሁን የደስታዬ ተካፋይ ከሆናችሁ ይበቃል» ብሎአቸው ብርጭቆአቸውን አጋጨ።

ሰማይነህ በልቡ ከፍተኛ የኩራትና የአሸናፊነት ስሜት እየተሰማው ነበር። እነዚህ ሁለት ሰዎች ህይወትን ፍለጋ እንደመጡ ያውቃል። ውስኪያቸውን የሚያወራርዱት የህይወትን ውበት እያደነቁና ከእሷ ጋር እየተሳሳቁ ነው። አሁንም በዓይናቸው ግራ ቀኙን ሲማትሩ ወደ ጓዳ ሲቀላውጡ ምን እንደሚፈልጉ ገብቶት በልቡ «እርማችሁ አውጡ» እያለ ነበር።

«ወ/ሮ ስራሽ..... ዛሬ ምነው ብቻሽን ሆንሽ?».... አላት ይትባረክ በጎድን ጥያቄ።

«የምን ብቸኝነት አመጣህ?..... ይኸው እናንተ አላችሁ አይደል እንዴ? አለችው ወ/ሮ ስራሽ፣ አውቃ ጥያቄው ያልገባት ለመምሰል።

«እኛማ ጠጪዎች ነን።..... አንቺን የሚረዳ ቀጂ ነው የጠየቅነው።»

የሰማይነህን ስሜት ለማጤን ወ/ሮ ስራሽ ሰረቅ አድርጋ ተመለከተችው። እንዳይናደድባት ለመንከባከብ ታጥቃ የተነሳች ትመስላለች።

«ለመቅዳቱ እኔ መች አነስኩ!.... ይልቅ አርፋችሁ ጠጡ» አለቻቸው በደፈናው።

ሰማይነህ የውሸት ጥርሱን እያሳያቸው በልቡ ‹ህይወትን ለአንዴም ለሁሌም በድል አድራጊነት ወስጄያታለሁ። ከአሁን በኋላ እዚህ ብታ አታገኟትም፤ በከንቱ አትድከሙ። የራሴ - የግሌ አድርጌያታለሁ። እግንዲህ እርማችሁን አውጡ፤ በቅርብ ቀን ለሠርጓ ስትጠራችሁ ቁርጣችሁን ታውቁታላችሁ። ተሸናፊነታችሁን አምናችሁ፣ ምቀኝነታሁ እንደያዛችሁ ሌላ ቦታ ሄዳችሁ ብታፈጡ ይሻላችኋል። ህይወትዬ ከንግዲህ የእኔ ብቻ ነሽ› እያለ ያስብ ነበር።

ከሀሳቡ መልስ በደስታ ውስኪውን በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አደረገና «እባክሽ ቅጂልኝ ልጠጣ። እናንተም ጠጡ - እንጠጣ» እያለ ተንቀባረረ።

አቡበከርና ይትባረክ ተያዩ። ከስማነህ አነጋገር አንድ ነገር ሸተታቸው። የንግድ ተወዳዳሪዎቹ እንደመሆናቸው መጠን ‹ምን ይሆን› የሚለው ጉጉት ልባቸውን አልሰቀለውም። የሆነውን ሁሉ ያወቁ ይመስላሉ። ከወ/ሮ ስራሽ ጋር ተጠቃቀው ተሳሳቁ።....

# ክፍል ሁለት

የጥቅምት ወር ከማለቁ በፊት አስፈላጊው ዝግጅት ሁሉ ተደርጎ የሠርጉ ቀን ደረሰ። «አይቻልም» የተባለው ሁሉ በገንዘብ ኃይልና ብዛት ተከናወነ።

«ወቸጉድ! ማልቀስስ ለገንዘብ ነው።..... ይመር ይሙት! እንዲያው ምኑን ከምኑ አድርገው እንዲህ አሳመሩት እባካችሁ!..... እኛንም ሳያደክሙን፣ ማድ ቤት ሳያርመጠምጡን፣ ከአተላና አምቡላ ጋር ሳያጨማልቁን ገላገሉን» አለች ወ/ሮ ስራሽ በሆቴል ቤቶች አስተናጋጅነት የተዘጋጀውን ሠርግ እያደነቀች።

የምሳ ግብዣና የፎቶ ግራፍ ፕሮግራም በግዮን ሆቴል፣ ትላቅ የኮክቴል ግብዛ በሒልተን ሆቴል ተደርጎ ማታ ወደ ሙሽራው ቤት ሲገቡ ደግሞ በነዚሁ በሆቴሎች አስተናጋጆች የተዘጋጀው ራት ይጠብቃችዋል። ብዙ ሰው የተጠራው በኮክቴል ግብዣው ላይ ነው። ውስኪ እንደ ውሀ እየተቀዳ ጭፈራውና እስከስታው የቀለጠውም እዚሁ ኮክቴል ላይ ነው። በሠርጉ ስፋትና በወጪው ብዛት አድናቆቱን የማይሰነዝር ተጋባዥ የለም። በተለይ በህይወት ዕድል የቀኑ ሴቶች በርካታ ናቸው።

«እንዴት ያለችው ዕድለኛ ነች እባክሽ!..... ተዝቆ የማያልቅ ሀብት ውስጥ ሰተት ብላ እኮ ነው የገባችው» ትላለች አንዷ።

«ለጥሎች የመጣላት ወርቅ ብቻ የትናየት! እንደ ልብስ ታጠልቀው እንደሆነ እንጂ አንገቷና እጇ ላይ ብቻ አድርጋ አትጨርሰውም» ትላለች ሊላዋ።

«የመኪና ቁልፍም እኮ ተሰጥቷታል። ያውም የዘጠና አራት ሞዴል አዲስ ቶዮታ!»

«ፐ!..... መታደል ነው። ምን ታደርጊዋለሽ!»

«የሚዜዎቹ ልብስ ራሱ እንዴት እንደሚያምር ታይዋለሽ?»

«በጣም እንጂ!...... ከሙሽሮቹ ልብስ ጋር ከጣልያን አገር በትዕዛዝ አብሮ ነው የመጣው ሲሉ ሰምቻለሁ። ያውም አስር ቀን በማይሞላ ጊዜ ውስጥ»

«ሚዜዎቹ ራሳቸው ዕድለኞች ናቸው። አሁን ጊዜ ልብስ ገዝቶ አጅቡኝ የሚል ሙሽራ የት ይገኛል?!»

ትንሽ ቆየት ብለው ደግሞ የህይወትን ቁንጅናና የሰማይነህን ሀብት ማወዳደስ ይጀምራሉ።

«እሷ ሲበዛ ቆንጆ ናት፤ ስዕል ነው የምትመስለው። በዚያ ላይ የሙሽራ ልብሷ ደግሞ አደመቃት።

«እድሜዋም ቢሆን ገና ልጅ ናት።»

«አዎ፤ በዕድሜና በቁንጅና እንኳ አይመጣጠኑም። እሱ ጠና ያለ ሰው መሆኑ ያስታውቃል። እንዲያውም ሰውነቱን በምቾት ይዞት ነው እንጂ ዕድሜውስ ብዙ ሳይገፋ አልቀረም።

«መልካም የለውም እንጂ። በሠርጉ ቀን ያላማረ መቼ ሊያምር ነው?! በውድ ጋዳ ያስመጣው የሙሽራ ልብስ እንኳ ከሱ ላይ ተራ ሳልቫጅ መለሰ እኮ።»

«ሀብቱ ይበቃዋል እባክሽ። የወንድ ልጅ መልኩ ሀብቱ ነው። ሀገር የሚገዛ ገንዘብ እንዳለው ሲያወሩ ሰምቻለሁ።

ባለ ሰባት ደረጃ ኬክ ተቆርሶ ሻምፓኝ ከተከፈተና ሙሽሪትና ሙሽራው ደንሰው ወደ ቦታቸው ከተመለሱ በኋላ ወ/ሮ ስራሽ የምታውቃቸውን እንግዶች ለማስተናገድ በአዳራሹ ውስጥ መንጎራደዷን ጀመረች። ባለ ረዣዥም ጥለት አዲስ ነጭ የሀገር ልብስ ለብሳ፣ አጭር ቁመቷን ከፍ የሚያደርግ ጫማ አድርጋ፣ ፀጉሯን አስጠቁራና በዘመናዊ ፋሽን ተሰርታ፣ ጨምደድ ያለውን ቀይ ፊቷን በቅባቅብቱ አሳምራ፣ ድምቅምቅ ብላ ነበር። ዕድሜልኳን ያጠራቀመችው ሳጥን ውስጥ ተቀብሮ የኖረው የወርቅ ዓይነት ዛሬ ወጥቶ አንገቷን፣ ደረቷን፣ ጆሮዋን፣ እጇንና፥ እግሯን አስጊጦላታል። በወርቅ የተንቆጠቆጠች ሴት ወይዘሮ!.....

«እንኳን ደስ ያለሽ ወ/ሮ ስራሽ» አሏት የሚያውቋት ሁሉ በአጠገባቸው እስኪታልፍ እየጠበቁ።

«በአምላካችሁ..... እንኳን አብሮ ደስ ያለን» እያለች የሴት ወይዝሮ ፈገግታዋን ረጨች።

«አንቺም ተድረሻል እንዴ?..... በጣም ደመቅሽ እኮ» በማለት ሁለቱ ሰዎች አስቆሟት።

አቡበከርና ይትባረክ ነበሩ። ከረቫታቸውን አላልተው ውስኪያቸውን እየናጡ እየጠጡ ሠርጉን በመፎተትና በንቀት ይመለከቱታል። ውፍረታቸው ሙቀቱን መቋቋም ስላልቻለ ንፋስ ለማግኘት ወደ መውጫው በር አጠገብ ቆመዋል።

«እንዴታ..... የልጄ ሠርግ ያው የእኔ ሠርግ ነው» አለች ወ/ሮ ስራሽ በኩራት።

ይትባረክ ባለ ትዳር ነው፤ ሆኖም ሚስቱን እቤት አስቀምጦ ውጭ ውጭውን ያያል። አቡበከር ግን አላገባም። ዕድሜው አንሶ ሳይሆን ከገንዘብ ጋር ፍቅር ላይ ስለ ወደቀ ሴቶችን ማፍቀር አልቻለም። የሚቀርቡትን ሴቶች ሁሉ ‹ሀብቴንና ንብረቴን ፍለጋ ነው የተጠጋችኝ› በማለት ያሸሻቸዋል። ሴቶችን የሚፈልገው ለጊዜያዊ ስሜቱ ማርኪያ ብቻ ነው። ሴቶችንም እንደ ሸሚዝ እየቀያየረ መቅመስና በገንዘብ ኃይል መጭወት ልማዱ አድርጎታል። በህይወትም ላይ ከዚህ የራቀ አመለካከት አልነበረውም። ነገር ግን ከይትባረክ ጋር የተማረከው ህይወትን ለሰማይነህ ለመልቀቅ የፈለጉትን ምክንያት አላቸው። ሆነ ብለው ሰማይነህን ያስቀኑታል እንጂ ህይወትን እንዲያገባት ከጀርባው ሆነው ጨዋታውን የሚመሩት እነሱ ናቸው።

«ነገሩ ሁሉ እንዳሰብነው ተፈፀመ አይደል!» አላት አቡበከር የወ/ሮ ስራሽን ትከሻ ያዝ አድርጎ።

«እንዴታ!.... እኔን የገረመኝ ሰማይነህ ከማግባቱ የመቸኮሉ። ለሠርግ መዘጋጃ የስድስት ወር ጊዜ ስጠኝ ብለው እንኳ እምቢ አለ። ተዓምር ነው የተሰራው!..... እናንተም ጉዋደኖች ናችሁ፣ ዘዴውን ማወቃችሁ» አለቻቸው።

«ባለውለታዎችሽ መሆናችንን አትርሺ»

«ምንጊዜም አልረሳም። እውነት እላችኋለሁ። ብድራችሁን ለመክፈል ያብቃኝ።»

«እንደተመኘሽው የሰማይነህ አማት ለመሆን በቃሽ።»

«በሚገባ......አሁን ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ መግባት አያስፈግም። ይልቅ ጠጡና ተጫወቱ» ብላ አርዕስቱን አሳጥራባቸው ሄደች።

ከእነሱ አልፍ እንዳለች ደግሞ እዚያው በሩ አካባቢ ባህሩ ፂሞን አየችው። እሱም ብቻውን ጥጉን ይዞ ቆሞ ውስኪውን እያጋባ ብርጭቆውን ይቀይራል። ከብርጭቆዋ በስተቀር ለማንም፣ ለምንም ደንታ ያለው አይመስልም።

«.....ምነው ብቻህን?! ወደ ጨዋታው ተቀላቀል እንጂ» አለችው ወ/ሮ ስራሽ።

«የሴቶቹ ጫጫታና ዝላይ አያስቀርብም። ታስረው የተፈቱ ይመስላሉ» አላት።

«ይልቅ ይቺን ጥላቻህን ትተህ አንተም እንደገና ለማግባት መዘጋጀት አለብህ። አይዞህ፤ እኛ ወገባችንን አስረን እንድርህለን።»

«ማ?..... እኔ ባህሩ?! ለጠላቴም አልመኝም። ማንኛዋም ሴት የግድ ማግባት አለባት። ወንዶች ግን ማግባት የለባቸውም። በማለት የቤንጃሚን ዲዝራኤልን ጥቅስ ጠቀሰላት።

«አይ አንተ....» ብላ በልቧ እያዘነችለት ወደ ሌሎች እንግዶቿ ሄደ። የምታውቃቸውን ሁሉ በአይኗ እየፈለገች «ብሉ ጠጡ» እያለች ጋበዘች።

ወጣቶቹ በአብዛኛው ጭፈራው መሀል ገብተው ያስነኩት ነበር። ከሀገረኛው ዘፈን ይበልጥ በውጭና ሙዚቃና የዳንስ ዓይነት ሲደሰቱ ይታያሉ። ዘመን አመጣሽ አስለባበሳቸው፤ ፀጉር አሰራራቸውና አደናነሳቸው ለአንዳፍታ የወ/ሮ ስራሽን ዕይታ ሳበ። የፋሽን ዓይነቶች ወደ ኋላ ተመልሰው ራሳቸወን እየደገሙ ይመስላል። የሴቶቹን አፈ ድስት ሱሪና ባለ ወፍራም ተረከዝ ነጠላ ጫማ ስትመለከት ወ/ሮ ስራሽ የራሷ የወጣትነት ዘመን ታወሳት። ያኔ ስትመለከት ወ/ሮ ስራሽ የራሷ የወጣትነት ዘመን ታወሳት። ያኔ የቢትልስ ዘመን ነበር። ፀጉራቸውን የከፈሉ ወጣቶች፣ አንገተ ሙሉ ቢትልስ ሹራባቸውን አጥልቀው ባለ ረዥም ኮሌታ ጃኬታቸውን ደርበው፣ አፈ ድስት ሱሪያቸውን እየጎተቱ በኩራት ተወጥረው በፒያሳ ሲዘዋወሩ ለአንዳፍታ በሀሳቧ ስለታዩዋት «አይ ዘመን!» ብላ ተከዘች።

የኮክቴሉ ግብዣ በደመቀ ሁኔታ ተከናውኖ እንግዶቻቸውን ካሰናበቱ በኋላ፣ ሙሽሮች አጃቢዎቻቸውን አስከትለው «ሀይሎጋ» እየተዘፈነላቸው መኖሪያ ቤታቸው ሲደርሱ የተደረገላቸው አቀባበልና የራት ግብዣም «ጉድ» የተባለ ነበር። በባህላዊ ሰርዓቱ መሠረት የሰማይነህ ዘመዶች ተሰብስበው ለህይወት የዳቦ ስም ካወጡላት በኋላ ሙሽሮቹ ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡ።

ሙሽርነት በአንድ ቀን ብቻ መወሰኑ ህይወት አናደዳት። ያ ሁሉ ዝግጅት፣ ያ ሁሉ መኳኳል፣ ያ ሁሉ ጥድፊያና ትርምስ ለዚችው ለአንድ ቀን እምታያ ብቻ መሆኑ አንዳች የስሜት መከፋት ፈጠረባት። ደምቃና ተውባ፣ በዚያ ሁሉ ህዝብ ታጅባ የዋለችበትን ቬሎ ማውለቁ አዛዘናት። ባልታወቀ ምክንያት ሆዷን ባር - ባር አላት። «አይዞሽ ሙሽሪት አይበልሽ ከፋ፤ ሁሉም ያገባል በየወረፋ» ተብሎ የተዘፈነላት አዕምሮዋ ውስጥ አቃጨለባት። ከአክስቷ ቤት ወጥታ እምብዛም ከማታውቀው ሰው ጋር፣ በፍቅር ካልተላመደውችው ወንድ ጋር በትዳር የመኖሩ ሀሳብ እንደ ተራራ ከበዳት። ከቀኑ ትርምስ ሆታ ወጥታ መኝታ ቤቱን በብቸኝነት ስትጋፈጠው ጨነቃት። ሆኖም ብዙ ሰዎች «ዕድለኛ ነሽ» እያሉ ያሚሙቋትንና የገባችበትን ሀብት እያሰበች ለመፅናናት ሞከረች።

ሰማይነህ ደግሞ በተገላቢጦሽ በሙሽርነት ታፍኖ መዋሉ ሰልችቶት፤ የበዓሉ ፍጻሜ ርቆበት ነው የቆየው። በዚያ ላይ በዓሉ እንዳይበላሽበት በዝምታ አሳልፎት ነው እንጂ ብዙ የሚያናድዱ ነገሮች አጋጥመውታል። አሁን ኮቱንና የሙሽራ ጌጣጌጦቹን በፍጥነት አወላልቆ ከወረወረ በኋላ ቀን ሲከነክኑት የቆዩትን ነገሮች ማነሳሳት ጀመሩ።

«አለቀ.... ደቀቀ.... አዳሜ እርሙን ያውጣ» እያለ የመኝታ ክፍሉን ቆላልፎ በአሸናፊነት ስሜት ተንጎራደደ። የህይወትን ስሜት ለማጥናት የጎድን ቢመለከታትም እሷ ምንም አልተነፈሰችም።

«....ብዙዎቹ የማያፍሩ ደፋሮች ናቸው። የሠርግሽ ዕለት እንኳ ዓይናቸውን አይሰብሩም። ዝም ብለው ያፈጣሉ።»

ህይወት በመናደድ ፈንታ ሳቋ በመጣባት። ሰርግ ደግሶ በእጁ ከስገባኝ በኋላም ገና ይቀናል እንዴ? ለዚያውስ አሁን እዚህ ጫጉላ ቤት መደሰት እንጂ እንዲህ አይነቱን ነገር ምን አመጣው? እያለች ነበር በልቧ።

«ለመሆኑ ያ ከጭፈራ መሀከል ወጥቶ ግንጮችሽን ግጥም አድርጎ የሳመሽ ማነው እሱ?!»

«የትኛው ነው እሱ?..... ትርምስ ስለ ነበር ብዙውን ነገር ልብ አላልኩትም እኮ»

‹ያ ቆጃ ጃኬት የለበሰ፣ ሰውነቱ የደነደነ ጎረምሳ ቢጤ.....»

«ውይ!..... ዘሪሁንን ነው እንዴ? የአጎቴ ልጅ እኮ ነው» ብላ ሳቀች።

«አያስቅም....» አላትና ተኮሳትሮ ጋጠወጥ ጎረምሳ ነው። ሠርግ ላይ ሳይሆን የዳንስ ክለብ ውስጥ ያለ ነው የመሠለው። በዚያ ኩበት በመሰለት ከንፈሩ የሙሽርነት ጉንጮችሽን ሲስምሽ በጣም ነው ያናደደኝ»

«እሱ እኮ ግን የዝምድናውን ነው.... የደስታውን መግለፁ ነው።»

«እነዚያ በቡድን ሆነ አንቺን ብቻ እያወደሱ ሲዘፍኑ የነበሩብትስ ምንድን ናቸው?»

«የሰፈሬ ልጆች ናቸው።.... በጣም ነው ስርጉን ያደመቁት»

«ከመሀከላቸው አንዱ ግን ልቡ ጨዋታው ላይ አልነበረም። ተጀምሮ እስኪጨረስ አንቺን እየሰርቀ ሲመለከትሽ ነበር። አስተያየቱ እስካሁን ይታየኛል።

«እኔ እንጃ እንግዲህ»

«አቡበከርና ይትባረክ ደግሞ እዚያ እናትሽ ቤት የለመዱትን ማፍጠጥ እዚህም ሠርግ ላይ ሙከራ አድርገው ነበር። ለመሆኑ ሲሰናበቱሽ በጆሮ ቱስ ያሉሽ ምንድነው?»

«ምንም..... ያው ‹እንኳን ደስ ያለሽ› ነው ያሉኝ።» እዚህ ላይ ስትመልስ ደንገጥ ብላ ነበር። ውሸቷን ነው። አቡበከር የሚሰናበታት መስሎ በጆሮዋ «አመለጥሽኝ አይደል?» ነበር ያላት። ይህን መናገሩ የሰማይነህን ቅናት ስለሚያብስበት የግዷን መዋሸት ነበረባት።

«አቡበከር እንኳንስ የለየለት ሸርሙጣ ነው። ይትባረክ ሚስቱን ጥሎ ከእሱ ጋር እየዞረ መሸርሞጡ ነው የሚገርመኝ።.....ለማንኛውም ዛሬ እርማቸውን ያወጡ፤ እናትሽ ቤት ሄደው ባዶ ባንኮኒ ላይ ያፍጥጡ» በማለት አጥላላባት።

ህይወት አንገቷን ደፍታ ሁሉንም በዝምታ ተቀበለች። ቀናተኛነቱን አውቃ የገባችበት ጉዳይ ቢሆንም በሠርጉ ዕለት ደስታውን ትቶ እንዲህ ይከታተለኛል የሚል ግምት አልነበራትም። ጫጉላ ቤት ውስጥ ይነዘንዘኛል ብላም አላሰበችም።

«ኮክቴል ላይ ኬክ ከቆረስን በኋላ ደረጃውን ስንወርድ ክንድሽን ደገፍ ያደረገሽ ሰውዬ ትዝ ይልሻል?»

«ሁኔታውን አስታውሳለሁ። የደረጃው ምንጣፍ ጫማዬን ጎትቶ ሲያስቀረኝ አንድ ሰው ክንዴን ደገፍ አድርጎኛል። ማን ደንደሆነ ግን ልብ አላልኩትም።»

«ሙሉ ጥቁር ሱፍ ከነከረቫቱ ግጥም ያደረገ አንድ እንጫጭባ ነገር ነው። የእሱም አስተያየት ደስ አለለኝም። ክድንሽንም ጠበቅ አድርጎ ሳይዝሽ የቀረ አይመስለኝም።»

«ዘመዴ ይሆናል እባክህ.....»

«አሄሄሄ!.....የዘመድና የባዕድን አመለካከት እኔ መች አጣሁት»

በዚህ አርዕስት ዙሪያ በተናገረ ቁጥር ቅናቱ ይበልጥ እያገረሸበት፣ ሰውነቱን እየለዋወጠውና እያስቆጣው ሲሄድ ይታይ ነበር። ይህወትም በበኩሏ የዛሬን ብቻ ሳይሆን የዘለቄታዋን እያሰበች

መጨነቋ አልቀረም። ይሄ አክስቷ እንዳለቻት የፍቅር ቅናት ሳይሆን የበሽታ ቅናት መሆን አለበት ብላ አሰበች።

«ዘመዶችሽን ተሰናብተሽ ስትወጪ ደግሞ አንገትሽን እቅፍ አድርጎ ከሴቶቹ እኩል ሰቅሰቅ የነበረው ማነው እሱ?»

«ዘመዴ ነዋ!..... ስታስበው ሌላ ማንደፍሮ እንደዚያ ያደርጋል?!» አለችው በተሰላቸው ድምጽ።

«ታዲያ ዘመድሽ ከሆነ ስታገቢለት ደስ ይለዋል እንጂ ምናባቱ ያስለቅሰዋል?!.... ለማንኛውም ዘመዶችሽን በሙሉ ወደ ፊት ስላማውቃቸው ችግር የለውም።»

ብር አምባር ጨፍረው ውስኪ ለመሸለም የሚጠባበቁ የአካባቢ ጎረምሶች በሩን ባያንኳኩበት ኖሮ እንዲሁ ከነሙሽራ ልብሷ ቁጭ አድርጎ ሲነዘንዛት ሲያድር ነበር።

# ክፍል ሶስት

ህይወት ልብሷን ስታወላልቅ ሰማይነህ ወበቷን በማድነቅ ምራቁን አሁንም አሁንም ይውጥ ጀመር። ይህች የተስተካከለ ቁመና ከተሚላ ውበት ጋር የያዘች ወጣት እንዲህ የእሱ ብቻ የግል ሚስቱ መሆኗን እስኪጠራጠር ድረስ በውበቷ ሰክሮ ፈዝዞ ተመለከታት። የገጿን ውበት የሚያጎሉት ትላልቅ ዓይኖች አገላለጥና አከዳደን ልቡን ፍቅርና ቅናት እሷነቷን አግንኖበት እንደማምለክ ቃጣው። አሁን የእሱ መሆኗ ቢያስደስተውና ቢያኮራውም በማንኛውም ሰዓት ከእጁ የምታመልጥ ወይንም የምትጠፋበት ወርቅ አድርጎ ሳሳላት። ይህችን መሳይ ቆንጆ ከምቀኞችና ከክፉዎች እንዲጠብቅላት ፈታሪውን በልቡ ለመነ።

ዋናው ሙብራት ጠፍቶ የራስጌው ባለ ጌጥ ሙብራት በርቷል። ህይወት በውስጥ ልብስና በውስጥ ሱሪ ብቻ ሆኖ እንዲህ ደብዘዝ ባለው ብርሀን ስትታይ በምሽት ጨረቃ የደመቀች ስዕል ትመስላለች። መኝታው ውስጥ ሳትገባ ሰውነቷን ዘረጋት ከላይ ተጋደመች። ሰማይነህም ጫማና ሱሪውን አወላልቆ ወደ ቤተ መቅደስ እንደሚገባ ፀሎተኛ በዝግታ እየተሳበ በአምልኮት አይነት ቀረባት።

«ህይወትዬ..... በጣም እወድሻለሁ። ይህ ውብ ሰውነትሽ ምንጊዜም የኔ ብቻ ሆኖ እንዲኖር እፈልጋለሁ። ምንም አይነት ሀይል አንቺን ከእኔ ሊቀማ አይችልም» አለና ግንባሯ ላይ ላማት።

«አመሰግናለሁ» እንደ ማለት ፈገግ ብላ የጥርሷን ብርሀን አሳየችው።

«.....ስለምወድሽ ደግሞ እቀናለሁ። ሰዎች እንዲያዩሽ አልፈቅድልሽም። ዓይን እንዳትገቢብኝ እፈራለሁ።»

«እሺ» አለችው ፈገግታዋን ሳትቀንስ ዓይኖቿን እያስለመለመች።

«ቆንጆ ስለሆንሽ ሁሉም ያይሻል፤ ይፈልግሻል። ይህ ደግሞ እኔን የሚያስቀና ጉዳይ ስለሆነ መጠንቀቅ ይኖርብሻል።»

እዚህ ላይ ግልጽ ሆኖ የውስጡን መናገሩ ህይወትን ደስ ያሰኛት። ሆኖም የሚያስቀኑትን ነገሮች መከላከያው መንገድ ግልፅ ሆኖ አልታያትም። ሰዎች እንዳይመለከቷት እንደ አረብ ሴቶች ፊቷን ሸፍና መሄድ ይኖርባት ይሆን? ወይንስ ማድ ቤት ውስጥ ተደብቃ ከሰው ርቃ ለመኖር ትገደድ ይሆን?..... ‹ፍቅር ጅል ያደርጋል፤ ወይንም ልጅ ያደርጋል› እንደሚባለው የሰማይነህ አቀራረብ የተጃጃለ ነበር።

ፀጉሩ ገባ - ገባ ያለ፣ በዕድሜው የበሰለና ሰውነቱ የጠነከረ ሙሉ ሰው እንዲህ በተጃጃለ መልክ መቅረቡ ህይወትን አስገርሟታል። ከእንግዲህ የኑሮ ጓደኛዋ መሆኑን በመቀበል የዕድሜያቸውን መራራቅ ለማጥበብና በጨዋታ ለመቀራረብ ጀምራለች። ሆኖም አንዳንድ «አንቱታውን» ትታ አንተ ማለት ጀምራለች። ሆኖም አንዳንድ አቀራረብና ሁኔታው አሁንም ግራ ያጋባታል።

«እግዜር የሰጠኝን ቁንጅና እኔ ምን ላድርገው ታዲያ? ሰዎችን ‹አትዩኝ› ማለት ይቻላል» አለች እየሳቀች።

«አንደኛ ነገር ይህንን ሳቅሽን ማሰወገድ አለብሽ። የዘመኑ ወንዶች ባለጌዎች ናቸው። ጥርስሽን ካሳየሻቸው ስተት ብለው ቤትሽ ድረስ ይመጡልሻል። ሁለተኛ ነገር ሌሎች እንዲያዩሽ ሆነሽ መቅረብ የለብሽም፤ ልታይ - ልታይ ማለት የለብሽም። ወጣት ብትሆኚም ባለ ትዳር መሆንሽን መርሳት የለብሽም። አሁን ባል አግብተሻል በቃ! ሰዎች እንዲያዩሽ ሆነሽ የምትቀርቢበት ምክንያት የለም።»

እስከ ሰርጓ ዕለት ድረስ ሲያዩዋትና ሲፈልጓት የነበሩ ወይንም ሰማይነህ የሚጠረጥራቸው ሁሉ ድንገት በሀሳቡ ውስጥ ተሰልፈው ብቅ ብለው የፍቅር ስሜቱን ወደ ቁጣ ለወጡበት።

«ከንግዲህ ልጅነት የለም። ይገባሻል ህይወት?!»

«ገባኝ፤ እያዳመጥኩህ ነው» አለችው ድንገት የስሜቷ መለዋወጥ አስደንግጧት «አሁን እንዲህ አይነቱን ጨዋታ እንተወው። የፍቅር ሰዓት ነው፤ የሠርጋችን የአለማችን፣ የደስታችን ቀን ነው። እንደሰት እባክህ።»

«ለፍቅሬ ቀናተኛ ስለሆንኩ ነው። እንዳሰለቸሁሽ ይገባኛል» ብሎ አንገቷን እየሳመ ወገቧን ዳሌዋን ሲደባብስ አንድ ቅናታዊ ስሜት እንደ ገና አገረሸበት።

ይህንን ወገብና ዳሌ እስከ ዛሬ ማንም እንደዚህ ነካክቶት አያውቅም ይሆን? አንገቱን፣ ጉንጮቿን፣ ግንባሯን፣ ከንፈሯን፣ እንዲህ ተጠግቶ የነካካና የሳማት የለም ይሆን?..... ዓይኖቹ ቀስ ብለው ወደ ጭኖቿ ወረዱ። የቅናት መንፈሱም ዓይነኞቹን ተከሎ ወረደ። በጭኖቿ በኩል የሚወስዱትን መንገዶች እየተከተለ እርግጠኛ ነኝ፤ ማንም በዚህ መንገድ አልሄደም..... ማንም ይህንን ለግላጋ ገላ አልዳበሰም..... ማንም ጭኖቿን ከማየትና ከመጎምጀት አልፎ ለማግኘት አልደረሰም እያለ በሀሳብ ዋተተ።

ህይወት በበኩሏ አንድ የሚያስጨንቅ ስሜት ሰፍሮባት ነበር። ሰውነቷ በወሲብ ስሜት በመነሳሳትና በመሟሟቅ ፈንታ በፍርሀት እየራደ ሲሄድ ይታወቃታል። «እሱ.... ምን ይል ይሆን?.... ምን ይሰማው ይሆን?.... ቅናቱ የተመሠረተው በወደፊት ላይ ነው ወይንስ ያለፈውም ያብሰከስከው ይሆን? እያለች በሀሳብ ተውጣ ስሜቱን ለማጥናት በሚሞክር አስተያየት ዓይኖቿን አስለምልማ ተመለከተችው። ሰማይነህ ጭንቀቷን አልተረዳላትም። አስተያይቷን በፍቅር ግብዣ ወስዶት የሰውነቱ ሙቀት እየጨመረና ጅማቶቹ እየተኮማተሩ በስሜት ተጠጋት።

ሁለቱም በተለያዩ የስሜት አቅጣጫ እንደ ተመሰጡ ተያይዘው አንሶላ ውስጥ ገቡ።

«ድሮውንም..... የሽርሙጣ ልጅ ሽርሙታ ነው» አለ ሰማይነህ፣ አልጋው ላይ እንደ ተዘረረ ትንፋሹን ለመሰብሰብ እየሞከረ።

ህይወት አስቀድማ እንደፈራችው ድንግልናዋን ያለማግኘቱ ሰማይነህ አናደደው። ትንፋሹን ሰብስቦ አረፍ እስኪል ድረስ እንኳ ቁጣውን መቆጣጠር አልቻለም። ሰውነቱ በአንዳፍታ ተለዋውጦ በንዴት እየተንጨረጨረ ህይወት ላይ ጮኸባት። ተኛችበት ቦታ እነቃት የሚል ስሜት ከውስጡ ታገለው። ቀናተኛ ስሜቱ ሺህ ሰይጣኖች አስከትሎ ይፈታተነው ጀመር።

«የእኛ ጨዋ! የእኛ ልጃገረድ! ጉድሽ ታየ ዛሬ። አሁኑኑ ስልክ ደውዬ ለእናትሽ ጉድሽን እነግራታለሁ። ወራዶች!»

የህይወት የልመና አስተያየት የሰማይነህን ልብ ሊያራራው አልቻለም። የውስጥ ሱሪና ሸሚዙን አጠላልቆ ከአልጋው ላይ ወርዶ ዙሪያውን እየተንጎራደደ ገረመማት። ምራቁን ፊቷ ላይ እንትፍ ሊልባት ሲል አንሶላውን ተሸፋፍና አመለጠችው።

«ትስቲ ቀና በይ አንቺ ሀፍረተ ቢስ!.... ደሞ በጨዋ ደንብ ስትሞሸሪ አታፍሪም?! አንሶላውን ገፈፋት።

«ህይወት በልቧ.... ይህን ያክል አስቆጥቶ ያሳብዳል እንዴ? እያለች እንደ መሳቅ ቢከጅላትም እዚያው አንቆ እንዳይገላት በመፍራት ሳቋን ውጣ ጭጭ አለች። የወትሮው ፈገግታው ጠፍቶ በጭንቀት ዓይኖቸዋን ስታንከባልል የሚያሳዝን ውበት በገፅዋ ላይ የነበባል። የውበቷን ግራም የሆኑት ዓይኖቿ ብቻቸውን ሰማይነህን ይታገሉት ጀመር።

«....ደሞ አፍጥጠሽ ታይኛለሽ እንዴ?!......አይን አውጣ! ይህን ቅንዝረኛ አይንሽን ጎልጉዬ እንዳላወጣልሽ!»

«እንዴዬ!..... ይህን ያክ ምን አጠፋሁ አለች ህይወት የልመና ይሁን የቁጣ መለየት በሚያስቸግር ድምፅ።

«ገና ጥፋትሽን ትጠይቂያለሽ እንዴ?!.....‹የሌባ አይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ› ሆነ እኮ ነገሩ»

«ማለቴ.....»

«ዝም በይ!.....አንቺን ለማግባት ምን.... ያክል ገንዘብ እንዳወጣሁ ታውቂያለሽን?.....ለጥሎሽ የላኩልሽን ስጦታዎች ሳይጨምር ለሠርጉ ብቻ ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር ወጪ አድርጌያለሁ።.... ይሄ ሁሉ ታዲያ ለእንዳንቺ አይነቷ ክብረቢስ ይገባታል?! ንገሪኝ እስቲ!....»

«እኔ ታዲያ ምን ላድርግ?..... ይህን ሁሉ ገንዘብ እንድታወጣ አልጠየቅሁህም።.....»

«ክብረንጽህናሽን የትም ሜዳ ያስወሰድሽ መሆንሽን ቀድመሽ መናገር ነበረብሽ።»

«አንተስ መጀመሪያ መቼ ጠየቅከኝ....»

«ምን መጠየቅ ያስፈልግሻል?!.....ብልግናሽን፣ ለወግ ለማዕረግ የማትበቂ መሆንሽን አስቀድመሽ መናገር ያለብሽ አንቺው ራስሽ ነሽ።

«እኔማ....ድሮ የሆነ ነገር ስለሆነ አንተን ይህንን ያክል የሚያናድድህ አልመሰለኝም ነበር።»

በጠላትነትና በምቀኝነት የሚፈራቸውና የሚጠረጥራቸው ሰዎች ላንዳፍራ በሀሳቡ ብቅ በለው ታዩት። አቡበከርና ይትባረክ የግንባር ቀደሙን መስመር ይዘው እየተጀነኑ መጡበት። ህይወት በዚህ መሐል ሻሞ የተባለች ኳስ ሆነችበት። ድንግሏን የወሰደው ወንድ ቤቱ ተኝቶ በዛሬው ሠርግና «ብር አምባር» ሲሲቅ አቁነጠነጠው፤ የቅናቱ ዛሩ ቀንዱን አሹሎ «አዶከበሬውን» እየመታ እረፍት ነሳው።

«ለመሆኑ ማነው?....እኔ ከማውቃቸው ሰዎች መሀል ነው?... እዚያ እናትሽ ውስኪ ቤት ከሚመጡት ውስጥ ነው?.... እኮ ማነው?!....» አላት እያንቀጠቀጠው።

«አንተ የምታውቀው አይደለም..... አትጨህ በናትህ ሰማይነህ። ድምፅህ እኮ ውጭ ድረስ ይሰማል። ረጋ ብለህ ካዳመጥከኝ እኔ ሁሉንም እነግርሀለሁ። የምደብቅህ ነገር የለኝም፤ ያለፈ ታሪክ ነው።»

«እኮ ተናገሪ…. ማነው?!»

«ሄኖክ የሚባል የልጅነት ፍቅረኛዬ…. የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ነበር፡፡»

ሰማይነህ ይህን….ስም ባያውቀውም የሚያውቀው ሆኖ ተቀረፀበት፡፡ ከዚች ሰዓት ጀምሮ እጅግ በጣም የሚጠላው ስም ሆነ፡፡

«ሂኖክ?…..ሄኖክ!…..ሥርግሽ ላይ በሰው መሀል አንገትሽ ላይ ጥምጥም ብሎ የሳመሽ ያ ዓይን አውጣ ጎረምሳ ነው?!»

«ኧረ አደለም፡፡ እሱማ ዘመዴ ነው አላልኩህም?!»

«…..ወይዝ ኮክቴል ላይ ዘመዶችሽን ስትሰናበቺ ስቅስቅ ብሎ ያለቀሰው ጎረምሳ?….»

«እሱም ዘመዴ ነው ብዬህ….›.

«…..እኮ የትኛው ነው?!»

«አሁን እዚህ የለም፡፡ አሜሪካን ሀገር ከሄደ ሁለት አመት አለፈው፡፡»

ይህን ሲሰማ ሰማይነህ ትንሽ መለስ አለለት፡፡ ጠላቱ አጠገቡ ባለ መኖሩ ተፅናና፡፡ ሆኖም በማያውቀው ወጣት ላይ ቂም መያዙና ጥርሱን መንከሱ አልቀረም፡፡

«ቀደም ብለሽ ነዋ ሁሉንም ነገር የጀመርሽው?!» እያለ በሀሳቡ ሄኖክና ህይወት ተቃቅፈው ተኝተው ፍቅር ሲሰሩ ይታዩት ጀመር፡፡ በቅናት ተብሰከሰከ፡፡ ሄኖክ የህይወትን ድንግልና ለመውሰድ ሲታገል ታየው፤ ጡቶቿን እያሻሸ፤ ከንፈሯን እየሳመ፣ ዳሌዋን እየደባበሰ በጭኖቿ በኩል የሚወስደውን ጠባብ መንገድ ይዞ ሱጓዝ ታየው፡፡ ይሄንን ለግላጋ ሰውነት የገሰሰውን «የተረገመ» ወጣት አሁንም በልቡ ረገመው፡፡ እሱ በገንዘቡ ኃይል ብቻውን የገዛትን ቆንጆ ቀድሞ የተጫረተው በመኖሩ ተናደደ፡፡

«እንዴት ነው ያደረገሽ?….እስቲ ተናገሪ! መቸም አታፍሪ» አላት ድምፁ በንዴት እየተንቀጠቀጠ፡፡

እንዴት ነበር?…..ህይወት በጭንቀትዋ ውስጥ ሄኖክን አስታወሰችው፡፡ ለአጭር ጊዜ በሀሳብዋ መስመር ላይ አለፈ፡፡ የዛሬ አራት አመት ገደማ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሆነው በፍቅር ያበዱበት ጊዜ ነበር፡፡ ሄኖክ ቀጭን መልከ መልካም ወጣት ሲሆን፣ ህይወትም ወንዶች ዓይን ውስጥ የምትገባበት አፍላ የቁንጅና ጊዜዋ ነበር፡፡ ያችኒ ትኩስ ፅጌረዳ አበባ ለማየት፣ ለማሽተትና ለመቅጠፍ የሚጓጉ በርካታ ተማሪዎች ቢሆኑም ለማግኘት የታደለው ግን ሄኖክ ብቻ ነበር፡፡ ጠዋት መንገድ ላይ ተጠባብቀው ት/ቤት አብረው ይሄዳሉ፣ አንድ ክፍል ውስጥ ጎን ለጎን አብረው ይቀመጣሉ፣ አብረው ያጠናሉ፣ ወደ የቤታቸውም ሲመለሱ መጀመሪያ ህይወትን መኖሪያ ቤቷ በር ላይ ሳያደርስ ሄኖክ ወደ ሠፈሩ አይሄድም፡፡ በዚህ አያያዝ በሌሎች ወጥመድ ውስጥ ለመግባት ሁኔታው አመቺ አልነበረም፡፡ ፍቅራቸው ከልብ የመነጨ፣ ትኩሳቱ ያልበረደ በጥቅም ያልተጋረደ ስለ ነበር የሁለቱም ዓይን ወደ ሌላ አያይም፤ ልባቸው አንዳቸው ሌላቸውን እያሰቡ በሀሳብ ሲናጡና በሰመመን ሲዋኙቁ ትምህርታቸው የመከታተሉ ነገር ጭራሹን ተረሳ፡፡ ለወጉ ክፍል ውስጥ ገብተው ይወጣሉ እንጂ አስተማሪውን አይከታተሉትም፤ ለወጉ መፅሐፍ ይሸከማሉ እንጂ አያነቡትም፤ ከጥናት ጋር ተረሳስተዋል፡፡ ሲበሉም፣ ሲጠጡም፣ ሲተኙም እረፍት የሚነሳ፣ የሚያቃጥል አፍላ ፍቅር ብቻ ሰውነታቸውን ይወርረዋል፡፡ በዚህ መንገድ አስራ ሁለተኛ ክፍልን አጠናቅቀው የኮሌጅን በር ለማየት ዕድል ሳያገኙ ቀሩ፡፡

በትምህርት ቤት ዘመናቸው ህይወትና ሄኖክ ተቃቅፎ ከመሽኛኘት፣ ተስፋፍቶ ከመተያየትና የልደት ካርድ ስጦታ ከመለዋወጥ ባሻገር አልፈው አልሄዱም ነበር። ግፋ ቢል በተወሰኑ አጋጣሚዎች ቤታቸው ሳይገቡ ትንሽ ጨለምለም ያለ እንደሆን ከንፈር ለከንፈር ተሳስመው ይለያያሉ። ለዚያውም አዩኛ አላዩኝ ብለው በፍርሃት የሚያደርጉት በመሆኑ በጥልቀት የመሳሳም ሳይሆን መነካካት ያህል ነበር። የወጣትነት ዕምቅ ፍቅራቸው ፈንድቶ አካላዊ ርካታን የጠየቀው ሁለቱም ስራ ፈትተው ቤት መዋል ከጀመሩ በኋላ ነበር።

አንድ ቅዳሜ ቀን ሄኖክ ኮንትራት ይዞ ከይወት ጋር ከከተማው ወጣ ብሎ ወደሚገኝ መናፈሻ ሄዱ። ለወትሮው ከተማውን በእግራቸው ዞረው፤ ካፌቴርያ ውስጥ ረዥም ሰአት አሳልፈው፣ ሻይና ኬክ ተገባብዘው ስለሚለያዩ ይህ ጉዞ ለህይወት እንግዳ ሆኖባት ነበር።

«ሄንዬ....ዛሬ ነው የምንሄደው?» ስትል ጣቶቿን ከጣቶቹ ጋር አገጣጥማ እየተላፋች ጠየቀችው።

«ከወደመናፈሻው ነዋ። አንዳንድ ቀን እንኳ ከከተማው ወጣ እንበል እንጂ። ዘመዶቼ ከአሜሪካን ትንሽ ገንዘብ ስለላኩልኝ እንድንደሰትበት ፈለግኩ።.....ቅር አለሽ እንዴ ህይወትዬ?»

«በፍፁም። ከአንተ ጋር እስካለሁ ድረስ ምንም ነገር ቅር አይለኝም»

ሄኖክ በልቡ ላሰበው ጉዳይ አረጓዴ መብራት እንዳሳየችው ቆጠረው። መናፈሻው ውስጥ ወደሚገኙት የመኝታ ክፍሎች ሲያመሩ የሁለቱም ልብ ድቤ መምታት ጀመረ። መነጋገር እንደተከለከሉ ሁሉ ሁለቱም በዝምታ ተውጠው ክንድ ለክንድ እንደተያያዙ አስተናጋጅ ወደ ከፈተላቸው ክፍል ገቡ። ክፍሉን ከውስጥ ከቆለፉ በኋላ የተጫጫናቸው የዝምታ አባዜ ለቅቋቸው ትንፋሽ መለዋወጥ ጀመሩ።

«አንተ ባለጌ.... ይህንን ቦታ እንዴት አወቅከው?» አለችው ህይወት ፈገግ ብላ ዓይኖቿን እያስለመለመች።

«አንድ ጓደኛዬ ነው የጠቆመኝ።....ስለዚህ ጉዳይ ሳስብ ምቹ ቦታ መሆኑን ነገረኝ።»

«ማነው እሱ?....እኔ አውቀዋለሁ?»

«አታውቂውም።»

«.....ደግሞ ደፋር ነህ። እኔ ሳታማክረኝ።.....»

«አሁንም ከአንቺ ፍላጎት ውጭ የሚደረግ ነገር የለም ህይወትዬ» ብዬ ከንፈሯ ላይ ሳማት።

እሷም አለቀቀችውም። የታመቀ ስሜቷን ዘርግፋ አውልቃ ከፍነሯን ገመጠችው። በክንዶቻቸው ተቃቅፈው ከንፈር ለከንፈር እንደተጣበቁ ሳያስቡት አልጋው ላይ ወደቁ። ልብሶቻቸውን እንዴት እንዳወለቁ አያውቁትም። መላዕክቶቻቸው የፍቅር ዜማ እያንቆረቆሩላቸው፣ ወፎች እየዘመሩላቸው የገነት በር ወለል ብሎ ተከፍቶላቸው፣ በፍቅር ሰረገላ ጭልጥ ብለው ሄደው ሲናፍቁት የቆዩትን ፍትወታዊ የደስታ ሲቃ አገኙ። ህይወት ድንግልናዋ ሲገሰስ ደቂቃ ለማይሞላ ጊዜ ያህል የህመም ስሜት ቢሰማትም፣ በዚያው ወቅት ከሄኖክ ጋር ያገኘችው ደስታ ለዘለአለሙ ከአዕምሮዋ የማይጠፋ ሆኖአል።

«ኤፍፍ..... እንዴት ደስ ይል ነበር አለች በልቧ፤ ከሀሳቧ እንደመመለስ ብላ።

«እንዴት እንደ ነእብር ተናገሪ እንጂ!.... ያኔ ስታደርጊው ያላፈርሽ አሁን ምን ያሳፍርሻል?!» ሰማይነህ እንዳፈጠጠ፣ መልሱና በጉጉት እየጠበቀ።

«በቃ.... ወጣቶች ስለነበርን አንድ ቀን ከሄኖክ ጋር ተሳሳትን አለችው።

«ሄኖክ አባቱ ይጥፉ!» አለና ጥርሱን አንቀጫቅጮ

«አንድ ቀን ብቻ ነው?....አላት»

«ምኑ?....» አለችው ግራ ተጋብታ።

«እኔን ምን ትጠይቂኛለሽ አንቺው መልስ ስጪኝ እንጂ!.....» እያለ በደመነፍስ የመኝታ ቤቱን ስልክ አነሳ።

ህይወት በልቧ ምን ያደርጋል፤ ሄኖክን ምን ያክል እንደምትወደውና ከእሱ ጋር የሳለፍኳቸው የፍቅር ቀኖች ምን ያህል እንዳስደሰቱኝ ብነግርህ አንተ በቅናት ታብዳለህ እያለች ነበር።

ሰማይነህ ስልኩን ያነሳው ወ/ሮ ስራሽ ቤት ሊደውል ቢሆንም ስለተናደደ ቁጥሩ ጠፍቶበት እያሰበ».... ከአቡበከርና ከይትባረክ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት አላረግሽም?!.... እውነቱን ተናገሪ» አላት በድንገት።

«ምንም.....» አለች አንገቷን አዝምማ።

«እንደሚፈልጉሽማ የታወቀ ነበር....»

«እኔ እንጃ እንግዲህ.....ያው ቤታችን መጥተው ተጫውተው፣ ተሳስቀው ይሄዳሉ እንጂ ሌላ ነገር.....»

«የሚያሳስቁሽ ለምን ይመስልሻል?!.....»

ህይወት ተናደደች። ‹ቆንጆ ስለሆንኩኝ ፈልገውኝ ይሆናል።.... አንተ እንደፈልግኸኝ ሁሉ እነሱም ቢፈልጉኝ ምን ያስደንቃል!› ልትለው ፈልጋ ስሜቷን አፍና ተወችው። የሰማይነህ ሁኔታ የሚያስፈራ በመሆኑ ራሷን መቆጣጠር ነበረባት።

ሰማይነህ የወ/ሮ ስራሽን ስልክ ቁጥር አስታውሶ ደወለ። ከሰርጉ መልስ እሷም መኖሪያ ቤቷ ውስጥ ከዘመዶቿ ጋር እየተጫወተች ነበር።

ስልኩን አንስታ «ሀሎ....» ከማለቷ የሰማይነህ ድምፅ እንደነጎድጓድ አምባረቀባት።

«ጉድ ሰራችሁኝ አይደል!.... ቀለዳችሁብኝ።»

«ማነህ....ሰማይነህ?.... ምነው ምንሆንክ?.... እንዴ ቆይ እስቲ። ድምጽህ አይሰማም። በምኝታ በቴ ስልክ ላነጋገርህ።»

አዝማሚያው ስላላማራት ለብቻዋ ማነጋገሩን መርጣ መኝታ ቤቷ ገባች።

«ሀሎ.... እሺ?.... ምን ችግር ገጠመህ?.....»

«ነገ ጠዋት የምስራች እንዲላክልሽ ትጠብቂያለሽ?!»

ነገሩ ቶሎ ገባት። ሆኖም ግን ከግምቷ ውጭ ስለ ነበረ ደነገጠች። «እንዴዬ.... ታዲያ ባህላችን አይደል እንዴ?»

«ባህሉማ... ክብሯን ጠብቃ በንፅህናዋ ለምትገኝ ልጃገረድ ነበር። ላንቺ ልጅ አይገባትም።

«እንዴት እንዴት?! የህወትን ክብር አላገኘሁም ነው እንዴ የምትለኝ? እኔ አላምንም።»

«የለ፤ ድርብ ድርብርብ ክብር ስላላት እኔ መገሰስ አቅቶኝ ነው።»

«አትቀልድ እንጂ ሰማይነህ.....»

«መቀለጃ ሆንኩ እንጂ እኔስ አልቀለድኩም።»

«ወይ ዕድሌ!.....መከራዬን አይቼ በጨዋ ደንብ ያሳደግኳት ልጄ እንዲህ ታዋርደኝ....»

«ለሠርጉ ምን ያህል ገንዘብ እንዳወጣሁ ታውቂያለሽ?!» አላት ድንገት ቁጣና ለቅሶ በተቀላቀለበት አነጋገር።

«አውቃለሁ ሰማይነህ አውቃለሁ» አለችው እሷም በማስተዛዘን ቅላፄ።

«ነገ ጠዋት በታክሲ አሳፍሬ እልክልሻለሁ»

ወ/ሮ ስራሽ ክው ብላ ቀረች። የሰማችውን ማመን አልቻለችም።

«.....ማንን?.....ምን?....»

«ይቺን ወራዳ ልጅሽን ውርደቷን እንደተናነበች እመልስልሻለሁ። ከእኔ ጋር ልትኖር አትችልም።»

«ተው እንጂ ሰማይነህ.... ቆይ እስቲ ረጋ በል የኔ ጌታ።»

«በፍፁም!.... ምንም ርጋታ አያስፈልግም....»

«አድምጠኝ እኮ።......ሰውስ ምን ይላል?!......ሀገር ድምሩ ‹ጉድ!› ሲል ይክረም እንዴ?.... የዛሬ ልጆች እንደሆነ ግድ የላቸው።

ውርደት እኮ የኔው የእህትህ ነው። ለኔም እዘንልኝ እንጂ የኔ ጌታ።

መለመኑ የባሰውን አቅበጠበጠው፤ አነጫነጨው።

«ለማንም ለምንም ሐዘኔታ የለኝም። እንዲያውም ይህን ሁሉ ገንዘቤን ገደል ስለጨመራችሁብኝ እፋረዳችኋለሁ።»

«እኔ ምናባቴን ላድርግ ሰማይነህ.....ተው እባክህ አንተም አትበሳጭ፤ ለእኔም እዘንልኝ። የኔና ያንተ ቤተሰባዊ ፍቅር እንዲህ በቀላሉ መናጋት የለበትም። ይቺን ሰሞን ብቻ በትዕግሥት አሳልፋት። እኔም ያዘጋጀሁትን መልስ በሰላም ላውጣው። ከዚያ በኋላ እንደሚሆን እናደርጋለን። ለእሷው ይብላልኝ እንጂ አንተ ሺህ ሴቶች አማርጠህ ማግባት ትችላለህ። የራሷን ዕድል ነው ያበላሸችው።

እዚህ ላይ ሰማይነህ ትንሽ መለስ አለ። «ትልቅነቱ» ስለነረተው ልቡ በኩራት ሞላ። በቋሚ የውስኪ ደንበኝነቱ ወ/ሮ ስራሽ ፀባዩን አውቃ አቀራረቡን ሳትችልበት አልቀረችም።

«ስንቶቹ ሴቶች ሲለምኑኝ.....ሲያስለምኑኝ አሻፈረ ብዬ እንደኮራሁባቸው ታውቂያለሽ»

«አውቃለሁ እንጂ በሚገባ።»

«ጨዋ አገኘሁ ብዬ ነበር አንቺ ቤት የገባሁት»

«ግድ የለህም በቃ። ይቺን ሰሞን ብቻ ታገስ፤ ለሰው ወሬ አትመች....አሁን እሷን አገናኘኝ።»

ህይወትን ገለማምጧት በመወርወር አይነት የስልኩን እጅታ ሰጣት።

«ሀሎ...» አለች ህይወት በቀዘቀዘ ድምፅ።

«ህይወቴ.....ምነው እባክሽ..... እንዲህ ጉድ ታደርጊኝ?! እንዲህ ታዋርጂኝ?! ስኮራብሽ.....ስመካብሽ ኖሬ ቃል አባይ ታደርጊኝ!......»

ህይወት መልስ መስጠት አልቻለችም። የአክስቷ አነጋገር ቢያሳዝናምት፣ ጉዳዩን ይህን ያህል ክብደት ሰጥታ ልታዝንበት አልፈለገችም። ለማንኛውም ዝምታን መረጠች።

«በይ አሁን ይቅርታ ጠይቂው። እግሩ ላይ ለጥ ብለሽ ወድቀሽ ይቅር በለኝ በይው....ካለበለዚያ ዕድልሽን አበላሽተሽ መቅረትሽ ነው.....እግዜር ያንን ሁሉ ሀብት አሳይቶ ሊነሳሽ ነው። ቶሎ ብለሽ ለምኚው....እግሩ ላይ ውደቂና ለምኚው ኋላ! የሚበጅሽን ብታውቂ ይሻልሻል።»

ህይወት የአዎንታም ሆነ የአሉታ ምልክት አሳይታ ስልኩን ዘጋችው። በሙሽርነትና በትዳር ዓለም ጣፋጭ ደስታ አግኝቼ እኖራለሁ የሚል ህልም ነበራት። ሆኖም ይህ ህልሟ ገና ከጅምሩ ደበዘዘባት። ከሰማይነህ ባትስማማ ተመልሳ የምትሄደው አክስቷ ቤት ነው። አክስቷ ግን የምትመክራትና የምትሰጣት ማስጠንቀቂያ ሆድ የሚያስብስ ነው። ልቧ ማመፅ ፈለገ። ‹እግሩ ላይ የምትወደቅበት ምንም ምክንያት የለም› አለች በሀሳቧ። ወጣትነቷ ለሀብት መስገድ አልፈቀደላትም። ‹ከነሀብቱ ገደል ሊገባ ይችላል› አለች እንደ ገና በሀሳቧ። ሌሎች የሚያንደቁት ውበትዋ ደግሞ ሞቅ ደመቅ ብሎ ለራስዋ ታያት። የውበት ሰይጣን ሔዋናዊ ኩራት ሊያሰፍርባት አኮበኮበ። አክስቷ ቤትም ሆነ ከዚያ ውጭ ውበቷን ያደነቁላትና የቋመጡላት ወንዶች ሁሉ በሀሳብዋ ውስጥ ብቅ ጥልቅ እያሉ ታዩዋት። ለአንድ አፍታ አዕምሮዋ ይህ ነው የማይባል ውዥንብር ውስጥ ገባ።

«ነገ በጠዋት ወፍ ሳይንጫጫ ጓዝሽን ጠቅልለሽ ህፍረትሽን እንደተናነብሽ ወደ እናትሽ ቤት ትመለሺያለሽ» አላት ሰማይነህ፤ ከስልኩ በኋላ በይህወት ላይ ምንም አይነት ለውጥ ያለማየቱ አናድዶት።

«እሺ.....» አለችው ህይወትም ነገሩን ሳታመዛዝን፣ እንዲያው አፏ እንዳመጣላት።

ይኸኛው መልሷ ደግሞ ሰማይነህን ይበልጥ አናደደው እንደ እናቷ ትለምነኛለች ብሎ ሲጠብቅ የኩራት መልስ መስጠት አንድ የተመካችበት ነገር ቢኖር ነው ወደሚል ጥርጣሬና ዕልህ ውስጥ ጨመረው። በልቧ ሌላ ልታገባው ያሰበችው ወንድ አለ ማለት ነው በሚል ግምት መከረኛ ልቡ በቅናት መኮማተሩን ጀመረ።

«......ትሄጃለሽ?!.....መሄድ ትፈልጊያለሽ?!..... ለመሆኑ የት ነው የምትሄጂው?.....እናትሽ ቤት ነው ወይንስ ሌላ ባል አዘጋጅተሻል?!» እያለ ጮኸባት።

«እኔ እንጃ....» አለችው ስሜት በሌለው ድምፅ።

«ያዘጋጀሽውን ተናገሪ እንጂ!»

«ምንም»

«ደሞ የትም አትሄጂያትም!»

«እሺ።»

እሱ በንዴትና በቅናት ተብከንክኖ ሲጠይቃት የእሷ መልስ የመሰላቸትና የመፍዘዝ ዓይነት ሆነበት። ‹ይህንን ኩራቷን ከአፈር ደባልቄ ልክ አገባታለሁ። ገንዘቤን አስከስክሳኝ ቀልዳብኝ ለመሄድ አስባ ከሆነ ሞኟን ትፈልግ የሚል ዕልህ ተናነቀው።

ለነገሩ ወ/ሮ ስራሽንም ያስፈራራት እንዲያ መለመን ፈልጎ ነው እንጂ ያንን ያህል ገንዘብ ካወጣ በኋላ ህይወትን እንደማያባርራት ልቡ ያውቀዋል። ፈልጊዎቿንና ተቀናቃኞቹን ላለማስደስት

እንዳደረገም ቢሆን ቤቱ ቢያስቀምጣት ይመርጣል። የአሁኑን ግዴለሽነቷንና ኩራቷን ሲመለከት ደግሞ ለግርድናም መሆኗን በመገምት ሌላ ዕልህ ውስጥ ገብቷል።

ይህ ፀባይዋ ያለ አባት በማደጓ ምክንያት የተከተ ይሆናል የሚል ዕምነት አድሮበታል። ወ/ሮ ስራሽ ለህይወት አክስቷ መሆኗን አያውቅም። በመሸታ ቤት ስራዋ ምክንያት በአንድ ወቅት በውሽምነት ከተያዘ ወንድ ወይንም በሌላ አጋጣሚ የወለደቻት ልጇ አድርጎ ነው የወሰዳት። ወ/ሮ ስራሽም ያለ አባት ያሳደገቻት ልጇ እንደሆነች አድርጋ ነው የምታወራው። ለበርካታ አመታት ቤተኛ የሆኑ የቅርብ ዘመዶቿ ካልሆኑ በስተቀር የህይወት እናትና አባት በልጅነቷ መሞታቸውን የሚያውቅ የለም። ብዙም የውጭ ሰዎች ግምት ወ/ሮ ስራሽ የህይወት ወላጅ እናት ናት። ለሰማይነህ የዳረችለትም እንደወለደቻት ልጇ አድርጋ ነው።

‹.....አስፈላጊ ከሆነም ልጅነቷን እስክጨርስ ድረስ በእግር ብረት ጠፍሮ ቤት ውስጥ ማስቀመጥ ይቻላል› አለ ሰማይነህ በልቡ።

# ክፍል አራት

የገና ፆም ከመግባቱ በፊት መልሱና ቅልቅሉ በሁለቱም ቤት ተዘጋጅቶ የህይወትና የሰማይነህ ቤተ ዘመዶች ተቀላቀሉ። ሰማይነህ ቅሬታውን ከልቡ ያላስወገደ ቢሆንም በቅርብ ዘመዶቹና በወ/ሮ ስራሽም ጭምር ተመክሮ ባህላዊ የጋብቻ ወጎች ያለ ምንም ረብሻ በሰላም ለመከናወን በቅተዋል። ሌላው ቀርቶ በሠርጉ ማግስት ሚዜዎች በጥዋት ተነስተው እንደ ወጉ የምሥራች ለማድረስ ወ/ሮ ስራሽ ቤት ሄደዋል። በርግጥ ሚዜዎቹ መህረብ ይዘው የዶሮ ደም ሲፈልጉ የሰማይነህ እናት ተከታትለው ደርሰውባቸው የመረረ ቅሬታቸውን ማሰማታቸው አልቀረም።

«አይ የዘንድሮ ልጃገረዶች!....እንዲያው ላይ ላዩን መሽኮርመምና መኳኳል ምን ዋጋ አለው?! ላይ ላዩን አንገት መድፋት ምን ዋጋ አለው?! ላይ ላዩን ፊት ማሳመር፣ መቆነጃጀት ብቻ ምን ዋጋ አለው?! ሁሉም ወግ ነው። ዋናው ነገር ውስጣዊ ክብርን ከመጠበቁ ላይ ነበር!.....ክብርን ጠብቆ በንፅህና መገኘት ነው ቁም ነገሩ!» እያሉ በአግቦ ህይወትን ጎነታትለዋት ነበር።

የበኩር ልጃቸው ሰማይነህ ያንን ያህል ገንዘቡን ከስክሶ ድንግል ልጃገረድ ባለማግኘቱ ያዘኑ መሆናቸውንም ሳይናገሩ አላለፉም። ሆኖም ያው እሳቸውም እንደሰማይነህ ንዴታቸውን እንዲቋቋሙት በቅርብ ዘመዶቻቸው ተመክረው «ሆድ ይፍጀው» እያሉ ከህይወት ዘመዶች ጋር ተቀላቀሉ።

ህይወት ባሜጉላ ቤት ውስጥ በሰነበተችባቸው ቀናት አብራቸው ከምትኖራቸው ሰዎች ውስጥ ወዳጅ ጠላትዋን ለይታ ለማወቅ ችላለች። ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ከሚመጡ ሰዎች ውስት አብዛኞቹ የሚሰነዝሩት አስተያየት የቅናት ይመስላል። ሁሉ የሚነግሯት የሰማይነህ ሀብት ተጋሪ በመሆኗ ዕድለኛነቷን ነው። ሰዎች በከፍተኛ ደረጃ ገንዘብን እያመለኩ የመጡበት ጊዜ መሆኑን ለመታዘብ በቅታለች። ሴት ሚዜዎቿ ሳይቀሩ የሠርጉ ዕለት ማታ ሰማይነህ እንዴት እንደጨቀጨቃት ስትነግራቸው፤ «በቅናት ሲቃጠልና ሲጨስ ቢኖር አንቺ ምን ቸገረሽ? እግዜር ሀብቱ መሀል አስገብቶ ቁጭ አድርጎሻል። ከእሱ መጥጦ ሊፈታሽ ከፈለገም ሀብቱን እኩል - ለኩል እንዲያካፍልሽ ፍርድ ቤት ትገትሪዋለሽ። አሁን ፀጥ ብለሽ መቀመጥ ነው ያለብሽ» የሚል ምክር ነበር የሰጧት። ሀብቱን እያየችና ሆዷን እየሞላች፣ ፍቅርና ሰላም በሌለበት ቤት ውስጥ፣ መንፈሷ ተርቦ የመኖርን አስፈላጊነት ግን የህይወት ልብ አልተቀበለውም። ሰማይነህ ቤት ውስጥ የምትኖረውም በሌሎች ቁጥጥርና ጥበቃ ስር መሆኑን በተዘዋዋሪም ቢሆን ማወቋ ደግሞ ብሶቷን አባብሶታል።

እናቱና ሁለት ወንድሞቹ ከሰማይነህ ጋር አብረው ነው የሚኖሩት። አባቱ አቶ ሽብሩ መርሻ ገና በጎልማሳነት ዘመናቸው በድንገተኛ ህመም ስለ ሞቱ የመጀመሪያ ልጅ እንደ መሆኑ መጠን ቤተሰቡን የማስተዳደሩ ኃላፊነት የወደቀው በሰማይነህ ላይ ነበር። አባቱ ጊዜውና ገበያው ሰምሮላቸው ባይከብሩበትም የታወቁ የወርቅ አንጥረኛ ነበሩ። ሰማይነህም ይህንኑ ሙያ ወርሶ ቤተሰቡን በማስተዳደር እየኖረ ዕድሉ ሲፈቅድለት ንግዱ በጣም ዳብሮ ከበረ። ቤተሰቡንም ከኪራይ ቤት አውጥቶ አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ አሁን የሚገኝበት ሰፊ ቦታ በመግዛት የተንጣለለ ቪላ ሰርቪስ ቤቶች ሠርቶ ይኖሩ ጀመር። ጊዜና አጋጣሚ ረድቶት ከወርቅ ስራው በተጨማሪ ገንዘቡ እየመራው በተለያየ የንግድ አቅጣጫ በመግባቱ ብዙ ዓይነት ጨረታዎች በማሸነፉ እንደ ሮኬት ተተኩሶ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በገንዘብ ብዛት ከሚነገርላቸው ቱጃሮች አንዱ ለመሆን በቅቷል። ትምህርቱን በልጅነቱ አቋርጦ ወደ ስራ ስላዘነበለ ከስድስተኛ ክፍል መዝለል አልቻለም። ቅጡን ባጣ የንግድ ሁኔታ የከበሩ ሰዎች እንደሚሉትም «ትምህርትና ገንዘብ አይዋደዱም.....ከአስር ዲግሪ አንድ ግሮሰሪ» እያለ ከትምህርት ጋር ተጣልቶ ቀረ። ለዚያችውም ለስድስት ክፍል ያቃጠላት የልጅነት ጊዜው ሳትቆጨው አልቀረችም። የሂሳብ ስሌት ስለተማረባት ብቻ ይፅናናል።

እናቱ ወይዘሮ ትርፌ በሻህ በዕድሜያቸው ወደ ሰባ አመት የተጠጉ ቢሆንም በኑሮ ምቾት ምክንያት ገና የሀምሳ አመት ሴት ወይዘሮ ይመስላሉ። ቀይ ፊታቸው ቢጨማደድም ወዛቸው እንዳለ ነው። ዓይናቸው በደንብ ያያል፤ ጆሮአቸው አጣርቶ ይሰማል፣ እግራቸው ያለምርኩዝ ይራመዳል። በአብዛኛው ሰው የሚጠሩት «የሰማይነህ እናት» በሚል ስም ነው። ልጆቻቸውን ከልጅነታቸው ጀምረው እንደ አባት ሆነው ከማሳደጋቸው የተነሳ ቁጡነትና ኃይለኛነት ይታይባቸዋል። በቅርብ አመታት ወዲህ ደግሞ በልጃቸው በሰማይነህ ሀብት በጣም በመመካት ፀባያቸው እንደ መቀባረር እያደረገው፣ በመንደራቸው ውስጥ የበላይነት ስሜት እየተሰማቸው መጥቷል። ሰውነታቸው ጤነኛ በመሆኑና ቤት ውስጥ መቀመጥ ሰለሚሰለቻቸው ታቦት የሚወጣበትን ቀን እየቆጠሩ በየቤተክርስቲያኑ በመዞር ነው የሚያሳልፉት።

ሁለቱ የሰማይነህ ወንድሞች ጎርፍነህ ሽብሩ እና መደምደሚያሽ ሽብሩ «የእናት ሆድ ዥንጉርጉር» እንደሚባለው በባህሪም፣ በድርጊትም የተለያዩ ናቸው። ጎርፍነህ በሁለት አመት ልዩነት ከሰማይነህ ቀጥሎ የተወለደ ሲሆን በዕሜ አሁን አርባ አምስተኛ አመቱን ይዟል። መደምደሚያው የሁለቱም ታናሽ ከመሆኑም በላይ እናትየው መውለድ ካቆሙ ከረዥም አመታት በኋላ በመወለዱ አሁን ገና የሀያ አምስት አመት ወጣት ነው። ወይዘሮ ትርፌ መደምደሚያውን እንደወለዱ ጠያቂያቸው በመገረም «የአሁኑ ደግሞ ምን ይባላል?» ሲሏቸው «መደምደሚያ ነዋ» በማለት ይመልሱ ነበር። መጠሪያ ስሙም በዚያው መደምደሚያ ተብሎ ቀረ። የመጨረሻ ልጅነቱና የተወለደበት የጊዜ ልዩነት ርቀት ተደምረው መደምደሚያን በእናቱ ዘንድ በጣም ተወዳጅ አድርገውታል። ከሁለት ልጆቻቸው በበለጠ ለእሱ ያላቸው አንጀት የተለየ ነው።

የሰማይነህ ተከታይ ጎርፍነህ ሽብሩ አጭር መጠሪያው ጎርፉ ነው። ከዕድሜው መግፋት በስተቀር ብስለትም ሆነ የሥራ ፍላጎትና የሙያ ብቃት አይታይበትም። እሱም እንደ ሰማይነህ በትምህርቱ አልገፋም። የሚያስገርመው ግን የአካዳሚክ ትምህርቱን ሲጠላ ስሜቱን በሌላ ስራ ወይም ሙያ ያለማዳበሩ ነው። ስራ አይወድም። እንዲሁ ቁጭ ብሎ እየተቀበለ፣ ሰውነቱን እያደነደነና መንደር ውስጥ እያውደለደለ ቢኖር ይመርጣል። በገጠር መንገዶች እየተመላለሰ እንዲሰራበት ሰማይነህ አንድ ትልቅ የጭነት መኪና ገዝቶ አስይዞት ነበር። የማይረቡ ምክንያቶች እየፈጠረና መኪናውን በንዝህላልነት እያበላሸ ከጥቅም ውጭ አድርጎት በመጨረሻ በኪሳራ ተሸጦአል። አሁንም አስራ ሁለት ሰው የሚያሳፍር ትልቅ ታክሲ ተገዝቶለታል። ለመጠጫው ያህል ብቻ እየሰራበት ሌላው ጊዜ ያውደለድልበታል። ትዳር የመያዝና ኑሮውን የማሻሻል ፍላጎት አይታይበትም። ለዕለት ሆዱ ግን ሟች ነው፤ ሰማይነህም የሚወደው ለሆዱ ሲል ያዘዘውን ሁሉ ስለሚፈጽምለት፣ ነው። እንደ ወንድም ሳይሆን እንደ «ቦዲጋርድ» ሊያገለግለውም ይሞክራል። እንደሰላይ ሆኖ የሰማይነህን ምቀኞችና ተቀናቃኞች ለመጠብቅ ይሞክራል። እንደ አቃጣሪነትም ይዳዳዋል። ውሸቱንም ሆን

እውነቱን ወሬ ለቃቅሞ ስለሚያመጣለት ሰማይነህ ይቀርበዋል። ስንፍናውንና ዝርክርክነቱን ባይወድለትም ወንድማዊነቱን» ይመካበታል።

ከቤታቸው ውስጥ የትምህርት ፍቅር ያደረበት ትንሽየው መደምደሚያ ብቻ ነው። በግል ጥረቱ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ በሶሺዮሎጂ ተመርቆ የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል። አሁን ደግሞ ሰማይነህ እየከፈለለት ለሁለተኛ ዲግሪው ሶሻል አንትሮፖሎጂ እያጠና ነው። ለአንድ አመት ያህል ከሰማይነህ ጋር በንግድ እንቅስቃሴው ውስጥ ገብቶ መስራት ጀምሮ ነበር። ሆኖም ለዕውቀት ባለው ጉጉት ስራውን ትቶ ትምህርቱን መቀጠሉን መርጧል። ከሁለቱም ታላላቅ ወንድሞቹ ጋር አብዛኛውን ጊዜ በአስተሳሰብ ያለመግባባት እየተፈጠረ ግጭት ውስጥ ይገባሉ። ሁለቱንም ለገንዘብ ብቻ የሚኖሩ ፍጡራን አድርጎ ስለሚወስዳቸው ይንቃቸዋል፤ በትምህርት ላይ የሚያሳዩት ጥላቻ ያናድደዋል፤ እምነት፣ እውነትና፥ ፍቅር፣ በውስጣቸው ስለሌለ ይዘልፋቸዋል። ታናሽ ታላላቆቹን ሲዘልፍ እየገሰፁ፣ ታላላቆቹም አስማምተዋቸው ለመኖር የሚሞክሩ እናትየዋ ናቸው።

ህይወት ለዩም ትዳር የጀመረችው እንዲህ አይነት ግቢና ቤተሰብ ውስጥ ነው። የቤት ችግር የለም፣ ለሁሉም ለየብቻቸው ክፍል ተሰጥቷቸዋል። የግቢው ስፋት ገና ሌላ ቤት ያስጨምራል። ከፊት ገፅታው በዕብነበረድ የታነፀው ቪላም ውስጡ ምርጥ በሆኑ የወለል ምንጣፎች፣ የሳሎን ጌጣጌጦችና የቤት ዕቃዎች የተሞላ ነው። በተለያዩ አበቦች የተሞሉ የአትክልት ቦታዎች መንፈስን ይማርካሉ። በተለይ ጠዋት ህይወት የመኝታ ቤት መስኮት ከፈት አድርጋ ስትመለከታቸው ዓይኖቿን ከመሳባቸውም ሌላ ጥዑም መዓዛ ወደ አፍንጫዋ እየመጣ የገነትን ስሜት ይፈጥርባታል። እንዲህ በተሟላ ግቢና ቤት ውስጥ በሚስትነት ስትኖር በሌሎች ጥበቃና ቁጥጥር ስር መሆኗንም ከዕለት ወደ ዕለት እያወቀች መጣች።

የሰማይነህ እናትና ተከታይ ወንድም ጎርፋ እንቅስቃሴዋን ሁሉ በዓይነ ቁራኛ እንደሚከታተሉ ታዝባቸዋለች። ጫጉላ ቤት ውስጥ ሆና እያንዳንዳቸውን ፀባይና ሁኔታ ለማጥናት እሱ ሲቆጣ የሚቆጡ፣ ጎርፋ ሲስቅ የሚስቁ እሱ ሲያኮርፍ የሚያኮርፉ መሆናቸውን ተረድታለች። ሰማይነህ ለማስደሰት በእሷም ላይ እነዚህን የፀባይ መለዋወጥ አሳይተዋል። ህይወት ከግቢው የምትወጣበት ጉዳይ ካለ ጎርፋ እየተከተለ እንደሚያጅባት በግልፅ ተነግሯታል። ይህም የቁም እስር አይነት ጥበቃ መሆኑን ህይወት አላጣችውም። በፀባዩም ሆነ በአቀራረቡ የተስማማት ታናሽ ወንድማቸው መደምደሚያ ብቻ ነው ጫጉላ ቤት ውስጥ ሆና ብቸኝነት እንዳይሰማት እየቀረበ ሲያጫውታት፣ የምታነብበው መፅሐፍ ሲያመጣላትና ባነበበችው ጉዳይ ላይ ሲያወያያት የልቡን ንፅህና ለማወቅ ችላለች። ሀሳቧን ልታካፍለውና ሊያዳምጣት የሚችል ለወደፊቱም የምትመካበት ሰው እሱ እንደሚሆን ለመገመት ብዙ ጊዜ አልወሰደባትም።

የሠርጋቸው ቪዲዮ ክር ታርሞና ቅንብሩ ተጠናቅቆ አንድ እሁድ ቀን ቤተሰቡ ሁሉ ተሰብስቦ ይመለከተው ጀመር። ወ/ሮ ስራሽም ከቤተሰቡ ጋር ቪዲዮውን አብራ እንድታይና በሰበቡም እንድትጫወት ተጋብዛ ስለ ነበር አለባበሷን አሳምራ መጥታ ተሰይማለች። በሰርጉ ዕለት የነበረችው እያንዳንዷ እንቅስቃሴ በቪዲዮው ካሴት ተቀርፃ በመቅረቧ ሁሉም ይህን የቴክኖሎጂ ዘመን እያደነቁ፣ የሰርጉን ዕለት አስታውሰው እየፈነደቁ፣ በቪዲዮው ውስጥ ራሳቸውን ይፈልጉ ነበር። ሰማይነህና ህይወትም የራሳቸውን የሙሽርነት ስዕል እየተመለከቱ፣ በዕለቱ ልብ ያላሉትን አንዳንድ ሁኔታ ሁሉ እያስተዋሉ፣ የተጋባዡን መስተንግዶ እየገመገሙ በተመስጦ ቆዩ። በቤቱ ውስጥ ንግግር የተከለከለ ይመስል ሁሉም ፀጥ - ረጭ ብሎ አትኩሮቱን ወደ ቪዲዮው አድርጓል።

በመስታወቱ ሙሉ ለብቻዋ የህይወት ምስል ቦግ ብሎ ሲቀርብ፣ «ያን ዕለት እኮ የኔ ልጅ ልዕልት ነበር የመሠለችው» በማለት ወ/ሮ ስራሽ ተነፈሰች። እግረ መንገዷን የዝምታውን አየር ሰብራ ጨዋታ መክፈቷ ነበር።

«እኔስ?......» አላት ሰማይነህ ፈጥኖ።

«አንተም ልዑል ነበር የመሰልከው»

«ምነው እንዲህ ንፉግ ሆንሽ……ንጉስና ንግስት ብታስመይስን ምነ ነበረበት?» አለና ቀላለደ።

«ሥርጉም ሀገር ጉድ ያለለት ዕፁብ ድንቅ ነበር። ያገኘኝ ሰው ሁሉ የሚነግረኝ በአድናቆት ነው» ብላ ሰማይነህ ሞቅ - ሞቅ አደረገችው።

የሰማይነህ እናት ድጋፋቸውን በመስጠት ራሳቸውን በአዎንታ ነቀነቁ። ሰማይነህ ራሱም «ትክክል ነው» እንደ ማለት ኮራ ብሎ ደረቱን ነፋ አድርጎ ተቀመጠ።

ሆኖም ኩራቱና ጨዋታው ብዙ አልቆየም። ድንገት ሰማይነህ የሚያስቆጣ ነገር ተከስቶ ሰውነቱን በአንዴ ለዋወጠው።

«.....ይኸውልሽ እንግዲህ ወ/ሮ ስራሽ.....የልጅሽን ጉድ ተመልከቺ» አለ፣ የፊልሙን እንቅስቃሴ በርቀት መቆጣጠሪያው አንድ ብታ ላይ አቁሞት።

ወጣቶች ህይወቱን ሲሰናበቷት ያሳያል።

አንደኛው ወጣት ቆዳ ጃኬት የለበሰ፣ በጨዋታ ብዛት ፊቴ በላብ እንደተጠመቀ በደስታ ሰክሮ የሙሽሪነቷን ጉንጮች ግጥም አድርጎ ሲስም ይታያል።

«ውይ በሞትኩት!.....ያ ዘሪሁን አይደለም እንዴ?! የወንድሜ ልጅ እኮ ነው። እህቱ ስላገባችለት በደስታ የሚሆነው ጠፍቶታል» አለች ወ/ሮ ስራሽ። የሰማይነህ አመጣጥና ቁጣ ቢገባትም ጥርጣሬው ከንቱ መሆኑን በተዘዋዋሪ መናገሯ ነበር።

«ታዲያ ዘመድስ ቢሆን ይህን ያህል ቅጥ ማጣት ለምን ያስፈልጋል!» አለና ፊልሙን አሳለፈው።

ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ቅናቱ ስላገረሸበትና ቁጣው ስላየለበት ደህና ነገር ማየቱን አቆመ። ከዕድምተኞቹ መሀል ወንዶቹ በሙሉ ህይወትን የሚያዩዋትና የሚፈልጓት አድርጎ በመውሰድ በጥላቻ አይን እየተመለከታቸው ጥርጣሬ የነላበት ቦታ ፊልሙን በመቆጣጠሪያው ያቆመዋል።

«ህዝቡ በሠርግ ስም እየጨፈረና እየተጠቃቀሰ ስሜቱን ይግለፅ - ግዴለም። እኔን የገረመኝ የሙሽሪቷ አብራ መፍለቅለቅና ማዶ ለማዶ መተያየት ነው» አለ ትንሽ ቆይቶ «ይኸውላችሁ ተመልከቷት እዚህ ጋ….በሙሽርነት ሰዓት ይህን ያክል መሳቅ ተገቢ ነው?!»

«ኧረ አይገባም። ቁጥብ መሆን ያስፈልግ ነበር። የሙሽርነት ክብሩ ጥርስን ከደን አድርጎ ኮራ ብሎ ከመቀመጡ ላይ ነው እንዲያው ሲገለፍጡማ ግርማ ሞገሱም ይጠፋል» በማለት የሰማይነህ እናት ድጋፋቸውን አሳዩ።

«እኔን ተመልከቱ እስቲ። የት ቦታ ነው የሳቅኩት?! የትም። የሚጨብጡኝን ሁሉ ኮስተር ብዬ ያሰናበትኳቸው»

«አዎ፤ ህይወት ያን ዕለት ሳቅ አብዝታ ነበር። እኔ እንኳን በአቅሜ የሴት ሚዜዎቿን ጠርቼ ኮስተር እንድትል ንገሯት ብያቸው ነበር» አለ ጎርፉ ውሽቱን፤ ነገር ለሚሟቅ።

በሠርጓ ዕለት፤ በደስታዋና በዓለሟ ቀን የመሳቅ ነውርነት ለወ/ሮ ስራሽ አልተዋጠላትም። የተቃውሞ ሀሳቧን ልትሰነዝር አስባ የሰማይነህ ቤተሰብ አንድ አቋም በመያዛቸው ላለመቃቃር ዝምታ መረጠች።

ህይወትም በበኩሏ ‹ታዲያ የሠርጌ ዕለት እንዳለቅስላችሁ ትፈልጋላችሁ እንዴ?› ማለት ፈልጋ ነበር። ከአክስቷ ጋር በዓይን እንደተግባቡ ሁሉ ነገር ላለማባባስ ዝም አለች። ደግነቱ ስሜቷን የተረዳላት ሰው አልጠፋም።

«የሠርጋችሁ ዕለት ካልሳቃችሁና ካልተደሰታችሁ መቼ ልትስቁ፣ ልትደሰቱ ነው ታዲያ?» አለ መደምደሚያ በድፍረት ጣልቃ ገብቶ።

የህይወትና የወ/ሮ ስራሽ አንጀት ቅቤ ጠጣ። ለሰማይነህ ግን ንዴቱ ጨምሮ አይኖቹን አጉረጠረጠበት። የመናቅና የእልህ ስሜት ሰለተናነቀው ቶሎ መልስ አልሰጠውም። ይልቁንም ጎርፉ እንደሰማይነህ ሆኖ ተቆጣ።

«ሙሽሮች በሠርጋቸው ዕለት እንዲገለፍጡ የተደነገገ ህግ አልሰማንም። አስፈላጊ ያልሆነ ጥብቅናህን ብታቆም ይሻላል»

«ጥብቅና ሳይሆን እምነቴን ነው የተናገርኩት። ሆዴ ሳይሆን አዕምሮዬ ነው ያናገረኝ» በማለት መደምደሚያ የብሽቀቱን በምፀት ተናገረ።

ሁለቱ እንዳይካረሩ እናትዬው ጣልቃ ገቡ።

«ተው እንጂ መደምደሚያ። የማታቀውን አትዘላብድ። ባህላችን የሚፈቅደውንና የማይፈቅደውን የምናውቀ እኛ ነን። አንተ ገና ልጅ ነህ። እንዲያው ገና ለገና ፊደል ቆጠርኩ ብለህ የእርጎ ዝንብ መሆንህን ተወው።

«አይ እማማ፤ አንቺን እንኳን አልፈርድብሽም....» አለ መደምደሚያ። «ለማንኛውም እኔ እስከማምንበት ድረስ በሠርጓ ዕለት የህይወት መሳቅ፣ መደሰት ትክክል ነው። ይልቁንም ግራ የሚያጋባው የሰማይነህ ተኮሳትሮ ሠርጉን ማሳለፉ ነው። ለተጋባዡም ደስ የሚለው ሙሽሮች ፈገግ ብለው ሲታዩ ይመስለኛል»

«አሁን ለምን አትተወኝም!?....ያንተን ጣልቃ ገብነት እንደማልፈልግ ደጋግሜ ነግሬሃለሁ። እዚያው ኮሌጅ ሂድና ተፈላሰፍ። ይሄ የቤተሰብ ጉዳይ ነው። ቤተሰብን እንዴት እንደማስተዳድር የማውቀው ደግሞ እኔው ራሴ ብቻ ነኝ» በማለት ሰማይነህ ጮኸበት።

«ተው እንጂ መደመደሚያ! በቃህ፤ ዝም በል» እናትየዋም ገሰጥ አደረጉት።

ሰማይነህ ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ፊልም አንሺውን ጠመደው። እሷን ብቻ እየለየ የሚያነሳው ለምንድነው? እሱም ህይወትን ፈልጓት ነበር ማለት ነው?!.....ካሜራውን እኮ ከእሷ ላይ መንቀል አልቻለም። ፊሉም የሞላችው እሷ ብቻ ሆናለች። እሷ ትስቅለታለች፤ እሱ ያነሳታል። ደህና ተለማምደው ነበር ማለት ነው። እኔንማ ሙሽራ መሆኔንም ጭራሽ ረስቶኛል። ይሄ ቅንዳሻም ሌባ! ቆይ አገኘዋለሁ። እያለ ሲያስብ ከቆየ በኋላ ፊቱን ወደ ወይዘሮ ስራሽ መልሶ «ወ/ሮ ስራሽ፤ እኔ ሁሉንም ነገር ላንቺ ትቼዋለሁ። ያለፈው አልፏል፤ ለወደፊቱ ግን ያለፉት ስህተቶች እንዳይደገሙ ምክር መስጠት ያስፈልጋል» እያለ በሠርጉ ዕለት የተፈጠረውን ቅሬታ በቪዲዮው ውስጥ ማየቱ አገርሽቶበት በተነጫነጨ በኋላ መደምደሚያው እንዲያምር ለወ/ሮ ስራሽ ውስኪ የራት ግብዣ አደረገላት።

ከግብዣው በኋላ ለልጇ ምክር ቢጤ ለመስጠት ወ/ሮ ስራሽ ህይወትን ይዛት ወደ መኝታ ክፍል ለብቻቸው ገቡ።

«መኝታ ክፍላችሁ እንዴት ያምራል እባካችሁ?....ከወበቱ ደግሞ የስፋቱ!....እኔ መቸም ሰፊ መኝታ ክፍል በጣም ነው የምወደው።.....አልጋው ራሱ ይዟችሁ ቁልቁል የሚሰምጥ ይመስላል፤

ምቾቱ የዘለዓለም እንቅልፍ ሳያስወስድ አይቀርም፡፡.......ጠዋት ጠዋት የምትነቁት በቀስቃሽ መሆን አለበት» እያለች ወ/ሮ ስራሽ መኝታ ቤታቸውንና መታጠቢያ ክፍሉን ካደነቀች በኋላ በሹክሹኪታ ወደ ቁም ነገሩ ገባች፡፡

«ምንድን ነው ሰማይነህ እንዲህ የሚያነጫንጨው?.....ያን ዕለት ይቅርታ አልጠየቅሽውም እንዴ?»

«አልጠየቅኩትም፡፡ አስፈላጊም አልመሰለኝም፡፡....እሱም ከእኔ በፊት ሴት ያውቃል፡፡ አይደለም እንዴ?.....ላለፈ ነገር ምን ይቅርታ መጠያየቅ ያስፈልጋል?!» አለቻት ህይወት ድርቅ ብላ፡፡

«እንደሱ አይደለማ ህይወቴ፡፡ እናንተ ጥሩ ዘመን ላይ ተወልዳችሁ ነው እንጂ ድሮ ሴት ልጅ እንዲህ አይነቱን የሙብት ክርክር ለመግጠም አቅሙም፣ ሥልጣኑም አልነበራትም፡፡......ዋናው ነገር ግን የወንዶችን ልብ ማራራት መቻል ነው፡፡ ልጅ አትሁኚ እንጂ ህይወቴ አየሽ፣ ሰማይነህ አሁን የሚቀናውና የሚነጫነጨው ልቡ ተረጋግቶ በአንቺ ላይ ዕምነት መጣል ስላቃተው ነው፡፡ ወጣት ስለሆንሽ ገና ውጭ - ውጭ የምታይ ሊመስለው ይችላል፡፡ ታዲያ አንቺ ዘዴኛ ሆነሽ እንደ ፀባዩ ብትይዢውና ቃሉን ብትፈፅሚለት እንኳን ንብረቱን ቀርቶ ህይወቱን አሳልፎ ይሰጥሻል፡፡ ከንግድ ድርጅቶቹ መሀል አንዱን በስምሽ ያደርግልሻል፡፡ ወይም ወርቅ ቤቱን አንቺ ተቆጣጠሪው ይልሻል፡፡ »

«አይ አማዬ.....እኔ ሁሉም ነገር ቀርቶብኝ ነፃነቴን ባይነፍገኝ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ መሀል መርካቶ ውዬ ወርቅ ቤቴን ልቆጣጠር ቀርቶ ከዚህ አጥር ግቢ ብቻዬን እንድወጣ እንኳ አይፈቀድልኝም፡፡ .....»

«ስለሚቀና ነዋ፡፡ ወንዶች ሲቀኑ የራሳቸውን ጥላ እንኳን አያምኑም፡፡ ደግሞም ሰማይነህ ቢቀና አይፍረድበትም፡፡ አንቺ ገና ወጣት ነሽ፤ ቆንጆ ነሽ፤ ወደ አደባባይ ብቅ ስትይ ፈላጊሽና ተመልካችሽ ብዙ ሊሆን ይችላል፡፡....እኔም እሱን ብሆን ለአንዳፍታም ከአይኔ እንድትርቂ አልፈቅድልሽም፡፡»

«እስረኛ ሆነሽ ተቀመጪ ነው እንዴ የምትይኝ እማዬ?»

«አይደለም፤ አመኔታ እስኪጥልብሽ ድረስ እንደ ፀባዩ አስታማሚው ነው የምልሽ፡፡ አንድ ልጅ ከወለድለት በኋላ ፍቅሩ ወደ ልጁ ስለሚከፈል ቅናቱ እንዳሁኑ አይሆንም፡፡ የልጁ እናት በመሆንሽ ብቻ ያምንሻል፡፡ እስከዚያው ድረስ ግን የሚልሽን ሁኚ፤ የሚጠላብሽን ተጠንቀቂ፡፡ አንድ የሚጠላብሽ ነገር ይህንን ሳቅሽን ነው፡፡ ቢያንስ በእሱ ፊት ጥርስሽን ከድነሽ መቀመጥ እንዴት ያቅትሻል?!.....»

«እሺ.....» አለችና ህይወት ሳታስበው ሳቀች፡፡

«እኮ አሁን ምን እያደረግሽ ነው?»

«ውይ የኔ ነገር!.....ለካ ስቄያለሁ፡፡»

«ታዲያስ!.....ይሄ ይሄ ነው ሰማይነህን የሚያናድደው፡፡»

«ድሮውኑ እንዳልስቅ አድርገሽ ብታሳድጊኝ ኖሮ አሁን አልቸገርም ነበር፡፡ በልጅነቴ ስቁ ተጫውቼ እንዳድግ ፈቀድሽልኝ፡፡ አሁን ደግሞ በአንድ ጀንበር ራሴን መለወጥ ያስቸግረኛል፡፡»

«ሁሌ ልጅነት የለማ! አሁንኮ ‹አንቱ› የምትባይ ሴት ወይዘሮ የኮራሽ የቤት እመቤት ነሽ፡፡ ዋና ነገር ማሰብ ያለብሽ ከዘላቂ ጥቅምሽ አኳያ ነው፡፡ ሰማይነህ ከአንቺ አልፎ ለሁላችንም የሚተርፍ ባለ ፀጋ ነው፡፡ አያያዝ ብቻ ነው የሚያፈልገው፡፡ ተመልከቺ እስቲ፣ ይህን መሳይ ሰፊ ግቢና የተንጣለለ ቪላ ማን ያገኘዋል?! የተደረደሩት መኪናዎች እኮ ከእንግዲህ ያንቺም ንብረት ናቸው፡፡ ሽቅብ

ሳትወጪ፣ ቁልቁል ሳትወርጂ፣ ሳትደክሚ፣ የዚህ ሁሉ ንብረት ባለቤት መሆን ማን ያገኘዋል?!....ሀብቱንና ምቾቱን እያሰቡ ፀባዩን መቻል ያስፈልጋል።»

«ኡፍ!....እንዴት ያናድዳል!» አለች ህይወት በከፊል አክስቷን እያዳመጠች፤ በከፊል በራሷ ሀሳብ ውስጥ ስትዋዥቅ ቆይታ።

«ምኑ?....አለቻት አክስትዬዋም በንቃት።

«ተሟልቶ ያለመገኘቱ ነዋ!....ከዚህ ሁሉ ሀብት ጋር ጤናማ ፍቅር ቢኖረን እኔና ሰማይነህ ቆንጆ ኑሮ እንኖር ነበር። ሰውነቴን በቅናት ከሚመለከተውና ከሚከታተለው በፍቅር ቢቀርበውና ቢያቅፈው ለራሱ ደስታ አግኝቶ ለእኔም ሰላም ይሰጠኝ ነበር። እኔ መቼም ከፍቅር በላይ ምንም ነገር ያለ አይመስለኝም።»

«አይ ሞኚት! እሱ የወጣተንት ህልምሽ ነው። አሁን ይልቅ እኔ የምመክርሽን አድምጪኝ። በጊዜሽና በውበትሽ ተጠቀሚበት። ፀባይሽን አሳምረሽ የመኪናዎቹን ቁልፍ በእጅሽ አስገቢ፤ የቤቶቹን ቁልፍ ተረከቢ። ከተማው ውስጥ ከሚታዩት የደመቁ ወይዛዝርትና በሽንጣም ከሚንፈላሰሱት ቆነጃጅት እንዷ እንድትሆኚ ዕድሉ ተመቻችቶልሻል፤ ተጠቀሚበት። ለእኔም መኩሪያ ሁኚኝ። ወንድን በዘዴ ከያዙት በቁጥጥር ስር ማዋል ይቻላል፤ እመኚኝ» ካለቻት በኋላ ለጥሎሽ የመኪና ቁልፍ እንደ ተላከላት ድንገት አስታውሳ «ለመሆኑ መኪና መንዳት እየተማርሽ ነው ወይንስ ዝም ብለሽ ተቀምጠሻል?» ስትል ጠየቀቻት።

«መማር ጀምሬያለሁ። ሆኖም እስረኛ ስለሆንኩ በአጃቢ እየሄድኩ ነው የምማረው። አጃቢዬ ወንድምዬው ጎርፉ ነው። ወደ ፊት መኪና ራሴ መያዝ ስጀምር ያለ አጃቢ የሚለቀኝ አይመስለኝም። ምናልባት መኪና የተፈቀደልኝ በሠሌዳ ቁጥሩ እንቅስቃሴዬ ለመከታተል ይሆናል» አለች አንዴም እየሳቀች፣ እንዴም እያዘነች።

«ምንም ይሁን፤ አንቺ ብቻ ዕድሉን ተጠቀሚበት።»

«ወ/ሮ ስራሽሽ ስትናገር ከልቧ ነው። ግንባሯን ኮስተር አድርጋ፣ ንግግሯን አጣፍጣ ይሄ «ሲሣይ» ከእጃቸው እንዳይወጣ የተቻላትን መከረቻት። የራሷን ፍላጎን በልጁ ውስጥ ለማየትም ከፍተኛ ጉጉት አድሮባታል። በአማትነቷ የሚቀርቡላት ስጦታዎችም ገና ከአሁኑ በሀሳቧ ይታያታል። ምክሯ በህይወት ልብ ውስጥ ዘልቆ መግባት ያለመግባቱን ለማረጋገጥ በሚጥር አስተያየት ትኩር ብላ አየቻት። ህይወት ገፅታ ላይ የሚነበበው ነገር ግን ቅሬታ ነበር።

በመጨረሻ ተሰናብታት ከመሄዷ ጥቂት ከባድ ቃሎች ጨመረችላት።

«ሁለት ነገሮች ልብ በይልኝ። ከሰማይነህ ጋር ብትፋቺ ባል እንደማታጪ አውቃለሁ። ነገር ግን ለሁለተኛ ባል የምትቀርቢው ‹ፈት› ተብለሽ ስለሚሆን ደረጃሽን በጣም ዝቅ ያደርገዋል፤ ውበትሽን ይቀንሰዋል፤ ክብርሽን ያኮስሰዋል። ሁለተኛ ነገር ደግሞ ይሄ ዕድል በድጋሚ ላይገኝ ይችላል፤ ይህን ውበት ይዘሽ ከድኃ ባል ጋር ስታከኪ የምትኖሪበት ምክንያት አይታየኝም።»

ህይወት ባዶ ክፍል ውስጥ ብቻዋን በሀሳብ ዋዠቀች። አክስቷ ያሳደገቻት እንድትስቅ፣ እንድትጫወት፣ ነጻ እንድትሆን አድርጋ ነበር። ባሏ ደግሞ አሁን ነፃ እንድትሆን አይፈቅድም። ታፍና እንድትኖር ይፈልጋል።

‹በአንድ ህይወት ውስጥ ራስን ስንቴ መለዋወጥ ይቻላል?› አለች በሀሳቧ....

# ክፍል አምስት

ህይወት እንደ ተባለችው ለመሆን ሞከረች። ወ/ሮ ስራሽ ከነገረቻት ነገሮች ውስጥ «ፈት» የሚለው ቃል አዕምሮዋን ከንክኗታል። ከሰማይነህ ጋር ተጣልታ ብትወጣ በእርግጥም «ፈት» መባሏንና ምርጫዋን ወይንም ተፈላጊነቷን ማጥበቡን ስታስብ እዚሁ ከእሱው ጋር እንደ ፀባዩ ተቻችሎ የመኖር ፍላጎት ስሜቷን ይጎትተዋል። ‹የመጀመሪያ ዕድልሽን ያበላሸውን ይህን ሰው በዋዛ ፈዛዛ እንዳትለቂው። ልጅነት አጥቅቶሽ ይህን ሁሉ አዱኛ ጥለሽ እንዳትሄጂ። እሱ ዕድልሽን አበላሽቷልና አንቺም የንብረቱ ተካፋይ በመሆን መጠቀም አለብሽ› የሚል ስሜት በአንድ በኩል ሲታገላት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ‹ፍቅር ከሌለ ለሀብት ብቻ ተሳስሮ ተቻችሎ መኖሩ ምን ዋጋ አለው? ዕድልሽ በፈትነት የሚጠብበት ምንም ምክንያት የለም፤ በስራሽ ተማምነሽ በውበትሽ እስከተመካሽ ድረስ ምንጊዜም ፈላጊሽ ብዙ ነው› የሚል ስሜት ይፈታተናት ነበር።

በአንድ እሷነቷ ውስጥ ሁለት ስሜቶች እየታገሏት ቀስ ብላ ወደ መስታወቱ ቀረበች። የባሏን ፈቃድ ለመፈፀም ሁልጊዜም ጥርሷን ከድና፣ ፈገግታዋን ደብቃ፣ ኮስታራ ሆና ለመኖር ብትሞክር ትችል ይሆን?.... ሞከረች። ግንባሯን ከስክሳ በመስታወት ውስጥ መልኳን ስታየው ለራሷም አስጠላት። ትላልቅ ዓይኖቿና ረዥም አፍንጫዋ እንዲሁ ፀይም ፊቷ ላይ የተቀመጡ ቅርጾች መሰሏት። የራሷን ሳይሆን የሌላ ኮስታራ ሰው ምስል በመስታወት ውስት የምትመለከት መሰላት። ዋናው የውበቷ ማድመቂያ ፈገግታዋ መሆኑን ተረድታለች። የሰው መልኩ ውጭያዊ ቅርፁ ሳይሆን ውስጣዊ ስሜቱ መሆኑን ለማመዛዘን ቻለች። ‹ታዲያ ሰማይነህ የሚያምረውን መልኬን ትቶ አስጠሊታውን መልኬን የሚፈልገው ለምንድን ነው? ይሄ የበሽታ መሆን አለበት፤ ቅናት የሚሉት ነገር ራሱ በሽታ መሆን አለበት› ብላ ሰማይነህ ቅናት እንዴት እንደሚያደርገው ስታስብ ሳቋ መጣባት። ጥርሶቿ ገለጥ ብለው ፈገግታዋን በመስታወቱ ውስጥ አሳዩአት። ‹አዎ፤ የኔ ትክክለኛ መልኬ ይህ ነው› አለች በልቧ።

ይህን ሁሉ የምታስበው መታጠቢያ ቤቷ ውስጥ ሆና ነበር። ሰማይነህ በጠዋት ተነስቶ ፂሙን ተለጫጭቶና ልብሱን ለባብሶ ወደ ስራ ለመሄድ ተዘጋጅቷል። እንደ ልማድ ሆኖ አየሩ ሞቅ እስኪልላቸው ድረስ ሁለቱም ቁርስ አይበሉም።

«ዛሬ ልብስ ሰፊ ቤት መሄድ እፈልጋለሁ» አለችው ህይወት ከመታጠቢያ ቤት እንደ ወጣች።

«ለምን አለ ሰማይነህ እንደ ተኮሳተረ።

«ያንን ለጥሎሽ የላክልኝን የቀሚስ ጨርቅ ለማሰፋት አስቤያለሁ።»

«ምን ዓይነት ቀሚስ ነው የምታሰፊው?»

«የጊዜውን ፋሽን ነዋ። ለአንተ ብነግርህ አታውቀውም»

«አጭር ነው ወይንስ ረዥም?»

«በጣም ረዥም ቀሚስ ነው፤ ቁርጭምጭሚቴ ድረስ የሚደስር። እሱ ነው አዲሱ ፋሽን»

ሰማይነህ ደስ አለው። አጭር ቀሚስ አሰፋለሁ ብትለው ኖሮ ቤታቸው ውስጥ በጠዋት ጦርነት ሊነሳ ነበር። እንኳን የራሱ ሚስት ሌሎች ሴቶችም አጭር ቀሚስ ሲለብሱ አይወድም። በተለይ ከጉልበታቸው በላይ አጣብቂኝ ጉርድ የሚለብሱ ሴቶች ሲመለከት ደሙ ይፈላል። ከህይወት ጋር የተገናኘበት ወቅት የረዥም ቀሚስ ፋሽን የሰፈነበት በመሆኑ ፈጣሪውን አመሰገነ። በአጭር ቀሚስ ተጣብቃ ጭኗንና ባቷን ለአደባባይ አጋልጣ፣ ወጣት አዛውንቱ ዓይኑን ተክሎባት ቢመለከት ምን

ይወጣው ነበር?! ወንዶቹ አይናቸውን እንዲነቅሉ በየደረሰበት ጦርነት ከሚገጥም ይልቅ ቀድሞውንም ህይወት አጭሩን እንዳትለብስ ማገዱን ይመርጥ ነበር። ይህንን ፋሽን ባለመከተሏ ሚስትህ ኋላቀር ነች የሚለው ቢኖር ገደል ሊገባ ይችላል። እስካሁንም የህይወትን የልብስ ሳጥን ስላልፈተሸ ነው እንጂ አጠገቧ እሳት አንድዶ የሚያቃጥላቸው በርካታ ጉርድ ቀሚሶች ሊኖሩ ይችላሉ።

«የት ነው ቀሚሱን የምታሰፊው?»

«መርካቶ የቀድሞ ደንበኛዬ አለ።»

«በጣም ጥሩ። አብረን እንሄዳለን። ሱቁን ስለምከፍት ለእኔም መንገዴ ነው። አሁን ቶሎ ቶሎ ልበሺና ተነሽ።

ይህወት ሰውነቷን እየቀፈፈው ልብሷን ለባብሳ የሚሠፋውን ጨርቅ ይዛ ተነሳች። እንደተለመደው ከወንድምዬው ጋር የሚልካት መስሏት ነበር እንጂ ሰማይነህ ራሱ አብሮኝ ይሄዳል የሚል ግምት አልነበራትም። ነፃነት ስለማይሰጣትና ሁለመናዋን ስለሚከታተላት ከሰማይነህ ጋር መሄድ አትወድም። ከእሱ ተለይታ የምትሰራው ነገር ባይኖርም የሚያስቀይመውን ነገር ስለማታውቀው አብራው ስትሄድ ሁሌም እንደ ተሸማቀቀች ነው።

የሰማይነህ ወርቅ ቤት በዝና ሲወራለት ካልሆነ በስተቀር ሄዳበት አታውቅም ነበር። ዛሬ በአጋጣሚው ቦታውን ለማየት በቃች። እዚያው መርካቶ ውስጥ ጨረታ የሚካሄድባቸውና ሌሎች የንግድ እንቅስቃሴዎቹን የሚከታተልባቸው ሌላ ቢሮ እንዳለውም ሰምታለች ወርቅ ቤቱ ስለ ሰማይነህ ሀብት የሚነገረውን ያህል ግዙፍ አይደለም። ከአራት ያልበለጡ ሰራተኞችን የያዘ መጠነኛ ንግድ ቤት ነው።

በተለያዩ ቅርፅና አይነት የተሰሩት የወርቅ ጌጦች በመልክ በመልካቸው ተደርድረው ስትመለከት ህይወት ልቧ ተነካ። ብዛታቸውና ብርቅርቅነታቸው ተደምሮ አንዳች ድንገተኛ መስህብ ፈጠሩባት። መኖሪያ ቤቷ ሆና በሀሳቧ የናቀችውን ወርቅና ሀብት አሁን ልትንቀው አልቻለችም። ለሀብት የሚያጓጓ ብልጭልጭ ስሜት ተፈታተናት። ወዲያውኑ አክስቷን አስታወሰች። ምክሯን ለሀብት ያላት ከፍተኛ ግምት ትዝ አላት። ‹እውነቷን ይሆን እንዴ?....› ስትል አሰበች። ዓይኗን የሳባት በልብ ቅርፅ የተሰራ የአንገት ሀብል ሳታስበው አንስታ በአድናቆት ተመለከተችው።

ሰማይነህ ሁኔታዋን በጥሞና እየተከታተለ ነበር። በወርቅ ጌጣጌጦቹ ስሜትዋ መመሰጡን ሲመለከት ደስ አለው። ባላሰበችው መንገድ ወጥመድ ውስጥ የገባችለት መስሎ ታየው። በሀብቱ ሁሉንም ነገር ማድረግና ማስደረግ የሚችል ሆኖ ስለሚሰማው እጅግ በጣም ይመካል። የህይወት ኩራትና ለሀብት ያለመጓጓት አስደንግጦት በሀብት መመካቱ እየኮሰሰበት መጥቶ ነበር። ዛሬ ወርቅ ፊት ቆማ ልቧ ሲሰለብ በማየቱ ያ ስሜት እንደገና ከውስጡ አንሰራራ። ‹የወርቅ ማብለጭለጭ ዓይኑን የማያውረው ሰው የለም። እንኳን አንቺንም ለዚህ አደረሰሽ አለ በልቡ።

«ጌጣጌጦቹ ደስ ያሉሽ ትመስያለሽ.....» አላት ወደ አጠገቧ ቀርቦ

«አዎ.....ቆንጆዎች ናቸው።»

«በጣም ደስ ያለሽ የትኛው ዓይነት ነው?»

«ይኼኛው» ብላ በእጇ የነበረውን ባለ ልብ ቅርፅ አሳየችው።

«የበለጠ እንዲያምር ተደርጎ ካራቱ ተጨምሮ ይሰራልሻል። አሁን ወደ ጉዳያችን እንሂድ» ብሎአት ወጡ።

ባህሩ ጊሞ ስለ ሴቶች ከነገረው ጥቅሶች ውስጥ አንዱ ትዝ አለው። «ወርቅ አልፈግም ያለች አንድ ሴት ብቻ አጋጥማኛለች። እሷም አልማዙን ወሰደች።» የጥቅሱ ባለቤት ስም ሆሬስ ዋልፖል መሆኑን ሰማይነህ ሊያስታውስ አይችልም። አባባሏ ብቻ ልቡን ስለ ነካችው አዕምሮው ውስጥ ተቀምጣለች።

የሚሄዱበት የልብስ ሰፊ ቤት ከወርቅ ቤቱ ብዙም እንደማይርቅ ህይወት ብትነግረውም፣ ሰማይነህ ቆንጆ ሚስቱን ይዞ ከተራ ሰው ጋር እየተጋፋ ማለፉ ስላስጠላው በመኪናቸው ሄደው ልብስ ሰፊው አካባቢ ቆሙ።

«ጋሼዬ፤ መኪናውን ልጠብቅ?» አለው አንዱ በረንዳ አዳሪ ወጣት፣ ቡትቶውን እየጎተተ።

«ጠብቅ እሺ።»

«እትዬ.....ራበይኝ» አለ ሌላኛው ተመሳሳይ ወጣት ወደ ህይወት ተጠግቶ።

«ዞር አትልም እንዴ አንተ!» አለው ሰማይነህ ተቆጥቶ።

«ምነው ፋዘር!.....እኔ የለመንኩት እሷን ነው» እያለ ወጣቱ ወደ ኋላው አፈገፈገ።

«ምንድን ነው የጠየቅካት?» በማለት ሌላ ሦስተኛው እጣት ለከፋ ጀመረ።

«......እንደትሰጠኝ ነዋ» አለውና ተሳሳቁ።

ሰማይነህ በንዴት የደምስሮቹ ተገታትረው ልጆችን ለመቆጣት ቢሞክርም፣ የሚበገሩ አይነት አልሆኑለትም። ለዱላም ወደ ኋላ የማይሉ አይን አውጣዎች ሆነው ድርቅ አሉበት። መናደዱን ሲመለከቱ ደግሞ ከኋላ - ከኋላቸው እየተከተሉ አበሸቁት።

«ሚስቱ ነች ወይስ ልጁ?!» አለ አንደኛው ድምፁ እንዲሰማ ሆኖ።

«ልጁ ትሆናለች እንጂ!.....ሰውዬው የጨረሰ ሽማግሌ አይደለም እንዴ?!» አለ ሌላኛው በፌዝ ቅላፄ።

«ብር ይኖረው ይሆናላ። ካሹ ነው የሚሰራው፤ ፋዘሯ ቢሆን ኖሮ አይናደድም ነበር። ሀዝባንዷ ነው እባክህ»

«ቆንጅዬ ልጅ ናት። እኔን ብታገባ ነበር የሚሻላት።»

«ምን ታደርግላታለህ?! በረንዳ ልታሳድራት ነው?»

«የለ፤ አይሮፕላን ልገዛላት ነው።»

ሰማይነህ ንዴቱን መቆጣጠር አልቻለም። ሽጉጡን መኪናው ውስጥ ረስቶ መውረዱ ይበልጥ አናደደው። ለአንድ አፍታ ቆሞ ወጣቶቹ ላይ ሲያፈጥባቸውና ጥርሶቹን እያንቀጫቀጨ ራሱን ሲነቀንቅ ፀብ እንዳይነሳ ፈርታ ህይወት ክንዱን ያዘችው።

«ተዋቸው እባክህ ሰማይነህ። ከእነዚህ የሜዳ ዱርዬዎች ጋር ልትደባደብ ነው እንዴ? እነሱ እኮ ስድ አደጎች ናቸው።»

«ቆይ ግዴለም! ዛሬውኑ ፖሊስ አምጥቼ ከዚህ አካባቢ ባላስለቅማችሁ እኔ ሰማይነህ አይደለሁም!»

ልብስ ሰፊው ቤት ገብተው ሲቀመጡም ንዴቱ አልለቀቀውም፡፡ የህይወት ልብስ ሰፊ ደንበኛ ወንድ መሆኑን ሲመለከት ደግሞ ይብስ ሌላ ንዴት ጫረበት፡፡ ‹ሴት ልብስ ሰፊ አጥታ ነው የወንድ ደንበኛ የያዘችው?› እያለ ቅናቱ ከውስጥ ብቅ ማለት ጀመረ፡፡

ሜትሩን ትከሻው ላይ ያንጠልጠለው ልብስ ሰፊ ህይወትን በሞቀ ፈገግታ ተቀብሏት ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፤ «……ማግባትሽን ሰማሁ፤ ሠርግ ሳትጠሪኝ በመቅረትሽ ተቀይሚሻለሁ» እያለ ቀላለደ፡፡

‹እርምህን አውጣ!› አለው ሰማይነህ በልቡ፡፡

«…..ስለ ረሳሁህ ይቅርታ፡፡ ባለቤቴ እሱ ነው» አለችው ህይወት ፈጥና ወደ ሰማይነህ እያመለከተች፡፡

«እሺ» ብሎ ልብስ ሰፊው ፈገግታውን ሳይቀንስ ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ ለሰማይነህ ሰላምታ ሰጠው፡፡

ሰማይነህ ግንባሩን እንዳኮሳተረ አንገቱን ሰበር አድርጎ ለሰላምታው ምላሽ ሰጠ፡፡

«እንዴት ነበር?….. ሠርጋችሁ በጥሩ ሁኔታ አለፈ?»

‹ምናባክ አገባህ!› አለው ሰማይነህ በልቡ፡፡

«አዎ…. ጥሩ ነበር» ስትል መለሰች ህይወት፡፡

«የሚዜዎችሽንና የመልስ ልብሶችሽን እኔ ጋ ማሰፋት ነበረብሽ»

«ውይ!…..ሁሉም የመጣልኝ ከውጭ ሀገር በትዕዛዝ ተሰፍቶ ነው፡፡»

«ንገሪው! እሱ የሰፋውን አቡጀዲ የማለብስሽ ደህ ያለ መሆኔን ይወቀው፡፡ የእሱን ቡትቶ ወደ ፊትም ለዕድልሽ አታሳይው› አለ ሰማይነህ በልቡ፡፡

«በዚህ ዓይነት ሚዜዎቹም ታድለዋል፡፡»

‹አትጠራጠር፤…. አንተንም ያን ሰሞን ባገኝህ ድንኳን ጠባቂ ዘበኛ አድርጌ አለብስህ ነበር› አለ አሁንም ሰማይነህ በልቡ፡፡

«…..እሺ አሁን ምን ልርዳሽ?»

ልብስ ሰፊው ፈገግታውን ሳይቀንስ በፍጥነት ወደ ስራው ተሸጋገረ፡፡

«ቀሚስ እንድትሰፋልኝ ነው፡፡ ጨርቁን ይዤ መጥቻለሁ» ብላው ጨርቁን ካወጣች በኋላ» ይኸውልህ ለጥሎሽ የመጣልኝ ጨርቅ ነው» አለችው፡፡

«ፐ!….. በጣም ኩዋሊቲ ጨርቅ ነው» በማለት አድናቆቱን ገለፀላት፡፡

‹ሰውዬው እኮ እኔ ሰማይነህ ነኝ፡፡ ለሙሽራዬ ተራ ጨርቅ የምልክላት ተራ ሰው አይደለሁም፡፡ › አሁንም ሰማይነህ በልቡ አጉረመረመ፡፡

የስፌቱን ዓይነት ከጠየቃት በኋላ ልብስ ሰፊው ልኳን ለመመዝገብ ሜቱን ይዞ ሲቀርባት የሰማይነህ የቅናት ስሜት አብሮ ተነሳሳ፡፡ በሜትሩ በእጁ የትኞቹን የሰውነቷን ክፍሎች መነካካት እንደ ፈለገ ዓይኖቹን አፍጥጦ በጉጉት ይጠባበቀው ጀመር፡፡

ፈገግታ ለልብስ ሰፊው የገበያ ምልክቱ ይመስላል። አልፎ አልፎ እንደመኮመክም አንዳንድ ቃሎች ወርወር ያደርጋል። ሰማይነህ ግን በጠቅላላው ሁኔታውን አልወደደውም።

‹ሽርሙጣ ይመስል ምን ያቅለሰልስዋል?!.....ግልፍጥ!› እያለ ነበር በልቡ።

ልብስ ሰፊው ጎበስ ብሎ የህይወትን ቁመት በሜትሩ ሲለካ ሰማይነህ ምንም አላለም። የወገቧንና የደረቷን ስፋት ሊለካ በእጁ ሲደባብሳት ግን ሰማይነህ ስሜቱን መቆጣጠር ስላቃተው ከተቀመጠበት ብድግ አለ። ልብስ ሰፊው ስራው ላይ ስላተኮረ የሰማይነህን ሁኔታ አላጤነውም። አጠገቡ ያሉት ሌሎች ልብስ ሰዎች ግን ሁኔታውን ተመልክተው ችግር እንዳይፈጠር እየሰጉ ነበር። ጓደኞቸውን በዓይን ጥቅሻ ለማስጠንቀቅ ቢሞክሩም እሱ ቀና ብሎ አላያቸውም።

‹እጅህ ቢያርፍ ይሻላል! አንተ ወራዳ ልክስክስ›

ሰማይነህ አንበሳ መስሎ ቆሞ በሆዱ ቢያጉተመትም ስላሆነለት፣ ዓይኖቹን አጉረጥርጦ እየተንጎራደደ የውሸት ሳል ሳለ። እንደገናም አንገቱን ወደ በሩ ወጣ አድርጎ አኪታውን በረኸም ተፋ።

ህይወት ቀና ብላ ስትመለከተው የፊቱን መለዋወጥ ስላጤነች ልቧ በድንጋጤ መዝለል ጀመረ። ፀብ እንዳይፈጠር ፈርታ በልቧ ፀለየች። ‹ውይ አምላኬ!....ደሞ ምን ይሆን ያስቀናው?....አመለካከቱ የጤና አይመስልም።»

«ወንድም!... ጤና የለህም እንዴ?!» በማለት ትዕግሥቱ አልቆ ልብስ ሰፊው ላይ አንዴ ጮኸበት።

«አቤት?.....ምን አጠፋሁ ጌታዬ?» አለ ልብስ ሰፊው ደንግጦና ሁኔታው ግር ብሎት።

«እጅጅህን ከሰውነቷ ላይ ብታነሳ ይሻልሀል! ውርደት እንዳይከተልህ!» እንደታዘዘው አድርጎ ሜትሩን ሰበሰበ።

«ከብብቷና ከጡቷ ምን ጉዳይ አለህ?!..... የምትሰፋላት ቀሚስ እንጂ ካፖርት አይደለም።»

«ሙሉ ቀሚስ እንድሰፋላት ሳለዘዘችኝ እኮ ነው።»

«እንዲያም ቢሆን መለኪያው ሜትሩ ነው እንጂ እጅህ አይደለም።»

«ሜትሩን በእጄ ካልያዝኩት እንዴት መለካት ይቻላል ጌታዬ?»

«ስራህን ትተህ፣ አይኖችህ ፈዝዘው፣ ጡቶቿን ስትመለከት ያላየሁህ መሰለህ?!.....አይቼሀለሁ።»

«ተሳስተዋል ጌታዬ....መቼም ዓይኖቼን ጨፍኜ ልለካት አልችልም» አለና ሁኔታው አስገርሞት ሳቁ አመለጠው።

«ጥርስህ ይርገፍ!»

«ተው እንጂ አይሳደቡ!.....ትልቅ ሰው አይደሉም እንዴ!»

ህይወት በመሀል ቤት ተጨንቃ ሞተች። አስፈላጊ ያልሆነ ግጭት በመፈጠሩ እያዘነች» ኧረ በናታችሁ ታገሱ። ምን ዓይነት የተረገመ ቀን ነው ዛሬ። እባካችሁ ተው» ትላለች በደፈናው።

«እንሂድ በይ!....አንቺ ነሽ ያዋረድሽኝ» ብሎ ሰማይነህ እሷው ላይ አፈጠጠባት።

ህይወት ጨርቋን ሰብስባ ለመሄድ ሲነሱ ልብስ ሰፊው ገበያው በመበላሸቱ ቅር ብሎት ሊያባብላቸው ፈለገ። በህይወት ዙሪያ እየተከረከረ ደጋግሞ የለካትና ሆን ብሎ ስራ ያበዛው ሞቅ ያለ ክፍያ ለመጠየቅ ነበር። ጭራሹን ጥለው መሄዳቸው አናደደው።

«ለነገሩ መለካቱን ጨርሼ ነበር እኮ» አላቸው እንደ መቅለስለስ እያደረገው።

«የዛሬውንማ ጨርሰሀል። ገና ደግሞ ለፐሮቫ ቀጥረሀት ልትደባብሳት ያምርሀል?!» ብሎት በንቀት አይን ከተመለከተው በኋላ».....የሰው ሚስት ማባለግ የለመዳችሁ ጋጠወጦች መሆናችሁን አውቃለሁ» በማለት ሁሉንም ሰድቧቸው እየተንጨረጨረ ወጣ።

«ክብርህን ብትጠብቅ ይሻልሀል!.....አንተ ቅሌታም!» አለው ልብስ ሰፊው ተከትሎት ወጥቶ። ንዴት ሲጀምረው ያ ሁሉ ፈገግታ መቅለስለስ በአንድ ጊዜ ከፊቱ ላይ ጠፋ።

«ይሄ ሰውዬ ምን ነካው?.....ደህናም አልነበር እንዴ? እዚያ እላይ ሰፈር ወርቅ ቤት አለው እኮ!.....ኸረ የታወቀ ሀብታም ነው አላቸው ሌላኛው ልብስ ሰፊ ከመሀል። ከዚህ በኋላ ሌሎቹም እየተቀባበሉ ይተርቡት ጀመር።

«ብር ልቡን አሳብጦት ይሆናላ»

«ይሄ መቼም የጤንነት አይመስለኝም።»

«ልጅቷ ይቺ መሆኗን አላወቅኩም እንጂ በቅርቡ ቅልት ያለ ሠርግ ደግሶ ማግባቱን ሰምቻለሁ።
»

«እሷ ግን ነፍስ የሆነች ልጅ ነች። ከእሱ ጋር አትሄድም፤ ፈርዶባት እዚህ ፋራ ላይ ወደቀች።

«ብሩ ይሆናላ የሳባት። ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ ይባል የለ!»

«መሆን አለበት እንጂ በዕድሜም አይመጣጠኑም።»

«አየህ....እንደዚህ የሚቀናው እኩያው ስላልሆነች ይሆናል።»

«ለነገሩ እንኳ ቁንጅናዋም ያስቀናል። ከሰው ዓይን ይጠብቅለት.....አደባባይ ይዘዋት የሚወጡ ዓይነት አይደለችም።»

«ያላቻ ጋብቻ የሚለውን ቲያትር አይተኸዋል?» እያሉ ቀላልደው ወደ ስራቸው ተመለሱ።

ሰማይነህ ከልብስ ሰፊው ቤት ከወጣ በኋላ መኪናቸው እስኪደርሱ ድረስ ቁጣውን ህይወት ላይ እያዥጎደጎደባት ነበር።

«አሰደብሽኝ አይደል!» አላት አፍጥጦ

«እኔ ምን አደረግኩ ሰማይነህ?» በልመና ድምፅ ልታግባባው ሞከረች።

«ሴት ልብስ ሰፊ አጥተሽ ነው እነዚህ ጋጠ ወጦጥ ጎረምሶች ጋ ያመጣሽኝ?!»

«እኔ እንዲህ ዓይነት ችግር ይፈጠራል ብዬ አላሰብኩ። ሰውዬው የቆየ ደንበኛዬ ስለሆነ.....»

«ብዙ ጊዜ ደባብሶ ለክቶሻል ማለት ነው! ወይኔ ሰማይነህ እንደ ሁኔታው መቼም ልብስሺን ሁሉ አውልቂና ልለካሽ ሳይልሽ የቀረ አይመስለኝም» ብሎ በቅናት እንደ ጦፈ፣ እነዚያ ቀድሞ ለከፈውት የነበሩት በረንዳ አዳሪ ወጣቶች አይተውት እየተሯሯጡ መጡ።

ለከፋቸውን ለመሸሽ የመኪናውን በር ቶሎ ከፍቶ ሁለቱም ገቡና ለጠባቂው ጉርሻ ሰጥቶ በአስቸኳይ ሞተር አስነሳ። ሆኖም የመርካቶ ትርምስ ፈትለክ ብሎ ለመውጣት አላመቸውም።

ዱርዬዎቹ የመኪናውን መስታወት ከብበው በሰማይነህ እያሾፉ ህይወትን «ሳንቲም ግፊ እንጂ» አሏት።

አውቃ እንዳላየቻቸውና እንዳልሰማቻቸው ለመሆን ሞከረች።

«ፐ! ኬክ የሆነች ልጅ ነች። ያውም ቼኮሌት ኬክ!....ይቺን ፀጉሯን ላጨት አድርጎ፣ ጥፍሮቿን ነቀል ነቀል አድርጎ ማግመጥ ነበር« እያለ አንደኛው ለሌሎቹ የፀጉር አለጫጨቱን፣ የጥፍር አነቃቀሉንና አጎራረሱን በትርኢት መልክ ያሳያቸዋል።

«እንደ ጭራቅ?!....» ይለዋል ሌላኛው።

ህይወት በሁኔታቸው ተገርማ ሳቋን መቆጣጠር አልቻለችም። የሰማይነህን ንዴት ባትዘነጋውም ሳቋ አሸንፏት ገንፍሎ ወጣ። ሆኖም ሳቋን ከመጨረስዋ በፊት የሰማይነህ ቡጢ መንገጭላዋ ላይ ሲያርፍ ተሰማት። ቡጢው ወዲያውኑ ጥርሷን አስከድኗት፣ የተመታችበትን ቦታ በእጇ ይዛ አንገቷን አቀረቀረች።

እሷ ሳታስበው እንደ ሳቀች ሁሉ ሰማይነህ በንዴት ቡጢ የሰነዘረው ሳያስበው ነበር። እሷ ስሜቷን መቆጣጠር አቅቷት እንደ ሳቀችው ሁሉ እሱም ንዴቱን መቆጣጠር አቅቶት ጡንቻውን ሰነዘረ። ንዴቱ እስኪበርድለት ድረስ ምኗ ላይ እንደ መታት እንኳ ዘወር ብሎ አላያትም። ዝም ብሎአት መኪናውን ከሰዎች ጋር የትታከከ ለማውጣት ይታገል ጀመር።

ዱርዬዎች የሰማይነህ ድርጊት ወዲያውኑ ቀድተው እዚያው እርስ በርስ ይቀላለዱበት ጀመር።

«ቅናት እንዴት ያደርጋል?»

«እንደ'ኒህ ሰውዬ ያደባድባል......በቡጢ ጥርስ ያስከድናል።

«እኔ ልሳቅ፤ አንተ ምታኝ»

«መጀመሪያ በፍቅር ወስውሰህ አስቀናኝ»

ሰማይነህ እንደ ምንም መኪናውን አውጥቶ ፈልተከ ሲል «አሽዬ በረሩ.....በቅናት ሰከሩ!» እያሉ እያፌዙበት እስከተወሰነ መንገድ ድረስ ተከትለው ሸኙት።

ወደ ቤታቸው ተመልሰው የውጭው በር እስኪከፈትላቸው ድረስ ህይወት ካቀረቀረችበት ቀና አላለችም። ጥርሷን ደግፋ እንባዋን አያዘነበች ከቤቷ ደረሰች። አሁንም ከመኪናው ውስጥ መውረድ አልፈለገችም። ሰማይነህ ቀድሞ ወርዶ በእሷ በኩል ያለውን በር ከከፈተ በኋላ ሊያወርዳት እየታገለ «ለምን ታናድጂኛለሽ?....ለምን ታበሳጭኛለሽ?! በንዴት ተገፋፍቼ እንጂ አውቄ ያደረግኩት ነገር አይደለም» ብሎ ቀና ሲያደርጋት ከጥርሷ የሚወርደውን ደም ተመለከተ። ከዓይኖቿ እንባ እየፈሰሰ ፊቷን አነፍርቶት፣ ከአፏ ውስጥ የሚወጣው ደም ከንፈሯን አጨማልቆታል።

ሰማይነህ ደነገጠ። ይህን ያክል የጎዳት አልመሰለውም ነበር። ፊቷ የዚያች የሚያውቃት ህይወት ሳይሆን የሌላ ሰው ፊት መስሏል ከህመሙም ሌላ ዕልህ ስለተናነቃት ህይወት ሰውነቷን ግርትር አድርጋ እያለቀሰች ከመኪናው አልወርድ ብላ አስቸገረችው ዘበኛውን ጠርቶ ለሁለት ግራና ቀኝ ተሸክመው ወደ መኝታ ክፍል አስገቧት።

የሰማይነህ እናት ጭንቅላታቸውን ይዘው እየጮሁ «ወይኔ ልጄን!.....ምን ሆናችሁ?.....ምን ነካችሁ?.... የመኪና አደጋ ነው?!.....ኧረ ምንድን ነው?....» እያሉ ገቡ።

«አትጨነቂ፤ ቀስ በይ፤ ምንም አልሆንም። ስላናደደችኝ ትንሽ ገጨት አድርጊያት ነው» አላቸው ሰማይነህ።

መጀመሪያ በመኪና ግጭት ሰማይነህም የተጎዳ መስሏቸው ተደናግጠው ፊቱ ላይ ጭረት እየፈለጉ ነበር። ነገሩን ካወቁ በኋላ ስሜታቸው ቀዝቅዞ» ታዲያ ጎዳህት እንዴ?....ደምታለችና!» አሉት።

«ሳላስብ የሰነዘርኩት ቡጢ ጥርሷ ላይ አረፈ መሰለኝ»

«አንተ ወደ ፊቷ ላይ ለምን ትሰነዝራለህ?! ለወደፊቱ ቢሆን ከአንገቷ በታች ነው መምታት» ብለው በልጃቸው ወንድነት በልባቸው እየተኩራሩ ህይወትን ቀረብ ብለው ይደባብሷት ጀመር።

ህይወት እንዲነኳት አልፈለገችም። እርስዎን አልፈልግዎትም ዘወር ይበሉ! ሁላችሁንም አልፈልጋችሁም!.....በቃችሁኝ› ለማለት አማራት። ሆኖም በእነሱው እጅ ላይ ናት። ሌላ የምትወድቅበት ሰው አጠገቧ የለም። በሰማይነህ ዘመዶች መሀል ብቻዋን መሆንዋ ጠልቆ ተሰማት። ሆድ ብሷት ተንሰቅስቃ አለቀሰች።

«ተይ በቃሽ አታልቅሺ ልጄ.....እሱም ለክፋት ብሎ አይደል.....ሰይጣን በመሀላችሁ ገብቶ ነው» እያሉ የሰማይነህ እናት ሲያባብሏት ሠራተኞቹ ውሀና ፎጣ አምጥተውላቸው ደሟን እየጠራረጉ ፊቷን አጠቡላት።

«እኔ ልሂድና ሐኪም ላምጣ?.....» ብሎ ሰማይነህ እናቱን ወደ ውጭ ከጠራቸው በኋላ «አምልጣችሁ ከግቢ እንዳትወጣ ተጠንቀቁ።.....ከአጠገቧ ሆናችሁ እንቅስቃሴዋን ተከታተሉ። ከአጠገቧ አትራቁ» በማለት አስጠንቅቋቸው የመኝታ ቤቱን ስልክ ወዲያውኑ ነቅሎቶ ሄደ።

መኪናውን አስነስቶ የውጭውን በር ሲወጣም ለዘበኛው ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ ሰጠው። በእነሱ ብቻም አልተማመነም። በእንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ ላይ በጣም የሚመካበትን ወንድሙን አዘውትሮ ታክሲ በሚሰራበት መንገድ ላይ ፈልጎት ነገረው። ጎርፉ ትዕዛዙን በደስታ ተቀብሎ በፍጥነት ወደ በኢት ሄደ።

ሐኪሙ ብዙ ጊዜ ከሰማይነህ ቤት የማይጠፋ ወዳጁ በመሆኑ ያለ ምንም ማንገራገር የርዳታ መስጫ መሳሪያዎቹን ይዞ ተነሳ። እንዳጋጣሚ በክሊኒኩ ውስጥ የእሱን ርዳታ የሚፈልግ ታካሚ አልነበረም። የሰማይነህ አገላለፅ ህይወት ራሷን ስታ እንደ ወደቀች አድርጎ ስለ ነበር፣ መኪና ውስጥ ከገቡ በኋላ አጥብቆ ጠየቀው።

«.....በወደቀችበት ጊዜ ጭንቅላቷ አካባቢ ተመትታ ይሆን?.....ድንጋይ ወይም ብረት ነገር አግኝቷት ይሆን?»

ሰማይነህ በውሸቱ መቀጠል እንደማይችል በመገመት እውነቱን ነገረው።

«......ወድቃ አይደለም እባክህ.....እኔ ነኝ የመታኋት። መንገድ ላይ ትንሽ ያለ መግባባት ተፈጠረና እጄን ስሰነዝር ወደ አገጯ አካባቢ አገኘኋት።......ጥርሷም ደምቷል።»

ሐኪሙ ሳቁ መጣበት። የአደጋውን መቅለል ስለገመተ ድንጋጤው በአንዳፍታ ወደ ቀልድ ለወጠው።

«ምነው ምን ነካችሁ?.....ገና ፊርማችሁ እንኳ ሳይደርቅ!.....ሙሽርነታችሁ ሁለት ወር ሳይሞላው?!....አዲስ ሙሽሮችን ሰይጣን ይፈታተናቸዋል መሰለኝ። መላዕክት የሰርጉ ዕለት ብቻ ሆይሆይ ብለው፣ አጨብጭበው፣ ሁለቱን አገናኝተው ስለሚሄዱ፣ ከዚያ በኋላ በሙሽሮቹ ጣሪያ ስር የሚያንዣብበው ሰይጣን ነው።.....የሚገርም ነው።»

ሰማይነህ የሐኪሙን ቀልድም ሆነ የፌዝ ንግግር አልወደደውም። በልቡ ‹በእኛ መሀል ስለተፈጠረው ግጭት አንተ ምንም አያገባህም። አርፈህ መርፌህን ብትወጋ ይሻልሀል። የቤቴን ችግር የማውቀው እኔ ነኝ› እያለ ነበር።

የመኝታ ክፍሏ በር ተከፍቶ ሰማይነህና ሐኪሙ ሲገቡ ህይወት የመጣውን ሰው ለማወቅ ከአንገቷ ቀና አለች። ጎርፉና እናቱ አጠገቧ ቆመዋል፤ አሁን ደግሞ ሰማይነህና ሐኪሙ ተጨመሩ። ጎርፉ ገብቶ ሁኔታዋን ሲመለከት ትንሽ እንኳ ያለ መንደንገጡና ያለ ማዘኑ ህይወትን በጣም አስገርሚታል። ጭራሹን ሰብአዊነት የጎደለው ፍጡር አድርጋ ከብዷታል። በር በተከፈተ ቁጥር ልቧ የሚጓጓውና ዓይኖቿ የሚጠብቁት የመደምደሚያን መምጣት ነበር። ዓይቷት ሊደነግጥ፣ ሊያዝንና ቅሬታዋን ከገፅዋ ላይ ሊያነብ የሚችል ሰው መደምደሚያ ብቻ ነው።

«እስኪ እናንተ ዘወር በሉ። ከዚህ ክፍል ውጡልን» አላቸው ሐኪሙ ወደ ህይወት ቀርቦ አገጯን እየደባበሰና አፏን አስከፍቶ ጥርሶቿን እየተመለከተ።

ሰማይነህ ብቻ እዚያው ሲቀር እናቱና ወንድሙ በታዘዙት መሠረት ወጡ።

«አንድ ጥርሷ ተነቃንቋል - መነቀል ይኖርበታል» አለ ሐኪሙ ደሙን እየጠራረገና በአልኮል እያጠበ።

«እንግዲህ ምን ይደረግ.....ይነቀልና ወርቅ እናስተክልላታለን። «ሰማይነህ በችግሩ መክበድ አዘነ።

ህይወት አፍዋ በሐኪሙ ተይዞባታል እንጂ ‹ያንተ ወርቅ ገደል ይግባ! ጥርሴን እንዳወለቅክ ልብህን አወልቅልሀለሁ› ማለት ፈልጋ ነበር።

«.....እንዴት እንዲህ ጨከንክባት እባክህ!.....ልጅቷ እንኳ የሚጨከንባት አይነት አይደለችም። እንኳንስ ሊመቷት ቀርቶ ሊነኳት የምታሳሳ ቆንጆ ናት» እያለ ሐኪሙ ቀላለደ።

ሰማይነህ የማይወደው እንዲህ አይነቱን ቀልድ ነው። ‹ይቺ ማደናነቅ ያለ ምክንያት አልመጣችም› አለ በልቡ። ስሜቱ እየተቆጣ መጥቶ ሐኪሙን ስለጠመደው ቶሎ ህክምናውን ጨርሶ ከቤቱ እንዲወጣለት ተመኘ።

«በአስቸኳይ ወደ ጥርስ ሐኪም መሄድ አለባት።.....እስከዚያው ድረስ ህመሙ እንዳያሰቃያት የማደንዘዣ መርፌ እወጋታለሁ» ብሎ ሐኪሙ መርፌውን አውጥቶ መድሐኒቱን ቀመመ።

«ምኗ ላይ እንው የምትወጋት?» አለው ሰማይነህ፣ ቀናተኛ ስሜቱ የህይወትን ገላ ላለማስነካት ከውስጡ እየታገለው።

«ታፋዋ ላይ ነዋ....»

«.....በሌላ ቦታ መስጠት አይቻልም?»

«አመቺው ቦታ ታፋዋ ነው» ብሎ ሐኪሙ በሙያው ስለገባበት እንደ መቆጣት አደረገው።

ለእሱ የዘወትር ስራው ስለሆነ ምንም አልመሰለውም። በርግጥ የሚስቶቻቸው ቀሚስ ተገልቦ ታፋቸው ሲታይባቸው የማይወዱ፣ ሐኪሞችን በጥርጣሬ ዓይን እየተከታተሉ ነፍስና ስጋቸው የሚሟገት፣ ‹አምሮት ከዓይን ይጀምራል› ብለው የሚፈሩ አንዳንድ ባሎች ይኖራሉ። ሆኖም ሰማይነህን በዚህ ደረጃ አልገመተውም።

«.....በክንዷ በኩል ብትሰጣት ምናለበት?»

«ከትባት አይደለም እኮ የምወጋት።»

«አአይ.....ቀሚስ ከመግለብ ይሻላል ብዬ ነው» በማለት ዕቅጩን ነገረው።

«ምነው?.....የውስጥ ሱሪ አላደረገችም እንዴ?»

«ኧረ አድርጌያለሁ» አለች ህይወት በደከመ ድምፅ። ገላዋ በሐኪሙ እጅ በመነካቱ ሰማይነህ መብሸቁን ገምታለች። ህመምና ንዴት ባይጫጫናት ኖሮ ሳቋን በለቀቀችው ነበር። ‹ጥርሴን አውልቆ አስተኝቶኝ፣ አሁንም ገና በገላዬ ይቀናል እንዴ? ምን ጉድ ነው ፈጣሪዬ!› እያለች ነበር በሆዷ።

«ታዲያ ምንድነው ችግሩ?!.....የምትፍር ከሆነ ዓይነህን መጨፈን ወይንም ከክፍሉ መውጣት ትችላለህ» አለው ሐኪሙ በምፀት ድምፅ። ነገሩ ቢገባውም እንዲህ በተራ ነገር በመጠርጠሩ እልህ የያዘው ይመስል።

ሰማይነህ በልቡ ‹አይንህ ይውጣ!› አለና ብሽቀቱን ሳይደብቅ «አንተ ያላፈርክ....እኔ ባሏ ማ እንዴት አፍራለሁ!» አለው።

ሐኪሙ በሽቆ ‹እንደዚህ ትንሽ ሰው ነህ እንዴ?.....ምነው ቀለልክብኝ!› ሊለው ፈልጎ ነበር። ሆኖም የረዥም ጊዜ ወዳጅነታቸውን በማሰብ በትዕግሥት ማሳለፉን መረጠ። ህክምናውንም ትቶ ቢሄድ የምትጎዳው ህይወት መሆኗን በማመዛዘን ቻለው። ‹ጥርሷንም ያወለቃት በቅናት መሆን አለበት፤ አሁን ደግሞ ዓይኗን እንዳያጠፋት ያሰጋል እያለ በሆዱ የንዴቱን አጉመተመተ።

«አዬዬዬ!.....ምነው ጃል!.....እንዲህ በዋዛ......» ብሎ ንዴቱን ለመሸፈን እየቀላለደ የህይወትን ቀሚስ ወደ ላይ ሰብሰብ አድርጎ መርፌውን ታፋዋ ላይ ወጋት። ‹እንግዲህ ይኼውልኽ፤ ታብድም እንደሆነ ይለይልህ› የሚል ይመስል ነበር፤ ሁኔታው።

ሐኪሙ ዕቃውን ሰብስቦ ለመሔድ ሲነሳ፣ ሰማይነህ ከኪሱ የመቶ ብር ኖት አውጥቶ «ሒሳብህ ስንት ነው?» ስላለው ተናደደ። ከአሁን በፊት ግንኙነታቸው በዚህ ዓይነት አልነበረም። አሁን ቤቱ ድረስ መጥቶ ያከመለት በወዳጅነት እንጂ በገንዘብ አይደለም። ገንዘብ መክፈል ቢኖርበት እንኳ በዚህ ሁኔታ ሳይሆን ስነ ሥርዓት ባለው መንገድ ነበር። ንቀቱ አናደደው።

«እሱን አንተ ራስህ ታከምበት» አለው ትዕግሥቱን ጨርሶ።

«እኔ ምን ሆኜያለሁ?....»

«ተመርመር። ጤነኛ አልመሰልከኝም። የህመምህን ዓይነት ሐኪሞች ይነግሩሀል» ብሎት ጥሎት ወጣ።

# ክፍል ስድስት

ሰማይነህ ያን ዕለት ማታ በቀጥታ ወደ ወ/ሮ ስራሽ ቤት ሄደ። ከህይወት ጋር የመረረ ፀብ ላይ ደርሰው ቤቱ ከመቀጣጠሉ በፊት የእሳት አደጋ መከላከያዎችን በተጠንቀቅ ማቆም እንዳለበት ያውቃል። ወ/ሮ ስራሽን የፈለጋት ለዚሁ ጉዳይ ነው። በጓሮ በኩል ገብቶ ሊያስጠራት ፈልጎ ነበር። ወዲያው ደግሞ ውስኪ ቤቷ ገባ። ለንግድ እንቅስቃሴ የሚፈላለጉ ሰዎች እዚያ እየመጡ ስለሚያመሹ ምናልባት ከሚፈልገው ሰው ጋር የመገናኘቱን ዕድል ለመጠቀምም አዕምሮው አስቧል።

ወ/ሮ ስራሽ አማቿን በደመቀ ፈገግታ ተቀብላ አስተናገደችው። ከወትሮው ደንበኞቿ ውስጥ ባህሩ ፂሞ እና አቡበከር ደሜ ብቻ ነበሩ። ሌሎቹ ጠጪዎች ከሰማይነህ ጋር በርቀት የሚተዋወቁና ከአንገት ሠላምታ ያላለፈ ግንኙነት የነበራቸው ናቸው። የህይወት ማግባት በወ/ሮ ስራሽ ውስኪ ቤት ንግድ ላይ መጠነኛ ትፅዕኖ ቢኖረውም የተፈራውን ያህል ጭር አላደረጋትም። ደንበኞቿ አይናቸውን ማረፊያ ቢያጡም ቤቷን የንግድና የነጋዴ መገናኛ አድርገው ስለወሰዱላት አልጠፋባትም።

«ህይወቴ እንዴት ናት?» አለችው ወ/ሮ ስራሽ ለሰማይነህ ውስኪ ቀድታለት ካስተናገደችው በኋላ።

«ደህና ናት» አለ ሰማይነህ ሁሉንም ነገር ሸፋፍኖ።

«የወይን ጠርሙስ እንዴት ነች?» አለው ባህሩ ፂሞ መለኪያውን እንደጨበጠ በማሾፍ ዓይነት።

«የምን ወይን?» አለ ሰማይነህ ግር ብሎት።

«ቻርለስ በድሌር እንደሚለው ‹ፍቅረኛ ጠርሙስ ሙሉ ወይን ስትሆን ሚስት ግን የወይን ጠርሙሰ ነች።»

«አይ!....ይህን መራቀቅህን ወዲያ ብትተወው ምን አለበት አለችው ወ/ሮ ስራሽ በሰለቸ ድምፅ» ደግሞም የኔ ልጅ ምንጊዜም የወይን ጠርሙስ ልትሆን አትችልም።.....ሁልጊዜ ሙሉ ወይን ናት።

«ባልየው ይናገር እንጂ.....ስለ ጣዕሟ አንቺ ምን ታውቂያለሽ?» አላት አቡበከር ሰማይነህን እንደመልከፍ አፉን አጣሞ።

«ከወንደላጤዎች ጋር ለመነጋገር ደረጃዬ አይፈቅድልኝም» በማለት ሰማይነህ ኩራቱን አሳየ።

«ይልቅ ያ ጓደኛህ ዛሬ የት ሄደ? ብቸኛ አድርጎህል።»

አቡበከርና ይትባረክ አብዛኛውን ጊዜ ስለማይለያዩ ማንም ሰው ቢሆን አንዳቸውን ሲያይ ሌላኛውን መጠየቁ አይቀርም።

«ሚስቱ ተቆጣችው። ከእኔና ከእሷ እንዲመርጥ ነገረችው። የማግባት ችግሩ እዚህ ላይ ነው፤ ፀሐይ ሳትጠልቅ ቤቱ እየገባ ድስት ማማሰል ሳይጀምር አልቀረም።»

«ልክ ነውና!.....የዕኩልነት ዘመን ነው» አለች ወ/ሮ ስራሽ ጣልቃ ገብታ።

«ሞኝ አትሁኚ። ወንዶች ሁሉ በጊዜ ወደ ቤታቸው ከገቡ ያንቺ ውስኪ ቤት ማን ያሞቅልሻል?!»

«ግዴለም። ለእኔም እግዜር አለኝ።>

«ሳሙኤል በትለር እንደሚለው ‹እግዚአብሔር ሴትን የፈጠረው ለወንድ ረዳት አድርጎ ከሆነ፣ ለወንድ ልጅ ያለው አመለካከት በጣም ደካማ ነበር ማለት ነው» አለና ባህሩ ፂሞ ደብለቅ አደረገ።

ሰማይነህ ሁሉም በሙሉ ልብ አልተከታተላቸውም። ሀሳቡ በሌላ ነገር ተወጥሮ ስሜቱ ወ/ሮ ስራሽን ለብቻዋ ለማነጋገር ተቻኩሏል። አጠጣጡ መቻኮሉን ያስታውቅበታል።

«......ትዳር የተስማማህ ትመስላለህ። ሚስትህ በደንብ ሳይትዝህ አልቀረችም» በማለት አቡበከር ጎተጎተው።

«አግባና ሞክረዋ!» ሰማይነህም አጭር የመስላቸት መልስ ሰጠው።

«ቆንጆ ሴት አጥቼ ነው እኮ!.....አንዲት ቆንጆ እዚህ ቤት ብትኖር አንተው ወሰድካት።»

ሰማይነህ መብሸቅ ጀመረ። ይሄ በነገር መነካካት አላማረውም።

«ይቅርታህን.....ጨዋታህን ብትቀይር ይሻላል» አለው በጎረና ድምፅ።

«ምነው?....አሁንም ትቀናለህ እንዴ?.....አግብተህት የግልህ አድርገሀታል እኮ!»

«በሚስቱ የማይቀና ባል ወንድ አይደለም!....ይልቅ አሁን አትነጅሰኝ!» አለውና ውስኪውን ጨልጦ በልቡ ‹ነጃሳ› እያለ ወ/ሮ ስራሽን አስከትሏት ወደ ጓደ ሄደ። ለጥብቅ ጉዳይ እንደሚፈልጋት ሲነግራት በምትኳ ደምበኞቿን እንድታስተናግድላት ሠራተኞችዋን ወክላት ከሰማይነህ ጋር ወደ ዋናው ቤት ሳሎን ገቡ።

«ለሁለት ነገሮች ነው የፈለግኩሽ.....» ብሎ እጁን ወደኪሱ ሲሰድ የወ/ሮ ስራሽ ልብ ተሰቀለች።

«.....ምንና ምን ይሆን አምላኬ?› አለች በልቧ።

የወርቅ ማስቀመጫ ባለፈር ፓኮ ከኪሱ አውጥቶ በስጦታ እጁን ሲዘረጋላት ‹እንደጠረጠርኩት ወርቅ አመጣልኝ› ብላ ወከክ አለች።

«እሱን ላንቺ ነው ያመጣሁት፤ ለልጅሽም ሌላ አሰርቼላታለሁ።»

በጉጉት ከፍታ ተመለከተችው። መቶ ግራም ያህል የሚመዘን የእጅ አምባር ነው፤ የወርቅ ስጦታ።

«እግዚአብሔር ይስጥልኝ!.....እግዚአብሔር ያክብርልኝ» ብላ ከአንገቷ ዝቅ እያለች ምስጋናዋን ከደረደረች በኋላ «እንዲያው ምን አሳሰበህ የኔ ጌታ?» አለችው ለመግደርደር ያህል።

«ዛሬ አይደለም ያሰብኩት፤ በትዕዛዝ ካሰራሁልሽ አንኳ ቆይቷል። እየዘነጋሁት ሳላመጣልሽ ብዙ ቀናት አለፉ» አላት ውሸቱን።»

ዛሬ የመጣው ለሌላ ጉዳይ ነው። የወርቅ ስጦታውን ያበረከተላት ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ምክንያት እንዳይመሰልበት መሞከሩ ነው። ወ/ሮ ስራሽ ደግሞ እንኳንስ ይችን ታህል ብልጠት ‹የዝንብ ሽውርራ› አውቃለሁ የምትል ናት።

ከተቀመጠችበት ተነስታ ሰማይነህን እንደ እናት እየሳመችው በወጣ ይተካእብት! ብድርህን የሚከፍል ልጅ ይሰጥህ.....በሀብት ላይ ሀብት ይጨምርልህ» በማለት እንደገና በምርቃት አምበሸበሸችው።

«ይህች ምን አላት ብለሽ ነው! ሰው ለወደደው ብዙ ያደርጋል። ከእንግዲህ እኮ ተሳስረናል.....» አላት ኮራ ብሎ።

‹ሁለተኛውም ስጦታ ይሆን?....ወይንስ ምን ይሆን አምላኬ?› እያለች እሷ አንዱን ጨርሳ ሁለተኛውን ጉዳይ ለማወቅ ልቧ ተሰቅሏል።› አንዱን ድርጅቴን በልጅሽ ስም አድርጌዋለሁ ሊለኝ ይሆን?.....ወርቅ ቤቱን ራሱን በልጄ ስም አድርጎላት ይሆን?.....ወይንስ እኔን በታዛቢነት አቁሞ ሊያደርግላት ያሰበው አንድ ትልቅ ነገር ይኖር ይሆን?....የወደደና ያበደ እኮ የሚያደርገውን አያውቅም....›

ክፉ - ክፉውን ማሰብ አልፈለገችም። ‹ከልጄ ጋር ፀብ ወይም ፍቺ ቢያስብ ኖሮ ወርቅ አያመልጠኝም ነበር› ብላ ተፅናንታለች።

«.....ሁለተኛው የመጣሁበት ጉዳይ ህይወትን በተመለከተ ነው» አላት በረዥሙ ተንፍሶ።

አተነፋፈሱ አላማራትም። ግንባሩም እየተኮሳተረ መጥቷል።

‹.....አደራህን፤ ክፉ እንገር አታሰማኝ› ብላ በልቧ ፈጣሪዋን ለመነች።

«ከህይወት ጋር መጠነኛ ግጭት ተፈጥሯል። ዛሬ ጠዋት ከመርካቶ ስንወጣ በሆነ ነገር ተጋጭተን እጇን እንደዋዛ ስሰነዝር ጥርሷን መትቻት.....»

«ውይ አፈር በሆንኩት!.....ጥርሷ ተጎዳ?»

«አንድ ጥርሷ ወልቋል.....ሌሎቹ ደህና ናቸው።»

«አዩ! ምነው ልጄ!....እጅህ እንዴት እንዲህ ጨከነባት?....ከሆነም ደግሞ እንደ ልጅነቷ መጠን ወደ ጭኖቿ መሀል ጣትህን አስገብተህ ለምዘግ ነው እንጂ ፊቷ ላይ እንዴት ትሰነዝራለህ?» አለችው ሳትቆታ ድምጿን ለስለስ አድርጋ።

በልጇ ጥርስ መውለቅ ማዘኗ አልቀረም። ሆኖም ሰማይነህን ማስቀየሙ ደግሞ «ትርፍ» የለውም ብላ አሰበች። የወርቅ ስጦታውም አፍ ማስያዣ መሆኑን ወዲያው ተረዳች።

«....ያን ያህል ይጎዳታል ብዬ አላሰብኩም። ድንገት ነው የሰነዘርኩት።.....ሠይጣን በመሀላችን ገብቶ መሆን አለበት።»

«ልክ ነህ.....እሱስ ሰይጣን በሰው እጅ የሚፈፅመው ተንኮል ነው....አሁን ታዲያ በምን ሁኔታ ላይ ትገኛለች?»

«በቂ ህክምና ተደርጎላት ወደ ቤቷ ተመልሳለች። ያው የተነቃነቀው ጥርሷ ወልቋል። ......ሰሞኑን በወርቅ ጥርስ ይተካላታል።»

«ለመሆኑ ምን አለች?....ወይ ልጄን!....መቼም ላቅሳ አታባራም።»

«አዎ፤ ትንሽ ስሜቷ ተጎድቷል። ያዘነች ትመስላለች። ለጊዜው መጥፎ ነገር እንዳታስብ ቤተሰቦቼ እንዲጠብቋት አድርጌያለሁ። አንቺም ስልክ ደውይና አፅናኚያት።»

«የምን ስልክ!.....ኧረ አሁኑኑ ሄጄ አያታለሁ። ልጄም አይደለችም እንዴ?!»

«ግዴለሽም፤ ነገ ሄደሽ ብታያት ይሻላል። ብስጭቷም በረድ ብሎላት ይደር። አሁን ስታይሽ የባሰ ሆድ ሊብሳት ይችላል። ጉዳቷ ይሰማኛል፤ አንዴ በመሆኑ ምንም ማድረግ አይቻልም። የምትወደውን ዓይነት የወርቅ ጌጥ አሰርቼ ካሳ እከፍላታለሁ።»

ወ/ሮ ስራሽ ወዲያውኑ ስልኩን አንስታ ደወለችላት። ሆኖም የሰማይነህ ቤተሰቦች ህይወትን ሊያገናኟት አልፈለጉም። ሰማይነህ ራሱ አጠገቧ መሆኑን በስልክ ካረጋገጠላቸው እብኋላ ልጇን አገናኟት።

«ህይወቴ....እናትሽ ነኝ....አሁን ገና ነው እኮ የሰማሁት ለመሆኑ ተርፈሻል?» አለቻት፤ ‹አይዞሽ ደርሼልሻለሁ› በሚል ዓይነት የማስተዛዘን የድምፅ ቅላፄ።

«....ምንም አልተረፍኩም።.....ቶሎ ድረሽልኝና ከዚህ ጉድ ውስጥ አውጭኝ!.....ከዚህ የሰቀቀን ኑሮ አድኚኝ። አልፈልግም፤ በቃኝ፤ ህሊናዬ ቆስሏል።»

ህይወት በህመምተኛ ድምፅ እያቃሰተችና እየታገለች ይህን ሀይለ ቃል ስትናገር የሰማይነህ እናትና ወንድምየው ጎርፉ አጠገቧ እየተንጎራደዱ በዓይናቸው ይገረምሟታል፡፡ እሷ ግን ዕልህ ሰልተናነቃት የእነሱን ግርመማ ከቁብም አልቆጠረችው፡፡ የአቅሟ መድከም ነው እንጂ እንዲያውም የስልኩን እጀታ አስቀምጣ ‹ምናባታችሁ ትከታተሉኛላችሁ! ሁላችሁንም አልፈልጋችሁም፤ ቤታችሁንም አልፈግላችሁም! ሌላ የምትሰሙት አዲስ ነገር የለም፡፡ ይኼው ነው› ማለት አምሯት ነበር፡፡

«ቆይ እስቲ ረጋ በይ ህይወቴ.....አይዞሽ አትበሳጪ፡፡ መጀመሪያ ህመምሽን አስታሚው፡፡»

«ት - ት ትዕግሥቴ አልቋል ነው የምልሽ እማዬ፡፡ እዚህ ቤት ውስጥ መኖር አልፈልግም፡፡ ጠፍቼ እንዳመጣ አቅም አጥቼ ነው፡፡ የቁም እስረኛ አድርገውኝ ዙሪያዬን ከብበው እየጠበቁኝ ነው፡፡ በዚህ ምድር ላይ ያለሽኝ ዘመድ አንቺ ብቻ ነሽ አማዬ፡፡ ቶሎ ድረሺና ውሰጂኝ፡፡»

ወ/ሮ ስራሽ በርግጥም አዘነች፡፡ በህይወት አነጋገር ሆዷ ባባ፡፡ ሆኖም ሰማይነህ ፊት - ለፊቷ ተቀምጧል፤ ያመጣላት የወርቅ አምባር አጠገቧ ጠረጴዛው ላይ አፍጥጧል፡፡ ስሜቷ በሰማይነህ ወርቁ ተጠፍንጎ ስለ ታሰረ የእናትነት ቢቀር የአክስትነት ጥልቅ ሐዘኗን እንኳ ልትገልፅላት አልቻለችም፡፡

«....የምትይው ይገባኛል ህይወቴ፡፡.....ሆኖም መታገስ ይኖርብሻል፡፡.....ሁሉም ያልፋል.....ሰይጣን መሀላችሁ ገብቶ ነው እንጂ ሰማይነህ ይህን ያህል ሊጎዳሽ እንዳለሰበ ነግሮኛል፡፡ በስህተቱ በጣም አዝኗል፡፡ የምትፈልጊውን አይነት ወርቅ አሰርቶ ካሳ እንደሚከፍልሽ ቃል ገብቶልኛል፡፡»

«የእነሱን ካሳ አልፈልግም፡፡ ወርቁም ይቅርብኝ፡፡ እኔን ብቻ በሰላም ይልቀቀኝ፡፡ በፍፁም ከእሱ ጋር አብረን መኖር አንችልም፡፡»

«ቆይ እስቲ አሁን ለውሳኔ አትቸኩይ፤ መጀመሪያ ህመምሽን አስታሚው ነው እኮ የምልሽ፡፡ ሁሉም ነገር ከአንቺ ጤንነት በኋላ ይደርሳል፡፡ በጋራ እንመክርበታለን፡፡.....ሁሉም ጥርስሽ የወለቀበት ቦታ እንዴት ነው? ይጠዘጥዝሻል?....»

«ከጥርሴ ይልቅ የልቤ ቁስል ነው እንቅልፍ የነሳኝ፡፡ አልቻልኩም ነው የምልሽ! ሲኦል ውስጥ ያእልሁ ነው የሚመስለኝ!»

ጎርፉ ህይወት የተናገረችውን በሙሉ ለሰማይነህ እንዴት አድርጎ ቀምሞ እንደሚያቀርብለት እያሰላሰለ፣ ስራዬ ብሎ ጆሮውን ጥሎ ያዳምጣት ነበር፡፡ ይሉኝታ ማጣቱ ህይወትን በጣም አናደዳት፡፡

«.....ሰው እንዴት ከብት ሆኖ ይፈጠራል?! ቆሞ የሚሄድ ከብት!» ኧልችው፡፡

ይህን የተናገረችው የስልኩን እጀታ እንደያዘች ስለ ነበረ ጎርፉ እሱን የሰደበችው አልመሰለውም፡፡ የስልኩ ንግግር ክፍል መስልት፡፡ ዝም ብሎ መዘገበ፡፡

ወ/ሮ ስራሽ ራሷ የህይወት ንግግር ከአርዕስታቸው ውጭ ስለሆነባት ግራ ተጋባች፡፡ በንዴት ሰማይነህን መሳደቧ መስሏት እሱ ፊት «ከብት» የሚለውን ቃል ላለመድገም አደባብሳ አለፈችው፡፡

«.....እንዲህ አታምርሪ ነው የምልሽ ህይወቴ፤ ደግሞ አይደል፡፡ ለዚያውስ በዛሬ ዘመን ደብድቦ ከቤት የሚያስወጣ እንጂ ካሳ የሚያቀርብ ባል የት ይገኛል?! አንቺ ብዙውን ነገር ገና ስላልደረስሽበት ነው.....ለማንኛውም አሁን መሽቷል፤ ጠዋት ወፍ ሳይንጫጫ እመጣልሻለሁ.....አጥሚትና ጭማቂ አዘጋጅቼ ይዤልሽ እመጣለሁ፡፡ አይዞሽ የኔ ቆንጆ....»

ህይወት በንዴት ስልኩን ጆሮዋ ላይ ዘጋችባት፡፡

«….ውይ! ዘጋችው እንዴ?….እንዴት ቀበጠች እባካችሁ አለች ወ/ሮ ስራሽ በብሽቀት የስልኩን እጀታ ከቦታው እየመለሰች።

ሰማይነህ ለብሶቱ መንደርደሪያ አገኘ።

«ይኸውልሻ!….ስልኩን ጆሮሽ ላይ ዘጋችው አይደል!…ልጅቷ ኃይለኛ ትዕቢት አለባት። ገና በለጋ እድሜዋ በወበቷ ከፉኛ መመካት የጀመረች ይመስለኛል። ባህሩ ዒሞ የነገረኝ አንድ የጣሊያኖች አባባል ትዝ ይለናል። ‹ለሴት ልጅ ቁንጅናዋን ንገራት፤ ሰይታን ደግሞ አሥር ጊዜ ያህል ይህንኑ ይደጋግምላታል› ብሎኝ ነበር።»

«ውበት አላፊ ረጋፊ ነው። ምን ዋጋ አለው? አይምሰልህ፤ ህይወቴን የሚፈታተናት ልጅነት ነው።…»

«ከሀያ አመት እኋላ ልጅነት አይገባኝም። አንዳንድ ሁኔታዎቿን ስመለከት ሆነ - ብላ እኔን ለማስቀናትና ለማናደድ የምታደርግ ይመስለኛል።»

«አልኩት እኮ!…..እንደ ልጆች እንቁልጭልጮ ጨዋታ መሆኑ ነው። ብስለት ማጣት ማለት ታዲያ ይሄው አደል!….ለማንኛውም አሁን አንድ ልጅ ስትወልድ ትበስላለች። ልጅነቷን ጨርሳ እናት ትሆናለች። የልጇ እናት፣ የአንተ ሚስት መሆኗን መጠን ቶሎ ፍሬ መያዝ ነበረባት።

«…..አውቃ ሊሆን ይችላል። ላለመውለድ በድብቅ መድሐኒት እየተጠመቀች ይሆናል» በማለት ሰማይነህ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ጥርጣሬውን ነገራት።

«ምናባቷ ቆርጧት!…..ደግሞ አንተን ከመሰለ ፀባየ - ሸጋ ባለ ፀጋ ፍሬ ግንኙነት ትጠላለች እንዴ?….አይመስለኝም….ለማንኛውም እኔ ራሴ እጠይቃታለሁ» ስትለው «አስፈፅምልሀለሁ» የማለት ያህል ኩራት ተሰምቷት እሱንም አኮራችው።

# ክፍል ሰባት

በህይወት ላይ ቁስሉ አልጠነከረበትም። ከአስር ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከህመሟ ድና፣ ከአልጋዋ ተነታ፣ የወርቅ ጥርስ ተተክሎላታል። በእርግጥ ይህ የሆነው መደምደሚያ በሙሉ ስሜትና ርህራሄ ከጎኗ ቆሞ እያፅናናት ህክምናዋን በአግባቡ መከታተል በመቻሏ ነው። «…..ሳይደግስ አይጣላም» እንደሚባለው በሰይጣኖች በተከበበችበት እዚያ ግቢ ውስጥ እንደ መልአክ የምታየው መደምደሚያ መፅናኛ ሆኗታል። አንጀቷ እያረረ ቤቷን ትለሽው ብረሪ ብረሪ የሚል ስሜት ይፈታተናትና መደምደሚያ አጠገቧ መኖሩን ስትመለከት ተፅናንታ ትረግባለች። ከታመመች ጀምሮ ከአጠገቧ ሳይለያት ነው የከረመው።

ወ/ሮ ስራሽም በተከታታይ እየመጣች ስታስታምማትና ስትመክራት ሰንብታለች። በመታችባቸው ቀናት ሁሉ የተለመደ ደረቅ ምክሯን ሳታዝጎደጉድላት ተመልሳ አታውቅም። አነጋገሯና ምክር አስጣጧ በህይወት አዕምሮ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ቀላል አልሆነም። መጀመሪያ ፊት ሆኖ ሌላ የማግባትን የደረጃ ችግር እንደነገረቻት ሁሉ፤ አሁን ደግሞ የወለቀ ጥርሷን በማስመልከት እንደነገረቻት ሁሉ፣ አሁን ደግሞ ነገር አዕምሮዋ ውስጥ ተቀርጿል። ታዲያስ! የተፈጥሮ ጥርስሽን አጥተሽ አካለ ስንኩል ሆነሽ፣ ቤቱን ጥለሽለት የምትሄጂው ለማን ጀቴ ብለሽ ነው! አርፈሽ ተቀመጪ። ካሳሽን ከፍሎ የንብረት ባለቤትነትሽን ያረጋግጥልሻል» ነበር ያለቻት። በእንዲህ አየንቱ አስተሳሰብ የህይወትን አዕምሮ ደጋግማ ተብትባ፣ የተዘጋጀላትን የወርቅ ካሳ አቅርባ

ከሰማይነህ ጋር ያስታረቀቻትም ሌላ ሰው ሳይጨመር ወ/ሮ ስራሽ ብቻዋን ነው። የመጨረሻ ንግግሯ»……ፀባችሁን የሰይጣን ጆሮ አይስማው» የሚል ነበር።

ህይወት ግን የጥርሷ ቁስል ቢድንም የልቧ ቁስል አልዳነም። ገና በሙሽርነት ወራቷ በዱላ መደፈሯ አናድዷታል። በሚረባው በማይረባውም በቅናት ከሚብከነከን ባልና በጭፍን ከሚተጋገዝ ቤተሰብ ጋር እስከ መቼ ድረስ እንደምትኖር ግራ ገብቷታል። አንድ የተፈጥሮ ጥርሷን አጥታ በወርቅ ትርስ ማስተካቷ ውስጥ - ውስጡን አቃጥሏታል።

ደጋግማ እንዳደረገችው ሁሉ አሁንም ከነፒጃማዋ ድንገት ከአልጋዋ ላይ ወርዳ የመልበሻው መስታወት አጠገብ ቆመችና የወርቅ ጥርሷን መመልከት ጀመረች። ከወበትዋ ላይ የጎደለ ነገር ታያት። እንደ መሳቅ ብላ ጥርሶችዋን ሙሉ በሙሉ ስትከፍት በወርቅ የተተካው ቦታ ከሌሎች ልዩነት ፈጥሮ ሌላ ሰው አስመሰላት። የህይወት አንዱ ውበትዋ ፈገግታዋ ሳቋ ነበር። አሁን ግን ወርቁ ጥርሷ በቀድሞ ሳቋና ውበትዋ ላይ እንከን መፍጠሩን አየች። እንዲያውም ወርቁን ለመደበቅ ጥርሷን መከደኑ እንደሚሻላት በመስታወት ላይ ካደረገችው ልምምድ ተረዳች። ‹ለነገሩ ከእንግዲህ በኋላ ምን የሚያስቅ ነገር ይኖራል? አንሰቅስቆ የሚያስለቅስ መራራ ህይወት ነው ከፊቴ የተረጋገጠው› ስትል አሰበች «…..አካለ ስንኩ ሆነሻል» ያለቻት ትዝ አላትና ፊቷን አጨፈገገችው። አሁን ሳትወድ በግዷ ጥርሷን ልትከድን ነው። ሰማይነህም የሚፈልገው ይህንኑ ነበር። ባላሰበው መንገድ ምኖቱ ተሳካለት። ህይወትም የባሏን ፈቃድ ለመፈፀም የሞቱት እናትና አባቷን እያስታወሰች ማዘን ወይንም የልጅነት ፍቅረኛዋን ሄኖክን እያሰበች መተከዝ አያስፈልጋትም። ጥርስ መከደኑም ሆነ ትካዜው በራሱ መንገድ እየመጣ ነው። ለመሳቅ ብትሞክር እንኳ እንጀቷ እያረረ የማሽላ ሳቅ ነው።

የወርቅ ጥርሷን ገምግማ ከመስታወቱ ስትመለስ ለጉዳቷ የተከፈላት ካሳ ታወሳትና ሳጥኗን ከፍታ አወጣችው። ወ/ሮ ስራሽ ከሰማይነህ ጋር አስታርቃት ስጦታውን ሲያበረክትላት ላይ - ላዩን ብትታረቅም ውስጧ እየተቃጠለ ስለ ነበር ስጦታው ወርቅ ከመሆኑ በቀር ምን ዓይነት እንደሆነ ከፍታ የማየት ጉጉት አልነበራትም። እንደተቀበለችው ሳጥኗ ውስጥ አስቀመጠችው። ከዚያም በኋላ ውስጣዊ ህመሟን ማስታመም እንጂ ሰለ ውጪያዊ ጌጥ የምታስብበትም ሆነ የምትጓዝበት ጊዜ አልነበራትም። አሁን የወርቁን ፓኮ ‹ከፍታ ስትመለከተው ተገረመች። ልብስ ሰፊው ቤት ከመሄዳቸው በፊት ሰማይነህ ወርቅ ቤት ውስጥ ቆመው በእጁ አንስታ ያየችውና የወደደችው ባለ ልብ ቅርፅ የአንገት ሀብል ነው «…..አንጀት ሊበላ?» አለች በንዴት። ሆኖም የያዘችው ወርቅ ልቧን መሳቡ አልቀረም። ‹ምን ዋጋ አለው?!…..የዚህን ጌጥ ፍላጎቴን የተረዳልኝን ያህል ውስጣዊ ስሜቴን ቢረዳልኝና እኔነቴን ቢያከርብርልኝ ጥሩ ነበር። የእኔነቴን ቢያከብርልኝ ጥሩ ነበር። የእኔነቴን ነፃነት ባይነፍገኝና መልኬን ለማስለወጥ ባይሞክር ጥሩ ነበር።…..እያቆሰሉ ማከም ምን ዋጋ አለው?!› አለች ለራሷ።

ልቧ ጓጉቶለት የነበረውን ባለ ልብ ቅርፅ የወርቅ ሐብል አንገቷ ላይ አጥልቃ ተመለከተችው፤ ጥሩ ጌጥ ነው፤ የማይወረዛ ሀብትም ነው። እንዲህ እንደ ውጪያዊ ጌጥ የውስጥ ልቧን የሚያደምቅ፣ እንደማይወረዛው ሀብት ልቧን እይሚያበለፅግ ሰው ግን አልገኘችም። አሁም ሁለት ምርጫዎች ዓይናቸውን አፍጥጠው ከፊቷ ቆመዋል። ውስጣዊ ሰላም ወይንም ውጫያዊ ሀብት! ከሁለት አንዱን መምረጥ የግድ ነው።

የወርቅ ማብረቅረቅ ትንሽ እንድትመራመር አደረጋት። ቀድሞ የነበራትንና ለጥሎሽ የመጣላትን የወርቅ ጌጣጌጦች በሙሉ ከሳጥኗ አውጥታ እያቅጨለጨለች ተመለከተቻቸው። አሻንጉሊቱን እንደሚያደንቅ ህፃን ልጅ አተኩራ ተመለከተቻቸው። በወርቅ ሱስ የሠከረችው አክስትዋም ትዝ አለቻት። የወርቅ ሀይል የዋዛ አይደለም፤ የስሜት ንዝረት ይፈጥራል፤ ዓይን ይስባል…..ልብ ይሰልባል……አዕምሮ ያስታል፤ ዓይን ተስቦ፣ ልብ ከተሰለበና አዕምሮ ከሳተ ደግሞ ደደብነት ይከተላል። የወርቅ ጌጦቹ ጆሮ ላይ ተንተልጥለው ጉትቻ ሲሆኑ፣ አንገት ላይ ጠልቀው ሀብል ሲሆኑ፣

እጅ ላይ ታስረው አምባር ሲሆኑ፣ ጣቶች ላይ ተደርድረው ቀለበት ሲሆኑና እግር ላይ ታስረው አልቦ ሲሆኑ ሰውነትን ያደምቃሉ። ሆኖም የደም ስር ሆነው እነዚያን የሰውነት ክፍሎች አይቆጣጠሯቸውም። ሰውና የሰውነቱ ክፍሎች ከሌሉ በስተቀር የወርቅ ጌጦች ጌጥነት አይታወቅም፤ በጌጥነት የሚያርፍበት ቦታ አያገኝም። ሰውነት ይቀድማል፤ ወርቅና በወርቅ የተሸቆጠቆጠ ህይወት ይከተላል። የወርቅ መመዘኛና የሰውነት መመዘኛም ይለያያል። የወርቅ መመዘኛ ከውጭ ነው፤ የሰውነት መመዘኛ ከውስጥ ነው። ወርቅ የሚፈተነው በእሳት ነው፤ ሰውነት የሚፈተነው በህይወት ነው!.....

የመኝታ ቤቷ በር ተንኳኩቶ «መግባት ይቻላል» የሚል ድምፅ ሰማች። ወዲያውም መደምደሚያ ቀጭን ፊቱን አስቀድሞ ፈገግ ለማለት እየሞከረ ገባ። የሰውነት ቅጥነት የሚግላው በፊቱ መቅጠንና በቁመት መርዘም ነው። በልቶ የሚያበድር አይመስልምና። በቀጭን ፊቱ ላይ ትላልቅ ዓይኖቹ ጎልተው ይታያሉ።

«......ግባ የኔ ደንገጡር» አለችው ህይወት ከሀሳቧ ባንና።

«ቁርስ ምን ይዘጋጅልሽ?»

«ይቆየኝ......አሁን ምንም አላማረኝም። መጀመሪያ የጠዋት ፀሐይ መሞቅ እፈልጋለሁ።»

መደምደሚያ ህይወት እጅ ላይ በርካታ የወርቅ ዓይነቶች ሲመለከት ትንሽ ደነገጠ። ‹ወርቆቿን ሰብስባ ልትጠፋ ይሆን?› የሚል ስጋት አደረበት።

«.....ዛሬ ወርቆችሽን ምን ልታደርጊ አወጣሻቸው?» አላት ስጋቱን ደብቆ ፈገግ ለማለት እየሞከረ።

«ልመራመራቸው.....» አለችው።

«ታዲያ ምርምሩ በጠዋቱ ነው እንዴ?»

«አዎ፤ አዕምሮ በቀኑ ግርግር ወይንም በምሽቱ ሽብር ሳይረበሽ በጠዋቱ ማሰብና መመራመር ጥሩ መሆኑን የነገርሽኝ አንተው ነበርክ.....ረሳኸው እንዴ?»

«አልረሳሁትም፤ ልክ ነሽ» አለ መደምደሚያ ጎበዝ ተማሪ እንዳገኘ ሁሉ ልቡ በደስታ እየተሞላ።

የሚነግራትን በጥሞና ስለምታዳምጠው፣ የሚሰጣትን መፅሐፎች በጥንቃቄ አንብባ ስለምትመልስለትና የእሱንም ትምህርት ስለምታደንቅለት ደስ ይለዋል። በአጭር ጊዜ ውስጥ የአስተሳሰብ ብስለት ማሳየቷን ለመገንዘብ በመቻሉ የአዕምሮዋን ብሩህነት እያደነቀ ነው።

«የወርቅን የማብረቅረቅና ልብ የመስለብ ባህሪይ ስመራመር ነበር የቆየሁት» አለች።

«ወርቅ ማለት በቁንጅና ላይ ብሩህ አዕምሮ ሲጨመርበት ነው» ነበር የቆየሁት» አለች።

«ወርቅ ማለት በቁንጅና ላይ ብሩህ አዕምሮ ሲጨመርበት ነው» ብሎ በተዘዋዋሪ ራሷን ገለፀላት።

«እንዴት......እንዴት?»

«በአካልና በአዕም የተዋቡ ሰዎች ወርቅ አያስፈልጋቸውም።»

የሀሳቡ አመጣጥ ደስ ስላላት በውይይት ልትገፋፋው ፈልጋ ነበር፡፡ ሆኖም ለመደምደሚያ ልትነግረው ያስበችውን ነገር የሚያዘናጋት ስለመሰላት ቸል አለችውና በሀሳቧ ወደአንጠለጠለችው ጉዳይ ተሸጋገረች፡፡

«.....የሴት ጠላት ቢኖረው ምን ብዬ እንደምረግማት ታውቃለህ?»

«ምን ብለሽ ትረግሚያለሽ?»

«ወርቅ እየሰጠ የሚደበድብ ባል ይዘዝብሽ! ነው የምላት»

መደምደሚያ ነገሩ ገባውና ሳቀ፡፡ የእሷ ባል የእሱ ወንድም ሰማይነህ በሀሳቡ ብልጭ ብሎ ታየውና «ቀላል ርግማን አይደለም» አላት፡፡

«ሁለተኛው ርግማኔ ደሞ ‹ቀናተኛ ባል ይስጥሽ› የሚል ይሆናል፡፡

«አዎ፤ ሁለቱም.....ምርቃት የሚመስሉ ርግማኖች ናቸው ካላት በኋላ «....ፀሐይ ለመሞቅ ፈልጌያለሁ ብለሽ ነበር፡፡ ለምን ወደ ውጭ አንወጣም?» ሲላት ነገሩ ቶሎ ገባት፡፡

መደምደሚያ ከህይወት ጋር እንዲህ በመቀራረቡ ቤተሰቡ ጠምደውታል፡፡ ቅርበቱን እንዲቀንስና መፅሐፍ እያመጣ ማስነበቡና እንዲያቆም ሰማይነህ ራሱ በግልፅ አስጠንቅቆታል፡፡ አሁንም መኝታ ክፍሏ መቆየቱንና የሰማይነህን ስም ማንሳቱን እንዳልፈለገ ገባት፡፡ ምናልባትም ጎርፉ በሩ ላይ ወይንም ግድግዳው ጥግ ተለጥፎ የሚያወሩትን ያዳምጥ ይሆናል፡፡ መደምደሚያ ዕምነቱን በግልፅ ከመናገር ወደ ኋላ የማይል ሰው ቢሆንም፣ በእሱ ሳቢያ በህይወት ላይ ተፅዕኖ ጭቆና እንዳያበዙባት ይጠነቀቃሉ፡፡

ህይወት ወርቆቿን ወደ ሳጥኗ መልሳ ከመደምደሚያ ጋር የጠዋት ፀሐይ ለመሞቅ ወጡ፡፡ ሀሳባቸውን ያለ ስጋት ለመለዋወጥ እንዲያመቻቸው ከበረንዳው «ይልቅ የአትክልት ቦታውን መረጡ፡፡ ዙሪያውን በጥድ ዛፍ ተከቦ ውስጡ በተለያዩ የአበባ ተክሎች የተዋበው መናፈሻ ዓይናቸውን እየማረከ በጥዑም መዓዛው ተቀበላቸው፡፡

«......የርግማኖችሽ ምንጭና ምክንያት ሰማይነህ መሆኑ ገብቶኛል» አላት መደምደሚያ ቦታ መርጠው ከተቀመጡ በኋላ፡፡

«አዎ፤ እሱ ነው፡፡.....» አለችና ህይወት እንደማዘን ብላ ይገርምሀል መደምደሚያ!.....ከሰማይነ ጋር ከመገናኘቴ በፊት የጠዋት ፀሎቴን ሳደርስ እግዚአብሔር አንድ ነገር እለምነው ነበር፡፡»

»ምንድን እሱ?.....»

«ፈጣሪ አምላኬ ሆይ፤ ውበቴ ሳይረግፍ፣ ወጣትነቴ ሳያልፍ ለትዳር የሚሆን ባል ስጠኝ እያልኩ እለምነው ነበር፡፡.....ይሆን የምለምነው ለምን መሰለህ?......»

«ለ.....ለምንድን ነው?»

«የአክስቴን ምክር እያስታወስኩ ነው፡፡....አክስቴ መሀን ናት በመሀንነቷም ታዝናለች፡፡ በወጣትነት ዘመንዋ ቆንጆ እንደነበረችና ብዙ ወንዶች እንዳፋጁት፣ ብዙ ወንዶች ሊጋብቻ ሲጠይቋት ባለመፈለግ መጠቀሚያ ጊዜዋን እንደዋዛ እንዳሳለፈችና በመጨረሻም ለትዳር የሚፈልጋት ጠፍቶ በብቸኝነት እንደኖረች አዘውትራ ታጫውተኝ ነበር፡፡ እና ሁልጊዜ ወጣትነትና ውበት ኃላፊና ረጋፊ መሆኑን ስለምትመክረኝ በአዕምሮዬ ውስጥ አንዳች ተፅዕኖ አሳድራብኝ ቶሎ ማግባት እንድመኝ አድርጋኛለች፡፡.....»

ህይወት «አክስቴ ስትል ወ/ሮ ስራሽን መሆኑን መደምደሚያ አላወቀም። እሱም እንደማንኛውም ሰው ወ/ሮ ስራሽ የህይወት እናት መሆኗን ነው የሚያውቀው። ህይወት ታሪኳን የምታወራለት አንድ ሌላ መህን አክስት ያላት አድርጎ ወስዶታል። ህይወትም «አክስቴ» ብላ ያወራችው ሳታስበው በስሜት ተመስጣ ቢሆንም፣ መደምደሚያ ሚስጥረኛዋ እየሆነ እንደመምጣቱ መጠን ወደፊት ሚስጥሩን ያውቀዋል በሚል ግምት ነው።

«እ....ሺ?» አለ መደምደሚያ በስሜት እየተሳበ።

«.....አሁን ደግሞ ፀሎቴ እግዚአብሔር ከሰማይነህ እንዲገላግለኝ ነው» አለችና ስሜቱን እያጠናች» መቼም....ወንድሙ ብትሆንም ስሜቴ የሚገባህ ይመስለኛል። ከአንተ የምደብቀው ነገር የለኝም። ሀሳቤን ሳዋይህ የታመቀው ስሜት ይከፈልልኛል» አለችው።

«ልክ ነሽ.....እኔ ለሰማይነህ ወንድሙ ብሆንም አንቺን መሳይ ልጅ ህይወትሽን በስቃይ ኑሮ እንድትገፊ አልፈርድብሽም። ከቶውንም ከሰማይነህ ጋር በምንም መንገድ አትገናኙም።»

«አዎ......ነገር ግን ከሰማይነህ ጋር መፋታትም ቀላል አይሆንም።»

«እንዴት?....»

«እንደኛ ነገር ‹ፈት› የሚለው ቅፅል በሚቀጥለው የባል ምርጫዬ ላይ ተፅዕኖ ያሳድርብኛል፤ ሁለተኛ ነገር ደግሞ ሰማይነህ ጥርሴን አውልቆ አካለ ስንኩል አድርጎኛል። እነዚህ ሁለት ነገሮች ወጥመድ ሆነውብኛል «በማለት የአክስቷን የአስተሳሰብ ተፅዕኖ በቀጥታ አስተጋባች።

«ሁለቱም ነገሮች አንቺነትሽን የሚለውጡ አይመስለኝም።....ቢሆንም እንኳ ወጥመድ ሆነው ቀሪውን ህይወትሽን በእስረኝነት እድንታሳልፊው ማድረግ ያለባቸው አይመስለኝም....»

«እስረኝነቴን የምታውቅልኝ አንተ ብቻ ነህ።....እንዲህ ባማረ ግቢና በተዋበ ቪላ ውስጥ የታሰርኩ ይመስለኛል። ጎርፉ የታሰርኩበትን ሰንሰለት ለማጥበቅ የሚጥር እኩይ ሆኖብኛል። የእናታችሁ ጥቃቅን ድርጊቶች የአሽሙር ንግግራቸው ያስጠላኛል። ሁለቱም ዓይናቸውን ጨፍነው ሰማይነህን ሲደግፉ ይገርመኛል። እኔም ከሰው የተፈጠርኩ መሆኔን እንኳ ይረሱኛል።»

መደምደሚያ ከጎርፉ ጋር እንደማይግባባ ታውቃለች፤ በየአጋጣሚው ሲጋጩም ተመልክታለች። እናቱ ሲዘልፉበት ግን ቅር ይለው ይሆናል ብላ ስሜቱን ለማጥናት ሞከረች። ሆኖም ስሜቱን ከመልሱ አገኘችው።

«በሁለቱም አትፍረጂባቸው። ከእነሱ ከፋትና ፊት መንሳት የሰማይነህ የስሜት ነፀብራቅ ነው። ሁለቱም የእሱን ፊት እያዩ እሱን ሆነው የሚያድሩ ናቸው። ጎርፉ የሆዱ ባሪያ ስለሆነ ህሊና የለውም። እናታችን ደሞ ሰማይነህን በመጀመሪያ ልጅነቱ መውደድ ብቻ ሳይሆን በሀብት አመንጪነቱና ‹ትልቅነቱ› ወደ ማምለክ ደረጃ ደርሳለች ሰማይነህ ከአንቺ ጋር ጤናማ ፍቅር ቢኖረውም የእነሱም አመለካከት ይለወጣል የሚል ዕምነት አለኝ። ጎርፉን ሆዱን እየሞላሽና ማወራረጃውን እየጋትሽ አንቺም ልትገዢው ትችያለሽ።......የችግሩ ቁልፍ ያለው ሰማይነህ ጋ ነው።»

«.....እሱ ግን ምን ሆኖ ነው?» አለች ህይወት የሰማይነህ ሁኔታ ግራ እንዳጋባት በማመልከት»......ድርጊቱ ሁሉ የጤንነት አይመስለኝም።»

«አዎ.....አስቸጋሪ ነው። ምናልባት ሀብት የሚፈጥረው በሽታ ይሆናል። ገንዘብ ከዕውቀት ጋር ሲሆንና ዕውቀቱ ገንዘቡን ሲያዘው ጥሩ ነው፤ ገንቢና ቀና መንገድ የሚከተልም ይሆናል። ገንዘብ ባዶ ጭንቅላት ውስጥ ገብቶ ካዘዘበትና ከፈነጨበት ግን በሽታ ይሆናል፤ አጥፊም ነው። ችግሩ ግን አብዛኛውን ጊዜ ዕውቀትና ገንዘብ አይገናኙም። ይፈራራሉ። ገንዘብ እንዳሻው የሚጨፍርበትንና

የሚያመልከውን የማይማን አዕምሮ ይመርጣል፤ ዕውቀት ደግሞ ድህነትን ተጣብቆ ሲፈላሰፍ ይኖራል። ዋናው ነገር ሰዎች ከሁለቱ በአንደኛው መንገድ የራሳቸውን ደስታ ፈጥረው የራሳቸውን ስካር ሰክረው ይኖራሉ። የሌላውን መብት ሳይነካና ሳይጎዳ ራስን ብቻ የሚያስደስት ስካር ጥሩ ነው። ሌላውን እየጎዳ ደስታ የሚሰጥ ስካር ግን መጥፎ በሽታ ነው።......»

መደምደሚያ ንግግሩን አቋርጦ የህይወቱን ስሜት ለማጥናት ሞከረ። እየተከተለችው ነው። ከመስመሩ ወጥጦ እንዳያዘበራርቅባት እየተጠነቀቀ ወደ ርዕሱ ገባ።

«ሰማይነህ ዕድሜው ያሳልፈው ሀብት በማግበስበስ ነው። እስትንፋሱ ገንዘብ ነው፤ ማህበራዊ ግንኙነቱ ገንዘብ ነው፤ በደሙ ውስጥ የሚዘዋወረው ገንዘብ ነው፤ ባዶ ጭንቅላቱን የሞላው ገንዘብ ነው፤ የሚያስበውም በገንዘብ ሀይል ነው። እሱ ገንዘብን አምልኮ እንደሰገደልት ሁሉ የሱን ባለሀብትነት የሚያመልኩ ሰዎች ከስሩ ሲመለከት በገንዘብ ላይ የተመሰረተ የበላይነት ስሜት ያሳብደዋል። ይህ ሰው በገንዘቡ ምንም ነገር ማድረግና ማስደረግ ወደ ሚችልበት ደረጃ ደርሶ ይሆናል። ገንዘብ የሚፈጥረው ዕብጠት ቀላል አይደለም። አንዳንዴ ሰማይነህን ሳየው በገንዘብ ኃይል የሚንቀሳቀስ ማሽን ይመስለኛል፤ ሰውነቱ ይጠፋብኛል። ዕድሜውን ያሳለፈው ሀብት በማግበስበስ እንደመሆኑ መጠን ሴት ለመምረጥም ጊዜ አልነበረውም። ምን ዓይነት ሴት እንደሚፈልግም አያውቅም። ሀብት ቆንጆ ሴትን ጭምር ይገዛል የሚል ዕምነት ይኖረዋል። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ችግሩ። ከሴቷ የሚፈልገው ወሲብ ከሆነ ሊገዛ ይቻላል፤ ፍቅርን ግን ሊገዛው አይችልም። ሴቷ ዕቃ አይደለችም፤ ሰው ናት። ስሜቷን በተለያዩ መንገዶች ትገልፃለች። ገላውን ሰጥታው ስሜቷን ልትከለክለው ትችላለች። ስሜቱና ማጣቱና በገንዘቡ ሊገዛው ያለ መቻሉ ያናድደዋል.....»

«.....የሚገርምህ ግን.....ስሜቴን ለማወቅ እንኳ ዕድል አልሰጠኝም። ከተዋወቅንበት ቀን ጀምሮ በቅናት ሲገላምጠኝና ሲቆጣጠረኝ ነው የኖረው» አለች አቋርጣው።

«ምናልባት ቁንጅናሽን ይሆናል የገዛው። እሱ እንደሚናገረው ከሆነ ብዙ ገንዘብ አውጥቶብሻል። በገንዘብ ኃይል ሁለመናሽን መግዛት ይፈልጋል፤ የሰውነት ስሜትንሽ ረግጦ እንደ አሻንጉሊት ሊያንከባልልሽና ግዑዝ አድርጎ ሊያስቀምጥሽ ይመኛል። ሌሎች እንዲያዩበትና እንዲመኙበት አይፈልግም። ሴትነትሽንና ቁንጅናሽን እንጂ ስሜትሽን ስላልገዛው ዕምነት የለውም፤ አቅፎች ተኝቶ ከእሱ ጋር ያለሽ አይመስለውም፤ አጠገቡ ሆነሽ ሩቅ የሄድሽበት ይመስለዋል፤ ካዩሽና ከቀረቡሽ ጋር ሁሉ ልብሽ የሚሸፍት ይመስለዋል። ምናልባት የቅናቱ ምንጭ ይሄ ሊሆን ይችላል። በሀገራችን ‹ቅናት የፍቅር ጥላ ናት› የሚባል አነጋገር አለ። ስህተት ይመስለኛል። ጤናማ ፍቅር ቅናት አያውቅም። በቅናት ተሸብቦ ከማሰቃየትና ከመሰቃየት ይልቅ በነፃነት መተማመንን ያዳብራል። ሊቃውንቱ እንደሚሉት ‹አንድን ሰው ማፍቀር ማለት አንዲኖር መኮትኮትና እንዲያድግ መጋበዝ ነው።› እነዚህ ነገሮች ደግሞ ነፃነትን ይጠይቃሉ። አፍነው ጭለማ ውስጥ በማስቀመጥ መኮትኮትና ማሳደግ አይቻልም።.....

‹ቅናት ተፈጥሮአዊ ነው የሚሉ አሉ› በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ መፅሐፍ ውስጥ ያገኘሁት ሀሳብ ትዝ ይለኛል። ቅናት በመሠረቱ በባህላዊ ሁኔታዎች የሚወስነው ማህበራዊ ልምድ ነው። በዓለም ውስጥ ከሚገኙ በርካታ የህብረተስብ ክፍሎች ኤስኮም፣ ማርቆሳን፣ የምዕራብ አፍሪካው ሎኢ፣ የቦሊቪያው ሴራኖ እና በመሳሰሉት ሀገሮች ቅናት የሚባል ነገር ፈፅሞ አይገኝም። ቅናት ተፈጥሮአዎ ላለመሆኑ እነዚህ በቂ ምሳሌዎች ናቸው።

«ሊቃውንቱ እንደሚተነትኑት ከሆነ ቅናት የሚመሰረተው በጋብቻው ዓይነት ላይ ነው። ‹ነፃ ጋብቻ› እና ‹ዝግ ጋብቻ› ብለው በሁለት ይከፍሉታል። ነፃ ጋብቻ ከአንድ በላይ ጋብቻንና የግብረ ስጋ ግንኙነት ሲፈቅድ፣ ዝግ ጋብቻ ግን ‹አንድ ለአንድ› የሚለውን ውል ይደነግጋል። ይህ የዝግ ጋብቻ ውል በባህላዊ ሁኔታዎች አስገዳጅነት የግል ይዞታን ይፈጥራል።

«ከአንድ ሰው ጋር ብቻ የግብረ ስጋ ግንኙነት የማድረግና አንድ ሰው ብቻ የመያዝ ፅንሰ ሐሳብ የሆነ ጥገኝነትን፣ ህፃናዊ ቅብጥብጥ ፀባይንና በራስ ያለ መተማመንን ያከትላል። በራስ ባልተማመኑ ቁጥር ደግሞ የበለጠ ቀናተኛ እየሆኑ መሄድ አይቀርም። አብርሀም ማስሌው እንደሚለው ‹ቅናት ሁልጊዜ የበለጠ መራራቅንና ስር የሰደደ በራስ ያለመተማመንን ያስከትላል። ደግሞም ቅናት፣ ልክ እንደ አጥፊ ካንሰር፣ የበለጠ ቅናት እየፈጠረ ይሄዳል።› የሰማይነህ የቅናት ዓይነት በዚህ ደረጃ የሚመደብ ይመስለኛል። ይህ ቅናት ፍቅረኛን ላለማጣት ከሚደረግ ፍራቻ የሚመነጭ ነው። ሆኖም ፍቅርን ያጠፋዋል።»

ህይወት የስሜት ህዋሶቿ ሁሉ የተኮረኮሩ ያህል ነቃች። መደምደሚያ የውስጥ ስሜቷን ሲገልፅላት ደስ አላት። የጠዋት ፀሐይ ፊቷ ላይ ስታርፍ ወገግ አደረገቻት። ሰሞኑን በህመም ደብዝዞ የከረመው ገፅታዋ ከአበቦቹ ጋር እየተያያዘ ፈካ።

«.....ፍቅረኛ አለችህ እንዴ?» አለችው በድንገት።

መደምደሚያ ያላሰበው ጥያቄ በመሆኑ ክው ብሎ ደንግጦ ምላሱ ተሳሰረ። ላቡ በጀርባው በኩል ጠብ ጥብ ሲል ተሰማው። ዓይኖቹን ማሳረፊያ ያጣ ይመስል ከወዲያ ወዲህ አቅበዘበዛቸው። ግን ምን አስደነገጠው? ህይወት እንደሆነ የወንድሙ ሚስት ናት። እሱም «ደንገጡሯ» ሆኖ ነው የሚያጫውታት!....

«.....ይ......ይ....ይህንን ጥያቄ እንዴት ጠየቅሽኝ?»

«ማለቴ.....አንተን ያፈቀረች ሴት ዕድለኛ ነች ለማለት ፈልጌ ነው። ነፃ አስተሳሰብ ያለው ወንድ ማግኘት ትልቅ ፀጋ መሆኑን የተረዳሁት አሁን ነው።»

የመደምደሚያ ቁመናም ሆነ ምልክ አይስብም። ቀለም የመጠጠው ቀጭን ሰነቱ እርቃኑ ቢታይ ምናልባትም ያስፈራ ይሆናል። ነገር ግን እንዲህ ቀርበው ሀሳቡን ሲካፈሉትና ዕምነቱን ሲጋሩት ፍቅር ላይ ይጥላል። ሰው የሚወደው በውጪያዊ አካሉ ሳይሆን በውስጣዊ ማንነቱ መሆኑን ያስመሰክራል። ህይወት መደምደሚያን ቀርባ ካወቀች ጊዜ ጀምሮ ይህንን ታዝባ ‹ለታላላቅ ወንድሞችህ የአንተን አስተሳሰብ ግማሽ ቢሰጣቸው ምን ነበረበት?› ብላለች።

«አትጨነቅ.....ጥያቄዬን መመለስ ካልፈለግክ ተወው» አለችው የመደምደሚያን መደናገጥ ስለታዘበች ስለ ፍቅረኛው መናገር አይፈልግም ይሆናል በማለት።

«አአይ.....ሌላ ሳይሆን... በሀያ ስምንት አመቴ ፍቅረኛ የለኝም ማለቴ ከብዶኝ ነው።»

«ግን.....ለምን?»

»እኔ እንጃ!.....ወንድሜ ሀብት በማግበስበ ዕድሜውን እንደፈጀ ሁሉ፣ እኔም ዕውቀት በማግበስበስ ዕድሜዬን እየፈጀሁ ይሆናል። ምናልባት ሀሳባዊ ሆኜ በአፌ ከማነብነብ በቀር በተግባር የሴቶችን ልብ ማሸነፍ ሳልችል ቀርቼ ይሆናል። ወይንም ደግሞ ሴቶቹን እንደምፈልጋቸው ሳላገኛቸው ቀርቼ ይሆናል። በሁሉም ወይንም በአንዱ ምክንያት እስካሁን በፍቅር ስለ ፍቅር የያዝኳት ሴት የለችም ፡

‹የወንድምህ ሚስት ሆኜ ባንገናኝ ኖሮ እኔ አልለቅህም ነበር› አለች ህይወት በልቧ።

«እንዲህ ስልሽ ጭራሹን ከሴት ጋር ግንኙነት የለኝም ማለቴ አይደለም። በወሲብ የቀረብኳትን ሴት ፍቅረኛዬ አድርጌ አልቆጥራትም። ሬይሞንድ ጋሌ ‹አንተ ማን ነህ?› በሚለው መፅሐፉ እንደ ገለፀው ፍቅርና ወሲብ ተመሳሳይ አይደሉም። ወሲብ ከሰውነት ጋር የተቆራኘ ተፈጥሮአዊ ፍላጎት ሲሆንም ፍቅር ግን በሁለት የተለያዩ ሰዎች መሀከል ያለ ስሜታዊ ግንኙነት ነው። የወሲብ ዓላማ

የሰውነት እንቅስቃሴ የደምስሮችን እብጠት ማኮማተር ሲሆን፣ የፍቅር ዓላማ ግን የመንፈስ ውጥረት ማርገብ ነው። ወሲብ ርካታን ይፈልጋል፤ ፍቅር ደግሞ ደስታን ይፈልጋል። ወሲብ የተፈጥሮ ክስተት ሲሆን ፍቅር ግን የባህል ዕድገት ውጤት ነው።»

«እንደ ባህሩ ፂሞ ሴቶችን ጠልተህ እንዳትቀር ቶሎ ማፍቀር ይኖርብሀል» በማለት ነገሩን እንደ ቀልድ አጠፍ አደረገችበት።

ባህሩ ፂሞን መደምደሚያም ያውቀዋል። በግብዣና በተለያዩ አጋጣሚዎች ቤታቸው ሲመጣ ትንሽ ሳይከራከሩ አይለያዩም። በሴቶች ላይ ሁለት ያላቸው አመለካከት ፍፁም የተራራቀ ነው።

«እኔ እንደ ጋሼ ባህሩ ሴቶችን የመጥላትና የመናቅ ባህርይ የለብኝም። በፍቅር፣ በክብርና በነፃነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ነው የምፈልገው። ጋሽ ባህሩ ይህን መሳይ ፀባይ ያመጣው ሚስቴ ከከዳችው በኋላ መሆኑን ሰምቻለሁ።.....»

«አዎ እኔም ሰምቻለሁ።»

«ሁሉንም ሴቶች በእሷ አይን እያያቸው ነው።»

«ሰማይነህም ላይ ይህንን በሽታውን እንዳያጋባበት ያስፈራል። ከማንም ይልቅ የሚቀርበውና የሚያዳምጠው እሱን ነው።»

«ቅናትን በሚያክል በሽታ ላይ ጥላቻና ንቀት ከተጨመረበትማ አዲዮስ! ቪላ ቤት ውስጥ በክብር መታሰርሽ ቀርቶ ወደ ማድ ቤት ተወርውረሽ ይቆለፍብሻል» ብሎ እንደ መቀለድ ጥርሱን ብልጭ አደረገ።

ህይወት ግን አልሳቀችም። ስለ ፍቅር ምንነት ሲወያዩ በደስታ ፊቷ የፈካውን ያህል አሁን ስለ ሰማይነህ ስታስብ በአንድ ጊዜ ሰውነቷ ተለዋወጠ። የመደምደሚያ ገለፃ ደስታ የሚፈጥር ቢሆንም ሀሳባዊ ነው፤ አሁን እሷ የምትገኘው ግን ተግባራዊ ጭለማ ውስጥ ነው። ከጭለማው መውጫ መንገድ ስታሰላስል ግራ ይገባታል።

«ጥፋት የፈፀምሽ መጀመሪያ ነው» አላት መደምደሚያ የገጿን መለዋወጥ ሲመለከት ስሜቷ ገብቶት።

«እንዴት?....ምን አይነት ጥፋት?»

«ከሰማይነህ ጋር መጋባትሽ በፊት ምርጫሽን ማስተካከል ነበረብሽ። ጋብቻን መወሰን ቀላል ነገር አይደለም። በአስተሳሰብ መቀራረብን፣ በስሜት መተሳሰርን፣ በፍቅር መከባበርን፣ መቻቻልን፣ አንተ ትብስ - አንቺ ትብሽ መባባልን ይጠይቃል። ይህን ያህል የአስተሳሰብ ልዩነት ኖሮአችሁ እንዴት ለጋብቻ እንደተፈቃቀዳችሁ ይገርመኛል። በዚያ ላይ ደግሞ በጣም ሰፊ የዕድሜ ልዩነት አላችሁ» በማለት ፍርጥርጥ አድርጎ ነገራት።

«ልክ ነህ። ሆኖም ግን ምርጫው የእኔ ሳይሆን የአክስቴ ነበር። ያኔም አካልባ ያጋባችን አሁንም እንዳልፋታ የምትከላከለኝ እሷ ናት» አለችው በምሬት።

»እንዴት?......እንዴት?»

«የገንዘብ ፍቅር ከሰማይነህ ጋር አንድ አድርጎ ስላሰማማቸው እኔን ሸጣለት ግንኙነቷን ከጠነከረች፤ አሁንም፣ ከባርነት እንዳልወጣ አጥብቃ ትታገለኛለች......» ካለችው በኋላ ድምጿን ሰብስባ «......አክስቴ ክፉ ሰው አይደለችም። ስቄ፤ ተጫውቼ በደስታ እንዳድግ የተቻላትን ያህል ተንከባክባኛለች። በማይመስላት ነገር ብትቆጣና ብትገስፀኝም ባመነችበት ነገር ሁሉ ፍቅሯንና

ደግነቷን አሳይታኛለች፡፡ ሆኖም ግን አሁን እንደምረዳው ከፍተኛ የገንዘብ ፍቅር ሰፍሮባታል፡፡ ምናልባትም ከዘመዶቿ ሁሉ ርቃ ብቻዋን የምትኖረው ለዚህ ይሆናል፡፡ ማንኛውንም ግንኙነትና እንቅስቃሴ በገንዘብ ማስላት የጀመረች ይመስለኛል.....ቅድም አንተ ስለሰማይነህ ገንዘብ መውደድና ማምለክ ስታወራልኝ እኔም አክስቴን እያሰብኩ ነበር፡፡ ሰዎች ገንዘብን ማፍቀርና ማምለክ ሲጀምሩ ለሰው ያላቸውን ፍቅርና ፍቅርና ክብር መቀነሳቸው አይቀሬ ነው......»

መደምደሚያ ግር እንዳለው ከፊቱ ላይ አነበበች፡፡ አክስቷና እናቷ እንደምተምታቱበት ስላወቀች ታሪኳን ልትነግረው ፈለገች፡፡ ላቀረቡትና ለአመኑት ሰው ሆድ ውስጥ ያለውን በሙሉ ዘክዝከው ሲያጫውቱ የህሳቡ መከፈልና መጠነኛ እፎይታ ይገኛል፡፡ ‹ህይወትን እንድትተነፍስ ከውስጥ የሚገፋፋት እንዲህ አይነቱ ስሜት ነው፡፡

«አክስቴ የምልህ እናንተ በእናትነቷ የምታውቋትን ወ/ሮ ስራሽብዙን ነው.....እሷ አሳዳጊዬ እንጂ ወላጅ እናቴ አይደለችም» ከማለቷ ፊቷን ክፍት አለው፡፡

«ወላጅ እናትሽስ?....» አለ መደምደሚያ ይበልጥ ግራ እየገባውና የእሷን ስሜት ተከትሎ እያዘነ፡፡

እናትና አባቴ ገና በህፃንነቴ ሞተዋል፡፡ ታላቅ ወንድሜን ይዘው ሽርሽር ሲሄዱ በመኪና አደጋ ሁሉ አም አለቁ፡፡ እኔ አክስቴ ቤት ቀርቼ ስለ ነበር ተረፍኩ፡፡ አክስቴ እንደ እናት ሆና ‹ልጄ› እያለች አሳደገችኝ፡፡ እኔም እንደ እናት ‹እማዬ› እያልኳት አደግኩ፡፡ ወላጆቼን ማጣቴ እንዳይሰማኝ ተንከባክባና አሞላቅቃ ነው ያሳደገችኝ፡፡ ወላጆቼ ነፍስ ሳላውቅና ፍቅራቸውን ማጣጣም ሳልጀምር ስለተለዩኝ ካደግኩም በኋላ ሐዘኑ ጠልቆ አልተሰማኝም ነበር፡፡ አሁን ግን ወደ ኋላ ተመልሼ እያዘንኩ ነው፡፡ የአክስቴን አንዳንድ ሁኔታዎች ስመለከት ‹ስላልወለደችኝ ይሆናል› የሚል ስሜት እየፈጠረብኝ ነው....»

ሳታስበው እንባዋ ቀድሞ በጉንጮቿ ላይ ወረደ፡፡ መደምደሚያ ስሜቱን መቆጣጠር አልቻለም፡፡ ዓይኑ ላይ ደርሰው ግጥም ያሉትን የእንባ ዘለላዎች መንገድ ለቀቀላቸው፡፡ ለአንዳፍታ ያህል የጋራ ስሜታቸውን በእንባ ገለፁ፡፡

«ይህች ዓለም ጨካኝ ናት» አለ መደምደሚያ ከኪሱ መሐረም አውጥቶ ዓይኖቹን እየጠራረገ፡፡

«....አሁን ከሰማይነህ ጋር ተፋትቼ ብሔድ እንኳን የአክስቴ ቤት መሸሻ እንደማይሆነኝ እየገባኝ ነው፡፡ ኃይለኛ ግንባር ፈጥረዋል፡፡....መሔጃ የሌለኝ መሆኔ እየተሰማኝ ነው፡፡ አክስቴ የኖረችው ከዘመዶቻችን ርቃ ስለሆነ አሁን መሸሻ ሊሆነኝ የሚችል ቀድሞ የቀረብኩት ዘመድም የለኝም፡፡»

«አንቺን መሳይ ቆንጆ ወጣት እንኳ መሸሻ አያጣም» በማለት ሊያፅናናት ሞከረ፡፡

«የት ነው መሸሻዬ?.....ቡና ቤት ውስጥ ሽርሙጥና?!.....አሁን ያለው ክፍት ቦታ እሱ ብቻ ይመስለኛል» አለችው ጠይም ፊቷ ላይ ሐዘንና ምሬት እየተነበበ፡፡

«ኧረ ምን በወጣሽ!.....ለዕድልሽም አይስጠው!....ዓለም ሰፊ ናት፤ አንቺም ገና ወጣት ነሽ፤ ከፊትሽ ብዙ ዕድል ይጠብቅሻል፡፡ ለማንኛውም በተስፋ መጓዝ ይኖርብሻል፡፡ ጭለማ የምትመለከቺበት ዕድሜ ላይ አይደለም ያለሽው»

«አዎ፤ ወጣትነቴና ውበቴ ልበ ሙሉ አድርገውኝ ቆይተዋል፡፡ እንዲህ የማዝንም፣ የምጨነቅም ሰው አልነበርኩም፡፡ ዕድሌ ሰማይነህ ላይ ከጣለችኝ ጀምሮ ግን መፍራት ጀምሬአለሁ፡፡ ጭለማ እንጂ ብርሀን አልታይሽ ብሎኛል፡፡»

«አንዳንዴ በትንሽ እንቅፋት ዓለም የጨለመ መስሎ የሚታየን ጊዜ አለ። እንዲህ ዓይነቱ ስሜት ጊዜያዊና ሰይጣናዊ ስለሆነ ተስፋ ሊያስቆርጠን አይገባም።

«ሰሞኑን ግን አንድ ነገር እያስብኩ ነው» አለችው እንባዋን ጠራርጋ ወደ ሩቅ እየተመለከተች።

«ምንድን ነው እሱ?.....»

«ሄኖክ የሚባል የልጅነት ጓ....ጓደኛዬ ነበር። ቅድም ስለ ዕውነተኛ ፍቅር ስትገልፅልኝ ሀሳቢ ውስጥ የመጣው እሱ ነው። የፍቅርን ትኩሳት የማውቀው በእሱ ነው.....አሁን ያለው ውጭ ሀገር ስለሆነ በአድራሻው ልፅፍለት አስቤያለሁ። ምናልባት እሱ መሸሻ ይሆነኝ ይሆናል። ማን ያውቃል?!.....

የሰማይነህ እናትና ጎርፉ ወደነሱ ሲመጡ ስለተመለከተች ንግግሯን አቋረጠች። ጎርፉ ሁለቱ የተነጋገሩትን ባይሰማም በርቀት ተደብቆ እንቅስቃሴያቸውንና ሁኔታቸውን ሲከታተል ነበር። ሁለቱም ሲላቀሱ ተመልክቷል፤ እንባቸውን እየጠራረጉ ሲተዛዘኑና ሲወያዩ ተመልክቷል። በዚህ ምክንያት ጥርጣሬው ወደ ሌላ አቅጣጫ ሄዶ ‹ይህንን ጉድ እናታችን ማየት አለባት› ብሎ ነው እየጎተተ ያመጣቸው። ለሰማይነህ አቀነባብሮ የሚያቀርብላትን ትርዒት በማየቱ ደስ ብሎታል። እንዲህ ዓይነቱ የሰለላ ሪፖርት ጠቃሚ ጉርሻ ሊያስገኝ ይቻላል በሚል ግምት ፈንድቋል።

አጠገባቸው ሲደርሱ መደምደሚያ እንባውን የጠረገበትን መሐረብ ወደ ኪሱ ሳይመልስ በእጁ እንዳንጠለጠለው አገኙት።

«እጅ ከፍንጅ!.....» በማለት ጎርፉ እንደ ቡሀቃ የሰፋ አፉን እንዴ ለቀቀው።

«ምኑ?.....» አለ መደምደሚያ ተደናግጦ።

«ምን እያደረጋችሁ ነው?!» አሉ የሰማይነህ እናት በቁጣ።

«ፀሐይ እየሞቅን ነዋ» አላቸው መደምደሚያ።

«ፀሐይ መሞቅ ያስለቅሳል እንዴ?....ሆሆሆይ!.....ያልታያችሁ እንዳይመስላችሁ። ጉዳችሁን አይቼላችኋለሁ።»

የጎርፉ ንግግር ህይወትን አስደንግጦ ክው ሲያደርጋት፣ መደምደሚያን ደግሞ አናድዶት ብው አደረገው።

‹የ - የምን ጉድ ነው የምታወራው?!.......›

«የወንድምህን ሚስት የመከጀልን ጉድ ነዋ!....»

«ማ?....እኔ?›...»

«አዎ፤ አንተ! በዓይኔ በብረቱ አይቼሀለሁ።»

«እኔ እኮ እንዳንተ ከብት አይደለሁም። ህሊና ያለኝ ሰው ነኝ። በእንዲህ አይነቱ የሥነ ምግባር ብልሹነት ፈጽሞ ልትጠረጥረኝ አይገባውም ነበር። ወንድሜን ሚስት የሚያስደፍረኝ ምንም ዓይነት የሞራል ውድቀት አልደረሰብኝም፤ ሰብዕናዬም አይፈቅድልኝም። እንዲህ ዓይነቱን ምግባረ ብልሹነት ማሰብህ ራሱ የውስጥ ፍላጎትህን ያንፀባርቃል። ከብት!.....

«ማነው ከብት?!.....እኔ ጎርፉ?!»

«አዎ አንተ!.....ራስህን አታውቀውም እንዴ!»

ወንድማማቾቹ ሊተናነቁ ሽቅብና ቁልቁል ተፋጠጡ፡፡ ጎርፉ ግዙፍ ሰውነቱን ሊያሳርፍበት ጡንቻውን ወጣጥሮ ዓይኖቹን አጉረጠረጠ፡፡ መደምደሚያ «ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ» እያለ ጅማቶቹ ቀጭን ፊቱ ላይ ተገታትትረው ለፍልሚያ አነሳሱት፡፡ የጎርፉ የአካል ግዝፈት ከምንም አልቆጠረም፡፡ ‹ደደብ ጭንቅላቱ ግዙፍ ሰውነቱን እንደ ልቡ ማዘዝ አይችልም፡፡ አሳቻ ቦታ ፈልጌ ዕልህ ተናነቀው፡፡ መጀመሪያ ዘልሎ በቴስታ ቢመታው ሰማይ ምድሩን ሊያዞርበት እንደሚችል ገመተ፡፡

ጎርፉ በበኩሉ በአካል እንቅስቃሴ መደምደሚያ ሊወራጭበት እንደሚችል በማሰብ በፈረጠመ ጡንቻው አንዴ ተሸክሞ ሊያፈርጠው ፈለገ፡፡ ‹ይሄንን ስንጥር ሰውነቱን ሰባብሬ የአልጋ ቁራኛ አደርገዋለሁ!› ብሎ በልቡ ፎከረ፡፡ ‹ሁለተኛ አይለምደኝም!› እስኪል ድረስ አስተኝቶ ለመርገጥ ተመኘ፡፡

ከሁለት አንዳቸው እጃቸውን ከመሰንዘራቸው በፊት እናትዬው መሀላቸው ገብተው ቆሙ፡፡

«እንዴ!.....ምን ልትሆኑ ነው?.....ልትደባደቡ?....ጉድ አትፈሩም እንዴ?....በሉ መጀመሪያ እኔን ደበደቡኝ!....እኔ እናታችሁ በህይወት ቆሜ እናንተ ልጆቼ አትደባደቡም» እያሉ የጎርፉን ክንድ ይዘው ወደ ኋላ እየገፉ አሸሹት፡፡

ህይወት በጭንቀት ተውጣ፣ በእሷ ምክንያት የተፈጠረው ችግር እያሳሰባትና የቀድሞው ብሶቷ ከውስጥ እየፈነቀላት በማልቀስ ላይ ነበረች፡፡ እናትዬው ጎርፉን ሲይዙ እሷም የመደምደሚያን ክንድ እየጎተተች ገላገለችው፡፡

«ልቀቂኝ!....» አላት መደምደሚያ ዕልህ እየተናነቀውና መገላገሉ እያባሰበት፡፡

«እባክህ ተው በናትህ!.....አፈር ድሜ ባላስግጥህ እኔ ወንድ አይደለሁም!» እያለ ጎርፉ ከወዲያ ፎከረ፡፡

እናትዬው ጎርፉን እየተቆጡና እያባበሉ ወደ ቤት አስገብተውት ለቁርስ ከተዘጋጀው ገንፎ በትልቅ ሳህን ሙሉ ሰጥተው አፉን አስያዙት፡፡

«አደራህን ጎርፉ...ይህንን ነገር ሰማይነህ እንዳይሰማ»

«ምን ማለትሽ ነው እማማ!....እነግረዋለሁ፡፡ የወንድሜን ጥቃት ማየት አልፈልግም፡፡»

«በአባታችሁ አጥንት ይገቱሀለሁ ጎርፉ.....ሰማይነህ ይህንን ከሰማ ዕብድ ነው የሚሆነው፡፡ ልጆቼን እኛ እንመከራቸዋለን፡፡ ልጅነት ነው እንዲህ የሚያደርጋቸው»

«ማነው ልጅ?.....መደምደሚያ?....እሱ የሚሰራውንና የሚናገረውን ማንም አያደርገው፡፡ አንቺ ነሽ እያሞላቀቅሽ ለዚህ ያበቃሽው፡፡»

«ግድ የለም፤ ለሁሉም ነገር መላ ይፈለግለታል፡፡ አሁን ብቻ ይችን ነገር ለማንም ትንፍሽ እንዳትል፡፡ በአባታችሁ አፅም ይገቱሀለሁ!.... ኋላ ፀብህ ከእኔ ጋር ነው፡፡»

የእናታችነው ልብ ወደ መደምደሚያ እንደሚያደላ ጎርፉ ያውቃል፡፡ አንዳንዴ የከረረ ፀብ ተጣልተው ሊጨክንበት የማይችለውም እሳቸውን እየፈራ ነው፡፡ አሁንም ነገሩን ቻል ብሎት የቀረበለትን ገንፎ መሰልቀጥ ጀመረ፡፡

«አሁን ደግሞ ወደ ቤት አትገቡም እንዴ?!......እዚያ ምን ታደርጋላችሁ?» አሉ የሰማይነህ እናት ወደ ህይወትና መደምደሚያ ተመልሰው፡፡

ህይወት አዝማሚያቸው ስላላማራት ቁጣቸውን ፈርታ ፈጠን እያለች ወደ ቤት ገባች። ሆኖም የፈራችው አልቀረላትም።

«ምንድነው እንዲህ መልከስከስ?!....ምንድነው እንዲህ ቀሚስ መጣል?! ክብሩን የሚጠብቀው ባለቤቱ ነው። ሴት ልጅ የምትከበረው ከሁሉም ነገር ቁጥብ ሆና ስትቀመጥ ነው። በየሜዳው መገልፈጥና መላቀስ ምን ዋጋ አለው?!.....» ሲሏት እንዳልሰማች ሆና ወደ ፊቷ ገሰገሰች።

አሮጊቷ ደግሞ ጀርባዋን ሰጥታቸው በመሄዱ ተናድደው ይበልጥ በግልፅ መናገር ጀመሩ።

«አአይ!....ምነው እቴ!....ልጆቼን እንድታጣያቸው እንድታበጣብጪያቸው አልፈልግም። ትኖሪ እንደሆነ ክብርሽን ጠብቀሽ ኑሪ!»

ህይወት ይህንን በዝምታ መቋቋም አልቻለችም። ለአንዳፍታ ቆም ብላ በንዴት ራሷን እየነቀነቀች «ምንድን ነው የሚያወሩት እማማ?.... እንዴት አይነት መጥፎ ንግግር ነው የሚናገሩት?!....የእኔን ልብ ንፅህና የሚውቀው አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው» አለቻቸው።

ከእሳቸው ሽሽታ ወደ ቤት ስትገባ ጎርፉን አየችው። አንዳች ቆሻሻ ነገር እንዳየች ሁሉ ተፀየፈች። ሆኖም ከንቱ ጥርጣሬው ዕውነት አድርጎ ለሰማይነህ ቢነግረው በሷም ሆነ በመደምደሚያ ላይ የሚደርሰው ችግር በመገመት ቢያንስ ጥርጣሬው ልታስተባብልለት ፈለገች።

«ጎርፉ፤ የምታምነኝ ከሆነ እኔ ዕውነቱን ልንገርህ። ከመደምደሚያ ጋር አንተ የጠረጠርከው ዓይነት ግንኙነት የለንም። ከቶውንም አላሰብንም። የየግል ታሪካችንን ስንጨዋወት ተዛዝነን ነው የተላቀስነው። በምንፈልገው ነገር ዕምልልሀለሁ» አለችው።

በሆዱ ግን እየረገመችውና ብሽቀቷን የሚገልፅላት ስድብ ሁሉ እየሰደበችው ነበር።

«አንቺ አታውቂውም የእሱን ነገር። እያሳሳቀሽና እያስለቀሰሽ በኋላ ልብሽን ሊያሸፍተው ነው። ባለጌ ስለሆነ ተጠንቀቂው» ብሎአት የገንፎውን ሰሀን እየጠራረገ ማንካውን ሲልስ፣ ህይወት በልቧ ‹ባለስ አንተው ነህ። ሆዳም!› ብላው ወደ መኝታ ክፍሏ ገባች።

ጎርፉ ቁርሱን ጨርሶ ወደ ታክሲ ስራው ለመሰማራት ከቤት ሲወጣ እናቱና መደምደሚያ ውጭ ቆመው ሲጨቃጨቁ ተመለከተ። መደምደሚያ ገና ንዴቱ ስልልበረደለት ጥርሱን እያንቀጫቀጨ በርቀት አፈጠጠበት። ጎርፉ ግን ሆዱ ሲሞላ ፀቡን ጭራሽ የረሳው ይመስላል። የከፋቱን ያህል ቂም ይዞ መቆየት አይችልም። ዘወር ሲል ይረሳዋል። አሁንም ነገር አለሙን ወዲያው እንደረሳው ሁሉ «በሉ ደህና ዋሉ» ብሎአቸው ታክሲውን አስነስቶ ሄደ። መደምደሚያም ከእናቱ ጋር ክርክሩን ቀጠለ።

«እማማ.....እኔን እንድታምኚኝ እፈልጋለሁ። የዚህን የከብት ልጅሽን ምክር ሰምተሽ እኔንና የህይወትን ግንኙነት በሌላ መንገድ መጠርጠር የለብሽም። በጣም ተሳስተሻል። እሷንም መጥፎ ቃል ስትናገሪያት በመስማቴ በጣም አዝኜብሻለሁ።»

«አንተ ከእሷ ጋር መጣበቁ ቢቀርብህ ምነው? ለምን ሰው የሚመክርህን አትሰማም ልጅጄ?»

«እሷስ ማን አላት?! ብቻዋን እኮ ናት። አንዳችሁ ከሌላችሁ ተሽላችሁ ‹አይዞሽ› አትሏትም። መሀላችሁ ገብታ መከራዋን አየች። ገና በወጣትነትዋ ለዚህ ዕድል በመዳረግዋ ልክ እንደ እህቴ ታሳዝነኛለች። ይህን መሳይ ውበትና የወጣትነት ብሩህ አዕምሮ ይዛ በሰማይነህ የቅናት ሰንሰለት መጠፈሯ ያሳዝነኛል።»

«እንዴዬ?!.... ምን ጎደለባትና ነው የምታሳዝንህ! ሰማይነህ እንደሆነ እንኳን ለእሷ ለሌሎች የሚተርፍ ሀብት አለው። አንቀባርሮ ነው የያዛት። በወርቅ ላይ ወርቅ.....በጨርቅ ላይ ጨርቅ

እያምበሸበሻት ነው። ቤቷም እንደሆነ ሙሉ ነው። በሳምንት ሁለት ጊዜ በግ ይታረዳል፤ የቁርጥ ስጋ ጮማው ጠብ እያለ በየቀኑ ይገባል።......ምን አጣችና ነው የሚታዘንላት!?....»

«ተይ እንጂ እማማ፤ እንደሱ አትበይ.....ለሆድ ብቻ የሚኖሩ ከብት ነው። ለጌጥና ለጨርቅ ብቻ የሚኖርም ዕቃ ነው። የሰው ልጅ ከሁሉም በላይ የአዕምሮ ሰላም፤ ፍቅርና ከበሬታ ያስፈልገዋል። ህይወት እነደዚህን ነገሮች እዚህ ቤት ውስጥ አላገኘችም.......እንደኔ ቀሪውን ዕድሜዋን ከምታቃጥሉባት ከሰማይነህ ጋር አሁኑኑ ቢፋቱ ይሻላቸዋል። ፈፅሞ አብረው የሚሄዱ ሰዎች አይደሉም» ብሎ ዕቅጩን ነገራቸው።

የሰማይነህ እናት ራሳቸውን ይዘው ጮሁ። ሰውነታቸው በአንዴ ተለዋወጠ።

«በል በቃህ....በቃህ። እኔ እንደሰማሁህ ማንም እንዳይሰማህ። የመፋታት ነገር ፈፅሞ የማይነሳ ነው።

«ለምን?....እስካልተስማሙ ድረስ በግድ አብረው መኖር የለባቸውም። ዓለም ሰፊ ናት። ለእሷ ብቻ ሳይሆን ፍቺው የሚጠቅመው ለሱም ነው።....»

«ኧረ እባክህ በቃህ መደምደሚያ።.....የማታውቀውን ነገር አትዘባርቅ እኮ ነው የምልህ....»

«ምንድነው ችግሩ?.....»

እናትዬው ትንሽ አሰብ ሲያደርጉ ቆዩና «አንድ ሚስጥር አለ» አሉት «ከአሁን በኋላ በሁለቱ መሀል እንዳትገባ ሚስጥሩን እነግርሀለሁ።»

መደምደሚያ ልቡ ተሰቀለ። በጆሮው ብቻ ሳይሆን በአይኖቹም ጭምር የሚያዳምጥ ይመስል አፈጠጠ።

«ይቺ ልጅ ሰማይነህ ገዱ ናት። ከእሷ ጋር ከተፋቱ ንግዱ እንደማይቀናውና ሀብቱም እንደሚረግፍ አዋቂ እንግሮታል። ቀድሞውንም ልጅቷ ፈላጊዋ ብዙ ነበር። በገንዘብ ሀይል አሸንፎ እንዲይዛት አዋቂ መክሮት ነው ያገባት። ስለዚህ መፋታት የሚባለው ነገር ፈፅሞ የማይታለም ነው። ሰማይነህ ፈፅሞ የማይታለም ነው። ሰማይነህ ፊት እዘላብዳለሁ ብለህ ታላቅ ችግር እንዳትፈጥር። ነግሬሀለሁ ኋላ!.....»

‹የዘለዓለም እስረኛ አድርጋኋታላ!› ብሎ መደምደሚያ በልቡ ለህይወት እያዘነ «.....ለመሆኑ ጠንቋዩ ማነው?» አላቸው።

«እሱ አይጠየቅም።.... ዝም ብለህ አትዘላብድ። ቁርጡን እንድታውቅ ብዬ ነው የነገርኩህ» እያሉ ተቆጥተው ከአጠገቡ ዘወር አሉ።

# ክፍል ስምንት

ወ/ሮ ስራሽ የህይወትን መምጣት በናፍቆት ስትጠባበቀው ነበር። በግ አርዳ፣ ጥሩ ምሳ አዘጋጅታ፣ በተሟላ መስተንግዶ ተቀበለቻት። ህይወት የተፈለገችበትን ጉዳይ በውል ባታውቅም፣ እሷ ራሷ አክስቷ ቤት መሄድ የምትፈልግበት ሌላ ጉዳይ ስለ ነበራት አጋጣሚው ደስ አሰኛት። የሄኖክን አድራሻ ለማግኘት ካሰበች ሰንበትበት ብላለች። አድራሻውን የምታገኘው ቀድሞ ከፃፈላት ደብዳቤ ላይ ነው። ቀድሞ የተፃፃፉት ደብዳቤዎች አክስቷ ቤት በሚገኘው የግል ሳጥኗ ውስጥ ከደብተሮች መሀል ደብቃ ማስቀመጧን በደንብ ታስታውሳለች።

እንደተለመደው አክስቷ ቤት የመጣችው የሰማይነህ ፍቃድ ተጠይቆ በጎርፉ ሹፌርነትና ጠባቂነት ነበር። ምሳቸውን አብረው ከበሉ በኋላ ጎርፉ ህይወትን ሊወስድ የሚመጣበትን ሰዓት ረዘም አድርገው ቀጥረውት ለጊዜው ሊወስድ የሚመጣበትን ሰዓት ረዘም አድርገው ቀጥረውት ለጊዜው ሸኙት። ህይወትና አክስቷም ተዝናንተው መጫወት ጀመሩ።

«.....ያረድኩትን ሙክት በግ ማን እንዳመጣልኝ አውቀሻል?» አለቻት ወ/ሮ ሰራሽ አርዕስቱን መክፈቻ እንዲሆናት።

«ማን አመጣልሽ?»

«ባልሽ ነዋ....ሰማይነህ።

‹በደንብ ይዞሻላ!› አለች ህይወት በልቧ።

«ከአሁን በፊት የወርቅ ስጥቶአ እንዳመጣልኝ ነግሬሻለሁ» ብላ ድንገት ተነስታ ወደ መኝታ ክፍሏ ሄዳ አመጣችው። «ይሄውልሽ....ያውም ትልቅ የእጅ አምባር ነው። ያለ ጥርጥር መቶ መሐለቅ ያወጣዋል።»

«ጥሩ ነው» አለች ህይወት ስሜት በሌለው ድምፅ።

«ይገርምሻል.....በተለይ አንቺን ካገባ ወዲህ በቅርበት እንዳየሁት፣ ሰማይነህ ልቡ ውስጥ ክፋት የሌለው ቅን ሰው ነው። ልቡ ለወደደውና ላመነበትም ቸር ነው። እንዲሁ ላይ ላዩን ቁጡ በመሆኑና ግንባሩ ስለማይፈታ ብቻ ለማያውቀው ሰው ክፉ ሊመስል ይችላል»

ህይወት መከራከር አልፈለገችም። አክስቷ ወደ ሰማይነህ እየወገነች መምጣቷንና የቅስቀሳ ተልዕኮዋን እየተወጣች መሆንዋን በመገመት ክፉም - ደግሞ ሳትናገር ማሳለፍ ፈልጋ ነበር። ሆኖም ድንገት ስሜትዋ ፈነቀላት።

«ለእኔ ግን ሰማይነህ ክፉኛ ጨካኝ ነው። በአደባባይ ጥርሴን ከማውለቅ ሌላ ምን እንዲያደርገኝ ትፈልጊያለሽ?!»

«አሰነዛዘሩ ላይ ሰይጣን ተጨምሮበት ነው እንጂ ሊጎዳሽ አስቦ አልነበረም። በተፈጸመበት ሁኔታ በጣም ማዘኑን ነግሬሻለሁ። ዱላው የክፋት እንዳይመስልሽ.....የቅናት ነው። አብዛኛውን ጊዜ የሚቀኑ ባሎች ደግሞ ደጋጎች ናቸው። ቀናተኛ ስሜታቸው ግልፍተኛ ያደርጋቸዋል እንጂ ሆዳቸው ባዶ ነው.......»

«እኔ እንዲህ አይነት ደግነት አይገባኝም።.....»

«ታዲያ ለእኔና ለአንቺ የስጦታ መአት ማዥጎድጎዱን ምን ትይዋለሽ?!......በተፈፀመው ነገር ልቡ ማዘኑን አያሳይሽም?!......»

«ደብድቦ ካሳ መክፈል የክፉዎች የሽንገላ ዘዴ ነው። ለስጦታ እጁን ከሚዘረጋልኝ ልቡን ንፁህ ቢያደርግልኝ እመርጣለሁ» አለቻት በምሬት።

«ቅድም እንዳልኩሽ.....አሰነዛዘሩ ነው እንጂ....ባል ሚስቱን የመቅጣቱ ነገር ድሮም ያለ ነው። ሚስቶቻቸውን በፍልጥ የሚያገላብጡ፣ የወጥ ማማሰያዋን ከእጇ ላይ ቀምተው የሚዠልጡ ባሎች እንዳሉ አውቃለሁ። በዚህን ጊዜ ሚስት ማኩረፏም ወግ ነው። በኋላ ካሳው ሲመጣላት ፈገግ ትላለች። እኔ ክፉዎች የምላቸው ወንዶች ከሴቷ ላይ የሽንኩርት መክተፊያ ቢላዋውን ቀምተው ለመውጋት የሚሰነዝሩትን ነው......»

«ይህ ሁሉ ግፍ ለምን ያስፈልጋል?!......» አለች አሁንም ህይወት በምሬት ድምፅ» ባልና ሚስቱ ከተስማሙ አብረው መኖር.....ካልተስማሙም በሰላም መለያየት ነው እንጂ ሴቷ እንደ አህያ የምትደብደብበት ምንም ምክንያት የለም። አሁን በዚህ የሚያምኑ ወንዶች ኋላ ቀርነት ብቻ ሳይሆን ሌላ ትልቅ በሽታ አዕምሮአቸው ውስጥ ሳይኖር አይቀርም።»

«ድሮ ሲደረግ የኖረ ነው»

«እባክሽ ተይኝ እማዬ....ድሮና ዘንድሮ የተለያየ ዘመን ነው።

«ለማንኛውም የወንዶችን ቅናት ማርከሻ መድሐኒቱ ልጅ መውለድ ነው «በማለት ወ/ሮ ስራሽ አዕምሮዋ ውስጥ ስታውጠነጥነው ወደቆየችውና ወደ ተዘጋጀችበት ጉዳይ በቀጥታ ገባች። «....የአብራካቸውን ክፋይ ሲያገኙ ፍቅሩ ስለሚከፈልላቸው ቅናቱ ይቀንሳል።»

አክስቷ ለምን አጥብቃ እንደፈልገቻት ህይወት አሁን ገባት። ዙሪያ ጥምጥም ውይይቱ እዚሁ ነጥብ ላይ ለመድረስ መሆኑን ገመተች። ሰማይነህና እናቱም በፊት ለፊትና በጎድን ሲጠይቋት የከረሙት ጥያቄ በመሆኑ የአክስቷን ተልዕኮ ደረሰችበት።

«እንዴት ነው?.....አንቺ ገና ነሽ እንዴ?» አለቻት ወ/ሮ ስራሽ የህይወትን ሆድ በፈገግታ እየተመለከተች።

«.....ምን?» አለቻት ህይወት አውቃ።

«እርግዝናውን ነዋ።.....ፍሬ መያዝሽን?»

«ይህንን ጥያቄ የሰማይነህ እናት ከሙቶ ጊዜ በላይ ጠይቀውኛል።»

«ታዲያ ምን መልስ ሰጠሻቸው?.....የልጅ ልጅ ለማየት በጣም ጉጉ መሆናቸውን መዘንጋት የለብሽም።»

ሆዷን ‹በእጇ መዳፍ እየተጫነች «ይኸው..... ምንም ነገር የለም» አለቻት።

«እንዴት ሊሆን ይችላል?.....መከላከያ መድሐኒት ሲጠቀሙ የኖሩ ሴቶች ናቸው ቶሎ የማይወልዱት» በማለት የጎድን ጥያቄ አቀረበችላት።

«እኔ እንጃ» አለች ህይወት ትከሻዋን ነቅንቃ።

«የኔ ልጅ መቼም.....መድሃኒት እንደማትጠቀሚ እተማመንብሻለሁ»

«እኔ ምንም አይነት መከላከያ አልተጠቀምኩም። ሆኖም ግን እስካሁን ያለ ማርገዜ በጣም ደስ ይለኛል።

«እንዴት?...... ለምን?»

«አብሬ መኖር ከማልፈልገው ሰው መውለድ ምን ያደርግልኛል?! እውነቱን ልንገርሽ እማዬ.....ልጅ የመውለድ ስሜቱም ሆነ ፍላጎቱ ፈፅሞ የለኝም። እግዚአብሔርም ልቤን አይቶ እየተከላከለልኝ ይሆናል።»

«ተይ እንጂ ህይወቴ፤ እንደሱ አይባልም። የሰው ልጅ ዘሩን ካልተካ ምን ዋጋ አለው?!.....የትዳር ትርጉሙ የሚታወቀውም ልጆች ተወልደው ቤቱን ሲያደምቁት ነው። ወልዶ መሳምን የመሰለ ፀጋ የለም። አንቺም በሰማይነህ ላይ ያለሽ ቅሬታ ልጆች ስትወልጂ እየተከፈልሽ ይሄዳል። ልጆቻችሁ የትዳራችሁ ማጥበቂያ ዋልታ ይሆኑላችኋል።»

ህይወት በመከራከር ግምት ውስጥ መግባቱ አስጠላት። ምናልባት ስሜት ፈንቅሏት አክስቷን መጥፎ ነገር እንዳትናገራትም ፈራች። ምርጫው ዝም ብሎ ማዳመጥና በአንድ ጆሮ ሰምቶ በሌላኛው ማፍሰስ ነው። ይልቁንም ልቧ የቸኮለው የአክስቷ ምክር አልቆ ወደ ጓዳ የምትገባበትንና የሄኖክን የደብዳቤ አድራሻ የምትፈልግበት ጊዜ ነው።

«......ደግሞም አንድ ትልቅ ነገር ማወቅ አለብሽ......» በማለት ቀጠለች ወ/ሮ ስራሽ» ይሄን ሁሉ የተትረፈረፈ ሀብት የሚያወርሱ ልጆች ያስፈልጉሻል። ካለበለዚያ ሀብታችሁ ሁሉ ሜዳ ላይ ተበትኖ የማንም መጫወቻ ሆኖ ነው የሚቀረው»

«ይቅርታ አድርጊልኝና.......የሰማይነህ ሀብት የኔ ሀብት ሆኖ አይሰማኝም። እንዲሆንም አልፈልግም» አለች ህይወት ሳታስበው ስሜት ፈንቅሏት።

«እንዴ!.....ያንቺም ሀብት ነው እንጂ!.....ባልና ሚስት.....አንድ አካል አንድ አምሳል ከሆናችሁ በኋላ ህጉም ይፈቅዳል። በዚህ ላይ ደግሞ ልጆች ሲጨመሩበት የጋራ ባለቤትነቱን ያጠነክሩታል። የሰማይነህ ሀብት ካንቺም አልፎ የልጆችሽ ሀብት ይሆናል። ‹ከደህና ተወለድ ወይንም ከደህና ተጠጋ› የሚባለው ያለ ምክንያት ይመስልሻል እንዴ?› አይደለም። ልጅ ራሱ ሀብት ነው። ሀብት ውስጥ የሚወለድ ልጅ ደግሞ የሀብት ሀብት ነው።»

በድግግሞሹ የአክስቷ ምክር ህይወት ተሰላቸች። የልጅ - ልጅ ማየት የማንኛውም እናት ጉጉት ቢሆንም ከሀብት ጋር አያይዞ ማስላት ግምት ላይ ይጥላል። ደሀ እናቶች ልጅ ሲወልዱ ፍቅርና ተስፋን ተመርኩዘው እንጂ ምንም የተጨበጠ ነገር ይዘው አይደለም። ህይወት ስለ አክስቷ ይበልጥ ለማሰብ ተገደደች። በልጅነት ዘመኗ በቂ የእናትነት ፍቅር ሰጥታ በእንክብካቤ ማሳደጓና አሁን የአማቿ ጠበቃ ሆና የልጇን ስሜት እየተጋፋችና እያፈነች የመቆሟ ነገር ተቃራኒ አቋሞች ሆኑባት። ለእርድ የሚዘጋጁ የቤት እንስሶችና የሚደልቡ ከብቶች በሀሳቧ ውስጥ መጡባት። ‹በልጅነታቸው እንስሶች ፍቅርና እንክብካቤ የሚደረግላቸው በጥሩ ሁኔታ አድገው እድኒታረዱ ወይንም ሲሸጡ ደህና ዋጋ እንዲያወጡ ነው፤ ከብቶች የሚደልቡትም ሰብተው ጮማቸው እንዲቆረጥ እንጂ በፍጡርነታቸው ታዝኖላቸው አይደለም ስትል አሰበች። ምናልባትም አክስቴ በጥሩ ሁኔታ ያሳደገችኝ አሁን ጥሩ ዋጋ እንዳወጣላት ይሆናል። ስሜቱን ያለመረዳቷና ከእኔ ላይ መፍረዷ የሚያሳየኝ ይህንን ብቻ ነው› በማለት አምርራ አሰበች።

በሌላ በኩል ደግሞ አክስቷ ይህን ያክል ክፉ ያለመሆኗንና ለጥቅም መታወሯም የተፈጥሮ ሳይሆን የውስኪ ቤት ስራዋ ያተረፈላት በሽታ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ምሬቷን ለመቆጣጠር ሞከረች። የውስኪ ቤቷ ንግድ የመጣውን ሁሉ ሙብለጥን ይጠይቃል፤ ማትረፍን ይጠይቃል። በማንም ላለመበለጥና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለማትረፍ ማስላት እያደር ሰብአዊ ፍቅርን ሊቀንስና ፈፅሞም ሊያጠፋ በማንኛውም ጊዜ ከውስጥ ብቅ ብሎ ሊያጥፈው ይችላል። አንዳንዴም ይሉኝታንና ምክንያታዊነትን ደምስሶ ሰዎችን ለጥቅም ብቻ የቆመ አራዊት ያደርጋቸዋል። የሰው ፍቅር በፍቅረ - ነዋይ ሲተካ ለማንም፣ አለምንም ደንታ ያሳጣል።....

«.....ካልሆነ ሐኪም ዘንድ ሄደሽ ብትመረመሪስ?» በማለት ወ/ሮ ስራሽ ስትተነፍስ ህይወትን ከሀሳቧ አባነነቻት።

ለምኑ?.....»

«ለእርግዝናው ነዋ።....ሐኪሞች ዘዴውን ይነግሩሽ ይሆናል። የጤና ችግርም ካለ በህክምና ያቃሉታል።»

«ካገባሁ ገና አጭር ጊዜዬ ነው። ይህን ያህል አጣድፎ ዘዴ የሚያስፈልግ አይመስለኝም።»

«ጊዜው እንኳ ፍሬ ለመያዝ የሚያንስ አይደለም።.......የባልና ሚስት ፍቅር ቀንሶ መሰላቸት ሳይከተል ፈጠን ብሎ ልጅ መስጠት ያስፈልጋል። ተመርመሪ ግድየለሽም። ምንም አይጎዳሽም ህይወቴ።»

ህይወት ሌላ ሀሳብ ውስጥ ገባች። ‹ይሄ ሁሉ ምክር ማሰሪያ ገመዴን ለማጥበቅ ነው› አለች በልቧ። መጀመሪያ የፈትነት ሀሳብ በአዕምሮዋ ውስጥ ለኩሳ እንዳሰረቻት አስታወሰች። የጥርሷን መውለቅ በአካለ ስንኩለነት ጋር ስታያይዝባት ሁለተኛው ማሰሪያ ሆነ። አሁን ደግሞ ልጅ መውለድ ሦስተኛውና ዋናው ማሰሪያ ገመድ ሆኖ እንደቀረበላት አድርጋ ወሰደችው። የዕድሜ ልክ እስረኛ!.....

‹ሞኛችሁን ፈልጉ!....በአጋጣሚ ባረግዝ እንኳ ተደብቄ አስወጣዋለሁ እንጂ ከሰማይነህ ልጅ አልወልድም አለች በልቧ።

«ትሰሚኛለሽ ህይወቴ?....»

«አዎ ሰምቼሻለሁ እማዬ.....መጀመሪያ ሰማይነህ ራሱ ይመርመር።»

«እሱማ ወንድ ነው....»

«ታዲያ ወንድ አይመከንም ያለው ማነው?.....»

«ኤጭ! ከርከር ምንም ያደርጋል?!.....መጀመሪያ አንቺ ተመርመሪ እስኪ.....»

«መመርመሩ ችግር የለውም። እኔ ግን መውለድ የምችል ሴት መሆኑን ሙሉ በሙሉ እተማመናለሁ።» ብላ መልሷን አድፈንፍና አልፋ ከተቀመጠችበት ተነሳች። አሁንም ስሜቷን የወጠረው የሄኖክን አድራሻ ፈልጎ የማግኘቱ ሀሳብ ነው። አክስቷን በጨዋታ አዘናግታት፣ ጎርፉ ተመልሶ ከመምጣቱ በፊት፣ ወደ ጥንቱ መኝታ ክፍሏ ገባች። አክስቷ አላወቀችም፤ ወደ መፀዳጃ ክፍል የገባች ነው የመሰላት።

ህይወት የድሮ ሳጥኗን ከፍታ የትምህርት ቤት ደብተሮቿን ስታገላብጥ የሄኖክ ደብዳቤ ተጣጥፎ እንደ ተቀመጠ አገኘችው። ገና ውጭ ሀገር የሄደ ሰሞን የሚልክላት ደብዳቤዎች በፍቅር ስሜት የተሞሉና የፍቅር እንባ ያረጠባቸው ነበሩ። ህይወት ሄኖክን በአካል ያገኘችውና ያየችው ያል ልቧ ተሸብሮ ከደብዳቤው መሀል አለፍ አለፍ እያለች አነበበች።

«.....ህይወትዬ!....የኔ ፍቅር!.....ናፍቆትሽ አላስቆም፣ አላስቀምጥ ብሎኛል። ከተለየሁሽ ጀምሮ አዕምሮዬ ሰላም አላገኘም፤ ልቤም አልረጋም። ምግብ አልዋጥ ብሎኝ ጉሮሮየ ላይ ይታገለኛል፤ እንቅልፍም ነስቶኛል.....የባዕድ ሀገር ባዕድነት ከማንም ይበልጥ ለእኔ ተሰምቶኛል.....የኔ ቆንጆ.....የኔ ዓይናማ!.....ህይወትዬ......ናፍቆትሽን አልቻልኩም.....ሳስብሽ ውዬ! ሳስብሽ አድራለሁ። ፈፅሞ ከሀሳቤ አትጠፊም። ብቸኝነቱን መቋቋም አልቻልኩም።.....»

የህይወት ዓይኖች እንባ አቀረሩ። ትዝታ ውስጥ ስምጣ በእንባ ጎርፍ ከመጥለቅለቋ በፊት ደብዳቤውን መልሳ አጠፈችው።

‹ያን እንዲህ አይነት ደብዳቤ ይፅፍልኝ የነበረው ሄኒ አሁን ድምፁ የጠፋው ለምን ይሆን?.....ችግር ደርሶበት ይሆን? ወይንስ ሌላ መተኪያ ፍቅረኛ አግኝቶ ይሆን?› ስትል አሰበች። የኋለኛውን ሁሳብ መንፈሷ አልተቀበለውም። ‹አያደርገውም!.....ሄኒ ከእኔ ሌላ አያፈቅርም። .....ለማንኛውም ጥፋቱ የእኔ ነው። ያኔውኑ ሄኒን ተከትዬ መጥፋት ነበረብኝ› አለች።

ደብዳቤውን ይዞ መሄዱ ለጥንቃቄም እንዳያመች ገምታ አድራሻውን የመኪና ከላዩ ቀድዳ ጡት መያዝዋ ውስጥ ደበቀችው።

ወደ ሳሎን ተመልሳ ከአክስቷ ጋር ትንሽ እንደ ተጨዋውተች የምታውቀው የመኪና ጥሩንባ ድምፅ ሰማች።

«ሹፌሬ መጣ» አለችና በፈዝ ሳቀች።??

ሙቀት ስለ ነበር ጎርፉ የሸሚዙን ቁልፎች ፈትቶ፣ ደረቱን ገልብጦ፣ ላቡን እየጠራረገ መኪናውን አዙሮ አቆመ።

«ቶሎ መጣህ» አለችው ህይወት አክስቷን ተሰናብታ መኪናው ውስጥ ከገባች በኋላ።

«አዎ፤ ስራ የለም።.....ቢኖርም ሙቀቱ አያሰራም›. እያለ ጎርፉ መሾፈሩን ቀጠለ።

‹በአንተ ቤት እኔን ጠብቀህ ልብህ ወልቋል። ጅል!....አክስቴ ቤት ምን እንደሰራሁ አታውቅም። የፍቅረኛዬን አድራሻ ፈልጌ ማግኘቴን ብታውቅና ለወንድምህ ብትነግረው እብድ እንደሚሆን ይታየኛል። ከእንግዲህ ወዲያ ዓይናችሁ ስር የምጫወተውን ትርኢት ማየት አትችሉም› አለች ህይወት በልቧ።

ነገሩን ስታስበው አሳቃት። የሰማይነህ ስጋትና የጎርፉ ክትትል ህይወት በማንኛውም መንገድ ሌላ ወንድ እንዳታይ ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዳትገናኝና ልቧ እንዳይሸፍት ለመጠበቅ ነው። ሆኖም የአካል እንቅስቃሴዋን ቢወስኑትና ቢያግዱትም ቅሉ ልቧን ማግኘትና ማገድ አልቻሉም። ልቧ አሁን ሀገር አቋርጦ ሄዶአል፤ ወጣት ፍቅረኛዋን ፍለጋ ኮብልሏል። ስሜቷ የእስረኛነት ገመዱን ለመበጣጠስ ተነሳስቷል።

‹ጅሎች!....አስራችሁኝና ጠብቃችሁኝ ልባችሁ ወልቋል!› አለች እንደገና በሀሳቧ።

«ምነው ሳቅሽ?» አላት ጎርፉ

«አካሄዳችንና መንገዱ ያስቃል» አለችው።

«መንገዱ ብላሽ ነው። ለዚህ ነው እኮ እየመረጥኩ የምነዳው፤ ምቾትሽን ባለመጠበቄ ይቅርታ።
»

«ምንም አይድለእም፤ ችግርህ ይገባኛል» ካለችው በኋላ ‹ያንተም አስተሳሰብ እንደ መንገዱ ብላሽ ነው› አለች በልቧ።

«እንዲህ አይነት መንገድ ብራቾ ይሰብራል። መጥፎ ነው» አላት።

‹እናንተም የሰው ልብ ትሰብራላችሁ። መጥፎዎች ናችሁ› አለችው እሷም በልቧ።

ሳታስበው ነገረኛ ሆናለች። በጎርፉ ላይ ያላትን ብሽቀት የምትወጣው እንዲህ የጎድን በመናገርና በማይገባው መንገድ በመዝለፍ ነው።

«አደራህን ለሰማይነህ እንዳትነግረው....» አለችው ትንሽ ስታስብ ቆይታ።

«ምኑን?....እ» አለ ጎርፉ ግር ብሎት።

«የመንገዱ ብላሽነት ነዋ!»

«ምነው....ይህን ያህል ወሬኛ አደረግሽኝ እንዴ?» ብሷት አኮረፈ።

«አንተ ደግሞ ቀልድ አይገባህም። እኔ የተናገርኩት የቀልዴን ለጨዋታ ያህል ነው» ብላ ካባበለችው በኋላ ‹ከብት ሆነህ ነው እንጂ፣ ወሬኛነትህን ሌላ ሰው እስኪነግርህ መጠበቅ አልነበረብህም አለችው በልቧ።

ትንሽ አለፍ ብለው እንደሄዱ አንድ የደነበረ በሬ መንገደኛውን ሁሉ ቦታ እያስለቀቀና እያንሜጫጫ ሲፈረጥጥ ተመለከተ። ሁኔታው ህይወትን ቢያስፈራትም ጎርፉ ይበልጥ ተደናግጦ ማየቷ ደስ አሰኛት። የመኪናውን መሪ እንደያዘ ላብ እያሰመጠው ነበር።

«በሬ ትፈራለህ እንዴ?.....» አለችው።

«የደነበረ በሬ ማስፈራቱ የት ይቀራል!»

‹አንተ ራስህ በሬ ነህ› አለችው በልቧ።

«.....የፈራሁት እንኳ ለራሴ ሳይሆን የመኪናውን መስታወት እንዳይሰርብርብኝ ነው» ብሎ ላማስተባበል ሞከረ።

‹ሆዳም ሰው ፈሪ መሆኑን አውቃለሁ እባክህ። እንዲያው በከንቱ አትዘላብድ› አለችው እንደገና በልቧ።

ቤታቸው ሲደርሱ ጎርፉ ቆሞ የህይወትን ወደ ውስጥ መግባትና የሰማይነህ እናት መረከባቸውን ካረጋገጠ በኋላ ወደ ታክሲ ተመልሶ ሄደ።

«ደህና ዋልሽ?.....እናትሽ እንዴት ናት?» አሏት አሮጌቷ።

«ደህና ናት። ታዲያ?.....መላ መላ ፈልጋችሁለት?»

«ለምኑ?....»

«ለሁሉም ነገር ነዋ።....እናትና ልጅ ሲገናኝ መመካከሩ አይቀርም ብዬ ነው።»

ህይወት ነገሩ ገባት። ሆኖም አዕምሮዋን ወጥሮ የያዛት ለሄኖክ የምትፅፍለት ደብዳቤ ሀሳብ ስለ ነበር ከሰማይነህ እናት ቶሎ የምትለይበትን መንገድ ፈለገች።

በሀሳቧ ‹የልጅዎትን አንጀት የምቀድበትን መላ አግኝቻለሁ። የፍቅረኛዬን አድራሻ ይገኙ መጥቻለሁ› እያለች ውሸቷን ምክንያት ፈጥራ «እማማ፤ ራሴን በጣም ስላመመኝም ለትንሽ ሰዓት በዕንቅልፍ ማሳለፍ እፈልጋለሁ» ብላቸው ወደ መኝጣ ክፍሏ ገባች።

መኝታ ክፍሉን ከውስጥ ቆልፋ የመስኮቶቹን መዘጋት ካረጋገጠች በኋላ ደብዳቤዋን ለመፃፍ ብዕርና ወረቀቷን ይዛ ቁጭ አለች። እንዴት እንደምትጀምረው ከብዷት ከወረቀቱ ጋር ተፋጥጠው ትንሽ ከቆየች በኋላ አንዴ ሀሳቧን ማስፈር ስትጀምር ተዥጎደጎደላት።

«ሄኒ፣ እንደምን አለህ? ምነው እንደዚህ ድምፅህ ጠፋብኝ? በሰላም ነው ወይንስ.....መቼም እኔን በሌላ ሴት ትለውጠኛለህ የሚል እምነት የለኝም። ተለይተኸኝ የሄድክ ሰሞን የፃፍክልኝን ደብዳቤ ሳነብ የተሰማኝን ስሜት ልገልፅልህ አልችልም። አሁን ደብዳቤህ ተቋርጦ በመቆየቱ ተናደድኩ።

«ሄንዬ! ዛሬ ይህን ደብዳቤ የምፅፍልህ እስር ቤት ውስጥ ሆኜ ነው፤ ያውም ጭለማ ክፍል ውስጥ!....የታሰርኩበትን የብረት ሰንሰለት ሰባብሬ ለመውጣት ያለኸኝ ተስፋ አንተ ብቻ ነህ። የርቀት ድምፅህን አሰማኝ፤ አለሁልሽ በለኝ፤ ምንጊዜም ያንቺው ነኝ በለን ሄንዬ!

«ነገሩ ግራ እንዳያጋባህ ግልፅ ላድርግልህ። መጀመሪያ ግን በሆነው ነገር ሁሉ እንዳታዝን ልብህን አጠንክር። ከአቅሜና ከቁጥጥሬ ውጭ የሆነ ነገር ነው። በያዝነው አመት መጀመሪያ ላይ ተከታልቤ ባል አግብቼ ለትዳር በቅቻለሁ። እስር ቤት የምልህ ይህንን ትዳሬን ነው። ካገባሁት ሰው ጋር የቆየ ትውውቅ አልነበረንም፤ በፍቅር አልተቀራረብንም፤ አብረን ለመኖር በቅድሚያ አልተጠናናንም። ሰውዬው በሀብቱ የታወቀ የአክስቴ ውስኪ ቤት ደንበኛ ነበር። ድንገት እንደ ዱብ

ዕዳ የጋብቻ ጥያቄ አቀረበልኝ። ጥያቄው አስደንግጦኝ እንዳስብበት ጊዜ እንዲሰጠኝ ብጠይቀውም የማይቻል ሆነ። አክስቴ አካልባ ወሰነችበት፣ እኔም ተከታልቤ ወሰንኩ። በውሳኔ መሀል አንተን አስታወስኩ። ሆኖም ደብዳቤህ ርቆን ስለቀየ ምንም ማድረግ አልቻልኩም። ለትዳር ለመጠየቅ ሰውዬ እጄን ሰጥቼ በቀጥታ ወደ እስር ቤት ወረድኩ።

የባሌን የቅናት ደረጃ በቃላት ልገልፅልህ አልችልም። ሲበዛ ቀናተኛ ከመሆኑ የተነሳ ሽንት ቤት ስገባ እንኳ ተከትሎኝ ይገባል። የቅናት ንዝንዙ የጀመረኝ የሠርጉ ዕለት ማታ ነበር። አሁን ከተጋባን ከሦስት ወራት በላይ ሆነን። ሆኖም ለእኔ ይህ ጊዜ ከሠላሳ አመታት በላይ ሆኖ ነው የተሰማኝ። በየቀኑ ዕድሌን እየረገምኩት ነው። ሰውዬው በዚች አጭር ጊዜ ውስጥ ከጭቅጭቅ አልፎ በቦክስ ጥርሴን አውልቆታል። የየዕለት ግንኙነታችን እንዴት እንደሚያስጠላ ልነግርህ አልችልም። ጤናማ ፍቅር ከሌለ በስተቀር በአንድ ጣራ ስር መኖር ምንም ትርጉም እንደሌለው የተረዳሁት አሁን ነው። ሀብት ሞልቶ ቢተርፍ ፍቅር ከሌለበት ዋጋ የለውም።

«ሄንዬ። አሁን ብታየኝ ታዝናለህ። ድሮ የምታውቀኝ ህይወት አይደለሁም። እንዳልስቅ እንዳልጫወት ተከልክዬ ጥርሴን ከድኜ እያለቀስኩ ለመኖር ተገድጃለሁ። አንዳንዴ አንተን እያስታወስኩ እተክዛለሁ፤ እናትና አባቴን እያስታወስኩ ብቻዬን አለቅሳለሁ። አልጋዬ ላይ ተደፍቼ ከማልቀስ በቀር ምርጫ የሌለኝ ፍጡር ሆኜልሀለሁ። አንዳንዴ ተነስተሽ ብረሪ ጥፊ የሚል ስሜት ይፈታተነኛል። ግን ወዴት አባቴ እሄዳለሁ?! ምን መሄጃ አለኝ?! አክስቴ እንደሆነች የድሮዋ እማዬ መሆኗ ቀርቷል፤ ገንዘብ ለውጧታል። ሁልጊዜ አንተን አስብሀለሁ። አንተ ያለህበት ሀገር ደግሞ ሩቅ ነው።

«ሄኒ፤ የወጣትነት አፍላ ፍቅራችንን ታስታውሰዋለሁ?.....እንዴት ደስ ይል ነበር! ያንን ዓይነት የፍቅር ትኩሳት መቼውንም ደግሜ የማገኝ አይመስለኝም። ፍቅርን የማውቀው በአንተ ነው፤ ለፍቅር የመጀመሪያዬም የመጨረሻዬም ነህ። ትምህርት ቤት ስንሄድና ስንመጣ፣ ማታ ማታ ወደ ቤቴ ስትሸኘኝ፣ አብረን እያጠናን ፍቅር አሸንፎን ደብተሩ ሳናስበው ከእጃችን ላይ ተንሸራትቶ ሲወድቅ የነበረው ሁኔታ ሁሉ አዕምሮዬ ውስጥ እንደ ስዕል ተቀርጾ ይታየኛል። ብቻችንን ጨለማ ውስጥ ለረዥም ሰዓት ቆመን ያወራንበት ጊዜና ሁኔታ እስካሁን ይታወሰኛል። ለመጀመሪያ ጊዜ ከንፈር ለከንፈር የተሳሳምንበትን ቦታም ሁልጊዜ ዓይኔ ላይ ይመጣብኛል። ዘፈን ለማዳመጥ አዘውትረን የምገባበት ካፌቴሪያ እስካሁን ትዝ ይለኛል ከሁሉም በላይ ደግሞ ከከተማው ወጣ ብሎ ወደሚገኘው መናፈሻ የሄድን ዕለት......ይህንን አንተም በደንብ ታስታውሰዋለህ። ሄኒ ለዘለአለሙ የማይረሳ ቀን ነው። ኡፍ! አሁንም ትዝታዬን ቀስቀስከብኝ። አልቅሽ - አልቅሽ አለኝ። የፍቅር ረመት መላ ሰውነቴን አበለበኝ። የትዝታው ትኩሳት ከእግር እስከራሴ ነዘረኝ።....

«እባክህ ድምፅህን አሰማኝ ሄኒ። አለሁልሽ በለኝ። ከታሰርኩበት የጭቆናና የባርነት ቀንበር አላቅቀኝ። በነፍሴ ድረስልኝ ሄንዬ! በዚህ ምድር ላይ ከአንተ ሌላ ተስፋ የምጥልበት ምንም ዘመድ የለኝም። የፍቅር እጆችህን ከርቀት ዘርጋልኝ፤ ወፍ ሆኜ እመጣለሁ። ደብዳቤዬ እንደ ደረሰህ መልስህን በአስቸኳይ ፃፍልኝ። ቻው ሄንዬ።

ምንጊዜም አፍቃሪህ

ህይወት ስዩም።

ደብዳቤውን ፅፋ ጨርሳ የሄኖክን አድራሻ ከፃፈችበት በኋላ የራሷን አድራሻ የትኛውን እንደምትፅፍለት ግራ ገባት። ድሮ የምትፃፃፍበትን የአክስቷን አድራሻም ሆነ አሁን የሚጠቀምበትን የሰማይነህ አድራሻ መስጠቱ ለሚስጥሩ መጠበቅ አመቺነት እንደሌለው ገመተች። ቀድሜ ያላሰበችበት ጉዳይ ስለ ነበር ለጊዜው ትን አስጨነቃት። ወዲያው ግን ከመደምደሚያ ጋር ተነጋግሮ ቤተሰብ በማያውቀው አድራሻ የመጠቀሙ ሀሳብ መጣላት።

መደምደሚያ ወደ ቤት እስኪመጣ ድረስ ደብዳቤውን በጨርቅ ጠቅላላ ደበቀችው። ጭለማ ከመያዙ በፊት መደምደሚያ መፅሐፎቹን ተሸክሞ መጣ። መፃህፍቱን በያዛበት ክንዱ በኩል ሰውነት አጋድሎ ስታየው ህይወት በቅጥነቱ አዘነችለት። ጎርፉም ሆነ ሰማይነህ ማታ ማታ መጠጥ ሳይቀማምሱ ሰለማይመጡ ከመደምደሚያ ጋር በነፃነት ማታ ማታ መጠጥ ሳይቀማምሱ ሰለማይመጡ ከመደምደሚያ ጋር በነፃነት ለመነጋገር ጊዜ ከማግኘቷ ህይወት ደስ አላት። እናትየዋ ለመደምደሚያ እንደሚሸነፉ ታውቃለች።

«.....መምጣትህን በጉጉት ስጠብቀው ነበር» አለችው ሰላምታ ተለዋውጠው እድነ ተቀመጠ።

«ምን አዲስ ነገር ተገኘ?.....» አላት።

«በቀደም የነገርኩህ.....የልጅነት ፍቅረኛዬ.....» ብላ በጨርቅ የጠቀለለችውን ደብዳቤ አውጥታ ሰጠችው።

«.....ፃፈልኝ እንዳትይኝ?» አላት ተቻኩሎ።

«እኔ ፃፍኩልት እንጂ።....አንብበው» አለችው፡

እሱ ደብዳቤውን በተመስጦ ሲያነብ፣ ህይወት በድንገት አንዳች የጥርጣሬ ስሜት ሰፈረባት። እስካሁን ድረስ በቅርብ ያላት ሚስጥረኛዋና የልቧን የምታዋየው መደምደሚያ ነው። አሁንም ከሄኖክ ጋር የምታደርገውን የደብዳቤ ልውውጥ በእሱ በኩል ልታደርግ ነው። ‹ነገር ግን ምናልባት መደምደሚያ ሥጋነቱ አሸንፎት፣ ለወንድሙ ተቆርቁሮ ሚስጥሬን ሁሉ ቢዘከዝክና ጉድ ቢያደርገኝ?....ምናልባት፣ ወጣት እንደ መሆኑ መጠን፣ ራሱ እኔን ቢፈልገኝና መልዕክቴ ለሄኖክ እንዳይደርሰው ቢያደርግብኝስ?› ብላ ተጨነቀች። ሆኖም ሌላ አማራጭ እንደ ሌላት ስታስብ ወስነች። ‹እግዚአብሔር ልቡን አይለውጥብኝ እንጂ እኔ እስረኛ ነኝ፤ ከውጭው ዓለም ጋር ሊያገናኘኝ የሚችል ድልድይ እሱ ብቻ ነው አለች። ዓይኖቹን ትኩር ባል ተመልክታ እሱእንቱን ከውስጡ ነው አለች። ሁሉ ‹ገና በወጣትነቱ በስሏል። በጥቅምም ሆነ በሌላ በቀላሉ የሚለውጥ ሰው አይመስልም› ብላ ተፅናናች።

«እውነት ይህን ደብዳቤ የፃፍው አንቺ ነሽ?» አላት መደምደሚያ፣ አንብቦ ከጨረሰ በኋላ እያደነቃት።

«ታዲያ.....ተጠራጠርክ እንዴ?»

«በዚህ ዓይነት ደራሲ የመሆን ተስፋ አለሽ።»

«በስሜት ስለፃፍኩት ይመስለኛል። በሙሉ ስሜት የሚሰሩት ስራ ይዋጣል። ለቅንብሩ አንተ ያስነበብከኝ የፍቅር መፅሐፎች ሳይረዱኝ አልቀሩም።»

«በጣም ቆንጆ ነው። ህይወት ሙች።»

«አመሰግናለሁ።....አሁን ችግሩ መላኪያው አድራሻ ነው። በአክስቴም ሆነ በሰማይነህ ሳጥን በኩል መላላክ ለአደጋ መጋለጥ ነው። ስለዚህ የአንተን ምክርና ድጋፍ እየጠበቅኩ ነበር።»

«ታዲያ ምን ችግር አለው?......በእኔ አድራሻ በኩል ሊመጣልሽ ይቻላል።»

«በዩኒቨርስቲ በኩል ማለትህ ነው?....»

«አይደለም። በራሴ ቁልፍ እኔ ብቻ የምከፍተው የግል ሳጥን አለኝ» ሲላት ደስታዋ ገደብ አጣ። በአስቸኳይ እንዲልከው ተስማምተው ደብዳቤውን ወሰደው።

‹እግዜር ሀሳብሽን ባሳካልሽና መውጫ መንገድሽን ባመቻቸልሽ› አለ መደምደሚያ በልቡ። ጠንቋይ ነግሮናል ብለው እናቱ ያጭውቱት ትዝ አለው። ‹ህይወትን ያንገፈገፋት ጊዜያዊው መታፈንና ፍቅር ማጣት እው። በጠንቋይ ምክር ተነሳስተው እስከዘለዓለሙ እስረኛ ሊያደርጉዋት ማሰባቸውን ብታውቅ ታብዳለች!› አለ እያዘነ። እናቱ እንደ ነገሩት እሱም ለህይወት ሊነግራት አስቦ ነበር። ሆኖም ግን ነገሩን ሲያመዛዝነው አዕምሮዋን ሰላም ከመንሳት በስተቀር ምንም አይጠቅማትም።

«አይዞሽ በርቺ። ሀሳብሽ እንዲሳካልሽ ምንጊዜም ከጎንሽ እቆማለሁ። ብሏት ወደ ንባብ ክፍሉ ሲሄድ በልቡ ‹የየዋህነት፣ የወጣትነትና የውበት አምላክሽ ቶሎ አንቅቶሻል› እያለ ነበር።

«እሺ የኔ ደንገጡር አመሰግንሀለሁ» ብላ እሷም በፈገግታ ሸኘችው።.....

ሰማይነህ የመጣው በጣም አምሽቶ ቤተሰቡ ሁሉ ከተኛ በኋላ ነው። ሰክሯል። በር አከፋፈትና አዘጋጉ ስካሩን ያስታውቅበታል። እግሩንና ምላሱንም ጎተት አድርጎበታል። ሳሎን ሲገባ ጭር ብሏል።

«ራት ላቅርብ?.....» አለችው እንቅልፍ ሲያንጎላጅጃት የቆየችው ሠራተኛ።

«እሷ የታለች?!....» አለና አፈጠጠ።

‹ሲጠቁዎት ቆይተው አሁን ነው የተኙት።.....»

«አንቺም ተኚ። ምንም አልፈልግም»

የመኝታ ክፍሉን በር በኃይል ከፍቶ ሲገባ ህይወት ከእንቅልፏ ባንና «በስመ አብ!» ብላ አማተበች።

«ተኝተሻል?!.....የኔ ሴት ወይዘሮ!....በይ ተነሽ! አንቺ ሚስቴ ተኝተሽ ገረዴ ራት የምታቀርብልኝ በምን ምክንያት ነው?» አላት ምላሱ እየተሳሰረ።

ህይወት ከኃይለኛ እንቅልፍ ላይ ሰለባነነች ሁለመናዋን ከብዷታል። በእንቅልፍ ልቧ ስትመለከተው ሰይጣን አጠገቧ የቆመ መሰላት። በጣም መሰከሩን ስለተገነዘበች አለሳልሳ ልታበርደው ሞከረች።

«በጣም ስለመሸ.....ራት አትበላም ብዬ ነው የተኛሁት።»

«ብበላም.....ባልበላም!......ቁጭ ብለሽ መጠበቅ አለብሽ። እስቲ የሚስት ወጉ ይድረስሽ?.....»

በብሶት አመለካከት ቀና ብላ አይታው መልሳ እንገቷን ደፋች። ሰሞኑ አከታትሎ እየሰከረ መምጣት ጀምሮአል። ድብን ብሎ ከሰከረ አርፎ ይተኛል፤ እንዲህ ዓይነት መካከለኛ ስካር ግን ያስለፈልፈዋል፣ ያስቀባጥረዋል፤ አንዳንዴም የውስጥ ብሶቱን እየቀሰቀሰበት ዱላ ይቃጣዋል። ህይወት ገና በለጋ ዕድሜዋ እንዲህ ዓይነቱ ወንድ ላይ የጣላት ዕድሏን እያማረረች ትተክዛለች።

«ምን ታይኛለች?!.....አይነስብሽን እንዳላጠፋው!» በማለት ነገር ፈለጋት።

አሁንም ዝም አለችው። የቀኑ አንሶ በውድቅት ሌሊት እንዲህ መነዝነዙ ስሜቷን አስከፍቶትና ሆድ ብሏት ከውስጧ ፈንቅሎ ሊወጣ የደረሰ እንባዋን እየታገለችው ነበር።

ሰማይነህን ስርቅታ አስቸገረው።ስ ርቅ እያለውም ግን መነዛነዙን አላቋረጠም።

«ፈላጊዎችሽ እያሙኝ ነው ስርቅ የሚለኝ። የታባታቸው ሁሉም አሽንፌ ይኸው አገባሁሽ። እንግዲህ ምን ይዋጣቸው?!.......ጠላቶቼ እያነሱኝ ነው። አፈር ይብሉ!» ብሎ እየተንገዳገደ ወደ

ህይወት አጠገብ ሲቀርብ የመጠጡ ሽታ ገፈተራት። የአሁኑ ብቻ ሳይሆን ሌሊቱን ሙሉ ይህንን መጥፎ ሽታ ስትታጠን ማደሩን ስታስበው ዘገነናት።

«ምነው ፈጣሪዬ!.....ምን አረግኩህ!» ብላ ከመማረሯ ስትታገለው የቆየችው እንባዋ ፈንቅሎ ወጥቶ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።

«አሁን ምን የሚያስለቅስ ነገር ተገኘ?!....› አላት ሰማይነህ የፌዝ ሳቅ እየሳቀ» ሰሞኑን ምክንያት እየፈለግሽ የምታለቅሽበት ሚስጥሩ ምንድነው?!.....የድሮ ውሽሞችሽ እየታወሱሽ ነው?....ወይንስ እነዚያን የሠርግሽ ዕለት የተሰናበትሻቸውን ውርጋጦች እያስታወስሽ ነው?.....እናትሽ ቤት ስትገለፍጪላቸው የነበሩትን የሚያሸኮረሙሽን የውስኪ ደንበኞች እያስታወስሽ ነው?.....ወይንስ ያንን ወጠጤ ልብስ ሰፊ እያስታወስሽ ነው?.....ተናገሪ እንጂ!.....ማን ትዝ ብሎሽ ነው እንዲህ የሚያስለቅስሽ?!.....»

አዕምሮው ውስጥ የተቀረፀ አንድ በጣም የሚጠላው ስም ትዝ አለውና ንዴቱን ቀሰቀሰበት። ስሙን አስታውሶ በሀሳቡ ደጋገመው። ሄኖክ.....ሄኖክ....ሂኖክ.....

«.....ወይንስ ያንን ድንግልሽን የወሰደውን ባለጌ እያስታወስሽ ነው የምታለቅሺው?....እሱን እያስታወስሽ መሆን አለበት። አለቃቀስሽ ያስታውቃል። ከውስጥ እየፈነቀለ ነው የሚያስለቅስሽ። ያ ባለጌ ጎረምሳ ልብሽ ውስጥ ቀርቷል ማለት ነው። ልብስሽ በሳንጃ ዘክዝኬ ካላወጣሁ እኔ ወንድ አይደለሁም። በድን ሰውነትሽ እኔ ቤት ተቀምጦ ልብሽ የሚወሰልትበት ምንም ምክንያት የለም!»

ህይወት እንባዋን ውጣ ከንፈሯን እየመጠጠች ‹አሁን ገና ጥርጣሬህ ትክክክል ሆኗል። ልቤ ባህር ማዶ ተሻግሮ ሄዶአል፤ በድን አካሌ ነው ከአንተ ጋር የሚኖረው። ይህንን ሚስጥር ሰይጣን በጆሮህ ሹክ ብሎህ መሆን አለበት› አለች በልቧ።

«ተናገሪ አንጂ!......መልስ የማትሰጪበት ምክንያት ንቀት ነው? ወይንስ ምንድነው?!» አላት ቁልቁል አፍጥጦባት።

«ምን አድርጊ ትለኛለህ! ኧረ ተው ሰማይነህ ግፍ ነው......»

«የሚያስለቅስሽን ምክንያት ተናገሪ!....»

»አትሳቂ ብለህ ጥርሴን አወለቅከው፤ መሳቁን አቆምኩ። ጥርሴን ከድኜ አቀረቀርኩ። አሁን ደግሞ ማልቀስ ልትከለክለኝ ነው?!......ምን እንድሆንልህ ነው የምትፈልገው?» አለችው በንዴት።

«.....እስካሁን ያላረገዝሽበት ምክንያት ደግሞ ምንድነው?.....ከእኔ ከሰማይነህ ልጅ አትፈልጊም ማለት ነው?» አላት አፉ ላይ እንደመጣለት» መሀን ከሆንሽ ንገሪኝና ወላዷን አምጥቼ አስቀምጣታለሁ።»

«ትችላለህ.....» በግዴለሽነት ዓይነት ትከሻዋን ነቅንቃ።

ግዴለሽነቷን አናደደው። «አሁንም ጥጋብሽ አልበረደልሽም ማለት ነው?! ገና በትዕቢት እንደተወጠርሽ ነሽ! ቆይ ግዴለም፤ ትዕቢትሽን አበርድልሻለሁ። ይህንን የምትኮሪበትን መልክሽን አጨማድድልሻለሁ።.......ሰውነትሽን በጥይት በታትኜ ከአፈር አደባልቅሻለሁ» እያለ ኮቱን አወለቀ።

አዝማሚያው አላማራትም። በመጠጡ ላይ ንዴት ተጨምሮ፣ የቅናት ዛሩ ሲነሳበት እንደሚሆነው የደም ስሮች ተግተረተሩ። በምን መንገድ እንደምታባብለው ግራ ገባት። ስቃ

እንዳታጫውተው መሣቅ ከልከሏታል፤ አልቅሳ ልቡን እንዳታባባው ማልቀስም ከልከሏታል። ከሁለቱ ውች ስሜት አልባ ደረቅ ፍጡር ሆና ስትቀርበው ደግሞ ግዴለሽነቷ ያናድደዋል፤ ተጨነቀች።

ሰማይነህ ከግል ቁልፎቹ መሀል በጣም ትንሿን መክፈቻ ለይቶ አውጥቶ ወደ አልጋው ራስጌ ሲሄድ፣ ህይወት በዓይኗ ተከተለችው። ድፍን የሚመስለውን የእንጨት አልጋ በቁልፉ ከፍቶት ሽጣጣ ሳጥን ስትመለከት ፈዝዛ ቀረች። እስካሁን ያላየችው ነገር ነው። የራስጌው የአልጋ እንጨት ማሰሪያ ቢቴ ከሚመስሉት ውስጥ አንደኛው ቁልፍ ሲሆን የሚስጥር ዕቃ ለመደበቂያ የተሰራ ነው። ሰማይነህ ከአልጋው ሳጥን ውስጥ ክላሽንኮብ መሣሪያ አውጥቶ፣ ለህይወት አሳያት።

«ይሄውልሽ.....በዚህ ነው ሰወንትሽን የምበሳሳልሽ!.....»

ህይወት በድንጋጤ ደነዘዘች። ሰውነቷ በፍሀት ተንቀጠቀጠ። መጮህ አማራት። አንዴ እሪታዋን አቅልጣው ሰዎች እንዲሰበሰቡላት አሰበች። ግን ማንን ረዳት ታገኛለች? የሰማይነህ እናትና ጎርፉ ሬሳዋን ለማውጣት መድረሳቸውም አጠራጠራት። መደምደሚያ ሊደርስላት ቢችል እንኳ ሰማይነህ ደርቦ እንዳይመታው ፈራች። ከዚህ ሁሉ ፀጥ ብላ ትንፋሽዋን ውጣ በዓይኖቿ ብቻ መለመኑን መረጠች። መሣሪያ የሚያስመዝዝ ምንም አይነት ጥፋት ባይፈፀምም ሰማይነህን የያዘው አባዜ በል - በል እንደሚለው ገመተች።

«ም - ምን አረግኩህ ሰማይነህ?......ምን አጠፋሁ?»

«እኔ ላይ እበጣጠሳለሁ ብትይ በዚህ ነው የምበጣጥስሽ!»

«እባክህ እሱን መሣሪያ አስቀምጠው፤ ሠይጣን ነው።»

«በዚህ ዓለም ላይ ከልብሽ የምትወጂውን ሰው ተናገሪ።»

«አንተን ነው» አለችው በደመ ነፍስ መሣሪያውን እንዲጥል በዓይኖቿ እየተማፀነች።

«እኔን አትወጂኝም። ውሸትሽን ነው።»

«እወድሃለሁ ሰማይነህ፤ እውነቴን ነው። መውደዴን አንተ ስለማታውቅልኝ ነው።»

የመሣሪያው አፈሙዝ ለህይወት ፍቅርን ሳይሆን ዘዴን አስተማራት። እንደወጣትነቷ እሳት ውስጥ ዘልላ መግባትን ሳይሆን ከእሳት ውስጥ በዘዴ መውጣትን አሰላች።

ሰማይነህ ‹እወድሃለሁ» የሚለውን ቃል ሲሰማ ውሀ የፈሰሰበት ያህል ቀዝቅዞ መሣሪያውን አልጋው ላይ ወረወረው። ሳይታሰብ ስሜቱ ተለዋውጦ ዓይኖቹ በእንባ ተሞልተው «አታሰቃይኝ ህይወት፤ አታሰቃይ። ውደጂኝ እባክሽ - ውደጂኝ! በቅናት አታቃጥይኝ......ወይንም ግደይኝና ገላግይኝ። ያውልሽ መሣሪያዬ ግደይኝ!.....» እያለ በሚያሳዝን ሁኔታ ዘለባብዶ አልጋው ላይ ወደቀ።

‹ምን አረግኩህ ፈጣሪዬ.....እንዲህ ዓይነት ጉድ የምታሳየኝ?› አለች ህይወት ሰማይነህ መተኛቱን ካረጋገጠች በኋላ እጆቿን ወደ ላይ ዘርግታ ‹እባክህ አውጣኝ....ከዚህ ስቃይ ገላግለኝ። .....»

መሣሪያውን የነበረበት ቦታ መልሳ አስቀምታ እሷም ለመተኛት ሞከረች። ሆኖም ጭንቀትና ስጋት አዕምሮዋ ስለወጠሩት ዕንቅልፍ ሊወስዳት አልቻለም። በዚያ ላይ ደግሞ ጎረቤት የሚቀሰቅሰው የሰማይነህ ኩርፊያው ሰላም ነሳት።

‹ምን አይነት አለም ነው!› እያለች እንዲሁ በሀሳብ ስትገለበጥ አደረች።

# ክፍል ዘጠኝ

ቀንም ሆነ ሌሊት ሰማይነህ የሚያስበው ህይወትን ነው፡፡ አጠገቡ ተኝታ የራቀችው ይመስለዋል፡፡ ከእንቅልፉ በየጋጣሚው ሲባንን ህይወትን በዳበሳ ብቻ ማግኘት አይበቃውም፤ መብራት አብርቶ ማረጋገጥ አለበት፡፡ ቀን ስራው ላይ ሆኖም በሀሳቡ እየመጣች ታባንነዋለች፡፡ ድንገት ከስራው ላይ ተነስቶ ወደ ቤት ይሄድና መኖርዋን አረጋግጦ ይመለሳል፡፡ አንዳንዴም አሳቻ ሰዓት እየመረጠ ሳታስበው ከተፍ ይልና ያስደነግጣታል፡፡ ዓለም ሁሉ እሷን የሚፈልግበትና ከእጁ ላይ ለመንጠቅ ያሰፈሰፈበት ስለሚመስለው የእናቱና የወንድሙ ጥብቃ ብቻ አያረካውም፡፡ እሱም ራሱ በስውርና በግልፅ ይከታተላል፡፡ ተቀምጦ፣ ተኝቶም፣ ስራ ላይ ወይንም መንገድ ላይ ሆኖም ድንገት ብንን ይልና ሳትጠፋ ይፈልጋታል፡፡

ይህንን ያህል እንደሚያስባትና እንደሚፈልጋት ሁሉ አጠገቡ ስትሆን ወይም አጠገቧ ሲሆን የወንድ ፍቅሩን የሰኢት ፍቅሯን በቅጡ አይቀበልም፡፡ ጭቅጭቅ ያስቀድማል፤ ወይንም በተለመደው የቅናት አስተያየቱ እየቃኘት ምቀኞቹንና ጠላቶቹን ያስባል፡፡ ህያውነቷን ረስቶ እንዳትጠፋበት የሚስገበገብላትና የሚጠብቃት እንደ ውድ እቃ አድርጓታል፡፡ በየአጋጣሚው በባነነ ቁጥር አጠገቡ መኖርዋንና ከእጁ ያለመውጣትዋን ማረጋገጡ ይበቃዋል፤ እፎይታ ይሰጠዋል፡፡ በየደቂቃውና በየሰአቱ የእሱ መሆኗን ካረጋገጠ በቃው፣ ሌላ ነገር አይፈልግም፡፡

አንድ ቀን ከቀትር በኋላ እንደ ልማዱ ህይወትን እያሰበ ባለ ዘጠና ሞዴል ነጭ ማርቸዲሱን ይዞ በአስመራ መንገድ ለስራ ጉዳይ ሲጓዝ ድንገተኛ ፈተና ገጠመው፡፡ ከፊቱ ቀድማ የምትሽከረከረው «ለማጅ» የሚል ምልክት የተለጠፈባት ቮልስ ዋገን መኪና ውስጥ የተመከታት ሴት ተማሪ አስደነገጠችው፡፡ ከጎኗ የተቀመጠው አስተማሪ ወንድ ነው፤ እያጨዋወተና እያሳሳቀ ያስተምራታል፡፡ ሰማይነህ አቅጣቻውን አስተካክሎና ፍጥነቱን ቀንሶ ከኋላ ከኋላቸው እየተከተለ ጉዳቸውን ለማየት ወሰነ፡፡

ጆሮዋንና አንገቷን ሸፍኖ ጀርባዋ ላይ የተኛውን ረዥም ፀጉሯን በቮልስ ዋገኑ ጠባብ መስታወት አሻግሮ ከተመለከተ በኋላ ‹ህይወት ራሷ ናት!.....ዛሬ አገባጠመኝ.....እጅ ከፍንጅ ያዝኳት በማለት ተነፈሰ፡፡ የቅናት ዛሩ ፈረሱን ጭኖ ተነሳ፡፡ ህይወት መኪና እንድትማር የፈቀደላትን ዕለት ረገመው፡፡ መሰናከል ጨርሳ የከተማ ልምምድ መጀምሯን ሰሞኑን ነግራዋለች፡፡ መኪና በምትማርበት ሰዓት ከአጠገቧ ሳይርቅ እንዲከታተላት ጥብቅ ትዕዛዝ የተሰጠው ለጎርፉ ነበር፡፡ አሁን ግን በአካባቢው የለም፡፡ ሰማይነህ በወንድሙ ዝርክርክነት በሸቀ፡፡ ‹ይሄ ሆዳም! ይሄኔ ምግብ ቤት ወይንም መጠጥ ቤት ተቀምጦ ይጠብቃት ይሆናል፡፡ እንዲህ ከአስተማሪዋ ጋር ስትማግጥ አያይም፡፡ በዚህ አይነትማ በሄደችበት ሁሉ ብቻዋን እየለቀቃት ከማንም ጋር ስትዳራ ከርማለች ማለት ነው› በማለት ተማረረ፡፡

አስተማሪው በአፍ ከመጫወት አልፎ ትከሻዋን በግራ እጁ ነካ ያደርጋታል፡፡ እና ያስቃታል፡፡ እሱም ተከትሏት ይስቃል፡፡ ደግሞም እጆቹን እያወናጨፈ በስሜት ያወራላታል፤ እሷም እጆቿንና አይኖቿን ከመሪው ላይ ሳትነቅል እያዳመጠችው ትሾፍላራለች፡፡

ሰማይነህ ምን እንደሚያወሩ ለማወቅ ጓጓ፡፡ ንግግራቸውን እየሳበ የሚያመጣለት የሬዲዮ መገናኛ ማግኘት ተመኘ፡፡ ወ/ሮ ስራሽ ድንገት በሀሳቡ ውስጥ መጣችበት፡፡ ‹በዚህ ሰዓት ተገኝታ የልጇን ማጋጣነትና ብልግና ለማየት ብትችል ጥሩ ነበር› ሲል አሰበ፡፡ ከፊት በኩል ቀድሞ ወይንም ከጎን በኩል ሆኖ ድርጊታቸውን ለማየት ልቡ ቢከጅልም ቀናተኛ አዕምሮው ነገሩን ቶሎ ማስነቃት ስላልፈለገ ከለከለው፡፡ ህይወት የሰማይነህን ማርቸዲስ ስለምታውቃት ካየችው ጥንቃቄ ልታደርግ ትችላለች፡፡ ስለዚህ ከኋላቸው እየተከታተሉ መጨረሻቸውን ማየቱ ያዋጣል፡፡

‹አሪፍ ብትሆን ኖሮ እንዲህ ከኋላዋ ስከታተላት በመስታወቷ አይታኝ ልትፍር ወይንም ልትደነግጥ በተገባ ነበር። ነገር ግን ይሄ ደደብ አስተማሪዋ የመስታወት አጠቃቀም እንኳ አላስተማራትም። እንዲሁ ሲያማግጣት ውሎ ትራፊውን ይልክልኛል። ባለጌ የባለጌ ልጅ! እንኳን ብቻ ዛሬ ሁለታችሁም እጄ ገባችሁልኝ!› ብሎ ጥርሱን ነከሰ።

ፊቱን በመኪናው መስታወት ሲመለከተው ጥቀርሻ መስሏል። የደም ስሮቹ አባብጠው ግንባሩ ላይ ተጋድመዋል። እንደገና ጥርሱን አንቀጫቅጮ መከታተሉን ቀጠለ። መቆሚያቸው ጊዜ ራቀበት። አሁንማ ጭራሽ ሆነ - ብለው እሱን ለማናደድ› የተነሱ ይመስል ጨዋታቸው እየሞቀና እየደመቀ ሄደ። የአስተማሪው ወጉ እንዳይቀር አልፎ አልፎ መሪውን መለስ ሲያደርግላት እግረ መንገዱን እጇን ጠበቅ አድርጎ ይነካካታል። ኧረ እንዲያውም ይቆነጥጣታል መሰል!.....አንድ ጊዜ ከመቀመጫዋ እንደ መዝለል አደረጋት፤ ሞተሩም ሊጠፋባት ነበር። ምናልባት እሱ ፍሬሲዮን ረግጦ ይዞላት ይሆናል ከመጥፋት ያዳነው።

አስተማሪው ትከሻው ያበጠ ወጠምሻ ጎረምሳ መሆኑን ከጀርባው ሲያዩት ያስታውቃል። በዚያ ላይ ደግሞ ደረቱን ገልብጦ በካኒተራ ብቻ ስለ ነበረ በሰማይነህ ላይ አንዳች የጥላቻ ስሜት አሳደረበት። በጠራራ ፀሀይ የሰው ሚስቶችን የሚያድን ሽለምጥማጥ መስሎ ታየው። ሽጉጡን ዛሬም ያለመያዙ አናደደው። እስካሁን በአንድ ጥይት በታትኖ ባሳረፈው ነበር።» መሣሪያ ሠይጣን ነው፤ ቤት ውስጥ አስቀምጦ ሌሊት ሌባ መከላከያ ማድረግ ነው እንጂ በየስራውና በየመዝናኛው ቦታ ይዞ መዞር አያስፈልግም። ያሳስታል» ብለው እግሩ ላይ ወድቀው፣ ወገቡ ላይም ሆነ መኪናው ውስጥ መሣሪያ እንዳይዝ ያደረጉት እናቱ ናቸው። በእንዲህ አይነቱ ሰዓት ታዲያ እናቱን ይረግማቸዋል።

‹ወይኔ ሰማይነህ!.....እናቴ ናት ያስጠቃቺኝ!.....ሚስቴ በአደባባይ ስትማግጥ ከነወዳጅዋ በአንድ ጥይት ደራርቤ አሳርፋቸው ነበር!፤ አለና አሁንም በረዥምሙ ተነፈሰ። ትንፋሹ ከተቃጠለ ቤት የሚወጣ ጭስ መሰለው፤ ደሙ ፈልቶ ሲንተከተክ ተሰማው።

ገላጣ ቦታ ሲደርስና መኪኖቹ ጭር ሲሉ እንዳይታወቅ ወደ ኋላ እየቀረ፣ መኪኖቹ ሲጨናነቁ ደግሞ እየቀረበ ብዙ መንገድ ተከተላቸው። አዝማሚያቸውን ሲመለከተው በቅርብ የሚያቆሙ ወይንም አዙረው የሚመለሱ ዓይነት አልመሰሉትም። ‹እንዲህ እየተላፉና እየተቀላለዱ ወደ ሆቴል ሊሄዱ ይሆናል› ሲል አሰበ። በዚያ መስመር መኝታ ጨምረው የሚያስተናግዱ በርካታ ሆቴሎች መኖራቸውን ያውቃል። የትኛው ሆቴል እንደሚገቡ ለማየት ቸኮለ። ህይወትን እጅ ከፍንጅ ይዞ በጥርሱ የሚዘለዝልበት ሰዓት ራቀበት ሴሰኛ ገላዋን እንደ ሽንኩርት በቢላዋ ከታትፎ ማሰቃየት ተመኘ። ‹ሴት አስተማሪ ሳይጠፋ ወንድ አስተማሪ የመረጠችበት ምክንያት ግልፅ ነው። ያኔ ሴት ልብስ ሰፊ ሳይጠፋ ወንድ ልብስ ሰፊ መርጣ እንደሄደችው መሆኑ ነው። በየትኛውም አቅጣጫ የምትቅበዘበዘው ሴሰኝነቷን ለማርካት ነው!......አይ ህይወት!.....አይ የኔ ጨዋ!....አይ የኔ አይነ አፋር! እንኳን እግዜር ዛሬ እጄ ላይ ጣለሽ› አለና የመኪናውን መሪ በቡጢ ነረተው።

የሚያየው ነገር ራሱን አዞረው። አሁን ደግሞ አስተማሪው እግሮቿን እየተመለከተና አጎንሶ ጉልበቷን እየነካካ ‹ማስተማሩን ተያያዘው። እግሮቿን ይዞ ፍሬን አያያዝና ነዳጅ አሰጣጥ እያስተማራት ይሆን?.....ወይንስ ጭኖቿ ስር አጎንብሶ የቀረበት ሌላ ጉዳይ አለው?!......

‹ልክስክስ የተልከሰከሰ!.....ወራዳ ድመት!› አለው ሰማይነህ። አጎንብሶ ምን እንደሚሰራ ሊታየው አልቻለም።

‹እስቲ ቀና በል በናትህ!......እንግዲህ አትድረቅ! የሚያየን ሰው ምን ይላል?!.....ለሁሉም ነገር ትደርስበታለህ፤ ምን ያስቸኩልሀል?› ብላ እሷም ሳትገስፀው አልቀረችም። አስተማሪው ካጎነበሰበት ቀና አለ።

‹እንዲህ ዓየንት ትምህርት ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም፡፡ እግር ይዞ ማስተማር!.....እሷም እግሯን ይዞ የሚያስተምራትን መምረጧ!.....ለመሆኑ ለህይወት እኔ አንሺያት ነው ከተራ የመኪና አስተማሪ ጋር የምትልከሰከሰው?.....ወይንስ ሴሰኝነቷ አላሳርፍ ብሏት ነው?!› እያለ ሰማይነህ ዕልህ ተናነቀው፡፡ ‹አንድ ጥርሷን ብቻ ሳይሆን ሠላሳ ሁለት ጥርሶቿን ማርገፍ ነበረብኝ፡፡ እግሯንም ሰብሬ ዶሮ ጠባቂ አድርጌ ማስቀመጥ ነበረብኝ፤ ጥፋቱ የኔው ነው› አለና እንደ ገና ዛተ፡፡

ከአኳኋናቸው መረዳት እንደሚቻለው ሁለቱ በደንብ ተለማምደዋል፡፡ በመኪና ትምህርት ሰበብ ወደ የሆቴሉ ጎራ ማለቱንም ደጋግመውታል የሞከሩት ጉዳይ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ምናልባትም ብዙ ጊዜ ተቃቅፈዋል፤ ብዙ ጊዜ ተሳስመዋል፤ ብዙ ጊዜ ተደብቀው ተኝተዋል፡፡......ሰማይነህ ይህን ሲያስብ ስሜቱን መቆጣጠር አልቻለም፡፡ ይሄ ባለጌ ወጠምሻ የህይወትን ገላ አቅፎ ሲዳራ በሀሳቡ እየታየው ራሱን ሳተ፡፡ የግሉ ብቻ ያደረጋትን መስሎት ቀን ከሌሊት የሚባንንላትን ህይወትን የአደባባዩ ሁሉ መሆንዋ አናደደው፡፡ ለእሷ የወጣ ገንዘብና ያቃጠለው ጊዜ አብከነከነው፡፡ ......በትዕግሥትተከትሎ መጨረሻቸውን ማየት አልቻለም፡፡ መኪናውን መንዳቱን ራሱ ከቁጥጥሩ ውጭ ሆኖ በንዴቱ ላይ ሰይጣን ተጨምሮበት ለጥፋት ጋበዘው፡፡ አፅምሮው በንዴት ተወጥሮ እንደ ጦር የመኪናውን የነዳጅ መስጫ በሀይል ሲረግጠው፤ ዘመናዊው ማርቸዲስ እንደ ሮኬት ተወርውሮ ከቮልስ ዋገኗ የማስተማሪያ መኪና ጋር ተላተመ፡፡

ወሬ የጠማው ህዝብ ከየት መጣ ሳይባል በአንዳፍታ መኪኖቹን ከበባቸው፡፡ ግማሹ በማያገባ ገብቶ ፈራጅ ሊሆን፣ ግማሹም አጋጣሚውን ተጠቅሞ እይተሻሸ ሊዳብስ.....አንዱ በአንዱ ትከሻ ላይ እየተረባረበ «ጉድ!......ጉድ!......»ይል ጀመር፡፡

ሰማይነህ ራሱው ገጭቶ፣ ራሱ «አካኪ ዘራፍ!» እያለ ከመኪናው ወረደ፡፡ መሪው ደረቱ አካባቢ ቢመታውም ለጊዜው ዕልህ ውስጥ ስለሆነ አልታወቀውም፡፡ አስተማሪው ከመኪናው ወርዶ በብሽቀት እየጮኸና ሰውነቱን አሳብጦ እየተጎማለለ ይፎክራል፡፡ ተማሪዋ ከመቀመጫዋ ጋር የታሰረች ይመስል በድንጋጤ ክው ብላ እዚያው ቀርታለች፡፡ እርምሱና ከበባው ሲበዛ ደግሞ በድንጋጤዋ ላይ ሀፍረት ተጨምሮበት አደነዘዛት፡፡

ሰማይነህ ልክ እንደ መኪናው ተወርውሮ ወጥቶ ልጅቷን ለማነቅ ሲጋበዝ፣ አስተማሪውም ከሰማይህነ ጋር ቦክስ ለመግጠም ከሌላ አቅጣጫ ይዝት ጀመር፡፡

«......እንዳታስመልጡኝ!.....ሚስቴን እንዳታስመልጡኝ! ከዚህ በአደባባይ እፋረዳቸዋለሁ» እያለ ሰማይነህ ግራና ቀኝ ወጥረው የያዙትን ገላጋዮች ታገላቸው፡፡

«የማነው ጥጋበኛ እባካችሁ!.....ራሱ ከኋላ መጥጦ ገጭቶን ይቅርታ በመጠየቅ ፈንታ ገና ይደነፋል እንዴ?.....ልቀቁት እስኪ የሚሆነውን እናያለን» በማለት አስተማሪውም በበኩሉ ተጋበዘ፡፡

«አንተ ወራዳ ልክስክስ!....የሰው ሚስት ማማገጥ የለመድክ ሽለምጥማት!»

«ክብርህን ብትጠብቅ ይሻልሀል ሰውዬ!.....ዛሬ እዚህ ህዝብ መሀል ደምህን እንዳልጠጣው!»

ገላጋዮቹና ተመልካቾቹ ግራ ተጋብተው ከየአቅጣጫው አጉተመተሙ፡፡

«የመኪና ግጭት የአጋጣሚ ጉዳይ ነው፡፡ በግል እንደሚታየው ደግሞ ጥፋተኛው ከኋላ የገጨው ማርቸዲስ ነው፡፡ አሁን የሁለቱ ፀብ ምን ይባላል?! በአደባባይ መዘላለፍ ለተመልካች መሳቂያ ከመሆን ሌላ ምን ያተርፍላቸዋል?!.....ይልቅ ጥፋታቸውን ተማምነው በሰላም ቢጨርሱት አይሻልም?!......» አለ አንዱ በሁኔታው በማዘን፡፡

«ከግጭቱ ጀርባ ሌላ ነገር ያለ መሰለኝ። አስተማሪው መኪና ውስጥ ያለችው ሴት የባለማርቸዲሱ ሚስት ሳትሆን አትቀርም። ተከታትሎ ደርሶባቸው ሆነ ብሎ ገጭቶ ነው ያስቆማቸው። አታየውም ተናድዷል እኮ!.....» አለ ሌላኛው ግምቱን ተንተርሶ።

«አሃ!.....እንደዚያ ነው እንዴ ነገሩ?!.....ሴቷ ምን አይነቷ አይን አውጣ ነች እባክህ?! ባለጌ!....አይ ሴት!.....መኪና ውስጥ ክው ብላ ደርቃ የቀረችው ለካስ እጅ ከፍንጅ ስለተያዘች ነው!.....» እያሉ አንዳንዶቹ ሴትየዋን በመጥፎ አስተያየት ተመለከቷት።

ተማሪዋ ድንጋጤው ቀለል ብሎላት ከመኪናው ውስጥ ለመውጣት ስታስብ ያፈጠጡባት ዓይኖች መቋቋም ስላልቻለች ሰውነቷ የተሳሰረ መሰላት። ለአንዳፍታ ቀና ብላ ግራ ቀኙን ከተመለከተች በኋላ «ውይ ፈጣሪዬ!....» ብላ መልሳ ፊቷን መሪው ላይ ደፋች።

በዚህ መሀል ትራፊክ ፖሊስ መጥቶ ወሬኛውን ገለል እያደረገ አደጋው የተፈፀመበትን ቦታ እየመተረ ያስምር ጀመር። የማርቸዲሱ አንደኛው የፊት መብራት የረገፈ ሲሆን የገጨበት ቆርቆሮው ተጣሟል። የቮልስ ዋገኑም የኋላው መብራቶች ተሰብረው የሞተሩ ኮፈን ተሰርጉዷል።

«ህግ ፊት ውሰደን ፖሊስ!.....በአስቸኳይ ህግ ፊት ውሰደን!.....» እያለ ሰማይነህ ጮኸ።

«ረጋ ይበሉ እንጂ ጌታዬ.....ጥፋተኛው እኮ እርስዎ ነዎት!» አለ ትራፊኩ ፊቱን እንዳጨማደደ።

«የኔ ጥፋት አይደለም። ሚስቴን ይዞ ሊያመልጥ ሲል ገጭቼ አስቆምኩት። ሌላ መያዣ መንገድ አልነበረኝም።»

«ምንድነው ይሄ ሰው የሚያወራው?....» አለና አስተማሪው ህዝቡ እየገፋ ሄዶ የመኪናውን በር ከፍቶላት ተማሪዋን እንድትወርድ ካደረገ በኋላ «እኔ እስከማውቀው ድረስ ይህች ተማሪዬ ባል የላትም። እንግዲህ ሚስቴ ነች የሚል ከሆነ ማስረጃውን ያቅርብ» አለ።

«ዋአአይ!......ኸረ እኔ ባል የለኝም» አለች ተማሪዋም ይኸኛው ነገር ደግሞ ይበልጥ አስደንግጦአት።

ሰዎች ሁሉ ወደ ሰማይነህ ተመለከቱ። ሰማይነህም ተማሪዋን ትክ ብሎ ተመለከታት። ህይወት አይደለችም። ከፀጉርዋ መርዘም በስተቀር ፊትዋ ላይ የምትመሳሰልበት ምንም ነገር የላትም። ሰማይነህ የራሱን ዓይኖች ማመን አቃተው። ስህተቱንና ከንቱ ጥርጣሬውን አምኖ መቀበል አልቻለም። ‹እዚሁ ዓይኔ ስር መድግምት በምናምን ለውጠዋት ይሆናል› ብሎ ይበልጥ ዓይኖቹን አፈጠጠ። በዳበሳ ጭምር ሊያረጋግጥ ፈለገ።

«እስቲ ነይ ወደኔ ጠጋ በይ»

«ዋአአይ!....ምን ጉዳይ አለህ?!»

«አንቺ ህይወት አይደለሽም እንዴ?»

«የማነች ህይወት!.....»

«.....ወይንም ህይወት የምትባል እህት አለችሽ?»

«ኸረ እኔ አላውቃትም።»

ዙሪያቸውን የከበባቸው ህዝብ እየተሳሳቀና እየተገረመ ተበተነ። «ሚስቱን የያዘ መስሎት የሰው መኪና ቦድሶ ጣለ። አይ ቅናት!.... አይ ጥርጣሬ!» እያለ በዚያ አካባቢ የተሰበሰበው ሁሉ የወሬ ስንቁን እየያዘ ሄደ።

የቮልስ ዋገኑ ሞተሩ ስለ ተጎዳ መነሳት አልቻለም። ማርቸዲሱ ራዲያተሩ ቢጣመምና ውሀ ቢያፈስም ሞተሩ ስላልተነካ ከትራፊክ ጋር ሁሉም ተያይዘው ቃላቸውን ለመስጠት ወደ ጣቢያ ሄዱ።

የሰማይነህ አዕምሮ አንዳች ምስቅልቅል ተፈጥሮበ በንዴት ተወጥሮ ነበር። የራሱንም ሆነ የገጨውን መኪና የሚያሰራለት ሙሉ የመድህን ዋስትና አለው። የተናደደው በግጭቱ ሳይሆን ጥርጣሬው በመክሸፉና «አገኘሁ» ብሎ የጨበጠው ነገር ሲከፍተው ባዶ አየር መሆኑ ነው። የአካባቢው መሣቂያ ሆኖ መቆየቱም አናድዶት ‹ዓይኔ ስር ህይወትን አሸሽተው ሌላ ሴት አምጥተው ይሆን?› የሚለው ጥርጣሬም በሙሉ አልለቀቀውም።

«ዛሬ ቀን ህይወት ከቤት ወጥታ ነበር?» በማለት ሰማይነህ እቤቱ እንደ ገባ እናቱን ጠየቃቸው።

«አዎ......ከጎርፉ ጋር ውጭ ውላ ነው የመጣች» አሉት እናትየው።

«የት እንደ ሄደች ነግራሻለች?»

«ሐኪም ቤት ብላ ነው የወጣችው።.....መቼም በየቀኑ መውጫ ምክንያት አታጣ!»

«አሁን ጎርፉ የታለ?»

«ገና አልመጣም። እሷን አድርሷት ተመልሶ እንደሄደ ነው.....ምነው? ደህናም አይደለህ እንዴ? አሉት የተጎሳቆለ ፊቱን እየተመለከቱ።

«የለ ደህና ነኝ። መኪናዬ ትንሽ ግጭት ደርሶባት ነው» አለና ነገሩን አደባብሶ ወደ ህይወት ሄደ። እሷም አንድ ችግር መፈጠሩን ከፊቱ ላይ አነበበች። ሆኖም፣ በጎ ስለማይመልስላት መጠየቁን ፈራች።

«ዛሬ የት ሄደች ነበር?.....» በማለት እሱው ቀድሞ ጠየቃት

«ሐኪም ቤት ሄጄ ነበር.....» ካለች በኋላ ጥርጣሬ ውስጥ እንዳይገባ «ከጎርፉ ጋር ነው የሄድነው» በማለት አከለችበት።

ሰሞኑን ከሰማይነህ ጋር አብረው ወደ ማህፀን ሐኪም ሄደው ነበር። ሽንትና ደም ስትሰጥ አብሯት እየተከታተለ አይቷታል። በመጨረሻም ህይወትን የምትደባብሳትን የማህፀን ሐኪሟ ሴት መሆኗን ካረጋገጠ በኋላ ተረጋግቶ በቀጠሮዋ ቀን ከጎርፉ ጋር እንድትሄድ ፈቅዶላት ነበር። የቀጠሮዋ ቀን ዛሬ መሆኑ ትዝ አለው።

«ሐኪሟ ምን አለች?....»

«ምንም ዓይነት የማህፀን ችግር እንደሌለብኝ ነው የነገረችኝ።»

«ታዲያ የማትወልጂው ለምንድነው?....»

«ሐኪሟ እንደነገረችኝ ከሆነ የአዕምሮ መረበሽ ወይንም ጭንቀት እንድኒህ አይነት ችግር ሊያከትል ይችላል.....»

«ታዲያ አንቺን የሚያሳስብና የሚያስጨንቅ ምን ነገር አለ?» አላት በጥርጣሬ ዓይን እያያት።

«ምንም.....» አለችው። እሷም በልቧ ‹ምናልባት ችግሩ ከአንተ ይሆናላ። ነገር ግን እኔ ካንተ የመውለድ ጉጉት ስለሌለኝ ደንታ አይሰጠኝም› አለች።

«ምናልባት ልብሽ ረግቶ ስላልተቀመጠ.....ማህፀንሽም ውስት ፍሬ ረግቶ መቀመጥ አይችልም ይሆናል» በማለት ለከፋውን ጀመራት።

‹ይሆናል። እስከመቼውም ልቤ ከአንተ ጋር ረግቶ ሊቀመጥ አይችልም› ልትለው ፈልጋ ነበር። ነገሩን ላለማባባስ ዝምታ መረጠች።

«መልስ አትሰጭኝም እንዴ?»

«የምኑን?»

«ልብሽ ያለመርጋቱን?!.....»

«እኔ እንጃ!»

«ልብሽን.....ለማስመርመር ሐኪም ቤት መሄድ አያስፈልግሽም።.....አኳኋንሽ ይናገራል፤ ድርጊትሽ ይመሰክራል፤ ዓይነ ውሀሽ ያጋልጥሻል «እያለ ካስፈራራት በኋላ ዓዕምሮውን ወጥሮ ወደያዘው ጉዳይ ተመልሶ «ዛሬ ከሀኪም ቤት ሌላ የትም አልሄድሽም?» አላት።

«የትም አልሄድኩም።»

«መኪና ለመማርም አልሄድሽም?»

«እንዲያውም።.....ከአስተማሪዬ ጋር ቀጠሮ አልነበረኝም።»

«እኔ የማላውቃት እህት አለችሽ እንዴ?»

«እህትም ወንድምም የለኝም።»

«እንግዲያው አንቺን ራስሽን ወይንም አንቺን የምትመስል ሴት መኪና ማስተማሪያው ቦታ አይቻለሁ።

«ተሳስተሀል ሰማይነህ፤ ካላመንከኝ ወንድምህን ልትጠይቀው ትችላለህ።»

«የመኪና አስተማሪሽ ወንድ ነው ወይንስ ሴት?»

የጥያቄው አቅጣጫ ቢገባትም ህይወት ልትዋሽ አልቻለችም። ጎርፉን ጠይቆ ሊያውቅ የሚችለው ነገር በመሆኑ እውነቱን ነገረችው።

«ወንድ ነው።»

«ሴት አስተማሪ ለምን አልፈለግሽም?»

«ከጎርፉ ጋር ፈልገን ነበር። ማግኘት አልቻልንም።»

«ወንድ እጅሽን ይዞ ነዋ የሚያስተምርሽ?....»

የደምስሮቹ እያባበጡ ግንባሩ ላይ መጋደም ሲጀምሩና ዓይኖቹ ሲፈጡ ህይወት ነገሩ ገባትና ዝምታን መረጠች።

«ተናገሪ እንጂ!.....በደንብ እንዲገባሽ እያሳሳቀ ያስተርምሻል አይደል? ምናልባት እግርሽን ይዞ ፔዳል አረጋገጥ ያስተምርሽ ይሆናል።»

አሁን ህይወት ዝም!

«ከዛሬ ጀምሮ የመኪና ትምህርትሽ እንዲቋረጥ አዝዣለሁ።....አስፈላጊ ከሆነ ሴት አስተማሪ ተፈልጎ እዚሁ ግቢ ውስጥ እድንትለማመጂ ይደረጋል።»

# ክፍል አሥር

ሰማይነህ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ስለ ህይወት እንቅስቃሴና ፀባይ በጠባቂዎቿ አማካኝነት እንዲነገረው ይፈልጋል። አንድ ቅዳሜ ቀን ጎርፉን ጠርቶት «......ዛሬ ምሳ ከኔ ጋር ነህ። ልክ በሰባት ሰዓት ኢትዮጵያ ሆቴል እንገናኝ።« ሲለው፣ ጎርፉ የተፈለገበት ምክንያት ገብቶት ተዘጋጅቶ ሄደ። አንዳንዴ ሰማይነህ ጎርፉን እንደ አፒታይዘርም ይጠቀምበታል። ብዙ ጊዜ ምግብ ስለማይበላለት ፊት ለፊቱ ጎርፉ ተቀምጦ እየጠቀለለ ሲጎርስ በመመልከት ወስፋቶቹ ይነቃቃሉ። ዛሬ የተፈለገው ግን ለወሬ መሆኑን ቅንታት ታህልም አልተጠራጠረም። ስለ ህይወት ሳያወራለት ብዙ ቆይቷል።

ሰማይነህ ቀጠሮ ማክበር አይሆንለትም። በጣም የሚያስፈልገውና የሚጠቅመው ጉዳይ ካልሆነ ብዙውን ጊዜ ቀጥሮ መጥፋትም ልማዱ ነው። ጎርፉ የወንድሙን ፀባይ ቢያውቅም ከቀጠሮአቸው አንድ ሰዓት ያህል አሳልፎ መምጣቱ አብሽቆታል። ወስፋቶቹ እየተንጫጩ የሌሎቹን ተመጋቢዎች ምግብ በዓይኖቹ ሲቀላውጥና አብሮአቸው በስሜት ሲውጥ ነው የቆየው። በጣም ከመራቡ የተነሳ ለሰማይነህ ራሱን ከነነፍሱ ቢጎርሰው በወደደ ነበር።

«.....በረሀብ ገደልከኝ እኮ» አለው እንደ መጣ።

«አይዞህ እክስሀለሁ» ብሎት ተቀመጠ።

አሳላፊዎቹ የሰማይነህን ጉርሻ ደጋግመው የቀመሱ በመሆናቸው ፈጠን - ፈጠን ብለው አስተናገዷቸው።

ጎርፉ አሳላፊዎቹን ፋታ በመንሳት ሣህኑን እያቀያየረ ምግቡን ሲያከታልበው ሰማይነህ ገና የመጀመሪያውን ሰሀን ሾርባ እንኳ አልጨረሰም ነበር።

‹ታድለሀል። የአንተን ሆድ ግማሽ እንኳ ለእኔ ቢሰጠኝ ጥሩ ነበር‹ አለ ሰማይነህ በልቡ። «እግዜር ሀብት ሲሰጥ ጥርስ ነቅሎ ነው» የሚባለው አነጋገር ታወሰውና ‹እውነት ይሆን?.....› ሲል ራሱን ጠየቀ። መጀመሪያ ነገር የምግብ አምሮት የለውም፤ እንዲህ እንደአሁኑ ወስፋቱን የሚከፍትለት ሰው አጠገቡ አስቀምጦ የግዱን ሲበላ ደግሞ ለጤናው አይማማውም። ጨጓራውን ያመዋል። ‹ያገኘውን ጠርጎ መብላት የሚችል ሰው ዕድለኛ ነው› አለ እንደገና በወንድሙ እየቀና።

በሌላ በኩል ደግሞ «ሆዳም ሰው ፍቅር አያውቅም» የሚባለውን አስታውሶ ‹ምናልባት ጎርፉ ሚስት የማያገባው ለዚህ ይሆን? በሆዱ የምትይዘው ሚስት ቢያገኝ ሊያገባ ይችላል› ሲል አሰበ።

«የተስማማህን ምግብ ድገም» አለው።

«ሁሉም ተስማምቶኛል። የዶሮ አሮስቶውን ብደግም ጥሩ ይመስለኛል» ብሎ ጎርፉ ፊቱ ላይ የተቸፈቸፈውን ላብ እየጠራረገ አሳላፊውን ጠርቶ አዘዘ።

ሆዱ በደንብ መሙላቱን ካረጋገጠ በኋላ ሰማይነህ ዋናውን ጥያቄ ጀመረ።

«.....የተጣለብን አደራ ዘንግተህዋል መሰለኝ?.....» አለው እንደ መቆጣት ግንባሩን ኮስተር አድርጎ።

«የቱን አደራ?.....» አለ ጎርፉ ተደናግጦ።

«ህይወትን የመጠበቅና እንቅስቃሴዋን የመከታተሉን ነዋ!»

«ኧረ በሚገባ እየተወጣሁ ነው።»

«መኪና አስተማሪዋ ወንድ መሆኑን እያወክ ዝም ብለህ መልቀቅ አልነበረብህም።»

«በምትማርበት ሰዓት አብሬአት ሆኜ እየተከታተልኳት ነው እንጂ አንድም ቀን ለብቻዋ አልለቀቅኳትም።»

«ወደ ውጭ ስትወጣ እንዴት ናት?......ዓይኖቿ ወደ ሌላ ያያሉ ወይንስ አቀርቅራ ነው የምትሄደው?»

«ኧረ ዓይኖቿስ አያርፉም። አንዳንዴ ስለ እሷ አስተያየት እኔ አፍራለሁ» አለው ለመመስገን መዋሸትና ማጋነን እንደሚያስፈልግ አምኖበት።

«......የምታየው ወንዶችን ወይስ ሴቶችን?»

«ሴቶችንም ታያለች። በጣም የምታተኩረው ግን ወንዶች ላይ ሲሆን ነው።»

«እነሱም አተኩረው ያይዋታል?»

«የወንዶቹማ ምን ይነገራል! መንገድ ላይ ቀሚሷን ገልበው መዳራት ነው የሚቀራቸው።»

«ታዲያ አንተ ዝም ብለህ ታያለህ?»

«ሁሌም እንድ ተጣለሁና ለዱላ እንደ ተጋበዝኩ ነው።»

«እሷ በዓይኗ ስትጋብዛቸውና ፊት ስትሰጣቸው ወንዶቹ ምን ያድርጉ!.....አንተ ሳታያት ምናልባትም ጠቅሳቸው ይሆናል።»

«ይህን ያህልስ አልደፈረችም። እኔ በጥብቅ ስለምከታተላት ትፈራለች።

«ገበያ ስትወጣ ሁሌም አብረሀት ትሄዳለህ?»

«ሁልጊዜም አብሬአት ነኝ። አንዳንዴ እንዲያውም እማማም ጭምር አብራን ትሆናለች.....??

«የምትገበያይባቸውን ቦታዎችና ሰዎች ታውቃቸዋለሃ?»

«በሚገባ!....»

«ወንዶች ናቸው ወይንስ ሴቶች?»

«የሽንኩርትና የቅቤ ደንበኞቿ ሴቶች ናቸው። ቅመማ ቅመም ቡና የምትገዛውም ከሴቶች ነው። የወንድ ደንበኛዋን ያየሁት ጥራጥሬ ልንገዛ እህል በረንዳ የወጣን ዕለት ብቻ ነው።»

«ጥራጥሬ የምትሸጥ ሴት ጠፍታ ነው ወንድ ጋ የሄዳሁት?»

«አይደለም። በደንብ ይሰፍራል ብላ ህይወት ስለፈለገች ነው። ከዚያም በላይ የዱሮ የእናቷ ደንበኛ መሆኑን ነግራኛለች።»

«የምትፈልጋቸውን ወንዶች የምታገኛቸው እንዲህ ዓይነት ምክንያት እየፈለገች መሆኑን መጠርጠር ነበረብህ። ጅል!»

«መጠርጠር እንኳ ጠርጥሬያለሁ።.....ሆኖም ሰውዬው ሽማግሌ ስለሆነ በሌላ ጉዳይ አይፈላለጉም ብዬ ነው ቸል ያልኩት።»

የሽማግሌ ልብ ቆንጆ እና ወጣት ሴት አይመኝም ያለህ ማነው?!..... ሞኝ አትሁን።»

«እሱስ ልክ ነህ።.....እህል ነጋዴው ገና ህይወትን ሲያያት የሚያደርገውን አሳጥቶት ሲቅነዘነዝ ታዝቤዋለሁ። ስንዴ እንዲያሳያት ስትጠይቀ ተንደናብሮ በቆሎ ዘግኖ ሰጥቷታል። እየተቅለሰለሰና ዓይን - ዓይኑና እያየ ሲሰፍ ሚዛኑን ስቶ ስንዴውን መሬት ላይ ዘርግፎታል። እሱና ካየ ስለሚፈዝ ሌሎች ሰዎች ማስተናገድ አይችልም። ብዙ ገበያ ያመልጠዋል።......የሴት እግር ናየት ደግሞ ይወዳል። የእህል ዓይነቶች የሚያመርጥ እየመሰለ አጎንብሶ የሴቶቹን ባትና ተረከዝ መመልከት ልማዱ ነው። ደግነቱ ህይወት ሁልጊዜም ወደ ገበያ ስትሄድ ሱሪ ለብሳ ነው»

የሽማግሌው ዓይኖች የህይወትን ሱሪ ቀድደው አልፈው ሽንቃጣ ዳሌዋና ባቷን ሲመለከቱ ሰማይነህ በሀሳቡ እየታየው የማያውቀውን እህል ነጋዴ ጠመደው። ግንባሩን አኮሳትሮ ጥርሱን እያንቀጫቀጨ ‹የታባቱ ይሄ ወራዳ ሽማግሌ! ይሄኔ አሮጊት ሚስቱን ቤቱ አስቀምጦ ይሆናል ውጭ መማገጥ የሚያምርው!› አለ በልቡ።

«.......ህይወት ገበያዋን ጨርሳ ተሰናብታው ከሄደች በኋላ ደግሞ ከኋላዋ ትኩር ብሎ የማየት በሽታ አለበት» በማለት ጎርፉ ነገሩን ለማጣፈጥ መቀደድ ጀመረ።

«ማን?.....ይሄው እህል ነጋዴ?»

«ታዲያስ!.....እሱ ራሱ። አንድ ቀን እንደ ልማዱ ትኩር ብሎ ሲመለከታት ከእኔ ጋር ዓይን - ለዓይን ግጥም አልን።»

«ታዲያ ዝም አልከው?!......»

«እኔ ወንድምህ! በግልምጫ ከእግሩ እስከ ራሱ አነሳሁት እንጂ!.....»

«ግልምጫ ምን ዋጋ አለው?!.....ጢጋ ብለህ ዓይነስቡን በቦክስ ብታጠፋለት ኖሮ ሁለተኛ የሰው ሚስት ዘወር ብሎ አያይም ነበር......»

«አስቤ ነበር። በእጄ ሰበብ እንዳይሆን ፈራሁ።»

«ምን አስፈራህ። እይጉዳት ካሳውን እኔ እከፍላለሁ።»

«ሁለተኛ ከደገመ አልለቀውም።»

«ከአሁን በኋላ ምን ልታደርጉ እሱ ዘንድ ትሄዳላችሁ?!.....ሴት እህል ነጋዴ ከአገሩ ጠፋ እንዴ?!.......በአስቸኳይ ደንበኛ እንትለውጡ።»

ጎርፉ እጅ ነስቶ ትዕዛዙን ተቀበለ።

«ሌላስ?....» አለ ሰማይነህ የሚጠይቀውን እያሰበ «ፀጉሯን የምትሰራው የት ነው?»

ፀጉሯን እያሻሸ የሚሰራና አንገቷን የሚደባብስ አንድ የማይታወቅ ወንድ በሰማይነህ ሀሳብ ውስጥ ብቅ አለ። እስካሁን ያያቸውን ወይንም በዝና የሚያውቃቸውን የሴት ፀጉር ሰሪ ወንዶች በሙሉ ጠላቸው። ‹የሴት ልጅ ፀጉሯ በወንድ ከተደባበሰ፣ ጆሮዋን ከተሻሸ ግንባሯና አንገቷ ከተነካካ በቃ አለቀላት! ከዚህ በኋላ ልቧን ማሸፈት ቀላል ነው። ወደ ጆሮዋ ጠጋ ብሎ በቀስታ ቀጠሮ መለዋወጥም ይቻላል። የሚስቱን ፀጉር ወንዶች እንዲሰሩለት አምኖ የሚልክ ባል ያበደ መሆን አለበት። የሴቶችን ፀጉር ለመስራት የተሠለፉ ወንዶችም የሰው ሚስት የማባለግ ሱስ

የተጠናወታቸው ጋጠወጦች መሆን አለባቸው› በማለት በሀሳቡ በጅምላ ረገማቸው የህይወትን ፀጉር የሚሰራት ወንድ ከሆነ ለማወቅ ቸኮለ።

«መጀመሪያ ህይወት የበፊት ደንበኛዬ ነው ብላኝ የወሰድኳት ፀጉር ሰሪ ወንድ ነበር። በዚያ ላይ ወጠጤ ጎረምሳ.....» አለ ጎርፉ ነገሩን ለማጣፈጥ።

«ታዲያ አንድ ወጠጤ ጎረምሳ የሚስቴን ፀጉር እያሻሸ ሲያጫውታት ዝም ብለህ ተመለከትክ?!» ብሎ ሰማይነህ ጮኸበት።

«እንዲያውም!.....ሞቼ ነው ቆሜ!»

«ታዲያ ምን አረግክ?»

«ዓይኔ እያየ የወንድሜን ሚስት ፀጉር ላይ የወንድ እጅ አያርፍባትም ብዬ ህይወትን ይዤአት ወጣሁና ሴቶች የሚሰሩበት ሌላ ፀጉር ቤት ደንበኛ እንድትይዝ አደረግኳት። አሁን በቋሚነት ፀጉሯን የምትሠራው ሴቶች ቤት ነው።»

«ጎበዝ!......እንዲህ ነቃ በለህ ስትከታተልና የነገሮች አቅጣጫ ሲገቡህ ደስ ይለኛል» ብሎት ሰማይነህ መጠነኛ እፎይታ ካገኘ በኋላ «ከፀጉር ሠሪው ጋር ዱሮ ግን ተላምደው ነበር ማለት ነው.....ሲያሻሻትና ሲያጫውታት ኖሯል!» በማለት ወደ ኋላ ሄዶ ቅናቱን ቀሰቀሰ።

«ዱሮማ ደንበኛው ከነበረች.....መላመዳቸው የት ይቀራል! እኔ አከላከዬ ይዤበት ስወጣ እንዴት እንደገላመጠኝ ልነግርህ አልችልም» እያለ ጎርፉም ነገሩን አሟማቀ።

«ለዚህ ሁሉ ተጠያቂዋ እናቷ ነች። በሥነ ሥርዓቱ ተከታትላ አላሳደገቻትም። እሷ አረቄዋን ስትቸረችር ልጅቷ ከጀርባዋ የምትጫወተውን ጨዋታ መመልከት አልቻለችም። ልብስ ሰፊ ደንበኛዋ ወንድ!.....ፀጉር ሰሪ ደንበኛዋ ወንድ!......ያውም ገና ዘልለው ያልበቃቸው ጎረምሳዎች!......በወንዶች የተደባበሰ ዳሌና ፀጉር! ደግሞ በልጁ እንደምትተማመንባት ትነግረኛለች። ደደብ አሮጊት!.....»

«ድሮማ እኛ የማናውቀው ሌላም ብዙ ነገር ይኖራል። ብቻ እሱን ትቶ አሁን ጠበቅ አርጎ መያዝ ነው።»

«ሌላ የሰማኸው ነገር አለ እንዴ?»

«......ያው ፈላጊዋ ብዙ እንደ ነበረ......ወይዘሮ ስራስ ውስኪ ቤት የሚመጣው ሁሉ ህይወትን ፈላጊ እንደ ነበር.....እሷም ከመጣው ጋር ሁሉ መሳሳቅ ታዘወትር እንደ ነበር ሰምቻለሁ።»

«ለመሆኑ አሁን ከማንም ጋር መሳሳቋን ትታለች ወይንስ በድብቅ ትሳሳቃለች?»

«እንደ በፊቱ አትስቅም። በተለይ ጥርሷ ከወለቀ ወዲህ በጣም ቁጥብ ሆናለች።»

«ዓይኗስ እንደ በፊቱ ይንቀዠቀዣል?.....»

«ዓይኗስ ምንም አያርፍም። አቀርቅራ መሄድ ፈፅሞ አትችልበትም። ደግሞ ከምታየው ነገር ላይ ዓይኖቿን ቶሎ አትነቅልም። የልጅነት ይሁን የሌላ አይገባኝም። የደነበረ በሬ ሳይቀር ትኩር ብላ ትመለከታለች።»

«የሰው አንሷት ነው በሬ የምትመለከተው?!»

«ምን አውቄላት!.....»

«አተኩራ የምታየው ወንዶችን ነው ወይንስ ሴቶችን?»

«ሁለቱንም ነው። ሴቶቹን የምታየው የአለባበሳቸውንና የአረማመዳቸውን ፋሽን ለመቅዳት ሊሆን ይችላል። ወንዶችን አተኩራ የምታይበት ምክንያት ግን አይገባኝም።.....»

«ዝም በላት!.....ዓይነ ስቧን እንዳጠፋላት ፈልጋ ነው። አንድ ቀን ያጋጣጥመኝ ይሆናል» ብሎ ከዛተ በኋላ «ስልክ የምትደውልላቸውን ቦታዎች ትከታተላላችሁ?» አለው።

«ቤት ውስጥ ስውል መቼም እኔ ከአጠገቧ አልለይም። ለሥራ ውጭ በምውልበት ጊዜ እማማን አደራ እያልኩ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የምትደውለው ከእናቷ ጋር ነው።

«ምንድነው በስልክ የሚያወሩት?....»

«እናትየዋ የምትለው አይሰማንም። ህይወት ግን ስትማረር ነው ሁሌ የምንሰማት።»

«ምናባቷ ነው የሚያማርራት?.....ምን ጎደለብኝ ነው የምትለው?!.....»

«ምን አውቄ! ለምን ቁጥጥር ይደረግብኛል ብላ ይሆናላ!.....እንደ ልቧ መውጣት መግባትና ከማንም ጋር የመዝለል ልማዱ ስለ ቀረባት ይሆናል።»

«እሷን ፍለጋ እኛ ቤት የሚመጣ ሰው አለ?»

«እስካሁን ማንም የለ። የሠርጋችሁ ሰሞን ሚዜዎቿ አከታትለው ይመጡ ነበር። አሁን ግን ቀርተዋል።»

«እኔ እንዳይመጡ አዝዤያቸው ነው። በተለይ አንደኛዋ አቃጣሪ ቢጤ ናት። በእኔ ላይ ሌላ ባል ሳትፈልግላት አትቀርም።»

«እኔም አንደኛዋን ጠርጥሬያት እየተከታተልኳት ነበር። ሾካካ ቢጤ ናት።

«ቡና ለመጠጣት የሚመጣ ጎረቤትም የለም?....»

«የእማማ የዱሮ ወዳጆች ናቸው እንጂ ህይወትን ፈላጊ አይመጣም።»

«እሱ ላይ በጣም ተጠንቀቁ። ቡና መጠራራትና አብሮ መጠጣት አመቺ የወሬ መድረክ በመሆኑ......ሌላ መዘዝ ሊያመጣ ይችላል።»

«ልክ ነህ። እንጠነቀቃለን።»

«ሌላስ?.....» አለ ሰማይነህ ስለ ህይወት የበለጠ ወሬ ለማግኘት በመጓጓት ቅንድቡን እያርገበገበ።

«ሌላ....ሌላ.....ሌላ......» እያለ ጎርፉ የሚያወራለት አጥቶ ተጨነቀ።

«ለቅሶ ቤት ወይንም ሠርግ ቤት ሄዳ ታውቃለች?»

«ሠርግ ቤት እንኳ ሄዳ አታውቅም። ለቅሶ ቤት ግን አንድ ሁለት ጊዜ ያህል ሄዳለች።»

«ብቻዋን?!....» ብሎ ጮኸበት።

«አይደለም። ከእማማ ጋር ነው።»

«አንተም ተከትለህ መሄድ ነበረብህ ለቅሶ ቤት ደንበኛ የሴትና የወንድ መተዋወቂያ ቦታ ሆኗል። ሴቶቹ ነጠላቸውን ተከናንበው የሚያዝንኑ እየመሰሉ በዓይናቸው ወንዶችን ሲያድኑ ነው የሚውሉት። ወንዱም ካፖርቱን ለብሶ እየተጎማለለ ሐዘነተኛ መስሎ ሴቶች መምረጥ ነው ስራው። ‹አይዞህ አይዞሽ› እየተባባሉ የተዛዘኑ መስለ ሲንሾካሾኩና ሲደባበሱ ተመልካች ሳያውቅባቸው አድራሻ መለዋወጥ ይችላሉ። ለቅሶ ቤት በመሆኑ ማንም ሳይጠረጥራቸው የፍቅር ቀጠሮ ይዘው ሊለያዩ ይችላሉ። እኔ በሌለሁበት ህይወት ለቅሶም ሆነ ሠርግ መሄድ የለባትም። ምናልባት የጥንት ፍቅረኛዋን እያስታወሰች ለመተከዝና ለማልቀስ እንዲመቻት ይሆናል ለቅሶ ቤት የምትሄደው። ሠርግ ቤት ደግሞ በዓይኗ ለመቀላወጥ ይመቻታል።»

«ምንጊዜም ወደ ውጭ ስትወጣ ደግሞ ለባብሳ ደምቃ እንድትታይ ሆና መውጣት የለባትም። እንዲያውም ከዛሬ ጀምሮ ልብሶቿ ላይ እንቆልፍባቸዋለሁ። ተውሳ እዳታጌጥ ጠብቃት።

«እሺ።»

የሚጠጡትን እየተጎነጩ ሁለቱም ለተወሰነ ጊዜ በዝምታ ቆዩ። ሰማይነህ የህይወትን ማሰሪያ ገመድ የሚያጠብቅባቸውን መንገዶች እያወጠነጠነ ነበር። ጎርፉ ደግሞ ለሰማይነህ ያቀረበው ወሬ በቂ መስሎ ስላልታየው ፈጥሮም ቢሆን የሚጨምርለትን እያሰበ ነበር። እንደ ገና ሳይርበውም አልቀረም። እያዛግና እየተንጠራራ እርፍደው የመጡ ተመጋቢዎችን ምግብ በዓይኖቹ መቀላወጥ ጀምሯል።

«ስራህስ እንዴት ነው?....በደንብ እየሰራህ ነው?» አለው ሰማይነህ በድንገት።

ጎርፉ የማይወደው ጥያቄ ነው። ከመልሱ በፊት ራሱን ማከክ ጀመረ። እግረ መንገዱንም ብሶቱ መግለጽ ፈልገ።

«የታክሲ ስራ ስቃይ ነው። ጠዋት ብርዱ፣ ቀን ሙቀቱ አያሰራም። በዚያ ላይ ከተሳፋሪው ጋር ጭቅጭቅ ነው አሁን። አሁንማ ሰው በእግሩ መሄድ ጀምሯል መሰለኝ። ገበያም የለም። አንተን እየፈራሁ ነው እንጂ ሥራው በጣም አስመርሮኛል።»

ሰማይነህ ሳቁ መጣበት። ወንድሙ ስራ እንደማይወድ ያውቃል። የስራ ነገር ሲነሳበት እሮሮ መስማት ልማዱ ነው። ቤት ውስጥ ሲልከስከስ ቢውል ይመርጣል።

«እንዲያውም ብዙ ጊዜ እነግርሀለሁ እያልኩ....»

«ምኑን?....» አለው ሰማይነህ።

«ትርፍ ለሌለው ስራ ፀሐይ ሲያቃጥለኝ ከምውል....ውስጥ ህይወትን መጠበቁ ራሱ ትልቅ ስራ ነው። እማማ እያረጀች ስለሆነ የህይወትን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ መከታተል አትችልም። በተለይ በስልክ የምትገናኛቸውንና የምታወራውን ልትቆጣጠራት አትችልም። ምናልባት በወፍ ቋንቋ እየተናገረች ልታታልላትም ትችላለች።

ሰማይነህ የአዎንታም ሆነ የአሉታ መልስ ቶሎ አልሰጠውም። ቤት ውስጥ ውሎ ህይወትን ቢጠብቅለት ይወዳል። ነገር ስራ ከፈታ በተለይ የሚያስበው ሆዱን ብቻ ስለሚሆን ህይወት ራሷ በሆዱ ገዝታው ምሥጢሯን እንዲደብቅላት ታደርገዋለች የሚል ፍርሀት አለው። በሌላ በኩል ደግሞ ማድ ቤት እየገባ ገረድየዋን እንዲያስለችበትም ይፈራል።

ጎርፉ በበኩሉ ቤት የመዋሉን ጥያቄ የሚያጠናክርበትን ዘዴ ሲያሰላ አንድ ነገር ብልጭ ስላለለት በደስታ ፊቱ ፈካ።

«.....ህይወት እንዲያውም ከውጭ ይልቅ መጠበቅ ያለባት ቤት ውስጥ ነው» አለው አቀማመጡን አሳምሮ ለወሬ ደረቱን እየነፋ።

«እንዴት?.....» አለው ሰማይነህም ጆሮውን ይበልጥ እየሰጠው፡፡

«ቤታችን ውስጥ የምጠረጥረው ሰው አለ.....»

«በማን?.....ህይወትን!?.....»

«አዎ ህይወትን..... በአንተ ሚስት፡፡»

«ከዚያ ከረፈፍ ዘበኛ ጋር ግንኙነት ጀምራለች እንዳትለኝ!»

«ኧረ ዘበኛው ምን በወጣው፡፡»

«ታዲያ ሌላ ማን አለ?!.....ሁላችንም ያለነው ቤተሰብ ነን፡፡»

«እኮ!.....ችግሩ ያለው ከቤተሰቡ መሀል ነው፡፡»

«መደምደሚያን ማለትህ ነው?» አለው በንዴት ስሮቹ እየተግተረተሩና ዓይኖቹ እየፈጠጡ፡፡

«.....ብቻ ይሄንን ነገር እንዳልናገር እማማ በአባታችን አጥንት ገዝታኝ ነበር፡፡»

«ንገረኝ እንጂ!.....ከዚህ በላይ ምን ጥቃት አለ?!»

«አዎ፤ መደምደሚያን እጠረጥረዋለሁ፡፡ ብዙ ነገሩ ደስ አላለኝም፡፡»

«እነዚያን ትርኪ ምርኪ መፅሐፎቹን እያመጣ ሲያስነብባት መጠርጠር ነበረበኝ!.....መቀራረቡን አብዝቶታል፡፡ ለእሷ ጥብቅና መቆምም ጀምሮ ነበር፡፡ እኔ ይህን ያህል ይዳፈራል ብዬ አልገመትኩም እንጂ!.....ወይኔ ሰማይነህ!.....» ብሎ ጥርሱን ነከሰ፡፡

«ትዕቢተኛ እየሆነ መጥቷል፡፡ ታላቅነታችንን እንኳ አያከብርም፡፡ እኔንማ አፍ አውጥቶ ‹ከብት› ብሎ ሰድቦኛል፡፡»

«ምን አደረግከውና?!.....»

«እጅ ከፍንጅ ስለያዝኩት ነዋ!.....»

«ምን ሲያደርግ?.....»

«ከህይወት ጋር ሲ.....»

«ምንድነው የምታወራው?!.....ተናገር እንጂ!.....ጨርሰው እንጂ!.....ወይኔ ሰማይነህ!.....»

«አንድ ቀን ጠዋት.....አንተ ስራ እንደሄድክ.....ሁለቱ ተያይዘው ወደ አትክልቱ ቦታ ሄዱና ፍቅር መስራት ጀመሩ.....»

«መደምደሚያና ህይወትን?!.....»

«አዎ፡፡ በዓይኔ በብረቱ ያየሁትን እኮ ነው የምነግርህ፡፡.....እኔ ተደብቄ እንደምመለከታቸው አላወቁም፡፡ እጅ ለእጅ ተያይዘው እየተሻሹ መላቀስ ጀመሩ፡፡»

«ምን አባታቸው ነው የሚያስለቅሳቸው?!.....»

«እኔ እንደ ገባኝ ከሆነ ፍቅር መሰለኝ፡፡ መደምደሚያ ከኪሱ መሀረብ አውጥቶ እንባውን ሲጠርግ እሷም ተከትላው እያለቀሰች የሚነግራትን ስትሰማው ብዙ ቆየች፡፡ በመጨረሻም ተቃቅፈው

ሊሳሳሙ ሲሉ እናታችን ይህን ጉድ ማየት አለባት አልኩና እማማን ይገፔ እየጎተትኩ አጠገባቸው ስደርስ ከው አሉ.....»

«ታናሽ ወንድሜ ሚስቴን ሳማት ነው የምትለኝ?!.....» አለው ሰማይነህ በንዴት ራሱን ወደ መሣት እየተቃረበ።

«አዎ አዝማሚያቸው እንደዛ ነበር።.....እኔንም የሰደበኝ ስለደረስኩበት ነው።»

«ይህንን ብልግና እማማም አይታለች ነው የምትለኝ?»

«አብረን ነው ያየነው።»

«መደምደሚያ ብቻ ሳይሆን እናንተም በቁሜ ገድላችሁኛል። ከዚህ የበለጠ ምን እስኪፈፀምብኝ ድረስ ነው የምትደብቁኝ?!»

«እንደምታውቀው እማማ መደምደሚያን እንዲነካባት አትፈልግም። በአባታችን አስምላ ስለከለከለችኝ....እኔ ምን ላድርግ!.....»

«ወይኔ ሰማይነህ!......ተደፍሬያለኋ!.....በቁሜ ሙቻለኋ!....በእጄ በልቶ ጠጥቶ ያደገ ወንድሜ እንዲህ ያዋርደኝ!.....እንዲህ መቀለጃ ያድርገኝ!......የኔ የሰማይነህ ሚስት በወንድሜ ትደፈር?!.......» እያለ ጥርሱን ነክሶ ጠረጴዛውን በቡጢ ደበደበ።

ጎርፉ ከሰማይነህ አፍ የሚጠብቀው ‹ከዛሬ ጀምሮ የታክሲ ስራህን ትተህ ቤት ውስጥ ቁጭ ብለህ ህይወትን እንድትጠብቅ። ከመደምደሚያ ጋር ፈፅሞ እንዳይገናኙ በዓይነ ቁራኛ ጠብቃቸው› የሚል ትዕዛዝ ነበር። ይህን ባለማግኘቱ ውሸትም ቢሆን ጭምሮ ማጠናከር ፈለገ። እስካሁን በሰማይነህ ልብ ውስጥ የጫረው ክብሪት ብቻ በበቂ ሁኔታ እያነደደው መሆኑን አልተረዳለትም። አንደኛውን ፈንጂ ሰጥቶት ሊያፈነዳው አሰበ። ቀፎ ጭንቅላቱን ትንሿን የግል ፍላጎቱን እንጂ የሚያወራው ነገር የሚያስከትለውን አደጋ ሊያስብለት አልቻለም።

«እኔን የገረመኝ መደምደሚያ ከዚያ በኋላ ያለመታረሙ ነው.....» በማለት ጀመረ ውሸቱን ሲያቀነባብር ከቆየ በኋላ።

«ከዚህ በላይ ምን አደረገ ልትለኝ ነው?!....»

«ኧረ እሱ ሀፍረተ ቢስ ነው....»

«እኮ ንገረኝ!.....ሆድ ቁርጠት አትሁንብኝ!.....» ብሎ ጮኸበት፤ የሚነግረውን እየጠረጠረና በሀሳቡ እየዘገነነው።

«መቼም እማማን በቀላሉ ማታለል ይችላል። የኔ ውጭ መዋል ደግሞ እንደ ልቡ ከህይወት ጋር ለመላመድ ሳይመቸው አልቀረም።...አንድ ቀን በአሳቻ ሰዓት ስራዬን አቋርጬ ወደ ቤት ስመጣ በህልሜም በውኔም ያልጠበቅኩትን ጉድ ተመለከትኩ!....»

«እኮ ምን?!.....»

«መደምደሚያ ከህይወት ጋር.....መኝታ ቤት ውስጥ.....»

«ም - ም - ም - ምን?!.....የትኛው መኝጣ ቤት?!.....»

«እናንተው መኝታ ቤት ውስጥ......ሱሪውን እያጠለቀ ሲንደፋደፍ ደረስኩበት.....»

«መደምደሚያ ከሚስቴ ጋር ተኝቷል ነው የምትለኝ?!» አለው ብድግ ብሎ እንድ ዕብድ እጆቹን እያወራጨ።

«ቢሆን ነዋ!.....ካለበለዚያ ሱሪውን ምን አስወለቀው!»

«ወይኔ ሰማይነህ!.....በገዛ ወንድሜ ተጠቃሁ!.......ወይኔ!......ወይኔ!.......» እያለ አጠገቡ ያገኘውን ጠርምሙስ በዕብደት ሲያነሳ፣ አዝማሚያው ስላላማረው ጎርፉ ከተቀመጠበት ተነስቶ ሸሸ። ሆኖም ግን ፅዋውን መቅመሱ አልቀረለትም። «አንተስ ብትሆን ይሄንን ጉድ ገና ዛሬ የምትነግረኝ የት ከርመህ ነው?!» ብሎ ያነሳውን ጠርሙስ ሲወረውረው ግንባሩን ጨርፎት አለፈ።

«እኔ ምን አጠፋሁ?».....ብሎ ግንባሩን እያሻሸ ወደ ውጭ ሮጦ አመለጠው። ሰማይነህ ብቻውን እየጮኸ አካኪ ዘራፍ አለ። «ወንድሜ ሚስቴን ደፈራት!» እያለ ፀጉሩን ነጨ። የሆቴሉ አስተናጋጆች ግራ ተጋብተው ሊገላግሉት ቢሞክሩም አልቻሉም። እንድ እብድ እየጮኸ ወደ መኪናው ሄደ።

# ክፍል አስራ አንድ

በዚህ ዕለት ህይወት ከሄኖክ የተላከላት አስቸኳይ ደብዳቤ በመደምደሚያ በኩል ደርሷት እያነበበች ነበር። ሄኖክ ራሱን በአካል ያገኘችው ይመስል ወረቀቱን አቅፋ እያለቀሰች ደጋግማ አነበበችው።

«ህይወትዬ! እንደምን አለሽልኝ የኔ ፍቅር። ደብዳቤሽ ሲደርሰኝ የተሰማኝን ስሜት ልገልፅልሽ አልችልም። በቀድሞው አድራሻዬ ስለላክሽልኝ ለአንድ ጉዳይ ወደ ዋሽንግተን ስመጣ ዘመዶቼ ጋ ተቀምጦልኝ ነው ያገኘሁት። አጋጣሚ ሆኖ ደብዳቤው እነሱም እጅ ከገባ ገና ሁለተኛ ቀኑ ነበር። ደብዳቤውን ከፍቼ የእጅ ፅሁፍሽን ስመለከት ልክ ፎቶ ግራፍሽን ያገኘሁ ይመስል በዓይኖቼ ሙሉ እንባ ግጥም አለ። ውበትሽ ዓይኔ ላይ መጣብኝ። የልጅነት ፍቅራችንና ያሳለፍነው ጊዜ በሙሉ በፊቴ ላይ ተመላለሰብኝ። ምን ልበልሽ ህይወትዬ!.....ቢወጣልኝ ብዬ ለብቻዬ ተደብቄ አለቀስኩኝ።

«ደብዳቤሽን ሳነብ ገና በወጣትነትሽ መጥፎ ባል ላይ ወድቀሽ መሰቃየትሽ አሳዘነኝ። የልጅነት ፍቅሬን መነጠቄ አናደደኝ። ምን ያደርጋል! ያለሁበት ሀገር ሩቅ ሆነና ነው እንጂ፣ ሌሊቱን ገስግሼ መጥቼ ነፃ ባወጣሽ በወደድኩ ነበር። አሁንም ይዋል ይደር እንጂ አንቺን ፍቅሬን ነፃ ካላወጣሁሽ ነፍሴ እረፍት አታገኝም። ህይወትዬ ሙች እልሻለሁ፤ በልጅነት ፍቅራችን እምልልሻለሁ፤ ምንጊዜም ልቤ ካንቺው ጋር ነው። ሁልጊዜም አስታውስሻለሁ።

«ሳልፅፍልሽ በመቆየቴ ቅር እንዳለሽ ይሰማኛል። ወድጅጂ እንዳይመስልሽ፤ የነበርኩበት አስቸጋሪ ሁኔታ እንኳን አንቺን ራሴንም እንረሳ አድርጎኝ ነው። የዋሽንግተን ቆይታዬ ጥሩ አልነበረም። መጀመሪያ እዚያ የሚኖሩትና የወሰዱኝ ዘመዶቼ ሞቅ - ሞቅ አድርገው ተንከባከበው ተቀበሉኝ። ሆኖም ግን ወረታቸው ቶሎ አለቀና ቶሎ ሰለቹኝ። የሀገራችን ሰዎች አሜሪካኖችን ሆነዋል። ከአንድ ሳምንት በላይ ሊያስተናግዱሽም ሆነ ሊያኖሩሽ አይፈቅዱም። ትምህርት ቤት ወይንም ስራ ፈልገሽ በፍጥነት ከአጠገባቸው እንድትርቂ ይጎተጉቱሻል። በተለያየ መንገድ መሰልቸታቸውን ያሳዩሻል። መኖሪያ ፈቃድ ካላገኘሽ ስራ ማግኘት ደግሞ ከባድ ነው። ቦዘኔ ትሆኛለሽ። በባዕድ ሀገር ቦዘኔ መሆን ያስጠላሻል። ቦዘኔነትሽን የሚያውቁ ሁሉ ከሰው አይቆጥሩሽም፤ ይንቁሻል። የሀገሬ ሰዎች አገኘሁ ብለሽ ስትቀርቢያቸው ቦዘኔነትሽን ካወቁ ፊት ይነሱሻል። በቃ፤ ራስሽን ትጠያለሽ። ከርቀት የተመኘሽው ዋሽንግተን የሚባል ታላቅ ከተማ ባዶ አስፋልትና ግንብ ይሆንብሻል። ትጠይዋለሽ። በሀምበርገር ማስታወቂያ ሆድሽ ይቀበተታል፤ በበረዶ ብናኝና አጥንት

ሰብሮ በሚገባ ብርድ ሰውነትሽ ይኮማተራል። ሁሉም የሚያምረው ሲኖርሽና ስትርኖር መሆኑ ይገባሻል። የአስፋልት መንገዶቻቸውን ስፋትና ብዛት፣ እንዲሁም በስርና በላይ እንደ ውሀ የሚፈሱትን ተሽካርካሪዎች ስትመለከቺ ስልጣኔያቸው ይታይሻል፤ ከታች ባቡር ከላይ መኪና ሲበርሩ ትመለከቻለሽ፤ በህንፃዎቻቸው ውስጥ በርካታ የስልጣኔ ውጤቶች መኖራቸውንም ትገምቻለች። የስልጣኔያቸው ተጠቃሚ ለመሆን ግን ገንዘብ ያስፈልጋል። እና ሁሉም ሌሊት ከቀን ከገንዘብ ጋር ይሮጣል። እዚህ ሀገር ሰው ማለት ገንዘብ ነው፤ እንቅስቃሴ ማለት ገንዘብ ነው፤ ሁሉም ነገር ገንዘብ ነው። ‹ከሌለህ የለህም› የሚለውን ዘፈን ያስታውስሻል።

«ይሄውልሽ ህይወቴ፤ ደብዳቤ ሳልፅፍልሽ የቆየሁት ብልጭልጩን ታላቅ ከተማ እንዲህ በቦዘኔነት ባሳለፍኩበት መራራ ወራቶች ጊዜ ውስጥ ነው። እንደማትፈርጂብኝ ተስፋ አለኝ። አሁን ግን ዋሽንግተንን ለቅቄ ወደ ፍሎሪዳ ሄጄያለሁ። ኑሮዬንም እያስተካከልኩ ነው። ፍሎሪዳ የሚገኝ አንድ ኢትዮጵያዊ የልጅነት ጓደኛዬ መክሮኝ ነው ከዋሽንግተን የወጣሁት። እንደ በረዶ አቅልጦ፣ እንደ ንፋስ አንሳፍፎና እንደ ባህር አስምጦ ከሚያስቀረው ከዚህ ከተማ በመውጣቴ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። ይሄውልሽ፤ በዚህ ሁኔታ ነጩ ቤተ መንግሥት ፊት ለፊት ተቀምጠው ሀሺሽ የሚያጨሱትን ዓለም አቀፍ ቦዘኔዎች ከመቀላቀሌ በፊት ዋሽንግተንን ለቀቅኩ።

«ፍሎሪዳ ረጋ ያለ ከተማ የህይወት እንቅስቃሴ የሚታይበት ሀገር ናት። እኔ የምኖርባት ከተማ ቅዱስ ፒተርበርግ ትባላለች። አብዛኞቹ ነዋሪዎቿ ጡረተኞች ሲሆኑ ቀሪ የህይወት ዘመናቸውን በሰላምና በተረጋጋ ሁኔታ ለማሳለፍ የሚመርጧት ከተማ ናት። ፀጥታ የሰፈነበት አየሯ ለእኔ ተስማምቶኛል። ግርግርና ቦዘኔነትን በአጭር ጊዜ አጣጥሜ ስላስጠላኝ ይሄኛው ቦታ የመንፈስ እረፍት ሰጥቶኛል። የመኖሪያ ፈቃዱንም ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በእጄ አስገባለሁ። ከዚያ በኋላ የመጀመሪያው ርምጃዬ አንቺን ወደ እኔ ማምጣት ይሆናል። እንደ አሞራ በርሬ እደርስልሻለሁ፤ እናም የታሰርሽበትን ሰንሰለት በጣጥሼ ነፃ አወጣሻለሁ። አጭር ጊዜ ብቻ ታገሺኝ ህይወትዬ!....

«ለጊዜው ራሴን የማሸንፍበት ሥራም አግኝቻለሁ። የቢሮ ስራ እንዳይመስልሽ። አውራ መንገዶች የመጥረግና የማፅዳት ስራ ነው። እዚህ ስትመጪ የምትመለከቺው ጉዳይ በመሆኑ ልደብቅሽ አልችልም። አሜሪካን ሀገር ውስጥ የቢሮ ስራ ማግኘት የቻሉ ኢትዮጵያውያን በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። አብዛኞቹ የሚሰቱት ይህንኑ አይነት ስራ ነው። ይህንን የጠላ ምርጫው ቦዘኔነት ነው። ዘመናዊ መኪና ተደግፎ ፎቶ ግራፍ እየተነሱ ወደ ዘመድ በመላክ የስራችንን አይነት መደበቅ የሚቻል አይመስለኝም። ከሀገራችን ስንወጣ ፅዳት ሠራተኝነት፣ ልጅ አጫዋችነት፣ መኪና ጠባቂነት፣ ግርድናና ዘበኝነት የመሳሰሉት ተራ ስራዎች ናቸው የሚጠብቁን። ደግነቱ እዚህ ሀገር ማንኛውም ስራ ክቡር ነው። ሳንቲም እስካስገኘ ድረስ ሁሉ ይረባረብበታል። እኛም ከአገራችን ስንወጣ ስራ ማክበር እንጀምራለን፣ ሁሉንም እንሰራለን። ባዕድ ሀገር ስንደርስ ኩራታችንን ታጥበንና አራግፈን፣ የስራን ክቡርነት ተገንዝበን ሁሉንም እንሰራለን። አንዳንዴ እዚያው አገራችን ይህንን ልምድ ብናዳብር የት በደረስን ያሰኛል።

«ህይወትዬ፤ አስለቸሁሽ መሰለኝ። ትንሽ ስለ ራሴ ልናዘዝ ብዬ እኮ ነው። አዕምሮ ውስጥ የታመቀን ነገር ለሚወዱት ሰው ማዋየት መጠነኛ እፎይታ ይሰጣል። አሁን ደብዳቤሽ ከደረሰኝ ወዲህ ትልቁ ህመሜ ምን መሰለሽ? የአንቺ ወደ እኔ መምጣትና በደስታዬም ሆነ በሀዘኔ ጊዜ አጠገቤ መሆንሽ ብቻ ነው የሚታየኝ። እንዴት እንደቸኮልኩ ልነግርሽ አልችልም። ነፍሴ ነሽ!.....ብቸኝነቱ ገና ከአሁኑ እያመመኝ ነው። በዚህ ቀዝቃዛ ፀጥታማ ከተማ ውስጥ አንቺን ከጎኔ ሳገኝሽና ብቸኝነቱ ሲለቀኝ ህመሜ ይጠፋል። የርቀት ፍቅራችን ተቀራርቦ በጋራ ስንተነፍስ ኑሮአችንም የተሟላ ይሆናል። ምግብ ማስበሉን ስለተመማመድኩት አንቺን አላስቸግርሽም። አንቺ ብቻ ነይልኝ እንጂ እኔ አብስዬ አበላሻለሁ።

«አንቺ ከቶውንም በሌላ የምትቀየሪ ሴት አይደለሽም። ይህን ማሰብሽ ተሳስተሻል። ልቤ ውስጥ ያለሽው የመጀመሪያም የመጨረሻም ፍቅሬ አንቺው ነሽ። አንቺን ባቀፍኩበት ክንዴ ላይ ሴት

አላቅፍም። የአንቺን ወላላ ከንፈር በሳምኩበት ሌላ ሴት አልነካም። ውበትሽ የነፍሴ እስትንፋስ ነው። ረሀብ - ጥማቴ አንቺው ነሽ። ረዥም ፀጉርሽ ውስጥ ፊቴን ቀብሬ በፍቅር ማልቀስ አምሮኛል። ትላልቅ ዓይኖችሽ አሁንም ከርቀት ቦግ ብለው ይታዩኛል። ሸንቃጣ ቁመናሽ ዓይኔ ላይ ይመጣብኛል።

«በገንዘብ በዝቶ የሚያሰቃይሽን ያንን ቀናተኛ ባልሽን ለአንዴም ለሁሌም እንዳያገኝሽ አደርገዋለሁ። ከጭቆናው ቀንበር አውጥቼ እገላግልሻለሁ። አንቺን ከእጆቹ መሀል ፈልቅቄ ወስጄ፣ ጥርስሽን እንዳወለቀ ሁሉ፣ እኔ ደግሞ ልቡን አወልቅለታለሁ። የልጅነት ፍቅሬን የወሰደብኝን ቀማኛ እኔም በተራዬ አሳየዋለሁ። በአስቸኳይ እደርስልሻለሁ። አይዞሽ ፍቅርዬ!.....

«ህይወትዬ፤ ገና ከአሁኑ ይታየኛል። በቅዱስ ፒትርስበርግ ከተማ አንቺን መሳይ ቆንጆ ይዤ ስጎማለል ነጮቹ ሁሉ ውበትሽን ሲያደንቁ ይታየኛል። እኔም በአንቺ ተከብሬ የህይወቴና የዕድሌ እመቤት ሆነሽ ስታንቀባርሪኝ ይታየኛል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ይሄ ህልሜ ዕውን እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ። የሚመችሽን የስልክ አድራሻ ላኪልኝ። እኔም የስልክ ቁጥሬን ልኬልሻለሁ። ቻው ህይወትዬ። በአካል የምንገናኝበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም።

ናፍቆቴ ነሽ።

እወድሻለሁ።

ያንቺው ሄኖክ አንበሴ።

ህይወት ደብዳቤውን አጣጥፋ ከደበቀችው በኋላም እንባዋ ሊቋረጥ አልቻለም። እንዲያውም ሲቃ ተናነቃት።

«.....ለምን ታለቅሻለሽ?» አላት መደምደሚያ የደብዳቤው መልዕክት ምን እንደሆነ ለማወቅ ጓጉቶ።

«እኔ እንጃ።......የደስታ ሲቃ ነው መሰለኝ የሚያስለቅሰኝ። እና ደግሞ ትዝታ» አለችው ዓይኖቿን እየጠራረገች።

«ልክ ነሽ። አንዳንዴ በለቅሶ ውስጥ ሳቅ አለ፤ በሳቅም ውስጥ ለቅሶ ይኖራል። የስቃይም ሆነ የደስታ ሲቃ መግለጫው እንባ ነው ቁም ነገሩ ከውስጥ ገንፍሎ ወጥቶ እፎይታ ከመስጠቱ ላይ ነው። »

«ይሆናል። አሁን ከውስጤ የሚሰማኝን ስሜት በቃላት መግለፅ አልችልም።»

«ከቃላት ይበልጥ ሁኔታሽ ይናገራል» ብሎ፣ ይህንን አይነት ስሜት የፈጠረባትን ደብዳቤ ማንበብ ፈልገ። ‹ብጠይቃት ቅር ይላት ይሆን?› የሚል ስሜት ደግሞ ከውስጡ ታገለው። በግልፅ ያልታወቀው ስሜት ከውስጥ ስለጨመደደው ለመጠየቅ ፈራ።

እሷም ስሜቱን ተረድታለች። ስለ ደብዳቤው ማወቅ እንደ ፈለገ ገባት። ሆኖም ግን የደብዳቤውን መንፈስ መንገር እንጂ ደብዳቤውን ሰጥታው ቃል - በቃል እንዲያነብባት አልፈለገችም።

«ሄኖክ ከአንድ ወር በኋላ እንደሚወስደኝ ቃል ገብቶልኛል። ከዚህ ባርነት ሊያወጣኝ ሙሉ ተስፋ ሰጥቶኛል» አለችው።

በቃ። ሌላው ደብዳቤው ውስጥ የሰፈረው የፍቅር ቃል የእሷ ብቻ የግሏ ነው። ሌላ ማወቅ የለበትም፣ ቢያውቅም እንደ እሷ አይገባውም። ሄኖክ የእሷ ብቻ የግሏ ነው፤ የሄኖክ ቃላትም እንደዚያው ሌላ ሰው ቢያነብባቸው ፊደላቱ የሚደበዝዙና ጣዕማቸው የሚጠፉ መስሎ ታያት። ሳሳችላቸው በእሷ ዓይኖች ብቻ ተነብበው እሷ ልብ ውስጥ መቀመጥ ያለባቸው የፍቅር ቃላት!....

መደምደሚያና ህይወት የሚያውቁትን የመኪና ጥሩንባ ከርቀት በድንገት ሲሰሙ አንዳች ወንጀል ሲፈፅሙ የቆዩ ይመስል ሁለቱም ተደናገጡ።

«የሰማይነህ መኪና መሰለኝ» አለች ህይወት።

«ልክ ነሽ.....እንዴት በዚህ ሰዓት ሊመጣ ቻለ?!» አለ መደምደሚያ መጋረጃውን ገልጦ በመስኮት ወደ ውጭ እየተመለከተ።

ዘበኛው የውጭውን በር ከፍቶ ሲያስገባው ሰማይነህ መሆኑን አረጋገጡ። ጎርፉ ታክሲውን ይዞ ከኋላው ተከታትሎታል።

«አብረን መታየታችን ጥሩ አይደለም። ከአጠገቤ ዘወር በል። ለአጓጉል ጥርጣሬ እንዳንመቻቸው.....» አለችው ህይወት፣ ውስጧ የቆየውን ስሜት ከገጿ ላይ ለማጥፋት ዓይኖቿንና ፊቷን እየጠራረገች።

«ባትይም እኔ ወደ ንባቤ ክፍል መሄዴ ነው ‹አንኳን ዘንቡብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ.....› ብሎ ተለያት።

ሰማይነህ እሳት ጎርሶ እሳት ለብሶ እየፎከረ ወደ ቤት ሲገባ እናትየው ወጥተው ተቀበሉት።

«ምን ሆነሃል የኔ ጌታ?....ምንድነው ነገሩ?!....»

«ገድላችሁኛል!......ሁላችሁም በቁሜ ገድላችሁኛል!.....አዋርዳችሁኛል። ዘወር በሉልኝ ከፊቴ!....አንቺም እናቴ ክብሬን አስገፍፈሽኛል......አዋርደሽኛል!.....›.

«እኮ ምንድነው ነገሩ?!›.......ረጋ በል እስቲ ልጄ»

«ዘወር በይልኝ ከፊቴ!......ረጋ የምልበት ትዕግሥት የለኝም። ተዋርጃለሁ!......ተደፍሬያለሁ!»

ጎርፉ ከኋላ ከኋላው በፍርሀት እየፈገፈገ ይከተለዋል። ያቀምሰኛል ብሎ ስለ ፈራ ቀርቦ ሊይዘው አልደፈረም። ህይወት መኝታ ክፍሏ ውስጥ እንደ ሆነች የሰማይነህን ጩኸትና ፉከራ ስምታ ‹ደሞ ምን ተገኘ ይንሆን ፈጣሪዬ?› እያለች ነበር። ጉዳዩ ከእሷ ጋር የተያያዘ መሆን ያለመሆኑን ለማረጋገጥ ጆሮዋን ጣለች። እንደሚስትነቷ በባሏ ሁኔታ ደንግጣ ሮጣ ልትወጣ አደፈረችም፤ ፈራችው።

«ተደፍሬያለሁ!.....የገዛ ወንድሜ ሚስቴን ደፍሯታል!.....መደምደሚያ ከሚስቴ ጋር ተኝቷል።......ዛሬ የሁለቱንም ደም እጠጣለሁ። እኮ የታሉ?!.......ሁለቱንም እፈልጋቸዋለሁ! እያለ ሲጮህ ህይወት ሰማችው።

ነገሩ ወዲያው ገባት። አንድ ቀን መደምደሚያን ያስፈራራበትን ጉዳይ ጎርፉ ለሰማይነህ እንደነገረው አወቀች አሳብዶታል ማለት ነው፤ ምንም ነገር ሊመልሰው እንደማይችል ገመተች። ለራሷም ነፍስ ፈራች። አንድ ማታ ያየችው የጦር መሣሪያ ታወሳት። ወዴትም ልትሸሽ አትችልም። በቁሟ አንቀጠቀጣት፣ አሁን አሁን ሰማይነህ ዘልሎ ገብቶ ሲያንቃት ታያት። የደመነፍሷን ተንደርድራ የመኝታ ቤቷን በር ቆለፈችው። በጭንቀቷ ውስጥ ልታስብ የቻለችው የመከላከያ ዘዴ ይህ ብቻ ነበር።

ሰማይነህ ደርሶ የመኝታ ቤቱን በር ሊከፍት ሲሞክር ከውስጥ ተቆልፏል። ከውስጥ ሲንኮሻኮሽ ስለሰማ ህይወት እንደዘጋችበት ገባው።

«ብትከፍቺ ይሻልሻል አንቺ ሸርሙጣ!.....ዛሬ ጉድጓድ ውስጥ ብትገቢ ተከትዬሽ እገባለሁ እንጂ አልለቅሽም። እንዳቃጠልሽኝ አቃጥልሻለሁ!.....እንዳዋረድሽኝ አዋርድሻለሁ!....ይህንን ሴሰኛ

ሰውነትሽን በእሳት እለበልበዋለሁ! ክፊቺ በሩን!.....ደምሽን እጠጣዋለሁ!› እያለ በሩን በቡጢ እየደበደበ ታገለው።

እናትዬው በአንድ በኩል ሰማይነህ እግር ላይ ወድቀው እየለመኑት በሌላ በኩል ህይወትን እየረገሟት ነበር።

«እግዜር ይይልሽ አንቺ ልክስክስ!.....ልጄን በጠበጥሽው፤ አቃጠልሽው፤ ለበለብሽው። ልጆቼን አፋጀሻቸው።.....ምን ዓይነቷ ርኩስ ነሽ እባክሽ!.....ሰላማዊ ቤታችንን አደፈረስሺው። .....መሲና!»

ህይወት የተደበቀችበት ቦታ ሆና ስድባቸውንና ርግማናቸውን ስታዳምጥ እንባ አተናነቃት። ጭፍን ጥላቻቸውን ወገናዊነታቸው አናደዳት። ዘልላ ወጥታ ጉሮሮአቸውን አንቃ እንደ ዶሮ ሲት ብታደርጋቸው በወደደች ነበር። አሮጊቷ ጭራቅ መስለው ታዩዋት። አቃቂር ከሚያወጣው አስተያየታቸውና ከተናካሽ ምላሳቸው የምትቀርበት ጊዜ ናፈቃት።

«ክፊች ብዬሻለሁ ዛሬ ቀን!......ብምርሽ ነፍሴን አይማረው። የትም አታመልጪኝም!..... ወጥተሽ እጅሽን ብትሰጪ ይሻልሻል። መቃብርሽን በገዛ እጅሽ እየቆፈርሽ ነው፤ አንቺን ልክ ካላገባሁ እኔ ሰማይነህ ቁጭ ብዬ እሸናለሁ.....»

መደምደሚያ የሰማይነህን ድምፅና ረብሻ ሲሰማ ቀስ ብሎ ከክፍሉ ወጥቶ መጣ። የሱ ክፍል ከዋናው ቤት ራቅ ስለሚል የሰማይነህ ድምፅ እንጂ የሚናገረው ነገር አልተሰማውም። ጉዳዩ እሱን የሚመለከት መሆኑ አልገባውም። በዋናው ቤት ኮሪደር በኩል ገና አንገቱን ከማስገባቱ ሰማይነህ ተመለከተው። ልክ እንዳየው አንዳች ስሜት ብልጭ አለበት። ከመኝታ ቤቱ በር ጋር ያደርግ የነእብረውን ትግል አቋርጦ መደምደሚያን ዘልሎ ለማነቅ ተንደረደረ። እናትዬዋ እጁንና እግሩን ይዘው ለመነተት ቢሞክሩም አልቻሉትም።

«ና አንተ ውርጋጥ!.....አንተ ወራዳ ልክስክስ! አንተ ነህ የኔን ሚስት የምትደፍር?!.....አንተ ነህ ህይወትን የምትተኛት?....በእጄ በልተህ ጠጥተህ በእጄ ተምረህ....በእጄ አድገህ ሚስቴን ታባልግብኛል.....አንተ የማትረባ ከንቱ!» ብሎ አሮጊቷን መንጭቆአቸው ሲንደረደር መደምደሚያ የነገሩ አቅጣጫ ገባውና ወደ ኋላው ሸሽት አለ።

ሰማይነህ ኮሪደሩን ላይ ያገኘውን ነገር ሁሉ አንስቶ እየወረወረበት ተከታተለው። የመኪናውን ቁልፍ ሳይቀር ወረወረበት። መደምደሚያ ባልጠበቀው ነገር በመጠርጠሩ ንዴት ይዞት ቆሞ ሊጋተረው ልቡ ከጅሎ ነበር። ያልሆነ ወሬ ሰምቶ እንዳበደ ገባው። ወሬ አቀባዩም ከጎርፉ ሌላ ማንም እንደማይሆን ገመተ። ሰማይነህ ታላቅ ወንድሙ ነው፤ አሳድጎታል፤ አስተምሮታል፤ አብሮት በኖረበት ይህን ሁሉ አመታትም ለእሱ ክፉ አልነበረም። የጠየቀውን ሁሉ ሲያሟላለትና ፈቃዱን ሲፈፅምለት ኖሯል። መደምደሚያ ይህን ሲያስብ እናባ ተናነቀው፤ ከባለውለታው ታላቅ ወንድሙ ጋር መሰዳደብም ሆነ ዱላ መግጠም አልፈለገም። ይልቁንም ፈሪ ሆኖ ተንሸንፎ መሸሽን መረጠ። ቆሞ ዕውነቱን ሊያስረዳው ቢሞክርም ሰማይነህ ፍፁም የማይሰማበት ሁኔታ ላይ መሆኑን ገምቶ ወደ ውጭው በር እየሮጠ ሸሸ። ሰማይነህ የሚወረውረው ነገር አጥቶ በረንዳው ላይ ሆኖ እየጮኸ የመጨረሻውን ርግማን አወረደበት። «ሁለተኛ ግቢዬን እንዳትረግጥ!» ብሎ አባረረው።

መደምደሚያ ሸሽቶ የውጭውን በር ከወጣ እብኋላ እንደ ገና ዕልህ ተናነቀው። ተመልሶ ገብቶ ከጎርፉ ግብ - ግብ መግጠም አሰኘው። በበረንዳው በኩል ጥጉን ይዞ ቆሞ አይቶት ነበር። ከአንድ እናት የተወለደ ወንድሙ ሊመስለውም አልቻለም። በደህና ድንጋይ አናቱን ተርክኮ ሊጥለው ተመኘ። ሆኖም ግን ወደ ግቢው ከተመለሰ ከሰማይነህም ጋር መጣላቱ አይቀርም። የከፋ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ባለ ውለታ ወንድሙን በጨዋነት ለመሸሽ ሲል በውሸት ስብቀት ተንሸንፎ ሄደ።

ሁለተኛ ተመልሶ የሚመጣበት ቤት አልመሰለውም። ሆዱን በጣም ከፋው። ሳያስበው ልቡን ፈንቅሎት ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። እያለቀሰ ሄደ።

እናትዬውም በረንዳ ላይ ሆነው ሰማይነህን እየገላገሉ መደምደሚያን በእንባ ሸኙት። ብሶቱ እሳቸውንም ሆድ አስባሳቸው፤ ለቅሶው ከርቀት የታያቸው ይመስል እሳቸውንም አስለቀሳቸው። የሚወዱት የመጨረሻ ልጃቸው፣ ትንሹ ልጃቸውም ማሚጠጫ ልጃቸው መደምደሚያ በዚህ መልክ ከግቢው መውጣጡ ሆዳቸውን አንቦጫቦጨው። ሰማይነህ ማብረድ የማችይቻልበት ደረጃ ላይ መሆኑ ታውቋቸው ነው እንጂ፣ ልባቸው ለመደምደሚያ አድልቶ «ተው እንጂ ልጄን እንዲህ አታስከፋብኝ - ያወም የመጨረሻዬን ማሚጠጫዬን ማለት አምሯቸው ነበር።

ለአንዳፍታ ዘወር ብለው ጎርፉን ተመለከቱት። በአንድ በኩል ቤተሰቡን እንዲህ ተንጦ መደምደሚያና ህይወት ዒላማ መሆናቸው ልቡን እያስደስተው ትርዒቱን ለመመልከት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰማይነህ ወደ እሱም ዘወር ያለበት እንደሆን እግሬ አውጭኝ ለማለት እንዲመቸው ሆኖ ጥጉን ይዞ እንደ ቆመ ነው።

«አንተ ደደብ!.....አሁን አንተ ሰው ነህ?» አሉት እናትዬው አየገላመጡት።

«ምን አረግኩሽ?.....» አላቸው እሱም እየተልጎመጎመ።

«ለሰማይነህ እንዲህ አይነት ነገር እንዳታወራ አስምዬህ አልነበረም?!»

«ታዲያ ምን ላድርግ!....እሱ አፋጠጠኝ።»

«እኝኝዋ!......ከብት!.....» አሉት አሮጊቷ በንዴት።

ሰማይነህ ወደ በኢት ውስጥ ሲመለስ ቅጭል - ቅጭል የሚል የስልክ ድምፅ በመስማቱ፣ ወደ መኝታ የሚሄደውን መስመር በጥሶ ህይወት ከምትደውልበት ቦታ አቋረጣት። እና እንደገና የመኝታ ክፍሉን በር ለማስከፈት እየደበደበ መጮሁንና መሳደቡን ቀጠለ።

ህይወት የስልኩ መስመር ሲቋረጥባት የምታደርገው ነገር ጋራ ገባት። መጀመሪያ ከዚህ ችግር ውስጥ የምትወጣበትን መንገድ ስታስብ አክስቷ ጋ መደወል አማራት። ሆኖም በአክስቷ ላይ ዕምነት ስላጣች ጉዳዩን ለፖሊስ አመልክታ እንዲደርሱላት ለማድረግ ወሰነች። የፖሊስን አድራሻ ለማግኘት የቴሌኮሙኒኬሽንን ማዞሪያ በመጠየቅ ላይ እያለች ነበር ሰማይነህ መስመሩን የቆረጠባት። አሁን ደግሞ ሌላ ዘዴ ማሰብ ጀመረች። ሰማይነህ በሩን ሰብሮ ገብቶ ሳያንቃት በፊት የንዴት አቅጣጫውን ማስቀየር እንዳለባት አሰበች። ባዶ ክፍል ውስጥ በጭንቀት ተውጣ ስታስብ የመጣላት ውሸት ፈጥሮ ራስን የማዳን ዘዴ ጎርፉንም የምትበቀልበት በመሆኑ ደስ አሰኛት።

ውሸት መናገር ስላልለመደች ህሊናዋ ትንሽ ታገላት። ሆኖም ግን ምርጫ የላትም። ፊልም ለመስራት የተዘጋጀች አድርጋ ራሷን ወሰደች። መዋሸት ቀላል ነገር ነው። ፊልም ላይ መርዝ ቀምመው ወዳጆቻቸውን የሚገድሉ ሴቶች ታወሷት። ‹እና፤ እኔ አሁን ራሴን ለማዳን መዋሸት እንዴት ያቅተኛል?› አለች። የምታቀርበው ውሸት በሰማይነህ ዘነ ተቀባይነት ሊያገኝም ላያገኝም ይችላል። ሆኖም ግን ቢያንስ ለጊዜው የንዴት አቅጣጫውን እድነሚያስቀይረው ተማመነች። አብሮ በመኖር የሰማይነህን ፀባይ ስላወቀችው ማታለሉም ቀላል ሆኖ ተሰማት።

«......የምታምነኝ ከሆነ ምንም ነገር ሳልደብቅ ዕውነቱን እነግርሀለሁ» አለችው በሩን ሳትከፍት ከውስጥ እንደሆነች።

«እውነቱን አውቄዋለሁ። በሩን ብቻ ክፈቺልኝ። አንቺ ወራዳ!.....» አላት እሱም እየጮኸ።

«ዕድል ስጠኝ ሰማይነህ። ዕውነቱን ልንገርህና ብትፈልግ ግደለኝ። ፍርድህን መጨረሻ ላይ አድርገው»

«እኮ በሩን ከፈቺ!.....»

«ዕውነቱን እስኪታውቅ እንደማትነካኝ ቃል ግባልኝ»

«አልነካሽም።.....ብቻ ከፈቺ።»

ሰማይነህ መደምደሚያ ላይ የወረወረውን ቁልፍ እናትዬው ቶሎ ብለው በእጃቸው አስገብተዋል። ከመኪና ቁልፎቹ ጋር የጦር መሳሪያው የሚቀመጥበት የአልጋ ሳጥን መክፈቻ ትንሿ ቁልፍ እንዳለች ያውቃሉ። የመጀመሪያው ስጋታቸው መኝታ ቤት ገብቶ መሣሪያውን ካወጣ አደጋ ያደርሳል ብለው ነበር። አሁን ቁልፉን ከያዙበት በሁላ ግን ወደ ውስጥ ገብቶ ህይወትን ትንሽ በክርኑ እንዲያቀምሳት ልባቸው ሳይመኝ አልቀረም።

በሩ የመከፈት አዝማሚያ ሲታይበት ወደ ሰማይነህ ጆሮ ጠጋ ብለው በሹክሹክታ ድምፅ «አደራህን ልጄ..... ቀስ ብለህ.....በእጅህ ሰበብ እንዳትሆን። እጅህ ላይ እንዳታልፍ ተጠንቀቅ። ......ደግሞም አዋቂው የነገረንን አትርሳ» አሉት።

በሰማይነህ ጭንቅላት ውስጥ የጠንቋዩ ምክር ለአንዳፍታ አቃጨለ።

‹.....ይቺ ልጅ ገድህ ናት። የብዙ ሰዎች አይን ያርፍባታል። ገላጊዋም ብዙ ነው። እሷን ካጣህ ይረግፋል፤ ህይወትህም መቅኖ ያጣል።›

ይህን ቢያስታውስም፣ ከጎርፉ የሰማው ወሬና የቅናቱ ዛር ስላሰከሩት ንዴቱን መቆጣጠር አልቻለም። ህይወት በፍርሀት እየተንቀጠቀጠች በሩን እንደከፈተችለት ዘልሎ አንገቷን አነቃት።

«በይ ተናገሪ። አንቺ ሸርሙጣ!»

ህይወት ትንፋሿን ውጣ ዓይኖቿን ሳላፈጠጠች እንዳትሞትበት አሳሳቸውና ሰማይነህ ነፍስ ገዝቶ አንገቷን ለቅቆ፣ ፀጉሯን ጨምድዶ ያዛት።

«.....እኔ ምን ላድርግ?......እሱ ነው አስገድዶ የደፈረኝ.....ቆይ ልንገርህ ሰማይነህ» አለችው ህይወት ፊቷን በእጇ ሸፍና እየታገለች።

‹አሃ! ራሷም.....ልታምን ነው› ብሎ ሰማይነህ ደስ አለው። ጎርፉ የነገረውን ህይወት በራሷ አፍ እንድታረጋግጥለት ቸኮለ። የበለጠ ለማበድና ለመጮህ መላ ህዋሳቶቹ ተነቃቁ።

«እኮ ተናገሪ!.......» ብሎ ፀጉሯን እንደጨመደደ ሲገፈትራት ተውተርትራ አልጋው ላይ ወደቀች።

ህይወት ራሷን ለመከላከል ቶሎ ተነስታ ስትቆም የሰማይነህ እናትና ጎርፉን አየቻቸው። ሁለቱም ትርዒቱን ለመመልከት ሰማይነህን ተከትለው ገብተው ነበር።

«እውነቱን እነግርሀለሁ።......መጀመሪያ እነሱ ይወጡልኝ» አለችው።

«ማነው የሚወጣው?!.....» አሏት አሮጊቷ በቁጣ።

«ሁለታችሁም ውጡልኝ» አለቻቸው በድፍረት።

«እስኪ ውጡላት። የምትለውን ልስማ.....» አለ ሰማይነህም ንዴትና የወሬ ጉጉት ተጣምረው የሚያደረገውን እያሳጡት።

አሮጊቷና ጎርፉ ገላምጠዋት ሲወጡ ህይወት የመኝታ ክፍሉን መልሳ ከውስጥ ቆለፈችው። የምትለውን ለመስማት ጎርፉ እዚያው በር ላይ ተለጠፈ።

«ለምን የሌላ ሰው ወሬ ትሰማለህ ሰማይነህ?!......እኔ ሚስትህ ነኝ። እንድታምነኝ እፈልጋለሁ። እውነቱን ማወቅ የምትችለው ከእኔው ከራሴ እንደበት ነው።.....»

«ተናገሪ እኮ አልኩሽ!.....»

«እኔ ከወንድምህ ጋር አላጣላህም ብዬ ነው ሳልነግርህ የቆየሁት።.....»

«ይሄንን ቅጥፈትሽን ወዲያ በይ!.....አንቺ መጀመሪያ ፊት ባትሰጪው ኖሮ እሱ ሊደፍርሽ አይችልም ነበር።»

«ፊት ልነሳው አልችልም ነበር። አንደኛ ነገር ወንድምህ ነው። ሁለተኛ ደግሞ እኔን እንዲቆጣጠርና እንዲጠብቅ ሀላፊነት የሰጠኸው ለእሱ ነው። በሄድኩበት ቦታ ሁሉ ይከተለኛል፤ ይጠብቀኛል። ስለዚህ አንተ አምነህ ሀላፊነት የጣልክበትን ወንድምህን እኔ ልጠረጥረውና ፊት ልነሳው አልችልም ነበር። አብሮኝ በመዋሉ ሊደፍረኝ ሞከረ.....»

«ስለማን ነው የምታወሪው?! እኔ እኮ የምጠይቅሽ ስለ መደምደሚያ ነው።»

«እኔ ደግሞ የምነግርህ ስለ ጎርፉ ነው። መደምደሚያ ምንም አላደረገኝም። መኝታ ክፍሌ ድረስ ገብቶ ሊደፍረኝ የሞከረው ጎርፉ ነው። ምናልባት ይህን ብልግናውን ለመሸፋፈን መደምደሚያን ጥፋተኛ አድርጎ ነግሮህ አሳስቶህ ይሆናል።.....»

ጎርፉ በሩ ላይ እንደ ተለጠፈ ይህንን ሲሰማ ሰውነቱ በአንድ ጊዜ በላብ ተዘፈቀ። በድንጋጤ የሚሆነውን አጣ። የማጥወለወል ዓይነት ስሜት ተሰምትቶ ፊቱ አመለጠው። ሽቅብ እንደ ማቅለሽለሽም አለው። ሾርባውና ተከታይ ምግቦች ሳይቆጠሩ፣ ሁለቱ የዶሮ አሮስቶዎች እንኳ ቢወጡ ከባድ ኪሳራ መስሎ ታየው። ከዚያ በኋላ የጎደለውን ለመሙላት የሚያስፈልገው ወጪም ከወዲሁ አሳሰበው። በጭንቀቱ ውስጥ የሆዱን ነገር ማሰቡ ሊያስደንቅ አይገባም። ሰማይነህ የህይወትን ወሬ አምኖ ከቤቱ ካባረረው ጎርፉ ሌላ መግቢያ የለውም። በስፋት የለመደ ሆዱን አጥብቦ ለናድ ራሱ ተፍጨርጭሮ መኖር የሚችል ሰው አይደለም። ዓለም የጨለመበት መስሎ ታየው። ሮቶ ማምለጥ ወይንም የህይወትን ወሬ ለአምስተባበል መጮህ አማረው።ሆኖም የሰማይነህ ምላሽና የወሬውን ውጤት ለማወቅ ስለጓጓ በግንባሩ በኩል የሚጎርፈውን ላቡነ የጠረገ በሩ ላይ እንደ ተለጠፈ ቆየ።

ሰማይነህ ተምታቶበት የሚሰራውንና የሚናገረውን አጥቶ ነበር። ከህይወት የሰማው ነገር በአዕምሮው ይዞት የመጣውን አዘበራረቀበት።

«ም - ምንድነው የምታወሪው?!.....» ብሎ ጮኸባት።

«ዕውነቱን ነው የሚወራው......» አለች ህይወት ድርቅ ብላ። «ያን ዕለት እናትህ ግቢ ውስጥ አልነበረም። ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደሄዱ ቆይተው ነበር። አንተም ወደ ስራህ ሄደሃል። ጎርፉ የብቸኝነቴን አጋጣሚ ተጠቅሞ ሊደፍረኝ መኝጣ ክፍሌ ድረስ ዘው ብሎ ገባ። አጠገቤ ደርሶ ሲይዘኝና ለድሪያ ሲታገለኝ ጮህኩ።.....»

«ሰማይነህ ራሱ ላብ አሰመጠው። ሚስቱ እንዴት እንደ ተደፈረች በህሳቡ ቁልጭ ብሎ እየታየው ቅናቱ አገረሸበት፤ ሰውነቱን አንቀጠቀጠው።

«ጎ - ጎርፉ.....ያ ያመንኩት ወንድሜ?!....»

«አዎ፤ ያመንከው ወንድምህ!......»

«ጎርፉ ደ - ደፈረኝ ነው የምትይኝ?!....»

«አልደፈረኝም.....ድፍረት ስልህ መታገሉንና መሞከሩን ነው እንጂ.....ቀሚሴን ገልቦ የፈለገውን ማድረግ አልቻለም፡፡ በእምቢታ እየታገልኩት ስጮህ መደምደሚያ ሰምቶ ከጥናት ከፍሉ እየሮጠ ደረሰልኝ፡፡ ሁኔታውን ሲመለከት ነገር ገብቶት ጎርፉን ሰደበው፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መደምደሚያና ጎርፉ ፀበኞች ናቸው፡፡»

ህይወት በጭንቀት ተውጣ ያቀረበችው ውሸት ውጤት ማምጣቱን በሰማይነህ ገፅ ላይ ስትመለከት መጠነኛ እፎይታ አገኘች፡፡

«ያው ነው!.....እንደደፈረሽ ይቆጠራል፡፡ ይሄ ደደብ አህያ!.....እሱም በአቅሙ የእኔን የሰማይነህን ሚስት ደፈረ?!.....በቁሜ ሞቻለኋ!......ወይኔ!.....» ብሎ መሣሪያውን ለማውጣት ቁልፉን ቢፈልግ የለም፡፡ ኪሱን ቢዳብስም አላገኘውም፡፡ መደምደሚያ ላይ መወርወሩን ረስቶታል፡፡

ጎርፉ ከውጭ ሆኖ ከለቅሶ ባልተለየ ድምፅ»......የነገረችህ ሁሉ ውሸቷን ነው፡፡ አትመናት ሰማይነህ፡፡ እኛን ልታጣላን ነው» እያለ እየጮኸ ሲሮጥ ይሰማል፡፡

ሰማይነህ በዕብደት የመኝታ ቤቱ በር ከፍቶ ሲወጣ ጎርፉ በሩጫ የውጭው በር አጠገብ ደርሷል፡፡

«ና! አንተ ውሻ፡፡.....የትም አታመልጠኝም፡፡ አንተ ነህ የኔን ሚስት የምትደፍር?!.....ልክስክስ!.....ከርሳም አሳማ!......»

ጎርፉን የሱሪውን ቀበቶ ሽቅብ ይዞ እየሮጠ የውጭውን በር ወጣ፡፡ ሱሪውን አላመነውም፡፡ የተበላሻሸ ስለመሰለው በአካባቢው መፀዳጃ ቤት ፍለጋ ጀመረ፡፡

ዘበኛው በግቢው ውስጥ የተፈጠረው ድንገተኛ ተዓምር ግራ አጋብቶትና በወንድማማቾች ፀብ መሀል መግባቱ አስፈርቶት ጥጉን ይዞ ቆሞ ነበር፡፡

«ዝጋ በሩን!.....ሁለተኛ እዚህ ግቢ እንዳይደርስ!» በማለት ሰማይነህ ሲጮህበት፣ ዘበኛው በሩን ጥርቅም አድርጎ ዘጋው፡፡

የሰማይነህ እናት እንደገና በተፈጠረው ሌላ ችግር ግራ ተጋብተው እያዘኑና እየተቆጡ ኮሪደሩ ውስጥ በመንጎራደድ ላይ ነበሩ፡፡

«....ይቺ እሾክ!.....ደሞ ምን ብላህ ይሆን? ልጆቼን እኮ አፋጅታ ጨረሰቻቸው፡፡ እንዴት አይነት ቁጣ ነው እባካችሁ!» እያሉ ሰማይነህን ወደ ቤት ውስጥ አስገቡት፡፡

ሰማይነህ ጩኸቱን አላቋረጡም፡፡ የደረሱት ወሬዎች ስለተምታቱበትና ወዳጅና ጠላቱን ስላምታቱበት በማን ላይ እንደሚጮህ በቅጡ አያውቀውም፡፡ ነገር ግን በንዴት ጦፏል፡፡ በጅምላ ሁሉንም ይራገማል፡፡ ጎርፉን ይሳደባል....መደምደሚያን ይሳደባል.....ህይወትን ራሷን ይሳደባል.....አሮጊት እናቱን ሳይቀር ይሳደባል፡፡ ግድግዳውን በቡጢ ይደበድባል.......እግሩ ስር ያገኘውን በካልቾ ይረግጣል፡፡

እናትዬው አዝማሚያው አስፈራራቸው፡፡ ወደ ዕብዶች የሚያመራም መሰላቸው፡፡ ድርጊቱ ሁሉ ከመቼውም የተለየ ነበር፤ እንደልማዳቸው ህይወትን ረገሚት፡፡

«እግዜር ይይልሽ አንቺ ከይዚ!....ይኸው ልጄን አሳበድሽው፡፡»

ሰማይነህ ሀይሉን እስኪጨርስ ድረስ እየጮኸ ተሳድቦና በቅናት ተንፈራግጦ ሲያበቃ በአፉ አረፋ ደፈቀ፡፡ በመጨረሻም ስላኦን ውስጥ ሶፋ ላይ እንደ ተቀመጠ ድካሙ አሸንፎት እንቅልፍ ሽለብ አደረገው፡፡

ቶሎ አልነቃም። ሶፋው ላይ በአንድ ጎኑ እንደ ተኛ ሳይገላበጥ፣ ጭልጥ ያለ የድካም እንቅልፍ ወስዶት አደረ። ይልቁንም እናቱን ህይወት በመጠራጠርና ድንገት እንዳይነቃ በመፍራት፣ ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ በዓይናቸው ሳይዞር ቁጭ ብለው አደሩ።

በማግስቱ ጠዋት ሲነሳ ሰማይነህ ንዴቱ ቀለል ቢልለትም ነገሩ ከአዕምሮው አልጠፋም ነበር። ሁኔታውን ለማመዛዘን ሲሞክር ሁሉንም ሙሉ በሙሉ ለማመን ያስቸግራል፤ ሙሉ ለሙሉ ቸል ማለትም አይቻልም። መደምደሚያ ከህይወት ጋር የሚያደርገውን መቀራረብ ቀድሞውንም አልወደደለትም። አሁን ደግሞ አዲሱ ጥቆማና ጥርጣሬው ዕውነት ይሁንም አይሁን ከህይወት አጠገብ መራቅ እንዳለበት ወሰነ። በጎርፉም ላይ ህይወት የሰጠችውን ጥቆማ ንቆ ሊተወው አልቻለም። መፍትሔው እሱንም ከህይወት አጠገብ ማራቅ ነው ወደሚል መደምደሚያ ደረሰ። እናቱን ለብቻው ጠርቶ ይህንኑ አቋሙን ነገራቸው፡

«እማማ።.....መሀላችን ያለሽው አንቺ ነሽ። በስተመጨረሻ ዕድሜ ላሳዝንሽ አልፈልግም። የሆነውን ሁሉ ስምተሻል፤ ወይንም አይተሻል። ከእንግዲህ ወንድሞቼ ከእኔ ጋር መኖር አይችሉም። በእነሱ ምክንያት ትዳሪ መበላሸት የለበትም። ሁለቱም እዚህ ቤት ተመለሰው እንዳይገቡ። ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን በሙሉ በውጭ አሟላላቸዋለሁ። በርቀት እረዳቸዋለሁ» አላቸው።

«እሺ» አሉ እሳቸውም ፈርተውት።

«ህይወት ከእኔ ጋር ካልሆነ በስተቀር ከቤት እንዳትወጣ። ወደ ውጭ የስልክ ግንኙነትም እንዳታደርግ አንቺ ጠብቂልኝ። ዘበኛውንም በተጨማሪ አስጠነቅቀዋለሁ።»

«ኧረ እኔውም እበቃለሁ። ድሮውንስ ይሄን መች ዘነጋሁት?!......»

«የለም እማማ፤ እንደሱ አትበይ። እግርሽ እድነማያርፍ አውቃለሁ። አሁን ግን ንቅንቅ ሳትይ እንድትጠብቂልኝ እፈልጋለሁ። ፀሎቱንም ፀሎቱንም ቤትሽ ውስጥ ሆነሽ ብታደርጊው ይበቃል።

«እሺ እንዳልክ ልጄ.....ብቻ በሆነ ባልሆነው አትናደድብኝ። ራስህን ትጎዳለህ።

# ክፍል አሥራ ሁለት

መደምደሚያ ከቤቱ እንደወጣ አልተመለሰም። ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከጓደኞቹ ጋር እያደረና እየተመገበ ሦስት ቀናት አሳለፈ። እናቱ እድነሚጨነቁ ቢያውቅም በደፈናው የሰማይነህ ቤት ስላስጠላው ስልክ እንኳ አልደወለላቸውም። የሰማይነህ ሁኔታ ከፉኛ ስላናደደው ከቤተሰቡ በመራቅ ነገሩን ለመርሳት ሞከረ። ሆኖም ግን ሊረሳው አልቻለም። ባልፈፀመው ድርጊት ወንጀሉ እየከነከነውና ጥቃት እየተሰማው ይበልጥ እንቅልፍ ነሳው።

ምን ማድረግ እንዳለበት በሀሳቡ ሲያወጣና ሲያወርድ ከቆየ በኋላ ባህሩ ፂሞ ለማነጋገር ወሰነ። ይህንን ሰው ምናልባት ሰማይነህ ያዳምጠው ይሆናል። ዕውነቱን በእሱ በኩል እንዲያውቅ ማድረግ አለብኝ የሚል ዕምነት ስላደረበት በስራ ሰዓት ወደ ቢሮው ሄደ።

ባህሩ ፂሞ ስራ ይበዛበታል። የሙያ ምክርና የህግ አገልግሎት የሚፈልጉ ደንበኞቹ ቢሮውን ሞልተው ወረፋ እየጠበቁ ነበር። መደምደሚያን ሊያነጋግረው ስላልቻለ ከስራ ሰአት ውጭ ለመገናኘት ተቀጣጠሩ።

ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ሲገናኙ ባህሩ ፂሞ መደምደሚያን ይዞት በመኪናው በቀጥታ ወደ ወ/ሮ ስራሽ ውስኪ ቤት ወሰደው። የዘወትሩ ልማዱ ስለመራው ለመደምደሚያ የምርጫ ዕድል እንኳ አልሰጠውም።

«ይሄ የነህይወት ቤት አይደለም እንዴ?.....» አለው መደምደሚያ ከመኪናው ሳይወርድ።

«ልክ ነህ። የወንድምህም ማምሻ እዚሁ ነው።»

«እኔ ግን ሌላ ቦታ ብንሄድ ደስ ይለኛል። ሰማይነህን ማግኘት አልፈልግም። አንተን ለብቻህ ማነጋገር የምችልበት ቦታ ቢሆን እመርጣለሁ።»

ባህሩ ፂሞ የመደምደሚያን ፈቃድ ለመፈፀም መኪናው ውስጥ ተመልሶ ገብቶ በሀሳቡ ቦታ ይመርጥ ጀመር። መደምደሚያ የብዙ ጊዜ ታናሹ ቢሆንም በአስተሳሰቡ ያከብረዋል፤ ብስለቱንና ለዕውቀት ያለውን ጉጉት ያደንቅለታል። ትምህርታዊ ክርክሩንም ይወድለታል። ከሱ ጋር የማይግባቡት በሴቶች ላይ ባላቸው የአመለካከት ልዩነት ብቻ ነው። ከሰማይነህ ጋር ባለው ቅርበት ሳቢያ አልፎ አልፎ ከመደምደሚያ ጋር ለመቀራረብና ለመጨዋወትም ዕድል አግኝተዋል።

አንድ ቦታ ትዝ ሲለው መኪናውን በፍጥነት አስነስቶ ወደ ቀበና በረረ። ይሄኛውም የመጠጥ ግሮሰሪ ነው። ሌላ የመዝናኛ ቦታ ማሰብ ያለ መቻሉ መደምደሚያን አስገረመው። የምርጫውን ዕድል ለእሱ ያልሰጠውም በምሽቱ ኬክ ቤት እንዳይወስደው ፈርቶ መሆኑን ገመተ። መጠጥ በጣም እንደሚወድ ያውቃል። ቀን ይሰራል፤ ማታ ይጠጣል። የኑሮው ዑደት በዚህ አጥር የተከለለ ይመስላል።

«እንዲያውም እዚህ ይሻለናል፤ በደንብ ይቀዳሉ። ወ/ሮ ስራሽ እኮ እንዳንዴ ስትቀዳ ትሸቅባለች» አለው ወደ ውስጥ ገብተው ጥጋቸውን ይዘው ከተቀመጡ በኋላ።

ቤቱ ሰፊ ሆኖ ፀጥ ያለ ነው። የሚያውቁት ሰው የማይደርስበት ቦታ ሆኖ ስለተሰማው መደምደሚያ ለውይይቱ አመቺ መስሎ ታየው። እንደየምርጫቸው ለባህሩ ውስኪ ለመደምደሚያ ቢራ ቀረበላቸው። ባህሩ የመጀመሪያዋን መለኪያ ዳብል ውስኪ በአንድ ትንፋሽ ከወረራት በኋላ ሌላ እንዲጨመርላት አዝዞ ፂሙን እየላገና ቁልቁል እየጎተተ ጨዋታውን ጀመረ። ልማድ ሆኖበት ረዥም ፂሙን መነካካት የሚጀምረው መጠጥ ሲጀምር ነው።

«እሺ እባክህ......ዛሬ ለብቻዬ የፈለግከኝ ምክንያቱ ምንድነው?» አለው። መደምደሚያ እንዴት እንደሚጀምርለት ጨንቆት እያሰበ ነበር።

«ምን መሰለህ ጋሽ ባህሩ.....እንደምታውቀው ሰማይነህ የማከብረው ታላቅ ወንድሜ ነው። እንደ አባት ሆኖ አሳድጎኛል፤ አስተርምሮኛል.......መሠረት በሌለውና በማይረባ ወሬ ተነሳስቶ እንዲያዝንብኝ አልፈልግም።......ሰሞኑን ተጣልተን እኔም ከቤቱ ወጥቻለሁ። እስከ መጨረሻም ወደ እሱ ቤት መመለስ አልፈልግም። ነገር ግን ዕውነቱን እንዲያውቅና እንደተከባበርን እንድንለያይ እፈልጋለሁ። እሱ እንደገመተኝ እኔ ይህንን ያህል ሞራሌ የላሸቀና ምግባሬ የተባላሸ ሰው አይደለሁም። ልሆንም አልችልም.....»

ሲናገር ሲቃ ተናነቀው። እንዲህ ያናደደው ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ ባህሩ ቸኮለ።

«የፀቡ መንስኤ ምንድነው እሱ?»

«እኔን በሚስቱ......በህይወት ጠርጥሮኝ ሙልጭ አድርጎ ሰደበኝ። ከቤቱ እንድወጣም አባረረኝ። ሊደበድበኝም ሞክሮ ነበር።.....»

«አሃ!.....» አለ ባህሩ ፂሞ የሚፈልገውን ነጥብ እንዳገኘ ሁሉ ተደቶ «ሴቶች የፀብ ምንጭ መሆናቸው የሚያስደንቅ ነገር አይደለም። ፅጌረዳ አበባ ግንዱ እሾህ ነው.....ህይወትን ሳውቃት ገና ልጅ ነበረች። ወንድማማቾችን ለማጣላት የደረሰችና የምታስብ አትመስልም። ሆኖም ግን ‹የሴትና የእንትን ትንሽ የለውም› የሚባለው እውነት ነው። ሴቶችን ማመን አይቻልም» አለው።

የራሱን ስሜት መናገር እንደ ጀመረ መደምደሚያ ገባው። ስለሴቶች ክርክር ገጥሞ፣ የመጣበትን ጉዳይ ረስቶና ነገሩ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይሄድ ተጠነቀቀ።

«ጥፋተኛዋ ህይወት አይደለችም። እሷ ምንም አላደረገችም። እንደ ራሱ እየመሰለው ተራ ጥርጣሬውንና ግምቱን በወሬ አጣፍጦ ለሰማይነህ የሚያቀርብለት ሌላው ወንድማችን ጎርፉ ነው። አሁንም ያጣላን እሱ ነው። እኔን ያናደደኝ ሰማይነህ የጎርፉን ወሬ ሰምቶ ማመኑ ነው።»

«አንተ እንኳን ጠንቃቃና ቀጥተኛ ልጅ እንደ ሆንክ እኔ አምንበሀለሁ። ሰማይነህ በእንዲህ አይነቱ ተራ ነገር ከጠረጠረህ ከቶውንም አያውቅህም ማለት ነው።»

«አመሰግንሀለሁ። አንተን ፈልጌ የመጣሁትም ለዚሁ ነው። በተገናኘንባቸው አጫጭር ጊዜያቶችም ቢሆን ማንነቴን ያወክልኝ ይመስለኛል። ይህንን ማንነቴን ለሰማይነህ እንድትነግርልኝና አጓጉል ጥርጣሬውንም ሆነ ጥላቻውን እንዲያነሳልኝ ነው። ካስፈለገም ከእኔ ጋር በግንባር ተገናኝንተን እንድንነጋገር አድርግልኝ። ምኞቴ እውነቱን እንዲያውቀው ብቻ ነው። ሌላ ከእሱ የምፈልገው ነገር የለኝም።

ባህሩ ፂሞ በድጋሚ የተቀዳለትን ውስኪ እየተጎነጨ ለአጭር ጊዜያት በዝምታ ፂሙን ሲልግ ከቆየ በኋላ».....ግን አንተን ወንድሙን እንዴት በሚስቱ ሊጠረጥርህ ቻለ?!» አለው።

ጥያቄው ራሱ ጥርጣሬን ያዘለ መስሎ ታየው። የህግ ባለሙያዎች አብዛኛውን ጊዜ ተጠራጣሪ መሆናቸውን መደምደሚያ ያውቃል።

«ምናልባት ለህይወት የማሳየውን ሀዘኔታና ድጋፍ ስለተመለከተ ይሆናል። ከሰማይነህ ጋር በብዙ መንገድ ስለማይመጣጠኑ ታሳዝነኛለች። የወጣትነት ውበትዋና ብሩህ አዕምሮዋ አልባሌ ቦታ ወድቆ የተበላሸ ይመስለኛል። ከወንድሜ ይልቅ ለእሷ አደላለሁ። እና አዝንለታለሁ።....»

ባህሩ ፂሞ ዒላማው ውስጥ የገባለት መሆኑን ለማሳየት ኮራ ብሎ ሳቀ።

«ፍሌቸር ምን ይላል መሰለህ! ‹ወደ ሴት ፍቅር ከሚወስዱት መንገዶች ሁሉ ቀጥተኛው ሀዘኔታ ነው› ኤሄሄሄሄ!.....»

«እኔ ግን ህይወትን የምቀርባትም ሆነ የማዝንላት በንፁህ ወንድምነት ነው» አለ መደምደሚያ ደንግጦ።

«አይዞህ፤ ስቀልድብህ ነው። አንተን እኔ አውቅሀለሁ።.....ሰማይነህ ቢጠረጥህ ደግሞ አትፍረበት። ሚስቱ ቆንጆ ስለሆነች ማንንም ሊጠረጥር ይችላል። ቅድም እንደገለፅኩልህ ከሴቶች ቁንጅና ጋር እሾህ አብሮ መኖሩን መዘንጋት የለብህም።»

«ቁንጅና የፈጣሪ ፀጋ ነው። ህይወት ደግሞ በውበትዋ የምትመፃደቅ ዓይነት አይደለችም። በአስተሳሰብ የሚመጥናት ባል ባለማግኘቷ ነው እንጂ ብሩህ አዕምሮና ቀና አስተሳሰብ ያላት ልጅ ናት.....»

«ዞሮ ዞሮ ግን ሴት ናት። ይህንን አትርሳ። ሴቶችን አምነህ ልትከራከርላቸው አትችልም። እንደ እስስት መልካቸውን የሚለዋውጡ ፍጡራን ናቸው።»

የባህሩ ፂሞ ጥላቻ ስር የሰደደ መሆኑን ቢያውቅም መደምደሚያ በዝምታ ሊያልፈው አልቻለም። ስሜቱ ፈነቀለው።

«በዚህ አባባልህ እንኳ አልስማማም።......ከወንድም መጥፎ፣ ከሴትም መጥፎ ይኖራል። በጅምላ ሴቶችን ብቻ መወንጀሉ ግን ሀጢያት ነው። እኔ ስለ ሴቶች ጥሩነት፣ አርቆ አስተዋይነት፣ የትዳር ዋልታነትና ታማኝነት በርካታ መፃህፍት አንብቤያለሁ......» ከማለቱ አቋዋረጠው።

«አየህ፤ አንተ ገና ልጅ ነህ። አመለካከትህ የተገነባው ከመፃህፍት በምታገኘው ነገሮች ላይ ነው። እኔ ግን በህይወት ገጠመኝ ካገኘሁት ተነስቼ ነው የምነግርህ።.....» አለው።

«እኔም በትንሿ ዕድሜዬ በጥሩ አርአያነታቸው የማውቃቸውና የያኋቸው በርካታ ሴቶች አሉ። የመጀመሪያ ዲግሪዬን ማሟያ የጥናት ወረቀት ያቀረብኩት በተግባራዊ ትዳር ላይ መርኩዤ ስለ ነበር የበርካታ ቤቶችን በር አንኳኩቼ ጠንካራ ሴቶችን ተመልክቼያለሁ። ሙሉ በሙሉ በሚስቶቻቸው የሚመኩና የሚተማመኑ ባሎችም አግኝቻለሁ......መልካም ፈቃድህ ቢሆን በዚህ ጉዳይ ላይ ቀጠሮ ይህን በደንብ ብንወያይበት ደስ ይለኛል።.....»

«እኔን ለመለወጥ ስለማትችል በከንቱ ትክድከም። ዕድሜ ይስጥህና ‹እኔ ያየሁትን ለማየት ያብቃህ እንዳልልህ ርግማን ይሆንብኛል። አየህ.....ለሴት ልጅ ፍቅር ትሰጣት ይሆናል፤ ብር ትሰጣት ይሆናል፤ ከዚህ በላይ ህይወትህን ትሰጣት ይሆናል። ይህ ሁሉ ግን አይበቃትም። በእውነቱ ምን እንደምትፈልግ አይገባህም። ታዋቂው ሊቅ ሲግመንድ ፍሩድ ምን እንዳለ ታውቃለህ?›......እስካሁን ድረስ ያልተመለሰ አንድ ከባድ ጥያቄ አለ። እኔ ራሴ የሴቶችን መንፈስ ለማወቅ ለሰላሳ አመታት ምርምርና ጥናት ባደርግም፣ መልስ ላገኝለት ያልቻልኩት ጥያቄ ነው። አንዲት ሴት የምትፈልገው ምንድነው? ብሏል። እንግዲህ ይህንን ያልኩት እኔ ተራው ባህሩ አይደለሁም፤ ፍሩድ ነው።»

መደምደሚያ ቢራውን ተጎንጭቶ ባህሩን ለመጋተር አዕምሮውን ፈታተሸ። ሳያስቡት ወደ ክርክሩ ሊገቡ ነው። ቢተማመኑም ባይተማመኑም የየበኩላቸውን መተንፈስ ፈለጉ።

«ሲግመንድ ፍሩድ የሥነ ወሲብ ጠቢብ መሆኑን አውቃለሁ ሆኖም ግን እሱም በዘመኑ ስሜታዊ ሆኖ ጠባብና ስሜታዊ አስተያየቶች ሊሰነዝር ይችላል። ሎርድ ሊቴልቶን እንደሚለው ከሆነ ግን ሴቶች ልክ እንደ ልዑላን ጥቂትና እውነተኛ ጓደኞች ይፈልጋሉ። ጆርጅ ሜርዲዝ በበኩሉ ‹ብልህ ሴት ሀብት ናት፤ ብልህ ውብ ደግሞ ሀይል ናት› ይላል። አንድ ሰሙን የማላስታውሰው ፈላስፋ እንደገለፀውም ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ብልህ ናቸው፤ ምክንያቱም ትንሽ አውቀው ብዙ መረዳት ይችላሉ።......»

«ይቅርታ አድርግልኝና፣ ጆርጅ ሜርዲዝ ስለ ሴቶች አንተ ያልከውን ከተናገረ የተምታታበት ሰው ነበር ማለት ነው። ምክናይቱም ‹ሴት ልጅ በወንድ ልጅ ከሰለጠኑት ነገሮች የመጨረሻ ናት› የሚለው ጥቅስ የተወሰደውም ከእሱው ነው።

«ምናልባት ተምታቶበት ይሆናል.....›. አለና መደምደሚያ አዕምሮው ላይ የመጣለት ሀሳብ እንዳይጠፋበት ቶሎ ብሎ» ስለ ሴቶች ፍላጎት አውደን የተናገረውንና የፃፈውን ልጨምርልህ። ‹ወንዶች ደስታና ጨዋታን ፈላጊዎች ናቸው።›....ቆየኝ አንዴ፤ አሁንም አውደንን ልጥቀስልህ። ‹የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከወንዶች እጅ ተነጥቆ ለሴቶች መሰጠት አለበት። ወንዶች ማሽን መስራታቸውን ይቀጥሉ፤ ምን አይነት ማሽን መስራት እንዳለበት መወሰን ያለባቸው ግን ሴቶች ናቸው። እነሱ የተሻለ አስተሳሰብ አላቸው። ለጥፋት ተግባር የሚውሉ ማሽኖችን አሰርተው አያውቁም› ይላል አውደን የተባለው ደራሲ። ከዚህ ሌላ ምን ትፈልጋለህ?!.....ተኩራርቶ እየተቀመጠ።

«ጎበዝ ነህ። አንዳንድ አባባሎችንና ጥቅሶችን ከተናጋሪዎቻቸው ወይንም ከፀኃፊዎቻቸው ጋር የመያዝ ችሎታህን አደንቀዋለሁ። ዛሬ ብቻ ሳይሆን ከሁን ቀደምም ስንጨዋወት የታዘብኩት ነገር ነው» አለው ባህሩ።

«ያንተን ያህል እንኳ ችሎታ የለኝም። አንተ ከእኔ ይልቅ ብዙ ጥቅሶች መያዝ ትችላለህ» አለው መደምደሚያ መልሱ።

«ልክ ነህ። እኔ ምክንያት አለኝ። በተለይ የሴቶችን አሉታዊ ጎን የሚገልፅ ፅሁፍ ስራዬ ብዬ ፈልጌ አነባለሁ። ከውስጡም እየመረጥኩ ጥቅሶችን እይዛለሁ። በወር አንድ ጥቅስ መርጬ ብይዝና እንዳይረሳኝ ደጋግሜ ባነበው በአመት አስራ ሁለት ጥቅሶች ያዝኩ ማለት ነው። በዚህ ዓይነት የአመት ስንቄን እሰንቃለሁ። ካለበለዚያ መኖር አልችልም። የህይወት ትጥቄ እነዚህ ጥቅሶች ናቸው።......»

«ግን ለምን?.....» አለ መደምደሚያ እንዳላወቀ ሆኖ። የምክንያቱን ጫፍ ጫፍ ከሌሎች ሰዎች የሰማ ቢሆንም አሁን ከባለቤቱ አፍ መስማት ፈለገ።

«ሴቶችን ለመጥላትና ለመራቅ ይረዳኛል» አለው ባህሩ በደፈናው። መደምደሚያ ነገሩ እንዳልገባው አስመስሎ ግንባሩን ከሰከሰ።

«ሚስቴ እንደከዳችኝና የልጆቼን አባትነት እንኳን እንደፈለገችኝ ሳትሰማ የቀረህ አይመስለኝም።»

«ኧረ እኔ አልሰማሁም።»

«የቆየ ታሪክ ነው እኮ!....» አለውና ድንገት በቁጣ ስሜት ግንባሩን አጨማድዶ ውስኪውን ጨለጠው። መደምደሚያ የአጠጣጡን ኃይለኝነት እየታዘበ ነበር። በላይ - በላዩ ነው የሚያስቀዳው፤ አሁን ደግሞ ነገር ስላሰበ ባሰበት።

«ሚስት ነበረችኝ፤ ሁለት የወለደችልኝ፤ ከአስራ ስድስት አመት በፊት ያስገባኋት.......» በማለት ጀመረለት። ከብዙ ጊዜ አንዴ እንዲህ የሚቀርበው ሰው ሲያገኝ ስለሚስቱ ማውራት ሀሳቡን የሚከፍልለት ይመስለዋል።

«ከሚስቴ ጋር እንዋደድ ነበር። አንተ እንደትለውም እንተማመንና እንከባበር ነበር። ከመጋባታችን በፊት ሁለት አመት ያህል በውጭ አሳልፈናል። ለመጠናናት በቂ ጊዜ ነበር ለማለት ይቻላል። የተገናኘነው በአጋጣሚ ነበር። አንድ ጓደኛዬ ቤት ለግብዣ ሄጄ፣ እስዋም የቢሮ ባልደረባው ስለ ነበረች እዚያው መጥታ ተያየንና ተፈቃቀድን። በጨዋታው መሀል እንደ ቀልድ አድራሻ ተለዋውጠን ስለተለያየን ከዚያ በኋላ መጠያየቅ ጀመርን። የምትሰራበት መስሪያ ቤት ድረስ እየሄድኩ ከስራ ስትወጣ ወደ ቤቷ እሸኛት ጀመር። አንዳንዴም የከተማውን መዝናኛ ስፍራዎች እየተዘዋወርን አብረን እንንበኛለን። ተላመድን። ከመላመድ ጋር ፍቅር መጣ። የቁንጅናዋን ነገር ልነግርህ አልችልም። መጨረሻዬን ሳላውቅ ‹እግዜር ለእኔ ስላሰበሽ ከሌሎች ወንዶች ወጥመድ ሰውሮ ያቆየልኝ ቆንጆ ነሽ› አላት ነበር። ሀገር ጉድ እስኪለን ድረስ በፍቅር አበድን። ሬቱን ከማስከተሉ በፊት የፍቅርን ጣዕም ያወቅኩት ያኔ ነው.....»

ንግግሩን አቋርጦ ውስኪውን በብዛት ተጎነጨ። ግንባሩ አልተፈታም። ግራ እጁም ፂሙን መጎነታተሉን እንደ መደበኛ ይዞታል።

«አሁን ሳስበው ምናልባት በስተኋላ ላይ ስሜቴን ከፋኛ የጎዳው መጀመሪያ በጣም ማፍቀሬ ይመስለኛል። ኦስካር ዋይልድ እንደሚለው ‹ወንድ ልጅ ፍቅር ላይ እስካወደቀ ድረስ ከማንኛዋም ሴት ጋር ደስተኛ ሆኖ መቆየት ይችላል። ‹......ለማንኛውም ታሪኬን ልቀጥልልህ። ያን ጊዜም እኔ የምሰራው የግል ቢሮዬን ከፍቼ ይህንኑ የአማካሪነት ሥራዬን ነበር። ከፋብሪካዋ የገዛኋት አንድ ዘመናዊ ቮልስ ዋገን መኪናና በርካሽ ዋጋ የተከራየሁት መጠነኛ ቪላ ቤት ነበረኝ። ከዚያ በፊት ጥቂት አመታት ስለ ሰራሁ የቤት ውስጥ ዕቃ አደረጃጀቴም ለከፉ የሚሰጠኝ አልነበረም። በእሷም በኩል ለጋብቻ ከተፈቃቀድን በኋላ ቤት ውስጥ የሚጎድሉትን ነገሮች እያየች አሟላች። በሥርግ ተጋብተን በፍቅር መኖር ጀመርን። ወደ ፊት የራሳችን የሆነ ቤት የመስራትና ኑሮአችንን የማሻሻል ዕቅድ በጋራ ነደፍን። ሁለት ሰኤትች ልጆችም አከታትለን ወለድን።

«ትዝ ይለኛል፡፡ ችግሩ የተፈጠረው በሀገሪቱ ውስጥ አብዮት ፈንድቶ ለውጥ ከተካሄደ በኋላ ነው፡፡ ሥልጣኑን በጠመንጃ የተከቡት ወታደራዊ ገዢዎች ስድሳዎቹ ከፍተኛ የኃይለ ስላሴ ባለስልጣናት ያለ ፍርድ ሲረሽኗአው አዝማሚያቸው አላምር አለኝ፡፡ ገና ከጅምሩ በደርጎች ላይ ጥላቻ አደረብኝ፡፡ የህግ ሰው እንደ መሆኔ መጠን ያለ ፍርድ የሚካሄደው ዘግናኝ ጭፍጨፋ ያስቆጣኝ ጀመር፡፡ ሲውል ሲያደር ያለ ፍርድ የሚሞተው የሚታሰረውና በዱላ ሥቃይ የሚያየው ዜጋ ቁጥር እየጨመረ መጣ፡፡ በየሜዳው ላይ የወደቀ ሬሳ መመልከት ተራ ነገር ሆነ፡፡ በቅርብ የማውቃቸው ጓደኞቼ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገደሉ፡፡ ከፊሎቹም እስር ቤት ተወርውረው ማቀቁ፡፡ ማምለጥ የቻሉም በየበረሀው አቆራርጠው ተሰደዱ፡፡ በርካታ ምህሯንና ወጣቶች ተጨፈጨፉ፤ ያለ ፍርድ ታረዱ፡፡ የተራ ጉዳይ ነው፡፡ ይሄ ፅዋ እኔ በኢት መቸኤ እንደሚመጣ አላውቅም፡፡ ተምሮ መገኘት ወንጀል የሆነበት ጊዜ ነበር፡፡ ጫካ ገብቶ ለመታገልም ሆነ ከሀገር ተሰድዶ ለመኖር ወኔ አልነበረኝም፡፡ ነገር ግን በየቀኑ በማየው አስከፊ ሁኔታ እናደዳለሁ፤ እቃጠላለሁ፤ እጨሳለሁ፡፡ ንዴቱን ለማስታገስ ይሁን ለማባባስ ደረቅ አልኮል መጠጣት ጀመርኩ፡፡ አዕምሮዬ ሰላም ስላጣ ‹ስብእናዬ መላ ቅጡን አጣ፡፡ ብስጩ ሆንኩ፡፡ ከብስጭቱ ማምለጫ ወኔ ስላጣሁ እዚች የምታያት መለኪያ አረቄ ውስጥ ራሴን ደብቄ መኖር ጀመርኩ፡፡ የምጠላቸው ገዢዎች ድርጌ እየከረፋኝ አፍንጫዬን ይገፉ አፍንጫቸው ስር እየጠጣሁ ተቀመጥኩ፡፡

«የአዕምሮዬ ሰላም ማጣት በቤቴም ውስጥ በተለይ መልኩ መንፀባረቅ ጀመረ፡፡ ጠጪነት እንግዳ ነገር ሆነ፡፡ በሀገሬ ላይ ዕምነትና ተስፋ ስላጣሁ የግል ጎጆዬን ለማሻሻል ቅንጣት ታህል ደንታ አጣሁ፡፡ ሀገርና መንግስት በሌለበት ሁኔታ ግዑዝ መሬት ላይ ጎጆ መቀለስም ሆነ ቁሳቁስ መሰብሰብ ሊዋጥልኝ አልቻለም፡፡ ከሚስቴ ጋር እብጋራ የነደፍነው ዕቅድ በሙሉ ፉርሽ ሆነ፡፡ ነጭናጫ ሆንኩ፡፡ ሚስቴ ደግሞ በበኩሏ ‹አንተን እስካልነኩህ ድረስ ምን ቸገረህ?!› እያለች ታናድደኝ ጀመር፡፡ ያለ ፍርድ የተጨፈጨፉት፣ በየአደባባዩ የረገፉትና በየእሥር ቤቱ የታግሩት የእኔነቴ አካሎች መሆናቸውን ብነግራትም ልትረዳልኝ አልቻለችም፡፡› የሞቱትም እይነሱም፤ የታሰሩትም እግዜር ይርዳቸው፤ በአንተ ማዘንና መበሳጨት የሚከሰት ተዓምር የለም፡፡ ይልቅ እኛ ድምፃችንን አጥፍተን ኑሮአችንን ብናሻሽል ይሻላል፡፡ እነዚህ ወታደሮች እንደሆን ለማንም የሚመለሱ አይደሉም› አለችኝ ጭራሹን፡፡ ይህ መሠረታዊ ያለ መግባባትን መፍጠሩ ይሰማኛል፡፡

«ያንኑ ሰሞን ሚስቴ ከመስሪያ ቤቷ፣ በሹፌር መመላለስ ጀመረች፡፡ ‹እንዴት ነው?....እነዚህ ሰዎች ሹመት ሰጡሽ እንዴ? አልኳት፡፡ ‹አዎ፤ ሳያጩኝ አልቀሩም፤ እንደምታየው ሹፌር መድበውልኛል› ብላ እንደ ቀልድ መለሰችልኝ፡፡ ለሹመት የታጨች መስሎኝ ነበር፡፡ ሚስቴ ለባለስልጣን ሚስትነት የታጨት መሆኗ የገባኝ ውሎ አድሮ ነው፡፡ ሰንበትበት ስትል እያመሸች በሹፌ መምጣት ጀመረች፡፡ ምክንያቱን ስጠይቃት በመሥሪያ ቤታቸው ውስጥ አዲስ መዋቅር ለመዘርጋት ጥድፊያ ላይ መሆናቸውንና ስራ ስለሚበዛ ለማምሸት እንደተገደዱ ትነግረኛለች፡፡ ‹ባለሥልጣኖቹ አምሽተው ይስሩ እንጂ አንቺ ታዲያ ምን ቤት ነሽ!› ስላት› ፀሐፊ ነኛ! በዚያ ላይ ታጭታለች፡፡ አምሽታ ስትመታ ከስራ ሳይሆን ከመዝናኛ ቦታ መምጣቷ በደንብ ያስታውቅባታል፡፡ ይባስ ብሎ መኖሪያ ቤቴ ድረስ ስልክ ይደውልላት ጀመር፡፡ ያ ጎርናና ትዕቢተኛ ድምፅ እስከዛሬ ድረስ ጆሮዬ ላይ ያቃጭልብኛል፡፡ ድንገት ስልኩን እኔ ከነሳሁት ሚስቴን እንዳገናኘው የሚያዝዘኝ በቁጣ ነበር፡፡ ሚስቴ ደግሞ ስልኩን ሌላ ክፍል ትወስደውና በሩን ቆልፉ ለረዥም ሰዓት ተዝናንታ ታወራለች፡፡ ጥርጣሬና ፍርሀት በላዬ ላይ ሰፍረው ያናውዙኝ ጀመር፡፡ አዝማሚያው አላምር ስላለኝ ‹ይሄ በምሽትና በዕረፍት ቀን ቤታችን በተደጋጋሚ የሚደውለው ሰውየ ምንድነው? ብዬ ጠየቅኳት፡፡ ‹የደርግ ባለሥልጣን ነው› አለችው ድርቅ ብላ፡፡ ማስፈራራቷ ይሁን ወይንም በተዘዋዋሪ ቁርጤን እንዳውቀው መንገሯ አልገባኝም፡፡ የስልኩ ጋጋታ አሁንም ለስራ ጉዳይ መሆኑን ነገረችኝ......እሷ የምትፈልግበት ምክንያት ደግሞ መታጨቷ፡፡

«ሚስቴ ለስልጣን ሳይሆን ለባለሥልጣን መታጨቷ እየገባኝ መጣ። የቤት ውስጥ ኑሮአችን ከአንገት በላይ ሆነ። መነጋገር አቆምን። አልጋ ለይተን የደባል ኑሮ መኖር ጀመርን። ሰውዬውን የማወቅ ጉጉት ስላደረብኝ በቀጥታ ወደ መስሪያ ቤቷ ሄጄ አንድ ቀድሞ የማውቀውን ሰው ጠየቅኩት። ገና ጉዳዩን ሳላነሳበት እንዲሁ አዝኖልኝ ከንፈሩን ሲመጥ አየሁት። ከጋብቻችን በፊትም ሆነ በኋላ የሚያውቁኝ አንዳንድ የመስሪያ ቤቷ ሰዎችም ከርቀት ከንፈራቸውን እየመጠጡ ሲያዝኑልኝ አየኋቸው። ቡና ማጣጫና ከንፈር መምጠጫ ሆኜ መከረሜ ገባኝ። የማውቀው ሰው እንጄን ይዞ በርጋታ ወደ ውጭ ከወሰደኝ በኋላ ‹ውይ ወንድሜን!.....የማይጋፉት ባለጋራ ገጠመህ አይደል!.....አይዞህ ግዴለም፤ ይህ ጊዜ ያልፋል› አለኝ።

‹ሰውዬውን ማወቅ ፈልጌ ነበር› አልኩት ጉሮሮዬ ላይ እልህ እየተናነቀኝ።

‹የቱ ሰውዬ?.....›

‹የሚስቴን ውሽማ....›

‹እንደዬ.....እስካሁን አላወቅከውም እንዴ? ከፍተኛ የደርግ ባለሥልጣን እኮ ነው። የመስሪያ ቤታችን የበላይ ተጠሪም እሱ ነው› ብሎ ስሙን ነገረኝ። እንደገናም የሚስቴን ስም ጠርቶ.......‹እሷም ይህንን የደርግ ባለሥልጣን መወሸሟ ከታወቀ ጀምሮ ሁላችንም የምንፈራበት አዋሬ ሆናለች። የመስሪያ ቤታችን ፈላች ቆራጭም ሆናለች። ሁሉንም ነገር በስልክ ነው የምትጨርሰው› አለኝ።

«እርሜን አውጥቼ ወደ ቤቴ ተመለስኩ። ሀገር የለኝም፤ መንግሥት የለኝም፤ አሁን ደግሞ ሚስት የለኝም። የመኖር ትርጉሙ ጠፋኝ። አጥፍቶ መጥፋት አማረኝ። በሌላ በኩል ደግሞ ንቆ የመተውና ኖሮ የማሳየት እልህ ውስጥ ገባሁኝ። ቅድም እንደነገርኩህ ፈሪ በመሆኔ አጥፍቼ መጥፋት አልፈለግኩም። እየኖርኩ ማሳየቱን መረጥኩና ከሚስቴ ጋር በሰላም መለያየት እንደሚኖርብን ወሰንኩ። ማታ አምሽታ ስለ መጣች ላነጋግራት አልቻልኩም። እግዜር ይስጣጥ! ታመሻለች እንጂ አድራ አታውቅም። ምናልባት ልጅቷን ፈርታ ይሆናል። ልጆቻችን በዚያ ጊዜ አስራ አንድና አስራ ሁለት አመት ዕድሜ ላይ ደርሰዋል።

«ጠዋት ተነስታ ስትኳኳል እኔም ያሰብኩትን ልንገራት ተነሳሁ። አዲስ ሙሽራ ስለሆነች መሽቀርቀሩን አብዝታዋለች። አዳዲስ የሽቶና የቅባት ዓይነቶች ስትለቀለቅና ለመኳኳል ብዙ ሰዓት ሲወስድባት የጥንቱን የሙሽርነት ዘመናችንን ታስታውሰኛለች።

‹.......በዚህ ዓይነት አብረን መኖር ይበቃናል። መለያየት ያለብን ይመስለኛል› አልኳት።

‹ይቻላል!› አለችኝ ጥያቄዬን ከምንም ሳትቆጥረው የከንፈር ቀለም እየተቀባች።

«ሸርሙጣ መስላ ታየችኝ። ለብዙ ዓመታት አቅፌያት የተኛሁት ሚስቴ ሳትሆን ፍጡር መሰለች። ፊልም እንደምትሰራ ዓይነት ለአንዳፍታ ወደኔ ዘወር ብላ ሙሉ በሙሉ ከተመለሰች በኋላ።

‹ታዲያ ቤቱን መልቀቅ ያለብን ማንኛችን ይመስልሀል?....እኔ ወይስ አንተ?› ብላ በምፀት ድምፅ ጠየቀችኝ።

‹መቼም እኔ ያዘጋጀሁት መሸሻ የለኝም። ግን የምትገቢበት ቤት ተዘጋጅቶ የሚጠብቅሽ ይመስለኛል......› ከማለቴ

‹ያልተጠየቅከውን አታውራ! መዘባረቁን ትተህ ጥያቄዬን በትክክል እንድትመልስልኝ እፈልጋለሁ› አለችኝ።

«በአጭር ቀናት ውስጥ ወታደራዊ ትዕዛዝም ላትለምድ አልቀረችም። ባለሥልጣኑ እንዴት የልብ ልብ እንደሰጣትና እንዳሳበጣት ተሰማኝ።

‹የተናገርኩት ትክክል መሰለኝ፤ የአደባባይ ሚስጥር ነው በማለት ልነካካት ሞከርኩ።

‹!ፋ!....ነገር የማይገባው ሰው ያናድደኛል። ቅል ራስ ይመስለኛል። አይገባህም እንዴ?!.....ለምን ትረብሸኛለህ?! ደግሞም ክብርህን ብትጠብቅ ይሻልሀል› ብላኝ ተሸቀንጥራ ወጣች።

«የቆምኩበት ቦታ በድኔ ሆኜ ቀረሁ። ሚስቴ.....የልጆቼ እናት ‹ቅል ራስ› ብላ ሰድባኝ ስትሄድ ተገትሬ ተመለከትኳት። ለጥቂት ሴኮንዶች ራሴን የሳትኩ መሰለኝ። ራሴን ሳውቅ እንደ ጀግኖች ሽጉጥ ተመኘሁ። አንድ ሽጉጥ ከሦስት ጥይት ጋር ብቻ! ይህንን ሁሉ ንብረት ሳፍራ አንድ ሽጉጥ ሳልገዛ በመቆየቴ ተናደድኩ። ለነገሩ ልቡ ቢኖረኝ ኖሮ ሚስቴን ተከትዬ መደብደቢያ ሌላ ነገር አላጣም ነበር። የፍልጥ እንጨት ግቢዬ ሞልቷል፤ ወደ ጉዳም ገባ ብል ቢላዋ ወይንም መጥረቢያ ይኖራል፤ ሌላው ቢቀር ደጃፌ ላይ ተራ ድንጋይ አገኝለሁ። እንዲሁ ገትሮ ያስቀረኝ አንድም ፈሪነት ነው፤ ካለበለዚያም ሚስቴ ጭራሹን አፍዝዛለች ማለት ነው።

«ይገርምሀል! ከሚስቴ ጋር ለብዙ ዓመታት አብሬያት ስኖር ይህንን ድብቅ መልኳን አላውቅም ነበር። ፍፁም ሌላ ሰው፤ ፍፁም እንግዳ ፍጡር ነው የሆነችብኝ። ‹መጀመሪያ በመሀከላችን የተፈጠረው ያለ መግባባት ለዚህ ደረጃ የሚያደርስ አልነበረም። ጥሩውን ጊዜ በፍቅር እንዳሳለፍነው ሁሉ፤ መጥፎውንም ጊዜ በመቻቻል እናሳልፈዋለን የሚል ዕምነት ነበረኝ። ሚስቴ ግን ከጊዜው ጋር ተመሳስሎ መኖር የማይችል ባል አልፈልግም ብላ የጊዜውን ባለስልጣን ወሸመች። በመሀላችን ያሉትን አብረን ያፈራናቸው ልጆች የወደፊት ዕጣ እንኳ ቅንጣት ታህል አላሳሰባትም። ጭራሹን የሰውዬው ሥልጣን የእሷ ሥልጣን ሆኖ አቅነዘነዛት።

«ያን ዕለት ቢሮዬ ገብቼ የምሰራው ሥራ ሁሉ ትክክል አልነበረም። የኔን የምክር አገልግሎት የሚፈልጉ ደንበኞቼ ሁኔታዬን አይተው በተገላቢጦሽ ለእኔው ምክር እየሰጡኝ ተመለሱ። ከቀኑ ስድስት ሰዓት አካባቢ የታጠቁ ወታደሮች ቢሮዬ ድረስ መጥተው የመኪናዬን ቁልፍ እንዳስረክባቸው አዘዙኝ። ምክንያቱን ለመጠየቅ ዕድል አልሰጡኝም። አፍጥጠው ጠመንጃቸውን እያሳዩኝ አከታልበው ካስወጡኝ በኋላ ቢሮዬንም አሸጉት። የፈፀምኩትን ወንጀል ሳላውቀው ወደ እስር ቤት ተወስጄ ተወረወርኩ። እኔን እስር ቤት ወርውረው እነሱ መኪናዬን እየነዱ ተመለሱ። በዚህ ዓይነት ሚስቴና መኪናዬን ከቀሙኝ በኋላ ያለ ምንም ጥያቄና ምርመራ ሦስት ዓመት ሙሉ እስር ቤት ውስጥ ተቆልፎብኝ ቆየሁ። የባለሥልጣኑ የግል እስረኛ ስለ ነበርኩ ወዳጅ ዘመድ እንኳ እንዲጠይቀኝ አይፈቀድም ነበር።

«ይህንን ፂሜን ታየዋለህ! ለመጨረሻ ጊዜ የተላጨሁት እስር ቤት የገባሁ ዕለት ነው። በቃ! ከዚያ ጀምሮ ምላጭ ነክቶት አያውቅም። የዘለዓለም ሀዘንተኛ ሆንኩ። ወደ እስር ቤት ስወርድ ሚስቴን ምን እንዳስቀየምኳት እያሰብኩ ነበር። አፍ እላፊ ተናግሬያት ይሆን? አይመስለኝም። ባይሆን ‹ቅል ራስ› ብላ የሰደበችኝ እሷ ናት። ምናልባት ጥፋቴ በጥፊ እንድትመታኝ ጉንጬን አመቻችቼ ያለ ማቅረቤ ይሆናል።

«ከሦስት አመት በኋላ ከእስር ቤት ወጥቼ ወደ ባለሥልጣኑ ልዩ ቢሮ ተወሰድኩ። ሚስቴን ከቀማኝ ባለሥልጣን ጋር በግንባር ፊት ለፊት ቁጭ ብለን የተያየነው ያን ዕለት ነው። ሚስቴንም እሱው ቢሮ ውስጥ ተቀምጣለች። ለጊዜው ተጠርታ ትምጣ......ወይም ከአጠገቡ የማትጠፋ ልዩ ፀሓፊው ሆና ትመደብለት እንጃ! አምሮባት የተወለወለ ብርጭቆ መስላለች። ለካስ ሚስቴን ምቾት ነፍጊያት በድያት ኖሬያለሁ!

«እንዴት ነው?.....ጥጋቡ አልበረደልህም?!» አለኝ ባለሥልጣኑ ወደ ኋላው ተለጥጦ ወንበሩን እያሽከረከረ።

«ጥጋቤን ስለማላውቀው የምመልሰው አልነበረኝም። ዝም አልኩ። ‹ከቅጣት ተምረህ ከሆነ ቀሪውን ዕድሜህን ፀባይህን አሳምረህ ሰርተህ መኖር ትችላለህ። ወደ ኋላ ሄደህ የምትጠይቀው አይኖርህም። ወደ ድሮ ቤትህ ለመመለስ እንዳትሞክር፤ እንፈራገጣለሁ ብትልና እሷን ለመተናኮል ብትሞክር በራስህ ላይ መፍረድህን እወቀው። ወደ ዘለአለማዊው ቤትህ ትወሰዳለህ። በቃ፤ ይኸው ነው፤ አሁን በነፃ ተለቅቀሀል› » አለኝ።

«ምን ማለቱ እንደሆን ስለገባኝ አንድ ጥያቄ ብቻ ለመጠየቅ አስፈቀድኩት። ልጆቼ በጣም ናፍቀውኝ ነበር። ሁሉንም ነገር ወስዶ ልጆቼን ለእኔ ቢተውልኝ ተመኘሁ።

«የልጆቼ ነገር እንዴት ነው?.....» አልኩት ስፈራ ስቸር።

«እነሱ ከእኔ ጋር ናቸው። አሳድጋቸዋለሁ» አለች ሚስቴ ተሽቀዳድማ ‹ዘጠኝ ወር ተሸክሜ የወለድኳቸው ልጆቼ መሆናቸውን አትርሳ!›

«ለመጀመሪያ ጊዜ በሙሉ ዓይኖቼ ቀና ብዬ ስመለከታት አውሬ መስላ ታየችኝ። እንደ ጭራቅም መሰለችኝ። ቆንጆ አውሬና ጭራቅ!......ባለሥልጣኑ ደግሞ አሣማ መስሎ ታየኝ። ገፁ ላይ ከፍተኛ ትዕቢትና ጥጋብ ይነበባል። ጀግንነቱ ቢኖር እዚያው ሁለቱም ላይ መትፋት ነበረብኝ። ነገር ግን ፀጥ ብዬ ወጥቼ መኖርን መረጥኩኝ። ቢያንስ ለመፅናኛዬ አረቄ በመለኪያ እንደማላጣ ተስፋ አደረግኹኝ። ቢቸግረኝ ወደ ኋላዬ ኄጄ እንዲህ ፈሪ አድርገው ያሳደጉኝን ወላጆቼን ረገምኩ።

«ልጆቼን አላገኛቸውም ማለት ነው?.....» አልኩ ከልመና ባልተለየ ድምፅ። «አታገኛቸውም!» አለችኝ ሚስቴ በንቀት።

«የልጆቼንም አባትነት ተነፍጌ እጅ ነስቼ ወጣሁ። ‹በሴት ባህሪይ ውስጥ መሠረታዊው ጥፋት የፍትህ ስሜት ማጣቷ ነው› ይላል ሾፖን አወር። ለልጆቼ የነበረኝን ፍቅር ስለምታውቅ ቢያንስ እነሱን ልትፈቅድልኝ ይገባ ነበር። አላደረገችውም።

«ከእስር ቤት ወጥቼ «ሀ» ብዬ አዲስ ኑሮ ነው የጀመርኩት። እንደ ሚስቴ ሁሉ መኪናዬም ተወስዳለች፤ ቢሮዬ ተወስዷል፤ መኖሪያ ቤቴም ተወስዷል። በነዚህ ዙሪያ ምንም አይነት ጥያቄ እንዳላቅርብ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኛል። በኋላ ስሰማ ለካስ ከዕስር ቤት የተፈታሁት በሚያውቁኝና በሚወዱኝ ሰዎች ምልጃና አስታዋሽነት ነበር። እነዚሁ ወዳጆቼ ረድተውኝ እንደ አዲስ አቋቋሙኝ፤ እንደገና ቢሮ ከፍቼ የብቸኝነት ኑሮ ጀመርኩ። ብዙ ሰዎች እየመጡ ምንም አይነት ምሬት እንዳላሰማና ዕድለኛ እንደሆንኩ ነገሩኝ። «እንዴት?» አልኳቸው። ሚስቶቻቸውን በባለሥልጣን የተነጠቁ የሁለት ወንዶች ታሪክ አጫወቱኝ። አንደኛው ተገድሏል፤ ሌላኛው ወደ በረሃ ተልኳል።

«ይኼውልህ እንዲህ ፀጥ ብዬ ለመኖር ብርጭቆና መለኪያ ውስጥ መደበቅ ነበረብኝ። ከዚህ በተጨማሪ ሴት የምትባል ፍጡርን የጠላሁበት ትጥቄ እንዳይላላ በየጊዜው አዳዲስ ጥቅሶች መታጠቅ አለብኝ» ብሎ በረዢሙ ተነፈሰና ብርጭቆውን አነሳ።

መደምደሚያ በሙሉ ስሜት ተመስጦ ሲያዳምጠው ከቆየ በኋላ የተንዠረገገ ፂሙን ትክ ብሎ እንደ አዲስ ሰው ይመለከተው ጀመር። እውነትም የዘለዓለም ሀዘነተኛ......ተንፍሶ ከወጣለት በኋላም አከታትሎ መጠጣቱን ቀጠለ። መደምደሚያ አዘነለት። የተሰበረ ልቡ በቀላሉ የሚጠገን አይደለም።

«አሁንስ......በሀገሪቱ ውስጥ ለውጥ ከተካሄደና ወታደራዊ ደርግ ከወደቀ በኋላ.....ምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ?» ብሎ ጠየቀው።

«ባለሥልጣኑ በተራው እስር ቤት ገብቷል፡፡ እሷም ስንቅ አቀባዩ ሆናለች፡፡»

«ልትፋረዳቸው አልሞከርም?»

«በጭራሽ! ወሬያቸውንም የሰማሁት ከሰው ነው እንጂ እኔ መከታተልም አልፈልግም፡፡ ፍርድ የእግዚአብሔር ነው፡፡ በህይወት ቆሜ ይህንን ማየቴ ይበቃኛል፡፡ በተረፈ የተሰባበረን ሸክላ መልሶ መገጣጠም አይቻልም፡፡»

«ቢያንስ መኪናህን ንብረትህን ለማስመለስ.....ማለቴ ነው»

«ንብረት ምን ዋጋ አለው?! ከንብረቶች ሁሉ በላይ ውድ የሆነው ትዳሬና ኑሮዬ ፈርሷል፤ ህይወቴ ተናግቷል፡፡ የንብረትን ጥያቄ ፈጽሞ አላስበውም፡፡»

«የልጆችህንስ ነገር.......አሁን መጠየቅ አልቻልክም?»

«ወደ ውጭ ሀገር ልከዋቸዋል አሉ፡፡ ለሁሉም ነገር ደንታ እያጣሁ አልተከታተልኳቸውም፡፡

«ምነው?.....ሌላው ቢቀር የምትወዳቸውን ልጆችህን.....»

«እኔ እንጃ!.....እነሱም ሴቶች ስለሆኑ ጠልቻቸዋለሁ መሰለኝ፡፡»

መደምደሚያ ከዚህ በላይ ሊጠይቀው አልቻለም፡፡ ሀዘኑ ጠልቆ ተሰማው፡፡ ይህን ዓይነት ለራሱም ለሀገርም የሚጠቅም ሰው በህይወት እንቅፋት ተመትቶ አረቄ ውስጥ ወድቆ መቅረቱ አሳዘነው፡፡ በአማካሪነት ሙያው የሙያ ግዴታውን በትክክል መወጣቱም አጠራጠረው፡፡ አዕምሮው በጥላታ የተመረዘና የልብ ስብራት የደረሰበት ሰው እንዴት ብሎ ሚዛናዊ ምክርና ፍርድ ሊሰጥ ይችላል?!.....ቀላል የህይወት እንቅፋት እንደ ምንም ይታለፋል፡፡ ከባድ እንቅፋት ግን ሰባብሮ ይጥላል፡፡ በዕድሜ ልክ ማገገም ያስቸግራል......

መጠጣቸውን ጨርሰው ወደ ዩኒቨርሲቲ ማደሪያ በኢት ሲሸኘው ሁሉ መደምደሚያ ይህንኑ እያሰበ ነበር፡፡ የሰማይነህ ጉዳይ እንዳይረሳበት ሲለያዩ ካስታወሰው በኋላ የባህሩ ፂም አዲስ ስዕል አዕምሮው ውስጥ ተቀርጾ ቆየ፡፡

የህይወት ከባድ እንቅፋት.....የተሰበረ ልብ......የተንዠረገገ ፂም.....የዘለዓለም ሀዘንተኛ.....የአረቄ ጓደኛ.....አይ ይህች ዓለም!.....

# ክፍል አስራ ሦስት

ህይወት በበረንዳ በኩል ወጥታ የጠዋት ፀሐይ እየሞቀች ከውሻ ቡችሎች ጋር ትጫወታለች፡፡ ብቸኝነቷን የሚያረሳሷት አጫዋቾች ጓደኞቿ የቤት እንስሶች ሆነዋል፡፡ ቤት ውስጥ ስትሆን፣ የድሙቶች ግቢ ውስጥ ስትዘዋወር ደግሞ ከውሾች ጋር ካልሆነ በስተቀር ሀሳቧን የሚካፈልላትም ሆነ የሚያጫውታት ሰው የለም፡፡ መደምደሚያ ከሰማይነህ ተጣልቶ እንደሄደ አልተመለሰም፡፡ የሰማይነህ እናት አይጥሟትም፤ አንድ ቀን ደህና ነገር ቢያወሩና በሰላም ቢያጫውቷት በሁለተኛው ቀን አይደግሙትም፡፡ ገና ከወዲሁ የሚታያት ክፉ ምላሳቸው ስለሆነ ከእግዜር ሰላምታ ውጭ ባያነጋግሯት ትመርጣለች፡፡ ከጎርፉ ጋር ከፀቡ በኋላ ተኮራርፈዋል፤ እሱ እየረሳው አንዳንዴ ሊያነጋግራት ቢሞክርም እሷ ዘግታዋለች፡፡ ሰማይነህ እንደ ባልነቱ በፍቅር ከሚያነጋግራት ሴኮንከዶች ይልቅ በቅናት የሚጨቀጭቃትና የሚያሰቃያት ሰዓቶች ይበልጣሉ፡፡ ስለዚህ ከሁሉም በላይ የቤት እንስሶችን ለጓደኝነት መርጣለች፡፡

ጎርፉ የፀቡ ዕለት ማታ ወደ ቤት ሳይመለስ ስላደረ አንደኛውን መቅረቱ መስሏት ህይወት ተገላገልኩ ብላ ተደስታ ነበር። ሆኖም በማግስቱ ጥዋት አማላጅ ይዞ መጥቶ ሰማይነህ እግር ላይ ወድቆ ወደ ቤቱ ተመልሷል። ጥገኝነት ስለተጠናወተው ታክሲውን እየሰራ አንድ ራሱን አሸንፎ መኖር አይችልም። ሰማይነህ በአንድ በኩል ስንፍናውን ቢጠላበትም በሌላ በኩል ግን ድክመቱን መሣሪያ አድርጎ እንደ ባሪያው ስለሚጠቀምበት ይፈልገዋል። ስለዚህ ጥርጣሬው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ከህይወት ጋር ምንም ዓይነት መቀራረብና ግንኙነት እንዳያደርግ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ ወደ ሰማይነህ ቤት ተመልሷል። የጠባቂነት ማዕረጉን በመፈፉ ህይወት ደስ ተሰኝታ አሁን ንቀቷንና ጥላቻዋን በግልፅ ታሳየዋለች፤ እሱ ግን ልቡ አልተኛላትም። ለሌላ ጉዳይ ወደ ቤት የመጣ እየመሰለ በየአጋጣሚው በርቀት ይከታተላታል። አንድ ጥፋት አግኝቶባት ወይንም አሲሮባት ከሰማይነህ ጋር መታረቂያ ሊያደርጋት ይፈልጋል።

ህይወት የውሻ ቡችሎቹን ልፊያና ጨዋታ እየተመለከተች በሀሳብ ትንሽ ዋዠቀች። ቡችሎቹ የተወለዱት ሰሞኑን ነበር። በአጭር ቀናት ውስጥ ለልፊያ ደርሰው እናታቸውን ሲተሻሹና ሲንደባለሉ ደስ ይላሉ። የውሾቹ ዓለም ይህችው ግቢ ናት። ወደ ውጭ መውጣት አይፈቀድላቸውም። ህይወትም ራሷን ከውሾቹ ጋር ማመሳሰል ጀመረች። ‹እኔም እንደነሱው የውጭውን ዓለም ተነፍጌ ከዚህ ግቢ እንዳልወጣ የምጠበቅ እስረኛ ነኝ።.....እንዲያውም ከእኔ ይልቅ ውሾቹ የመላፋት የመጫወትና የመጮህ መብት አላቸው። እኔ ግን ይችን ታህል እንኳ መብት የለኝም› አለች በልቧ።

ከውሾቹ ጋር በመጫወት ላይ እያለች ጎርፉ ወደ ታክሲ ስራው ሊሄድ በአጠገቧ አለፈ። ሰማይነህ ከሄደ ቆይቷል። ጎርፉ ወደ ስራ መሄድ ስለማይወድ አልጋው ውስጥ ሲተሻሽ ሦስት ሰዓት አልፏል። ህይወት ጎርፉን ስታየው በአሽሙር ልትለከፈው ፈልገች «ና ኩቲ.....ቡች....ቡች.....ቡች.....» አለች ወደ ውሾቹ እያየች ጮክ ብላ። ሰማይነህ ፊት እንደ ነሳው ስለምታውቅ ጎርፉ ምንም ሊያደርግ አይችልም ብላ ተዝናንታለች። እንዲህ በአሽሙር እየለከፈች አንዳንዴ ንዴቷን ትወጣለች።

ጎርፉ አሽሙሩ ገብቶት ቆም ብሎ ከተመለከታት በኋላ «....ማንን ነው?» አላት በቁጣ።

«አንተ ውሻ ነህ እንዴ?!» አለችውና በፌዝ ዓይነት ከትከት ብላ ሳቀች።

«ብታርፊ ይሻልሻል አንቺ ልጅ.....»

«ምንድነው የምትለው?! ውሻ ከሆንክ ንገረኝ። እኔ የጠራሁት ውሻውን ነው።»

«ቆይ ግድየለም.....» ብሎ እየዛተና እየተነፋነፈ ታክሲውን አስነስቶ ወጥቶ ሄደ።

ስለተናደደላት ደስ ብሎአት እየሳቀች ከውሾቹ ጋር መጫወቷን ቀጠለች። ትንሽ ቆይተው ደግሞ አሮጊቷ እየተጎተቱ መጡ። ጠባቂ እንደመሆናቸው መጠን መኝታ ቤቷ ሲያጧት ወይንም ድምጿ ሲጠፋባቸው ሊፈልጓት መምጣታቸው ገባት።

«እንደምን አደርሽ» አሏት።

«ደህና፤ እግዚአብሔር ይመስገን።»

አይኖቻቸውን የውሻ ቡችሎቹ ላይ ሲተክሉ አንድ ነገር ጣል ሊያደርጉባት እንዳሰቡ ጠረጠረች።

«......ወላድ ውሻ ደስ ይለኛል። ቡችሎቹ እንዴት ያማምራሉ! ለጎረቤት ሰጥታቸው ነው እንጂ፣ ካቻምናም እንዲሁ ብዙ ቡችሎች ወልዳ ነበር። ፍሬ መስጠትን......ዘር መተካትን የመሰለ ነገር የለም፣ መሐን ውሻ አልወድም እኔ» አሏት። ህይወት በልቧ ‹ነገረኛ ምላሳቸውን ሊዘረጉብኝ ተነሱ እንግዲህ!› ብላ ዝም።

«ሰውም እንዲሁ ነው። ዘሩን ካልተካ ምን ዋጋ አለው? በተለይ ልጅ የሚያምርባት እናትነቷ ነው። እንዲሁ ሌላ ሆኖ መንጦልጦል ምንም ትርጉም የለው።»

ህይወት ጥላቻዋን በሚገልፅ አስተያየት ተመለከተቻቸው። እንደገና ጭራቅ መስለው ታዩዋት። ከአጠገባቸው መራቅ ስለፈለገች ጥላቸው ወደ ቤት ገባች።

ለጊዜው ብትሸሽም አንድ ግቢ ውስጥ በመሆናቸው መልሶ የሚያገናኛቸው ነገር አይጠፋም። ወደ አራት ሰዓት አካባቢ የውጭው በር የመጥሪያ ደወል ስላቃጨለ የመጣውን ሰው ለማየት አንገቷን በመስኮት በኩል ብቅ አደረገች። መደምደሚያ ነው። ለእናቱ እዚያው በሩ አካባቢ ስለ ነበሩ ቀድመው ተቀበሉት። ከእሳቸው ጋር ተሳስሞ ሁለት ቃል እንኳ ሳይለዋወጥ፣ ህይወት እየሮጠች መጥታ አንገቱ ላይ ተጠመጠመችበት። ስሜቷን መግታት አልቻለችም በፍርሃትና በይሉኝታ ተሸማቅቃ ወደ ኋላ ማፈግፈግም አልፈለገችም። አራት ቀን ሳይሆን አራት አመት ሳይተያዩ የከረሙ ነው የመሰላት። ሳታስበው በዓይኖቿ ሙሉ እንባ ግጥም አለ። ሁኔታው እናትየውን አናደዳቸው። «……ቀስ!……ኧረ ቀስ……የምን መንቀዥቀዥ ነው እሱ!» አሏት ፊታቸውን አጨማድደው።

ይህወት አሁንም ስምታ እንዳላሰማች ለመሆን ሞከረች። ይልቁንም አትኩሮቷን ከመደምደሚያ ላይ ሳትነቅል ይበልጥ አናደደቻቸው።

«……በጣም ጨካኝ ነህ ግን!……ሌላው ቢቀር ስልክ እንኳን ደውለህ ጤንነትህን ብትነግረን ምን አለበት?! እኔ በጣም ነበር የተጨነኩት። ደግሞም ግጭቱ በኔ ምክንያት መሆኑ በጣም ነው ያሳዘነኝ» አለችው።

«….እኔ እንጃ ሁሉም ነገር አስጠላኝ። ለሰማይነህ የነበረኝ የወንድምነት ግምት እጅግ በጣም ዝቅ ስላለ ግቢው ሆነ ስልኩ አስጠላኝ። ሁለት ጊዜ ያህል ልደውልላችሁ ስልኩን ካነሳሁት በኋላ እየቀፈፈኝ» አለ መደምደሚያ የነበረበትን ስሜት እንዴት እንደሚገልፅላቸው ግራ እየገባው በእጁም ጭምር እያስረዳቸው።

«እንዲህ አድርገህ አታምርር ልጄ። ወንድምህ ብስጩ ሆኖ ነው እንጂ ልቡ ክፉት የለውም። ደግሞም ታናሹ እንደ መሆንህ መጠን አንዳንዴ መሸነፍ አለብህ» አሉት እናትየው።

«ተይኝ እባክሽ እማማ። የሱ ነገር በቅቶኛል። አሁንም የመጣሁት ልብሶቼንና መጻህፍቶቼን ለመውሰድ ነው እንጂ ወደዚህ ግቢ አልመለስም……» አላቸው።

«ቆይ እስቲ ለማንኛውም ቤት ውስጥ ገብተን እንነጋገር። አትቸኩል» ብለውት ወደ ሳሎን ሲገቡ ህይወትን ደግሞ «አንቺም እንግዲህ በቃሽ፤ ወደ መኝታ ክፍልሽ ግቢ። ሰላምታ ከተለዋወጣችሁ ይበቃል። በፊትም ችግር የፈጠረው አብራችሁ መታየታችሁ መሆኑን አትርሺ። የሰማይነህ አመጣጥ አይታወቅም። በአሳቻ ሰአት ከተፍ ሊል ይችላል» አሏት አለሳልሰው። መደምደሚያን ላለማስቀየም እሷን አለሳልሰው ማነጋገራቸው ህይወትን አስደነቃት።

«እሺ፤ ሲወጣ ለአንዳፍታ እንዲያነጋግረኝ ብቻ ይፍቀዱልኝ። ሁላችሁም ያሻችሁን ልትሉ ትችላላችሁ። መደምደሚያ ግን ለእኔ ንፁህ ወንድሜ ነው» ብላቸው ገባች።

«ግድ የለም፤ ስወጣ አነጋግርሻለሁ» አላት መደምደሚያ ስሜቷ ገብቶት፤ እናቱም ጨክነው እንደማይከለክሉት በመተማመን።

«ለማን ጄቴ ብለህ ነው የወንድምህን ቤትና ሀብት ጥለህ የምትሄደው?! ጎርፉ እንኳን በማግስቱ ሽማግሌ ልኮ ታርቆ ተመልሷል» አሉት እናትየው ብቻቸውን ከሆኑ በኋላ «ከአንተም ጋር በሽማግሌ እናግባባችኋለን። ነገር ማክረር አያስፈልግም»።

«ጎርፉ ከቤት ውስጥ ነበር እንዴ?» አላቸው መደምደሚያ ግራ ገብቶት።

«ታዲያስ! ያን እለቱኑ ሰማይነህ ከአንተ እንደተጣላና እንደሄድክ ዘወር ብሎ ደግሞ ጎርፉን ተጣልቶት አባረረው እኮ! ደግነቱ ጎርፉ ቂም ስለማያውቅ በማግስቱ እግሩ ላይ ወድቆ ተመስሎ መጣ።»

«እሱም የእጁን አግኝቷል! እኛን ብቻ በበጣብጦ ያለ መቅረቱ ጥሩ ነው» አለ በንዴት ከንፈሩን እየነከሰ።

«የምታበጣብጣችሁማ ይች ልጅ ነች። ሴት የጫረችው እሳት መጥፎ ነው!......» ብለው ህይወትን ለማብጠልጠል መንገድ ሲጠራርጉ መደምደሚያ አቋረጣቸው።

«ተይ እባክሽ፤ እንደሱ አትበይ እማማ። አንቺ ከዚህ እድሜሽ በኋላ ለእግዚአብሔር ያደርሽ፤ ለእውነት የቆምሽ ሰው መሆን አለብሽ። የሌላውን ወሬ እየሰማሽ በከንቱ ጥርጣሬና ጥላቻ መመረዝ የለብሽም። ይች ልጅ ንጹህና ጥሩ ሰው ናት። ነገር ግን ማንም ሊረዳት አልቻለም። እኔንም ሁላችሁም የጠመዳችሁኝ ንጽህናዋን ተረድቼ ስለቀረብኳት ነው። እኛን የሚያበጣብጠን ይሄ ከብት ልጅሽ ሲሆን የሚበጠብጠን ደግሞ የሰማይነህ የራሱ ቅናትና እብደት ነው.....ግፍ የምታውቁ ከሆነ በዚህች ልጅ ላይ የምትሰሩት ነገር ሁሉ ግፍ ነው»

«እኛ ምን አደረግናት?!.....አዱኛው ሞልቶ የተረፈ ቤት አላስቀምጥ ብሏት ውጭ ውጭውን የሚያሳያት እሷን ነው።.....ይልቅ አሁን ይሄን እንተወውና የአንተኑ ጉዳይ እንነጋገር።»

«እኔማ ጨርሻለሁ። ከሰማይነህ ጋር ከእንግዲህ ወዲያ በምንም መንገድ አብሬ መኖር አልችልም.....»

«ቆይ እንጂ መደምደሚያዬ። እኔን እናታችሁን ሀዘን ላይ አትጣሉኝ።»

«አንቺ የምትጨነቂበት ምክንያት የለም። ሁላችንም የየራሳችንን ኑሮ እንኖራለን።»

«እንደሱ አይደለማ።.....ቢሆንም ተስማምታችሁ አብራችሁ ብትኖሩ፤ ካልሆነም ደግሞ ለየብቻችሁ ብትኖሩም ተፋቅቅራችሁ እየተጠያየቃችሁ እና እየተረዳዳችሁ መሆን አለበት።»

«አታስቢ......በርቀት እንጠያየቃለን።»

«እኮ.......ካለበለዚያ ቤቱ የማንም የባዕድ መፈንጫ ሆኖ ይቀራል። ሰማይነህ በውጭም ቢሆን ማንኛውንም ነገር ሊረዳህ ፈቃደኛ መሆኑን ነግሮኛል። አንተም የወንድምነት ፍቅርህን ሳትቀንስ ጠይቀው፤ ያለፈውን ይቅር ተባባሉ።

«አትጨነቂ አልኩሽ እኮ እማማ። ሰማይነህ ያሳደገኝና ያስተማረኝ ታላቅ ወንድሜ ነው። ውለታውን አልረሳም።

ከዚህ በኋላ ግን እሱን ጥገኛ ሆኜ መኖር አልፈግልም። ርዳታውንም አልፈልግም። ራሴን ችዬ መኖር አለብኝ። እየመጣሁ እጠይቃችኋለሁ» ብሎ ተነሳ።

ከእናቱ ጋር ብዙ መነጋገሩና ያዘነ ፊታቸውን ማየቱ ውሳኔውን እንዳያስቀይረው ስለፈራ፣ ልቡን አጠንክሮ እናትየውን እያበረታታና ነገሩርን አቅልሎ እየነገራቸው ወደ ክፍሉ ገብቶ ከልብሶቹና ከመጽሃፍቶቹ ውስጥ ለጊዜው የሚፈልጋቸውን መርጦ በሻንጣ አሰናዳ።

እናትየው ሆድ እየበሳቸው ወደ ክፍላቸው ሄደው ለቤት ውስጥ መጠባበቂያ ያስቀመጡትን አምስት መቶ ብር አውጥተው ሰጡት።

«ምንድነው እሱ?....» አላቸው።

«ያዘው። ብቻውን የሚሂድ ሰው የሚገጥመው አይታወቅም። ለማንኛውም ደግሞ ስሞኑን መጥተህ የምታርፍበትን ቦታ እንድታሳየኝ» አሉት።

በተዘዋዋሪይ ገንዘቡ የሰማይነህ መሆኑን ስለሚያውቅ ሊቀበላቸው አልፈለገም ነበር። ሆኖም እናቱ አምርረው እንዲያዝኑ በመፍራት አመስግኖ ከተቀበላቸው በኋላ «ለወደፊቱ ግን ፈጽሞ እንዳትጨነቂ። ራሴን አሸንፌ የምኖርበት በቂ ስራ አግኝቻለሁ» አላቸው ውሸቱን።

ምንም ቢላቸው የአሮጊቷ ልብ ማዘኑና ሆዳቸው መንቦጫቦጩ አልቀረም። ለብዙ ዓመታት በየሃዘን ቤቱ እንባ ያጎረፉ አይኖቻቸው አሁንም በስተርጅና ተጨንቀው የደም ጠብታ ያህል አነቡ።

ሻንጣዬ አሽክሚና አስወጭልኝ እማማ። እኔ ህይወትን ተሰናብቻት እመጣለሁ።»

አሮጊቷ የመጨረሻ ልጃቸውን ፈቃድ ለመፈፀም ዘበኛውን ጠርተው ሻንጣውን አሸክመው የውጪው በር ድረስ አብረውት ወጡ። መደምደሚያ ህይወትን ለብቻዋ ሊሰናበታት ፈልጎ ወደ ኋላ ቀረ። እሷም ተዘጋጅታ እየጠበቀችው ነበር።

«በቃ ጨክነህ መሄድህ ነው?.....» አለችው በኃዘን ቅላጼ።

«አዎ ህይወት። ራሴን ችዬ መኖር እንደምችል ላሳያቸው እፈልጋለሁ።»

«በጣም ያሳዝና። ይህ ሁሉ በእኔ ምክንያት ነው»

«ኖ ኖ! እንዲህ አይነት ነገር ሊሰማሽ አይገባም። አንቺ ምንም ያደረግሽ ነገር የለም። ......ይልቁንም አንቺ ምክንያት ሆነሽ አነቃሽኝ። አንቺ መቼ በጥገኝነት እኖራለሁ?!»

«አሁን የት ለመኖር ነው ያሰብከው?»

«ለጊዜው ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከጓደኞቼ ጋር ነኝ። በቅርቡ ግን ስራ ይገኙ ለብቻዬ መኖር እጀምራለሁ። ትምህርቴንም እየሰራሁ እማራለሁ።»

መደምደሚያ ስራ ስለማግኘቱ እርግጠኛ አይደለም። በእሱ ደረጃም ሆነ ከእሱ በላይ የሚገኙ ምሁራን ስራ አጥተው ሲንከራተቱ ተመልክቷል። ሆኖም ግን የእናቱንና የህይወትን ልብ አረጋግቶ መሄድ አለበት። በሌላ በኩል ደግሞ በምንም መንገድ ቢሆን ራሱን የመቻል እልህ ውስጥ ገብቷል።

«ታዲያ እንዴት ነው የማገኝህ?.....በአንተ አድራሻ የሚላክልኝ ደብዳቤ መኖሩን አትርሳ» አለችው ህይወት የትካዜ ድባብ ባይለቃትም፣ ፈገግ ለማለት እየሞከረች።

«አይዞሽ፤ እኔ የመጣሁ እጠይቃችኋለሁ። የደብዳቤ ጉዳይሽንም እንደጉዳዬ አድርጌ እከታተልልሻለሁ። አስቸኳይ ነገር ካለ ስልክ እደውልልሻለሁ» አላት።

«እስረኛ መሆኔን አትዘንጋ። ስትደውልልኝ በዘዴ ነው።»

«ግድ የለሽም፤ ሁሉንም ነገር ስለማውቅ እንደሚሆን እንደሚሆን አደርገዋለሁ»

«ቀናሁብህ መደምደሚያ......»

«እንዴት?......ምን ያስቀናል?»

«ነፃነትህን አውጀህ መውጣህ ነዋ። ከነፃነት በላይ ምንም ነገር የለም።.....እኔ ግን በእስረኛነቴ ላይ ከአጠገቤ አንተን ማጣቴ ብሶቴን የሚያሳስበው ይመስለኛል። ገና አሁን ሆዴ ባር ባር እያለው ነው።»

«አይዞሽ፤ አንቺም ነፃነትሽን ትጎናፀፊያለሽ። ተስፋ አትቁረጪ።»

«ባትልስ በትዕግሥት የሚመጣውን ከመጠበቅ ሌላ ምን ምርጫ አለኝ?!»......አለችውና ከጡት መያዣዋ ውስጥ በለስላሳ ወረቀት የተጠቀለለ ነገር አውጥታ ሰጠችው።

«ምንድነው እሱ?» አሁንም እንደ ቅድሙ።

«ስንቅ ነዋ......ዝም በልና ያዘው»

መደምደሚያ የእቃውን ምንነት ስለጠረጠረ በአስቸኳይ የተጠቀለለበትን ወረቀት ከፈተው። ትልቅ ወርቅ ነው። ለጥሎሽ ከተላከት ውስጥ አንዱ መሆኑን ገና ሲያየው አወቀ።

«ምንድነው የምትሰሪው ህይወት?!.....ጤነኛ ነሽ ወይስ አብደሻል?!»

«እኔ ሙሉ ጤነኛ ነኝ። በደንብ አስቤበት ያደረኩት ነገር ነው። እጄ ላይ ገንዘብ ስለሌለ ላደርግልህ የምችለው ይህንን ነው።»

«እንዴ!......ሀገር ለቅቄ ወደ ስደት የምሄድ አደረጋችሁኝ እንዴ!? እናቴም ገንዘብ ሰጠችኝ። አንቺ ደግሞ የከበደ ነገር ነው የምታደርጊ......እኔ ይሄንንም ስጦታ በምንም መንገድ አልቀበልም» ብሎ ሊመልስላት እጇን ሲዘረጋ ሸሸችው።

«ትጣላኛለህ መደምደሚያ።.....ስጦታዬን እንቢ ማለት አትችልም፤ ደግሞም ብዙ ወርቆች እንዳሉኝ ታውቃለህ፣ እኔ እስረኛ ስለሆንኩኝ አላጌጥባቸውም። ባይሆን አንተ ሸጠህ ተጠቀምበት። ይሄ ላንተ ማድረግ ከሚገባኝ በጣም ትንሹ ነገር ነው። ሰግነት ሳያሸንፍህ ለእኔ ለባዕዷ የቆምክልኝ ወንድሜ ነህ»

መደምደሚያ ራሱ እንባ ተናነቀው። ፍቃዷን በመፈፀም ደስ ሊያሰኛት ሲያስብ ሌላ ሀሳብ ደግሞ አእምሮው ውስጥ ብልጭ አለበት።

«ምናልባት ሰማይነህ ወርቅሽን ቢጠይቅሽና ጎድሎ ቢያገኘው ሌላ ብጥብጥ ይፈጠራል.....»

«አትጨነቅ፤ እሱንም አስቀድሜ አስቤበታለሁ።»

«.....ምን ታደርጊያለሽ?»

«አይጠይቀኝም።......ከጠየቀኝም እዚህ ቤት ሌላ ሰው ስለማይገባ ጎርፉ እንደ ሰረቀኝ አድርጌ እነግረዋለሁ።»

«አያምንሽም» አላት፤ የጎርፉ መወንጀል ግን ደስ እያሰኘው።

«በሚያሳምን ሁኔታ አቀርብለታለሁ። ፊልም መስራት እንደምችል ሰሞኑን እዚህ ቤት ውስጥ ሞክሬ አረጋግጫለሁ» አለችና በፀቡ ዕለት በጎርፍነህ ላይ ውሸት ፈጥራ እንዴት ከሰማይነህ ጋር እንዳጣላችው ነገረችው።

መደምደሚያ ተገርሞ እየሳቀ «ለካስ ጎርፍነህን ጉድ አድርገሽዋል!.....በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም። የሚያሳዝነው ግን አንቺን መሳይ ንጹህ ሀቀኛ ሴት ውሸት እንድትማሪ ማድረጋቸው ነው» አላት።

«ወድጄ አይደለም፤ ራሴን ለማዳን ያደረኩት ሙከራ ነው። ሰማይነህ በዚህ ዓይነት መንገድ የንዴት አቅጣቻውን ባላስቀይረው ኖሮ ዘሎ እንደገባ አንቆ ይገድለኝ ነበር።.....ርግጥ የጎርፉን ውሸት በሌላ ውሸት የመቀበሉ ሃሳብ የመጣልኝ ድንገት ነው።»

«እሱንስ ከዚያም የበለጠ ዋሽተሽ ብትበቀይልኝን ደስ ይለኛል።.....እስከ በቀደም ዕለት ድረስ ከብት አድርጌ እቆጥረው ነበር። አሁን ግን አውሬ ሆኖ ነው የሚታየኝ» ከማለቱ ንዴት ውስጥ ስለገባ ቶሎ ጨዋታውን መልሶ «እንግዲህ ስለ ስጦታሽ አመሰግናለሁ። እግዚአብሄር ብድርሽን ይክፈልሽ» ብሎአት ወርቁን ወደ ኪሱ ጨመረ።

እናቱ የነገሩትን ሚስጥር ሊነግራት ፈልጎ ትንሽ ሲያመነታ ቆየ። ብታውቂው ያነቃታል፤ እንድትጠነቀቅና እንድትዘጋጅ ያደርጋታል እንጂ ምንም አይጎዳትም አለና ነገራት።

«እንግዲህ አንቺ እንዳትዘናጊ።......እናቴን ሰማይነህ አንቺን ማጣት ስለማይፈልጉ በውድም ይሁን በግድ እስረኛ አድርገው ሊያኖሩሽ ያስባሉ። በፍፁም በእጃቸው እንድትወጪ አይፈልጉም። ይህንን አውቀሽ አስቢበት» አላት።

«ሳይወዱኝና ሳልወዳቸው በግድ ሊያኖሩኝ የሚፈልጉበት ምክንያት አይገባኝም» አለችው፤ እሷም እየገረማት።

«ሰማይነህ አንቺን ካጣ ሀብቱም እንደሚጠፋ ከጠንቋይ የተቀበሉት እምነት አላቸው። ስለዚህ የዘለዓለም ባሪያ ሊያደርጉሽ ያስባሉ።

ህይወት ነገሩ አስደነገጣ። የተዘጋጀላት የዕድሜ ልክ መታሰሪያ ገመድ ርዝመቱ በሃሣቧ ታያት። ከዚህ ወጥመድ ውስጥ ቶሎ ፈትለክ ብላ ማምለጥ እንዳለባት አሰበችበት። ሰማይነህም ሆነ እናቱ እንዲህ ባለው ተራ ነገር ተጠምደው የራሳቸውንም ሆነ የሌላውን ህይወት ለማበላሸት መሞከራቸው ደጋግሞ አስገረማት።

«ግድ የለህም፤ ፈለግህን ተከትየ እንደምንም እራሴን ነፃ አወጣለሁ» በማለት ቃል ገባችለት።

ያሮጊቷ ድምፅ ከርቀት እየተሰማቸው ነበር። መደምደሚያም ስለቆየባቸው ተመልሰው መጥተው «እንዴት ነው?......ስንብቱ አይበቃችሁም እንዴ?.....ዘበኛው እቃውን ተሸክሞ ቆሞ እየጠበቀህ እኮ ነው» አሉት።

«እሺ.....ጨርሰናል» ብሎ ህይወትን ተሰናብቷት ሲወጣ፣ እሷም እስከበረንዳው ድረስ ተከትላ ሸኘችው።

«አሁን እንዴት እንዴት ነው የምትሄደው?» አሉት እናትየው የውጪውን በር ሲያስወጡት።

«ምንም ችግር የለም። ታክሲ ኮንትራት እይዛለሁ።»

«እንግዲህ አደራህን መደምደሚያዬ ቶሎ ቶሎ ጠይቀኝ። እኔ ላንተ ያለኝን ልብ ታውቃለህ.....» ከማለታቸው አሁንም ዓይኖቻቸው ላይ እንባ ግጥም አለ።

ስሜታቸው እንዳይጋባበትና በር ላይ ቆመው እንዳይላቀሱ መደምደሚያ ቶሎ ብሎ ተሰናብቷቸው ሄደ። ብዙ ዓመታት በኖረበት መንደር ሻንጣውን አሸክሞ ሲያልፍ እሱም በተመሳሳይ የመባባት ስሜት ውስጥ መናጡ አልቀረም። እንባው ጠብ እንዳይል ጥርሱን ነክሶ እየታአገለ መንደሩን ወጣ።

# ክፍል አሥራ አራት

አይሮፕላኑ መሬት አርፎ መንገደኞቹ የእጅ ሻንጣቸውን እየያዙ መውረድ ሲጀምሩ የህይወት ስዩም ልብ ከበሮ መደለቁን ጀመረ። የደስታ ድንጋጤ ሲቃ መላ ሰውነወቷን እያናወጠው እሷም ካይሮፕላኑ ውስጥ ወጥጣ ፍሎሪዳ መሬት ላይ ቆመች።

ፈረንጆቹ ይተራመሳሉ። ተነፋፍቀው የተገናኙ ዘመድና ጓደኛሞች ተቃቅፈው ይሳሳማሉ። አይሮፕላን ማረፊያው በነጮችና በጥቁሮች ተጨናንቋል። የህይወት ዓይኖች ከዚህ ሁሉ ህዝብ መሃል ሄኖክ አንበሴን ፈልገው ለማግኘት ጓጉተዋል። ጥቁር በተመለከተች ቁጥር አይኖቿን ተከትሎ ልቧ ይደነግጣል። አጠገቡ መድረሷን ብታውቅም እስከታገኘው ድረስ ማመን አልቻለችም። ይህንን ወጣት ፍቅረኛዋን ለማግኘት ውቅያኖስ አቋርጣ፣ የብሱን ተሻግራ፣ ህዋውን ሰንጥቃ የመጣችባቸው ብዙ ሰዓታት የአሁኑን ደቂቃ ያህል አልራቁባትም። ሄኖክም ሊቀበላት ሲመጣ የሷን ያህል ናፍቆትና ጉጉት ይዞ እንደሚሆን እርግጠኛ ነች። ያች በአካል የመገናኛ ሰኮንድ ግን ረዥም ሆነችባቸው።

እሷ ተንጠራርታ ከወደሩቅ ስትፈልገው ሄኖክ ተሹለክልኮ አጠገቧ ደርሷል።

«ሄኒ.....» ባላ አንገቱ ላይ ተጠመጠመችበት።

«ህይወትዬ.....»

ሁለቱም ተቃቅፈው እየተሳሳሙ ተላቀሱ። የናፍቆትና የደስታ ሲቃ እየተናነቃቸው ፍቅራቸውን በቃላት መግለፅ ስላቃታቸው በዕንባ ገለፁ። ለአንድ አፍታ ያህል ተላቀው ዓይን ለዓይን ይተያዩና ተመልሰው ተቃቅፈው ይላቀሳሉ። መንገደኞችና አስተናጋጆች በአድናቆት ትክ ብለው እስኪያይዋቸው ድረስ ተቃቅፈው በመላቀስ ናፍቆታቸውን ተወጡ።

«ሄኒዬ.....ይህቺን ደቂቃ እንዴት በጉጉት ስጠብቃት እንደቆየሁ ልነግርህ አልችልም።»

«ለኔም መገናኛችን በጣም ርቆብኝ ነበር፣ ህይወትዬ»

«መቼም ከባርነት ቀንበር ነፃ እንዳወጣኸኝ ነው የምቆጥረው፤ እፎይ......አሁን ገና የነፃነት አየር ተነፈስኩ......»

«እኔም በብቸኝነት ተሰቃይቼ ነበር። አሁን አንቺን ሳገኝ ሙቀት ተሰማኝ፤ የብቸኝነት ብርድ ለቀቀኝ።»

«የፍሎሪዳን መሬት ለመርገጥ በመብቃቴ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ ያንተ ደብዳቤ ከደረሰኝ ጀምሮ በድን ሰውነቴን አዲስ አበባ ይሁን እንጂ ልቤ ፍሎሪዳ ነበር።......ባይሳካልኝ ኖሮ ምን እንደማደርቅ አላውቅም። ምናልባት ራሴን አጠፋ ይሆናል።»

«ምን በወጣሽ የኔ ቆንጆ.....አንቺ ሞተሽ እኔ ምን ህይወት ሊኖረኝ......አሁንም በዚህ ሁሉ ትርምስ መሃል ዓይን ውስጥ እንዳትገቢብኝ ፈራሁ። ቶሎ ወደ ቤታችን እንሂድ ህይወትዬ።»

ሄኖክ እየሾፈረ እንዴትና በየት በኩል እንደሄደች ሳታውቀው መኖሪያ ቤቱ ወስዶ ቁጭ አደረጋት።

«ቅዱስ ፒተርበርግ ማለት ይቺ ናት?.....ቆንጆ ከተማ እንደምትሆን ተስፋ አለኝ። ፀጥታማና የተረጋጋ ኑሮ ውስጥ ለመግባት ስናፍቅ ቆይቻለሁ። ሰላማዊ ህይወት የሚኖሩትን ጡረተኞችና አረጋውያንን ለማየት እንዴት ቸኩያለሁ መሰለህ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ እኔና አንተ በዚህች ከተማ ክንድ ለክንድ ተያይዘን የምሽቱን አየር የምንቀበበት ሰዓት በጣም ናፍቆኛል።»

«ሁሉንም ትደርሽበታለሽ። መጀመሪያ ትንሽ እረፍት ውሰጅ። እረኸም መንገድ ስለ ተጓዝሽ ደክሞሻል። ቀዝቃዛ ሻወር ብትወስጂ ጥሩ ነው።……እኔ ናፍቆቴን ለመውጣት ቸኩያለሁ ህይወትዬ። »

«ልክ ነህ ሄኒ፤ ሁሉም ይደርሳል።…….መጀመሪያ እኔም አንተን ልጥገብህ» ብላ ሁለመናውን በናፍቆት እያየችው» የፈረንጆች አገር ኑሮ ተስማምቶሃል፣ በጣም አምሮብሃል። ቀልምህም ሁሉ ወደነሱ እየሄደ ነው። ሰውነትህም ሞላ ብሏል» አለችው።

«አንቺም ቆንጆ ሆነሻል። ደብዳቤሽን ሳነብ በጣም የተጎሳቆልሽ መስሎኝ አዝኜ ነበር። አሁን ሳይሽ ግን እንዲያውም ደምሽ ሞልቶ የወይዛዝርት ውበት ሰጥቶሻል። ትንሽም የድሮ ቁንጅናሽን የለወጠው የወርቅ ጥርስሽ ነው» ብሏት ውበቷን ካደነቀ በኋላ በጥርሷ መውለቅ ተናዶ ራሱን እየነቀነቀ» ከሀገሬ ርቄ መምጣቴ ጎዳኝ እንጂ፣ አጠገብሽ ብሆን ኖሮ ጥርስሽን ያወለቀውን ደደብ ሳልበቀልልሽ አልቀርም ነበር» አላት።

«አይዞህ ሄኒዬ፣ አሁንም ተበቅለህልኛል። ሳያስበው እኔን ቀምተኸው ልቡን አውልቀኸዋል።»

«አሁንም ሲያጣሽ እንዴት እንደሚሆን ይታየኛል።»

«እብድ ነው የሚሆነው። ጨርቁን ጥሎ በአውራ መንገድ ሳይጮህ አይቀርም።»

«ለመሆኑ እንዴት አምልጠሽው መጣሽ?»

«ሁሉንም ነገር በድብቅ የጨረሰልኝና የሰኘኝ መደምደሚያ የሚባል የሱ ታናሽ ወንድም ነው። እንዴት ጥሩ ሰው መሰለህ። ከስጋ ወንድሙ ይልቅ ለኔ ለባዕዷ ያደላ ነበር።»

«ሰውየው ግን ባለጌ ነው። እንዴት ጥርስሽን ያወልቅልሻል?»

«ቅናቱ ነዋ። ሲበዛ ቀናተኛ ነው አላልኩህም?»

«ለነገሩ አንቺን መሣይ ቆንጆ አግኝቶ አይቀናም…..»

«ለማንኛውም አንተ እንደፎከርከው እኔን ከእጆቹ መሃል ፈልቅቀህ ወስደኸኛል፤ ድል አድርገሃል። ነፃ አውጥተኸኛል።…..ከሚወዱት ሰው ጋራ ለአንዲት ደቂቃ አብሮ መቀመጥ እንዴት ከሚወዱት ሰው ጋራ ለአንዲት ደቂቃ እንኳን አብሮ መቀመጥ እንዴት ደስ ይላል መሰለህ…..አህቺን ነፃነት አይቼ ብሞት ግድ የለኝም።»

«ኸረ ገና እንኖራለን፤ ልጆች ወልደን እንስማለን። በፍቅር፣ በደስታና በሰላም ቀሪ ዕድሜያችንን እናሳልፋለን።

«ልክ ነህ ሄኒዬ…..»

እንደገና ተቃቀፉ። ለረጅም ደቂቃ ተቃቅፈው ሲሳሳሙ ቆዩ። ሄኖክ ግንባሯን፣ ጉንጮቿን፣ ከፈሯን፣ አንገቷን እየሳመ ፀጉሯ ውስጥ ፊቱን ደብቆ አለቀሰ። ቁልቁል ወርዶ እግሮቿን እየደባበሰና ጭኖቿን እየሳመ የህይወትን ምላሽ ጠበቀ።

ህይወት ዓይኖቿን አስለምልማ፣ መላ ሰውነቷ በፍቅር ትኩሳት እየተቃጠለ በማቃሰት ላይ ነበረች።

«ኡፍ! እንዴት ደስ ይላል…..» የሚል ቃል በሙቀት ድምፅ ተነፈሰች። መላ ሰውነቷን አንዳች የደስታ ስሜት ወረራት።

«አዎ ህይወትዬ፣ አስታውሳለሁ።.....በተለይ ከከተማ ወጥተን መናፈሻ ውስጥ ያሳለፍነው ጊዜ ትዝ ይልሃል?......» አለችው።

«ድንግልናዬን የተረከብክ ቀን?.....ዛሬም ልክ እንደዚያ ቀን አይነት ስሜት እየተሰማኝ ነው። ......ኡፍ! የሚያፈቅሩትን ማግኘት እንዴት ደስ ይላል»

«ይህንን መሳይ ቆንጆ ገላሽን ያ ደደብ ሰውዬ መንካቱ ግን ሲያናድደኝ ይኖራል።»

«እሱን እርሳው ሄኒ። በድን ሰውነቴን እንጂ ልቤንና ፍቅሬን ሳያገኘው ነው የተለየሁት። ልቤ ምንጊዜም - ካንተው ጋር ነበር» ብላ ተራዋን ግንባሩ ላይና አይኖቹ ላይ እየሳመችው» አንተስ ሄኒ?.....እዚህ አገር እውነት በብቸኝነት ነው ያሳለፍነው?.....ሌላ ሴት አጠገብህ አልነበረችም?.....» ብላ ስትጠይቀው ሄኖክ ደንግጦ ዝም።

«ንገረኝ እንጂ ሄኒ.....»

«እውነት እልሻለሁ።......ማንም አልነበረችም።»

«ዋንሽግተን እያለህ ብቻህን ነበርክ?.....»

«ብቻዬን ነበርኩ.....»

«እኔ እንጃ ሄኒ.....ልቤ ጠረጠረ። አንድ የሆነች ፈረንጅ ካንተ ጋር በፍቅር ብን ብላ ተያይዛችሁ ስትከንፉ በሃሳብ ይታየኝ ነበር።»

«ተሳስተሻል ይህወትዬ....»

«ነግሬሃለሁ ሄኒ.....ከፈረንጅ ሴት ጋር ባይህ ወዮልህ ሴትዮዋንም በጣቶቼ ዓይኖቿን ጎልጉዬ፣ በጥፍሮቼ ቦጫጭሬ ነው የምለቃት።»

ሄኖክ ሲደነግጥ አየችው። እና እሷም ባልተጨበጠ ነገር ላይ መቅናቷ ለራሷ አስገረማት። ሰማይነህም የሚቀናው እንዲህ ነበር ማለት ነው በማለት በልቧ አሰበች።

«......አብስዬ አበላሻለሁ በለህ ደብዳቤ መፃፍህን ረሳኸው እንዴ? ተነስና ጉድ ጉድ በል እንጂ። አንተ የሰራኸውን ምግብ ለመብላት በጣም ቸኩያለሁ» ብላ ቀለደችበት።

«አትጠራጠሪ ሞያዬን አሳይሻለሁ። የምትፈልጊውን የምግብ አይነት ንገሪኝ።»

«አንተ የሰራኸው ማንኛውም እንነገር ይጣፍጠኛል....»

«እኔም አንቺን መንከባከቡ ብቻ ታላቅ ደስታ ይሰጠኛል።»

«.....ግን አሁን ወደ ስራ ስትሄድ እኔን ብቻዬን እቤት ውስጥ ልታስቀምጠኝ ነው?» አለችው በድንገት ልውጥ ብላ

«ለምን ተብሎ......ትሄጃለሽ እንጂ....»

«አዎ አብሬህ መሄድ ይሻለኛል። የፅዳት ስራህን ስትሰራ አግዝሃለሁ። አንተ ቆሻሻውን ስትጠርግ እኔ እሰበስባለሁ።»

«ምን በወጣሽ የኔ ቆንጆ.....እነዚህ አለንጋ ጣቶችሽ ቆሻሻ እንዲነኩብኝ አልፈልግም።....»

«አትጨነቅ ሄኒ፤ ድህነታችንን ይዘን በነፃነት መስራትና መኖር ለኔ ይልቅ ደስታ ይሰጠኛል። ነፃነቴን ገፈው፣ የማላጌጥበትን ወርቅ አሸክመውና የማልደሰትበት ሀብት ውስጥ ጨምረውኝ ምሬቱን አሳይተውኛል። በነፃነትና በፍቅር ቆርጥሞ ማደር እንደሚሻል በተግባር ተምሬአለሁ።»

በዚህ የሞቀ ፍቅር ጨዋታቸው መሃል ከውጭ የመጥሪያ ደወል ሲያቃጭል ይሰማሉ። ሄኖክ ተነስቶ ሄዶ በሩን ሲከፍት አንዲት ወጣት ፈረንጅ ዘው ብላ ትገባና ሄኖክን ከንፈሩ ላይ ትስመዋለች። ህይወት ይህንን ስትመለከት በድንጋጤ የምትሆነው ታጣለች። አይኖቿም ደም ለብሰው ፈርንጇ ላይ አፍጥጣ ከቆየች በኋላ ጥፍሮቿን አሹላ እንደ ነብር እመር ባላ ዘላ ልታንቃት ስትል ሄኖክ እጆቿን ይይዛታል። ህይወት እያለቀሰች መጮህ ትጀምራለች።

«.....እንደፈራሁት ይሄው ፈረንጇ መጣች.....እኔን በፈረንጅ ሴት ትለውጠኛለህ ሄኒ?.....ወይኔ እድሌ.....የልጅነት ፍቅረኛዬን ተቀማሁ....በባዕድ አገር ተዋረድኩ.....አንተን ብዬ መጥቼ እንዲህ ጉድ ታደርገኝ ሄኒ?....ልቀቀኝ፣ አትያዘኝ..... ይህችን ፈረንጅ በጥርሴ ቦጫጭቄ ሳላደማት አለቃትም።.....»

ሄኖክ ጥርጣሬዋ ትክክል ያለመሆኑን እያስረዳት ለመገላገል ይሞክራል። እሷ ግን አትሰማውም።

«ተወኝ ሄኒ፣ በቃኸኝ.....ይቺ ፈረንጅ በዚ ሰዓት ምን ልታደርግ እቤትህ ድረስ እንደ መጣች ማወቅ አያቅተኝም።.......ወይኔ ህይወት.....ተጠቃሁ» እያለች ስትወራጭ በክርኗ የሰማይነህን ደረት መታችው።»

«እ እ እ.....» ብሎ እያቃሰተ ሰማይነህ ከእንቅልፉ ባኖ የራስጌውን መብራት አበራ።

«በስመ አብ....» ህይወትም ከእንቅልፏ ነቅታ አጠገቧ የተኛው ወንድ ሰማይነህ መሆኑን ስታረጋግጥ ደነገጠች።

«ም......ምነው?......ምን ነካሽ?....» አላት ሰማይነህ ደረቱን እያሻሸ

«እኔ እንጃ፤ ቅዠት ላይ ነበርኩ መሰለኝ......» አለችው ህይወት እየተበሳጨች።

የቆየችበት ጣፋጭ አለም ህልም መሆኑ አናዷታል። ሰሞኑን በዓዕምሮዋ ስታስብ የከረመችውን መልሳ በህልሟ አየች። እዚህ ህልሟ ላይ በውን የምትደርሰው መቼ ነው? ሄኖክን አግኝታ ነፃነቷን ተጎናፅፋ....በፍቅር በሰላም የምትኖረው መቼ ይሆን? ከዚያ ሁሉ የህልም ፍስሃ በኋላ እራሷን የሰማይነህ ጉያ ስር ማግኘቷ አነጫነጫት።

በሌላ በኩል ደግሞ በህልሟ ከወጣቷ ፈረንጅ ጋር ያደረገችው ፍልሚያ ለራሷ አስገረማት። ለካስ ለምንወደው ነገር ሁላችንም ቀናተኞች ነን አለች በሃሣቧ። ምናልባት በሰማይነህ ላይ ግድ የለሽ የሆንኩትና ምንም ዓይነት ቅናት የማላሳየው ስለማልወደው ይሆናል ስትል ራሷን ጠየቀች። ባህር ማዶ ተሻግራ ሄዳ ባልተጨበጠ ነገር ላይ መቅናቷ አስደንቋት በሰማይነህ ቅጥ ያጣ ቅናት ላይ ትንሽ ምክንያታዊነት አገኘችበት።

«ምን ዓይነት ቅዠት ነው እንደዚህ ያወራጨሽ?» አላት ሰማይነህ ንዴት እየጀመረው።

‹.....ያዩሁትን ህልም ብነግህርማ እዚሁ አንቀህ ትገድለኛለህ! ፍሎሪዳ ድረስ ሄጄ ከልጅነት ፍቅረኛዬ ጋር ስጫወት ነው የቆየሁት፤ አንተን አጠገቤ ኢጋድሜ› አለች በልቧ።

«ተናገሪ እንጂ.....» ሲል እንደ ገና ጮኸባት።

«መጥፎ ቅዠት ነበር.....ዱርዬዎች ዙሪያየን ከበው ለማምለጥ ስታገል ነው ከእንቅልፌ የነቃሁት» አለችው ድንገት እዚያው ፊጥራ።

«እነማን ናቸው እነሱ?......ዱርዬዎቹን አታውቂያቸውም?.....›.

«ኸረ እኔ አላውቃቸውም.....»

«ይሄኔ አንቺ ራስሽ መጀመሪያ ፊት አሳይተሻቸው ይሆናል።.....ጥርስሽን ሳትገልጭላቸው እንዲሁ ከመሬት ተነስተው አይነኩሽም።»

«እንዴ.....የምነግርህ እኮ ቅዠት ነው።»

«እኮ.....የቀኑ አንሶአቸው ሌሊት እየመጡ ያቃዡሽ ጀመር። እነዚህ ጋጠ ወጥ ዱርዬዎች።»

‹መናደድህ ነው እንዴ?....ሞኝ ነህ። ይልቅስ የሚያናድድህ እዚሁ አንተ ጉያ ስር ተወሽቁ ያየሁትን የሩቅ ህልም ብታውቂ ነበር› አለች ህይወት በልቧ።

«.....ለመሆኑ ቁጥራቸው ምን ያህል ነው?» አላት ሰማይነህ ትራሱን ቀና አድርጎ ጥርሶቹን እያንገጫገጨ።

«የምኖቹ......የዱርዬዎቹ?....»

«ታዲያስ.....»

«እኔ እንጃ።.....ብዙ ናቸው።»

«ምናልባት ያ ልብስ ሰፊ ደምበኛሽ እነዚያ መርካቶ ውስጥ የለከፉን ቦዘኔዎች አሰባስቦ የፈፀመው ተግባር ይሆናል።.....ወይንም ደግሞ የቀድሞው ፀጉር ሰሪ ደንበኛሽ ግብረአበሮች ይሆናሉ።»

«ኸረ ከነሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። እኔ የምነግርህ ቅዠት ነው።......ዱርዬዎች ድንገት መንገድ ላይ ያጋጠሙኝ ናቸው።»

«ወዴት ስትሄጂ ነው ዱርዬዎቹ ያጋጠሙሽ?....»

«እኔ እንጃ.....ብቻ አንድ የሆነ መንገድ ላይ ነው።»

«መጀመሪያ ነገር አንቺ ከዚህ ግቢ እንድትወጪ ማን ፈቅዶልሽ ነው የሄድሽው? ያውም ብቻሽን»

«እንዴ....ምን ነካህ ሰማይነህ....ህልም እኮ ነው የነገርኩህ። እኔማ አጠገብህ እንደተኛሁ ነኝ። »

«ያው ነው።....ልብሽ ወጥቶ ሄዷል ማለት ነው።»

‹አይ ሞኜ....ልቤማ ከግቢ ከመውጣት አልፎ አሜሪካን አገር ድረስ ሄዷል› አለች ህይወት በሃሳቧ።

«ለመሆኑ በመጨረሻ ዱርዬዎቹን አመለጥሻቸው ወይንስ እንደያዙሽ ቀሩ?....» አላት በጉጉት ዓይኖቹን አፍጥጦ።

«አመለጥኳቸው እንጂ……መንጭቄ ሳመልጣቸው ነው እኮ ከቅንቅልፌ የባነንኩት» ብላ አረጋጋችው፡፡

ሰማይነህ መጠነኛ እፎይታ ቢያገኝም ተመልሶ እንቅልፍ አልወሰደውም፡፡ በለሊት የቅናት ዛሩ ተነስቶ ያሰቃየው ጀመር፡፡ በህይወት የሚጠረጥራቸውና አዕምሮው ውስጥ በመጥፎ ስዕል የቀረፃቸው ወንዶች ሁሉ በረድፍ ተሰልፈው እየመጡ በሃሣቡ ታዩት፡፡ የሰርጉ ዕለት በጥርጣሬ የጠመዳቸውን……በቪዲዮ ውስጥ ህይወት ላይ ሲያተኩሩ ያያቸውን፣ ይትባረክንና አቡበከርን፣ የተጣላውን ልብስ ሰፊ፣ ጎርፉን የገላመጠውን የሴት ፀጉር ሰሪ፣ ከባህር ማዶ ያለውን ሄኖክ፣ ሁሉንም በኃሳቡ እየተመለከተ በቅናት ተብከነከነ፡፡

ህይወት ስትገላበጥ ከቆየች በኋላ እንቅልፍ ወሰዳት፡፡ ሰማይነህ ግን አልተኛም፣ መብራቱንም አላጠፋውም፡፡

ምናልባት እንደ ገና ስትቃዥ ወይም ስታልም እንዲያጋጥመው ፈጣሪውን እየለመነ አፍጦ ጠበቃት፡፡ ይህ ብዙ ጊዜ የሚያደርገው ነገር ነው፡፡ ህልሟን ማየት ባይችልም ቅዠቷን ለማዳመጥ ግን ብዙ ሌሊቶች በተደጋጋሚ ሞክሯል፡፡ ከአልጋው ወርዶ ተምበርክኮ የሌሎቹን ወንዶች ስም በቅዠት ስትጠራ ለመስማት ጥረት አድርጓል፡፡ ሆኖም ግን አንድም ሌሊት አልቀናውም፡፡ ህልሟንና ቅዠቷን ማሳየት የሚችል ልዩ መነፅር ቢያገኝ በሚሊዮን ብር ቢገዛም አይቆጨውም ነበር፡፡ ቀና ብሎ ህይወትን በተኛበት ቦታ እንዳዲስ ፍጥሩ አትኩሮ ተመለከታት፡፡ እንዲህ የምታስቀናውና የምታቃጥለው በምኗ እንደሆነ ለመመራመር ሞከረ፡፡ ጥርሷ ከወለቀ ጀምሮ ፈገግታ መቀነሷን አረጋግጧል፡፡ ሌሎቹንም የሚያስቀኑትን የሰውነቷ ክፍሎች ደግሞ ተመሳሳይ እርምጃ ቢወስድባቸው እፎይታ ሊያገኝ እንደሚችል ሆኖ ስለ ተሰማው አስተያየቱና ምኞቱ ወደ አውሬነት እየተለወጠ ሄደ፡፡ የቅናት ዛሩን ተከትለው ሰይጣኖች «ሆይ….ሆይ…..» እያሉ እያጨበጨቡ ሰፈሩበት፡፡

መጀመሪያ የመጣለት ኃሳብ እግሯን ቆርጦ ከቤት እንዳትነቃነቅ ማድረግ ነው፡፡ ብዙ ወንዶች የህይወትን ተረከዝና ባት ሲያደንቁ ስምቷል፤ ዓይኖቻቸውን ዳሌዋ ላይ ተክለው መንቀል ሲያቅታቸው ተመልክቷል፡፡ እግሯ ከተቆረጠ የምታስጎመዥበት ባትም ሆነ የምታውረገርገው ዳሌ አይኖራትም፡፡ ሃሳቡን በመደገፍ ሰይጣኖች አጨበጨቡለት፡፡ ሆኖም ግን የድርጊቱ ክብደት በኃሳቡ ታየው፡፡ የሰው እግር መቁረጥ እጅግ በጣም ከባድ ጭካኔ የሚጠይቅ ነው፡፡ ስጋዋን እየቆራረጡና አጥንቷን እየገዘገዙ መታገሉ እራሱ በጣም ይዘገንናል፡፡ ከዚህም ሌላ ደግሞ እግሯን የተቆረጠች ሚስት ለራሱም ቢሆን ድቡልቡል ሙቀጫ ልትሆንበት ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ ትቶ ወደ ሌላው የሰውነቷ ክፍል ተሻገረ፡፡

ረዥም ፀጉሯ እንደተበታተነ አየው፡፡ አንዱ የሌሎቹን ዓይን መሳቢያ መሣሪያዋ ይህ ፀጉሯ ነው፡፡ ፀጉሯን መላጨት ትዕቢቷንና ውጭ ውጭ ማየቷን ሊቀንስላት ይችላል ሲል አሰበ፡፡ ፀጉሯን የተላጨችው ህይወት ምን እንደምትመስል በኃሳቡ ለማየት ሞከረ ለሱ አታስጠላውም፣ የሌሎቹን ዓይን ግን አትስብም፡፡ የሚፈልገው ይሄንኑ ነው፡፡ እንደገና ሰይጣኖች እያጨበጨቡ ገፋፉት፡፡ ሆኖም ግን ዘለቅ ብሎ ሲያስብ ፀጉሩ ነገ ተመልሶ ይበቅላል፣ ዘለቄታዊ እፎይታ ሊሰጠው የሚችል እርምጃ አይሆንም፡፡

ቀስ ብሎ ዓይኖቿ ላይ አተኮረ፡፡ ዋናዎቹን የውበት መሣሪያዎቿን ማግኘት ተሰማው፡፡ አሁን እንቅልፍ ስለወሰዳት ዓይኖቿ ተከድነዋል፡፡ አይኖቿን በምትገልጥበት ጊዜ ግን ብዙ ታይበታለች፡፡ በርካታ ወንዶች የሚሳቡት በነዚህ ትላልቅ ዓይኖቿ ነው፡፡ በሰማይነህ እምነት መሠረት ዋንኛዎቹ የማስቀኛ መሣሪያዎቿ እነዚህ ዓይኖቿ ናቸው፣ የቁንጅናዋ ማንፀባረቂያ ናቸው፡፡ በዓይኖቿ ሌላ ታይበታለች፣ ታማርጠኛለች፣ ታባብልበታለች፣ ትጠቅስበታለች፣ ትቀነዝርበታለች፣ ታፈቅርበታለች፡፡ ስለዚህ ዓይኖቿ መጥፋት አለባቸው፡፡ እንዲሁ እንደተከደኑ ዓይኖቿን ሳትገልጥ ለዘለዓለሙ መኖር አለባት በማለት ሰማይነህ ዛተ፡፡ ከሁሉም ይልቅ እፎይታን ሊሰጠው የሚችለው እርምጃ ይሄኛው መሆኑን አመነበት፡፡ ዓይነስውር ሚስት ይዞ የመቀመጡ ነገር ከህብቱና ከክብሩ ጋር

የማይሄድ ሆኖ ቢታየውም ቀናተኛው ስሜቱ አሸንፎ ለጥፋት ገፋፋው። ሰይታኖቹ በይበልጥ እያጨበጨቡና ከበሯቸውን እየደለቁ በሆሆታ ድጋፋቸውን ሰጡት። አመንትቶ ወደ ኋላው እንዳያፈገፍግ እያሟሟቁት የከፋትና የጥፋት ዱላቸውን አቀበሉት። ለአንዴም ለሁሌም ከቅናት የሚገላግልበትን መንገድ ሲያስበው ደሙ እየሞቀ ሄደ። ይህንን እርምጃ ለመፈፀም ትልቅ መሣሪያ አያስፈልገውም። ዱላ ውስጥ ተሳቢ ጨቤውን በውድቅት ሌሊት ፈልጎ አገኘ። ሰይጣኖቹም የጥፋት መሣሪያውን በማፍላለጉ ሌሊት ፈልጎ አገኘ። ሰይጣኖቹም የጥፋት መሣሪያውን መዞ ወደ ህይወት ዓይኖች ቀረበ። ዓይኖቿ ሲጠፉ ውበቷ ይበላሽ ይሆን? በፍፁም! ለሚያያዋትና ለምታያቸው ይባልኝላቸው እንጂ ሰማይነህ እንደሆነ ዕድሜ ልኩን በነዚህ ዓይኖቹ ምክንያት ሲቃጠል ከሚኖር ዓይነ ስውርነቷን መርጧል።

«በቃሽ......እንግዲህ አይኖችሽ አይገለጡም» እያለ ጩቤውን ባይኖቿ ትክክል ወድሮ፣ ግምባሩን አኮሳትሮ ጥርሶቹን ነክሶ ለጭካኔ ሲዘጋጅ፣ መላእክት ህይወትን ከእንቅልፍ ቀሰቀሷት።

«በስመ አብ ወወልድ.....ምንድነው እሱ የማየው?.....አለች ህይወት እየዘገነናት ጩቤውን እየሸሸች። እሷ ከእንቅልፏ ነቅታ ሳታማትብ ሰይጣኖቹ ድራሻቸው የጠፋ ይመስል ሰማይነህ በድንጋጤ ክው ብሎ አጠገቧ እንደተገተረ ቀረ።

«ምን ሊያደርግልህ ነው እሱን ጩቤ የያዝከው?....አንተስ በእኩለ ሌሊት ምን ልታደርግ ተነሳህ?....» እያለች እንደገና በጥርጣሬና በፍርሃት ጠየቀችው። ሁኔታውን ስታየው ጤነኛ አልመሰላትም። በውድቅት ሌሊት እራቁቱን ጩቤ ይዞ የቆመበት ምክንያት እብደት ወይንም ልክፍት ይሆናል ብላ ገመተች።......ወይንስ በተኛሁበት ሊያርደኝ አስቦ ይሆን? በማለት በጥርጣሬ ዓይን ተመለከተችው።

ሰማይነህ ድንጋጤው ሲለቀውና ሰይጣኖቹ ከአጠገቡ ዞር ሲሉለት ቶሎ ብሎ ሌላ ምክንያት ፈጠረ።

«ቅዠት በጣም ስላስቸገረሽ ይህንን ስለት ከራስጌሽ ላደርግልሽ ነው የተነሳሁት። ላንቺ አይታወቅሽ እንደሆነ እንጂ በጣም ነው የምትወራጪው.....ክፉኛ ያቃዠሻል» አላት።

ስለት ከራስጌ ማድረግ ለቅዠት መከላከያነት እንደሚረዳ ህይወት አክስቷ ስታወራ ትሰማ ነበር። አሁንስ ሰማይነህ እውነቱን ይሆን?......ዓይነ ውህው ግን አላምራትም። ለጥፋት እንጂ ለእርዳታ የቆመ ሰው አይመስልም። በሌላ በኩል ደግሞ መደምደሚያ የነገራት ከጠንቋይ ጋር የተያያዘው የሰማይነህ እምነት ታወሳትና ነገሮች ተምታቱባት።

«ይቅርብኝ ሰማይነህ......እሱን ስለት ካጠገቤ ዞር አድርገው» አለችው።

ሰማይነህ ጩቤውን ከቦታው መልሶ ተኛ። ሆኖም ግን ሁለቱም አልተማመኑም። እንደፈራሩና እንደተጠባበቁ እንቅልፍ ሳይወስዳቸው ነጋ።

# ክፍል አሥራ አምስት

ሰማይነህ ተነስቶ ወደ ስራው ከሄደበት ሰዓት ጀምሮ ህይወት ዓይኖቿን የመኝታ ቤቱ ኮርኒስ ላይ ተክላ ከዚህ የሰቀቀን ኑሮ የምትላቀቅበትን ዘዴ ማሰላሰል ጀመረች። የሌሊቱ የሰማይነህ ሁኔታ አዕምሮዋ ውስጥ ተስሎ ቀርቶ አሁንም አስጨነቃት፤ ራቁቱን ጩቤ ይዞ አጠገቧ እንደ ቆመ ታያት። ‹ለቅዠትሽ መከላከያ ከራስጌሽ ላደርግልሽ ነው› ያላት አልተዋጠላትም። ድንጋጤው መርበትበቱና ገፅታው መለዋወጡ ሊረዳት ሳይሆን ሊገድላት መቆሙን ጠቁመውታል። ‹ምናልባት በዚህ ውድቅት

ሌሊት ስለት አስይዞ እርቃኑን ያስቆመው የተጠናወተው የቅናት አባዜና ልክፍት ሊሆን ይችላል፤ የሚል ግምት ወሰደች። እሷን ለመርዳት ቢያስብ ኖሮ ስለት የሌለው ብረት ከራስጌዋ ሊያደርግ እንደሚችልም አሰላሰለች። ስለዚህ በልክፍትም ይሁን በጤናው እሷን ለመጉዳት መቆሙን ራሷን አሳመነች። ‹ጥርሴን በአደባባይ እንዳወለቀ ሁሉ አሁን ደግሞ በውድቅት ጭለማ አንዱን አካሌን ቢያጎድልብኝስ?!› ስትል ጠረጠረች። የየዋህነት አምላኳ ሳይረዳት አልቀረም። መልአክት ከፋቸውን ዘርግተው ወደ እሷ እየመጡ ‹ጥርጣሬሽ ልክ ነው። ቶሎ ራስሽን አድኚ፤ ከዚህ ቤት ውጪ!› የሚልዋት መሰላት።

ነፍሷ እረፍት አጣች። ከዚህ በኋላ አንዲት ለሊት እንኳን ከሰማይነህ ጋር ማደር እንደሌለባት ወሰነች፤ መደምደሚያ ስለ ጠንቋዩ የነገራትን አስታውሳ ይበልጥ እራሷን በጠበጠችው። እሷነቷ ከንብረት ጋር ተቆራኝቶ፣ እንዳትሞት እየተጠበቀች፣ ተረግጣና ታፍና እንድትኖር የተፈረደባት እቃ መሆኗ አሳዝኖአታል። ሰማይነህና ቤተሰቦቹ እርምጃቸው ከፍቶ እጅና እግሯን አስረው ፍፁም እንዳትንቀሳቀስ ከማድረጋቸው በፊት እሷ መቅደም አለባት። ሰማይነህ በመረረ ጭካኔ አካሷን አበላሽቶ እቤት ውስጥ ከማስቀረቱ በፊት እሷ መቅደም ይኖርባታል።

ለመጥፋት ወሰነች። እንዴትና በምን መንገድ መጀመሪያ ከዚህ ግቢ ውስጥ መውጣት እንደምትችል ግራ ገባት። የመጥፊያው ዘዴ ከኮርኒስ ላይ ጠብ የሚልላት ይመስል አፍጥጣ ብትመለከተው ነጩ ኮርኒስ ነጭ ነበር። ክፉም ደግሞ አይናገርም። ጎርፉ እንኳን ወደ ታክሲው ሰራው ቢሄድ በአሮጊቷና በር ላይ በቆመው ዘበኛ ጥበቃ ስር መሆኗን ታውቃለች። ቢያንስ ሁለቱንም አታልላ ልታመልጥ የምትችልበትን ዘዴ መቀየስ አለባት።

‹ዘበኛውን ለምኜና አባብዬ ለመውጣት ብሞክርስ?› ስትል አሰበች።

‹ትንሽ አስቢ ህይወት። አሮጊቷ ሊከታተሉሽ ይችላሉ። ዘበኛውም ሳይሸነገልልሽ ይችላል› አላት ሌላው አሰነች።

‹ትንሽ አስቢ ህይወት። አሮጊቷ ሊከታተሉሽ ይችላሉ። ዘበኛውም ላይነሸነገልልሽ ይችላል› አላት ሌላው የአዕምሮዋ ክፍል።

‹አሮጊቷን እራሳቸውን ባታልላቸውስ?›

‹በምን ዘዴ?.....›

‹አክስቴ ናፍቀችኝ፤ ሄጄ ልጠይቃት ብዬ ብለምናቸው.....›

‹አምነው አይለቁሽም።.....ይልቅ ሌላ ዘዴ አስቢ›

‹አንዳቸውም ሳይሰሙ ድምፄን አጥፍቼ ባጥር ላይ ዘልዬ ብወጣስ?›

‹ሊነቁብሽ ይችላሉ።......ሌላው ቢቀር ውሾች ይጮሁብሻል። በአጥር መዝለሉም ያለልመድሽው ነገር ስለሆነ ሊያዳግትሽ ይችላል› የግንቡን አጥር ለመዝለል ሞክራ ሲያቅታት ወይንም ውሾች ጮኸው ሲያስነቁባትና ተይዛ ለውርደት ስትጋለጥ በኃሳቧ ታያት። ሆኖም ማምለጥ ያለመቻሏ ያናድዳት እንደሆነ እንጂ ውርደት አያሳፍራትም። አሁን ካለሁበት ኑሮ የከፋ ውርደት የለም ብላ ወሰነች። አልፎ - አልፎ በፊልም እንዳየችው ሁሉ አደጋን ሳይጋፈጡ ማምለጥ ወይንም ድል ማድረግ እንደማይቻል ገመተች። እንዲያውም አሁኑኑ የጎርፉ ታክሲ የኋላ መቀመጫ ስር ገብቼ ብደበቅና እሱ ሳያውቅ ከዚህ ግቢ ይዞኝ ቢወጣ.....ስትል አሰበች። ይህ ደግሞ የበለጠ የፊልም ትርኢት ይሆናል። ነገር ግን የመጋለጡ እድል የሰፋ ነው።

በአሮጊቷ ስሜት ገብታ፣ ፅንስ የያዘች አስመስላ፣ አንድ ነገር በእርግዝናዋ ምክንያት እንዳማራት ወንድም ለብቻዋ ሃኪም ማማከር እንዳለባት አድርጋ ልታታልላቸው አሰበች። ይኸኛው የተሻለ ዘዴ

ሆኖ አገኘችው። ነገር ግን በሃሣቧ ቢስማሙ እንኳን አሮጊቷና ጎርፉ ተከትለዋት ሄደው መግቢያ መውጫዋን በመጠበቅ መፈናፈኛ ሊያሳጧት እንደሚችሉ ገመተች።

ብዙ ስታሰላስል ከቆየች በኋላ በዚሁ መንገድ አንድ ዘዴ ብልጭ አሰላት። ፈሪው የአእምሮዋ ክፍል መከላከያውን ከማቅረቡና ከማዘናጋቱ በፊት ቀድማው በፍጥነት ከአልጋዋ ወረደች።

‹ምንም ቢሆን አሮጊቷንና ጎርፉን ማታለል አያቅተኝም› ብላ ቆረጠች።

ልብሶቿ በሙሉ ቁም ሳጥን ውስጥ ስለተቆለፈባቸው ለብሳው የምትወጣው ደህና ነገር አልነበራትም። ረጅም የቤት ለቤት ቀሚሷና አንድ አሮጌ ጅንስ ሱሪ ብቻ ነው ውጭ የተቀመጠላት። ለቅልጥፍና እንዲረዳት ሱሪውን አጠለቀች። ትንሿ የእጅ ቦርሳዋ ውስጥ ያለው ገንዘብ አስር ብር እንኳን አይሞላም። ብዙ ነገር በገንዘብ ማድረግ እንደሚቻል ሰማይነህ ከልምድ ስለሚያውቅ ህይወት እጅ ላይ ገንዘብ እንዳይኖር የሚያደርገው ሆነ ብሎ ነው። ልብሶቿ ላይ እንደመቆለፉና ገንዘብ እንዳትይዝ የመጠንቀቁን ያህል የወርቅ ሳጥኗን አልነካባትም። ወርቆቿን ያለ ልብስ አታጌጥባቸውም......አውጥታም ለመሸጥ አትደፍርም ብሎ ቸል ያለ ይመስላል።

በህይወት አዕምሮ ውስጥ የተፈጠረው የመጥፋት ብልጭታ ሌላ ብልጭታን ፈጥሮ ወርቆቿን ይዛ ለመሄድ ወሰነች። መጀመሪያ ወርቆቿን የሰማይነህ ንብረት አድርጋ በመቁጠር ንቃቸው ነበር። በኋላ ግን እጇ ላይ ገንዘብ እንደሌለ ድረስ ለከፉም ለደጉም ወርቆቿን መያዝ እንደሚያስፈልግ አመነች። በሌላ በኩል ደግሞ የወለቀ ጥርሷና የፊትነቷ የጉዳት ካሳ አድርጋ በመውሰድ ተደፋፈረች። ወርቆቿን አውጥታ ሱሪዋ ኪስ ውስጥ ስትጨምር ልቡና ፍርሃት ፍርሃት አለው፤ የመደንገጥና የመደናገር ስሜት ተሰማት። መጥፋቷና ከሰማይነህ መለየቷ ዕውን እየሆነ ሲሄድ ተርበተበተች።

ሌላ መያዝ ያለባት ቀላል ነገር እንዳትረሳ ስታስብ የሄኖክ ደብዳቤ ትዝ አላትና ከደበቀችበት ቦታ አወጣችው። ተስፋ የጣለችበት አንዱና ትልቁ ኃብቷ ይህ ደብዳቤ በመሆኑ ወደ ኪሷ ከመክተቷ በፊት ወረቀቱን እንደ መስቀል ተሳልማውና ስማው ‹ሄኒዬ፤ ያንተ አምላክ ይርዳኝ እንግዲህ› አለች።

ጅንስ ሱሪ ከቀላል ጭማና ሹራብ ጋር ካደረገች በኋላ ከመኝታ ክፍሏ ጋር ወደተያያዘው ባኞ ቤት ገብታ ፊቷንና እጇን ተጣጠበች። ወዲያው ጎርፉን የምታጃጅልበት አንድ ዘዴ ብልጭ ስላለላት የጋብቻውን የጣት ቀለበት አውልቃ ሆን ብላ የእጅ መታጠቢያው ሸክላ ላይ አስቀመጠችው። ፊቷን በመታጠቢያ ቤቱ መስታወት ስታየው ዝግጁ ነው። መቁረጧንም ለራሷ ለማሳመን ግምባሯን አኮሳራ፣ ጥርሷን ነክሳ፣ ፊቷን ኩምጭጭ አድርጋ ተመለከተችው። ምናልባት ያሰበችው ዘዴ ቢከሽፍባት እንኳ፣ እንደ ምንም ከዚህ ግቢ ከወጣች «ኡ ኡ!» ብላ ፖሊስ ጠርታ ሰማይነህን ለማጋለጥና ለመገላገል አሰበች። ዋናው ነገር ከዚህ ግቢ መውጣት ብቻ ነው።

ወደ መኝታ ክፍሏ ተመልሳ በረዥሙ የመልበሻ መስታወት ቁመናዋንና አለባበሷን ተመለከተች። ለሩጫ የተዘጋጀች ትመስላለች። መነፅርና ኮፍያ ብታገኝ ደግሞ የበለጠ ራሷን መለወጥ እንደምትችል ገመተች። ኮፍያ የለም። እንደዋዛ የተወረወረ አንድ ተራ የፀሐይ መነፅር እዚያው የመልበሻ ጠረጴዛ ላይ አግኝታ በትንሿ ቦርሳዋ ውስጥ ያዘችው። ትንሽ ማበጠሪያም ቦርሳዋ ውስጥ መኖሩን አረጋገጠች።

ይህ አለባበሷ የሚረዳት በኋላ ነው፤ አሁን ከውስጥ መደበቅ አለበት። በሱሪዋ ላይ አሮጌውን እረዥም ቀሚስ ለብሳ ከላይ ጋቢ ደረበችበት። ፀጉሯንም በሻሽ ጇብን አድርጋ ሰረችው። ህመምተኛም ለመምሰል ፊቷን ማጨፍገግና አንገቷን ማዘንበሉን በመስታወት እያየች ተለማመደች። «የፊልም ተዋናዮችም ከዚይ የበለጠ ተአምር ይሰራሉ። እኔ ይቺን ዘዴ ተጠቅሜ ማምለጥ ሊሳነኝ አይገባም» በማለት እንደገና እራሷን አደፋፈረች። ከጎርፉ ይልቅ የፈራችው አሮጊቷን ነበር።

የአለባበስ ዝግጅት ከጨረሰች በኋላ አዕምሮዋ አንድ አዲስ ነገር ጫረባት። ተሳክቶላት ከዚህ ግቢ ማምለጥ ከቻለች ሰማይነህ እየተከታተላት እንዳይፈልጋትና ስጋት ላይ እንዳይጥላት ተስፋ

የሚያስቆርጥ ደብዳቤ ለመፃፍ አሰበች አሁንም ፈሪው የአዕምሮዋ ክፍል እንዳይስመነታት በፍጥነት ወረቀትና ብዕር ይዛ ጫር - ጫር አደረገች።

«ሰማይነህ፤ አብረን መኖር ስላልቻልን ጥዬህ ሄጃለሁ። በእስረኝነት መኖር ስላስመረረኝ ራሴን ነፃ አውጥቻለሁ። እኔን በመፈለግና በማፈላለግ ጊዜህን እንዳታቃጥል። አሜሪካን አገር የሚገኘው የልጅነት ፍቅረኛዬ በአስቸኳይ ጠርቶኝ ሄጃለሁ። እስከመጨረሻው አንገናኝም። የጋብቻ ቀለበቴን እዚሁ ጥዬልሃለሁ ከጎርፉ እጅ መውሰድ ትችላለህ። ለዘላለሙ ቻው!....

ህይወት ስዩም።»

ሰማይነህ በሚተኛበት በኩል ቶሎ ሊያየው በሚችልበት ቦታ ደብዳቤውን አስቀመጠችለት። ቀስ ብላ ወደ ሳሎን ሄዳ የስልኩን መስመር ከቀፎው ጋር የሚያያይዘውን ሽቦ በምላጭ በጠሰችው። የስልኩን እጀታ አንስታም መስመር መቋረጡን አረጋገጠች። ለማንኛውም ሁኔታ ጥሩ ጥንቃቄ ነው፤ ሰማይነህ ከእቤት ውስጥ ሊደወልለትም ሆነ ራሱ ከውጭ ሊደውል አችይልም ማለት ነው። መኝታ ቤቷን ከውጭ ስትቆልፍ አሮጊቷ ጆሮዋቸውን አቁመው በጠባቂነታአቸው መሠረት፣ እየሳሉ ድምጻቸውን አሰሙ። በንቃት እየጠበቁ መሆናቸውን ማስታወቃቸው ነበር። ይሄኔ ህይወትም በማታሰት ድምጿን አሰማች።

«ምንድነው እሱ?.....ምን ሆነሻል?» እያሉ አሮጊቷ ከመኝታ ክፍላቸው ወጥተው ሲመጡ፣ ህይወት በአንድ እጇ ወገቡና በአንድ እጇ ጭንቅላቷን ደግፋ ሳሎን ውስጥ ሶፋ ላይ ተቀምጣ አገኟት። ፊቷን አጠውልጋ ቅዝዝ ብላለች።

«አመመሽ እንዴ?....ምንድነው?»

«ማህፀኔ አካባቢ ነው።......ጥሩ ስሜት አይሰማኝም» አለቻቸው ሆዷን በእጇ እየነካካች። የታመመች ማስመሰሉን በደንብ ችላበታለች።

«እንዴት ነው?.....ፍሬ ይዘሻል እንዴ?» አሉዋት በጉጉት

«አዎ....አሁን የፈራሁት ፅንሱ እንዳይበላሽ ነው።» አሮጊቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ድንጋጤ አሳዩ።

«ታዲያ ምን ይሻላል?!....መላ እንፈልግ እንጂ»

«ቶሎ ሃኪም ቤት ውሰዱኝ.....»

«መጀመሪያ ሰማይነህም ጋ ይደወልለት እንጂ.....» ብለው ለማንኛውም ጎርፉን ሊያስነሱት እየተቻኮሉ ሄዱ።

ጎርፉ እንቅልፉን ቢጨርስም ካልጋው ላይ መውረድና ወደ ስራ መሄድ አስጠልቶት እየተሻሸ ነበር። እናቱ የህይወትን መታመም ነግረውት እያከታለቡ ሲያስነሱት ቁርሱንም ሳይበላ ከቤት የመውጣቱ ንገር አሳስቦት መነጫነጭ ጀመረ።

«ሃኪም ቤት ወረፋ ይኖር ይሆናል።....እንዴት በባዶ ሆዳችን እንወጣለን?!.....» እያለ ተነፋነፈ።

«ግማሽ ቀን ጾምህን ብትውል ትሞታለህ እንዴ?! አሁንማ አንደኛውን መጋዣ ሆነሃል» በማለት እናትየው ተቆጥተው እየገፉ ወደ ሳሎን ወሰዱት። «በል አሁን መጀመሪያ ሰማይነህ ጋ ደውልለት። ወርቅ ቤት ካጣኸው ላይኛው ሱቅ አይጠፋም።.....ቶሎ ድረስ በለው» አሉት።

ህይወት ስራዋን ስለምታውቅ፣ እነሱ ከስልኩ ጋር ሲታገሉ ሳቋ መጣባትና እንዳይታወቅባትን አንገቷን ደፋች።

«ስልኩ ተበላሹታል መሰለኝ.....ድምፅ የለውም» አለ ጎርፉ እየተነፋነፈ።

«ደጋግመህ ሞክረው እስኪ!.....» አሉት አሮጊቷ።

«ተበላሽቷል ስልኩ!.....ምንም ድምፅ የለውም። ከፈለግሽ አዳምጪ፣ ይሄውልሽ!»

«ብልሽቱ ከኛ ነው ወይስ ከወዲያ?....»

«ከኛ ነው እንጂ!.....»

«እንግዲያውስ ከጎረቤት ስልክ ብሞክርስ?»

እዚህ ላይ ህይወት ፈጠን ብላ ድምጿን አሰማች።

«እባካችሁ ጎረቤት አታስቸግሩ። የኔንም ስቃይ አታብዙብኝ፤ ቶሎ ብላችሁ ወደ ሃኪም ቤት ውሰዱኝ። ካሁን በፊት ከሰማይነህ ጋር የሄድንበት ሃኪም ቤት እኔ አሳያችኋለሁ.....ሃኪም ዘንድ ሳልደርስ ፅንሱ እንዳይበላሽ እየፈራሁ ነው» አለቻቸው፣ ድምጿን የህመምተኛ አስመስላ።

«በል እሺ፤ ጎርፉ መኪናውን አሙቅ» ብለውት አሮጊቷ ወደ ክፍላቸው ተመልሰው በፍጥነት ተዘገጃጅተው ወጡ።

ህይወትም እንደ በሽተኛ እግሮቿን እየጎተተች የጎርፉ ታክሲ ውስጥ ገብታ፣ አሮጊቷ ትከሻዋን ደገፍ አድርገዋት የውጭውን በር ሊያልፉ ሲሉ

«ምነው?.....አመማቸው እንዴ? አለ ዘበኛው

«አዎ፤ ሃኪም ቤት እየወሰድናት ነው። ምናልባት ሰማይነህ ተመልሶ ከመጣ ካሁን በፊት ከሱ ጋር የሄዱበት ሃኪም ቤት መሄዳችንን ንገረው። ፈልገነው ነበር፤ ስልካችን ተበላሽቶ ነው.....በል ግቢውን አደራ» አሉት አሮጊቷ።

ህይወት በሃሳቧ ቶሎ የመጣላት ዩኒቨርሳል ክሊኒክ ነው። ካሁን በፊት ስለምታውቀው የምርመራ ቦታና ሽንት ቤቱ የተራራቀ መሆኑን አስባ ለማምለጫ ዘዴዋ የሚጠቅማት ቦታ መሆኑን ገመተች። ታካሚም የሚበዛበት ቦታ በመሆኑ ትርምሱን ፈልጋዋለች። ጎርፉ በርሷ እየተመራ ዩኒቨርሳል ክሊኒክ በር ላይ ወስዶ መኪናውን ቀጥ አደረገ።

«አዬዬ......ቀለበቴን መታጠቢያ ቤት ውስጥ ረስቼው መጣሁ አለች ህይወት እያቃሰተች።

«ክፍላችሁን አልቆለፍሽውም እንዴ?.....ለነገሩ ማን ያነሳዋል ብለሽ ነው?!» አሉ የሰማይነህ እናት።

«......ይጠፋል ብዬ ሳይሆን.....ጣቴ ላይ ቀለበት ካላዬ ሃኪም ሊያስቸግረኝ ይችላል።»

«ምን አድርጊ ብሎ?!.....»

«ምን ይታወቃል......የወንዶች ነገር አይታወቅም። እኔ ምንጊዜም ወንዶችን የምከላከለው ቀለበቴን እያሳየሁ ባለ ትዳር መሆኔን በመግለፅ ነው።»

«ታዲያ ወደ ቤት ተመልሰን እናምጣው እንዴ?....»

«የለ፤ እኔና እርሶ እንግባ። እኛ የህክምና ወረፋ እስኪደርሰን ድረስ ጎርፉ ወደ ቤት ተመልሶ ቀለበቴን ሊያመጣልኝ ይችላል።»

«እሱም ጥሩ ዘዴ ነው» አሉ አሮጊቷ።

«ባኞ ቤት ውስጥ የፊት መታጠቢያ ሸክላ ላይ ታገኘዋለህ አለችና ህይወት የመኝታ ቤታቸውን ቁልፍ ለጎርፉ ሰጠችው።

ጎርፉ ባጋጣሚው ተጠቅሞ ቁርሱን መብያ ጊዜ ስላገኘ ደስ ብሎት ባስቸኳይ አውርዷቸው ተመለሰ። «አንዱን ጠባቂ ዘበኛ ከአጠገቤ አባረርኩ» አለች ህይወት በልቧ።

«ፍራንክ ይዘሻል እንዴ?....» አሉዋት አሮጊቷ ቦርሳቸውን ከፍተው እየደባበሱ። ሰማይነህ ገንዘብ እሷ ጋር እድነምያስቀምጥ ያውቃሉ።

«ኧረ ትንሽ ብር እንው ያለ፤ አይበቃኝም» አለቻቸው።

የሃምሳ ብር ኖት መዘው ሰጥተዋት አብረዋት ወደ ክሊኒኩ ምዝገባ ክፍል ገቡ። አንድ ቦታ ልታስቀምጣቸው ብትሞክርም እምቢ ብለው ተከተሏት። ዓይናቸው እያየ መመዝገቢያ ከፍላ ሽንትና ሰገራ የምትሰጥበት ብልቃጥ ወሰደች።

«ሽንትና ደሜን እስክሰጥ ድረስ እዚህ ቁጭ ብለው ወረፋዬን ያድምጡልኝ» ስትላቸው ተረጋግተው፣ ለወሬ እንዲመቻቸው በእድሜ የሚቀርቧቸውን አንድ ሴትዮ ጠጋ ብለው ተቀመጡ።

ህይወት ብልቃጧን ይዛ በቀሰስተኛ እርምጃ ደረጃውን እየወረደች ወደ ሽንት ቤት ሄደች።

አንደኛው መፀዳጃ ክፍል ውስጥ ገብታ ከውስጥ ከቆለፈች በኋላ ዝግጅቷን በፍጥነት አከናወነች። ከላይ የደረበችውን ጋቢና ያጠለቀችውን እረዥም አሮጌ ቀሚስ አውልቃ ወደ ጥግ ጣለችው። ሻሿን ፈትታ ፀጉሯን ካበጠረች በኋላ የፀሀይ መነፅሯን ከቦርሳዋ አውጥታ አደረገች።

በጋቢና በሻሽ ተጀቡና አሮጊት መስላ የገባችው ወጣት «ጆሊ» ሆና እየነጠረች የክሊኒኩ ግቢ ለቅቃ ስትወጣ ማንም አላወቃትም። የሰማይነህም እናት ወሬያቸውን እየሰለቁ ባይናቸው ውጭ ውጭውን ማየት ባያቋርጡም፣ ድንገት ውልብ ያለችባቸው ባለ ጅንስ ሱሪና ባለ መነፅር ወጣት ህይወት መሆኗን በፍፁም አልጠረጠሩም።

ህይወት አካባቢውን እስከትለቅ ድረስ እየተሳቀቀችና ከኋላዋ መጥተው «ጋማዋን» የሚይዟት ይመስል እየደነበረች ታክሲ ተሳፍራ ወደ ካዛንችስ አመራች......

ህይወት ወደ አክስቷ ግቢ ከማምራቷ በፊት ለአንድ አፍታ ቆም ብላ አሰበች። በአክስቷ ላይ እምነት ሊኖራት አልቻለም። ፈራች። ሆኖም ግን ሌላ መሄጃ የላትም። ከዚህም ሌላ አሳዳጊ እናት እንደ መሆኗ መጠን ‹ችግሬን አምርሬ ብነግራት በዚህ በቀውጢ ሰአት ታዝንልኝ ‹ይሆናል› በሚል ሀሳብ ተደፋፈረች። ‹ይህም ካልሆነ አስጨርሻት እለያያለሁ፤ አርተፊሻል እናትነቷ ምንም አይሰራልኝም። ብላ ዛተች። ፍርሀትና ጥርጣሬዋን በአዕምሮዋ እንደ ተሸከመች ምርጫ ማጣቷ በደመ ነፍስ እያንቀሳቀሳት ተጓዘች።

ህይወት አክስቷ ቤት ስትደርስ ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለና ልቧ ከፉኛ እየመታ ድንጋጤው ፊቷ ላይ ይነበብ ነበር። ወይዘሮ ስራሽ እራሷን አመም አድርጓት ተኝታለች። የመጣችው ሴት ህይወት ባትሆኖ ኖሮ ማንንም ከመኝታዋ ቀና ብላ ማነጋገር አትፈቅድም ነበር።

«ምነው?!.....ምን ሆነሻል?!.......ሰላም አትመስይም፤ ህይወቴ» አለቻት ከአንገቷ ቀና ብላ ትራሱን እየተደገፈች።

«አዎን፤ ሰላም የለኝም። ሰላም ካጣሁ ቆይቻለሁ። አሁን ግን ላንዴም ለመጨረሻም ከሰማይነህ ቤት ወጥቼ መጥቻለሁ» አለች ህይወት ድንጋጤና ድፍረት ተደባልቀው እንደማንቀጥቀጥ እያደረጋት።

«እስቲ ለማንኛውም ቁጭ በይና በእርጋታ ታጫውቺኛለሽ። ምንድነው የሆንሽው?»

«ቁጭ የምልበት ፋታ የለኝም፤ ረጋም የምልበት የተረጋጋ አእምሮ የለኝም። እነሰማይነ ተከታትለው ሊፈልጉኝ መምጣታቸው አይቀርም። አሁን አንቺን የምለምንሽ ለተወሰኑ ቀናት የምደበቅበትን ቦታ እንድታዘጋጂልኝ ነው። ሚስጥር ሊጠብቅ የሚችል ዘመድ ወይንም ወዳጅ ቤት

ውስጄኝና ደብቂኝ። ባንቺ በኩል ካልሆነ በስተቀር እኔ የማውቀው ሆነ የምቀርበው ዘመድ የለኝም። .....»

«እንዴ!....በሰላም ሀገር መደበቅን ምን አመጣው?!.....ወንጀል አልፈፀምሽ። ከባልሽ ጋር ካልተስማማሽ በሽማግሌ ፊት ቁጭ ብላችሁ ባደባባይ ትስማማላችሁ ወይንም ትለያያላችሁ......እንደ ህፃን ልጅ የምን ድብብቆሽ ነው እሱ?!»

‹እንደዚህ ሊሆን አይችልም እማዬ። ሽማግሌ ሆነ ፍርድ ቤት አያስፈልገኝም። መጥፋት ብቻ ነው መፍትሄው።»

«ይሄማ የልጅነት አስተሳሰብ ነው። አሁንም ገና አላደግሽም ማለት ነው?!.....» አለቻት፤ እንደ መቆጣት እያደረጋት።

«ህፃን ልጅም ቢሆን ሊያርዱት ቢላዋ ሲስሉ በዝምታ አንገቱን አይሰጥም» አለች ህይወት ግምባሯን አኮሳትራ በምፀት ድምፅ።

«አሁን መታረድን ምን አመጣው?.....»

«እንግዲያውስ እቅጩን ልንገርሽ.....በውድቅት ለሊት ጩቤ ይዞ ቆሞ ሊያርደኝ ሲል ነው የነቃሁት።»

«ማ?.....ሰማይነህ?» አለች ምንም ሳትደንግጥ።

«አዎ፤ ሰማይነህ!»

«እንዲያው ሊያስፈራራሽ ፈልጎ ይሆናል እንጂ ጨክኖ እንኳን አያደርገውም። ያፈቀረ ወንድ ይሄው ነው። በምኑም በምኑም በጠረጠረና በቀና ቁጥር ስለት አንስቶ ማስፈራራት ወይንም ሽጉጥ አውጥቶ ማስደንገጥ ልማዱ ነው። ታዲያ እኮ ስለቱን አይሰነዝርም፤ የሽጉጡንም ቃታ አይስብም....›.

«ምነው እማዬ?!.....»

«ቆይ እኮ አምጭኝ። አትቸኩይ እንጂ......ሰማይነህን በደንብ ስላወኩት እኮ ነው ይህንን የምልሽ። ላፈቀራት ሴት የሚሞት ወንድ እሱን አየሁ። እንዴት እንደሚወድሽ ዝክዝክ አድርጎ ነግሮኛል። ባንቺ ላይ ስለት ሊያሳርፍ ቀርቶ ትንሽ እንዲነካሽ እንኳን አይፈልግም። አብረሽው ስትኖሪ ይሄንን ያህል ስለሱ ማወቅ ነበረበሽ።»

ህይወት በአንድ አፍታ ፊቷ ጥቀርሻ ለበሰ። ውስጧ እያመረረ ሲመጣ ተሰማት። የሰማይነህ እናት ጭራቅ እንደሚመስሏት ሁሉ አሁን ደግሞ የራሷ አክስት ለጥቅሟ ብቻ የቆመች ልዩ አውሬ መስላ ታያቻት። ጥቅም አሳብዷት ዓይኗንም፣ ህሊናዋንም ጋርዷታል። በአማትነቷ ሳቢያ የሰማይነህ ሀብት የሷ ሀብት እየመሰላት ሳይመጣ አልቀረም። ስለዚህ መከራከር ምንም ዋጋ እንደሌለው ህይወት ተረዳች። ሳታስበው ጥላቻዋን በገፅታዋ ላይ እያሳየቻት መጣች።

«ልታደምጪኝ ትችያለሽ እማዬ!....ከዚህ በኋላ ስለ ሰማይነህ ምንም ነገር መስማት አልፈልግም። አንቺን ለመጨረሻ ጊዜ የምለምንሽ ላጭር ቀናት እንትደብቂኝ ብቻ ነው» አለቻት ጉሮሮዋ ላይ የንዴት ሳግ እየተናነቃት።

ወይዘሮ ስራሽ በበኩሏ ህይወት በያዘችው መንገድ ማባበልና ማስታመም የበለጠ ሆድ ማስባስ መስሎ ታያት። ይህም ደግሞ ባሰበችው የመጥፋት አላማ አንድትፀና ስለሚያደርጋት ፊት መስጠት አያስፈልግም ከሚል መደምደሚያ ላይ ደረሰች። አሁንም እንደ ጥንቱ እንደ ልጅነቷ ስላየቻት ገሰፅ፣ ቆጣ ማድረግ አስፈላጊ መስሎ ታያት።

«እኮ ቁጭ በይ ነው የምልሽ!....የምን መቆናጠር ነው እሱ?! ረጋ ብለሽ እንደ ትልቅ ሰው ሚስት አስቢ እንጂ ሁሌ ልጅነት የለም ብየሻለሁ። በወግ በማዕረግ እንደዳርኩሽ በክብር ትለያያለሽ እንጂ መደበቅና መጥፋት የምትይው አጉል ፈሊጥ ለኔ አይገባኝም» አለቻት ተኮሳትራ።

«እኔና ሰማይነህ በሽማግሌ ፊት በክብር ልንለያይ አንችልም። በጥንቆላ ላይ የተመሠረተ እምነት ይዞ እኔን የዘላለም ባርያው ሊያደርገኝ መወሰኑን ደርሽበታለሁ። እኔ ለሱ ከእጁ መውጣት የሌለብኝ ውድ እቃ ነኝ። በምንም ተዓምር ሊለቀኝ አይፈልግም» በማለት ህይወት ፍርጥርጥ አድርጋ ነገረቻት።

«ይህን ደግሞ ማን ነገረሽ?!.....» አለቻት ወይዘሮ ስራሽ ስለ ጠንቋዩ ሲነሳ ደንግጣ።

«መላዕከት ነገሩኝ። እኔም የንፅህናዬ አምላክ አለኝ።»

«ለነገሩስ ይህን ያህል የሚያስመርር ምን በደል ደረሰብሽ?.....አንዴ ተሳስቶ ጥርስሽን ቢያወልቅ በድርጊቱ አዝኖ ካሳ ከፍሏል። በተረፈ የሞላ የተትረፈረፈ ቤት ውስጥ መሆንሽን አውቃለሁ። እኔም በየጊዜው ስለ ኑሮሽና ጤናሽ እከታተላለሁ። ምን አጣሁ ብለሽ እንዲህ እንደምትሆኚ አይገባኝም!.....እስቲ ንገሪኝ.....ምን አጣሽ?!......» አለቻት፣ አልጋዋ ላይ እንደሆነች በአንድ እጇ ወገቧን ይዛ እየተቆጣች።

ህይወት በአክስቷ ላይ እምነቷን እያሚጠጠች ሄደች። በዚህ አኳኋኗ እጇን ይዛ ለሰማይነህ መልሳ እንደምታስረክባት ገመተች። ይህንን ባታደርግም በሽማግሌ አስታርቃና ሽምግላ ወደ እስረኝነት ኑሮዋ እንደምትመልሳት አወቀች። በምንም መንገድ መሸሻ መደበቂያ ልትሆናት እንደማትችል እዚያው የቆመችበት ቦታ አስባ ወሰነች። ጥላቻዋ እየበረታ ሄዶ በአክስቷ ላይ ያመፅ አይኖቿን አፈጠጠጭ።

«ሁሉንም ነገር ነው ያጣሁት!.....ነፃነት አጣሁ!......ፍቅር አጣሁ!.....ፍትህ አጣሁ!......ገና በወጣትነቴ ቅስሜ እንዲሰበርና አንገቴን እንድደፋ ተደረግሁ። የቤት ውስጥ እቃ ተደረግሁ!.....የቤት እቃ ታውቂያለሽ ወይዘሮ ስራሽ?!......ይሄ ላንቺ አይገባሽም።»

«አዎ፤ አይገባኝም። ሙሉ ቤት ጥሎ፣ የተንቀባረረ ትዳር ገፍቶ ሸሽቶ አይገባኝም።.....ይሄ ቅብጠት ነው፤ ጥጋብ ነው።»

«ጥጋብ አይደለም፤ እጦት ነው!.....የፍቅር እጦት ነው!.....የነፃነት እጦት ነው!......የፍትህ እጦት ነው!.....»

«ምንም ያጣሽው ነገር የለውም።......ያ ነገሩ አንሶሽ እንደሆነ እንጃልሽ!»

ህይወት አክስቷ አፍ እንዲህ አይነቱ ብልግና በመውጣቱ በጣም አዘነች። እንደ ተራ የቡና ቤት ሴት ቆጥራ ናቀቻት። ‹ይህንን ያህል የጨከነችብኝ ስላልወለደችኝ ነው፤ በማለት ስሜቷን ይበልጥ አመረረች። ‹እማዬ› ማለቷን አቁማ ለመጀመሪያ ጊዜ አክስቴ አለቻት።

«አልፈርድብሽም አክስቴ!.....ህሊናሽ በጥቅም ታውሯል።.....እኔ ግን በቃኝ!.....መሮኛል!.....ነፃነቴን እፈልጋለሁ.....ነፃነቴ ይበልጥብኛል!......ካንቺም ጋር በቅቶኛል!.....» ብላ ጥላት ለመሄድ ፊቷን አዞረች።

ከሀያ አመት በላይ ‹እማዬ› ስትላት የኖረች ልጇ አሁን በመረረ ድምፅ ‹አክስቴ› ስትላት ወይዘሮ ስራሽ እራሷን በዱላ የተመታች ያህል ክው ብላ ቀረች። ህይወትን ተቆጥታ የምትመልሳት እንጂ አስመርራ እዚህ ደረጃ ላይ የምታደርሳት አልመሰላትም ነበር። አንዳች ከባድ የሃዘንና የፀፀት ስሜት ስለ ተሰማት ባለቀ ሰዓት ልታባብላት ሞከረች።

«እኔ እኮ ላንችው ብዬ ነው ህይወትዬ። ምነው እንዲህ አመረርሽ?.....ቆይ እስኪ ረጋ በይ.....አሁን ወዴት ልትሄጂ ነው?......ነህ ብዬሻለሁ ኋላ!.....»

ህይወት እንደ እብድ አደረጋት። ይህቺ ውብ ፍጡር የደም ስሮቿ በቁጣ አባብጠውና ፀጉሯ ቆሞ ፊቷ ከሰል መሰለ። ከንፍሯ፣ ምላሷ፣ ጉሮሮዋ.....ለሁለመናዋ ደረቀ።

«አልመጣም! በቃሽኝ አክስቴ!......ስላልወለድሽኝ በጥቅም ለወጥሽኝ!.....ለጥቅምሽ ሸጥሽኝ!......ከእንግዲህ አንገናኝም፤ በቃሽኝ!.... ህሊናሽን ያጭበረበረውን ወርቅ እኔም ይዤዋለሁ፤ ይሄውልሽ!.....» ብላ ከኪሷ ውስጥ ወርቋን አውጥታ እያቅጨለጨለች ከሩጫ ባለነሰ እርምጃ ግቢውን ለቃ ሄደች። ወይዘሮ ስራሽ ካልጋዋ ወርዳ እያባበለች ልትከተላት ብትሞክርም አልደረሰችባትም። ድንጋጤና ፀፀት አድርቀው አስቀርተዋት የውጪው በር ላይ እንደቆመች ያሳደገቻት ልጇ ከአይኗ ርቃ ሄደች።

ህይወት ከዚህ በኋላ ወዴት እንደምትሄድ አታውቅም ከአክስቷ ጋር ሊፈጠር የሚችለውን ያለመግባባት አስቀድማ ሳትገምት ከሰማይነህ ቤት ጠፍታ መውጣቷ አሁን ተሰማት ‹ልክ አይደለሁም› ብላ መፀፀት ግን አልፈለገችም። በምንም መንገድ ቢሆን ከሰማይነህ ቤት መውጣት ነበረባት። ከአሁን በኋላ ወደ ኋላ የምታይበት ዓይን የላትም። በፍፁም! ወዴትም ቢሆን ወደፊት መገስገሷን መረጠች። ለዚህ ችግር ጊዜ የሚሆናትና ሚስጥሯን የሚጠብቅላት ዘመድ ወይም ጓደኛ በአዕምሮዋ ስታስብ አጣች። በተለይ አክስቷ ቤት በምትኖርበት ጊዜ ብዙ ሰው ታውቃለች። ነገር ግን ለዚህ ጊዜ የሚሆናት አንድም ሰው አንጥራ ማውጣት አልቻለችም። ሴት ሚዜዎችዋ ድንገት ትዝ አሉዋት፤ ልትተማመንባቸው ግን አልቻለችም። ለማንኛውም መጀመሪያ መደምደሚያን ፈልጋ ማግኘት እንዳለባት ወሰነች።

ባዶዋን የምትበር አንድ አነስተኛ ታክሲ አስቁማ ወደ ስድስት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ እንዲወስዳት ጠየቀች።

«ምን ያህል ትከፍያለሽ?» አላት ወጣት ባለታክሲው።

«አንተ ስንት ነው የምታስከፍለው?» አለችው፣ ዋጋውን እንዳያከብድባት በሚያስተዛዝን ድምፅ።

«ኮንትራት ስለሆነ.....ያው አስር ብር ትከፍያለሽ።»

አሁን የቆመችው ካሳንችስ ሰፈር ወደ ውስጥ ገባ ብላ ነው ትላልቅ ታክሲዎች የሚቆሙበት ቦታ ወጣ ብትልና ሁለት ታክሲ ብትይዝ በንትሽ ገንዘብ ካሰበችው ቦታ መድረስ ትችላለች። ነገር ግን ጠፍታ የምትሄድ ሴት እንደ መሆኗ መጠን ከሌሎች ጋር ሳትጋፋና ማንም ሳያያት በኮንትራት ታክሲ መሄዱን መረጠች።

«ከአምስት ብር በላይ ልከፍል አልችልም።.....በቂ ገንዘብ አልያዝኩም» አለችው።

«እሺ ግቢ። መንገድም ላይ ሰው ካገኘውሁ እጭናለሁ» ብሎ የፊት በሩን ከፈተላት። አይኖቹን ፊቷ ላይ ተክሎ በልቡ ‹አንቺን መሳይ ቆንጆ ማስቀየም አያስፈልግም› እያለ ነበር።

«የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነሽ?.....» አላት ጉዞ ከጀመሩ በኋላ።

«አዎ» አለችው ህይወት ነገር ላለማራዘም።

«የስንተኛ አመት ተማሪ ነሽ?»

«ምን ያደርግልሃል?......»

አመላለሷ የመሰልቸትና ‹ትጨቅጭቀኝ› የማለት ያህል ነበር የእሷም አዕምሮ በስጋትና በጭንቀት ተወጥሯል። ባለ ታክሲውም ደግሞ ውበቷን እያደነቀ በንግግር ሊቀርባት ፈልጓል። ቶሎ ብሎ ጣቶቿን ሲመለከት ቀለበት አላደረገችም። ስለዚህ ‹.....ማን ያውቅላ በለስ ይቀናኝ ይሆናል› እያለ ልቡ መዝለል ጀምሯል።

«ስትመረቂ እንድትጋብዢኝ ነው.....አበባ ይገባልሽ እመጣለሁ» አላት መሪውን እንደያዘ በስርቆት እየተመለከታት።

ህይወት ሳቋ ለጥቂት ደቂቃዎችም ቢሆን ጭንቀቷን ሳያስረሳት አልቀረም። ልቡ እንደ ከጀላት ወዲያው ገባት። ተሳፋሪዎች ሊያስቆሙት እጃቸውን ሲያወዛውዙ አላያቸውም፣ ወይንም ሊያያቸው አልፈለገም። በርግጥ ገና ወጣት ነው። ሆኖም ግን ‹ድንገት መንገድ ላይ ለጫናት ሴት ሁሉ ልቡ ከደነገጠ እንዴት ይዘልቀዋል? ስራውንስ እንዴት ይሰራል?› ብላ ስታስብ ነበር። የህይወት ሳቋ የመጣባት።

ህይወት ስትሰቅ ባለ ታክሲው የወርቅ ጥርሷን በጨረፍታ ተመልክቶ ‹ጥርሷን ያወለቃት አንዱ በውበቷ የሰከረ መሆን አለበት› ሲል አሰበ። ቁንጅናዋን ሊገልፅላት አስቦ ቃላቶች ሲመርጥ እሷ ቀድማ ተነፈሰች።

«ይገርማል.....በምን እዳህ....» አለችው፣ በምፀት

«ምኑ?....» አላት እሱም የተናገረው ጠፍቶት።

«ምናለበት፣ እንኳን ደስ ያለሽ ማለት አይከለከልም።»

«ማለቴ.....ካሁን በፊት ትውውቅ የለንም ብዬ ነዋ።»

«መቼስ ሰውን የሚያስተዋውቀው አጋጣሚ ነው» ህይወት ትንሽ ስታስብ ቆየችና ድምጿን ለውጣ «ወንዶች ስትባሉ ትገርሙኛላችሁ!» አለችው።

«እንዴት?.....» አላት ምንም ሳይደነግጥ

«ሴቶች እንዲሁ ከየመንገዱ ታፍሰው የሚወሰዱ ፍጡራን አድርጋችሁ ትገምታላችሁ....»

«አ....አልገባኝም።»

«ለማታውቋት ሴት ልባችሁ ሲደነግጥ ይገርመኛል።»

«ምን ይደረግ ትያለሽ?.....አይን አይቶ ልብ መደንገጡ አይቀር.....»

«ጥሩ ቀሚስና ቆንጆ መልክ ብቻ ያስደነግጣችኋል»

«ታዲያ ሌላ ምን ያስፈልጋል?»

«ፀባይ.....የአስተሳሰብ መቀራረብ.....የፍላጎት መጣጣም.....የስሜት መገጣጠም.....ብዙ ብዙ ነገር አለ። እናንተ ግን ድንገት ዓይናችሁ ያረፈበትን ዕቃ የመግዛት ያህል ብቻ ነው የምትጓጉት።»

«አንቺ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ስለሆንሽ ነው እንጂ ብዙ ሴቶች ይህን ያህል ጠልቀን እንድንመርምራቸው አይፈልጉም። መልካቸውንና ቀሚሳቸውን ካደንቅንላቸው በቂ ነው።.....»

«ከዚያ በኋላ የቤት ዕቃ ወይንም የአደባባይ ጌጥ ታደርጓቸዋላችሁ.....አይደል?» አለችው በንዴት፣ ሰማይነህ በሃሳቧ እየታወሳት።

«የሌሎች ወንዶች እንጃ....እኔ ግን ሴቶችን እንደ ዕንቁላል መንከባከብ የምወድ ሰው ነኝ። ለማንኛውም አደራሽን ስትመረቂ እንዳትረሺኝ» አላት፣ መውረጃዋ ቦታ መድረሱ እያናደደው።

«አይዞህ አልረሳህም» አለችው ህይወት ከአንገት በላይ በሆነ አነጋገር።

«ታዲያ የት አግኝተሽ ትሰጪኛለሽ?......» አላት ድርቅ ብሎ። ህይወት ኮስተር ስላለችበት አነጋገሩን ለማስተካከል ሞከረ። «የጥሪው ወረቀት ማለቴ እኮ ነው.....የእኔን አድራሻ ውሰጂ፣ ወይንም የአንቺን አድራሻ ስጭኝ»

«የአንተ አድራሽ ምንም አያደርግልኝም። የእኔ አድራሻ ይኸው እዚሁ ነው። ከፈለግከኝ ዩኒቨርሲቲ በር ላይ እየመጣህ መቆም ብቻ ነው» ብላ ቀልዳበት አምስት ብሩን ወርውራለት ወረደች።

ባለ ታክሲውም «ዛሬ በለስ አልቀናኝም» ብሎ እያዘነ መኪናውን አዙሮ ተመለሰ።

«ሰው ፈልጌ ነበር.....ልትረዱኝ ትችላላችሁ? «አለች ህይወት፣ በር ላይ ወደ ቆሙት የዩኒቨርሲትው የጥበቃ ኃይሎች ተጠግታ።

«ተማሪ ነው ሰራተኛ?»....አላት አንደኛው።

«ተማሪ.....» አለችው በልመና ድምፅ።

ወደ ውስጥ ከሚገቡት ተማሪዎች መሀል አንዱን አስቁሞት እሱን ጠይቂው ያስጠራልሻል አላት።

«መደምደሚያ ሽብሩ የሚባል ተማሪ ፈልጌ ነበር» አለችው ተማሪውን ተጠግታ።

«የምን ዲፓርትመንት ተማሪ ነው?.....የስንተኛ አመት ተማሪ ነው?»

«የመጀመሪያ ድግሪውን ይዟል....አሁ ለ‹ማስተርስ› እያጠና ነው»

«አሃ.....እንግዲያው ድህረ ምረቃ ሄደሽ ብትጠይቂ ታገኚዋለሽ። እነሱ ብዙ ስላልሆኑ ሊያውቁት ይችላሉ።»

ህይወት ዩኒቨርሲቲ ሲባ የሚታያት ስድስት ኪሎ ብቻ ነው። የድህረ - ምረቃውን ቦት እንደማታውቀው ለተማሪው ገልፃለት በጣቱ ሳይቀር እየጠቆመ አስረዳት።

ቁልቁለቷን ወረድ ብላ ከቦታው ስትደርስ በተመሳሳይ መንገድ በር ላይ የቆሙትን የጥበቃ ኃይሎች ጠይቃ፣ እነሱም ከአንድ የድህረ ምረቃ ተማሪ ጋር አገኟት። አሁን የህይወት ልብ በድንጋጤ መምታት ጀምሯል። መደምደሚያን ባታገኘው ወዴት ልትሄድ ነው? ከማንስ ጋር ልትመካከር ነው? ይህን ስታስብ መንገዱ ሁሉ ጭለማ እየሆነባት መስጋት ጀመረች። ከኪሷ የያዘችው ወርቅ ጊዜያዊ ችግርን ለማሳለፊያ እንደሚሆናት ብትተመመንም ሙሉ በሙሉ ሊያረጋጋት አልቻለም።

«መደምደሚያ አሁን የለም፣ ክላስ ሳይኖረው አይቀርም» አላት ተማሪው።

«ታዲያ እንዴት አገኘዋለሁ?» አለችው ህይወትም በአንድ በኩል መደምደሚያን የሚያውቅ ሰው ማግኘቷ አስደስቷት፣ በሌላ በኩል ደግሞ መደምደሚያን ማግኘት አስቸኩሏት።

«ለምሳ መምጣቱ አይቀርም።.....ሰባት ሰአት ላይ ብትመጪ ታገኚዋለሽ።» ሰዓቷን ተመለከተች። ገና አራት ሰዓት ከሩብ ነው። የሚቀጥሉትን ሦስት ሰዓቶች የት ተደብቃ እንደምታሳልፍ እየጨነቃት «እሺ በዚያ ሰዓት እመጣለሁ» አለች።

«ስምሽን ማን ለበል?....መልዕክት ካለ ልነግርልሽ እችላለሁ።» ህይወት ለጥንቃቄ ያህል ስሟን መናገር አልፈለገችም።

«ግድ የለም፤ ሰማት ሰዓት ላይ ብቻ እንዲጠብቀኝ ንገርልኝ። ስለ ትብብርህ አመሰግናለሁ» ብላው ወደ ኋላ ተመለሰች።

በምሳ ሰዓት ባይሳካላት እንኳ ማታ ሲገባ አጥምዳ ልትይዘው እንደምትችል በመገመት ትንሽ ተፅናናች። እስከዚያ ሰዓቱን ልትገድል የምትችልበት ቦታ ስታስብ ድሮ ከሄኖክ ጋር የሚገናኙበት አንድ ሻይ ቤት አራት ኪሎ መኖር ትዝ አላት።

ትልቅ ታክሲ ባየች ቁጥር እነ ጎርፉ የመጡባት እየመሰላትና እየተሸማቀቀች፣ በአደባባይ ራሷን ለመደበቅ እየሞከረች፣ ወደ ኋላዋ እየተገላመጥችና ግራ ቀኙን እያማተረች ቁልቁለቱን ወረደች።....

የሰማይነህ እናት ህይወት ጠፍታባቸው የክሊኒኩን ግቢ ሲያስሱ፣ ጎርፉ ቀለበቷን ይዞ ፊቱ ፈክቶ ተመለሰ።

«.....ይህን ያህል ሰዓት ምነው ቆየህ?» አሉት እናትየው በቁጣ።

«ቁርስ ስቀማምስ ነዋ» አላቸው ኩርፊያው ለቅቆት።

«አፈር ብላ.....እኔ እዚህ ልጅቷ ጠፍታብኝ መከራዬን አያለሁ፤ አንተ እዚያ ቀርተህ ሆድህን ታሳድዳለህ.....»

«ማ?.....ህይወት?....»

«አዎ የህክምና ተራዋ ደርሶ ስሟ ቢጠራም የለችም፤ ሽንት ቤት አካባቢ ብናስጠራትም የለችም።.....ወደ ውጪ ወጣች እንዳይባል እኔ ዓይኔን ተክዬ ስጠብቃት ነበር።»

«ቅድም እንደፈራችው.....ቀለበቷን ባለማድረጓ.....ሐኪሙ አስቸግሮአት አቆይቷት ይሆን እንዴ?....» አለ ጎርፉ ቀለበቷን ይዞ እንደ ተገተረ።

«አትሰማኝም እንዴ?.....ሐኪሙ ጋ አልደረሰችም እኮ ነው የምልህ። እኔ ሁሉም አጠያየኩ እኮ....»

«ታዲያ ምን ዋጣት ይባላል?»

«ጉዱ እሱ አይደል?»

አሮጊቷና ጎርፉ የክሊኒኩን ሠራተኞችና ግቢውን ሲያምሱ ከቆዩ በኋላ መፀዳጃ ቤቶች ውስጥ እየገቡ ሲፈትሹ አንደኛው ክፍል ውስጥ የተጣለውን ጋቢ፣ ቀሚስና ሻሽ ተመለከቱ። በተለይ ቀሚሱና ሻሹ ህይወት ለብሳው የነበረው ለመሆኑ ምንም አልተጠራጠሩም። ሁለቱም በድንጋጤ ክው ብለው ቀሩ። አንዳቸው ከሌላቸው መልስ ያገኙ ይመስል ተፋጠው ተያዩ።

«ራቁቷን የት ሄደች ታዲያ?......ሽንት ቤት ጉድጓድ ውስጥ ገብታ ይሆን እንዴ?» አለ ጎርፉ።

«ጠጠር አደረካት እንዴ! በዚህች ቀዳዳ የምትሾልከው?»

«ካለበለዚያ አዕምሮዋን ነካ አድርጓት እርቃኗን አስኪዷት ይሆናል።»

«እንደሱ ቢሆንማ ራቁቷን ስትሄድ አይተው ሰዎች ‹ጉድ› ሲሉ እሰማ ወይም እመለከት ነበር።
»

«ታዲያ የት ገባች ይባላል?.....»

«አታልላን ማምለጧ ይሆናል እንጂ......ግዴለህም ሳትጫወትብን አልቀረችም። ወጥተን ብንፈልጋት ይሻላል» አሉ የሰማይነህ እናት እየተቆናጠሩ።

«የት ብለን እንፈልጋታለን?.....እንደኔ እንደኔ ከሆነ እዚሁ ግቢ የተደበቀች ይመስለኛል። አጥምደን ብንጠብቃት አታመልጠንም» አላቸው ጎርፉ፣ ከጣራው ስር የሚያወርዳት ይመስል ዓይኖቹን በልጥጦ እያማተረ።

«እባክህ ተወኝ ጃል ጉድ ሆነናል» ብለው እናትዬው እየተቻኮሉ ከግቢው ሲወጡ ጎርፉ ተከተላቸው።

ለምናልባቱ ብለው በር ላይ ለቆመው ዘበኛ አስር ብር ጉርሻ ሰጥተውት፣ የህይወትን መልክና አንድ ጥርሷ ወርቅ መሆኑን አስረድተውት፣ ተደብቃ ቆይታ ልትወጣ ከሞከረች እንዲይዝላቸው አደራ ብለውት ሄዱ።

«አሁን ወዴት ትንሂድ?» አለ ጎርፉ ግራ ተጋብቶ።

«እስኪ ወደ አንቷ ቤት ንዳ። ሌላ የት አባቷ ትሄዳለች?» አሉ አሮጊቷ እየተበሳጩ።

በፍጠንት እየሾፈረ ወይዘሮ ስራሽ ቤት እንደ ደረሱ ከመኪና ሳይወርዱ የውጭው በር ላይ አስጠሯት።

«ያቺ ጉድሽ ወንዳንቺ አልመጣችም?» አሏት አሮጊቷ የእጊዘር ሰላምታ እንኳ ሳይለዋወጡ።

ወ/ሮ ስራሽ ራሷ እንደተደናገጠች ያስታውቅባታል። «መጥታ ሄደች እንጂ....የፀቡ መንስኤ ምንድነው እሱ?.......እኔንም አበሻቅጣኝ ነው የሄደችው።.....አሁን እኮ የት ብዬ እንደምፈልጋት ግራ ገብቶኝ ነው። የእናንተ ስልክ ደግሞ ተበላሽቷል መሰለኝ፣ ብቀጠቅጥ ብቀጠቅጥ አይመልስም። እኔ ፊት ስለነሳሁዋት ምናልባት ወደ ቤቷ ተመልሳ እንደ ሆነ ብዬ ነዋ» አለቻቸው።

ፊት መንሳትሽ ጥሩ ነገር ነው። ግን ሌላ ማኩረፊያ ይኖራት ይሆን?»

«ኧረ በጭራሽ.....እኛ ያን ያህል የምንቀርባቸው ዘመዶችም የሉን»

«በል እንግዲያው ፈጥነህ ወደ ቤት ንዳልኝ.....» አሉት ጎርፉን።

«....ካገኛችኋት ደውሉልኝ፤ አደራ» እያለች ወ/ሮ ስራሽም በመርበትበት ከውጭ ሸኘቻቸው.....

ልባቸው ቁርጡን ለማወቅ ተቻኩሎ እየከነፉ ከመኖሪያ ቤታቸው ሲደርሱ ወደ ውስጥ ከመዝለቃቸው በፊት ዘበኛውን ጠየቁት።

«ህይወት ወደ ቤት አልተመለሰችም እንዴ?»

«ኧረ እንዲያውም፤ አልመጣችም» ብሎ አረዳቸው። ሁለቱም በቆሙበት ቦታ ሐውልት ሆነው ቀሩ። ለሰማይነህ ምን ተብሎ እንደሚነገረው ከወዲሁ ጨንቋቸው እንደገና ተፋጠጡ።

«አሁን ምን ይባላል?......እንዴት አይነት ጉድ ነው» አለ ጎርፉ እየተርበተበተ ላብ እያስመጠው።

«እግዚአብሄር ይይላት እንጂ ምን ይባላል!.....በጠዋት እንከራተተችን» አሉ አሮጊቷ ተስፋ በቆረጠ ድምፅ።

ግቢው ውስጥ ተመልሳ ድንገት ከሰማይ ዱብ የምትልላቸው ይመስል ሁለቱም ወገባቸውን ይዘው ግቢውን ሲዞሩ ቆዩ።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሰማይነህ ራሱ እየተከታለበ መጣ። መኪናውን አቁሞ ሲወርድ ሁሉ የመቻኮል ስሜት ይነበብበታል። የተፈጠረው ችግር ሰይጣን ጆሮ ሹክ ሳይለው አልቀረም። ወይም ደግሞ የቅናት ዛሩ ተነስቶበት ህይወት ላይ ሊጮህባት መምጣቱ ይሆናል። ብዙ ጊዜ እንደሚያደርገው ለቁጥጥር ያህል ከሱቁ ወደ ቤቱ ደውሎ ነበር። ስልኩ ምቢ አለው። ደጋግሞ ቢሞክርም ስላልሆነለት ነው መኪናውን አስነስቶ የመጣው።

«ስልኩ ምን ሆነ?......ብቀጠቅጥ ብቀጠቅጥ እምቢ አለኝ» አላቸው ከመኪናው እንደ ወረደ።

«ገና ጠዋት ነው የተበላሸው፤ እኛም ልንደውልልህ ሞክረን እምቢ አለን» አሉት አሮጊቷ፤ ድምፃቸው በፍርሀት እየተንቀጠቀጠ።

«እኔን ለምን ፈለጋችሁኝ?» ሲል፣ ሰማይነህም ጥርጣሬና ፍርሀቱ ፊቱ ላይ መነበብ ጀምሯል።

«እስቲ ለማንኛውም ወደ ቤት ግባ ልጄ....»

«ንገሩኝ እንጂ!.....ምን ተፈጠረ?!»

«ህይወት ሄደች.....አታልላን አመለጠች!» አለው ጎርፉ ከጭንቀቱ ብዛት አፉን መቋጠር አቅቶት፡፡ ሁኔታውን ሲያዩት ቶሎ ሀጢያቱን ተናግሮ ቅጣቱን ለመቀበል የተዘጋጀ ህፃን ልጅ ይመስላል፡፡

«የት ነው የሄደችው?!.....» አለ ሰማይነህ ድንጋጤው ግራ አጋብቶት፡፡

«የታባቷ ታመልጣለች ብለህ ነው!.....ትገኛለች» አሉ እናትዬዋ ሰማይነህ ለማረጋጋት ያህል ራሳቸውን አረጋግተው፡፡

«እናቷ ጋ ሄዳ ይሆናል....» አላቸው ሰማይነህ፣ ራሱንም ጭምር ለማፅናናት በሚሞክር ድምፅ፡፡

«እዚያም ሄደን አጣናት» አሉት፣ ሁለቱም በአንድ ድምፅ

«እንዴ!.....መጀመሪያ ከዚህ ግቢ እንድትወጣ ማን ፈቀደላት?»

«አታለለችና!.....ይኸውልህ እዚችው ሶፋ ላይ ቁጭ ብላ ነው ጠዋት ያታለለችን.....ከአንተ ጋር ለመመካከር ስልክ ብንሞክርም ልክፋቱ ተበላሸብን፡፡ እኔ ደግሞ እውነቱንም የፅንስ ነገር ከሆነ ብዬ ጓጓሁ፡፡.....የመጥፋቱን ነገር መጀመሪያውኑ ታስበው ወይም ደግሞ ሐኪም ቤት ከደረስን በኋላ ታስበው እግዚአብሄር ብቻ ነው የሚያውቀው» እያሉ እናቱ በዝግታ ዝርዝር ሁናቴውን ገለፁለት፡፡

ሰማይነህ ፈዝዞ ሲያዳምጣቸው ከቆየ በኋላ «የማትረቡ ሁለት ጅሎች!» ብሎ ጮኸባቸው፡፡

የሰማውን ነገር ማመን እያቃተው፣ ህልም እየመሰለው እንደገና ዝም ብሎ ፈዝዞ ቆይቶ «ህይወት ጠፍታለች ነው የምትሉኝ?....» እያለ ከተቀመጠበት ተነሳ፡፡ «ለመሆኑ ምን ለብሳ ሄደች?.....ቁም ሳጥኑን ሰብራዋለች ማለት ነው?» እያለ የመኝታ ክፍሉን በር ከፍቶ ከባ፡፡ እናቱና ወንድሙም ሬሳ እንደሚያጅብ እጃቸውን ወደ ኋላ አድርገው ከንፈራቸውን እየመጠጡ ተከተሉት፡፡

ቁም ሳጥኑ አልተሰበረም፤ ልብሶቿን ይዛ አልሄደችም ማለት ነው፡፡ «ምናልባት ልብሶቿን ፍለጋ ትመጣ ይሆን?» የሚል ትንሽ ተስፋ ለማግኘት ሞከረ፡፡ የወርቅ ሳጥኗ ያለመቆለፉን ሲመለከት ግን ተስፋውን ቆርጦ ቶሎ ከፈተው፡፡ አንድም ወርቅ የለም፡፡ የዘለዓለሟን ይዛ ሄዳለች! አለ በልቡ፡፡

ሌላ ተስፋ የሚያስቆርጥ ወይንም ከቤት ውስጥ የጎደለ ነገር በመፈለግ ዓይኖቹን ሲያቅበዘብዝ ከመኝታው ራስጌ ታጥፎ የተቀመጠውን ወረቀት ተመለከተ፡፡ የወረቀቱን መልዕክት ፈርቶ ግንባሩን እንዳጨማደደ ተንደርድሮ አነሳና አነበበው፡፡ ቃላቶቹ በግልምጫ ይለወጡ ይመስል ወረቀቱ ላይ አፍጥጦ ከቆየ በኋላ «ቀለበቱ የታለ?!» በማእልት ጎርፉ ላይ ጮኸበት፡፡

ጎርፉ እየተንቀጠቀጠ ቀለበቱን ከኪሱ አውጥቶ ሰጠው፡፡

«ቀለበቷን ተቀብለህ ሸኘህልኛ!.....የእኔ አንበሳ!» ብሎ ሰማይነህ ቀለበቱን መልሶ ሲወረውርበት ጎንበስ በማለቱ ሳተው፡፡

እናቱም ላይ አፈጠጠ፡፡ ምን እንደሚያደርግ ግራ ገብቶት በቆመበት ቦታ ስሜቱ ተቁነጠነጠ፡፡

«የኔ ታማኝ ዘመዶች!.....የኔ ጠባቂዎች!.....ዓይናችሁ ስር ተቀምጣ አሜሪካ ሀገር ድረስ ተደዋውላ ወይንም ተላልካ ስትሄድ ማየት እንኳ አልቻላችሁም፡፡ እናንተን ማመኔ ነው ጉድ የሰራኝ» ብሎ እንደ ገና ጮኸ፡፡

እናቱና ጎርፉ ነእሩን ስላላወቁት ወይንም ስላልገባቸው ዝም አሉ፡፡ ሰማይነህ ወረቀቱን ጨምድዶ ይዞ «አሜሪካን!?» በማለት በሃይለ ቃል አጓራ፡፡ ፊደሉን እየቆጠረም ድምፁ እስኪደክም ድረስ ቃሉን ደጋገመው፡፡ ወዲያውም በጣም የሚጠላው ስም አዕምሮው ውስጥ አቃጨለ፡፡ ሄኖክ!.....ሄኖክ!.....ሄኖክ!

«እዚያ ውርጋጥ ጎረምሳ ጋ ነው የምትሄደው?!.....እኔን ገድላ?!....ሜዳ ላይ ጥላ?» ብሎ በተዘበራረቀ ስሜትና ራስን በሚያስት ሁኔታ እንደ ማልቀስም፣ እንደ መሳቅም አደረገው፡፡

ከህይወት መጥፋት ጋር የሃብቱ መርገፍና መጥፋት እየታየው ራሱን እስኪስት ድረስ አስጮኸው።

«ትናንት ለሊት ዓይኗን ባጠፋት ኖሮ ዛሬ አትሄድም ነበር!».....አለ እንደ መቃዠት እያደረገው።

«በእጅህ ለምን ሰበብ ትሁንብህ ልጄ?» አሉ እናትዬው ከንፈራቸውን በሀዘን እየመጠጡ።

«እነዚያ ዱርዬዎች ዛሬም ብቻዋን ሲያገኟት ቅርጫ ሊያደርጓት ከብበዋት ይሆናል» በማለት ወደ ሌላ ቅዠት ተሸጋገረ።

«የቶቹ ዱርዬዎች ልጄ?!....»

«የማታዎቹ ናቸዋ!...ያ ልብስ ሰፊው.....ፀጉር ሰሪው.....መኪና አስተማሪው ቦዘኔዎቹ ልጆች.....መርፌ ወጊው ሐኪም.....የሰርጓ ዕለት የነበሩት ጎረምሶች......ሁሉም ሲረባረቡባት ይታየኛል።

የቅዠት መሆኑ ስለገባቸው እናትየው ከንፈራቸውን እየመጠጡ ዝም!

«ይበሏት!....የታባቷ!....ማን ብቻዋን ሂጂ አላት!» እያለ ሲቀበጣጥር ቆየ።

ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ወሰድ መለስ ያደርገው ጀመር። አንዳንዴ ትክክለኛ ነገር ያወራል፤ አንዳንዴ ደግሞ ይቀበዣዥራል። ድምፁም እንደ ባህሪው ይለዋወጣል። አንዳንዴ ለመስማት እስኪያስቸግር ድረስ ድምፁ ደክሞ ያነበንባል፤ አንዳንዴ ሳይታሰብ ይጮሀል፤ በርጋታ የሚያዳምጥበትና የሚመልስበት ጊዜም አለው። ውጪያዊ ድርጊቱና ድምፁ የሚለዋወጠው ከውስጣዊው ስሜቱ ጋር ነው። የህይወት መጥፋት የሀብቱም ጥፋት አድርጎ ባሰበ ቁጥር ያብዳል፤ ህይወቱን የሚያስተካክልበት ሌላ ብሩህ መስመር ለማየት ሲሞክር ደግሞ ይረጋጋል። ችግሩ ግን ጠንቋዩ የነገረውን ከማመኑ የተነሳ በአብዛኛው ስለ ወደፊቱ የሚታየውን ጭለማ ነው።

አሁንም ለጥቂት ደቂቃዎች ድምፁን አጥፍቶ በዝምታ ጥርሱን ሲያንቀጫቅጭና ከንፈሩን ሲነክስ ከቆየ በኋላ ድንገት ዘልሎ ተነስቶ ግድግዳውን በቡጢ እየደበደበ «ወይኔ ሰማይነህ!.....ጉድ ሆንኩ!.....ጉድ ተሰራሁ» እያለ ጮኸ።

«በቃ ተወው እባክህ ልጄ፤ አትበሳጭ» አሉ እናትዬዋ።

«እማማ.....ታውቂያለሽ እኮ!.....ህይወት ጠፍታ ከቀረች፣ ከእጃችን ካመለጠች ካልተገኘች ይሄ ሁሉ ሀብትና ንብረት ረጋፊ መሆኑን ታውቂያለሽ?»

«አውቃለሁ ልጄ.....እንፈልጋታለን፤ የታባቷ ትጠፋለች»

«እሷ አትገኝም በቃ! ይኸው ፅፋለች.....አሜሪካን አገር ፍቅረኛዋ ጋ ሄዳለች። በእኔ ላይ ፈርዳ....በሀብቴ ላይ ፈርዳ ሄዳለች»

«ትሂዳ ምናባቷ!.....ሀብቱም ይርገፍ ምናባቱ......አንተ ብቻ ደህና ሁን ልጄ.....ድሮ ደሀ ነበርን እኮ። ከጊዜ በኋላ ነው ገንዘቡ የተገኘው። እኛ ደህና እንሁን ግዴለም።»

«ያለ ገንዘብ ደህንነት የለም እማማ!.....ሰዎች ሰማይነህን የሚያውቁ በሀብቱ ነው። ሀብቱ ከሌለ ሰማይነህ የለም። ድሀውን ሰማይነህ ማንም አያውቀውም።»

«.....ወይንም ደግሞ ማርከሻ ነገር እንዲያደርግልን አዋቂውን እናማክረዋለና። በምድር ላይ ገድህ አንድ ሴት ብቻ ልትሆን አትችልም። ሌላዋን ገህድን እንዲጠቁምህ አዋቂውን እንጠይቀዋለን። »

«አልቋል እኮ እማማ!......አዋቂው ነግሮኛል። ህይወት ከሌለች ሃብት የለም፤ ሃብት ከሌለ ሰማይነህ የለም!.....አለቀ ደቀቀ!.....ወርቅ የለም!....ብር የለም!.....ወርቁ ቀልጦ ውሀ ሲሆን

አይታያችሁም?!.......ብሩ በንኖ አመድ ሲሆን አይታያችሁም?!» እያለ ሲቀበጣጥር ከቆየ በኋላ፣ ድንገት ተነስቶ ከክፍሉ ወጣ።

«አሁን የት ልትሄድ ነው?» እያሉ እናቱ ተከተሉት።

«.....እፈልጋታለሁ!......ደሞም አገኛታለሁ!» ብሎአቸው ወደ መኪናው ሄደ።

አኳኋሁ አላማራቸውም። ጎርፉን ጠርተውት «ና ተከተለው እባክህ። ብቻውን እንዳይሄድ አብረኸው ሁን» አሉት።

«ህይወትን ከማግባቱም በፊት ሀብት ነበረው። አሁን እሷ ብትሄድ ሌላ ያገባል፤ ምን አስጨነቀው?!» እያለ ጎርፉ ተልጎመጎመ።

«የማታውቀውን አትቀባጥር። ይልቅ ሂድ ተከተለው፤ እንዲያውም እሱ ስለ ተበሳጨ መኪናውን አንተ ብትይዝለት ይሻላል» ብለው እናትዬው ሰማይነህን ለምነውት የመኪናውን ቁልፍ ተቀብለው ለጎርፉ ሰጡት።

«በየት አቅጣጫ ልንዳ?» አለ ጎርፉ የሰማይነህን መኪና መሪ ይዞ እየተመቻቸ።

«በቦሌ መስመር ሂድ!......» አለው ሰማይነህ እንደ ተኮሳተረ። በመንገዳቸው ላይ ወጣት ሴት በተመለከቱ ቁጥር እየደነገጠና ህይወት እየመሰለችው «አቁም!» ይለዋል። መኪናቸውን አቁመው ተመልከተው ህይወት ያለመሆኗን ካረጋገጡ በኋላ ይሄዳሉ። ሁለት ጊዜ ያህል በዚህ ሁኔታ ቆመው መስቀል አደባባይን ካለፉ በኋላ አንድ ሴት ሲመለከቱ ደግሞ ለሶስተኛ ጊዜ ቆሙ። ይህቺኛዋ ወጣት ዓይን አውጣ ቢጤ ነች። አጠገቧ ደርሰው ዘመናዊ መኪናቸውን ሲያቆሙ ሊፍት ሊሰጥዋት መስሏት በፈገግታ ቀረበቻቸው። ሁለቱም በመስኮት በኩል አፍጥጠው ሲመለከቷት ይባስ ብላ «ሀይ - ሀይ!» አለቻቸው።

«.....ታውቂያለሽ?» አላት ሰማይነህ የመኪናውን መስኮት ዝቅ አድርጎ።

«ማንን?....» አለች ወጣቷ «ለከፋ» መስሏት እየሳቀች።

«ህይወትን?!.....»

«የማናት ህይወት?.....!.....አሆሆይ.....!»

«ታዲያ ምን ያስቅሻል?!.......ግልፍጥ!»

«መሳቅ መብቴ ነው። ቅር አለህ እንዴ?!.....»

«ሸርሙጣ!» ብሎ ሰማይነህ ምራቁን ተፋባት።

ጎርፉ ቶሎ ማርሽ አስገብቶ ፈትለክ ባይል ኖሮ ሰማይነህ ከመኪና ወርዶ ሊያጋጫት ፈልጎ ነበር። ወጣቷ ምራቁን ከፊቷ ላይ እየጠረገች «የማነው ፋራ እባካችሁ!......በስባሳ» ብላ መንገዷን ቀጠለች።

ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ደርሰው መኪናቸውን አቁመው እየተካለቡ መሸኛ ቦታውን አልፈው ሊገቡ ሲሉ ለፍተሻ የቆመው ወታደር መንገደኞች መስለውት «ትኬታችሁን አሳዩኝ» ብሎ አስቆማቸው። በአኳኋናቸው በርግጠኝነት ህይወት ላይ የደረሱባትና ሊይዟት የቀረቡት ይመስሉ ነበር።

«ሰው ፈልገን ነው!» አለ ሰማይነህ

«የምን ሰው?!» አለ ወታደሩ

«ህይወት ስዩም የምትባል.....ወደ አሜሪካን አገር የምትሄድ.....»

«ክልክል ነው ጌታዬ.....ይመለሱ»

«ለምንድነው የምከለከለው?!.....ሚስቴ እኮ ናት የምትሄደው!.....ገብቼ አንገቷን አንቄ ከአሮፕላን ውስጥ ማውረድ አለብኝ»

«አትጩህ ሰውዬ!....ክልክል ነው በየሀሉሁ። ዞር በል ወደ ኋላ» አለው፣ በሽኝዎቹ ለቅሶና ልመና የተሳላቸው ወታደር ሰማይነህ ምን እንደተናገረ እንኳን በቅጡ ሳይሰማው።

ሰማይነህና ወታደሩ ሲገለማመጡና ሲፋጠጡ ጎርፉ ላብ አስመጠው። «ተው እባክህን እንመለስ፤ ወታደሩ ጠመንጃውን እያቀባበለ ነው» ብሎ ወንድሙን ለመጎተት ቢሞክርም አመናጭቆ ገፈተረው።

ሌላ ችግር እንዳይፈጠር የሰጉት መንገደኞችና ሽኝዎቻቸው ሰማይነህን እንደ ምንም ገለል ካደረጉት በኋላ ከመሃከላቸው አንደኛው በእርጋታ «ዛሬ እኮ ወደ አሜሪካን ሀገር የሚሄዱ መንገደኞችን የሚያሳርፍ አውሮፕላን የለም። ወደ ውስጥ የገቡት ወደ ጅዳ የሚሂዱት ብቻ ናቸው» አለው።

«ለምን?!.....አለ ሰማይነህ በቁጣ

«ቆይ ላስረዳዎት.....የኢትይጵያ አየር መንገድ ከሆነ ነገር ጥዋት፣ ሉፍታንዛ ከሆነ ደግሞ ቅዳሜ ማታ ነው የአሜሪካን አገር መንገደኞችን የሚያሳፍረው። ለማንኛውም እርስዎ የፈለጓት ሴትዮ ወይንም ባለቤትዎ በየትኛው በረራ እንደ ተመዘገበች መጀመርያ ትኬት ኦፊስ ብትጠይቁ የንግሮዎታል» አለው አሁንም በእርጋታ።

ሰማይነህ ሰውዬውን በአነጋገሩ አመነው። ሆኖም ግን «አመሰግናሁ» እንኳን ሳይለው አካባቢውን ሁሉ እየገላመጠ ወደ ኋላ ተመለሰ።

ሰማይነህን የሚነዳው ድንጋጤና ንዴት ስለሆነ አእምሮው በትክክል ማሰብ አልቻለም። የጎርፉ ዝም ብሎ ተጃጅሎ መከተል ግን ብዙዎቹን ሳያስገርም አልቀረም።

አሁንም ከቦሌ ሲበሩ ተመልሰው በቅርባቸው ያገኙት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቲኬት መሽጫ ቢሮ ገብተው ጠየቁ። የሰማይነህ አቀራረብ በቁጣ ቢሆንም ሰራተኞቹ ብዙ ሰው በማስተናገድ የተለያየ ፀባይ ስለሚገጥማቸው በትዕግስት ችለውት የህይወት ስም ኮምፒዩተር ውስጥ ያለመመዝገቡን ከነገሩት በኋላ ወደ ሉፍታንዛ የቲኬት ቢሮ ሄዶ እንዲጠይቅ መከሩት። እዚያም ሄዶ በተመሳሳይ ሁኔታ የህይወትን ያለመመዝገብ አረጋገጠ፡

«አሁን እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ተደብቃለች ማለት ነው!» አለ ሰማይነህ፣ መኪናቸው ውስጥ ተመልሰው ገብተው ከተቀመጡ በኋላ። «ወደ ክፍለ ሀገር ሄዳም ሊሆን ይችላል......» አለ ጎርፉ፣ እሷም መፈለጉ ከወዲሁ ስልችቶት።

«አትሄድም። የምትሄደው አሜሪካን ሀገር እዚያ ጎረምሳ ፍቅረኛዋ ጋ ነው። ዝግጅቷን ከመጨረሷ በፊት አሳድደን መያዝ አለብን። ምናልባት ጎረምሳው ፍቅረኛዋም እሷን ለመውሰድ መጥቶ፣ እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ ሲዘዋወር እናገኘው ይሆናል፤ ስሙ ሄኖክ ይባላል። እንዳትረሳው ፃፈው!.....» አለው።

ጎርፉ ቁራጭ ወረቀት ከኪሱ ፈልጎ በታዘዘው መሠረት የሄኖክን ስም ከፃፈ በኋላ «የአባቱ ስም ማነው?» ሲል ጠየቀው።

«አንጃለት!.....አባት ላይኖረው ይችላል። አንድ ተራ የሜዳ ዱርዬ ይሆናል።»

«መልኩስ ምን አይነት ይሆን?»

«አስጠሊታ ጎረምሳ መሆን አለበት!.....ሁለቱንም አስሰን ይዘን ልክ እናገባቸዋለን። በምንም መንገድ ሊያመልጡን አይገባም። ያንተንም ወንድምነት የምፈትነው አሁን ነው!።

«እሺ፤ ፍቃድህን ሁሉ እፈፅማለሁ።.....እንግዲህ ያው ሰሞኑን የታክሲ ስራዬን ማቆሜ ነው። »

«የምን ታክሲ?!.....የምን ወርቅ ቤት?!.....የምን ስራ!? አሁን ትልቁ ስራችን ህይወትን አድኖ መያዝ ብቻ ነው። ቢቻል ከፍቅረኛዋ ጋራ እንዳለች አንድ ላይ!.....»

«እሺ፤ ታዛዥ ነኝ» አለ ጎርፉ፣ የታክሲ ስራውን መገላገሉ ደስ አሰኝቶት። የራሱን ጥቃቅን ጥቅም ሲያስብ ደስ ቢለውም ቅሉ የሰማይነህ አነጋገርና ሁኔታ እንደ እብድ እየሆነበት ስለመጣ በውስጡ መደንገጡ አልቀረም።

«.....ምናልባት መንገድ ላይ ደርሰንባቸው ሊያመልጡን ቢሞክሩ በመኪናው ገጭተህ ትጥላቸዋለህ!። ነግሬሃለሁ ኋላ.....ስትርበተበት እንዳያመልጡህ።»

«....ገጭተናቸው በኋላ ትራፊክ ከያዘንስ?»

«አንተ ምን አገባህ!?....እኔ ነኝ ካሳ የምከፍለው.....ደግሞ ምን ጊዜም ከመኪናችን ውስጥ ሽጉጥና ጠመንጃ መጥፋት የለበትም። ተቀባብሎ መቀመጥ አለበት።»

«ምን ያደርግልናል?.....» አለ ጎርፉ የመሳሪያ ስም ሲነሳ ልቡን ፍርሃት ፍርሃት እያለው።

«እንገድልበታለና!.....ህይወትና ፍቅረኛዋ የተደበቁበትን ቦታ ደርሰን ሊያመልጡን ከሞከሩ ሁለቱም ላይ ተኩሰን መጣል አለብን። እነሱን በሁለት ጥይት መቅለብ አያቅተንም።»

«ቢሞቱስ?.....» አለው ድርጊቱ አሁን የተፈፀመ መስሎት እየተንቀጠቀጠ።

«ይሙቱ! ድብን ይበሉ። እንዲያውም ጎረምሳው ፍቅረኛዋ ላይ ስንተኩስ ለመግደል መሆን አለበት። እሷም እንዲህ እንዳደበነችኝ ድብን ትበል!.....»

«በኋላ ወንጀል ፈፀማችሁ ተብለን ከተያዝንስ?.....»

«ዝም በል!.....እኔ የምነግርህን አድምጠኝ»

«እሺ.....»

«እኔን ትገድለኝና ሬሳዬን ከህይወት ሬሳ ጎን አንድ ጉድጓድ ውስጥ አብረን እንድንቀበር ታደርጋለህ.....ሬሳዋን በሙታን መንደር ውስጥ ቀንዝሮ ሌላ ሬሳ ፍለግጋ እንዳትቅበዘበዝ እኔ ለዘለዓለም አጠገቧ ሆኜ እጠብቃታለሁ።....»

‹ወንድሜ አብዷል ማለት ነው፤ አለ ጎርፉ በልቡ። እብደቱን ካይኖቹ ላይ ማንበብ የሚችል ይመስል ሰረቅ አድርጎ ተመለከተው።»

«ምን ታየኛለህ?.....እንከፍ! መኪናውን አስነሳና እንሂድ እንጂ!»

«እሺ፤ ወዴት እንሂድ»

«ህይወትን ፍለጋ ነዋ!.....ከረፈፍ!»

መደምደሚያ እንደተጠበቀው ለምሳው ወደ አምስት ኪሎ ሲመጣ ሁለት መልእክት ጠብቆት ነበር። መጀመሪያ «አንዲት ቸኮሌት የሆነች ልጅ.....ቆንጅዬ ጥርሰ ወርቅ ፈልጋህ ነበር። ዘንድሮ ሊቀናህ ነው መሰል፤ ቆንጆ ሴት መያዝ ጀመርክ» ብለው ጓደኞቹ ሲያማሙቁ የሱ ልብ ምንም አልደነገጠም። ጥርሰ ወርቅ መሆኗን ሲነግሩት ህይወት መሆኗን ጠርጥሯል። ሲጠፋባት ናፍቃው አድራሻውን አፈላልጋ ልትጠይቀው የመጣች አድርጎ ገምቶ ነበር። ከሷ በኋላ አሁን በቅርቡ ደሞ

ሁለት ወንድሞቹ መጥተው ይፈልጉት እንደ ነበር ሲነግሩት ግን ቤታቸው ውስጥ አንዳች ረብሻ ተነስቶ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ ተደናገጠ። ወደ ቤት ስልክ ቢደውልም አይሰራም። ሰባት ሰዓት ሆኖ ህይወት እስክትመጣ ድረስ ምጥ ሆኖበት የውጭ በር ላይ እየተቁነጠነጠ ጠበቃት።

ህይወት በሰዓቱ መጥታ፣ ለጥንቃቄ ያህል ከአስፋልት ማዶ ቆማ፣ አካባቢውን እየፈራች አሻግራ ስትመለከት መደምደሚያን በማየቷ ደስ አላት። ልክ እሱን እንዳየች ከለላ ጋሻ ያገኘች ይመስል ፍርሃቷ ጠፍቶላት ተንደርድራ መጥታ ተጠመጠመችበት። አጠገቡ እስክትደርስ ድረስ መደምደሚያ አላወቃትም ነበር። አለባበሷም ከወትሮው ለየት ብሎበታል፤ ጂንስ ሱሪ ከሹራብ ጋር አድርጋ፣ መነፅር ሰክታ፣ «ጆሊ» ወጣት ሆናበታለች።

«አንተን እስካገኝህ ድረስ ልቤ በስጋትና በድንጋጤ እየተርበተበተ ነው የቆየሁት። አንተን ባላገኝ ኖሮ ምን እንደምሆን ወይንም ምን እንደማደርግ አላውቅም ነበር» አለችው ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ።

«ምነው?....ምን ተፈጠረ?»

«በቃኝ!.....ከሰማይነህ ቤት ሸሽቼ አምልጬ ወጣሁ። የታሰርኩበትንም ገመድ በጣጥሼ አመለጥኩ።

«እኔም ጠርጥሬያለሁ።.....»

«እንዴት ልትጠረጥር ቻልክ?»

«ጓደኞቼ በምልክት ሲነግሩኝ መጀመሪያ የመጣሽው አንቺ መሆንሽን አወቅሁ። ከዚያ በኋላ ሁለቱም ወንድሞችህ መጥተው እንደ ነበር ሲነግሩኝ ደግሞ ቤታችን ውስጥ አንድ ችግር መፈጠሩን ጠረጠርኩ....»

«.....ሊፈልጉኝ እዚህ ድረስ መጥተው ነበር ማለት ነው?» አለች ህይወት፣ ድንጋጤዋ አገርሽቶባት።

«መሆን አለበታ!.....ለምን እንደፈለጉኝ ለማወቅ ወደ ቤት ብደውልም ስልኩ አይሰራም።»

«ስልኩንማ እኔ በጥሼዋለሁ.....›.

«ለምን ብለሽ?...??

«ለጥንቃቄ ነዋ.....የእስር ቤቱን በር ሰብሬ ስወጣ ፖሊሶቹ እንዳይደውሉ የስልክ መስመር መቋረጥ ነበረበት።......ዝርዝሩን በኋላ አጫውትሃለሁ አሁን ግን ከዚህ አካባቢ እንራቅ።»

መደምደሚያ እየተገረመ፣ «እውነትሽን ነው። ከዚህ መራቅ አለብን» ብሎ፣ ወዴት እንደሚሄዱ እንኳን ሳያውቁት ከአካባቢው ለመሸሽ ያህል ብቻ አንድ «ውይይት» ታክሲ ውስጥ ዘው ብለው ገቡ።

ታክሲው ውስጥ ጎን ለጎን ተቀምጠው በጆሮ እየተንሾካሾኩ ሲያወሩ፣ ሌሎቹ ተሳፋሪዎች ፍቅረኛሞች መስለዋቸው በስርቆት እየተመለከቷቸው «እንዴት ያስቀናሉ!» ይሏቸው ጀመር። አንዳንዶቹ ግን የመደምደሚያን ቅጥነትና ሞጋጋ ፊት ከህይወት ቁንጅናና ቁመና ጋር አልሄድ ብሏቸው ያለ ጉዳያቸው ገብተው የጉረመርሙ ነበር።

ህይወት ከሰማይነህ ቤት እንዴት እንዳመለጠች ልታወራለት፣ መደምደሚያ ደግሞ ሊያዳምጣት የቸኮሉ ቢሆንም ታክሲው ውስጥ ከብዙ ሰዎች ጋር ስለተፋጠጡ ምስጢር መጫወት አልቻሉም። ያፈጠጡባቸውን ዓይኖች ለመሸሽ በዝምታ ተጉዘው እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ሲደርሱ ወረዱ። ህይወት መደምደሚያን ተከትላው ከመውረዷ ሌላ ወዴት እንደሚወስዳት እንኳን አታውቅም ነበር።

«ምሳ ልጋብዝሽ እስቲ.....እኔም አልበላሁም። ምርጫሽ የአበሻ ምግብ ነው ወይንስ የፈረንጅ?» አላት።

«አሁን ምንም የምግብ ፍላጎት የለኝም። ገና ስሜቴ ስላልተረጋጋ ነው መሰለኝ።.....ቁጭ ብለን የምንጫወትበት ደበቅ ያለ ቦታ ብቻ ነው የምፈልገው» አለችው።

ሌላ ታክሲ ይዘው በአስመራ መንገድ ከሄዱ በኋላ መደምደሚያ ቀደም ብሎ ወደሚያውቃት አንዲት ተራ ምግብ ቤት ይዞአት ገባ።

«ምግብ ቤቷ ዓይን ስለማትስብ ጥሩ መደበቂያ ትሆናለች ብዬ ነው»

«ትክክል ነህ»

ለወጉ ያህል የሚያስፈልጉትን ምግብ አዝዘው ቀረበላቸው። አዕምሮአቸው ስላልተረጋጋ ሁለቱም የምግብ ፍላጎት አልነበራቸውም። እንዲያው ለኮፍ - ለኮፍ እያደረጉ ጨዋታቸውን ቀጠሉ።

እናቱንና ጎርፉን እንዴት እንዳታለለቻቸው ህይወት ስትነግረው መደምደሚያ ተገረመ። እነሱን አታልላ አምልጣ እሱን ፍለጋ ወደ ዩኒቨርሲቲ ስትመታ ባለ ታክሲው ‹ሊለክፉት› መከጀሉንና ከዚያም በኋላ ያጋጠሟትን ‹ለከፋዎች› ካጫወተችው በኋላ

«አንድ ነገር በጣም እየገመረኝ ነው» አለችው።

«ምን?.....» አላት እሱም በጉጉት።

«እኛ ሴቶች ብቻችንን እንደ ልባችን መንቀሳቀስ እንዳንችል ተፅዕኖ የሚያሳድሩብንን ሁኔታዎች ተመለከትኩ....»

«እንዴት ማለት?.....»

«.....እንደነገርኩህ ከባለ ታክሲው ጀምሮ ብዙ ወንዶች ብቻዬን ስለተመለከቱኝ ‹ለከፉቸው› ሊያስኬደኝ አልቻለም። ያውም በዚች አጭር ጊዜ!.....በፉጨት የሚጥሩት!.....በዓይናቸው የሚጠቅሱት በስድብ የሚላከፉት.....ሊስትሮዎችን ልከው «አውቅሻለሁ» የሚሉት ስንቱን አየኋቸው መሰለህ። ደግሞ ይህንን የሚያደርጉት ወጣቶች ብቻ እንዳይመስልህ፤ እንዳውም በሽማግሌዎች ብሷል።.....›.

«ቆንጆ ስለሆንሽ ነዋ።.....ዛሬ ደግሞ ያለባበስሽ ዓይነት እንደ ባለትዳር ሳይሆን ገና መቅበጥ የምትፈልግ ልጃገረድ አስመስሎሻል.....» አላት ፈገግ ብሎ።

«እንዴ!.....ቆንጆ ሴት ብቻዋን በነፃነት መንቀሳቀስ አትችልም ማለት ነው?!.....ሙት፤ እውነቴን እኮ ነው። አንዱማ አራት ኪሎ አካባቢ ጭራሹኑ ከኋላዬ መጥቶ ክንዴን ድንገት አፈፍ ቢያደርገኝ በድንጋጤ ክው ብዬ ቀረሁ። እኔን ያስደነገጠኝ ሰማይነህ ወይንም ጎርፉ ደርሰውብኝ የያዙኝ መስሎኝ ነበር። ሰውዬው ኮሰተር ብሎ «ሶሪ!....ልተዋወቅሽ ፈልጌ ነው» ሲለኝ በንዴት መንጭቄው ሄድኩኝ። ጉድ እኮ ነው። ካንተ ጋራ የምንገናኝበት ጊዜ እስኪደርስልኝ ድረስ ደግሞ እዚያው አራት ኪሎ አካባቢ ድሮ ከሄኖክ ጋር የምንገባበትን ሻይ ቤት መርጬ ገብቼ ነበር። ከኍልት ሰዓት በላይ ሰለቆእሁበት ብዙ ትርዒት ያየሁት እዚያ ነው። አንዱ ሲያፈጥብኝ፣ አንዱ ሲቅለሰለስብኝ፣ አንዱ «ልጋብዝሽ» ሲለኝ ሁሉን በልቤ ስታዘብ ቆየሁ። እረዥም ሰዓት በመቆየቴ የተነሳ የኬክ ቤቱ ባለቤት ራሱ መጥቶ ሻይና ኬክ የሚያቀርቡ ልጃገረዶች እንደሚፈልግ አጫውቶኝ በተዘዋዋሪ የስራ እድል ሲሰጠኝ ገረመኝ። በሴትነቴ ብቻዬን በነፃነት መዝናናት አልችልም ማለት ነው?! እያልኩ አስብ ነበር።

«ይኸውልሽ እንግዲህ፤ ሰማይነህ ከቤት ውስጥ እንዳትወጪ ያደረገሽ ጠላፊሽ እንደሚበዛ ፈርቶ ነው.....›. አላት መደምደሚያ እንደ ቀልድ አድርጎ።»

«እኔ ደግሞ ቆንጆ እቃ ሆኜ መኖር ስለማልችል አመለጥኩት!....›.

«ለማንኛውም የአበሻ ወንዶች በሴቶች ላይ ያለን ደካማ አመለካከትና የምናሳድረው ተፅዕኖ ከጊዜ ወደ ጊዜ በጣም እየተሻሻለ መጥቷል። ድሮና ዘንድሮ አንድ አይደለም። ወደፊትም ደግሞ ከባህል እድገት ጋር ይበልጥ ይሻሻላል። የፆታ ልዩነት የሙብት ልዩነት መፍጠር የለበትም።»

«ወንዶች ግለ ሂስ መውሰድ አለባቸው» አለችና ሳቀች። መደምደሚያ ህይወት የምታወራለትን ቢያዳምጣትም አዕምሮው በሌላ ሀሳብ እንደ ተወጠረ ነበር።

«አሁን ወደ ውጭ አገር እስክትሄጂ ድረስ የት ነው የምትቀመጭው?!» አላት በድንገት።

«እኔ እንጃ!......ምንም መሄጃ የለኝም» አለችው እሷም በአንድ አፍታ ስሜቷ ተለዋውጦ እንባ እየተናነቃት።

ገበታው ተነስቷል። ሳያስቡት በሃዘን ስሜት እንደተዋጡ እጃቸውን ታጥበው ተመልሰው የአምቦ ውሃቸውን እያጠነፈፉ ጠጡ።

«.....ማለቴ.....እስከ ጊዜው ድረስ ወይዘሮ ስራሽ ቤት ተመልሰሽ የምትቀመጪ መስሎኝ ነበር። በርግጥ ሰማይነህ እዚያ መሆንሽን ካወቀ እንደሚያስቸግርሽ ይገባኛል» አላት መደምደሚያ ስሜቷን ለመጠበቅ እየሞከረ።

«እሱ ብቻ አይደለም። አክስቴ ራሷ በቅታኛለች። እሷ ከእንግዲህ ወዲያ ማረፊያም፣ መደበቂያም ልትሆነኝ አትችልም። ጠዋት ከሰማይነህ ቤት እንዳመለጥኩ መጀመሪያ የሄድኩት እሷ ጋ ነበር። ነገር ግን ስላልወለደችኝ በዚህ ቀውጢ ሰዓት አንኳን ጨከነችብኝ። የጭካኔዋን ልክ አሳየችኝ። እኔም በቃኝ - ቆረጠልኝ። ዓይኗን ማየት አልፈልግም። ወላጅ እናትና አባቴ መሞታቸው የታወቀኝና ጠልቆ የተሰማኝ ዛሬ ነው....»

እንባዋ ቀድሞ በጉንጮቿ ላይ መንከባለል ስለ ጀመረና ሳግ ስለተናነቃት ንግግሯን አቋረጠች። መደምደሚያ ስሜቷ ተጋብቶበት እንባው አይኖቹ ላይ ቢደርስም እንደ ምንም ጥርሱን ነክሶ እየታገለ እሷን ለማፅናናት ሞከረ።

«አይዞሽ ህይወት፤ አታልቅሺ......በቃ። ሁሉም ያልፋል። ለጊዜውም ማረፊያ የሚሆን ሌላ ዘመድ ከተገኘ.....»

«ምንም ዘመድ የለኝም አልኩህ እኮ!....ማንም! አክስቴ ዘመዶቼን እንዳልቀርብ የግል ንብረቷ አድርጋ ነው ያሳደገችኝ። ድሮ ያልቀረብኩትን ዘመድ ዛሬ መሸሻ ይሆነኛል ብዬ አልሄድበትም።.....»

«አና አሁን የት ነው የምታርፊው ወይንም የምትደበቂው?» መደምደሚያ ግራ ተጋባ። ከማንም ይልቅ አምናውና እርዳታውን ፈልጋ የመጣችውን እሱ ጋ በመሆኑ ኃላፊነቱ ከበደው። አቅሙ ቢፈቅድ የቻለውን ሁሉ ለማድረግ ወደ ኋላ አይልም። አሁን ግን እሱ ራሱ የሚኖረው የዩኒቨርሲቲ ጓደኖቹን ተጠግቶ ነው።

«ትንሽ ቸኩልሽ፤ የአሜሪካን ሀገሩን «ፕሮሰስ» ጨርሰን የጉዞ ቀንሽ እስኪቃረብ ድረስ ከሰማይነህ ቤት መውጣት አልነበረብሽም» አላት ሲያስብ ቆይቶ።

መደምደሚያ ግራ ከመጋባቱ የተነሳ የሰነዘረው አስተያየት ነው። ለህይወት ግን ፈፅሞ አልተዋጠላትም፤ እንዲያውም አስቆጣት።

«......እስኪያርደኝ ድረስ መጠበቅ ነበረብኝ?! ንገረኝ እስቲ መደምደሚያ.....በእኩለ ለሊት ተነስቶ ሊያርደኝ ጩቤ ይዞ አጠገቤ ቆሞ ነውኮ የነቃሁት። ከዚህ በኋላ ነው ለአንዲት ቀንም ቢሆን እሱ ቤት መቆየት እንደሌለብኝ የወሰንኩት።»

«እዚህ ደረጃ ደርሶ ነበር?!....» አላት መደምደሚያ እየዘገነነው።

«ታዲያስ!......ይህንን ያህል ምን እንዳደረኩት አይገባኝም።»

«እብደት ነው፤ ሌላ ንገር አይመስለኝም። የሱ የቅናት ዓይነት ራሱን የቻለ የምርመራ ጥናት የሚያስፈልገው ይመስለኛል።.......ባህሩ ፂሞን አማላጅ አድርጌ እኔ አነጋሬው ነበር። የተበደልኩት እኔ ሆኜ ሳለሁ የታለቅነቱ ውለታ ስለ ነበረብኝ እኔው ይቅርታ ጠይቄው ጥርጣሬው ሁሉ ከንቱ እንደሆነ ላስረዳው ሞከርኩኝ። በተለይ እኔን ባንቺ ከወንድምነት ውጪ በምንም መንገድ መጠርጠር እንደሌለበት ነገርኩት። ሆኖም ግን አዕምሮው ውስጥ የተፈጠረ ችግር ስላለ ሊያምነኝ አልቻለም። በውጭ ሊረዳኝ ፈቃደኛ መሆኑን ብቻ ገለፀልኝ። እንኔም ስላልፈው አመስግኜው ወደ ፊት ግን ርዳታውን የማልፈልግ መሆኔን ገልጬለት ተለያየን። እና ይሄ ሁሉ የጤንነት አይመስለኝም።»

«ይህን ተናግሮ ወዲያው ወደ ሌላ ሀሳብ ውስጥ ገባ። ሰማይነህ ለእኔ ባለውለታዬ የመሆኑን ያህል አክስቷም ለህይወት ባለውለታዋ ነች። ከልጅነት ጀምሮ ተንከባክባ አሳድጋታለች። አሁን በተለወጠው ፀባያቸው ምክንያት ፈፅሞ ልንጠላቸውና ውለታቢስ ልናደርጋቸው አይገባም። ውለታውን የማያከብር ትውልድ መቅኖ ቢስ ነው፤ እያለ በማሰብ ለህይወት እንዳይነግራት አሁን በአክስቷ ላይ ያላት አመለካከት መጥፎ በመሆኑ ሲጨነቅ ቆየ።

«ምን እያሰብክ ነው?.....ሀሳብ ውስጥ መሆንህ ያስታውቃል» አለችው ህይወት፣ እንባዋን ጠራርጋ ስሜቷን በማረጋጋት።

«ልክ ነሽ፤ ሰው ሆኖ ሀሳብ የት ይቀራል?»

«አይዞህ፤ ለኔ አታስብ። ወርቆቼን በሙሉ ይዤ ወጥቻለሁ። ወደ ውጭ ሀገር የመሄዱ ነገር እስኪሳካልኝ ድረስ የገንዘብ ችግር አይኖርብኝም።

«ተዘጋጅተሽ ነዋ የተጣሽው!» አላት መደምደሚያ እየተገረመ። «ዘመዶቼ አንቅተውሻል ማለት ነው፤ በዚህ መንገድ የምታስቢ አትመስይኝም ነበር»

«አዎ፤ ችግሩ ያሳሰብህል እኮ። ደግሞም ወርቆቹ ጥርሴ የወለቀበትና የፈትነቴ ካሳ ናቸው። ሰማይነህ ሀብት ውስጥ ገብቼ ይህቺን ታህል ይዤ መውጣቴ አይበዛብኝም።

«እሱስ ልክ ነሽ። ኧረ ለኔም ተርፈሽኛል። እናቴ የሰጠችኝ አምስት መቶ ብርና የአንቺ ወርቅ ኪሴን ብቻ ሳይሆን ልቤንም ሞልተውልኝ ኮራ አድርገውኛል» ካለ በኋላ ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ «ቅድም ስለ ሴቶች ነፃነት ያነሳሽውን ነጥብ አሁኑኑ ልትፈተኚበት ነው.....» አላት።

«እንዴት እንዴት?»

«ዛሬውኑ የሚከራይ ቤት ማግኘት ሊያስቸግረን ይችላል። ስለዚህ ለጊዜው ሆቴል ውስጥ ማረፍ ሊኖርብሽ ነው።»

«እኔም ቅድም ብቻዬን ቁጭ ብዬ እንደሱ እያሰብኩ ነበር። ለመደበቅም ያመቻል።»

«.....ብቻሽን ሆቴል ውስጥ መኖር አያስፈራሽም?»

«ለምን ያስፈራኛል?! ለከፋውን እንደሆን እየተለማመድኩት ነው። ሌላ ምን ይመጣብኛል?!»

በአስመራ መንገድ መስመር በርካታ አዳዲስ ሆቴሎች መሠራታቸውን መደምደሚያ ያውቃል። የህይወትን ማረፊያ ማዘጋጀት አጣዳፊ ተግባሩ መሆኑን በመገመት ወዲያውኑ ተነሳ። ሆኖም ግን ከህይወት ጋር ተያይዞ መዞሩን አልወደደውም። እንዲያው በአጋጣሚ እንኳን እነሰማይነህ ቢደርሱባቸውና አንድ ላይ ቢያዩዋቸው የእስካሁኑ ጥርጣሬ ሁሉ ትክክል እንደሆነ አድርገው እንደሚወስዱ ያውቃሉ። በአንድ በኩል ህይወት እሱን እንደ ብቸኛ ወንድም ቆትራ እምነት ስለ ጣለችበት ከብዶት ማንኛውንም መስዋዕትነት ሊከፍልላት ዝግጁ ሆኗል። በሌላ በኩል ደግሞ አብሮ የመታየቱና ሌላ ግምት ውስጥ የመግባቱ ፍርሀት መንፈሱን እያሸበረው ነበር።

«....እንግዲህ ብናደርግስ?.....» አላት ሲያስብ ቆይቶ።

«እንዴት?....»

«ሆቴል ለሆቴል አብረን ከምንዞር እዚሁ ሆነሽ ጠብቂኝ። እኔ በተመታጣኝ ዋጋ የምታርፊበትን ሆቴል ፈልጌ ልምጣ.....እዚህ መቆየቱ ቢሰለችሽም ሌላ አማራጭ የለም።»

«ጥሩ ሀሳብ ነው.....ግን ብዙ አትቆይ።»

በዚሁ ተስማምተው መደምደሚያ ወጥቶ ሲሄድ ህይወት እዚያው ቆየች። በርግጥም በብቸኝነት መቆየቱ አሰልቺ ነበር። ምግብ ቤቷ እምብዛም ሰው ስለማይገባባት እንደ ጠዋቱ ኬክ ቤት ውስጥ የሚለከፉትና የሚገላምጧት አላጋጠማትም። አስተናጋጁ ብቻ ግራ በተጋባ ስሜት እያያት ሙዚቃውን ሲለዋውጥላት ቆየ።

አንድ ሰዓት ከሩብ ያህል ጊዜ በብቸኝነት ከቆየች በኋላ መደምደሚያ ተመልሶ መጥቶ ወደ ተያዘላት ሆቴል ወሰዳት።

«እንግዲህ ለጊዜው እዚህ እረፊና በዋጋውም አነስ ያለ ለመደበቂያ አመቺ የሆነ ቦታ ደግሞ እንፈልጋለን» አላት የክፍሏን ቁልፍ ተቀብላ አብረው ከገቡ በኋላ።» ምግብና መጠጥም እዚሁ ክፍልሽ ድረስ ስለሚመጣልሽ መውጣት አያስፈልግሽም።»

«እዚህ ሆቴል ውስጥ ማረፌን እነሰማይነህ በምንም መንገድ ፈልገው የሚያገኙኝ አይመስለኝም» አለችው እሷም ራሷን ለማሳመን በሚጥር አነጋገር።

«እንደዚያ እንኳ ማለት አትችይም። ገንዘብ ሰርስሮ የማይገባበት ቀዳዳ የለም። በገንዘብ ኃይል ሊያፈላልጉሽ ይችላሉ....ስለዚህ እስከጊዜው ድረስ ጥንቃቄ ማድረግና ራስሽን መለወጥ መቻል አለብሽ። ወደ ውጭ የሚሄዱ ጉዳይ ብዙ ጊዜ ሊወስድ ይቻላል። ቀላል አይደለም።»

«ለማንኛውም ገንዘብ ያስፈልገናል። እነዚህን ወርቆች አስመዝነህ ሸጥልኝ» ብላ ከኪሷ አውጥታ ሰጠችው።

«ለሄኖክ ስልክ እንደውልለትና ነገሩ የሚፋጠንበትን መንገድ እንፈልግለታለን። እራሴን መደበቅ ከሰማይነህ ቤት ስወጣ ስለተለማመድኩ አያስቸግረኝም። እንዲያውም ወደ ፊት ፍሎሪዳ ሄጄ ከሄኖክ ጋር ስኖር የፊልም ተዋናይ መሆን እየተመኘሁ ነው» አለችው።

«ትችያለሽ። ጠንክረሽ ከሰራሽና መንፈስሽን ካዘጋጀሽው ካሰብሽበት የማትደርሽበት ምንም ምክንያት የለም» በማለት መደምደሚያ አበረታታት።

«ወርቁን ሸጠህ ስትመለስ የምትገዛልኝ ነገሮች ይኖራሉ። ባጋጣሚ ከክፍሉ ብወታ እንኳን ራሴን ለመቀያየር ብቁ ልብስና ጌጥ የለኝም።»

«እሺ፤ የምትፈልጊያቸውን ነገሮች በዝርዝር ትነግሪኛለሽ። በተጨማሪም ይሄ ወርቅ ጥርስሽ መጥፎ ምልክት ስለሚሆን አይቮሪ እንዲለወጥ እናደርጋለን።»

«በጣም ጥሩ»

የመደምደሚያ አዕምሮ በሌላም ኃሳብ እየተወጠረ ነበር። ስለሰማይነህ ለማወቅ ቸኩላሉ። የህይወትን መጥፋት ካወቀበት ሰዓት ጀምሮ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ መስማት ወይንም ማየት ፈልጓል። ራሱን በከፍተኛ ደረጃ እንዳይጎዳ፣ ችግር ላይም እንዳይወድቅ አሳስቦታል። የህይወትን ማረፍያ አዘገጃጅቶ ከጨረሰ በኋላ ወደዚያኛው ትዕይንት ለመሽጋገር እያሰበ ሄደ።

መደምደሚያ ወጥቶ ሲሄድ ህይወት ክፍሉን ከውስጥ ቆልፋ ወደ መታጠቢያ ክፍል ገባች።

ወይዘሮ ስራሽ ቀኑን ሙሉ ስትናደድ ነው የዋለችው፡፡ ህይወት ለዚህ ትደርሳለች ብላ አልገመተችም ነበር፡፡ በየዘመዱ ቤት ስልክ ደውላ፣ በቅርበት የምትጠረጥራቸው ሴት ጓደኞቿ ቤት እራሷ ሄዳ፣ በየአቅጣጫው ፈልጋና አስፈልጋ አላገኘቻትም፡፡ አሁን የጣቷ ወርቅ ሾልኮ ወልቆ የጠፋ ያህል አንገበገባት፡፡ እሷ በፊናዋ ህይወትን ልትፈልግ ወደ ውጭ ስትሄድ ሰማይነህ ሁለት ጊዜ ያህል ከጎርፉ ጋር መጥቶ እንዳጣት ሰራተኞቿ ነግረዋታል፡፡ የተፈጠረው ምስቅልቅልና ያልታሰበ ችግር አዕምሮዋን በጥብጦት ስለ ዋለ ወደ ምሽት ላይ ውስኪ ቤቷን ስትከፍት ከነ ሙሉ ልቧና ከወትሮው መስተንግዶ ጋር አልነበረችም፡፡

አንዳንድ ደምበኞቿ የሁኔታውን መለዋወጥ አይተው «ምን ሆነሻል ዛሬ ወይዘሮ ስራሽ? ፊትሽ ደህና አይደለም» ሲሏት

«አይ፤ እንዲሁ ነው፡፡ ምንም አልሆንኩም» እያለች ሽፋፍና ቆየች፡፡ በኋላ ግን ደንበኞቿ መጥተው ሲያፋጥጧት እውነቱን ለመናገር ተገደደች፡፡

ባህሩ ፂሞ ብቻውን ቀደም ብሎ የገባ ሲሆን ይትባረክና አቡበከር ደግሞ በኋላ ገብተው ሶስቱም የባንኮኒውን መደዳ ይዘው ቆመዋል፡፡

«የት ጠፋች?» አሏት ሁለቱም በጣም ተመስጠው፡፡ ባህሩ ፂሞ እምብዛም ደንታ አልሰጠውም፡፡

«ምን አባቴ አውቄ?!.....ጉድ አደረገችኝ እንጂ!» ብላ ወይዘሮ ስራሽ በንዴት ጠረጴዛውን ቀረቀረች፡፡

«ሰማይነህ አብዷላ!....» አላት አቡበከር፡፡

«እስካሁን አላገኘሁትም፡፡ ሁለት ጊዜ መጥቶ አጣኝ አሉ፡፡....ማበድ ይነሰው እንዴ?!.....ለእሷ ሲል ሀብቱን ከስክሶ ጉድ ስታደርገው!.....እኔንም ጉድ አደረገችኝ እንጂ»

«ቀናተኛ ባል አስጠልቷት ይሆናል፡፡ አትፍረጂባት» አላት ይትባረክ ጥርሱን ሳይከድን፡፡ የሰማይነህ ንዴት ከወዲሁ በመገመት ሁለቱ ጓደኛሞች የተደሰቱ ይመስላሉ፡፡

«ደግሞም ፋራ ባል ሰልችቷት ይሆናል፡፡ ቀድሞውንም ለእኛ የምትሆን ልጅ ነበረች» በማለት አቡበከርም አከለበት፡፡

ወይዘሮ ስራሽ ቀልዳቸው አልጣማትም፡፡ የእሷ አንጀት ምን ያህል እንደ ተቃጠለ ስላልገባቸው በሽቃ «ኤጭ!» ብላ ዘጋቻቸው፡፡

ትንሽ ቆይቶ ሰማይነህ ጎርፉ በመኖሪያ ቤቱ በር በኩል ገብተው እንደሚፈልጓት ሰራተኛዋ መጥታ ስትነግራት እየበረረች ሄደች፡፡ ሰማይነህ ገና ስታየው አስፈራት፡፡ ፊቱ በንዴት ተጨማዷል፤ ፀጉሩ ተንጨባርሯል፤ አፍንጫው ፀብ የሚያሸት ይመስላል፡፡

«ግቡ እንጂ ወደ ቤት....» አለቻቸው ድምጿ እየተንቀጠቀጠ፡፡

«አንተ ውስኪዋ ቤት ግባና ጠብቀን፡፡ እኔና እሷ እዚህ እንነጋገራለን» አለው ሰማይነህ ጎርፉን፡፡

ጎርፉ ትዕዛዙን ተቀብሎ ሲሄድ ወይዘሮ ስራሽና ሰማይነህ እንደተኮራረፈ ሰው ዝም ተባብለው ወደ መኖሪያ ቤቷ ሳሎን ገቡ፡፡

«ይቺ ሽርሙጣ ልጅሽ ተጫወተችብኝ አይደል!» አላት ሰማይነህ ዓይኖቹን አፍጥጦ፡፡

«እግዜር ይይላት!....እኔም እንዲሁ ቆሽቴ ሲደብን ነው የዋልኩት» አለችው በሚያስተዛዝን ድምፅ፡፡

«አሁን የት ነው የተደበቀችው?!......»

«እኔ ምናባቴ አውቄ ሰማይነህ! ቀኑን ሙሉ ፈልጌ አስፈልጌ አጣኋት»

«የምትሄደውማ አሜሪካን አገር ነው። ሄኖክ የተባለ ፍቅረኛዋ ጋ እንደምትሄድ በደብዳቤ አሳውቃኝ ነው የጠፋችው።....»

«እንደዚያ ነው እንዴ?!....አሜሪካን አገር ከሰማይነህ ቤት የበለጠ ምን አባቷ ልታገኝ!»

«እሱን የምታውቀው እሷ ነች። እዚያ ከመድረሷ በፊት የገባችበት ጉድጓድ ውስጥ ገብቼ ደሟን እጠጣለሁ እንጂ እኔን እንዲህ ቀልዳብኝና ሜዳ ላይ ጥላኝ ልትሄድ አትችልም። አሁን የምፈልገው የተደበቀችበትን ቦታ እንድትነግሪኝ ነው!»

«አላመንከኝም እንዴ ሰማይነህ?!.....እኔንም ሰድባኝና አመናጭቃኝ ነው እኮ የሄደችው። ምን ውስጥ እንደ ገባች ለራሴም ግራ ገብቶኛል።»

«እናቷ አይደለሽም እንዴ!.....እንዴት መደበቂያዋን አታውቂም?! እንዲህ ዓይነት ድብብቆሽ አይገባኝም!» ብሎ ጮኸባት።

«አይ ሰማይነህ፤ አትቆጣ ባክህ የኔ ጌታ። እኔንም አሳዝናኝና መሀንነቴን ነግራኝ ነው የሄደችው። መሀን መሆኔ በደንብ የታወቀኝ ዛሬ ነው። እንደ እናት አሳድጌ ለወግ አብቅቻት ዛሬ ከመጤፍም ሳትቆጥረኝ ጥላኝ ሄደች። መሃንነቴን አሳየችኝ.....» አለችው በአንድ በኩል የውስጧን ለመተንፈስ ተገፋፍታ፣ በሌላም በኩል ሰማይነህ እንዲያዝንላት ብላ።

ሰማይነህ ግን ደበቃው የቆየችውን ነገር እንደ አዲስ ሲሰማ በሃዘኔታ ፊንታ ንዴቱ እየጨመረ ሄደ።

«ምንድነው የምታወሪው?!.....»

«አዎ፤ ደብቄህ ነው ሰማይነህ። ህይወት ወላጅ እናትና አባቷን ያጣችው ገና በህፃንነቷ ነው። እኔ ያሳደግኳት አክስት ነኝ እንጂ አልወልዳትም። ያልወለዱት ልጅ ልጅ ያለመሆኑን ዛሬ አሳየችኝ!» አለችው አይኖቿ እንባ አቅርረው ድምጿ እየተንሰቀሰቀ።

«ህይወት ልጄ አደለችም ነው የምትይኝ?!.....»

«አዎ፤ አልወስለድኳትም፤ እኔ መሀን ነኝ።»

«አንቺ ግን አታላይ ነሽ!.....ሸርሙጣ!....ልጄ ናት ብለሽ አይደለም እንዴ የዳርሽልኝ?! ከሜዳ ላይ አግኝተሽ ያሳደግሻትን ልጅ ነዋ እኔ ላይ የጣልሻት?.....»

«ከሜዳ እንኳን አይደለም......የህቴ ልጅ ናት።»

«ዝም በይ!......ባልወለድሻት ልጅ ከኔ ከሰማይነህ ጋራ ጡት ልትጣቢ ፈልገሽ ነዋ የቀለድሽብኝ ያስቀለድሽብኝ?!.......የአሮጊት አታላይ እንዳንቺ አላየሁም።»

ሁለቱም ተነስተው ቆመው፣ እሱ እየጮኸ ሲያስፈራራትና እጁን እያወናጨፈ ሲዝትባት፥ እሷ በፍሀት እየተንቀጠቀጠች ስትሸሸው ትያትር የሚሰሩ ተዋናዮች ይመስሉ ነበር። «አይ ጊዜ» አለች ወይዘሮ ስራሽ በልቧ፣ የጊዜና ሁኔታዎች መለዋወጥ አስገርሟት። ካሁን በፊት እዚች ክፍል ውስጥ ለብቻዋ ጠርቷት ከኪሱ ወርቅ አውጥቶ የሸለማት ጊዜ ነበር። በአማችነት ፍቅር ከንፈው ንፋስ በመሀከላቸው አይግባ ያሉበት ጊዜ ነበር። ዛሬ ደግሞ ጊዜው ተለውጦ እዚችው ክፍል ውስጥ ፀብ ፈጠሩ።

«ለእኔ አታዝንልኝም ማለት ነው ሰማይነህ?» አለችው እንባ አውጥታ እያለቀሰች።

«ምንሽ ያሳዝናልና ነው የማዝንልሽ?!»

«እኔምኮ ከሀያ አመት በላይ ደክሜ ያሳደግኳትንና ያስተማርኳትን ልጅ ነው ያጣሁት....ባይቆጭ ያንገበግባል።»

«እሱ የራስሽ ጉዳይ ነው!» ብሎ ጥሎአት ወጣ። ከዚህ በኋላ ሕይወትን ለመፈለግ ወዴት እንደሚሄድ አያውቅም። ወ/ሮ ስራሽ እናቷ ያለመሆኗን መስማቱ ተጨማሪ ራስ ምታት ሆነበት። ፀጉሩን እየነጨና ጥርሱን እያንቀጫቀጨ ወደ ውስኪዋ ቤት ገባ። እሷም አገጯን በመዳፏ ደግፋ እያዘነች ተከተለችው።

ውስኪ ቤቷ ውስጥ አቡበከርና ይትባረክን ገና ከማየቱ ዓይኖቹ ደም ለበሱ። «ምቀኞቼ» ስለሚላቸው አሁን ህይወት ጠፍታበት በመጠቃቱ እንደሚደሰቱ ያውቃል። ስለዚህ ቀድሞ ሰደባቸው።

«ቤሽቲያ ሁሉ!» አላቸው በደፈናው።

ይትባረክና አቡበከር በመናቅ አይነት ደረታቸውን ነፍተው የራሳቸውን ጨዋታ የሚጫወቱ መሰሉ። ውስኪ ቤቷ ፀጥ ረጭ አለች። ሰማይነህን የሚያውቁት ሁሉ የዛሬው ሁኔታው ከስካር በላይ ስለሆነባቸው ደንግጠው ዝምታን መረጡ።

ጎርፉ የማይከፍልበትን መጠጥ በማግኘቱ እነ ይትባረክን ተጠግቶ ቶሎ ቶሎ እየጠጣ ነበር። አንድ ስፔሻል ክትፎ ጥርግ አድርጎ ከበላ አንድ ሰአት ያህል ባይሞላውም አሁን እንደ ገና ርቦት ነበር። ክትፎዋን እንደ ክኒን ነው የሚቆጥራት። እንጀራ በወጥ ካልበላ አይረካም። ወጥ ነገር ከአልኮል መጠጥ ጋር ለብዙ ሰዎች ባይስማማም ጎርፍነህን ምንም አይለውም። ተንዝናቶ ማግሳት ይጀምራል።

መደምደሚያ መጥቶ ከባህሩ ፂሞ ጋር እየተጫወተ ጥጉን ይዞ ቆሞ ነበር። የሰማይነህን ሁኔታ ለማየት ስለ ጓጓ እዚህ ውስኪ ቤት ሊያገኘው እንደሚችል ገምቶ ነበር የመጣው። ከበሩ ውጭ መኪናውን ሲመለከት ፀብ እንዳይፈጥርበት ፈርቶ ላለመግባት አመንትቶ ነበር። በኋላ የባህሩ ፂሞን መኖር ሲያረጋግጥ ከለላ እንዳገኘ ሰው ተደፋፍሮ ገባ።

ሰማይነህ ከጓዳ እንደ መጣ መደምደሚያን ቶሎ አልተመለከተውም። እነ አቡበከር ላይ ከአፈጠጠና ተሳድቦ መልስ ካጣ በኋላ ዘወር ሲል ተመልከተው።

«አንተ ደግሞ ምናባክ ልታደርግ መጣህ?!.....» በማለት ጮኸበት።

«ፈልገሽኝ ነበር ስላሉኝ ነው። ቤት ሄጄ ስላጣሁህ ምናልባት እዚህ አገኝህ ይሆናል ብዬ ነው የመጣሁት» አለው በተረጋጋ ድምፅ።

«ምናባክ ታደርግልኛለህ?።......»

«ተው እንጂ ሰማይነህ፣ ይሄ ልጅ ጥሩ ወንድምህ መሆኑን ነግሬሀለሁ» አለው ባህሩ ፂሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፁን በማሰማት።

«እንግዲያ ህይወት የተደበቀችበትን ቦታ ንገረኝ.....»

«የምታውቅ ከሆነ ንገረው.....»

«እኔ እራሴ ለወሬው እንግዳ ነኝ። እንዴት ብዬ የሄደችበትን አውቃለሁ?!.....» በማለት መደምደሚያ ዋሻቸው።

«አገኛታለሁ። የትም አታመልጠኝም» እያለ ሰማይነህ ሲዝት ጎርፉ ተደርቦ «እናገኛታለን አታመልጠንም» በማለት አጀበው።

መደምደሚያና ጎርፉ እንደ ጣውንት በርቀት ተገለማመጡ። መደምደሚያ ገና እንደ ገባ ያየው ቢሆንም ሊያነጋግረው አልፈለገም። የአሁኑ ፉከራው አናድዶት ነው የገላመጠው። በልቡ «.....ሆድህን ከሞላህ አነሰህና አንተን ብሎ ፍላጊ» እያለው ነበር።

ባህሩ ፂሞ የሰማይነህ ሁኔታ ስላሳዘነው ደፍሮ ሊያፅናናው ሞከረ። «አይዞህ ሰማይነህ፣ ሀሞትህን ኮስተር አድርገው። በሴቶች ለመጠቃት አንተ የመጀመሪያ ወንድ አይደለህም። ደግሞም ሀብት እስካልህ ድረስ ለሴት አትጨነቅ። ሚስትህ ብትሄድ ሌላ ሚስት ታመጣለህ።»

«እንደሱ አይደለም ባህሩ፤ ሀብቴ ሚስቴ ናት፤ ህይወት ከሌለች ሀብቴ የለም። አውቀዋለሁ......ተነግሮኛል!»

ሰማይነህ ይህን ሲናገር ወ/ሮ ስራሽ፣ ይትባረክና አቡበከር ሦስቱም በድንጋጤ እርስ በእርስ ተያይተው ቶሎ አይናቸውን ሰበሩ።

«እመነኝ ሰማይነህ፤ እኔ ልንገርህ። ለጊዜው ያለ እሷ የማትኖር ይመስልሀል፤ ያናድድሀል። አየህ ቅናት ከፍቅር ጋር ይወለዳል፤ ነገር ግን አብሮት አይሞትም፤ የሚል የጥንት አባባል አለ። ሀሞትህን ኮስተር አድርገህ ካልተውከው አይተውህም። ውስጥ ውስጡን ይቆረጥምሀል፤ ያኝከሀል፤ ይፈጭሀል። ናፖሊዮን እንደ ተናገረው «በፍቅር ላይ ድል መቀዳጀት የሚቻለው በመሸሽ ብቻ ነው» እያለ ብህሩ ፂሞ ወተወተው።

ሰማይነህ ከፊል ንግግሩን እንዲያውም አላዳመጠውም። ለብቻው በውስጡ እየዛተና ራሱን እየነቀነቀ ከቆየ በኋላ፣ «....ለእኔ ውስኪ አይቀርብልኝም እንዴ?!» በማለት ጮኸ። ወ/ሮ ስራሽ በንዴቱ ላይ መጠጥ ሲጨመርበት የሚያመጣውን መዘዝ ፈርታ አልቀዳችለትም ነበር።

«እሺ፤ የኔ ጌታ» ብላ በማባበል ጎደሎ ጠርሙስ አንስታ ልትቀዳለት ስትል «ሙሉ ጠርሙስ ከፈቺ» በማለት አመናጨቃት።

ጎርፉ ምግብ አሰኝቶት ሆዱን እያከከ ባለበት ሰዓት ሌላ አዲስ ጠርሙስ ውስኪ መታዘዝኑ ሲመለከቱ «ይህን ሁሉ የምንጠጣ ከሆነማ ምግብ ማዘዝ ይኖርብናል» እያለ ለብቻው እያጉረመረመ ነበር።

ወ/ሮ ስራሽ ሙሉውን የውስኪ ጠርሙስ አውርዳ ከመክፈቷ ሰማይነህ ከእጇ ላይ ቀማትና «በመለኪያ መጠጣት ትቻለሁ!» ብሎ ጠርሙስን አፉ ላይ ደገነ።

ሁሉም ደንግጠው ስለፈሩ ሊያስጥሉት አልሞከሩም። አንዴ በደንብ ተጎንጭቶ ሲያበቃ ጠጪዎቹን ሁሉ እየገረመመ «ብስብሶች!» አላቸው።

መለስ የሰጠውም ሆነ ቀና ብሎ የተመለከተው አልነበረም። ጎርፉ ጠጋ ብሎ ጠርሙሱን ከእጁ ላይ ሊቀበለው አመናጭቆ ገፈተረው።

«ወይ አበሳዬ!.....እንዲያው በምን ቀን ይሆን ዕዳ የገባሁት!» እያለች ወ/ሮ ስራሽ አማረረች። ሁሉም ነገር ከቁጥጥሯ ውጭ እየሆነ መሄዱና ያልታሰበ ረብሻ መነሳቱ ግራ አጋብቷት የምታደርገውን አሳጥቷት ነበር። ገፅዋ ላይ ታይቶ የማይታወቅ ጭንቀት ለመጀመሪያ ጊዜ እየታየ ነው። ለረዥም ዓመታት እጇን ያልሰጠች ሴትዮ ዛሬ በአንድ ቀን ውስጥ በደንበኞቿ ፊት ያረጀችና የወደቀች ሆና ተሰማአት።

ሰማይነህ ጠርሙሱን ሳይለቅ ለሁለተኛ ጊዜ ከልብሶ ሲጠጣ ባህሩ ፂሞ ተንደርድሮ ያዘው። ሆኖም ሙሉ በሙሉ አላስጣለውም። ጠርሙሱን በአንዴ ግማሽ አድርሶታል። የተረፈውንም ከባህሩ ጋር ታግሎ ለመጠጣት ስላስቸገረው እንደ ምንም መንጭቆ ወደ መደርደሪያው ሲወረውረው ሌሎች የመጠጥ ጠርሙሶችን ጨምሮ እየተሰበረ ረገፈ። ውስኪውም ሜዳው ላይ ፈሰሰ። ወ/ሮ ስራሽ መግቢያ እንዳጣች ዓይጥ ዓይኖቿን እያቁለጨለጨች ኩስስ ብላ ቀረች።

መጠጡ ወደ አእምሮው ደርሶ እስኪጥለው ድረስ ባለችው አጭር ደቂቃ ሰማይነህ የቻለውን ሁሉ አደረገ። ተሳደበ። ጮኸ። በእግሩም በእጁም ዕቃዎች ሰባበረ። ተንፈራገጠ። በመጨረሻም ወደቀ።

«ወይኔ ወንድሜን! ህይወትም በአቅሟ ሴት ሆና አሳደበችህ?! ግዴለም፤ በሴት ለማበድ አንተ የመጀመሪያ ወንድ አይደለህም» እያለ ባህሩ ፂሞ ከወደቀበት አነሳው። በኋላ ውስኪ ቤቷ ውስጥ የተሰበሰቡት ሁሉ ተረባርበው ተሸክመው አወጡት። ይትባረክና አቡበከር በልባቸው እየሳቁበት ነበር። በአንዱ ማበድ ሌላው ሲስቅ!......

መደምደሚያ በሁኔታው አዝኖ ራሱን እየነቀነቀ ሬሳ እንደሚያጅብ ግርግሩን ተከትሎ ሲወጣ ከሌሎቹ ድምፆች ሁሉ የወ/ሮ ስራሽ ድምፅና ንግግር ሳበው።

«ወይኔ አፈር በሆንኩት!.....እኔው ነኝ ጥፋተኛዋ!....በምንም አይፈረድም፤ ጥፋቱ የኔው ነው» እያለች ስታዝን ሰማት። ነገሩ ከነከነው።

«እርስዎ ምን አደረጉ?» አላት መደምደሚያ እንደሚያዝን ሰው ተጠግቷት።

«እኔ አውቃለኋ ስራዬ!.....ምነው ሁሉም በቀረብኝ ኖሮ.....ልጄንም አጣሁ! እኔ ጉድ ሆኜ እሱንም ጉድ አደረግኩት!.....አይ ፈጣሪ አምላኬ!.....ምነው አፈር ሆኜ ባረፍኩት!.....» እያለች ማልቀሷን ቀጠለች።

ንግግሯን መደምደሚያ አዕምሮ ውስጥ ተቀርፆ እየደወለበት ከቤቷ ወጣ።

ሰማይነህ በሰዎች ተደግፎ መኪናው ውስጥ ሲገባና ጎርፉ ቁልፉን ሲያስነሳ የሰመመን ያህል እንደ መንቃት ብሎ «ጎ - ጎ - ጎር - ፉ» አለው።

«አቤት?.....»

«ህ....ህይወት እን....ፈ - ልጋት።»

«እና - ገ - ኛ - ታ - ለ....» ተናግሮ ሳይጨርስ ለሀጩ እየተዝረከረከ ወንበሩ ላይ ክንብል አለ። ጎርፉ በሁኔታው እያዘነ ጭለማውን ሰንጥቆ እየነዳ የቤታቸውን አቅጣጫ ያዘ።

ባህሩ ፂሞም መደምደሚያን ለመሸኘት መኪናውን አስነስቶ ተከታትለው ሄዱ።

«.....የሚተርፍ ይመስልሃል?» አለው መደምደሚያ በስጋት።

«በሲህ አያያዙ ያሰጋል» አለ ባህሩ ፂሞ።

«ምን መሰለህ.....» አለና መደምደሚያ ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ «የሰማይነህ ፍቅር ህይወት ላይ ብቻ አይደለም። ከእሷ መጥፋት ጋር ተያይዞ ሀበቱ እንደሚረግፍ አድርጎ ስለሚያስብ ከእጁ እንዳትወጣ ሲታገል ቆይቷል። በዚህ አቅጣጫ እንዲያስብ ያደረገው የጠንቋይ ምክር ነው። የበሽታውም ምንጭ ይሄው ነው። ይህንን ከንቱ ዕምነት ከአዕምሮው ካላስወገደ ሊተርፍ አይችልም» አለው።

«በድንቁርና ላይ የተመሰረተ ሀብት ችግሩ ይሄ ነው። ባልተጨበጠ ነገር ላይ ማምለክ ይወዳሉ፤ እና ሀብታቸው ይዞአቸው ይጠፋል።»

«ምን ማድረግ እንደሚቻል አይገባኝም።»

«የሚሰማኝ ከሆነ መምከር ነው፤ ነገር ግን በዚህ ሁኔታው ማንንም የሚያዳምጥ አይመስልም። ራሱ በፈጠራው የውዥንብር ዓለም ውስጥ ሰክሮ እየሰመጠ ነው። ብቻ አምላክ ይጠብቀው.....»

ሁሉም ተደናግጦ ወጥቶ ሲሄድ አቡበከርና ይትባረክ ብቻ ውስኪዋ ቤት ቀሩ። ሁለቱም በድል አድራጊነት ስሜት እየተኩራሩና የውስኪ ብርጭቆአቸውን እያጋጩ ይጠጣሉ፤ ፊታቸው ያበራል፤ የአንገታቸውና የእጃቸው ወርቅ ያብለጨልጫል።

ወ/ሮ ስራሽ ግን ሳትጠጣ ሰከራለች። የመንፈስ ጥንካሬ አጥታ በአንድ ጊዜ ወድቃለች። አዕምሮዋ ፍፁም ሰላም ስላጣ የምትይዘውና የምትለቅቀውን አጥታለች።

«ይሄ ሰውዬ በቃው!....ማበዱ ነው፤ ከእንግዲህ ሰው አይሆንም» አለች እየተርበተበተች።

«ማን?.....ሰማይነህ ነው? አሏት ሁለቱም ተኩራርተው እየሳቁ።

«አዎ ሰማይነህ.....ሁሉም ነገር ተበላሸ። ልጄም ጠፋች፤ እሱም አበደ!....ከእንግዲህ ምን ህይወት አለኝ?!......ይልቅ ለሰማይነህ እንንገረው.....ምናልባት ቢሻለው እውነቱን ይወቀው።»

«ምንድነው የምትነግሪው?......ጤና የለሽም እንዴ?» በማለት አቡበከር አፈጠጠባት።

«ሴትዮ፤ ከመሬት ተነስተሽ አትርበትበቺ። ውስኪ ቤትሽን እንደሆን ሰማይነህ ቢቀር እኛ እናደምቅልሻለን። ይህንን መዘላበሽን አቁሚ» አላት ይትባረክም ተደርቦ።

«አልችልም!.....ዝም ማለት አልችልም። አዕምሮዬ ሰላም አጣ።....ቀፈፈኝ!»

«ምኑ ነው የቀፈፈሽ?!......»

«ሁሉም ነገር ነው የቀፈፈኝ!.....አሁን መናዘዝ አለብኝ። ዕውነቱን ተናግሬ መሞት አለብኝ።»

በሴትዮዋ መርበትበትና መቀባጠር ይትባረክና አቡበከር ተደናገጡ። አዕምሮዋን እየሳተች መሆኗንም ገመቱ። ህመሟ የገንዘብ ችግር ከሆነ ሊጠግኗት ይችላሉ፤ የህሊና ባዶነት የሚያስከትለው የአዕምሮ ቀውስ ከሆነ ምንም ሊረዷት አይችሉም። ይህ ሁኔታዋ ምናልባት ለእነሱም የሚያሰጋ ስለሚሆን ሊያሳስባቸው ይገባል። አንዳቸው ከሌላቸው ለችግሩ መፍትሔ የሚያገኙ ይመስል አቡበከርና ይትባረክ ዓይን ለዓይን ተፋጠው በዝምታ ተያዩ። ሁለቱም በዝምታቸው ውስጥ ከወ/ሮ ስራሽ ጋር የፈፀሙትን ምስጢር በሀሳባቸው እየቃኙ ነበር።

ሁለቱ ነጋዴዎች በሀብት ላይ ሀብት ለመጨመር በሚያደርጉት ሩጫና ትንቅንቅ ከብዙ ሰዎች ጋር ሲተናነቁ፣ ሲጠላለፉና ሲገዳደሉ ኖረዋል። ከቅርብ አመታት ወዲህ ደግሞ ዋናው የንግድ ተፎካካሪያቸውና ተቀናቃኛቸው እየሆነ የመጣው ሰማይነህ ሽብሩ ነበር። በተለያየ የንግድ ዘርፍ የዕቃ ግዢና የዕቃ አቅርቦ ጨረታዎች ተወዳድረው ሊያሸንፉት አልቻሉም። በሀብት እየበለጣቸው ስለመጣና በገንዘቡ ኃይል እያሸነፈ ስለሄደ እሱን ጠልፈው የሚጥሉበትን መንገድ ለረዥም ኃይል ጊዜ ሲያስቡበት ቆይተዋል። ከወርቅ ቤቱ በስተቀር ሌሎቹ የተሰማሩባቸው የንግድ ዘርፎች ተመሳሳይ ስለሆኑ ሊሸሹት ወይንም ንቀው ሊተውት አይችሉም። አብረው እየጠጡና እየተሳሳቁ፣ ላለመበለጥ ተጠባበቀው፣ በስውር ለመጠላለፍ ተዘጋጅተው «በሬ ካራጁ» ሆነው ሲኖሩ አጋጣሚው ወ/ሮ ስራሽ ቤት ተፈጠረ።

ወ/ሮ ስራሽ ቤት የሚተዋወቁ ነጋዴዎች መገናኛ መተያያ፣ መገበያያ፣ መገለማመጫና መፎካከሪያ ሆና ነበር የቆየችው። ህይወት ስዩም አክስቷን ለመርዳት ወደባንኮኒው ከመጣችበት ጊዜ ጀምሮ ደግሞ የብዙዎቹ ዓይንና ልብ እዚችው ቆንጆ ልጃገረድ ላይ በማረፉ እሷን የማጫወትና በእጅ የማስገባት ፉክክር ተጧጧፈ። ውስኪ ቤቷ ውስጥ ብዙ ብር በማፍሰስ ወ/ሮ ስራሽን ማደንዘዝና «ልጇን» ከጉያዋ ነጥቆ መውሰድ የብዙዎቹ ፍላጎት ሆነ። ቁመና፣ አዕምሮ፣ ምንትሴ የሚባሉት ነገሮች ወ/ሮ ስራሽ ውስኪ ቤት አይሰራም። የእሷም መፈክር «ገንዘብ ያለው ያሸንፋል» ነበር።

ሰማይነህ እንደ ሌላው የንግድ መስክ ሁሉ ህይወትንም «ለመግዛት» ግንባር ቀደም ተፎካካሪ ሆነ። ወ/ሮ ስራሽም ህይወትን ለከፍተኛ የጨረታ አሸናፊ ለሰማይነህ ሽብሩ ለመስጠት ልቧ መከጀሉ እያስታወቀባት መጣ።

አቡበከር ሴቶቹን እንደ ሸሚዝ በመቀያየር የታወቀ ነው። ይትባረክም ደግሞ አልፎ አልፎ ያጅበዋል። ሁለቱም ሴቶች ላይ ስፍስፍ ብለው የሚወድቁ ሳይሆኑ ሴትን ለወረት የሚፍልጉ፣

በገንዘባቸው ተመክተው በሴቶቹ የሚቀልዱ መሆናቸው ይታወቅባቸዋል፡፡ መጀመሪያ ሁለቱም ህይወትን ከጅለዋት ከሰማይነህ ጋር ፉክክር ጀምረው ነበር፡፡ ሰማይነህን በዚህ አጋጣሚ ጠልፎ መጣል እንደሚቻል አሰሉ፡፡ ህይወት ሰማህነህን በፍቅር እንድታሳብድላቸውና ስራውን እድንታዘናጋላቸው ተመኙ፡፡ በሴት ፍቅር ረገድ ምንም ልምድ እንደሌለው ያውቃሉ፤ በቀላሉ መጫወት እንደሚሆን አልተጠረጠሩም፡፡ ገንዘብ በመሰብሰብ ረገድ እሱ ቢበልጣቸውም በአዕምሮ ብልጠት አይደርስባቸውም፡፡ እነሱ አቅጣጫቸውን ቀይረው እንደሚያስፈልግ አመኑበት፡፡ ደካማ ጎኑን ተጠቅሞ በቁሙ ጠልፎ መጣል ይቻላል፡፡ ህይወት ለጠለፋው ጥሩ ገመድ ሆና ታገለግላቸዋለች፡፡ ልባቸው ሌላ ስራ እያውጠነጠነ ህይወትን ፈላጊ መስለው በመቅረብ ሰማይነህ ለዕልህ ጋብዘው የሚፈልጉት ወጥመድ ውስጥ አስገቡት፡፡ ሀሳቡን ሳይቀይር በማከታተል የበለጠ ዕብደት ውስጥ ሊጨምሩት ተዘጋጁ፡፡ ‹አትጠራጠር፤ ሰማይነህ በልጅቷ ውበት ሰክሮ ሲናውዝና ተመልካቾቿን በቅናት ሲከታተል እኔና አንተ ያለ ተቀናቃኝ ሥራችንን እንሰራለን› ተባብለው ተደፋፈሩ፡፡

አንድ ቀን ወ/ሮ ስራሽን ለብቻዋ አግኝተው አነጋገሯት፡፡

‹ይችን ልጅሽን.....እንዴት ነው?› አላት አቡበከር እንደ ቀልድ አድርጎ

‹እንዴት ነው ማለት ምንድን ነው? አለች ወ/ሮ ስራሽም አዝማሚያው እየገባት፡፡

‹እንቅመሳት ማለቴ ነዋ.....›

‹ምነው እባክህ!.....ልጄን ወጥ አደረግካት እንዴ?›

«አይደለም፤ የምታስጎመጅ ፍሬ ሆናለች ማለቴ ነው›

‹እንዲያው በከንቱ አትድከሙ፡፡ እኔ ልጄን በወግ በማዕረግ እድራታለሁ እንጂ ከማንም ጋር እንድትቀብጥ አልፈቅድላትም፡፡.....» ድንግልናዋም እንደ ተጠበቀ ነው፡፡›

‹ፈትሸሻታል እንዴ?› አላት ይትባረክ ጣልቃ ገብቶ፡፡

‹ባልፈትሻትም.....አስተዳደጓን የማውቀው እኔ ነኝ፡፡›

‹እኔ መቼም ባለ ትዳር ነኝ፡፡ እንግዲህ ለአቡበከር ዳሪለት፡፡›

‹ሁለታችሁም አንድ ናችሁ፡፡ አንተኛው ያገባህ ወንደላጤ.....አንተኛውም የዕድሜልክ ወንደላጤ!......ሁለታችሁም ለጥሩ ትዳር አትሆኑም፡፡›

‹ነቅተንብሻል እባክሽ፤ እኛን የምታከላክይው ህይወትን ለሰማይነህ ለመዳር አስበሽ ነው› አለና አቡበከር በነገር ጎሸም አደረጋት፡፡

‹ቢሆንልኝማ በምን ዕድሌ! ለሰማይነህ በአስር ጣቴ ፈርሜ እሰጠዋለሁ፡፡›

‹መቼም ሀብት አለው ብለሽ ነው.....፡፡›

‹በሀብቱ ብቻ አይደለም፡፡ ፀባዩስ ቢሆን!....አይንቀዠቀዥ፡፡ እንደናንተ ከአስሯ ሴት ጋር አይልከሰከስ፡፡ ኩራቱም ቢሆን ደስ ይለኛል፤ ወንድ ልጅ ኮራ ሲል ጥሩ ነው፡፡ ሴት ፊት የሚቅለሰለሱና ይቺንም ያቺንም ለመቅመስ የሚቅበዘበዙ ወንዶች ወረተኞች ስለሆኑ ለትዳር አይሆኑም፡፡ ሰማይነህን ሳውቀው እንዲህ አይነት ነገር የለበትም፡፡ እንዲያውም ከስራው ሌላ ሴት የሚያውቅ አይመስለኝም› ብላ ፈገግ አለች፡፡

‹እንኳን ቁርጣችንን አወቅነው፡፡ በይ ለእሱው ዳሪያትና እርማችንን እናውጣ፤ እሱም ቢሆን ወዳጃችን ስለሆነ ተቃውሞ የለንም፡፡ እኛም ባናገኛት የጓደኛችን ሚስት ሆና ማየታችን ደስ ያሰኘናል› አላት አቡበከር፡፡

‹ችግሩ የእሱ ፍላጎት በግልፅ ያለመታወቁ ነው› አለቻቸው፤ ለጨዋታው ቀዳዳ በማግኘቷ እየተደሰተች፡፡

‹እንዴት?.....› አሏት ሁለቱም በአንድነት

‹ህይወቴን እንደፈለጋት በእርግጥ ያስታውቅበታል፡፡ ነገር ግን ላግባሽ ብሎ ጠይቆአት አያውቅም፡፡ ምናልባት ሀብት ስላለውና ብዙ ሴቶች እናግባህ እያሉ ስለሚጠይቁት ተምታቶበት ይሆናል፡፡ ወይንም እንደሱው ገንዘብ ያላት ሴት ማግባት ሊፈልግ ይችላል፡፡ መቼም ያለ ምክንያት እስካሁን ሳያገባ አልቀረም፡፡›

‹ይሄ እንኳ ምንም ችግር የለውም፡፡ ቀላል ነው፤ መፍትሔው ይፈልገለታል› አላት አቡበከር ተዝናንቶ፡፡

‹እንዴት ያለ?› ስትል ወ/ሮ ስራሽ ጉጉቷ ፊቷ ላይ በግልፅ ይነበብ ነበር፡፡

‹ህይወት ለሰማይነህ መዳር የአንቺ ፍላጎት ከሆነ እኛ ልንረዳሽ እንችላለን፡፡ ጭራሽ ሀሳቡም ስሜቱም እንዳይወጣ ማድረግ ይቻላል፡፡›

‹እኮ እንዴት ተደርጎ?!›

‹ለጠንቋይ ነግሮ በጠንቋይ ማስነገር ነዋ!›

‹ሴጭ! እናንተ ትቀልዳላችሁ፡፡ እኔ ከልቤ ነው፡፡›

‹እኛም ከልባችን ነው፡፡ ከህይወት ሌላ ሴት ዕጣ ክፍሉ እንደማትሆንና ህይወትን ቶሎ በእጁ ማስገባት እንዳለበት ካለበለዚያ ፈላጊዋ ብዙ ስለሆነ እንደሚያገኛት፣ ካገባትም በኋላ ጠበቅ አድርጎ እንዲይይዛትና እሷን ካጣ ሀብቱም እንደሚረግፍ ጠንቋዩ እንዲነግረው ማድረግ ብቻ ነው፡፡›

‹የቱ ጠንቋይ?!› አለች ወ/ሮ ስራሽ፣ ድንጋጤ፣ ግር መሰኘት፣ እና ደግሞ ብርቱ ጉጉቷ ገጿ ላይ ተመሰቃቅሎ እየተነበበ፡፡

‹ሰማይነህ የሚሄድበት ጠንቋይ ነዋ!› አላት አቡበከር

‹እንዴት ታውቃለህ?....›

‹አንቺ ምን ቸገረሽ! እና እናውቀዋለን፡፡ መረዳት ከፈለግሽ ልንረዳሽ ዝግጁ ነን፡፡ ልጅቷን እኛ ወይንም ሌላው እንዲሁ ከሚያማግጣት፣ እንደ ሀሳብሽ ጥሩ ትዳር ይዛ ሀብት ውስጥ ስተት ብላ ገብታ እንድትቀመጥልሽ አንቺኑ ለመርዳት ነው፡፡ ምንም ቢሆን የረዥም ጊዜ የውስኪ ደንበኞችን ነሽ፤ ልጅሽን በወግ በማዕረግ ድረሽ አለምሽን እንድታይ እንፈልጋለን፡፡›

‹ቆይ - ቆይ.....ጠንቋዩ እሺ ብሎ ነገር የተባለውን ይነግራል ወይ?›

‹ይነግራል፡፡ ያው የሚጠይቅሽን ገንዘብ ትከፍያለሽ›

‹የገንዘቡ ምንም ችግር የለውም፡፡......ግን እንዲህ አይነቱ ጠንቋይ እውነት ባለ ውቃቢ ነው ወይንስ አባይ ጠንቋይ?›

‹ጉዳይሽ ይፈፀምልሽ እንጂ አንቺ ምንስ ቢሆን ምን አስጨነቀሽ!›

‹ተዓምር ነው!.....ሆሆሆ!....እውነት እንዳፋችሁ ከሆነልኝማ አንድ ጠርሙስ ውስኪ አወርድላችኋለሁ፡፡ ያውም ብላክ ሌብል!› በማለት እየተፍነከነከች ቃል ገባች፡፡

አቡበከርና ይተባረክ ሰማይነህ በድብቅ የሚሄድበትን ጠንቋይ ስለሚያውቁት የተፈለገውን ጉዳይ እንዲፈፅም አጋብቡት፡፡ መንገር ያለበትን ነገሩት፡፡ የህይወትን መልክ፣ ቁመና፣ ፀባይ፣ የዕድሜ ክልልና ሌሎችም ማወቅ ያለበትን ነገር ነገሩት፡፡ ህይወትን ፈላጊዎችና የሰማይነህ ‹ምቀኞች› ተብለው

የሚጠረጠሩትን አሳወቁ። ከዚያ በኋላ አዋቂ ሆኖ ቀርቦ በሰማይነህ ጭንቅላት ውስጥ ሰፈረ። አዶከበሬውን እየመታ ስለ ህይወት ለሰማይነህ የሚነግረው ትንሽ ጥርጣሬ ውስጥ የሚጨምር አልነበረም። ሰማይነህ የጠንቋዩን ትዕዛዞች አዕምሮው ውስጥ በማይለቅ ቀለም መዝግቦ ምቀኞቹን ለማሸነፍና የሀብቱን መርገፍ ለመከላከል ህይወትን የመግባቱን ፈጣን ርምጃ ወሰደ። ከጠንቋዩ እንደተነገረውም ሳያመነታና ሳይወላውል ተከታልቦ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ጋብቻውን ፈፀመ።

‹ወቸ ጉድ! ተዓምር ነው› እያለች ወ/ሮ ስራሽ ጉዳይዋ ለተፈፀመበት የተጠየቀችውን ሁለት ሺህ ብር ለጠንቋዩ ከፈለች። አቡበከርና ይትባረክ ደግሞ ሦስት ሺህ ብር በድብቅ ጨመሩለት። ሁሉንም እነሱ ቢከፍሉ በወደዱ ነበር። ሆኖም የእነሱን ስውር የጠለፋ መንገድ ደብቀው ጉዳዩን የእሷ ብቻ ለማስመሰል እሷን በግልፅ አስከፍለዋት እነሱ በድብቅ ጨመሩለት።

ሁሉም ደስተኞች ሆኑ። ሁሉም በውስጣቸው የአሸናፊነት ስሜት ተሰማቸው። ሰማይነህ ህይወትን በማግባቱ ሲደሰት ህይወት ለሰማይነህ በመዳሯ ወ/ሮ ስራሽ ተደሰተች። እነ አቡበከር ደግሞ ሰማይነህ ወጥመዳቸው ውስጥ በማስገባታቸው ተደሰቱ። ላይ ላዩን ግን ህይወትን የከጀሉ መምሰላቸውንና ሌሎቹንም በእነሱው አይነት እየቀሰቀሱ ሰማይነህን በቅናት ማሳበዳቸውን አላቋረጡም።

እንደ ጠበቁት ሆነ። ያሰቡትም ተሳካላቸው። ሰማይነህ በህይወት ቁንጅና ሰክሮ በቅናት ሲቅበዘበዝ እነሱ ያለ ተቀናቃኝ ስራቸውን ይሰሩ ጀመር። የአሁኑ ሁኔታው ከጠበቁት በላይ ቢሆንባቸውም ምንም ሐዘን አልተሰማቸውም። ጨርቁን ጥሎ ራቁቱን በአውራ መንገድ እየለፈለፈ ቢሄድም ደስ ይላቸዋል። ይልቅ አሁን ያሳሰባቸው የወ/ሮ ስራሽ መቀባዠርና በፍሀት መንቀጥቀጥ ነው።......

ይትባረክና አቡበከር ከወ/ሮ ስራሽ ጋር የፈፀሙትን ምስጢር ወደ ኋላቸው ዘወር ብለው በሀሳባቸው ከቃኙ በኋላ እንደ ገና አፈጠጡባት።

«ዝም በልሽ አትቀባዥሪ!....አብደሽ እንደሆነ ንገሪን» አላት አቡበከር በቁጣ ድምፅ።

«አሁን አይደለም፤ ድሮ ነው ያበድኩት። ‹የቀበጡ እለት ሞት አይገኝም› ይባላል።»

«ረጋ በይ እስቲ!.....የቀወሰው አማችሽ እንጂ ባልሽ ወይንም ልጅሽ አይድለእም እኮ!»

«የእሱስ ውለታ ከባልም - ከልጅም ይበልጥ ነበር እኮ። ባለውለታዬ እኮ ነው....ምስኪን ሰማይነህ!.....ከቅናት በስተቀር ምንም አያውቅም እኮ!....ውስጡ ባዶ እኮ ነው። እኛ ግን ለምንድነው እንደዚያ የጨከንበትና ጣጣ ውስጥ የጨመርነው?! ምስኪኑን ሰው እኮ አሳበድነው። አሁን አሳዘነኝ።.....ለራሴም አዘንኩኝ፡ መከራዬን አይቼ ያሳደኳትን ልጄን ማጣት አልነበረብኝም። ሁሉንም ነገር መናዘዝ አለብኝ። ነፍሴ እውነቱን አፍረጥርጣ እረፍት ብታገኝ ይሻለኛል» እያለች አለቀሰች።

«ይልቅ በርሽን ዝጊና ተኚ። አረፍ ብለሽ ስትነሺ ቀለል ይልሻል። ይሄ የሚረብሽም ነገር ይለቅሻል» ብሎ አቡበከር ሂሳቡን አወጣና ከፈለ።

«አልፈልግም፤ ገንዘባችሁን ይዛችሁ ሂዱ። ባዶ ቤት ውስጥ ገንዘብ ቢከማች ምን ያደርጋል?!......ባዶ ቤት ውስጥ ወርቅ ቢከማች ምን ያደርጋል?!......ቤታችን ውስጥ ሰው የለም እኮ! ህይወት የለም እኮ! ባዶ ሆኗል። ከውስጡ የፈሰሰውን ውስኪም ተመልከቱት፤ የእኛም ደም እንደዚሁ ፈስሶ አፈር ይመጥጠዋል» በማለት ስትቀበጣጥርባቸው ሁለቱ ነጋዴዎች ወጥተው ሄዱ።

«የዚች ሴትዮ አዝማሚያ አላማረኝም» አለ ይትባረክ በሯን ከወጡ በኋላ።

«አዎ፤ ደህና ሴት ስትመስል እንዲህ ጭንቀታም ናትና ለካ!» አለ አቡበከርም።

«ምን ማድረግ ይሻልላ?»

«ለምኑ?»

«ሚስጥሩን ልትለፈልፍ ትችላለች.....»

«ስትለፈልፍ ውላ ብታድር ራሷን ታሳጣለች እንጂ እኛን የምትጎዳን ነገር የለም። አጠገቧ ሆኜ ይሄንኑ ሳወጣ ሳወርድ ነበር።»

«እንዴት?.....»

«ይቺ ሴትዮ እኛ ሰማይነህን ጠልፈን ለመጣል ማቀዳችንን አታውቅም። ከጠንቋዩ ጋር ያገናኘናት እሷን ልንረዳት ነው የመሰላት። ስለዚህ ወንጀለኞች አይደለንም። ሰማይነህ የሚሄድበትን ጠንቋይ ቤት ጠይቃን አሳይተናታል። በቃ! ሌላው ሚስጥር ያከናወነችው እሷ ናት። ጉዳይዋንም የምታውቀው እሷው ናት። የእኛ እጅ ምንም ነገር ውስጥ የለበትም። ይህን ያህል መሸምጠጥ አያቅተንም።»

«እሱስ ልክ ነህ ግን.....»

«በሌላ በኩል ደግሞ ካየሽው ነገር ቢታወቅብን አደባባይ ቢወጣ እንኳ ወሬውና ሐሜቱ ያስጠላን እንደሆነ እንጂ በወንጀለኝነት የሚያስጠይቀን ተጨባጭ ነገር የለም። ሰማይነህ ላይ ጥይት አልተኮስንም። የአዕምሮ ጨዋታ ተጫውተን አሸነፍነው። አዕምሮው ደካማ ሆኖ ባልተጨበጠ እምነት ተሸንፎ መውደቁ እኛን አያስጠይቀንም።......»

«ለማንኛውም ጠንቋዩ ከአካባቢው እንዲሰወር ብናደርግስ!.....»

«ይሄም ጥሩ ሀሳብ ነው። የወ/ሮ ስራሽን ልፍለፋ ያልተጨባጭ ምስክር ያስቀረዋል።»

«በቃ ጠንቋይ በአስቸኳይ አሁን ያለበትን ቤት እንዲለቅ እናደርገዋለን።»

# ክፍል አስራ ስድስት

እሹሩሩ መውደድ፤ እሹሩሩ ፍቅር

እኔ እሻልሀልሁ፤ አንተ ልጅ አትቅር

ስበላ አይሀለሁ፤ ስጠጣ አይሀለሁ

ስተኛም ከጎኔ.....

አንተ ልጅ አትቅር እኔ እሻልሀለሁ።

.....በኔ ብሶ ፍቅሩ

ማባበል ይዣለሁ፤ እያልኩ እሹሩሩ....

የአስቴር አወቀ ዘፈን ነበር። ከየት መጣ ሳይባል ድንገት ህይወት ጆሮ ውስጥ ደወለላት። አጠገቧ ሬዲዮ ወይንም ቴፕ የለም። ከሄኖክ ጋር በጣም የሚወዱትን ዘፈን ወደ ኋላ አጠንጥኖ ያሰማት የገዛ አዕምሮዋ ነው። ከሄኖክ ጋር ያሳለፉትን የፍቅር ጊዜና ደጋግመው ይሰሙት የነበረውን ይህንን የአስቴር አወቀ ዘፈን ስታስታውስ እንባ ተናነቃት። ክፍን አውጥታ ሄኖክ ያለበት ድረስ በርራ ለመድረስ ተመኘች። ለትዝታዋ ማስታገሻ ይሆናት ይመስል፣ ብዙ ጊዜም እንደምታደርገው ሁሉ፣ የሄኖክን ደብዳቤ አውጥታ ደስ የሚሏትን መስመሮች ደጋግመማ አነበበቻቸው።

«.....ህይወትዬ ሙች እልሻለሁ። በልጅነት ፍቅራችን እምልልሻለሁ። ምን ጊዜም ልቤ ካንቺው ጋር ነው። ሁልጊዜም አስታውስሻለሁ።.....የታሰርሽበትን ሰንሰለት በጣጥሼ ነፃ አጠገቤ መሆንሽ ብቻ ነው የሚታየኝ። እንዴት እንደ ቸኰልኩ ልነግርሽ አልችልም። ነፍሴ ነሽ!....አንቺ ብቻ ነይል እንጂ እኔ አብስዬ አበላሻለሁ።.....ልቤ ውስጥ ያለሽው የመጀመሪያም የመጨረሻም ፍቅሬ አንቺው ነሽ። አንቺን ባቀፍኩበት ክንዴ ሌላ ሴት አላቅፍም።.....አንቺ ከሴቶች ሁሉ የበለጥሽ ነሽ።......የልጅነት ፍቅሬን የወሰደብኝን ቀማኛ እኔም በተራዬ አሳየዋለሁ። በአስቸኳይ እደርስልሻለሁ......በአካል የምንገናኝበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም!.....

የወደደቻቸውን ሀረጎች እንደ ዳዊት ደጋግማ እያነበበች ሄኖክን አስታወሰች። ከሰማይነህ ቤት በመውጣቷ ነፃነት አግኝታ፣ ማታ ከመደምደሚያ ጋር ሆነው ሁለት ጊዜ ሄኖክን ለማግኘት ወደ ውጭ ሀገር ስልክ ደውለው ነበር። ሆኖም ስልኩ አይመስልም። አሁንም እንደ ገና ለመደወል የመደምደሚያን መምጣት እየተጠባበቀች ነው።

ማታ መደምደሚያ ተለይቷት ከሄደ በኋላ ሆቴል ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቻዋን ስታድር ምንም ዓይነት ፍርሀት አልተሰማትም። ለአንዲት ቀንም ቢሆን ከሰማይነህ ቤት ነፃ መውጣቷ እፎይታ ሰጥቷት መንፈሷን አጠነከረው። ከዚያ በፊት የነበረው ሌሊትና ቀን በጣም የደከመችበትና የተንገላታችበት ስለ ነበር ያረፈችበትን ሆቴል እስክትረሳው ድረስ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወዷታል። በእርግጥ የቀን ሩጫዋና ጭንቀቷ በእንቅልፍ ልቧም እየታያት አስጨንቋታል፤ የእነ ሰማይነህ ፍለጋና ክትትል እንዲሁ ሲያቃዣት አድሯል።

ጠዋት ከመኝታዋ የተነሳችው ረፈድፈድ አድርጋ ነው። ለቁርስ መደምደሚያን ብትጠብቀውም ስለቆየባት ተላላኪውን ጠርታ መኝታ ክፍሏ ድረስ አስመጥታ ተመገበች። አሁን የገንዘብ ችግር የለባትም። ወርቆቿን መደምደሚያ ወስዶ፣ የሚያውቀው ቦታ አስገብቶ ዘጠኝ ሺህ ብር ሸጦላታል። ከዚያ ውስጥ ሁለት ሺህ ብር ማታውኑ በእጇ የሰጣት ሲሆን ቀሪውን ገንዘብ እሱው ጋ አስቀምጦላታል። ቅያሬ ልብሶችና ራሷን መለዋወጫ ነገሮችም እሷው ባዘዘችው መሠረት ገዝቶላታል። አሁን ልቧን የሰቀለው ወደ ውጭ ሀገር የምትሄድበትን ሁኔታ በአስቸኳይ

ያለመመለሱም ሀሳብ ላይ ጥሎአታል። ልብቧ ስለ ቸኮለ ሁሉም ነገር በአንድ ላይ እንዲሆን ትፈልጋለች። ይህ ሳይኖ ሲቀር ግን ታስባለች፤ ትጨነቃለች። ከኋላ የሚከተሏትን በፍጥነት ወደ ፊቷ ሮጣ ለማምለጥ ሀሳብ ትዋጣለች።

ከፍሏ ውስጥ ሆና ብቻዋን በሀሳብ ስትዋዥቅ የሰዓቱን መገስገስ ልብ አላለችውም ነበር። መደምደሚያ መጥቶ የከፍሏን በር ሲያንኳኳ ከጠዋቱ አምስት ሰዓት ተኩል ሆኗል።

«.....ተቀይሜሀለሁ» አለችው በሩን ከፍታለት ከገባ በኋላ፣ ከንፈሯን ጣል አድርጋ።

«ምነው ምን አጠፋሁ?» አላት እሱም ምክንያቷን ልቡ እያወቀው።

«ብቻዬን መሆኔን እያወክ ይህን ያህል ሰዓት ጥለኸኝ ትጠፋለህ? አስተዳደሬን ለመጠየቅ በጠዋት መምጣት ነበረብህ»

«ምክያቴን ስትሰሚ ቅያሜሽን ታነሺልኛለሽ። ከአንቺው ጋር ለተያያዘ ጉዳይ ውድያ ወዲህ ስል ነው ያረፈድኩት።»

«እኔ ደግሞ ቁርሴን ብቻዬን አልበላም ብዬ ብጠብቅህ ጠፋብህ.....»

«አይዞሽ ለምሳ ደርሼልሻለሁ።»

«በል አሁን ሄኖክ ጋ እንደውልለት። እኔን ያሳሰበኝ የእሱ ጉዳይ ነው። ቶሎ አግኝተነው የጉዞዬን ነገር መልክ ካላስያዝነው አየር ላይ ተንሳፍፌ መቅረቴ ነው»

ቁጭ ብሎ የነሰማይነህን ሁኔታ ለማውራት እንኳ ፋታ ሳይገኝ ተከታልበው ወደ ሆቴሉ እንግዳ መቀበያ ክፍል ሄዱ። የውጭ የስልክ መስመር ለማግኘት እዚያ ሄደው ሃላፊውን ማነጋገር ነበረባቸው።

አሁንም ደጋግመው ሞከሩ። የሄኖክ ስልክ ይጠራል፤ የደወሉት ቁጥር ትክክል ነው።

«አሜሪካን ሀገር አብዛኛዎቹ ስልኮች የመልዕክት መቀበያ እንዳላቸው ሰምቼአለሁ። የሄኖክ እንዴት ሳይኖረው ቀረ?.... እስቲ ለማንኛውም ቆይተን ደግሞ እንሞክርለታለን» በማለት መደምደሚያ ዘና ብሎ ተናገረ። ህይወት ግን እየተጨነቀች ነበር። ግራ መጋባቷ ፊቷ ላይ ያስታውቅበታል።

«.....ማታም፣ አሁንም......ይህን ያህል ጊዜ እንዴት እቤት ውስጥ አይኖርም?» ኧልችው።

«እንደምንሰማው ከሆነ የአሜሪካን ሀገር ኑሮ የሩጫ ኑሮ ነው። ብዙ ኢትዮጵያውያኖች ኑሮን ለማሸነፍ ሁለት ሦስት ቦታ ስለሚሰሩ ቤታቸው የሚያርፉበት ጊዜ አይኖራቸውም። የእንቅልፍ ሰዓታቸውም ውሱን ነው። ምናልባት ሄኖክም ከነዚህ ውስጥ አንዱ ይሆናል» አላት መደምደሚያ ጭንቀቷ ገብቶት ሊያፅናናት እየሞከረ።

«ስልክ የሚያነሳ ሌላ ሰው እንኳ ቤቱ ውስጥ የለም ማለት ነው?»

«እንግዲህ ባይኖር ነዋ።»

ወደ መኝታ ክፍሉ ሲመለሱም ህይወት በሀሳብ እንደተዋጠች ነበር። ውመደምደሚያ ስለሰማይነ ሊያወራት ቸኩሏል፤ እሷም ከአሁን አሁን በጉጉት ትጠይቀኛለች ብሎ ጠብቆ ነበር። ህይወት ግን ሃሳቧ ከሄኖክ ላይ ተነቅሎ ሌላ ነገር ልታስብ አልቻለችም።

«የንፅህና አምላክ እየረዳኝ ነው.....›. አላት በድንገት።

«እንዴት አለችው።

«ፈላጊዎችሽ እንዳይከታተሉሽ እግራቸውን ይዘልሻል። ሰማይነህ ሆነ ወይዘሮ ስራሽ ሁለቱም ታመው አልጋ ላይ ናቸው። በቀላሉ የሚነሱ አይመስሉም። ስለዚህ አንቺ ያን ያህል ራስሽን ለመለወጥም ሆነ ለመደበቅ መጨነቅ የለብሽም።»

«መታመማቸውን አንተ እንዴት አወቅህ?»

ማታ ከሷ ከተለየ በኋላ ጉዳዬ ብሎ ሁኔታዎችን ለመከታተል ወይዘሮ ስራሽ ውስኪ ቤት መሄዱንና እዚያ ያየውን በሙሉ ዝርዝር ከነገራት በኋላ «ሰማይነህ ለሊቱን ሀኪም ቤት ተወስዶ የህክምና እርዳታ ባይደረግለት ኖሮ በቁሙ የጨለጠው አልኮል ገድሎት ያድር ነበር። ከሞት አፋፍ ነው የተመለሰው። ቅድም ሄጄ ስጠይቀው ራሱን አያውቅም፤ በጣም አሞት ተኝቷል» አላት።

«እሱስ እሺ። አክስቴ ደሞ ምን ሆና ነው የሚያማት?» አለችው፣ ቀስ በቀስ ጉጉቷ እየጨመረ።

«አንችን ማታጣቸው ነዋ!.....በሆነው ነገር ሁሉ በጣም አዝነዋል። ማታ እንዳየኋቸውም በድርጊታቸው ሆነ በንግግራቸው ፀፀትና የአዕምሮ ጭንቀት ይነበብባቸው ነበር። ዛሬ ጠዋት ደግሞ ስራዬ ብዬ ልጠይቃቸው ስሄድ በጣም አሟቸው ተኝተዋል.....»

«ምኗን ነው ያመማት?»

«እሳቸውም አላወቁትም። ልብ ድካም ነው ይላሉ። የደም ብዛትም ሳይነሳብኝ አልቀረም ይላሉ። ለማንኛውም ሀኪም ቤት ሄደው እንዲታከሙ መከርኳቸው፤ እኔን እንደሚመስለኝ ግን የህመማቸው መንስኤ በተፈጠረው ያልጠበቁት ችግር ምክንያት ያንችን ልጅነትና የሰማይነህን ወዳጅነት ማጣታቸው ነው። ካነጋገራቸው መረዳት የቻልኩት ይህንን ነው። ከኒን በመዋጥም ሆነ በቀዶ ጥገና የማይድን አንድ ህመም አለ። ያም ባዶነት ነው።»

«የራሷ ጉዳይ!»....አለች ህይወት ለመጨከን በሚሞክር ድምፅ»

«እኔ ግን ሁሉቱም አሳዝነውኛል.....» አላት መደምደሚያ እራሱን እየነቀነቀ።

«ሰማይነህ ወንድምህ ስለሆነ፣ ምንም ቢሆን፣ ሊያሳዝንህ ይችላል። ላክስቴ ግን የምታዝንበት ምክንያት አይታየኝም። እሷ ለእኔ ያልሆነች ለማንም የምትሆን ሴት አይደለችም። ከግንዲህ ለሷ የማዝንበት አንጀት የለኝም....»

«ቆይ እንጂ!.....እንዲህ አድርገሽ አትማረሪ። ነገሩን በሌላ ጎን ተመልከችው። እኔንም እኮ ሰማይነህ ከቤቱ አባሮኛል፤ አስቀይሞኛል። አሁን ለሰማይነህ የማዝነው በወንድምነቱ ብቻ ሳይሆን በግለሰብነቱ ነው። እነዚህ ሰዎች፣ ሰማይነህም ሆነ ወይዘሮ ስራሽ የማህበረሰብ ውጤት የሆኑ ግለሰቦች ናቸው። ሁለቱም የኋላ ቀር ባህል ውጤቶች እንጂ ለብቻው የተፈጠሩ አውሬዎች አይደሉም። እነሱ የሚያንፀባርቁት በህብረተሰቡ ውስጥ ተደብቆ ያለውን እራስ ሁላችንም ውስጥ ያሉ ጥርጣሬና ቅናት ነው። ደረጃው የለያያል እንጂ ሁላችንም ውስጥ ያሉ በሽታዎች ናቸው። በሽታዎቹ ከፊሎቻችን ውስጥ ተደብቀው ይኖራሉ፤ እንደነሰማይነህ አይነቱ ላይ ደግሞ አፍጥጠው አደባባይ ይወጣሉ። እነዚህን በሽታዎች በትምህርትና በስልጣኔ ከውስጣቸው ያስወገዱ ጥቂት ሰዎች ይኖራሉ። አብዛኞቻችን ግን በውስጣችን ይዘናቸው ነው የምንኖረው። መደበቅ የቻልን እንደብቃቸዋለን፤ ያልቻልን እንገልጣቸዋለን። ይህ የድንቁርና በሽታ አንዳንዴ በተማሩትና በሰለጠኑትም ላይ ሲንፀባረቅ ታይዋለሽ። አባይን ከምንጩ እንደሚባለው ፀባችን ከግለሰቦች ሳይሆን ካራራቸው ህብረተሰብ ባህል ጋር መሆን አለበት። እነሱ ተራ ሟች ግለሰቦች ናቸው፤ ነገ ያልፋሉ። ሌሎቹ ከስር በእነሱ መንገድ እንዳይመጡ ነው ትግሉ የሚያስፈልገው....»

የመደምደሚያ ፍልስፍና ህይወትን እምብዛም አልሳባትም። በአስተያየቷ፣ አሁን ታዲያ እኔን ምን አድርጊ ትለኛለህ? የምትል ትመስላለች። መደምደሚያ ይህን ሳይታዘብ አልቀረም። እንደሌላ

ጊዜ ቢሆን ጥሩ ተማሪው ነበረች። አሁን የተረጋጋ አዕምሮ እንደ ሌላት ቢረዳም ስሜቷን ገፍቶ መናገር የፈለገውን አላቋረጠም።

«......አንዳንድ ነገር መገንዘብ አለብን። ሰማይነህ ለእኔ፣ ወይዘሮ ስራሽ ደግሞ ላንቺ ባለውለታዎቻችን ናቸው። ሌላው ቢቀር የዕለት እንጀራችንን መግበው አሳድገውናል። የረዥም አመታት ውለታቸው በአንድ ቀን ወይንም በአንድ አመት ግጭት ሊደመሰስ አይገባም.....»

«ይቅርታ አድርግልኝና.....የኔ አክስት ያሳደገችኝ ልትሸጠኝ ነበር። ጥሩ ዋጋ የሚያወጣ ከብት ነው ያደረገችኝ!.....»

«እኮ ቆይ! አድምጭኝ እስቲ። አክስትሽ ላደረጉት ነገር ሁሉ የራሳቸው የሆነ በጎ ምክንያት ይኖራቸው ይሆናል። ምክንያታቸው ባያሳምንሽ እንኳን ያለፈውን በማየት ማመዛዘንና መራራ ስሜትን ማስወገድ ያስፈልጋል። እኔ በበኩሌ ስር - ነቀል አብዮታዊነት ያስጠላኛል። ዛሬን ብቻ ማየት ጥሩ አይደለም። ውሳኒአችንም ሆነ የምንወደው እርምጃ፣ ያሁኑንና የወደፊቱንም ያመለካከትና ያመዛዘነ መሆን ይኖርበታል.....»

«አክስትሽ ቤት ተመልሰሽ ኑሪ እንደማትለኝ እርግጠኛ ነኝ» አለችው አነጋገሩ አስፈርቷት።

«አልልሽም። ከጉሮሽ አላደናቅፍሽም። ከእምነትሽ ውጪ እንድትሆኚም አላስገድድሽም.....ነገር ግን በአክስትሽ ላይ የፈጠርሽውን ጥላቻና መራራ ስሜት እንድታስወግጂ እለምንሻለሁ።»

«የጠላት እኮ የውስጥ ስሜት ነው። ለአፌ ያህል ብሸነግላት ምን ዋጋ አለው?!»

«የውስጥ ስሜትሽን አሳምኝው። ውለታ ቢስ አትሁን፣ ወደ ኋላ ዞር ብለህ አመዛዝን በይው። ብትበደይ እንኳን ይቅርታ በማድረግ የምታጪው ነገር የለም። ለአክስትሽ ግን ዘለዓለማዊ ደስታ ይሰጣቸው ይሆናል፤ ከባዶነት ህመም ያድናቸው ይሆናል።»

«እንዲያውም ባታስጨንቀኝ ደስ ይለኛል መደምደሚያ። እኔ ሃሳቤ ሁሉ ሄኖክ ጋ ነው። ስለ አክስቴም ሆነ ስለ ሰማይነህ በማሰብ መጨነቅ አልፈልግም።»

«አሁን አይደለም፤ ሁሉን ነገር ጨርሰን ወደ ውጭ ሀገር ስትሄጂ አክስትሽን ተሰናብተሽ ይቅርታን ማሳየት አለብሽ። አዕምሮሽ ውስጥ ቂም ይዘሽ መሄድ የለብሽም። ከዛ በኋላ ያንቺም፤ የሳቸውም አዕምሮ ጤነኛና ነፃ ይሆናል።»

«እሺ እዛው ያድርሰን። ጉዞው ከተሳካልኝ የዚህ ችግር የለውም» ስለጨቀጨቃት ተሸንፋ።

«እንዲህ የታላቅ ወንድምሽን ምክር ስትቀበይ ደስ ይለኛል።.....ሁላችንም አላፊዎች ነን፤ ነገ ከነገ ወዲያ ማቾች ነን። ላጭር እድሜያችን በቂም መስከር የለብንም» አላት መደምደሚያ ፈገግ ብሎ ከፍሏ ውስጥ እየተንጎራደደ።

ህይወት ለጥቂት ጊዜያት አንገቷን በመስኮት አውጥታ ወደ ውጭ ስትመለከት ከቆየች በኋላ ወደ መደምደሚያ ተመልሳ «ፍሎሪዳ ገብቼ እንደ ተመኘሁት የፊልም ተዋናይ ብሆን ምን እንደማደርግ ታውቃለህ?» አለችው።

«ምን ታደርጊያለሽ?»

«መጀመሪያ የምሰራው ፊልም የሴቶችን ነፃነት የሚመለከት ይሆናል። በደሉ በራሴ ላይ ስለደረሰብኝ በደንብ አድርጌ የምሰራው ይመስለኛል።??

«ብቻ ወንዶችን ልደምስስ እንዳትይ!»

«እንደ ሰማይነህ አይነቱን!.....»

«ሄኖክም እኮ ወንድ ነው።....»

እዚህ ላይ የምትመልሰው ያጣች ይመስል ከንፈሯን ወደ ውስጥ እየመጠጠች ዝም አለች።

«የጅምላ ጥላቻ ጥሩ አይደለም። መጥፎ ወንዶች የመኖራቸውን ያህል መጥፎ ሴቶችም አሉ። ቅድም እንደነገርኩሽ እነዚህ የመጥፎ አካባቢ ውጤቶች ናቸው። አንቺ ሰማይነህን ታማርሪያለሽ፣ ባህሩ ፂሞ ደግሞ ሚስቱን ያማርራል። ትዳሩን የማያከብር፣ ገንዘቡን በየሜዳው በትኖ የሚጨርስና ሚስቱን የሚያበሳጭ ወንድ የመኖሩን ያህል፣ ለትዳሯ ደንታ የሌላት፣ ብልጭልጭ ነገር ብቻ የሚያታልላትና የባሏን ልብ የምታቆስል ሴት መኖሯን መዘንጋት የለብሽም። እኔ ባለፈው ጊዜ እንዳጫወትኩሽ የጥናት ወረቀቴን ለማዘጋጀት የብዙ ቤቶችን ትዳር ተመልክቻለሁ። ባሎቻቸውን የሚያከብሩና የሚንከባከቡ ሴቶች እንደመኖራቸው መጠን ሚስቶቻቸውንም የሚንከባከቡና የሚያከብሩ ወንዶች አጋጥመውኛል። እንዲያውም አንድ ቤት ውስጥ ያጋጠመኝን ልንገርሽ። ሚስቱ በስራዋ ፀባይ ምክንያት ማታ አምሽታ ስለምትገባና ጥዋት በለሊት ስለምትወጣ የቤት ውስጥ ጣጣዋን ኃላፊነት ወስዶ የሚያስተዳድር ባሏ ነው። ሰራተኛ በሌለበት ጊዜ ባሏ ሽርጡን ለብሶ፣ ምግብ አዘጋጅቶ፣ ልጆች አጣጥቦ፣ እንጀራ ጋግሮ ሚስቱን ይጠብቃታል። ይህንን የሚያውቁት የመንደሩ ልጆች ባልየው ወደውጭ ሲወጣ ‹እንጀራ የሚጋግሩት ሰውዬ ቺ እያሉ ይቀልዱበታል.....እኔ እንደሚመስለኝ ዋንው ፍቅር ነው፤ መከባበር ያስፈልጋል። አንዱ የሌላውን ስብዕናና ነፃነት ማክበር መጠበቅ አለበት። በሁለቱም በኩል ፍፁምነት አይኖርም። ዋናው ነገር ‹አንተ ትብስ አንቺ ትብስ› ተባብሎ ጥፋትን እየተራረሙ መኖር ነው። ከየትኛውም ወገን ፍፁምነት መጠበቅ ጅልነት ይመስለኛል። ሁሉም ቢሆን ራሱን ወዳድ ነው። ጃክ ቢሊንግ ‹በዚህ አለም ከራሱ በላይ የሚወድህ ፍጡር ውሻ ብቻ ነው› ብሏል....»

መደምደሚያ ስሜቷ ውስጥ ገብቶ ሰፋ ያለ ገለፃ ሲያደርግላት ላጭር ጊዜም ቢሆን በስሜት ተከታትላዋለች አርዕስቱ ደስ ብሏታል። ሆኖም በሴቶች ላይ የሚፈፀመው በደል እንደሚያይል ልትነግረው ፈልጋለች።

«አንድ ምሳሌ ብቻ ልስጥህ.....» አለችው።

«እሺ ቀጥይ....»

«ሰማይነህ እድሜው ትልቅ ነው። ይህን ያህል እድሜ ሲኖር እኔን ከማግባቱ በፊት ሌላ ሴት ጋ ሳይሄድ ወይንም ሳይወሽም አልኖረም። ነገር ግን የራሱን ወደ ኋላ ዞር ብሎ አልተመለከተም፤ የኔን ድንግልና ባለማግኘቱ ብቻ እብድ ሆነ፤ በፊት የማታውቃቸውን ወንዶች ጠመዳቸው.....ይህንን አንድ በልልኝ.....»

«እሺ.....»

«ሁለተኛ ደግሞ ይህን ያህል እድሜ ሲኖር ሰማይነህ ያለመውለዱ ችግር እንዳለበት የሚያመለክት ሲሆን፣ እኔን ገና በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ባለማርገዜ ሁሉም ጣታቸውን ቀሰሩብኝ። ችግሩ ያለው ሰማይነህ ላይ መሆኑን ማንም ሊጠይቅም ሆነ ሊያምን አይፈልግም። እኔ ከሁለት አመት በፊት ተሳስቼ ሳላስበው ከሄኖክ አርግዤ ነበር። ያልተፈለገ እርግዝና ስለ ነበር አስወርጄ ነው። ቢያንስ ማርገዝ እንደምችል አረጋግጫለሁ። ለሰማይነህ ይህንን ብነግረው እብድ ሆኖ ስለሚያንቀኝ ደብቄዋለሁ። የመሀንነት ነገር ሲነገር ሲነሳ ሴቷ ላይ ብቻ ጣት የሚቀስረው እስከመቼ እንደሆነ አይገባኝም»

«ይህ የአስተሳሰብ ችግር በአንዳችን ቤት አሁንም ያለ ቢሆንም የዚያን ያህል በብዙ ቤተሰብ በኩል ግንዛቤ እያገኘ መጥቷል። በሰለጠነው ትውልድ መሀንነትን ለመመርመር ሁለቱም ወደ ሀኪም መሄዳቸው እየተለመደ መጥቷል።.....»

በዚህ ዓይነት ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ሲወያዩና ሲጫወቱ ብዙ ቆዩ። ህይወትም ከመደምደሚያ ጋራ የምታደርገው ውይይት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያበሰላትና ስሜቷን እያሰከነው ነበር። ትምህርታዊ ውይይታቸውን ሲጨርሱ ተመልሳ እዚያው ሀሳቧን ጭንቀቷን ውስጥ ገባች።

«ሆዴን ፍርሃት ፍርሃት ይለዋል» አለችው።

«ስለ ተደበቅሽ ይሆናል!»

«አይመስለኝም፤ ብቻ እኔ እንጃ.....»

«አሁን ምሳ ስንበላ ይተውሻል።»

«ምሳ መብላት አላማረኝም። ይልቅ እንደ ገና ሄኖክ ጋ ስልክ እንሞክር። ሄኖክን ካላገኘሁ ልቤ እረፍት አያገኝም።»

እንደገና ተያይዘው ወደ እንግዳ መቀበያው ወረዱ።

# ክፍል አስራ ሰባት

ሰማይነህ ህመሙ ተሽሎት አንገቱን ቀና ከማድረጉ ልብሱን እንደ ነገሩ ለባብሶ ፀጉሩን እንኳን ሳያበጥር ከቤቱ ለመውጣት ተነሳ። የጠጣው አልኮል እንዳይጎዳው በወቅቱ ፈጣን ህክምና ስለተደረገለት፣ ህመሙ ከሁለት ቀን በላይ አላስተኛወም። ይሁን እንጂ የውስጥ ህመሙና ድካሙ ለቅቆት ቢነሳም አእምሮው ጤነኛ አልነበረም። ህይወትን ከአጠገቡ በማጣቱ ሁሉም ነገር ተመሰቃቅሎበታል።

«እንሂድ እንጂ!....» አለው ጎርፉ ላይ አፍጥጦበት።

«ወዴት?.....» አለ ጎርፉ መኪናውን እያሞቀና የሰማይነህን ትዕዛዝ በተጠንቀቅ እየጠበቀ።

«ህይወትን ፍለጋ ነዋ!....»

«እሺ። ከየት አቅጣቻ ልንዳ?»

«ወደ መርካቶ ሂድ፤ ወደ ወርቅ ቤት።»

ዘበኛው በሩን ከፍቶላቸው መኪናው ከግቢያቸው ሲወጣ፣ እናትየው በረንዳ ላይ እንደ ቆሙ እጃቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው «ፈጣሪ አምላኬ ሆይ፤ አደራህን ከክፉ ነገር ጠብቅልኝ፤ ልጁ እንደሆን ራሱን ስቷል፤ የሚሰራውን አያውቀውም» በማለት የሐዘን ድምፃቸውን አሰሙ።

«ዝም ብለህ አትሩጥ! ግራ ቀኝህን እያየህ ንዳ። ህይወትን በዓይንህ ፈልጋት!» በማለት ሰማይነህ ሲቆጣው፣ ጎርፉ በድንጋጤ መኪናውን አቀዝቅዞ መንገደኛው ላይ ሁሉ ማፍጠጥ ጀመረ።

«....የነገርኩህን ደግሞ እንዳትረሳ!»

«እ - እ የትኛውን የነገርከኝን?»

«ህይወትን ስናገኛት ለማምለጥ ከሞከረች ገጭተህ እንድትገድላት ነግሬህ አልነበር?!»

«አዎ፤ አስታወስኩ።»

«እሷ ከሞተች ደግሞ እኔን ገድለህ አንድ ጉድጓድ ጎን ለጎን መቅበር እንዳለብህ እንዳትዘነጋ።» እዚህ ላይ ጎርፉ ደንግጦ ዝም አለ።

«እስቲ ወደኔ ተመልከት!» በማለት ሰማይነህ ጮኸበት፤ በታዘዘው መሠረት ላንድ አፍታ ዞር ብሎ ተመለከተ።

«ፈሪ ነህ። ድፍረት ይጎድልሀል። ዓይንህ ራሱ መቅዘን ጀምሯል» አለው። ጎርፉ ዘለፋውን ጠጥቶ እየተልጎመጎመ «.....ራሷ ትሙት፤ እሺ።.....አንተ ግን ለምን ትሞታለህ? እኔ እኮ የምወድህ፣ መመኪያ ወንድሜ ነህ» በማለት ድምፁን አሰማ።

«አታልቅስብኝ!....የታዘዝከውን ብቻ ፈፅም!» አለ ሰማይነህ። ወርቅ ቤቱ በር ላይ መኪናቸውን አቁመው ወደ ውስጥ ሲገቡ የሰማይነህ ሰራተኞች በጉጉትና በልዩ ስሜት ተቀበሏቸው። የሰማይነህን መታመምና የሚስቱን መጥፋት ሰምተው ተደናግጠው ስለ ነበር አሁን ድኖ የመጣ መስሎአቸው ተደሰቱ። በተለይ ሁለቱ ሰራተኞቹ ከሰማይነህ ጋር እዛችው ወርቅ ቤት ለብዙ አመታት አብረው ሰራተኞቹ ከሰማይነህ ጋር እዛችው ወርቅ ቤት ለብዙ ዓመታት አብረው የሰሩ በመሆናቸው እንደ ቤተሰብ መተያየት ጀምረዋል።

«ህይወት አልመጣችም እንዴ?» አላቸው ሰማይነህ ገና ከመግባቱ ለአንዳቸውም ሰላምታ ሳይሰጥ። የወርቅ ቤቱ ሰራተኞች ተደናግጠው ዝም አሉ።

«አትናገሩም እንዴ?» ብሎ እንደ ገና ጮኸባቸው።

«መልስ ስጡት እንጂ!» አለ ጎርፉም ተደርቦ።

«ኧረ አልመጣችም።» ከሰራተኞቹ ውስጥ አንደኛው እየተቅለሰለሰ መለሰ።

«ሶስት ቀን'ኮ ሆናት ከጠፋች» አለ ሰማይነህ ለራሱ እንደሚናገር አይነት ድምፁን አሳንሶ። ይህን ሲናገር ቅናቱ ከውስጥ ብቅ ብሎ ይቆረጥመው ጀመር። ሶስት ቀናት ሙሉ ከሱ የተለየውን የህይወትን ገላ ሌላ ወንድ አቅፎ ሲደባብሳት በሃሳቡ እየታየው ጥርሱን አንቀጫቀጨ። ዙሪያውን ከበው በሃዘን ከንፈራቸውን እየመጠጡ የቆሙት የወርቅ ቤት ሰራተኞቹ አስጠሉት።»

«እናንተ እዚህ ምን ታደርጋላችሁ?!....ወጥታችሁ ህይወትን አትፈልጓትም?!......ህይወት ከሌለች ሀብት የለም፤ በከንቱ እዚህ አትድከሙ» አላቸው ሰራተኞቹም በልባቸው ‹ሰውዬው ማበዱ ነው እንዴ?› እያሉ አንገታቸውን አቀርቅረው ዝም!

«ወርቆቿን በሙሉ ይዛ ነው የሄደችው። ወርቅ ቤት ከፍታ አደገኛ ተፎካካሪያችን ልትሆን ነው» የፌዝ አይነት ሳቅ በረዥሙ ሳቀ። ወዲያው ደግሞ ልውጥውጥ ብሎ ኩስትርትር አለና የወርቅ ሚዛኑን አንስቶ መሬት ላይ ከሰከሰው።

«ምን ዋጋ አለው!.....ይሄ ሁሉ ወርቅ ህይወትን አስሮ ማኖር ካልቻለ ምን ዋጋ አለው?!» እያለ መደርደርያውን ከፍቶ ወርቆቹን እያወጣ መሬት ላይ ዘረገፋቸው። በእጁ ዘግኖ እንደ ህፃን ልጅ ሽቅብ እየበተነ ተጫወተባቸው። በእጁም፣ በእግሩም እየተወራጨ የወርቅ ጌጣጌጦቹን ምስቅልቅላቸውን ካወጣና ከበታተናቸው በኋላ በመጨረሻ አንዱን መደርደሪያ ተደግፎ፣ አንገቱን ደፍቶ፣ ለጥቂት ደቂቃ በትካዜ ቆየ።

«የተበተነውን ወርቅ ሰብስቡ እንጂ! ምን ቆማችሁ ታያላችሁ?» በማለት ጎርፉ በተራው ሰራተኞቹ ላይ ጮኸባቸው።

ይህን ሁለት ቀን በሰማይነህ መታመም ምክንያት ጎርፉ የወርቅ ቤቱም የመኖሪያ ቤቷ አዛዥና ተቆጣጣሪ ሆኖ መታየት ጀምሯል። የሚንቁትና የሚያሸሟጥጡትን ሰራተኞች ገና ከወዲሁ ጥርሱን ነክሶባቸዋል። ሰማይነህ ሙሉ በሙሉ አብዶለት ድርጅቱም ሆነ ሀብቱ በሱ ቁጥጥርና ትዕዛዝ ስር የሚውልበትን ግዜ በናፍቆት የሚጠብቅ ይመስላል። በርግጥ የሰማይነህን እብደት ማስታመምና መንከባከብ ከታክሲ ስራው የበለጠ አድካሚና አሰልቺ ሊሆንበት እንደሚችል በዚሁ ሶስት ቀናት ውስጥ ገምቷል። ይህንን ሲያስብ ደግሞ ሰማይነህ አንደኛውን ሞቶለት ቢገላገልና ሀብቱን ቢወርስ ሳይመኝ አልቀረም። ሰማይነህ ቢያብድለት ወይንም ቢሞትለት፣ ጎርፉ ስራ ሳይሰራ ቁጭ ብሎ የሚበላውን የተትረፈረፈ ሀብት ሲያስብ አዕምሮው ከወዲሁ በጉጉት መስከር ጀምሯል። ‹እኔንም ገድለህ ከህይወት ጋር ቅበረኝ› ያለውን ሲአይስታውስ ያልደከመበትን ሀብት ማግኘቱ ነገር ወለል ብሎ ይታየዋል። ለታላቅ ወንድሙ ሳያዝን ቀርቶ ሳይሆን በጥቅም የሚደለለውና የሚሸነገለው ትንሹ ጭንቅላቱና ሆዱ ከዚህ ውጭ ማሰብ ባለመቻሉ ነው።.....

ሰማይነህ ካቀረቀረበት ቀና ብሎ ድንገት ዘልሎ ሲወጣ፣ የወርቅ ቤት ሰራተኞቹ በሐዘን ከንፈራቸውን እየመጠጡ ተከተሉት። ሆኖም ርቆ አልሄደም። ወደ ኋላው ዘወር ብሎ «ለምን ትከተሉኛላችሁ!.....ግቡ ወደ ውስጥ» በማለት ሠራተኞቹ ላይ እንደ ህፃን ጮኸባቸው። እነሱ ወደ ውስጥ ከገቡለት በኋላ ደግሞ ‹ጎርፉ ላይ አፍጥጦበት «እንድሂድ እንጂ! ምን ቆመህ ታየኛለህ?!» አለው።

«ወዴት?.....» አለ ጎርፉ እንደ ልማዱ።

«ህይወትን ፍለጋ ነዋ!.....»

ጎርፉ መኪናውን ሊያስነሳ ሲገባ ሰማይነህ እንደ ገና ተቆጥቶ «መኪናውን ተወው!.....በእግራችን ነው የምሄደው። ህይወት መኪናዬን ስለምታውቅ ስታየኝ ከሩቅ ልትሸሽ ትችላለች። እስካሁንም በመኪናው መንፈለጋችን ትክክል አልነበረም» አለው።

«እሺ» ብሎ ተከተለው ጎርፉ።

«እዚህ መርካቶ ውስጥ እናገኛታለን። በትርምሱ መሀል እንዳታመጠን ተጠንቀቅ።»

«እሺ»

«.....ያንን ጎረምሳ ታየዋለህ?» አለው ጥቂት እንደሄዱ ወደ አንድ ወጣት በጣቱ እያመለከተ።

«አዎ፤ አየሁት።»

«ሄኖክ ማለት እሱ መሆን አለበት።»

«እንዴት እናውቃለን?»

«አለባበሱን አታየውም እንዴ! ከአሜሪአን ሀገር የመጣ መሆኑ ያስታውቃል። ፀጉር አበጣጠሩንም ተመልከተው፤ እንደ ሴት ተጎንጉኖታል።.....እንዴት ንጥር ንጥር እንደሚል አረማመዱንም ልብ ብለህ እየው፤ ፊልም ላይ የሚታዩትን ፈረሳቸው ያመለጣቸው ቴክሶች አይምስልም?!.......አንዱ ጆሮ ላይ ደግሞ ሎቲ አንጠልጥሏል።.....አትጠራጠር ሄኖክ ራሱ ነው።»

«ልክ ነህ፤ ይሆናል።»

«አጠገቡ ስንደርስ እንዳያመልጠን ከዚሁ ተኩሰን መጣል አለብን.....»

«በምናችን?......»

«ሂድና ሮጠህ ሽጉጡን ወይንም ክላሹን መኪናው ውስጥ አምጣ።»

«መኪናው ውስጥ የለም እኮ»

«እንዴት?.....መሣሪያው ከመኪናችን ውስጥ እንዳይለይ ባለፈው ጊዜ ነግሬህ አልነበረም እንዴ?» ብሎ ሰማይነህ ሲያፈጥበት ጎርፉ ደንግጦ ከእናቱ ጋር የፈፀሙትን ምስጢር ነገረው።

«እማማ ቁልፉን ተቀበለኝ መሣሪያዎቹን ከአንተ ሳጥን አውጥታ ደብቃቸዋለች። ......እንዲያውም ለአንተ እንዳልነግርህ አስምላኝ ነበር» አለው።

«ቆይ ግዴለም!» እያለ ሰማይነህ እናቱን ረገመ። ሆኖም አሁን በዚህ ንዴትና ጭቅጭቅ ጊዜ ማቃጠል አልፈለገም። ወጣቱ እንዳያመልጠው፣ በዓይኑ እየተከተለው፣ ከእርምጃው ፈጠን - ፈጠን ብለው ደረሱበት።

«......ጋማው ላይ እነቀው!» አለ ሰማይነህ ወጣቱ ላይ ጀርባው አፍጥጦ ጥርሶቹን እያንቀጫቀጨ።

«መጀመሪያ በስሙ እንጥራው።......የምንፈልገው ሰው መሆኑን ብናረጋግጥ አይሻልም?»

«ሽንታም!.....እንግዲህ መፍራት ጀመርክ፤ ይህን የሚያክል ሰውነት ይዘህ አንድ ወጠጤ ጎረምሳ መዘረር ያቅትሀል?!»

«እሱማ አያቅተኝም.....» አለ ጎርፉ ልቡ እየፈራ።

‹ሰማይነህ ወጣቱ ላይ ደርሶ ከኋላው የጃኬቱን ኮሌታ ሲጨመድደው፣ ወጣቱ በንቃት ዘልሎ መነጨቀውና ራቅ ብሎ ቆመ። የጎርፉን ደንዳና ሰውነት ፈርቶ ነው እንጂ ሰማይነህ ላይ ዘልሎ የጫማ ጥፊ ሊያሳርፍበት ከጅሎ ነበር።

«ሄኖክ ነህ ወይንስ አይደለህም?» አለው ሰማይነህ ስሮቹ እየተግተረተሩ።

«የማነው ሄኖክ?!.....» አለ ወጣቱ ራሱን ለመከላከል እየተንቀጠቀጠ።

«ከአሜሪካን ሀገር አይደለም የመጣኸው?.....»

«አረባክህ ሰውዬ!.....እኔ አሜሪካንን የማውቃት በፊልም ነው።»

«አትዋሽ፤ አንተ ሌባ!» አለው ጎርፉ የሞት ሞቱን ልብ ገዝቶ።

ወጣቱ አዝማሚያቸው አላማረውም። በተለይ ጎርፉን መጋተር የሚችል መስሎ ስላልታየው አዘናግቶአቸው ፈትለክ ብሎ በትርምሱ መሀል እየተሽለኮለከ ሮጠ።

«አመለጠ ማለት ነው?» አለ ሰማይነህ።

«ደንግጦ ነው እንጂ የሸሸው ሄኖክ አይመስለኝም። አኳኋኑ ያስታውቃል» አለ ጎርፉ።

«አሜሪካን ሀገር አሁን በአስቸኳይ መሄድ አለብኝ፤ ህይወት በምንም መንገድ አታመልጠኝም.....አንተም አብረኸኝ ትሄዳለህ» አለው ወንድሙን።

«እሺ፤ አብረን እንሄዳለን»

ሰማይነህ ወዲያው ዘወር ብሎ አንድ የሚያውቀው የጫማ ሱቅ ውስጥ ገባና «ሰሞኑን ከአሜሪካን ሀገር የመጣ ሰው ታውቃላችሁ?» አላቸው።

«ማን የሚባል?» አለ፣ የጫማው ሱቅ ባለቤት በሰማይነህ አጠያየቅ ተደናግጦ።

«ሄኖክ የሚባል ጎረምሳ!»

«የለ።.....እኔ አልሰማሁም።»

«አጠያይቃችሁ ስትሰሙ እንድትነግሩኝ!» ብሎ እጆቹን እያወናጨፈ ሲወጣ የጫማው ሱቅ ባለቤት ግራ ተጋብቶ ‹ምን ነካው?› እንደ ማለት ያህል ጎርፉን በምልክት ጠየቀው። የቅርብ ወዳጆችም ባይሆኑ በርቀት ይተዋወቃሉ።

ጎርፉ በታቱ ወደ ራሱ ጭንቅላት እያሳየ ‹ነካ አድርጎታል› እንደ ማለት በጥቅሻ ጭምር አስረዳው።

ሰውየው ሰማይነህን በሀብታም ነጋዴነት ስለሚያውቀው በንግዱ ኪሳራ ደርሶበት የቀወሰ መስሎት በሀዘኔታ ራሱን ነቅንቆ ሸኘው።

«ህይወት የተደበቀችበትን ቦታ አሁን ደረስኩበት!› አለ ሰማይነህ፣ ከጫማው ቤት ከወጡ በኋላ ድንገት ብልጭ ብሎበት።

«የት ነው?» አለ ጎርፉ።

«ና ተከተለኝ፤ አሳይሀለሁ።»

አንድ ቀን ከህይወት ጋር ሄደው የተጣላውን ልብስ ሰፊ አስታውሶ በቀጥታ ወደ ሱቁ አመራ። የህይወት ደንበኛ የነበረውን ልብስ ሰፊ እዚያው ቦታ ሲያገኘው ያለ ምንም ሰላምታ ዘው ብሎ ገብቶ በጠላትነት ስሜት ዓይኖቹን አጉረጠረጠበት።

«.....የት ነው ያለችው?! የተደበቸበትን ቦታ በአስቸኳይ እንድታሳየኝ እፈልጋለሁ» ብሎ ጮኸበት።

«ማን ናት እሷ?!.....» አለው ልብስ ሰፊው በንቀትና ጥላቻውን በሚገልፅ አስተያየት።

«ህይወትን ቁጭ አድርጋት ነው የምልህ!»

«ሰውየው ጤና የለህም እንዴ?!..... ባላፈው ጊዜ እንዲሁ ከመሬት ተነስተህ ተሳድበህ ሄድክ። አሁን ደግሞ ምን እንደምትፈልግ አይገባኝም።.....ክብርህን ብትጠብቅ ይሻልሀል።»

«ህይወት ያለችበትን የምታውቅ ከሆነ ንገረው እባክህ። ሌላ ወሬ አታብዛ» አለ ጎርፉ በማስፈራራት አይነት።

«እኔ ህይወትን ጠባቂ አይደለሁም» ብሎ ልብስ ሰፊው ለፀብ እንደሚዘጋጅ አይነት የሸሚዙን ክንድ ጠቀለለ። ሌሎቹም ልብስ ሰፊዎች ነገሩ ገብቷቸውና ሰማይነህን አስታውሰው «ያቺ ቆንጆ ልጅ ፈነገለችው ማለት ነው?!» እያሉ ተንሾካሾኩ።

«አንዳንተ አይነት ቡትቶ ሰፊ የኔን ሚስት ቀምቶ አይደብቃትም።፡.....ደሞም የምታዋጣህ እንዳይመስልህ። ለጊዜው መደበቂያ አድርጋህ ይሆናል እንጂ ነገ ጠዋት ጥላህ ወደ አሜሪካን ሀገር ትሄዳለች» ብሎ ሰማይነህ ልብስ ሰፊው ፊት ላይ በጠላትነት ስሜት ተፋበት።

ልብስ ሰፊው ትዕግሥቱን ጨርሶ ድንገት በመነሳት ቡጢ ሲሰነዝር የሰማይነህ አገጭ በከፊል አገኘው። ጎርፉ ለወንድሙ ለማገዝ ሲንደረደር ሌሎቹ ልብስ ሰፊዎች ደግሞ ለጓደኛቸው ተደርበው ስለ ቆሙ ተፋጠጡ። ያም ሆኖ በሰማይነህ እምቢ ባይነትና መወራጨት ምክንያት ፀቡ ከርሮ ትንሽ ቡጢ እንደተቀማመሱ የአካባቢው ሰው ተረባርቦ መሐላቸው ገብቶ ገላገላቸው።

ሰማይነህ ከተገላገለም በኋላ አሻፈረኝ ብሎ አስቸገረ። ልብስ ሰፊውን ብቻም ሳይሆን የገላገሉትም ሁሉ እየተሳደበና ሁሉም ህይወትን የቀሙበት ጠላቶቹ አድርጎ እየጮኸ ልብሱን ከላዩ ላይ ለማውለቅ ሲታገል ሸሚዙን ቀዳደደው። እብደቱ እየጨመረ ሄዶ ላገላጋዮች ሁሉ አስቸጋሪ ሆነ። የገዛ ወንድሙ ሳይቀር አባብሎ ሊይዘው ቢሞክርም አልቻለም። በአካቢው ግርግር በዝቶ ሰው ሁሉ ጉድ እስኪል ድረስ መላቅጡን አጥቶ የአዕምሮውን መዛባት አስመሰከረ። ብዙዎቹ በዝና የሚያውቁት ነጋዴ ሆኖ በመገኘታቸው አዘኑለት። በመጨረሻም ተላላፊ የፀጥታ አስከባሪዎች መኪና ደርሶ፣ የሰማይነህ እጆችና እግሮች እንዳይወራጩ በእግር ብረት ታስሮ፣ ወደ አዕምሮ ህመምተኞች ሆስፒታል ተወሰደ።

«የት ነው የምትወስዱኝ?!.....ወደ አሜሪካን ሀገር ነው?» አለ የታሰረበት ቦታ ሆኖ አረፋ እየደፈቀ።

«አዎ፤ ወደ አሜሪካን ነው።»

«ይህወትን እዚያ አገኛታለሁ።.....ያንን ወጠጤ ደግሞ ሄኖክን ሳገኘው ምን እንደማደርገው አሳያችኋለሁ።»

«አሁን አሜሪካን ሀገር ለመድረስ ብዙ ሰዓታት ይፈጅብናል እንዴ?.....እኔ በጣም ቸኩያለሁ። »

«አይዞህ ቶሎ እንደርሳለን» በማለት ፖሊሶቹ እየሸነገሉት፣ እሱ እየቀባዠረ ሄዱ።....

የመርካቶ ልጆችም ወዲያውኑ ቀልዳቸውን በሰማይነህ ላይ ተመርኩዘው ጀመሩ። ወሬው በአንዳፍታ በአካባቢው ተሰራጨ።

«ቅናት እንዴት ያደርጋል?» ይለዋል አንዱ የመርካቶ ቀልደኛ ሌላውን ጓደኛውን።

«እንደ ሰማይነህ ያወራጫል.....በእምብርክክ ያስኬዳል።......ልብስ አስወልቆ ያሳብዳል» ይለዋል ሌላው።

«የቅናት መንስኤው ምንድነው?»

«እንደ ሰማይነህ በቆንጆ ሴት መለከፍ!»

«መፍትሄውስ ምንድነው?»

«እንደ ሰማይነህ አብዶ መገላገል።»

ሌላው ቀልደኛ ደግሞ ከመሬት ተነስቶ....» መቅናት አማረኝ» ይላል።

«ሂድና ሰማይነህ ጋ የቅናት ኮርስ ውሰዳ!» ይለዋል ጓደኛው።

«ሰማይነህ የቅናት መምህር ያደረገው ማነው?»

«ተግባሩ ነዋ። የቅናት አይነቶችን በተግባር አሳይቶ በከፍተኛ ማዕረግ ተመርቋል።»

«ስንት አይነት ቅናቶች አሉ?»

«እስካሁን የታወቁት ‹ለዘብተኛ ቅናትና አክራሪ ቅናት› የተባሉት ናቸው። የአክራሪ ቅናት አራማጅ ሰማይነህ መሆኑ ተደርሶታል።»

ነጋዴው እየሸቀለ፣ ቦዘኔውም ራሱን እያከከ፣ በቀልዶቹ ይዝናኑባቸዋል።……

# ክፍል አስራ ስምንት

ሰማይነህ በአዕምሮ ክህምና ሆስፒታል ውስጥ ራሱን ስቶ ተኝቷል። በሐኪሞቹ የተሰጠው የማድከሚያና የማስተኛ መድሐኒት ለረዥም ሰዓታት በእንቅልፍ ዓለም ውስጥ አቆይቶታል። እናቱና መደምደሚያ የሆስፒታሉ የውጭ በር ላይ ቆመው ሰማይነህን ለመጠየቅ የሚመጡትን እንግዶች እየተቀበሉ በመሸኘት ላይ ነበር። ጎርፉ በሀኪም የታዘዘ መድሐኒት እንዲፈልግ ተልኮ ሄዷል። ወሬው በአጭር ጊዜ ውስጥ ስለ ተዛመተ ብዙ ሰዎች የሰማይነህን ሁኔታ ለማወቅ እየመጡ ተመልሰዋል።

ከቀትር በኋላ አንድ ለየት ያለ ጠያቂ ከውጭ መጥቶ ሳይሆን፣ ከሆስፒታል ውስጥ ወጥቶ ድንገት የሰማይነህ እናት አጠገብ ቆመ። መደምደሚያም ሆነ እናቱ የዚህን ሰውዬ ፊት ያውቁበታል። የሚያውቁበት ቦታና ሁኔታ ግን ግር ብሏቸው በጥያቄ አስተያየት ተመለከቱ።

ሰውዬው ቀጭን፣ ረዥም ሆኖ ሰውነቱ የተጎሳቆለ አይነት ነው። ሽበት የወረረው አጭር ፀጉር በቅጡ አልተበጠረም። አለባበሱም እንደ ነገሩ ነው። ግንባሩን አኮማትሮና ፊቱን አጨማዶ ሲመለከቱት ነገር የሸተተው ይመስላል።

«.....የምታስታውሱኝ አይመስለኝም» አላቸው ግንባሩን እንዳኮሳተረ።

«አዎ፤ ትንሽ ግር ብሎኛል» አሉት የሰማይነህ እናት አኳኋኑ አስፈርቷቸው ትከሻቸውን እየከበዳቸው።

«የዛሬን አያድርገውና ድሮ የሰማይነህ ጓደኛ ነበርኩ። አንድ ሁለት ጊዜም ቤታችሁ መጥቼ ተስተናግጂያለሁ» ካላቸው በኋላ አፉን ጠረግ - ጠረግ አድርጎ ወንዴ ወደ መደምደሚያ፣ አንዴ ወደ አሮጊቷ እየተመለከተ ንግግሩን ቀጠለ።….» ዛሬ ሰማይነህ አብዶ ወደ ሐኪም ቤት ሲገባ እኔ ደግሞ እብደቴን ጨርሼ ከሀኪም ቤት ወጣሁ። የተራ ጉዳይ ነው። ሁሉም በየተራው ያብዳል። ሰማይነህን ለዚህ ላበቃው አምላክ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። አሁንም ክብር ምስጋና ይግባው። የሰው ደም! የሰው ላብ!.....የሰው እንባ እንዲሁ ፈስሶ አይቀርም። ይዋል ይደር እንጂ ሁሉም የእጁን ያገኛታል። ሰማይነህ በሀብት የደለበው የእኛን የእኛን ላብ ተቀብቶ የእኛን ደም ጠጥቶ፣ በእኛ እንባ ታጥቦ መሆኑን ልገልፅላቸው እወዳለሁ….»

«ምንድነው የሚያወራው?!….የማነው ይሄ እባካችሁ!» በማለት የሰማይነህ እናት በቁጣ አቋረጡት።

«የልጅዎን ወንጀል ያዳምጡ እንጂ!…..ለምን ይቆጣሉ!» አላቸው ሰውየው በፌዝ ቅላፄ።

«እስቲ ቆይ የሚባለውን እንስማ። ግዴለሽም እማማ» አላቸው መደምደሚያ በጉጉት።

«ሰማይነህ የማውቀው እንዳሁኑ ሳይሰፋ ሳይደረጅ ገና ተራ ወርቅ ሰሪ እያለ ነበር» በማለት ቀጠለ ሰውዬው «የወርቅ ስራው አባቱ ከነክርክራቸው የሞቱበት ክቡር ሙያ ነበር። እሱም እንዳባቱ ጎበዝ አንጥረኛ ወጥቶት ነበር። ሆኖም ግን ይኸው ሙያው ለሀብቱም ሆነ ለስሙ ሳያንሰው፣ በወንጀል ወደሚገኘው ሀብት ተሸጋገረ። ያልደከመበትን ሀብት ለማግኘት ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት ጀመረ። ለቤተክርስቲያን ማሰሪያ ገንዘብ መስጠትም ሆነ ለየታቦቶቹ ደግሶ ማብላት

ሐጢያቱን አያጥብለትም። መጀመሪያ የልብ ንፅህና ይበልጣል። እግዚአብሔርም የሚመለከተው እጅን ሳይሆን ልብን ነው። ሰማይነህ ሀብታም ለመባል እኔንና ሌሎች ጓደኖቹን መስዋዕት አድርጎ ጥሎናል። የመጀመሪያ መነሻው ምን እንደሆነ ልንገራችሁ.....የዛሬ አስር አመት ገደማ ነበር። እኔና አንድ ሌላ ሰው ሆነን ከሰማይነህ ጋር እያንዳንዳችን አምስት መቶ ሺህ ብር በማዋጣት ቡና ገዝተን ወደ ውጭ ለመላክ ተስማምተን ህላፊነቱንና ገንዘቡን በዕምነት ለሰማይነህ ሰጠነው። በግዜው ሁላችንም እንደየአቅማችን ነጋዴዎች ነበርን። ገንዘቡንም ያሰባሰብነው ተበድረን ነበር። ሰማይነህ ከአንድ ባለሥልጣን ጋር ተስማምቶ ቡናውን ሸጦ ገንዘቡን ከበላ በኋላ እኛን ካደን። ትርፉ ቀርቶብን ዋናው ገንዘባችንን እንዲመልሱልን አማላጅ ብልከም አልሆነም። ባለሥልጣኑ ይባስ ብሎ ሽጉጥ አውጥቶ ዛተብን። ጉዳዩን ሌላ የፖለቲካ ሽፋን ሰጥቶት ወህኒ ቤት ሊያወርደን እንደሚችልም በተዘዋዋሪ ነገረን። በጓደኛችን በሰማይነህ ክህደት ገንዘባችን የውሀ ሽታ ሆኖ ቀረ። ቤታችንና ንብረታችን ተሸጠ። ዕዳችንን ከከፈልን በኋላ እኛ ከነቤተሰቦቻችን ሜዳ ላይ ተበተንን። ሰማይነህም በእኛ ውድቀት ላይ ቆሞ የሚሊየርነቱን መንገድ ተያያዘው። ሦስተኛው ሸርካችን በብስጭት የደም ብዛት ህመምተኛ ሆኖ ብዙም ሳይቆይ ሞተ። ተገላገለ። እኔም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የአዕምሮ ህመምተኛ ተብዬ በየሆስፒታሉ ስመላለስ ይኸው አስር አመቴ!.....»

‹አስር አመት ሙሉ በዕደት ኀዳና!.....ይሄስ የጉድ ነው› አለ መደምደሚያ በልቡ።

«ሰማይነህ ክህደትን በኛ ላይ ተለማመደ። የገንዘብ ሱስ አሰከረው፤ ሳይደክሙ ሀብት ማጋበስ አንቀዠቀዠው። በለመደ እጁ ብዙ የንግድ ጓደኖቹን እያረደ ጣላቸው። የእሱ ስም ብቻ ገነነ። ባለሥልጣኖችም ሁሉ ጓደኞችም ሁሉ ጓደኖቹ ሆኑ። አብረው ይበላሉ፤ አብረው ይጠጣሉ፤ አብረው ጮማ ይቆርጣሉ፤ የሰማይነህ ተቀናቃኝና ጠላት የመሰላቸውን አብረው ያጠፋሉ.....በዚህ አይነት የሰማይነህ ጥቆማ ሰለባ የሆኑት ንፁሀን ነጋዴዎች ቤታቸው ይቁጠራቸው።.....»

«ኧረ በህግ አምላክ አንተ ሰውዬ!.....ወጊድልኝ ከአጠገቤ!» አሉት አሮጊቷ እንደ ገና።

«ምን ህግ አለ ብለው ነው?! ህግ የለም እንጂ ህግማ ቢኖር የእኛ ጩኸትና እንባ ሰማይነህ አፈር ድሜ ባስጋጠው ነበር!.....ሰማይነህ ያሳበደው እኔን ብቻ እንዳይመስላችሁ። እዚህ በር ላይ ከቆዩ ሰማይነህ ያሳበዳቸውና ሰማይነህን እየረገሙ የሚጮሁ ብዙ ምስኪኖች ያጋጥሞዎታል። መርካቶ መሀል ያንን የተንጣለለ መጋዘን ያሰራው የሰባት ምስኪን ሰዎች መኖሪያ ቤት አስፈርሶ እነሱን ሜዳ ላይ በትኖ መሆኑን እርስዎም ያውቁታል። ከሱቅ በደረቴ ጀርሞ እስከ ጅምላ ነጋዴዎችና ትላልቅ ጨረታ ተወዳዳሪዎች በሰማይነህ ያልተመረረ የለም። በገንዘቡ ባለሥልጣኖችን እየገዛና በወንጀል እየተመሳጠረ ያልደከመበትን ሀብት በልቶ ሳይጨርስ አሳበደው። በዚህ ሰዓት የእሱን ጅራፍ በግልፅም ሆነ በተዘዋዋሪ የቀመሱ ሁሉ በያሉበት ሆነው ‹እሰይ!› ይላሉ። እኔም እነሆ ‹እሰይ!› ብዬ ይህንን ሆስፒታል ተገላግያለሁ። በቃኝ! ለተረኛው ደግሞ ለቅቄለት ወጥቻለሁ። እግዚአብሔር በህይወት እያለሁ ፍርዱን ስላሳየኝ ተመስገን ብያለሁ። እንግዲህ የሰው ልጆችን ልብ የሚመለከት፣ ከገንዘብና ከስልጣን በላይ የሆነ አንድ እግዚአብሔር መኖሩን አውቆ ራሱን እንዲመረምር ለሰማይነህ ንገሩት!» ብሏቸው እጆቹን እያወናጨፈ፣ በመተንፈሱ እፎይታ አግኝቶ እየተዝናና ሄደ።

የሰማይነህ እናት ሰውዬው ከዓይናቸው እስኪርቅ ድረስ አላመኑትም። ድንገት ወደ ኋላው መለስ ብሎ መጥቶ የሚጨምረው ነገር እንዳይኖር እየፈሩ፣ በልባቸው እየተራገሙ ሸኙት።

«የማነው ወፈፌ እባካችሁ!......እንዲህ ከመሬት ተነስቶ የልጄን ሀጢያት የሚያበዛው ምን አደረገው?!.....ዝም ብሎ እኮ የቆጥ - የባጡን ነው የሚቀባጥረው» አሉ፣ ሰውዬው የተናገረውን የሰማ ሰው በአካባቢያቸው ካለ ለማስተባበል በሚሞክር አይነት ድምፅ።

ለአፋቸው ያህል ይህን ይበሉ እንጂ ሰውዬው የተናገረው ነገር እስከ ውስጥ እግራቸው ዘልቆ እያቃጠላቸው ነበር። የሰማይነህን ጠላቶች ተሰብስበው «እልል!» ሲሉ በህሳባቸው እየታያቸው ልባቸው በንዴት ተኮማትሯል።

መደምደሚያ በበኩሉ በሰውዬው ንግግር ተገርሞ እንደፈዘዘ ቀርቷል። በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ አልፎ አልፎ መጠላለፍ መኖሩን ቢያቅም፣ ሰማይነህ ይህንን ያህል ደም የተቃባና ወንጀል ውስጥ የገባ መሆኑን ሲሰማ የመጀመሪያ ጊዜው ነው። አጠገቡ የነበረው ወንድሙ ሳይሆን፣ ጭራሹን የማያውቀው ሌላ ሰማይነህ ስዕል ነው ፊቱ ላይ የመጣበት። «God Father!» በሚለው የማሪዮ ፑዞ መፅሐፍ መግቢያ ላይ ያነበበው ጥቅስ ድንገት ታወሰው።

«Behind every great fortune, there is crime»

እና እንደ ገና በመገረም ጭንቅላቱን ነቀነቀ።

እዚያው እንደ ቆሙ፣ ብዙም ሳይቆይ ወይዘሮ ስራሽ በዘበኛዋ ተደግፋ መጣች። በጥቂት ቀናት ውስጥ ሁለመናዋ ወዳድቋል። ፊቷ ጠቋቁሯል። ረዥም ቀሚስና ወፍራም ሹራብ አድርጋ በላዩ ላይ ነጠላ ደርባለች። እንደዚያ ኩንስንስ ያለች ሴት ወይዘሮ እንደዚህ በአንዴ ወዳድቃ፣ የተደበቀው ዕድሜዋ አግጥጦ ወጥቶ፣ ሞራሏ ተነክቶ ስትታይ ታሳዝናለች።

«ወይ ወንድሜን!.....ለየለትና አበደ?!.....እኔ እኮ ገና አሁን መስማቴ ነው» አለቻቸው ወደ ሰማይነህ እናት ቀርባ።

«የልጅሽ መዘዝ ነው ለዚሁ ሁሉ ያበቃው!.....ልጅሽ ናት ያሳበደችው!» አሉ አሮጊቷም ተማርረው።

«እኔ ነኝ ጥፋተኛዋ፤ በማንም አልፈርድም።.....ለራሴም ለሌላውም ሳልሆን ቀረሁ።....እኔም ታምሜ ነው የሰነበትኩት። አንደኛውን ለይቶልኝ እንደሱ እዚሁ ሐኪም ቤት ብገባ ይሻለኝ ነበር። አዕምሮዬ ፈፅሞ ሰላም አጥቷል። አሁን የሰማይነህን ወሬ ስለ ሰማሁ ብቻ ነው ከአልጋዬ ላይ እንደ ምንም ተነስቼ የመጣሁት። አስጠሩልኝ ወይንም አስገቡኝ እባካችሁ። ለሰማይነህ የምነግረው አንድ ሚስጥር አለኝ» አለች እንባ በዓይኖቿ ሙሉ ግጥም ብሎ።

«እሱን ማግኘት አይችሉም። መድሐኒት ተሰጥቶት ተኝቷል፤ መልዕክቱን ለእኛ ቢነግሩን እናደርስልዎታለን» አለ መደምደሚያ አንዳች ጥርጣሬ ሰውነቱን እየነዘረው።

«እንግዲያውስ ልንገራችሁ። ለእናንተ ለቤተሰቦቹ ከነገርኳችሁ ያው ለሰማይነህ እንደ ነገርኩት ነው። ጠንቋዩ የነገረው ሁሉ ውሸት ነው በሉት። ህይወትን በማጣቱ ሀብቱን አያጣም። ለጠንቋዩ ገንዘብ ከፍዬ በዚህ ዘዴ እንዲያደርስልኝ ያደረግኩት እኔ ነኝ። ሰማይነህ ህይወትን አግብቶኝ፣ በትዳር ተሳስረው ሳይለያዩ እንዲንኖሩ የሞከርኩት ዘዴ ነበር። ከሰማይነህ ጋር ወዳጅነቴን በዝምድናና በጋብቻ ለማጥበቅ የተጠቀምኩበት መንገድ ነበር። ለክፋት አልነበረም። ነገር ግን ዘዴው ለሁላችንም ሳይሆን ቀረ። የሁላችንንም ህይወትና ኑሮ አበላሸ። እኔም ሰማህነህን ጥሩ ወዳጄንና ደከሜ ያሳደኳትን ልጄን አጣሁ። ሰማይነህም እንዲህ ላለው አሳዛኝ ሁኔታ በቃ። ይሄው ነው። አሁኑኑ ይህንን ሚስጥር ንገሩትና ከእብደት አድኑት። አደራችሁን ቶሎ በሉ። ይህንኑ ሚስጥር ልንገረው ብዬ ነው እንዲህ እያመመኝ ከአልጋዬ ላይ ተነስቼ የመጣሁት» ብላ እንባዋን እያዘነበች በፍጥነት ፊቷን አዙራ በዘበኛዋ ተደግፋ ሄደች።

የሰማይነህ እናትና መደምደሚያ ድንጋጤና ደስታ ተደባልቆ የፈጠረባቸው ስሜት ግራ አጋብቷቸው አንዲትም ቃል ሳይተነፍሱ እንደፈዘዙ ቆመው ቀሩ።

# ክፍል አስራ ዘጠኝ

መደምደሚያ በጠዋት ተነስቶ ወደ ፖስታ ቤት ሲሄድ አዕምሮው በተለያየ ሀሳቦች ተወጥሮ ነበር። የሰማይነህን መታመምና ለአዕምሮው ህክምና ወደ ሆስፒታል መግባት እንዲሁም የወ/ሮ ስራሽን ምስጢር በዕለቱ ማታ ሄዶ ለህይወት ነግሯታል። ህይወት በሁኔታው ተገርማ ለረዥም ሰዓት ራሷን እየነቀነቀች ሐዘኗን ብትገልፅም፣ ከሰማይነህ ጋር ተመልሳ ለመገናኘትም ሆነ አክስቷ ቤት ተመልሳ ለመኖር ምንም ዓይነት ጉጉት አልታየባትም። ሀሳቧ ሁሉ ሄኖክ ብቻ ነው። የሄኖክ በስልክ ያለ መገኘትና የደብዳቤው መራቅ የእሷን ያህል መደምደሚያን አስጨንቆታል። በየዕለቱ ፖስታ ቤት እየሄደ ሳጥኑን ያልፈተሸበት ቀን የለም።

በአንድ በኩል ስለ ሰማይነህ ያስባል። የጠንቋዩን ምስጢር ካወቀ በኋላ ጤነኛ ሆኖ ኑሮውን መምራት ይጀምር ይሆን? ብሎ ይጨነቃል። በሌላ በኩል ደግሞ የህይወት መጨረሻ ናፍቆታል። በነዚህ የሁለት አቅጣጫ ሀሳቦች ተወጥሮ ፖስታ ቤት ሲደርስ፣ የሄኖክን አስቸኳይ ደብዳቤ በማግኘቱ ደስ አለው። ህይወት ወዳለችበት ሆቴል ለመድረስ ቸኮለ።

«....ፈገግ ብለሽ እንድትቀበይ እፈልጋለሁ» አለት ወደ ክፍሏ ደርሶ፣ በሩን ከፍታ እንዳስገባችው።

«ከዚህ በላይ እንዴት ላድርግ?» አለችው ህይወትም በመጠኑ ጥርሷን ገልጣ።

«ደስታኛ ሁኚ። ፈገግታሽ ከልብ ይሁን። ሳቂ። ተጫወቺ። ገና መጀመሪያ ስናውቅሽ የነበረሽን ዓይነት ፍልቅልቅነትና ብሩህ ገፅታ ይታይብሽ። በናፍቆቶት ስትጠብቂው የነበረውን ደብዳቤ ይዤልሽ መጥቻለሁ።

ህይወት በአንድ ጊዜ ፊቷ በራ። ከውስጥ ስሜቷ የመነጨ ፈገግታ ብልጭ ሲል የቀድሞው ውበቷም አብሮ ቦግ አለ። ለአጭር ጊዜም ቢሆን ሰማይነህን ከማግባቷ በፊት የነአብረችው ህይወት ብልጭ ብላ ታየች። ፖስታውን ከመደምደሚያ ላይ ተቀብላ ስትከፍተው ሁሉ አንዳች ስሜት ሰውነቷን ነዘራት።

ደብዳቤውን ማንበብ ስትጀምር ግን ሁኔታዋ ሁሉ የተገላቢጦሽ ሆነ። ለአንዳፍታ የታየው ፍልቅልቅነቷና የውበት ድምቀቷ ብልጭ ብሎ መስሎ ድርግም አለ። ፈገግታዋ እየጠፋ፣ ፊቷ እየጠወለገ፣ ትንፋሿ እየደከመ ሄደ። እንዲያም ሆና አላቋረጠችም። ጥርሷን ነክሳ ደብዳቤውን እስከ መጨረሻው አነበበችው።

«ህይወትዬ ደህና ሰንብችልኝ፤ ይህንን ደብዳቤ የምፅፍልሽ እስከመጨረሻው ልሰናበትሽ ነው። የራሴን መጨረሻ ሳላውቅና መቀመጫዬን ሳላመቻች አንቺን ለማምጣት በማሰቤና ስሜትሽን በማነሳሳቴ ሀጢአተኛ ነኝ። አዝናለሁ ህይወትዬ! ሁሉም ነገር ከቁጥጥሬ ውጭ ስለሆነ ምንም ማድረግ አልችልም። ይህን ደብዳቤ ጨርሼ ላንቺ ከላኩልሽ በኋላ ነፍሴን በራሴ እጅ አጠፋታለሁ። እንደ ፈረንጆቹ ከፎቅ ላይ አልወረውርም። እንደ ሀገሬ ሰዎች በገመድ ተንጠልጥዬ መሞትን መርጫለሁ። የገመዱን ሸምቀቆ በአንገቴ ልክ አስተካክዬ ሰቅየዋለሁ። አፉን ከፍቶ ሊቀበለኝ ተዘጋጅቷል። ለመሞት ስለ ወሰንኩ ፍርሀት የሚባል ነገር ፈፅሞ ከአዕምሮዬ ጠፍቷል። ላካስ ለምንም ነገር ዋናው የአዕምሮ ዝግጁነት ነው።

«ለዚህ ነው ያደረሰኝ ከአንዲት አሮጊት አሜሪካዊት ጋር የተደረገ ግጭት ነው። አሮጊቷ ጎረቤቴ ስትሆን ከሰብዓዊነት ይልቅ በቀልም ልዩነት የምታንም፣ የበላይነት ስሜት የሚንፀባረቅባት፣ ጥላቻውና በግልፅ የምታሳይ ግትርና ስሜታዊ ፍጡር ናት። ከእኔ ጋር በአንዳንድ አጋጣሚዎች ስንገናኝ ተጣልተን እንለያያለን። የዘረኝነት ፍልስፍናዋን ስትደሰኩር ዝም ብዬ አላዳምጣትም።

በምላሹ አፍንጭዋ ድረስ እነግራታለሁ። በነጮች የበላይነት እንዳምን የአስተሳሰብ ተፅዕኖ ልታደርግብኝ ሞክራ ስላልተሳካላት በጣም ጠላችኝ። ነጮን በሰብአዊ ፍጡርነታቸው ካልሆነ በስተቀር ለቀለማቸው ደንታ እንደሌለኝና ቅንጣት ያህል ክብር እንደማልሰጣቸው ነገርኳት። እንዲያውም በእኔ ብሶ እሷም ሆነ ለመሰሎቿ ያለኝን ንቀት በተለያየ መንገድ ገልፅኩላት። ሳልወድ በግድ የዘር ፖለትካ ውስጥ አስገባችኝ።

«እኔን ስታየኝ ደሟ ይፈላ ጀመር። ነጭ ፊቷ በርበሬ መስሎ እስኪቀላ ድረስ እየጮኸች ትሞግተኛለች። ስለናቅኳት አንዳች ዕልህ ውጽጥ መግባቷ ታወቀኝ። የተጠናወታት የበላይነት ስሜት ተቀባይ በማጣቷ አንቀዠቀዠት። አንድ ቀን ስራ ቦታዬ ድረስ መጥታ፣ ‹.....እረኛ የሚያስፈልጋችሁ ከብቶች ናችሁ› በማለት በአፍሪካ ህዝቦች ላይ ያላትን ንቀት ሰነዘረችልኝ። እረኞቻችን እነሱ ነጮች መሆናቸው ነው። ‹እኔ ደግሞ እናንተን አተኩሬ ሳያችሁ የሰለጠናችሁ ነጭ ዝንጀሮዎች ትመስሉኛላችሁ› ብዬ አናደድኳት። ጭቅጭቃችን እየከረረ መጥፎ አቅጣጫ ያዘ።

«ከሰረኝነት ጨኸቷ አልፋ ወደ ተራ ስድብ ተሸጋገረች ‹ከምታፀዳው መሬት ያልተሻልክ ቆሻሻ ነህ› ብላ ምራቋን ስትተፋብኝ ራሴን መቆጣጠር አልቻልኩም። ተንደርድሬ በቡጢ ስነርታት ተንገዳግዳ አስፋልቱ ላይ ተዘረረች።

«ከዚያ በኋላ ምኑ ቅጡ! ፖሊሶች እያዋከቡ ሲወስዱኝ ዘረኞቹ ነጮች ደሞ ጥቁርነቴን ተንተርሰው ይዘልፉኝ ነበር። አንደኛው ፖሊስ በእኛ ላይ ያለውን ጥላቻ አፉን ሞልቶ ተናግሯል። እስር ቤታቸው ውስጥ አስገበተው ለጥቂት ቀናት ያህል በስነልቦና ቶርቸር ካስቃዩኝና ጥላቻቸውን ካሳዩኝ በኋላ ለቀቁኝ። በነፃ የለቀቁኝ እንዳይመስልሽ! ከስራዬ አባረው፣ በአስቸኳይ ሀገራቸውን ለቅቄ እንድወጣ ማስጠንቀቂያ ሰጥተውኝ ነው። ገና የመኖሪያ ፈቃድ እንኳ ያለመያዜ ደግሞ በማንኛውም አቅጣጫ ለመወንጀል ተመቻቸው።

«ይኸውልሽ ህይወቴ! በባዕድ ሀገር ሁለተኛ ዜጋ ሆኖ መኖር ውጤቱ ይሄው ነው። እንዲያውም እኛ ሁለተኛ ዜጎች አይደለንም። ዘረኞቹ ነጮች በደረጃ ሲያስቀምጡን ከአውሮፓና ከኤሽያ የመጡትን ሁለተኛና ሦስተኛ አድርገው ለእኛ ለአፍሪካውያን አራተኛ ደረጃ ዜግነት ሳየምድቡን አይቀሩም። እኔ የተጣላሁት ከአንዲት ግለሰብ ጋር ነው። ነገር ግን ግጭቱ ለሁለታችንም በእኩል ዓይን ሊታይልንና ሊዳኝልን አልተቻለም። ሴትየዋ ለጊዜው ራሷን ስታ ወደ ሀኪም ቤት ብትወሰድም በህክምና ርዳታ ጤናዋ ተስተካክሎ ወደ ኑሮዋ ተመልሳለች። እኔ ግን ከስራና ከሀገር የመባረር ውሳኔ ተላልፎብኝላ። ወይኔ ሄኖክ! ያቺን ዘረኛ አሮጊት እዚያው የተዘረረችበት ቦታ ብጨርሳት ኖሮ ምንም አይፀፅተኝም ነበር።

«ያሳዝናል! ነጮቹን እንዲህ የሚያንጠባርራቸውና በበላይነት ስሜት የሚያስጋልባቸው የእኛ መጠጊያ መጣት ነው። ሀገራችን መኩሪያና መመኪያ ልትሆነን አልቻለችም። በገዛ ሀገራችን ተዋርደንና ስራ አጥተን ከመኖር በስደት መኖርን መርጠን ነበር። ተሰድደን ስንኖር ደግሞ ፈረንጆቹ ይንቁናል። ህይወትዬ፤ ተንቆ መኖር እንዴት ያስጠላል መሰለሽ! አጥንቴ ድረስ ዘልቆ የተሰማኝ አሁን ነው፤ አሮጊቷ ግልፅና ግትር ሆና ያንፀባረቀችው የበላይነት ስሜት በብዙ ነጮች ውስጥ የተደበቀ ነው። ፊት ለፊት ባይነግሩሽም ዘረኝነታቸውን በተለያየ መንገድ ያሳዩሻል። ስለ እኛ ጥሩ ነገር መስማት አይፈልጉም። ምንጊዜም የሚያመሳስሉን ከችግር ከጦርነትና ከጉስቁልና ጋር ነው። ለዚህ አመለካከታቸው ደግሞ እኛ ረድተናቸዋል። እርስ በእርሳችን እየተጣላን ሸሽተን እነርሱ ጉያ ስር እንሸጎጣለን፤ የምንዋጋበትን መሣሪያ እንዲሰጡን እንለምናቸዋለን፤ ሳናጣ ያጣን ሆነ የልመና እጃችንን እንዘረጋቸዋለን። ተፈጥሮም ለነሱ አድልታ፣ ሰብዓዊ ወንድማማችነታችን ቀርቶ በበላይነትና በበታችነት እንድትንተያይ አድርጋናለች።

«እንግዲህ በቃኝ! ከሀገሬ የወጣሁት ስራ ፈትነትን የድህነት ኑሮ አስመርሮኝ ነው። አሁን ወደዚያ ችግር ተመልሼ መምጣት አልፈልግም። አኩርፌ የምመለስበት የሚያኮራ ሀገር የለኝም። ወደ

ሌላ ሀገር ሂጄ በሌሎች ዘረኞች ተንቄና ተዋርጄ መኖር አልፈልግም። ስለዚህ ራሴን በራሴ ለማጥፋት ወስኛለሁ።

«ቻው ህይወትዬ! እንደገና ልሰናበትሽ። ሀዘኑ ሊከብድሽ እንደሚችል ይሰማኛል። ሆኖም ምንም ማድረግ አልችልም። በተፈጠርኩብሽ የስሜት መረበሽ ሁሉ አሁንም እንደገና ይቅርታ እጠይቅሻለሁ። ድንግል ፍቅርን በልቤ ውስጥ ትልቅ ቦታ ሰጥቼ እንደያዝኩት፣ ሳልልከሰከስና ሳልረክስ ወደ መቃብር መውረዴን ወድጄዋለሁ። እኔና አንቺ ተገናኝተን የጋራ ስቃይ ብናካሄድ ምን ዋጋ አለው?! የህይወት ትርጉሙ ይሄ አይመስለኝም። በዚች ፍትህ በሌለባት ምድር ከመኖር መሞትን መርጫለሁ። አንገቴን አስገብቼ የምንጠለጠልበት ገመድ አፉን ከፍቶ እየጠበቀኝ ነው። ደህና ሁኚ ህይወትዬ። እግዚአብሔር ፅናቱን ይስጥሽ

ያንቺው ሄኖክ አንበሴ»

የህይወት ዓይኖች እንባ እያዘነቡ፣ ስሮቿ እየተግተረተሩና ፊቷ እየጠወለገ ደብዳቤውን አንብባ ከጨረሰች በኋላ፣ አንዴ በኃይል ጮሀ ራሷን ስታ አልጋው ላይ ወደቀች።

መደምደሚያ፣ የምሥራች ይዞላት የመጣ መስሎት፣ ሲቧርቅ የቆየው ስሜቱ መርዶ ነጋሪ በመሆኑ አዝኖ በአንድ ጊዜ ኩምሽሽ አለ። ደብዳቤውንም ተቀብሏት በራሱ ዓይኖች የሄኖክን የመጨረሻ የስንብት ቃሎች ሲያነብ አንቀጠቀጠው። የሱም እንባ ዓይኖቹን ሞልቶ ወረደ። ስሜቱ ከቁጥጥሩ ውጪ ሆነ። ነገር ግን እሱ ከሷ የተሻለ ሆኖ ማፅናናት መቻል ነበረበት።

«አይዞሽ በቃ ህይወት ቀና በይ። ይህ የአለም መጨረሻ አይደለም» አላት እንባውን በመሀረብ እየጠራረገ።

ህይወት አንገቷን ቀና ማድረግ አልቻለችም፤ ፊፅሞ ተስፋ በቆረጠ ስሜት ተደፍታ ትንሰቀሰቃለች። የአልጋ ልብሱ በእንባዋ ታጥቧል።

«ጠንከር በር እባክሽ ህይወት፤ እባክሽ እንደ ምንም ቻይው» አላት እንደ ገና፣ ለቅሶዋ ተግ ሲልላት ጠብቆ።

«አልችልም፤ ከእንግዲህ ምንም የምችለው ነገር የለም። ቅስሜ ተሰብሯል» አልችው ለቅሶዋን ሳታቋርጥ።

«ተይ እባክሽ እንደዚህ ተስፋ አትቁረጪ.....»

«ከዚህ በኋላ ምን ልሆን ነው?....የታባቴ ልገባ ነው?.....ትልቅ ተስፋ የጣልኩበት መሸሻዬ ሄኖክ ነበር። እሱ ራሱን ገደለ። ጨካኝ ነው። እኔን ሜዳ ላይ ጥሎ ብቻውን ሞተ። እንግዲህ ምን መሄጃ አለኝ?! እስቲ ንገረኝ መደምደሚያ?!.....»

መደምደሚያ በምን መንገድ እንደሚያፅናናት ግራ ገብቶት ተጨነቀ። ትከሻዋን ደገፍ አድርጎ ከተደፋችበት ቀና አደረጋት። ፊቷ በእንባ ታጥቦ የጠወለገ አበባ መሰለች። እነዚያ ትላልቅ አይኖቿ የውሃ ኩሬ መስለዋል። ከንፈሮቿ ደርቀው ተጣብቀዋል።

«ምን ጊዜም ቢሆን ህይወት የራሷ የሆነ መንገድ አላት። ለኛ ግን አይታወቀንም። ማንኛውንም ነገር እንዳመጣጡ መቀበል ይሳነናል» በማለት መደምደሚያ በደፈናው ሊያፅናናት ሞከረ።

«አክስቴ ቤት አልመለስም። ሰማይነህ ቤትም ተመልሼ አልኖርም። ከንግዲህ ምንም መሄጃ የለኝም።»

«ግዴለሽም። እድልሽ ያዘጋጀልሽ ቦታ ይኖር ይሆናል። እንዲያው እንጨነቃለን እንጂ ሁላችንም ከተፃፈልን እድል አናመልጥም።»

«ኡፍ!......ዓለም እንዴት ጨካኝ ናት!»

«ጠንከር በይ ባክሽን ህይወት!.....»

«አልቻልኩም መደምደሚያ፤ አልቻልኩም። እኔም በዚህ ሰዓት ብሞት ደስ ይለኛል።»

«አይዞሽ። የሰው ልጅ ጥንካሬው የሚለካው በመከራ ሰአት ነው። ምድራዊ ዓለም በፈተና የተሞላ ስለሆነ ጠንከር ብሎ ብሩህ ተስፋ ማየት ያስፈልጋል።»

«እኔ ምንም አይነት ተስፋ አይታየኝም። ከፊቴ የተጋረደው ጨለማ ነው፤ ሆኖብኛል፤ ኃጢአተኝነት ይሰማኛል።»

«ተይ እንጂ ህይወት».....

«እውነቴን እኮ ነው። ምነው እግዚአብሔር እንደዚህ ጨከነብኝ! ገና በልጅነቴ እናትና አባቴን ነጠቀኝ። አሁን ደግሞ የምወደውን ፍቅረኛዬን ነጠቀኝ። እንዲህ ለማስቃየት ለምን ፈጠረኝ?!»

ሁኔታው መደምደሚያ እንደ ገና አስለቀሰው። በጠባቧ ክፍል ውስጥ ሁለቱ ብቻ እየተላቀሱና እየተከዙ ቆዩ። በርግጥም ለህይወት መንገድ ሁሉ ጨለማ ሆኖባታል። መደምደሚያ ግን ከዚህ በኋላ ምን መደረግ አለበት? በማለት በኃሳቡ እያወጣና እያወረደ ነበር።

«ወዴት እንደምሄድ አወቅኩት!» አለችው ህይወት በድንገት እንባዋን ጠራርጋ።

መደምደሚያ ደነገጠ። ሁኔታዋ አዕምሮዋን ነካ ያደረጋት አስመሰላት። ዓይኖቿን አፍጥጣ ድርቅ አለችበት።

«ወዴት ትሄጃለሽ?» አላት ተለሳልሶ።

«ገዳም መግባት አለብኝ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ለእኔ ተዘጋጅቶ የሚጠብቀኝ ቦታ ገዳም ብቻ ነው። ዓለማዊ ህይወት ይበቃኛል። መንኩሼ መኖር ይሻለኛል።»

«ምን በወጣሽ ህይወት! ገና በወጣትነሽ፣ ይህንን መሳይ ውበት ይዘት የምትመነኩሽበት ምንም ምክንያት የለም። ዓለም ሰፊ ናት። ምርጫሽን አጥበሽ አትመልከቺ»

«ወጣትነት ኃላፊ፣ ውበትም ረጋፊ ነው። ዓለማዊ ሰው ሁሉ አስጠልቶኛል። በገዳም የሚኖሩ መነኩሴዎችን ተቀላቅዬ ቅጠል እየተመገብኩ መኖር ይሻለኛል።»

«በፍፁም አይሆንም!.....አይደረግም!.....»

«ኡፍ! ተወኝ እባክህ መደምደሚያ። የዓለምን ጭካኔ መሸሻ ብቸኛ ቦታ ገዳም ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ገዳም መግባት ይሻለኛል።»

# ክፍል ሀያ

ሰማይነህ የአዕምሮ ህመሙ ተሽሎት ከሀኪም ቤት ሲወጣ እናቱ ተቻኩለው ወይዘሮ ስራሽ ስለ ጠንቋዩ የነገረቻቸውን ሚስጥር ነገሩት። ይህንን ማወቁ ሰማይነህን ፈጽሞ ያድነዋል የሚል እምነት ነበራቸው። ሁኔታው ግን የተገላቢጦሽ ሆነ። የነገሩት ነገር በሰማይነህ አዕምሮ ላይ እንደ ገና በሽታውን ጫረበት። የወይዘሮ ስራሽን ስም መስማቱ እራሱ አስጠላው። በሀኪም በተመከረው መሠረት ሊረሳው የሞከረው ጉዳይ አልረሳም ብሎ እንደ ገና አገረሸበት።

«እሷ ግን ምን አይነት ውሸታም ሴትዮ ናት! መጀመሪያ ልጁ ያልሆነችውን ሴት ልጄ ናት ብላ ዋሽታ ዳረችኝ። አሁን ደግሞ የጠንቋዩ አማካሪ ሆና ተገኘች! በዚህ ምድር ላይ እንደርሷ የቀለደብኝ

ሰው የለም!» በማለት ጮኸ።» ረጋ በል ልጄ። ዋናው ነገር እውነቱን ማውጥቷ ነው። ያንን አባይ ጠንቋይ ሄደን ማነጋገር አለብን። እውነት እሷ እንደነገረችን አታሎን ከሆነ እንፋረድዋለን» አሉ እናትየዋ ተናደው።

«ፋታ መስጠት የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም። ተነሱ እንሂድ!» ብሎ ሰማይነህ በቁጣ ተነሳ።

ጎርፉ እንደ ተለመደው በሾፌርነት አጀበው። እናትየዋም ለወሬው ቸኩለው አብረዋቸው ሄዱ። ጠንቋዩ ቤት እስኪደርሱ ድረስ ሰማይነህ አሁንም አሁንም ወይዘሮ ስራሽን እየረገመ ነበር።

«ለሷም አልደላት፤ በሽተኛ ሆና አልጋዋ ላይ ቀርታለች» በማለት እናቷ ሊያፅናኑት ሞከሩ።

«መታመም ሲያንሳት ነው። ለሷ ሞት ይገባታል» በማለት ሰማይነህ ዛተ።

ቀድሞ የሚያውቁት ቦታ ደርሰው ጠንቋዩን ሲፈልጉት ሊያገኙት አልቻሉም። የቤት በር ተቆልፎ ደጃፍ ጭር ብሏል። ካጥር ውጭ የሚጫወቱትን ህፃናት ቀረብ ብለው ሲጠይቋቸው «የሉም። ለቀው ሄደዋል» በማለት መለሱላቸው።

ወደ ግቢው ዘልቀው አዋቂ ሰው ሲያስጠሩ የቤቱ ባለቤት በሌላ በር በኩል ብቅ ብለው አነጋገሯቸው። ኩስምን ያሉ ሽማግሌ ነገር ናቸው።

«እዚህ ቤት የነበረውን ባለ ውቃቢ ፈልገን ነው የመጣነው አላቸው ሰማይነህ እንደ ተቆታ።

«የለም፤ ሰፈሩን ለቅቆ ከሄደ ዛሬ አራተኛ ቀኑን ይዟል» በማለት መለሱ ሽማግሌው።

«ወዴት ነው የሄደው?»

«እኔ እንጃ! አድራሻውን አልነገረኝም።»

«ቤቱ የማን ነው?» አሉ አሮጊቷ ጣልቃ ገብተው።

«የእኔ ነዋ!» አሉ ሽማግሌውም፤ «ለኑሮ መደጎሚያ ብትሆነኝ ብዬ ከመኖሪያ ቤቴ ከፍዬ የማከራያት ክፍል ናት።»

«ታዲያ ተከራዩ ቤትን ለቅቆ ሲሄድ አድራሻውን እንዴት አነግረዎትም?»

«እኔ ምን አውቄ! መንገር ቢፈልግ ኖሮ ይነግረኝ ነበር። መንገር ስላልፈለገ ማስጠንቀቂያ እንኳን ሳይሰጠኝ እንዳበደ ሰው ድንገት እቃውን ሰብስቦ ወጥቶ ሄዶ። እኔ ምን አገባኝ! የሄደውን ሸኝቼ የመጣውን ማከራየት ነው የኔ ተግባር»

የጠንቋዩ መጥፋት ሰማይነህን ከነከነው። በርግጥም አንድ የተደበቀ ነገር ይኖራል ሲል አስበ። በብስጭት ዓይኖቹን አጉረጥርጦ ጥርሶቹን አንቀጫቀጨ» ያከራዩት ሰውዬ አታላይ ሌባ ነበር። እውነተኛ ሰው ቢሆን ኖሮ አይሸሽም!» በማለት ሽማግሌው ላይ አፍጥጦ ደነፋባቸው።

«እኔ እሱን አላውቅም ጌታዬ። ግንኙነታችን ያከራይና - የተከራይ ብቻ ነበር» ብለውት ሽማግሌው ወደ ቤታቸው ተመልሰው ገቡ። ሶስቱ ብቻቸውን ተፋጥጠው እንደ ቆሙ ቀሩ። ጎርፉ ምንም አልተነፈሰም። ሰማይነህ ተመልሶ እብድ ሆኗል። እናትየዋ ለማፅናናት ይሞክራሉ።

«አይዞህ በቃ ልጄ። አትናደድ። ይሄ አባይ ጠንቋይ የነገረን ሁሉ ውሸት ከሆነ አንተም ከእንግዲህ በሰላም ትኖራለህ። ጤንነትህም ይስተካከላል» አሉት።

ሰማይነህ እሳቸውን የሚያደምጥበት የተረጋጋ አእምሮ አልነበረውም። በንዴት ጦፎ ሀሳቡ ሁሉ ተመልሶ ወይዘሮ ስራሽ ላይ አርፏል። አዕምሮው እሷን ለመበቀል ቸኩሏል።

መኪናው ውስጥ ገብተው ወደ ቤታቸው ጉዞ ሲጀምሩ እናትየዋ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ አሰቡ። ሀሳባቸው ባንድ አፍታ ከጠንቋይ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተሸጋገረ። የበደላቸውን ጠንቋይ ለእግዚአብሔር አሳፍለው ለመስጠት፣ ወይንም ደግሞ በጥንቆላ የተበላሸውን የልጃቸውን ህይወት በፀሎት ለማቅናት ቸኮሉ። ፈጣኑና ቀልጣፋ መንፈሳዊ ሽግግራቸው ይሉኝታን የሚያውቅ አልነበረም። ምናልባትም ጠንቋዩን እንዲደፋላቸው ለቤተ ክርስቲያን ስለት ያስገቡ ይሆናል። ቀኑን ሲያስቡ ሚካኤል ነው። ልጆቻቸው በቀጥታ ወደ ጎላ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን እንዲወስዷቸው ጠየቋት።

ሰማይነህ በሀሳቡ አንድ ሠይጣናዊ ሀሳብ ስለ መስጠት እናቱ ከአጠገቡ መራቃቸውን ወደደው። እሳቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን ካደረሷቸው በኋላ ጎርፉን በአስቸኳይ ወደ መኖሪያ ቤታቸው እንዲሾፍር አዘዘ።

«ወይኔ ሰማይነህ!......ይቺ የማትረባ ሽርሙጣ እኔን መጫወቻ አሻንጉሊት አደረገችኝ እኮ!» አለ እየሄዱ።

«ማን ናት እሷ?» አለው ጎርፉ፣ የተሳደበው ወይዘሮ ስራሽን ይሁን ወይንም ህይወትን ግራ ገብቶት።

«ደንቆሮ!......ስለማን የማወራ ይመስልሀል? ለዚህ ሁሉ ችግር የዳረገኝ ስራሽ ብዙ ነች።»

«ልክ ነህ......ይቅታ»

«የወንድምነትህን ልክ የማየው ዛሬ ነው......»

«እንዴት......ምን ልታዘዝ?»

«እንደዚህ በነፍሴ የጠጫወተችብኝን ሴት መበቀል አለብን።»

«እሺ። ፈቃድህን እፈፅማለሁ።»

ቤታቸው ከደረሱ በኋላ ሰማይነህ ዘበኛውን አያመናጨቀና የቤቱን ዕቃ አያተራመሰ በመቅበጠብቅ መጮህ ጀመረ። ጎርፉ ሁኔታው አላማረውም። ‹እብደቱ አገረሸበት ማለት ነው› ብሎ ፈራው።

«እናንተ ናችሁ ያስጠቃችሁኝ!......አንተና እናቴ ናችሁ ለዚህ ያበቃችሁ!» አለው ወደ እሱው ዞሮ።

«ምን አደረግንህ ሰማይነህ?»

«እናንተ የጦር መሣሪያዎቼን ባትደብቅብኝ ኖሮ እንደዚህ አልጠቃም ነበር። ባዶ እጄን መሆኔ ነው ያስጠቃኝ!»

ጎርፉ የመሣሪያ ነገር ሲነሳ ድንግጦ ዝም አለ።

«አሁን መሣሪያ የተደበቀበትን ቦታ በአስቸኳይ እንድታሳየኝ እፈልጋለሁ። ፈጠን በል!» ብሎ ጮኸበት።

ጎርፉ ደፍሮ እምቢ ሊለው አልቻለም። ሲፈራ ሲቸር እየተንቀጠቀጠ ወስዶ መሳሪያዎቹ የተደበቁበትን ቦታ አሳየው። ሰማይነህ መሳሪያዎቹን ሲያገኝ ልቡ ሞልቶ ደረቱን ነፋ። ሰይጣኖች ጭንቅላቱ ውስጥ ሰፍረው ከበሮአቸውን እየደለቁ አጀብ - አጀብ አደረጉት።

«ክላሽኑን አንተ ያዝ። ወንድምነትህንም ዛሬ አያለሁ። ሱሪ የታጠቀ ሁሉ እንድ አይደለም። በተግባር መፈተን አለበት። እንዲሁ ወንድሜ - ወንድሜ ብትለኝ ዋጋ የለውም» ብሎ ክላሽንኮፉን ለጎርፉ ከሰጠው በኋላ ለራሱ ኮልት ሽጉጡን ያዘ።

ጎርፉ መሣሪያውን ሲቀበለው እየተርበተበተ ነበር። በጀርባው በኩል ላቡ እየተንከባለለ ሲወርድ ተሰማው።

«ምን ያርበተብትሀል?!......ፈሪ!» ብሎ ጮኸበት።

«ኧረ አልፈራሁም» አለ ጎርፉ፣ ፍርሀቱ እያስታወቀበት።

«በል አሁን ቶሎ ወደ ስራሽ ብዙ ቤት ንዳ።»

ተከታልበው ገብተው፣ ተከታልበው መሳሪያ ይዘው ሲወጡ አንገቱን አቀርቅሮ በተገርሞ የተመለከታቸው ዘበኛ ራሱን እየነቀነቀ ‹አሁን ለአንዲት ሴት ይሄ ሁሉ ዘመቻ ያስፈልጋል እንዴ?› ብሎ አዘነ። እንደ ተለመደው ህይወትን ፍለጋ የሚሄዱ መስሎት ነበር።

«ይህች ህይወቴን በሙሉ ያበላሸች ሴት ዛሬ፣ መገደል አለባት!.....ይቺ ቀጣፊ አታላይ ደሟ ሲፈስ ማየት እፈልጋለሁ» አለ ሰማይነህ ወደ ወይዘሮ ስራሽ ቤት እየቀረቡ ሲሄዱ።

በዛተና በጮኸ ቁጥር ደሙ እየተሟሟቀ፣ ከውስጡ እየተደፋፈረና በል - በል የሚል ስሜት እየገፋፋው ነበር።

«አንተ ደግሞ ስትርበተበት እንዳታስይዘኝ። ለማንም እጅ መስጠት አያስፈልግም። የሚከታተሉን ቢኖሩ ጥይትህ እስኪያልቅ ድረስ ማንጣጣት አለብህ» በማለት ወንድሙን አስጠነቀቀው።

የጎርፉ ልብ የፍርሀት ከበሮውን እየደለቀ የወንድሙን ትዕዛዝ ተቀበለ።

ወይዘሮ ስራሽ ቤት ሲደርሱ ዘበኛው ትልቁን በር ከፍቶላቸው መኪናቸውን ወደ ውስጥ እንዲያስገቡ በቁጣ ጠየቁት። ዘበኛው ተደናግጦ የተጠየቀውን ፈፀመ። አኳኋናቸው ሁሉ አላማረውም። በሩ ላይ ያፈጠጠበትና የጮኸበት ሰውየ ዱሮ የሚያውቀውና ጠቀም ያለ ጉርሻ ያስለመደው ሰማይነህ መሆኑን ተጠራጠረ። ሰሞኑን የተፈጠረውን ችግርም ሰምቶ ስለነበር የወይዘሮ ስራሽ ዘበኛ አንዳች መጥፎ ነገር ሸተተው። ጭራሹን ከመኪናቸው ውስጥ መሣሪያ ይዘው ሲወርዱ ስለተመለከተ ጥርጣሬው ጎልቶ እሱ ራሱ ተርበተበተ። እነርሱ ወደ ውስጥ መሣሪያ ይዘው ሲገቡ ዘበኛው ፖሊስ ፍለጋ ወደ ውጭ ወጣ።

ወይዘሮ ስራሽ ከአልጋዋ አልወረደችም። አዕምሮዋም ሆነ መላ ሰውነቷ ጤና ስላላገኘ ተኝታ እያቃሰተች ነበር። ሰማይነህና ጎርፉ እየተከታተሉ ገብተው አልጋዋ ውስጥ ሲያገኟት ደስ አላቸው።

«አንቺ ሸርሙጣ!.....ቀጣፊ!......አታላይ!» በማለት ሰማይነህ አንዴ አምባረቀባት። «ወይ ወንድሜን....አሁንም አልተሻለህም?» አለችው በደከመ ድምጿ።

«እድሜ ላንቺ!.....አሁን ጠንቋይ ያለበትን ቦታ ባስቸኳይ ተናገሪ!»

«የጠንቋዩን ነገር እርሳው እባክህ። ሁሉም ነገር ውሸት ነው። ለናትህ ነግሬአቸው ነበር እኮ። አልነገሩህም እንዴ?»

«ጠንቋዩ የት ነው የተደበቀው እኮ ነው የምልሽ?»

«እኔ ምን አባቴ አውቄ።....»

«አሁን የመጣሁት ይህንን ቀጣፊ ምላሽን እስከ መጨረሻው ልቆርጥልሽ ነው። ትንፋሽሽን ልዘጋው ነው!»

«ይገባኛል.....ጥፋተኛ ነኝ።»

ሽጉጡን አጠገቧ አቀባብሎ እያነጣጠረባት «ለመሞት ዝግጁ ነሽ!» አላት።

ወይዘሮ ስራሽ በድንጋጤ ህመሟ....ሁሉ ጠፍቶ እየጮኸች መሳሪያውን ላለማየት ፊቷን ትራሱ ላይ ደፍታ ተሸፋፈነች። ጩኸቷ ሰማይነህን አስበረገገው። ሽጉጡን ሲያቀባብል በአጃቢነት ሞቅ አድርገው ከውስጡ ያጨቡጨቡለት ሰይጣኖች አሁን ደግሞ ቃታውን እንዲስብ አዘዙት።

ሁለቴ አከታትሎ ተኮሰ። የጥይቶቹ ድምፅና ብርድ ልብሱን አልፎ የፈሰሰው የወይዘሮ ስራሽ ደም ‹የሰማይነህ አዕምሮ ይበልጥ አንቀዠቀዠው። አጠገቡ የሚርበተበተው ወንድሙን ገፍትሮ እየተሯሯጡ ባስቸኳይ ወደ መኪናቸው ውስጥ ገቡ። ጎርፉ በድንጋጤ እየተንቀጠቀጠ የመኪናውን ቁልፍ ማስነሳት ስላቃተው፣ ሰማይነህ መንጭቆ ተቀበለውና እራሱ እየነዳ ከግቢው ወጡ።

በዘበኛው ጠቋሚነት መጥተው ካጥር ውጭ ግንቡን ከለላ አድርገው ሲጠባበቁ የነበሩት ፖሊሶች አንዴ ወደ ሰማይ ተኩሰው «ቁም!» የሚል ድምፅ አሰሙ። ሰማይነህ ግን አልቆመም። በፍጥነት እየነዳ ለማምለጥ ሲሞክር ፖሊሶች የመኪናውን ጎማ በጥይት መትተው አስቆሙት።

ሰማይነህ አሁንም እጁን አልሰጠም። ከመኪናው ውስጥ ዘልሎ ወርዶ በሽጉቱ እየተታኮሱ ሮጦ ለማምለጥ ሲሞክር በፖሊሶቹ ጥይት ተመቶ ወደቀ።

ፖሊሶቹ ያለመንፈራገጡንና ድምፁ መጥፋቱን አረጋግጠው በዘዴ ሲቀርቡት ሰማይነህ አርፏል። የፖሊሶቹ ጥይት አጓጉል ቦታ ስላገኘው ወዲያውኑ ፀጥ አሰኝቶታል።

ፖሊሶቹ በተጠንቀቅ መኪናውን ለመፈተሽ ሲቀርቡ ደግሞ ጎርፉ እጥፍጥፍ ብሎ የመኪናውን ወንበር ስር ተወሽቆ ተመለከቱት።

«እጅ ወደ ላይ!» ብለው ሲጮሁበት አንዴ ፈሱን ላጥ አደረገው።

«ይሄው.....በናታችሁ አትግደሉኝ» እያለ አንገቱን ወንበሩ ስር እንደ ቀበረ እጆቹን ወደ ላይ አደረገ። ያንን የሚያክል ግዙፍ ሰውዬ እንዲህ ተጣጥፎ ወንበር ስር መግባር መቻሉ ፖሊሶቹን ሳያስገርማቸው አልቀረም። ትከሻውን ይዘው እየጎተቱት ሲያወርዱት መላ ሰውነቱ በላብ ተጥለቅልቋል። የሆነ እንገር ስለሸተታቸው ሱሪውንም አላመኑትም።

«.....ብቻ እኔን አትንኩኝ። ሁሉንም ነገር እነግራችኋለሁ» ብሎ እንባ አውጥቶ አለቀሰባቸው።

«አትርበትበት! ቀጥ በልና ቁም» ብለው አንደኛው ፖሊስ በቁጣ።

«እሺ።.....መሳሪያው ያለው እዚህ መኪና ውስጥ ነው።»

«የምን መሳሪያ?»

«ክ - ክላሹ.....ጠ - ጠመንጃው»

«ምን ልታደርግበት ያዝከው?»

«እኔ አይደለሁም......ሰማይነህ ነው።»

«እሱን በኋላ ስትመረመር ትናገራለህ.....»

«እሺ።.....ወይዘሮ ስራሽንም የገደላት እሱ ነው። እኔ አንዲት ጥይት እንኳን አልተኮስኩም።

«አሁን ይሄንን ሁሉ ማን ጠየቀህ?»

«እንዳትመቱኝ ብየ ነው……ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ አትምቱኝ። ጫማችሁ ላይ እወድቃለሁ።»

«እንድ አይደለህም እንዴ?! ምን እንዲህ ያርበተብትሀል?!»

«ታላቅ ወንድሜ ነው ያሳሳተኝ። እሱንም ጠንቋዩ ነው ያሳሳተው…..»

«የማን ነው ጠንቋይ እሱ?…..»

«ቤቱን ለቆ የጠፋው።….የህይወትም ደግሞ ቤቷን ለቅቃ ጠፍታለች። ሰማይነህ ቢያገኛት ይገላት ነበር።»

«አሁን ያልተጠየከውን አትቀባጥር። ይሄ የምርመራ ቦታ አይደለም። ሁሉንም በኋላ ታወጣለህ።»

«እሺ።»

ፖሊሶቹ መኪና አስመጥተው የሰማይነህ አሬሳ ለምርመራ ወደ ሆስፒታል ከላኩት በኋላ ጎርፉን ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱት። የወንድሙ መሞት ቢያስደነግጠውም ይበልጥ ያሳሳችው የራሱ ነፍስ ነች።

«አትገድሉኝም አደል?!…..» እያለ እንደ ህፃን ልጅ ዓይኖቹን አቁለጨለጨባቸው።

«መጀመሪያ ላብህን ጥረግ። ከምርመራ በፊት ደግሞ ወደ ሽንት ቤት ሂድና ተፀዳድተህ ተመለስ» በማለት የፖሊሶቹ አዛዥ ትዕዛዝ ሰጠ።

ጎርፉን አጅቦት ወደ ሽንት ቤት የሄደው ፖሊስ አፍንጫውን ይዞ ከውስጥ የሚንተረተረውን ተኩስ እያደመጠ «መትረየሱን ሆዱ ውስጥ ደብቆት ኖሯል እንዴ?» አለና ሳቀ።

# ክፍል ሀያ አንድ

ምሽቱ ተቃርቧል። ፀሐይዋ ከዓይን እየራቀችና እየጠለቀች ስትሄድ ትታይ ነበር። የሰማይነህ ግቢ ትርምስምሱ ወጥቷል። እናትየዋ ጨርቃቸውን ጥለው እየጮሁ ያለቅሳሉ፤ የቅርብ ዘመዶቻቸውና ጎረቤቶቻቸው አብረዋቸው ደረታቸውን ይደልቃሉ። ወሬውን የሰማ ሁሉ ግልብጥ ብሎ መጥቶ ግቢውንና መንደሩን አጨናንቆታል። የሰማይነህ ሬሳ ተመርምሮ ለቤተሰቦቹ የተሰጠ ቢሆንም የሩቅ ዘመድ እስኪሰበሰብ ድረስ የቀብሩ ሥነ ሥርዓት እንዲያድር ተወስኗል። እስከዚያ ድረስ ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ሴቶች ከወደ ማድ ቤት ጭስ ያጫጭሳሉ። ወንዶች እየተንጫጩ ድንኳን ይተክላሉ።

«እንዴት አይነት ጉድ ነው እባክህ! እኔኮ ገና አሁን መስማቴ ነው» አለ ብህሩ ፂሞ አልቅሶ ሲያበቃ አይኖቹን በመሀረብ እየጠራረገ መደምደሚያ ወደ ተቀመጠበት ተጠግቶ።

«ያሳዝናል። መጨረሻው እንዲህ ሆነ» አለና መደምደሚያ እንደገና አንገቱን ደፍቶ ሲያለቅስ ከቆየ በኋላ «ከቅድም ጀምሬ በአይኔ ስፈልግህ ነው የቆየሁት» ብሎት የባህሩን ክንድ ይዞ ወጣ አድርጎ አነጋገረው።

«ምን ችግር አለ?….ምን ልርዳችሁ?» አለ ባህሩ በሙሉ ልቡ።

«ችግሩ እዚህ አይደለም። እዚህ ማንኛውም ዝግጅት እየተሟላ ነው።»

«ታዲያ ሌላ ምንድነው?»

«እኔን ወደ አንድ ቦታ እንድትወስደኝ ነው።»

«አንተማ የወንድምህን ሬሳ ጥለህ ከዚህ መነቃነቅ አትችልም። የምትፈልገውን ነገር እኔን እዘዘኝ።»

«አንተ ብቻህን የምትፈፅመው ጉዳይ አይድለእም። እኔ መሄድ አለብኝ። አንዳፍታ አብረን ደርሰን እንመለሳለን።.....ያውም የኔ ጉዳይ ነው።»

«ያት ነው ቦታው?....»

«ህይወት የተደበቀችበት ቦታ ነው። ብቻዋን ነች፤ ይህንን ሁሉ ጉድ አታውቅም። ከኔ ሌላ የተደበቀችበትን ቦታ የሚያውቅ ሰው የለም። ሄድን እናምጣት» አለው ልመናና ለቅሶ በተቀላቀለበት ድምፅ።

ባህሩ ፂሞ እየተገረመ የመደምደሚያን ፈቃድ ለመሙላት መኪናውን አስነስቶ ተያይዘው ሄዱ። ነገሩ ግራ ገብቶት ውስጥ ውስጡን እየከነከነው ነበር።

«.....አሁን ህይወት የተደበቀችው የት ነው?» አለው እየሄዱ።

«ሆቴል ውስጥ ነው።»

«እንዴ!.....እሷ ግን ከመጀመሪያው ለምን ተደበቀች?»

«አሜሪካን ሀገር ፍቅረኛዋ ያለበት ቦታ እስክትደርስ ድረስ ነበር የተደበቀችው። ሆኖም አልተሳካላትም። ፍቅረኛዋም እራሱን በራሱ መግደሉን የሚያረዳ ደብዳቤ ትላንት ስለደረሳት እሷም በለቅሶ ብዛት እራሷን ከፉኛ ታምማ አልጋዋ ውስጥ እንደ ተኛች ናት። እስከጊዜው ድረስ የሚከራይ ቤት ፈልጌ ከሆቴል ለማውጣት ከትላንት ማታ ጀምሮ ወዲያ ወዲህ ስልላት ነበር። ዛሬ በመሀል እንዲህ አይነት አስደንጋጭ ነገር ተፈጠረ» አለውና አዘነ።

«አንተ ከመጀመሪያው የተደበቀችበትን ታውቀው ነበር ማለት ነው?»

«አዎ። ሌላ በቅርቧ የሚረዳት ሰው ስላልነበረ ምስጢረኛ ወንድሟ አድርጋ የያዘችኝ እኔን ነው።»

«ይገርማል!» አለ ባህሩ ፂሞ ወደ ፊት እየሾፈረ።

«አሁን የአክስቷ ህይወት ሳያልፍ ብትደርስባቸው ጥሩ ነበር። ከታመሙ ጀምሮ የህይወትን ስም እንደ ተሩ ሊሞቱ ነው» አለ መደምደሚያ ትንሽ ቆይቶ።

«ወይዘሮ ስራሽን ማለትህ ነው?» አለው ባህሩ ግር ብሎት።

«አዎ። ወይዘሮ ስራሽ ለህይወት አክስቷ ናቸው፤ እናቷ አይደሉም» በማለት አሳጠረበት። ጥድፊያ ላይ ስለሆኑ፤ ባህሩም ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ መግባት አልፈለገም።

«.....ግን ወይዘሮ ስራሽ ህይወቷ ተርፏል ማለት ነው?» በማለት ወደ አጣዳፊው ጉዳይ ተሸጋገረ።

«ለጊዜው ህይወታቸው አላለፈችም። አደጋው እንደደረሰባቸው ፖሊሶች ወዲያውኑ ተረባርበው ሀኪም ቤት ስለወሰዷቸው ለጊዜው ቢሆንም ትንፋሻቸው ልትቆይ ችላለች። ነገር ግን በሁለት ጥይት ደረታቸውን አንጀታቸው አካባቢ ስለ ተመቱ አይተርፉም። ሀኪሞቹ ተስፋ ቆርጠዋል» አለው መደምደሚያ አሁንም እያዘነና እንባውን እያረገፈ።

«ያሳዝናል። ይሄ ሁሉ የሆነው በሴት ምክንያት ነው» ብሎ ባህሩ ፂሞ እራሱን ነቀነቀ። መደምደሚያ በዚህ የጭንቀት ሰአት የባህሩ ፂሞን የተሰበረ ልብ የሚያስታውስበትና ትርታውንም የሚያዳምጥበት አዕምሮ አልነበረውም። የተፈጠረውን አደጋ ለህይወት ምን ብሎ እንደሚነግራት እየተጨነቀ ነበር።

መኘታ ክፍሏ ደርሰው ሲገቡ፣ ህይወት አሁንም አልጋዋ ላይ ጥቅልል ብላ እንደተኛች አገኟት። እራሷን በትልቅ ጨርቅ ጠምጥማ አስራዋለች። ፊቷም እንደጠወለገ ነው። ትላልቅ ዓይኖቿ ረዳት በሚፈልግ አስተያየት ከወዲያ ወዲይ ይንከባላሉ። የመደምደሚያንና የባህሩን የሀዘን ፊት ብትመለከትም በሷ ምክንያት ያዘኑ እንጂ ሌላ ችግር የተፈጠረ መሆኑን አልጠረጠረችም።

«እንደ ምንም ቀና በይ ህይወት። ከጋሽ ባህሩ ጋር ልንወስድሽ ነው የመጣነው» አላት መደምደሚያ ከውስጥ የሚተናነቀው እንባ ለመግታት እየሞከረ። ቀና ለማለት ሞከረች። ሰውነቷ ሁሉ ተዝለፈልፏል። እነሱ ደጋግፈው ካነሷት በኋላ እንደ ምንም ልብሷን ለባበሰች። የሆቴሉን ሂሳብ ዘግተው፣ በአነስተኛ ሻንጣ ተዘገጃጅተው የተቀመጡትን እቃዎቿን አውጥተው መኪና ውስጥ ሲያደርጉ ሁሉ የሚቃወሙት ሆቴሉን ለቅቃ መውጣቷ ብቻ ነው። ወዴት እንደሚወስዷት እንኳን አታውቅም። ባህሩና መደምደሚያ ከፊት፣ እሷ ከኋላ በስፋት መኪና ውስጥ ተቀምጣ ጉዞአቸውን ቀጠሉ።

«ቤት አገኘህልኝ እንዴ? ወዴት ነው የምትወስደኝ?» አለች መንገዱን ከጀመረች በኋላ፣ በደከመ ድምፅ።

«አይደለም። መጀመሪያ ያክስትሽን ዓይን ማየት አለብሽ። ሌላ ያልታሰበ ነገር ተፈጥሯል። አክስትሽ ደጋግመው ያንቺን ስም እየጠሩ ነው» አላት እሱም ድምፁ እየተንቀጠቀጠና እንባው ጉንጮቹን አልፎ እየወረደ።

መጀመሪያ አደጋውን ላለመናገር አመንትቶ ነበር። በኋላ ግን ሲያስበው ሆስፒታል ውስጥ ድንገት ከምትደነግጥና አካባቢውን ከምትረብሽ እዚሁ መኪና ውስጥ አውቃ ቢወጣልት እንደሚሻላት በመገመት የሆነውን ሁሉ በዝርዝር ነገራት።

«ምንድነው የምታውራው መደምደሚያ?!.....ሰማይነህ ሞቷል ነው የምትለኝ?! ብላ ጮኸች። አዲሱ ድንጋጤ ያደረውን ሀዘኗንና ድካሟን ያጠፋላት ይመስል እንደ ገና ነፍስ ዘርታ ማልቀስ ጀመረች።

«አዎ ህይወት፤ በሰይጣን ተገፋፍቶ ለሞት በቃ፤» አላት መደምደሚያ እያለቀሰ።

«እኔ አላምንም!....ምንም ብጠላው ሞቱን አልመኘም ነበር» ብላ ራሷን ይዛ እየተንሰቀሰቀች አለቀሰች።

«መቻል ነው። አንዴ ከሆነ በኋላ ምን ይደረጋል?!» በማለት ባህሩ ፂሞ ሊያፅናናት ሞከረ።

«አክስቴም ሞታለች ማለት ነው?...አትደብቀኝ እባክህ መደምደሚያ»

«ህይወታቸው አላለፈችም። በርግጥ በሀኪሞች እጅ በጣር ላይ ናቸው። ምናልባት ያንቺን ድምፅ ሲሰሙ ይተርፉ ይሆናል።»

«ወይኔ አምላኬ!....ምን አይነት አስጠሊታ ዓለም ነው!.....ይህንን ሁሉ መከራ የሚያደራርብኝ ለምንድነው?!.....ኧረ እኔ አልችልም ፈጣሪዬ፤ ሁሉም ነገር ካቅሜ በላይ ነው» እያለች ተማርራ እንባዋን ዘራች።

«አይዞሽ፤ ተስፋ አትቁረጪ፤ ገና ወጣት ነሽ። ወደፊት የሚጠብቅሽን አታውቂም። ለሁላችንም ቢሆን በህይወት ፈተና ውስጥ ማለፍ የግድ ነው። ተስፋ ከመቁረጥ ተስፋ ማድረግ ይሻላል» በማለት ባህሩ ፂሞ ሊያፅናናት ሞከረ። ሐዘኗ አሳዝኖት ከብዙ ዓመታት በኋላ እንደገና ልቡ ለሴት ልጅ መራራት ጀመረ።

ሆስፒታል ሲደርሱ መደምደሚያና ባህሩ የህይወትን ክንድ ግራና ቀኝ ደግፈው ይዘው አስገቧት። ወይዘሮ ስራሽ ጣዕር ላይ ስለሆነች ማንም ሰው የተኛችበት ክፍል እንዳይገባ ተከልክሎ ነበር። ሆኖም ሰመመን ውስጥ ሆና የህይወትን ስም ደጋግማ ስትጠራ አስታማሚዋ ነርስ ሰምታ ስለ ነበር አሁን ከልጇ ጋር እንድትገናኝና እንድትሰናበታት ፈቀደችላት።

ህይወት ወደ ውስጥ ገብታ ያከስቷን ሁኔታ ስትመለከት እራሷን መቆጣጠር አልቻለችም።

«እማዬ!» ብላ እራሷን ይዛ ጮኸች።

ወይዘሮ ስራሽ በህይወትና በሞት መሀል ወድቃ፣ ወደ ሞት አመዝና አይኖቿን ጨፍና፣ ሰመመን ውስጥ ነበረች። የልጇን ድምፅ ስትሰማ ከረዥም የእንቅልፍ አለም እንደ ነቃች ሁሉ ጉልበት አግኝታ፣ ላንዳፍታ ዓይኖቿን ገልጣ፣ እንደ ምንም ትንፋሿን አሰማች።

«ህ - ህይወቴ ነሽ?.....ል - ልጄ ነሽ?»

«አዎን እማዬ። ልጅሽ ነኝ። ህይወት ነኝ።»

«አስቀይሜሻለሁ። ይቅር በይኝ....»

«ሁሉንም ትቼዋለሁ እማዬ፤ አንቺ ብቻ ትረፊልኝ»

ያከስቷ ትንፋሽ ድንገት ጉልበት በማግኘቱ ህይወት ትተርፍልኛለች ብላ ጓጉታ ነበር። ወይዘሮ ስራሽ ግን የመጨረሻ የጣር ኃይሏን ከውስጥ እየጨመቀች እየተሰነባበተቻት ነበር።

«ላንችው ብዬ ነበር እኮ ህይወትዬ። ለክፋት አልነበረም ሁሉንም ያደረኩት። ለ - ጠንቋዩ ሁለት ሺህ ብር ጥሎሽ ከፍዬ የዳርኩሽ ለክፋት አልነበረም። ላንቺ ለልጄ ጥሩ ኑሮ ተመኝቼ ነበር።»

«ይገባኛል እማዬ። አሁን ለሁሉም አውቄዋለሁ፤ ትንፋሽሽ እኮ ደከሟል። ብዙ አትናገሪበት። »

«እንዲህ አይንሽን አይቼ ብሞት ደስ ይለኛል። እማዬ ብለሽኝ መሞቴ ያኮራኛል። እናትሽ ነይ አይደል?.....ደጋግመሽ እማዬ በይኝ እባክሽ።»

«እናቴ ነሽ። ይሄው እማዬ እልሻለሁ። አትሞችብኝም። ትድኝልኛለሽ።»

«አልተርፍም ህይወት። ሀጢአተኛ ነኝ። አሁን ግን እማዬ ስላልሽኝ ተደስቼ ነው የምሞተው። ንብረቴን ሁሉ ላንቺ ተናዝዣለሁ። ሀብቴ ሁሉ ያንቺ ነው። በቅድሚያ ለነፍስ አባቴ ነግሬሻለሁ።»

«እባክሽ ተይ ሆዴን አትረብሽው እማዬ። አሁን እኔ ልጅሽ አጠገብሽ ነሽ። አትሞችም።»

«ህ - ህይወቴ»

«ወዬ፤ እማዬ....»

«አትርሺኝ። ሁ - ሁ - ሁልጊዜ አስታውሺኝ። እናትሽ ነኝ። በ - በደሌን ይቅር በ - ይ - ኝ....» ድምጿ እየደከመና እየተስለመለመ ሄዶ ድንገት ፀጥ አለች። በልጇ ፊት የመጨረሻ ትንፋሿን አሰምታ ህይወትን ተሰናበተች።

«እማዬ.....እማዬ!.....እማዬ....» እያለች ህይወት ብትጮህም መልስ ስልሰተቻትም። ለዘለዓለሙ አንቀላፍታለች።

ህይወት ሬሳዋ ላይ ተደፍታ እየጮኸች ስታለቅስ፣ መደምደሚያና ባህሩ ፂሞ እየተሯሯጡ ገብተው ክንዶቿን ይዘው ቀና አደረጓት።

እና፤ ከለቅሶዋ ጀርባ አንዳች ድምፅ እንደ ገና የሰማች መሰላት።

ገና ወጣት ነሽ። ተስፋ አትቁረጭ። ወደ ፊት የሚጠብቅሽን አታውቂም።......ይህም የዓለም መጨረሻ አይደለም።

**ተፈፀመ።**

# ስለደራሲው በጥቂቱ



አዲስ አበባ በ፲፱፵፮ ዓ.ም. የተወለዱት ሲሳይ ንጉሡ አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በባልቻ አባነፍሶ፣ የሁለተኛ ደረጃን ደግሞ በአዲስ ከተማ አጠቃላይ ተከታትለዋል፡፡ የከፍተኛ ትምህርታቸውን በአሥመራ ዩኒቨርሲቲ ከ፲፱፷፬-፲፱፷፯ ዓ.ም. ድረስ ተምረዋል።

በዩኒቨርሲቲ ሕይወት ዙሪያና በፍቅር ታሪክ ላይ በሚያተኩረው ሰመመን በሚባለው መጽፈሐፍቸው በብዙዎች ዘንድ የታወቁት ሲሳይ ንጉሡ፣ ጉዞው፣ ግርዶሽ፣ የቅናት ዛር የተባሉ ረጃጅም ልብወለዶች አሏቸው፡፡ ጉዞው የሚለውን ኖቬላ ጨምሮ ሌሎች አጫጭር ልብወለዶችን ጽፈዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ሥነ ጥበባትና መገናኛ ብዙኃን ሽልማት በሥነ ጽሑፍ ዘርፍ ተሸላሚም ሆነዋል፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት የደራሲያን ማኀበር ዋና ጸሐፊ በመሆን አገልግለዋል፡፡

ምንጭ: የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ለሚሊኒየም ያሳተመው አጀንዳ።

## የደራሲው ሥራዎች

1. ሰመመን (**ልብወለድ**)
2. ግርዶሽ (**ልብወለድ**)
3. ጉዞው (**ልብወለድ**)
4. የቅናት ዛር (**ልብወለድ**)
5. ረቂቅ አሻራ
6. ትንሣኤ